© ሜጋ አሳታሚ ድርጅት 1990
Mega Publishing Enterprise 1998

ስልክ 113190
Tel - 111825
- 128641

ፖ.ሳ.ቁ 12684
P.O.Box 22284

አዲስ አበባ
ኢትዮጵያ

Addis Ababa
Ethiopia

የመጀመሪያ እትም 1988
ሁለተኛ እትም 1990

መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው
All Rights Reserved

የሽፋን ስዕል በኤርሚያስ ዕቁባ

በሜጋ ማተሚያ ኢንተርፕራይዝ ታተመ

# ድህረ - ታሪክ

1988 ዓ.ም። ከእንቅልፏ እንደነቃች መብራቱን አብርታ ሰዓቷን ተመለከተች። ከሌሊቱ ዘጠኝ ሰዓት። ጆሮዋን አንቅታ አዳመጠች፣ ከሩቅ ከሚሰማ የውሾች ድምጽ በቀር ሌላው ረጭ ብሏል። የሌሊት ልብስ ላይ ጋቢ ደረበችና ወደ መፀዳጃው ክፍል አመራች። ልጇ መኝታ ቤት ስትቃረብ ግን ድምጽ የሰማች መሰላትና ቆም አለች። እጀታውን ጠምዝዛ በሩን በጥንቃቄ ከፈተችና ራሷን አስቀደመች።

በመኝታ ክፍሏ ውስጥ ካዘጋጀችው የጽህፈት ጠረጴዛ ጆርባ ተቀምጣ የፃፈችውን ታነብ የነበረችው ልጃገረድ በእንቅልፍ እጦት የደፈረሱ ትላልቅ ዐይኖቿን አፍጥጣ እናቷን ጥያቄ ባዘለ አስተያየት ተመለከተቻት።

"የእንቅልፍ ሰዓትሽ እኮ ነው ሄለን" አለቻት ሀዘኔታ ባዘለ ድምፀት።

"አውቃለሁ እማ..." ሄለን እንቅልፍ የተጫጫናቸውን ዐይኖቿን እያሸች አዛጋች።

"እና መተኛት አልነበረብሽም?"

"ነበረብኝ፣ ግን... ይሄን ተውኔት ደግሞ ጽፌ መጨረስ አለብኝ። አራተኛው ክፍል የሬዲዮ ድራማ ነው... ሦስቱ ለህዝብ መተላለፋቸውን ታውቂያለሽ..."

"አውቃለሁ፣ ቢሆንም አሁን..." ሰዓቷን ተመለከተች።

"አሁንማ ጨረስኩ..." ሄለን ጠረጴዛው ላይ የተበታተኑትን ወረቀቶች ሰብስባ በማቀፊያው ውስጥ ከተተቻቸው።

"ደግሞ ሌላ ነገር አትዘንጊ፣ ክረምቱ ሲያበቃ ኮሌጅ ትገቢያለሽ። ለዚያ ብትዘጋጂ አይሻልም?"

"ኮሌጅ ላለመግባት ወስኛለሁ!"

"ምን?"

"አልገባም!" የልጅቷ ድምጽ በእርግጠኝነት ሲጎላ እናቷ ደግሞ በመገረም ፈዛ ቀረች።

"ለምን?"

"ከኮሌጅ ዲግሪዬ በፊት ራሴን ማግኘት አለብኝ!"

"አልገባኝም!" እናቲቱ ፍጹም ግራ ተጋባች።

"ይሄን አልደብቅሽም እማ... ነፍሴ በትልቅ ጥያቄ ተወጥራ ልትፈነዳ የደረሰች ይመስለኛል" በርግጥም ጭንቀቷ በገጽታዋ ላይ ፈጧል።

"ምን አይነት ጥያቄ ሄለን?" እናት ግምባሯን ቅጭም አድርጋ በጥርጣሬ ዐይን ታስተውላት ገባች።

"እኔ ማን ነኝ?"

እናቷ አንድ ነገር ልትናገር አስባ አፏን ከፈተችና በዚያው ቀረች። ዐይኖቿ እንደተጉረጠረጡ፤ የግምባሯ ላይ የደም ሥሮች እንደፈጠጡ። አብነት መንገሻ ዛሬ እንዲህ ፊት ለፊት ልትጋፈጠው፣ ይህን ጥያቄ ስንቴን ዘመን ስትሸሸው ኖራለች።

# ክፍል አንድ

## ምዕራፍ አንድ

"ሮሜዎና ዡልዬት፣ ኦቴሎና ዴዝዴሞና በመቶዎች ከሚቆጠሩ ዓመታት በፊት የኖሩ ሃሣብ ወለድ የፍቅር አርበኞች ናቸው። ህይወት ግን ልቦለድ አይደለችም" ትላት ነበር ሣራ። በርግጥ አይደለች ይሆን? እንጃ።

ልቦለድና ህይወት፣ ህይወትና ልቦለድ የተሳከረባት ጓደኛዋ አብነትን ግን፣ በኦቴሎ ተውኔት ውስጥ ቃሲዮን ወክሎ የሚጫወተው ተዋናይ አነሁልሏት መዋሉ እውነት ነው።

ተዋናዩ የጦር ልብሱን አጥልቆና ሻምላውን ታጥቆ ብቅ ሲል መቁነጥነጧ እንዲሁም አንገቷን ማስገግ ራሷንም አስገርሟታል። በወንዳወንድ ቁመናውና በውብ ገፅታው መረታቷንም ቢሆን ፈጥና ልትገነዘበው ባይቻላትም ተውኔቱ አብቅቶ መጋረጃው ከተዘጋ በኋላ አዳራሹን ለቃ የወጣችው የመጨረሻው ሰው ግን እርሷ ነበረች።

ፍዝዝ እንዳለች ከአዳራሹ ወጥታ፣ የዴዝዴሞናን ገፀ-ባህርይ ተላብሳ ትጫወት የነበረችውን ሣራን መጠበቅ ጀመረች። ሣራ አብሮአደግ ጓደኛዋ ነች። የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን በዳግማዊ ሚኒልክ ትምህርት ቤት እንዳጠናቀቁ፣ አብነት በአባቷ አስመጪና ላኪ ድርጅት ውስጥ የሂሣብ ሠራተኛ ሆና ስትመደብ ሣራ ቲያትር ቤት ተቀጠረች።

ጓደኝነታቸው ግን በዚህ የተነሣ አልተቋረጠም። ሣራ የምትሣተፍባቸውን ተውኔቶች ሁሉ እንድትመለከትላት አብነትን ትጋብዛታለች። አብነትና ሣራ በአስተሳሰብና በዓላማ የማይጣጣሙ ቢሆንም ተለያይተው ግን አያውቁም። ዛሬም እንዲሁ።

አብነት ከቲያትር ቤቱ በር ላይ የተለጠፉትን የፊልም ማስታወቂያዎች እየቃኘች ስትንጎራደድ ሣራ ከወደ ኋላዋ ጠራቻት። መካከለኛ ቁመትና ቀጠን ያለ ሰውነት ያላት ሣራ በጭሩ የተቆረጠ ፀጉሯን መሃል ለመሃል በወርቃማ ቀለም አቅልማዋለች። ረዘም ያለው ጠይም ፊቷ፤ ትናንሽቹ ብልጭልጭ ዐይኖቿ፣ ጎረድ ያለው አፍንጫዋ ቀይ ቀለም የተቀባው ከንፈሯም ውቦች ናቸው።

ከጉልበቷ ትንሽ ወረድ ያለ ቢጫ ሱሪና ነጭ ሸሚዝ ለብሳ፤ ከትልቅ ቦርሳዋ ለተመለከታት ከጥቂት ደቂቃዎች ቀደም ሲል

የአንዲት ምስኪን ነጭ ሴት ገፀ ባህርይን ተላብሳ፣ የተውኔት ታዳሚውን በዴዝዴሞናነቷ አሳምና በሀዘን ስታስለቅስ በቁጭት ስታንጨረጭር የነበረች አርቲስት ለመሆኗ ይጠራጠራል።

"አቢ ዘገየሁ እንዴ?" ብላ የአብነትን ወገቧን አቀፈቻት።

"እንዲያውም።"

ሴቶቹ እንደ አስተሳሰባቸው ሁሉ በቁመናቸው በእጅጉ ይለያያሉ። ኑግ የመሰለ የአብነት ዞማ ፀጉር ቁልቁል ዳሌዋ ላይ ወርዷል። ቀጥ ብሎ የቆመው አፍንጫዋና የብር ኳሶች የሚመስሉት ዐይኖቿ ከረገረገም ሽፋሎቿና ነዶ ሙሉ ጥቁር ቅንድቦቿ ተደምረው ቀይ ፊቷን ግርማ ሞገስን አላብሰውታል። ውብ ቅርጽ ያላቸው ከንፈሮቿ ሲፈለቀቁም ፀአዳ ጥርሶቿ ፍንትው ይላሉ። ዘለግና ፈርጠም ባለው ሰውነቷ ላይ የበቀሉት ጡቶቿም ገና ያልፈነዳች እንቡጥ ጽጌረዳነቷን ያረጋግጣሉ።

ሣራ የአብነትን ወገብ እንዳቀፈች ወደ አስፋልቱ እየመራቻት "ቡና ልጋብዝሽ አቢ፣ ላየን ባር ሳይሻለን አይቀርም ሰው ቢበዛበትም ቀለል ይለኛል" አለቻት። አብነት አልመለሰችላትም። በፀጥታ ተከትላት ሄደች።

በሩ ላይ እንደደረሱ፣ የቃሲዮን ገፀ-ባህርይ ይጫወት የነበረው ተዋናይ ቡና ጠጥቶ ሲወጣ አገኙት። ሣራ ተወርውራ ተጠመጠመችበትና ግምባሩ ላይ ሳመችው። ተዋናዩም ጉንጯን ሳማት።

"ጋሽ ቻርሊ ዛሬ እንዴት ነበርኩ?" አለችው ሣራ እየተጣደፈች።

"ኅፍስ ነበርሽ" አላት በአ ነ። በዓይኖቹ ግን አብነትን ከላይ ወደታች ከታች ወደላይ ይ ታል። "ኅፍስህ ትለምልም!" ሣራ ወገቡን አቅፋ ግምባሩ ላይ ደግ ችው።

አብነት ግራ ተጋብታ ዓይኖቿ በአርቲስቱ ላይ በመትከል በአድናቆት ትመለከተዋለች። የልቧ ምት እየፈጠነ ውስጧ መሸበር ሲጀምር ግን ዐይኖቿን ነቅላ አቀረቀረች።

"ቀና በይ እንጂ የኔ እህት ይህን ውብ ፊትሽ ዓለሙ ሁሉ ሊያየው የሚገባ ነው።" አላት በጣቱ ከአገጯ ቀና እያደረጋት። አብነት ፈገግ አለች። ሣራ እግሯን እንስታ አሸካካች።



"ተሣሣትኩ?" ጥያቄው ለሣራ ነበር።

"አልተሣሣትክም ቢሆንም...ግን ቢሆንም" ሣራ አንገቷን በፌዝ ሳይና ታች ወዘወዘችው።

"ቢሆንም ምን?" ተዋናዩ ዐይኖቹን በአብነት ዐይኖች ላይ እንደተከለ ጠየቀ።

"ዐይንህን ንቀል ጋሽ ቻርሊ!"

"ባልነቅልስ?!"

"በህግ ብያለሁ ንቀል!"

"እኮ ባልነቅልስ?!"

"እ እ ሣራ በህግ!" |

"ባንቺው መጀን ነቅያለሁ" አለ ቻርሊ በሣራ ሁኔታ ከልቡ እየሣቀ።

ሣራ ዶሮ ጫጩቶቿን ከነጣቂ ለመከላከል በክንፎቿ እንደምትጋርዳቸው አይነት በአብነት ላይ እጆቿን ዘረጋችና አንገቷን ወደ ተዋናዩ መለስ አድርጋ "የማይበሉት እህል ከአፈር አንድ ነው" አለችው።

"ምነዋ?" የቻርሊ ዐይኖች በመገረም ተበለጠጡ።

"ኩርርርርርር ....." ሣራ አብነትን እየገፋች ወደ ውስጥ ይዛት ገባች። ተዋናዩ ለጥቂት ደቂቃዎች ቆም ብሎ ሲመለከታቸው ቆየና እያፏጨ መንገዱን ቀጠለ።

ነጭ ሸርጥ ያገለደመው አስተናጋጅ በቁራጭ ጨርቅ ጠረጴዛውን ካፀዳ በኋላ ሁለት ፍንጃል ቡና ሊያመጣ እንደሄደ ሣራ አካባቢውን በዐይኗ መፈታተሽ ጀመረች። አብነት የማትወድላት አንዱ ጠባይዋ ይህ ነው። ዐይኗም ቀልቧም አንድ ቦታ ረግቶ አያውቅም። ዘወትር እንደተራብ አውሬ ትቅበዘበዛለች።

"ዛሬ እንዴት ነበርኩ አቢ? ቂቂቂቂ ..." ሰዎች በተሰበሰቡበት ሁሉ ያለ ምክንያት መሳቅ ትወዳለች። "ኅፍስ ነበርኩ! አይደል? ቂቂቂቂቂ..." የምትሳተፍባቸውን ተውኔቶች ከጋበዘቻት በኋላ አንድም ቀን እንኳን ስለ ተውኔቱ ይዘት ወይም ስለ ዝግጅቱ መዋጣት አሊያም ስለሌሎች ተዋንያን ጠይቃት አታውቅም።ትንሽ ክፍል ብትጫወትም እንኳን ስለ ራሷ አብዝታ ትወተውታለች።

"ኅፍስ ነበርሽ!" አለቻት አብነት እንደሰለቸች። ዛሬ ስለ ሣራ የተውኔት ችሎታ ለመስማትም ይሁን እያደነቀች ለማወደስ

አልተዘጋጀችም። ጉጉቷ ቃሲዮን ተመስሎ ስለተጫወተው ታዋቂ አርቲስት የግል ሕይወት መስማት ብቻ ነው።

ማራ ግን ፋታ አልሰጠቻትም። "ወደ ተውኔቱ ፍጻሜ ላይ ... ልክ ኦቴሎ አንቆ እንደገደለኝ ከመጀመሪያዎቹ ረድፎች መካከል ስቅስቅ ብላ የምታለቅስ ሴት ድምፅ ስሰማ ሳቄን ልለቀው ነበር ... ቂቂቂቂ ... ሻይ ቅጠል ሕዝብ!... እኔ ግን ነፍስ ነበርኩ፤ አይደል አቢ?!"

"እምን፤ ነፍስ ነበርሽ" አለቻት አብነት በማራ የድምጽ ቅላጼ። ማራ ተፍነከነከች። አብነት ግን "ቃሲዮን ሆኖ የተጫወተው አርቲስትም ነፍስ ነበር" አለቻት ደፈር ብላ።

ማራ ፊት ላይ የፈካው ደስታ በአፍታ እንደ ጉም በነነ። መስማት የምትፈልገው ስለራሷ ብቻ ነበር። እናም "የርሱ ደግሞ ምን ነው ያስደሰተሽ?!" ስትል ግንባሯን ቋጥራ ጠየቀቻት።

አብነት የቡናውን ፍንጃል በእጆቿ መሃል እያሽከረከረች ፍዝዝ ብላ ስታስብ ቆየችና "ሁሉ ነገሩ ያስደስታል። ልብሱና አስተጣጠቁ፤ ወንዳ ወንድ አቋሙ ይማርካል። ውብ ገጽታው ይጥማል። ድምጹ ራሱ የምትሃት ያህል የሚያደነዝዝ አንዳች ሃይል አለው" አለቻት ዐይኖቿን ከዐይኗ እያሸሸች።

ይኼኔ ማራ በተለመደው የሽሙጥ ዘይቤዋ ከንፈሯን እንሻፈፈችና "'ሥጋ ቁጠር ቢሉት ሽኽና አንድ' አለ አሉ ማንትስ... ቀድሞ ነገር አንቺ ከመቼ ወዲህ ነው የወንድን ልጅ ውበት አድናቂ የሆንሽው?!" ስትል ጠየቀቻት። እውነት ነበራት ። አብነትም ከዚያ ቀደም ተናግራው የማታውቀው አድናቆት ከአንደበቷ በመውጣቱ ሀፍረት ተሰምቷት ተሸማቀቀች።

ደግሙ ከአጭር ጊዜ ዝምታ በኋላ ማራ ኩርፊያዋን ሁሉ ረስታ መቀበጣጠሯን ቀጠለች። "በዚህ ተውኔት ውስጥ በጣም የሚያናድደኝ ነገር ቢኖር ኢያጎን ሳልበቀለው እንደ በግ በፀጥታ መሞቴ ነው..." አባባሏ በታሪኩ ሂደት ላይ ሊያስከትል የሚችለውን መፋለስ ግን አላሰበችውም። ኢያጎን ስትበቀለው ሊፈጠር ይችል የነበረው የተመልካች አድናቆትና ጭብጨባ መቅረቱ ብቻ ነበረ የሚቆረቁራት።



"ግን ደግሞ ያስደሰተኝ ነገር የቃሲዮ ከአቴሉ ፕሮግራሙ ተ መሆንና እስከ ታሪኩ ፍጻሜ ድረስ በሕይወት መቆየት መቻሉ ነው" አለች አብነት በበኩሏ።

ማራ ብስጭት ብላ ቅንድቦቿን ቋጠረችና "ምነው ቃሲዮ፤ ቃሲዮ ማለት አበዛሽሳ ?! አሁን ከዚያ ሁሉ ተዋናይ የሚደነቅ ጠፍቶ ነው?! ማድነቅ ከፈለግሽ ለምን መሪ ተዋናዩን ኦቴሎን አታደንቂም?!" ብላ ጠረጴዛውን በቡጢ እየደበደበች አፈጠጠችባት።

"ማንን ማድነቅ ወይም አለማድነቅ እንዳለብኝ የምትወስኚልኝ አንቺ አይደለሽም የኔ እህት። እውነቱን መስማት ከፈለግሽ ቃሲዮን አደንቁዋለሁ!" አለቻት ። አብነትም በበኩሏ አራስ ነብር ሆና።

"ከቃሲዮሽ ጋር ገደል ግቢ! ቀድሞውኑ ጥፋተኛዋ እኮ እኔ ነኝ። ስለተውኔት ምን ታውቂና እነታረክሻለሁ" አለች ማራ በእንዳጭቹ ዐይኖቿ ዙሪያዋን እያማተረች። ለዐይኗ የሚሞላ ሰው በአካባቢዋ አላየችም። ልጃቸውን ኬክ በወተት እያራሱ የሚመግቡ ባልና ሚስት፤ ቡና እያማሰሉ የሚተክዙ ጡረተኞች፤ ጀላቲ እየላሱ የሚያሽካኩ ልጃገረዶች፤ ማንቲም የሚቃርሙ ለማኞች ብቻ ናቸው የታዩዋት።

ዐይኖቿ ቢባዝኑም አዕምሮዋ ግን በጥልቀት ማሰብ ጀምሮ ነበር። "ግን አንድ የሚያስደንቀኝ ነገር ልንገርሽ?" አለች ቡዝዝ ያሉ ዐይኖቿን አብነት ዐይን ላይ እንደተከለች... "ይሄ ቃሲዮን ሆኖ የተጫወተው ተዋናይ በተመልካቹ ላይ የሚደግመው አንዳች ምትሃት ሳይኖረው አይቀርም። ሁሉ የርሱ አድናቂ፤ ሁሉ የርሱ አጨብጫቢ ነው። እኩይ ገፀ-ባህርይን ወክሎ ሲጫወት እንኳን ከተውኔቱ ፍጻሜ በኋላ የሚዥጎደጎድለት ጭብጨባና አድናቆት ልዩ ነው። ቲያትር ቤቱን ምሶሶ ሆኖ የደገፈው እርሱ የሚመስላቸውም ብዙዎች አሉ። ይህን ሳስብ ሁልጊዜ ይደንቀኛል። ሌላው በመድረክ ላይ ስንት ሰዓት ሙሉ እየተንከባለለ አቧራ ሲቅም፤ ጉሮሮው እስኪተረተር ሲጮህና በላቡ ሲታጠብ ያልተደነቀና ያልተወደሰ፤ የታዋቂው እንግሊዛዊ ተዋናይ ቻርሊ ቻፕሊን ስም በቅጽልነት የተሰጠው ቻርሊ ገና መድረኩን ሲረግጥ ተመልካቹ ከመቀመጫው መቁነጥነጥ፤ ከአንገቱ ማስገግ ይጀምራል። ገና ቃለ-ተውኔቱን እንኳን ሳያወጣው ታዳሚው መሳቅ ወይም ከንፈር መምጠጥ ይጀምራል። ምን አይነት ምትሃት ነው?!" በመገረም ራሷን ነቀነቀች። "በዚህ ላይ ቲአትር ቤት ውስጥ የማይፈራው ሰው የለም። የሰላ ምላሱ የስንቱን ቅስም ሰብሮታል መሰለሽ። በሙያውም ቢሆን ራሱ ተበፋ ቆርጦ የብዙዎቹን ተስፋ አምክኗል! 'ወታደራዊውን መንግሥት የሚቃወም ኮሚኒስት ነው!'

እያሉ ውስጥ ውስጡን ቢያሙትም እንደ ራስ ጠጉር ከበዙ ጠላቶቹ አንዱ እንኳን ማስረጃ አቅርቦ አላስፈረደበትም። እንደ ጥጃ እንደታሰረና እንደተፈታ ይኖራል።" ቡዝዝ ያሉት ዐይኖቿ ወደ ውስጥ እንጅ ወደ ውጭ አይመለከቱም። ድምጿም ልክ የቃለተውኔት ጥናቷን እንደምታነበንበው አይነት ነበር።

አብነት ግን ስለ ቻርሊ መስማት የፈለገችው ይህን ብቻ አልነበረም። ስለዚህም ሣራ ትረካዋን ትቀጥላለች ብላ በጉጉት ትጠባበቃት ጀመር። ያሰበችው አልተሳካም። ሣራ ከትልቁ ቦርሳዋ ውስጥ ሣንቲሞች አውጥታ ጠረጴዛው ላይ ከዘረገፈች በኋላ ለመሄድ ተነሳች። አብነትም ስለ ቻርሊ ከዚያ በላይ ለመጠየቅ አልደፈረችም።

ለገሀር ላይ አብነት ወደ ቦሌ መስመር፣ ሣራ ደግሞ ወደ ልደታ የሚወስዱቸውን ታክሲዎች በመጠበቅ ላይ ሳሉ፣ ሣራ የዘነጋችውን ጉዳይ አስታውሳ "እውአቢ! ሳልረሳው... ማክሰኞ ሆም ፓርቲ አለብኝ፣ ... ዘናጭ የዳንስ ምሽት። እና ያን ወይን ጠጁን ቀሚስሽን እንድታውሽኝ ነገ ቢሮ እመጣለሁ እንዳትረሺ" አለቻት።

አብነት፣ ሣራ ተውሳ ያልመለሰቻቸውን ቀሚሶች፣ ሸሚዞችና ጫማዎች ብዛት አሰበችና ፈገግ አለች።

"ማሚን ደግሞ ሰላም በይልኝ ... ጉድ ናይት!" አምስቱን ጣቶቿን እውለብልባ የተከፈተ ታክሲ ውስጥ ጥልቅ አለች።... ለአነጋገሯ፣ ለአለባበሷ፣ ለአካሄዷ፣ ባጭሩ ለምንም ነገር ግድ የሌላት በመሆኗ ነው የሥራ ጓደኞቿ "ጋዴም" የሚል ስም ያከናነቧት። ሣራ ግን ስለተለጠፈባት ቅጽልም ሆነ ስለ ሰዎች ግድ አልነበራትም።

አብነት ቤቷ ስትገባም ይረብሻት የነበረው ስሜት አልለቀቃትም። ሰውነቷን ከብድ፣ ነፍሷን ጭንቅ እንዳላት እንቅልፍ አጥታ ስትወራጭ አደረች። በተከታታይ ባሉ ቀናትም እንደዚሁ።

በማምንቱ ለሣራ ጋዴም ሳትነግር ተውኔቱን በድጋሚ ተመለከተችው። የሌላውን ባታውቅም ለርሷ የተውኔቱ መሪ ኮከብ ቃሊዮ ነው። መድረኩ ላይ በወጣና በወረደ ቁጥር ነፍስና ስጋዋ እንደተቦጨቀ ተውኔቱ ተጠናቀቀ። ምን አይነት ምትሃት ነው?!

ሰኞ እለት ሣራ ጋዴም እቢሮዋ ደወለችላት። ለሌላ የዳንስ ምሽት ሌላ ልብስ ልትጠይቃት እንደደወለች አብነት አልተጠራጠረችም ነበር። ሣራ ግን ለዚያች እለት ብቻ ቁም ነገረኛ እንደሆነች ሁሉ "አንቺ አብነት፣ ያች አዜብ እኮ ታማ ሆስፒታል



ገብታለች እሉ። ለምን ነገ አንጠይቃትም?" አለች። አዜብ የትምህርት ቤት ጓደኛቸው ናት።

አብነት በሣራ ቁም ነገረኝነት እየተደነቀች "ምን ነካት ልጄ! ከሣምንት በፊት ደውየላት ነበር እኮ" አለች ከወዲህኛው የስልክ ጫፍ።

"እኔ እንጃ! የዘንድሮ በሽታ ደግሞ ምኑ ቅጡ... ለማንኛውም ነገ ይመችሻል?!"

አብነት ጠረጴዛዋ ላይ ያለውን ካላንደር ተመለከተች። ሚያዚያ 23 ቀን 1969፣ ሜይዴይ የወዛደሮች ቀን ይባል። "ነገ ሥራ እንደሌለ ግን አውቀሻል?!" ስትል ጠየቀቻት። ሣራ የእረፍት ቀኖችን በመዝናናት የምታሳልፍ በመሆኑ እንደማይሞላላት በመገመት።

"አውቃለሁ ... የተኛችው ዘውዲቱ ነው። ጠዋት ሶስት ሰዓት ለገሀር እንገናኝ። ቻው" አለችና መልስ ሣትጠብቅ ስልኩን ዘጋች።

አብነት ስልኩን አስቀምጣ ማሰብ ጀመረች። ዐይኖቿ ግን ከጠረጴዛዋ ላይ ባለው ካላንደር ላይ በደማቅ ቀይ ቀለም ከተጻፈው "ሜይደይ" ከሚለው ጽሑፍ ላይ ሊነቀልላት አልቻለም። ሁሉ ጊዜም ይገርማታል። በወታደሩ መሪነት የላብ አደሩ አምባገነንነት ከየት ተነስቶ ማረፊያው የት እንደሚሆን እያሰበች ይደንቃታል።

ያ ዓመት አብዮቱ በአፍላ ጉልበቱ ፊውዳሊዝምን በፈርጣማ ክንዱ የደቆሰበት፣ የቢሮክራሲውን ጆሮ በቁንጥጫ እያሸ ኢምፔሪያሊዝም ላይ የሚዝትበትና፣ በምድር ላይ ማንኛውም ኃይል አይቋቋመኝም እያለ የሚፎክርበት ነበር። እውነትም የተቋቋመው ኃይል አልነበረም። በሃያል ክርን የተደቆሰው ፊውዳሊዝም ከትቢያ ላይ ተኝቶ አከርካሪውን ያሻል። በቁንጢጥ የታሸው ቢሮክራሲ ዐይኖቹ በስጋት እንደፈጠጡ ጭራውን ወሽቆ መጭውን በትዕግሥት ይጠባበቃል። ዛቻ የተሠነዘረበት ኢምፔሪያሊዝም አብዮቱን እያሽሟጠጠ እጆቹን አጣምሮ ከሩቅ ይመለከታል።

በማግሥቱ በቀጠሯቸው መሠረት ለገሃር ላይ ተገናኙ። ከያቅጣጫው ወደ አብዮቱ አደባባይ የሚጎርፈው ሠራተኛ ቁጥር ስፍር ስላልነበረው የተገናኙት ከብዙ ችግር በኋላ ነበር። በሠልፉ መሀል እየተሹለከለኩ ኢትዮጵያ ሆቴል አካባቢ እንደደረሱም ከቸርቻር ጎዳና እየተመመ የሚመጣው የሰልፈኛ ማዕበል መንገዱን ዘጋባቸው። ሰልፈኛው ከሌሎች አቅጣጫዎች ከመጡት ለየት ይላል።

ጎዳናውን በሰፊው ሞልቶ የሚተመው ሰልፈኛ፣ መፈክሩን ችቦ አስመስሎ እየዘመረና እየፈከረ ይጓዛል። የማርክስን፣ የኤንግልስንና የሌኒንን ፎቶግራፎች በበርካታ ቀይ ባንዲራዎች አጅቦ ይዘምራል። "የዲሞክራሲያ" ቅጅዎች ታች ታቹን ይበተናሉ፣ "ጊዜያዊ ህዝባዊ መንግሥት አሁን!" የሚለው መፈክር ከሁሉም ደምቆና ልቆ በሰልፈኛው እንደተያዘ ይታያል።

ሱቅ በደረቴዎች የታቀፉትን ካርቶን አንቀው ሲሸሹ፣ ባለመኪኖች መንገድ እያሳበሩ ይበራሉ፣ ነፍስ የያዛቸው መንገደኞች ባገኙት ቀዳዳ ሁሉ እግሬ አውጭኝ ይሸመጥጣሉ። ከአመጸኞቹ ለመራቅ ቢቻላቸው በአየር ላይም ቢሆን ተንሳፈው ከምድአቱ በተሰወሩ።

ልበሙሉዎቹ ሰልፈኞች ግን እጅጌያቸውን እንደጠቀለሉ፣ ደረታቸውን እንደነፉና ግንባራቸውን እንደቋጠሩ እየዘመሩ ያልፋሉ።
"ለእምባገነን መንግሥት ሕዝቡን ሳልወከለ፣
አይገዛም፣ ሕዝቡ ግለ እየታገለ...
አይገዛም! አይገዛም! አይገዛም!..."

አብነት ዐይኖቿ በድንጋጤ ፈጠው ሰውነቷ በፍርሃት እየተንዘፈዘፈ የማራን እጅ ጭምቅ አድርጋ ይዛ "ማርዬ ዛሬ አለቅን! ወዴት እንሸሽ?!" አለቻት ማምለጫዋን ግራና ቀኝ እየቃኘች።

ማራ ግን ግንባሯ እንኳን ቅጭም አላለም። መዝሙራቸው ማርኳታል፣ በመፈክራቸውም እንጀቷ ርቧል፣ ልበ ሙሉነታቸውም ቢሆን ወኔዋን አጀግኖውታል። እናም ሰልፉን ተቀላቅላ መዝሙሮቹን ለመዘመር፣ መፈክሮቹን ለመፈክር፣ ባንዲራዎቹን ለማውለብለብ አቆበቆበች። ዘወትር "ጀብድ የማትሠራ ነፍስ እንቅልፋም ናት" የምትለው አባባሏም ትውስ አለቻት። ስለዚህ ይህንንም ጀብዱ ልታሳልፈው አልፈቀደችም። ለሚቀጥሉት ተከታታይ ቀናት ብዙ የምታወራበት ጉዳይ ነው።
"የምን መሸሽ!" ትናንሽ ዐይኖቿን እያርገበገበች ከንፈሯን እንዳጣመመች በአብነት አፌዘችባት።

"ይልቅ እቢ እንቀላቀል!" አለቻት በቁርጠኝነት።

አብነት ግራ ተጋብታ "አብደሻል እንዴ?" ብላት የጀመረችውን ሳትጨርስ ማራ እጇን ጎትታ አጠገባቸው ከነበረው የሰልፈኛ ሠራዊት መሃል ጨመረቻት።



በመጀመሪያዎቹ ጥቂት ደቂቃዎች ውስጥ ትርምሱ፣ ጫጫታውና ጩኸቱ ራሷን ስለአዞራት የማራን ክንድ አጥብቃ ይዛ፣ የወይን ጠጅ ጠግቦ እንደሚወላገድ ሰካራም እዚህና እዚያ እየረገጠች ትፍገመገም ጀመር። ዘግይታ ግን ከጩኸቱና ከትርምሱ ጋር በመላመዷ በአካባቢዋ የሚሆነውን ሁሉ መገንዘብ ቻለች። ሰልፉ የዘውዲቱ ሆስፒታልን አቅጣጫ ይዞ እየነጎደ ነበር።

ወደ ኢዮቤልዮ ቤተመንግሥት የሚያወጣውን ዳገታማ መንገድ እንደተያያዙም አብነት መዝሙሮቹን መዘመርና መፈክሮቹን መፈክር ጀምራለች። የመዝሙሮቹን ዜማ ስትሰማና የሰልፈኞቹን ከሞት ጋር ሳይቀር የመፋለም ቁርጠኛ ወኔ ስትመለከት፣ አንዳች ስሜት ልቧን እየፈነቀለ አልቅሽ አልቅሽ አላት። ማራ አንዳች የሚያክል መፈክር ተሸክማ ትዘምራለች። አብነት ቀና ብላ እየችው "ላብ አደሩ ያቸንፋል!" ይላል።

በእልህና በወኔ እየዘመረና እየፈከረ የሚተመው ሰልፍ አቀበቱን ጨርሶ ከቤተ መንግስት መግቢያ በር ትይዩ ባለው መንታ መንገድ ላይ ሲዳረስ ወታደሮች የጫኑ በርካታ ካሚዮኖች ደረሱ። ወታደሮቹም መሣሪያዎቻቸውን እያቀባበሉ ከካሚዩኖቹ ላይ በዝላይ ወርደው ሰልፈኛውን ከበቡት።

"ፋሽስቶቹ ደርሰዋል!" ከአብዛኛው ሰልፈኛ አንደበት የሚሰማው ቃል ነበር። የሰልፉ ጉዞ ተገትቶ ሠልፈኛው እጅ ለእጅ እንደተያያዘ ለከበባው ሳይሸበር ባንድነት ቆመ። አንዳንዶቹ በሰልፈኛው መሃል እየተዘዋወሩ ሠልፈኛው በወታደሮች ከበባ እንዳይሸበርና እንዳይደናገጥ ያበረታቱ ጀመር።

ቀይ ጥብጣብ ግንባሩ ላይ ያሠረ ረዘም ያለ ቀጭን ሰው እነ አብነት ወደነበሩበት አካባቢ ተጠግቶ "ጓዶች! የኛ መሸበርና መደናገጥ ለጠላቶቻችን ድል መሆኑን አትዘንጉ። ጩኸቱን የምንጮህለት ላብ-አደር በጠላቶቹ ፊት እንዲያፍር በር አትክፈቱ!" ሲል ድምፁን ከፍ አድርጎ ተናገረ።

"የፈጣሪ ያለህ!" ማራ በክንዷ አብነትን ጎሸም አድርጋ ወደ ጆሮዋ ጠጋ አለችና "ቻርሊ'ኮ ነው" አለቻት። ዐይኖቿ ፈጠዋል፣ አፏም እንደተከፈተ ነው። "ለካስ ቻርሊ በርግጥ ወታደራዊ ኮምኒስቶችን የሚዋጋ ኮምኒስት ኖራልና" አለች ማራ በሹክሹክታ። አብነት "ኮምኒስት" የሚለውን ቃል ስትሰማ ልቧ ቢደነግጥም ዐይኖቿ ግን ቻርሊን ተከትለውት ሄደዋል።

መፈክር ያነገቡ ሰልፈኞችና መግሪያ የታጠቁት ወታደሮች እንደተፋጠጡ ለአጭር ጊዜ ቆዩ። አብነትን ፍርሃት ያንዘፈዝፋት ታል። ሣራ ግን ትልቁን መፈክር እንደያዘች በዐይኖቿ ሁሪያዋን ታማትራለች። "በዚህ የሞት ጥላ ባንዣበበት ቅጽበት ሳይቀር አደን ላይ ትሆን?!"

የመጀመሪያዋ ጥይት ተተኮሰች፤ ብም! ብም! የሚያስለቅስ ጋዝ በምብ እንደ ኳስ በሰልፈኛው ጀርባ ላይ መንጠር ጀመረ። ተኩሱና ፍንዳታው ያለማቋረጥ ቀጠለ። እጅ ለእጅ የተቆላለፉት ሰልፈኞች ተላቀቁ።

ከፊሉ ሠልፈኛ በደረቱ ተኝቷል፣ ቀሪው ባአገኘው አቅጣጫ እግሬ አውጭኝ ይሸመጥጣል፣ ጥቂት ደፋሮች ግን ድንጋይ እየለቀሙ በወታደሮች ላይ ይወረውራሉ። "ሣራ ... ዛሬ አለቅን ... በቃ የመጨረሻችን ነው" አለች አብነት የሣራን ክንድ ለመያዝ አየሩን እየዳበሰች ። ሣራ አጠገቧ አልነበረችም፣ ይዛው የነበረው መፈክር ብቻ በጀርባው ተንጋሎ አጠገቧ ወድቋል "ላብ አደሩ ያቸንፋል!"

በአፍታ ሰማይ ምድሩ ዞረባት። የምታየው ሁሉ እውነት የሚመስል አልነበረም። በርቀት ስታይ ወታደሩ የአንዱን ጥርስ ያራግፋል፣ በሌላ ማእዘን የጭስ ጋዝ ቦምብ ፊቱ ላይ የፈነዳበት ወጣት በባሩድ የተለበለበ ፊቱን በእጁ ሸፍኖ ይጮሃል፤ በጥይት የተመታ ሌላ ሰው በጀርባው ተንጋሎ ደሙ ወደ አስፋልቱ ይንቆረቆራል፤ ሌሎች እየረገጡት ይሸሻሉ። ሣራ ይዛው የነበረው መፈክር ብቻ በጀርባው እንደተንጋለለ ቀርቷል "ላብ አደሩ ያቸንፋል!"

አብነት ካለችበት አልተንቀሳቀሰችም። ከደምና ከሥጋ የተገነባች ሀውልት መስላ ቆማለች። ማምለጫ መንገድም የለም በየማእዘኑ ወታደር፤ በየማእዘኑ የጭስ ጋዝ ቦንብ! በየማእዘኑ እንደ ተልባ የሚንጣጣ አፈሙዝ! ወታደሮቹ በእጃቸው የገባውን ሰው ሁሉ በሰደፍ እያጋጩ ከሚየኖን ላይ ይጭናሉ። ከጥይቱና ከሰደፍ ውርጅብኝ ብትተርፍ እንኳን በካሚዮኖቹ ላይ ከመጫን እንደማታመልጥ እርግጠኛ ነበረች ።

ጭሱ ጉሮሮዋን ስለከረከረው ያለ ማቋረጥ ትስላለች፣ እንባዋ ያለማቋረጥ ይፈሳል ። ዐይኖቿ ፍጹም ተጨናብሰዋል። በዚህ ሁኔታ ሳለች ነበር እንግዳ እጅ የግራ እጇን ጭምድድ አድርጎ ወደ ፊት እየጎተተ የወሰዳት። "በቃ... ተያዝኩ ማለት ነው" አለች በሃሳቧ። በቀኝ



እጇ እንደምንም ዐይኖቿን ጠራርጋ የያዛትን ሰው ለመመልከት ሞከረች። ወታደር አልነበረም።

ነጭ ለባሽ አለመሆኑን ያወቀችውም በትርምሱ መሃል የወታደሮቹን ከበባ ሲጥሱ ከለላ ሆኖ ከፊት ከፊቷ እየሮጠ የሚወርድበትን የሰደፍ ቅጥቀጣ ሲቀበል በተጨናበሱት ዐይኖቿ ጭላንጭል ከተመለከተች በኋላ ነበር። ወዴትና ለምን ያህል ጊዜ ይዟት እንደሮጠ አታውቅም። ከብዙ ሩጫ በኋላ ጨኸቱና ትርምሱ ጋብ እያለ በመሄዱ ከአደጋ ለመትረፏ ተስፋ አደረገች።

"አይዞሽ፤ በመጠኑም ቢሆን ለመሮጥ ሞክሪ... ወታደሮች እየተከተሉን ስለሆነ ወደ መንደሩ እንታጠፍ" አላት እጇን ይዞ የሚሮጠው ሰውዬ ። መላወስ ያቃታትና ትንፋሽ ያጠራት ቢሆንም ይህን ድምጽ መቼና የት እንደሰማችው ከማሰላሰል አልቦዘነችም።

በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴርና በካርታ ሥራ ድርጅት ህንፃዎች መካከል ያለችን ቀጭን የአስፋልት መንገድ አቋርጠው፣ ጠጠራማ በሆነው መንገድ እየተሹለከለኩ ብዙ ከሮጡ በኋላ መንደሩ ዳር የነበረች ደሳሳ ጎጆ ውስጥ እጇን እንደያዘ ዘሎ ገባ። ቤቱ ውስጥ ተቀምጠው ቡና ያፈሉ የነበሩት ባልቴት በድንጋጤ የፈጠጡ ዐይኖቻቸውን እያቁለጨለጩ ባሉበት ደርቀው ቀሩ።

"የመልአኩ ያለህ! ምንድነው እሱ ጉዳዩ... ማንን ፈለጋችሁ ወዳጆቼ?!" እያሉ ሲንተባተቡ "እባክዎ እናቴ ለአጭር ጊዜ ያሳርፉን ... ወታደሮች እየተከተሉን ነው" አላቸው ሰውየው በላይ በላዩ እየተነፈሰ። ባልቴቷ ከመደንገጣቸው የተነሣ ለአጭር ጊዜ የሚሠሩት ሁሉ ጠፍቷቸው ይርበተበቱ ጀመር። አብነት መልሳቸውን ለመጠበቅ አቅሙም፣ ትዕግስቱም ስላልነበራት የቤቱን ግድግዳ ተንተርሳ ወደምትታየው አግዳሚ ወንበር ሄዳ ዘጭ አለችባት።

ምን እንደተባባሉ ባትሰማም ሰውየውና ባልቴቷ ጥቂት ከተነጋገሩ በኋላ በሩ ተዘግቶ መብራት በራ። ሰውየው ክፍሉ ውስጥ ጥቂት ከተንጎራደደ በኋላም ከአብነት ፊት ለፊት በርጩማ ላይ ተቀምጦ ጣቶቹን እያፍተለተለና እያንቋቋ ያስተውላት ጀመር።

ከብዙ መቁጠጥ በኋላ "ተርፈሻል ጓድ?" ሲል ጠየቃት። አልመለሰችለትም። ባደረገላት ውለታም አላመሰገነችውም። ከተጠየቀችው ጥያቄ ይልቅ ያን ለስለስ ብሎ በመግባት ህሊና ውስጥ እንደ ኤሌክትሪክ የሚነዝረውን ጠንካራ ድምፅ የት እንደሰማች ለመቶኛ ጊዜ ለማስታወስ እየጣረች ነበር።

"ቲር ጋሡ ፀይንሽን ሳይጎዳው የቀረ.." ግና ንግግሩን ሳይጨርስ ማንነቱን ለየችው። "ኮምኒስቱ" ቻርሊ ነው። "አምላኬ እባክህ እርዳኝ?!" ስትል እምላኳን በልቧ ተማፀነች። ስለኮምኒዝምና ስለ ኮሚኒስቶች ማንነት በምዕራባውያን የተጻፉ ጥቂት መጽሀፍት አንብባ ስለነበር በውስጧ የሰረጸው ጥላቻ ፍርሃት ሆና ሰውነቷን ያንቀጠቅጠው ጀመር።

የተጨናበሱትን ዐይኖቿን አፍጥጣ ስትመለከት በግንባሩ ላይ አስሮት የነበረው ቀይ ጥብጣብ የለም። ግንባሩ ተፈንክቶ የደረቀ ደም በፊቱ ላይ ተረጭቷል። የለበሰው ጃኬት ከእጅጌው ተተርትሮ ቀኝ ክንዱ ራቁት ነው። በሩን ከፍተሽ ... ብረሪ ብረሪ የሚል ስሜት ከውስጥ ይተናነቃት ያዘ።

ከኪሱ ነጭ መሀረብ በማውጣት ባልቴቷ ቡና ሲያፈሉ ካቀረቡት የጣሳ ውሃ አፍስሶ ካረጠበው በኋላ "ፀይኖችሽ በጣም አብጠዋል... በውሃ ብናጥባቸው ምናልባት እብጠቱን ይቀንሰዋል" ወደእርሷ በመቅረብ ከአገጯ ቀና አድርጎ ዐይኖቿን ያብሰው ጀመር።

ልቧ ደረቷን ቀዳ ልትወጣ እየታገለች ድም!' ድም! ድም! አለች። ሰውነቷ በላብ ሲዘፈቅ ታወቃት። ፍርሃቷን እንዳያውቅባት ማድረግ የምትችልበትን ዘዴ ስታሰላስልም ባልቴቷ ከወደ ኋላቸው "... ሳይቸግራችሁ እኮ ነው! ሰው እንበለ ብልሃት ያልቃል!" ሲሉ ተሰማት።

"እየሞቱ ነው ትግል እናቴ፣ እየወደቁ ነው ድል!" አለና እጆቹን ከፀይኗ ላይ ሣያነሳ መለሰላቸው።

"አምላክ የተከለውን እርሱ እንጂ ሌላ ላይነቅለው... እንዲያው እለቁ ብሏችሁ እንጂ እውነትስ መንግሥትን ያህል ነገር በናንተ እጅ ይፈርሳል? መጥፊያችሁ በእጃችሁ ይሁን ቢላችሁ ነው!' ሲሉ ሞገቱት።

"ለጨቋኞች አንንበረከክም እናቴ"

ከንግግሩ ይዘት እኩል ድምጹ አንዳች የማሸበር ኃይል አለው። "እስኪ አሁን ዐይኖችሽን ግለጫቸው" አላት የልመና ቃና ባለው ድምፀት-ገለጠቻቸው። እናም ለመጀመሪያ ጊዜ በአጭር ርቀት ዓይኑን ውሃውን አየች። በዚያች ቅጽበት ልቧን እኩል ለእኩል ሰንጥቆ እርግብግቢቷ ድረስ የዘለቀ አንዳች ስሜት ነዝሯት አለፈ። የፍርሃት፣



የድንጋጤ ወይንም የጥላቻ እንዳልነበረ ግን እርግጠኛ ነች። ምናልባት የፍቅር አምላክ በቻርሊ ቀስቱ ሊግርካት ይሆን? በረዥሙ ተንፍሳ ዐይኗን ሰበረች። ይኼኔ በውስጧ ሲወራጭ የነበረው ፍራቻ ተንቅሎ ሲወጣና ቀለል ሲላትም ታወቃት። ስላደረገላት ውለታ ሊታመሰግነው ብትፈልግም አንዳችም ቃል ከአንደበቷ ሊወጣ አልቻለም። ቆይታ "የተፈነከትከውን በውሀ ባጥብልህና ደሙን ብጠራርግልህ አይሻልም?" ስትል እየተንተባተበች ጠየቀችው። ያች ሰዓት በሕይወቷ ውስጥ እኒነቷን ረስታ ከባህሪዋ ውጭ የሆነችበት ሰዓት ነበረች።

በጣቶቹ ግንባሩን ከደባበሰ በኋላ የያዘውን መሃረብ ሰጥቷት በርጩማው ላይ ተመቻችቶ በመቀመጥ ከጭንቅላቱ ቀና አለላት። የሰጣትን መሀረብ ውሃ ለመንከር ዞር ስትል ባልቴቷ በሩ ላይ በደረታቸው ተለጥፈው በጭላንጭል ውጭውን ያስተውላሉ። ሁኔታቸው አስገርሟት ፈገግ አለች።

አገጩን በግራ እጁ ደገፍ አድርጋ ከግንባሩ በስተግራ ያለውን ፍንክት ስትጠራርግለት በዞማ ፀጉሩ መሃል የተበተኑ ሽበቶች ታይዋት። ከግንባሩ ላይ የነበረው ደረቅ ደም ሲፀዳም ገጹ አንዳች ፀዳል መርጨት ጀመረ። ረዘም ብሎ ቀጥ ያለው አፍንጫው በልዩ ትእዛዝ ተቀርጾ የተተከለለት ይመስላል። የተጨፈኑት ዓይኖቹን ቁልቁል ስትመለከታቸው ሽፋላቸውን ቀደው ለመውጣት የሚወራጩ መሰላት። ስስ ከንፈሮቹ ቢደርቁም ማራኪ ቅርጻቸውን አላጡም።

አብዮት፣ ይህ ውብ ገጽታ የኮሚኒስት መሆኑ እውን ነው? ይህ ሰውስ አሸባሪ፣ ነፍሰ ገዳይ፣ እምነት የለሽ አረመኔ ሊሆን ይችላል?! ስትል ራሷን ጠየቀች። ፈጥኖ መርዛማ እሾህ ካለው ከዚህ ውብ አበባ እንድትጠነቀቅ አዕምሮዋ ውስጥ አንዳች የአደጋ ማስጠንቀቂያ ደወል ደጋግሞ በመጮህ እያሳሰባት መሰላት። ሸሚዙ ላይ የተንጠባጠበውን ደም ስትጠርግለት በተገለጠው ሸሚዙ መሀል ደረቱ ላይ የኮከብ ቅርጽ ያለው የብር ጌጥ ተንጠልጥሎ ተመለከተች።

ባልቴቷ ካፈሉት ቡና አንዳንድ ስኒ ጠጥተውና አመስግኗቸው ሲወጡ ነበር አብዮት የአንድ እግር ጫማዋ ተረክዞ መጎመዱን ያስተዋለችው። የደረበችውም ሹራብ የለም። ነጩ ጉርድ ቀሚሷ የፊት ለፊት ከፈፍ ተተርትሮና አቧራ ጠጥቶ ተኰጎርጉሯል።

በጠጠራማው መንገድ ሲጓዙ ሚዛኗን ጠብቃ መራመድ ባለመቻሏ የግራ ክንዱን ጥብቅ አድርጋ በመያዝ ስርቃ ተመለከተችው። የደከመ የሰለቸና ተስፋ የቆረጠ ይመስላል። በመድረክ

ላይ ደጋግማ ያየቻውና ዛሬም በሰልፍ ላይ የተመለከተችው ጥልቅ የሀዘንተኝነት ስሜት በገጹ ላይ እንዳጠላ ነው።

"ደከመሽ ጓድ!" አላት ብዙ ከተጓዙ በኋላ።

ግንባሯን ቅጭም አድርጋ ቀና ብላ አየችው። አይመለከታትም። ድከም ያሉት ዐይኖቹ ከፊት ለፊታቸው በተዘረጋው ጠጠራማ መንገድ ላይ ተተክለዋል።" እኔ እኮ... ኮምኒስት አይደለሁም... ለምን ጓድ እያልክ ትጠራኛለህ?!

"ቢሆንም የትግላችን አንድ አካል ነሽ!"

"ተሳስተሃል ... ባይገርምህ ኮምኒስቶችን ከሚጠሉት አንዷ ነኝ!"

"ለምን?!"

"አሸባሪዎች፣ ነፍስ ገዳዮችና እምነት የለሾች ስለሆኑ!" ለቅጽበት ያህል መለስ ብሎ አስተዋላት። ቀዝቃዛና መርዛማ አስተያየቱ ልቡን ምን ያህል እንዳቆሰለችው አሳዩዋት። "ለኮሚኒስቶች ጥላቻ ቢኖርሽ አይደንቀኝም ግን ስለኮሚኒዝም ያለሽ እውቀት ምን ያህል ነው?" ድምጹ ግን በንግግሯ ቅር የተሰኘ አያስመሰለውም።

ስለ ኮምኒዝም ያነበበቻቸውን መፃህፍት በመጠቃቀስ የኮምኒስቶችን ማንነት በሚገባ እንደምታውቅ ስትገልፅለት ግን በቅሬታ ፈገግታ "የምትጠቅሻቸው መፃህፍት የተጻፉት የኮሚኒዝም ደመኞች በሆኑ ምዕራባውያን ነው፤ ለዚያውም ደግሞ ልብወለዶች ናቸው። ታዲያ እነዚያን ፀረ-ኮምኒዝም መፃህፍት በማንበብሽ ብቻ ኮሚኒስቶችን መጥላት ያለብሽ ይመስልሻል?" ሲል ጠየቃት።

ሳትሚገት ተረታች።

በዚያ ሰዓት ከጠጠራማው መንገድ ወጥተው አስፋልቱን በመሻገር በሰልፈኞቹና በወታደሮቹ መካከል ግጭት የተካሄደበትን አደባባይ አልፈው ነበር። መንገዶቹ ጭር ብለዋል። በዚያ ቀን የልጇን በድን የታቀፈች እናት፣ ባሎቻቸው እንደወጡ የቀሩባቸው ሚስቶች፣ "አባታችንን!" እያሉ የሚጮሁ ያለ አሳዳጊ የቀሩ ህፃናት ቁጥራቸው ምን ያህል ይሆን?

አብነት የቻርሊን ክንድ ይዛ በዱልዱም ጫማዋ የተተረተረ ቀሚሷን እንደለበሰች መንገደኛው ሁሉ ፊቱን እያዞረ አልፎም እየቆመ ያስተውላታል። የአብዮት አደባባይን አቋርጠው ፍላሚንጎ ባር አካባቢ ሲደርሱ ከኋላቸው የመኪና ጥሩምባ ሰማችና ዞር አለች። አሮጌዋ የሰዓሊው አጎቷ ቮልስዋገን ቆማለች።



ሰውነቷ በሀፍረት ተሸማቀቀ። አለባበሷና ጠጉሯ ግማሽ ሲታሰቧት ደግሞ መሬት ተቀዳ ብትውጣት ወደደች። ቻርሊን ቀና ብላ አየችው። ዐይኖቹ በመገረም ፈጠዋል፤ ገጽታውም ጥርጣሬ ይነበብበታል። ለመሰነባበትና አድራሻ ለመለዋወጥ እንኳን ጊዜ ስላልነበራት ከቆመበት ጥላው የመኪናውን በር ከፍታ ገባች።

አጎቷም በመገረም ሲመለከታት ቆይቶ "ዐይኖቼን ማመን አልቻልኩም አብነት። ሠራተኞች በጫሩት አመፅ ውስጥ ተካፋይ ነበርሽ? ይህን ብቻ መልሽልኝ?!" አላት በስጋት የሚቁለጨለጩ ዐይኖቹን በዐይኖቿ ላይ እንደተከለ።

"አዎን ነበርኩ!" አለችው ኮስተር ብላ።

ዘወትር ሲናደድና መንፈሱ ሲሸበር እንደሚያደርገው፣ እየተጣደፈ ኪሶቹን በመበርበር ሲጋራና ክብሪት አውጥቶ ከለኮሰ በኋላ የመኪናዋን ሞተር ቀስቅሶ የቦሌን አቅጣጫ በመያዝ ወደ አብነት ሰፈር አመራ።

"መላው ቤተሰብ አንቺን ፍለጋ በከተማው ውስጥ ተበትኗል። እኔ እንኳን ያልደረስኩበት ፖሊስ ጣቢያ፣ ያልጎበኘሁት ሆስፒታል የለም። በሠራተኞቹ አመጽ ሰልፍ ላይ ነበርኩ ነው ያልሽኝ?... ይህን ማመን አልችልም። አለዚያም አብደሽ ጨርቅሽን ጥለሻል ማለት ነው!" አላት የመኪናውን መሪ እየቀጠቀጠ። አልመለሰችለትም።

"ማን ነበር አብሮሽ ያየሁት ሰው?" አንገቱን መለስ አድርጎ ሲጠይቃት ዐይኖቹ ላይ ያየችው ስጋት ፈጥና መልስ ከመስጠት እንድትቆጠብ አደረጋት።

"ንገሪኝ እንጂ!" ጮኸባት።

ልትዋሸው አልፈለገችም። እውነትን ይዞ በተቃውሞና በአደጋ ፊት በፅናት መቆምን ገና ከልጅነቷ ጀምሮ የቀረፀባት እርሱ እራሱ ነውና። "ኮሚኒስት ነው!" አለችው ሳትጠራጠር።

"በትክክል ነው ያዳመጥኩሽ?!" ዐይኖቹ ፈጠጡ።

"አዎን ጋሼ፣ ቻርሊ የሚሰኘው ተዋናይ እርሱ ነው። ኮምኒስት ነው" እያለች እውነቱን አፍረጠረጠችለት። ሰዓሊው ያቀጣጠለውን ሲጋራ በመስኮት ወርውሮ በዝምታ ማሽከርከሩን ቀጠለ።

"ኮምኒስቶችን ትጠላለህ እንዴ?" ስትል እየተጠራጠረች ጠየቀችው። አልመለሰላትም። የመኪናዋን ፍጥነት እያበረደ የመንገዱን ጠርዝ አስይዞ ካቆማት በኋላ ሌላ ሲጋራ ለኮሰና በረዥሙ ተነፈሰ።

"ኮምኒዝምን እንጂ ኮምኒስቶችን የምጠላበት የጠቆረ ልብ የለኝም። በሥነጥበብ ስብዕናዬ ለመላው የሰው ዘር ፍቅርና ርህራሄ እንጂ ጥላቻ ፈፅሞ የለኝም። የምጠላው አንድ ነገር ቢኖር በአንቺ ላይ እያንዣበበ ያለውን አደጋ ብቻ ነው። አብነት፣ በዚህ ዓለም ላይ እኔንና ውጫዊውን ዓለም የምታገናኝው የመጨረሻዋ ድልድይ አንቺ ብቻ እንደሆንሽ ታውቂያለሽ... ይሄ ድልድይ እንዲሰበር ደግሞ አልፈልግም" አላት። እውነት አለው። የህይወት አዚሙን በሞያው ያጠረ፣ ብቸኛ ፍጡር ነው። የእናቷ ወንድም እንደመሆኑ ከቤታቸው አዘውትሮ ሲሄድም፣ ከአባትና ከእናቷ ይልቅ የሚግባባው እርሷ ጋር ነው። ለእርሷ ልዩ ፍቅር አለው እርሷም ለእርሱ። አንገቷን ደፍታ ድምጿን ውጣለች። አይቷት እንደገና ቀጠለ። "የእውነተኛ ኮምኒስት ሥነ ምግባር ምን እንደሆነ ታውቂያለሽ? ራስን አቀፀትና ቁልቁለት ለማይለየው ዓላማ ለኮሚኒዝም በመስዋዕትነት ማቅረብ ነው። ከሞት ጋራ እየተጋፉ መኖር። በተለይ ዛሬ፣ በሺ የሚቆጠሩ ዜጎች በሚረግፉበት ክፉ ጊዜ በሠራተኞች አመጽ ላይ ተሳትፈሽ ነበር አልሽኝ?" እንደመተከዝ ብሎ በረጅሙ ተነፈሰ። አልመለሰለችለትም።

"አብነት፣ ይሄን አድምጭኝ። እንደ አርቲስትነቴ ተፈጥሮ አብዝታ ውብትን የገለጸችብሽ ድንቅ ሥራዋ በመሆንሽ መኖር! መኖር! ገና ብዙ መኖር አለብሽ... እላለሁ። በስጋ ደግሞ የአንድ እህቴ ልጅ በመሆንሽ የሥጋና የመንፈስ ስቃይሽ የኔም ስቃይ ነው" ሊቀሰቅሳት ትከሻዋን መታመታ አደረገ።

"በመጨረሻ ልነግርሽ የምፈልገው፣ የመንገሻ የኔህ ልጅ መሆንሽንም ምንጊዜም እንዳትዘነጊው ነው። የአብራኩ ክፋይ አንቺ ብቻ እንደመሆንሽ የዚያ ሁሉ ሀብቱ ብቸኛ ወራሽም አንቺው መሆንሽን ሳስታውስሽ እወዳለሁ። እና ዐይንሽ እያየ በሚንቀለቀል እቶን ውስጥ የእሣት ራት ሆንሽ የምትመሰጊበትን ቢያንስ አንድ ምክንያት ንገሪኝ?" አላት በቁጭት እየተንጨረጨረ።

"ጋሽዬ፣ እኔ እኮ ኮምኒስት አይደለሁም። እንዲያውም ኮምኒስቶችን ከሚጠሉት አንዷ ነበርኩ" አለች ቀና ብላ እያየችው።

"ነበርኩ ስትይ አሁንስ ምንድነኝ ማለትሽ ነው?"

ጥቂት ካሰበች በኋላ "ማለቴ ... አሁንምኮ ኮምኒስቶችን እጠላለሁ" አለችው። አንደበቷ የሚናገረውን ግን እየተጠራጠረች ነበር።



"እንግዲያውስ ቻርሊ ከምትይው ሰው ልትርቂ ቃል ግቢልኝ!" ሲል ተማፀናት ሰዓሊው። ሆኖም ምክንያት ልትሰጥ በማትችልበት ምክንያት አንደበቷ ተሳስሮ በዝምታ ተዋጠች።

"አብነት፣ አብረን ባሳለፍናቸው ዓመታት እማፀንሻለሁ ቃል ግቢልኝ!" እላት ዐይን ዐይኗን እያየ። ከልጅነቷ ጀምሮ ያባትና የልጅ ያህል፣ ያስተማሪና የተማሪ ያህል ሆነው ያሳለፏቸውን ድንቅ ዓመታት እየጠራ ሲማፀናት መንፈሷ ተሸበረ።

በመጨረሻም "ጋሽዬ፣ በፈጣሪ ይሁንብህ አታስጨንቀኝ! አሁን ቃል ልገባልህ አልችልም" ስትል መልሳ ተማፀነችው።

ሰዓሊው ተስፋ በቆረጠ ስሜት ለረዥም ጊዜ በዝምታ ሲመለከታት ቆይቶ በቅሬታ ራሱን ወዘወዘና "አብነት፣ ወደ ህይወትና ወደ ሞት በሚያመራ መንታ መንገድ ላይ እንደቆምሽ ይሰማኛል። እርግጠኛ ነኝ አሁን ልጅ አይደለሽም፤ የሃያ አምስት ዓመት አድሜ የሚፋጀውን እሳትና የሚቀዘቅዘውን ውሃ ለመለየት ትንሽ እድሜ አይደለም። የአፈር መፍጫዎቹ ዓመታት አልፈዋል። ከንግዲህ ለራስሽ እወቂበት፤ ምርጫሽ የህይወትን ጎዳና መከተል እንደሚሆን ግን አምናለሁ" አላት ትንፋሹን ሳብ እያነቀው።

መኪናዋ አብነት መኖሪያ ቤት በር ላይ እስክትደርስ ድረስ አንዲትም ቃል ከአንዳቸውም አንደበት አልወጣችም። በሩን ለማስከፈት የመኪናዋን ጥሩምባ እያስጮኸ "በዚህ ሁኔታ አባትሽ ቢያዩሽ ምን እንደሚፈጥሩ ለመገመት ትችያለሽ?" ሲል ጭንቀቱን ሳይደብቅ ጠየቃት። አልመለሰችለትም።

"ገላሽን ለመታጠብያና ልብስሽን ለመቀየሪያ ጊዜ እንድታገኚ አባትሽ እቤት እንዳይኖሩ ፀልይ" አላት ማንባሩን እንደቋጠረ።

"እምላኬ፣ እባክህ እርዳኝ?!" ስትል አጉተመተመች።

አባቷ አለመኖራቸውን ያረጋገጠችው ጥቁሯ ማርቸዲስ በግቢው ውስጥ አለመኖሯን ከተመለከተች በኋላ ነበር። የሰዓሊው መኪና ገና የግቢውን የብረት በር አልፋ እንደገባች የቤቱ ሠራተኞች ከበቧት። እናቷ አጭር ደልዳላ ሰውነታቸውን እያንከባለሉና ነጠላቸውን እየጎተቱ በሳሎን በር በኩል ወጡ።

አብነት ከመኪናው እንደወጣች ሁኔታዋን ሲመለከቱም ነጠላቸውን ወርውረው ቀሚሳቸውን ለመቅደድ እየታገሉ "አብነቴ፣ ...

ትገድይኝ? ትገድይኝ? በበሽታዬ ላይ በሽታ ሆነሽ ትጨርሽኝ?" እያሉ መጮህ ጀመሩ።

ልጂ በሀዘን ተኮማተረ። እንደዚያ ሲሆኑ ቆማ መመልከት ባለመቻሏም በሁለት እጆቿ ጆሮዎቿን ደፍና በዋናው በር በኩል ወደ መኝታ ቤቷ ሮጣ ገባች።

ገላዋን ተለቃልቃና ፒጃማዋን ለብሣ በረንዳ ላይ እንደቆመች ነበር አባቷ ከፍለጋ የተመለሱት። የውጭው በር ተከፍቶ በሾፌር የምትሽከረከረው ማርቸዲስ ወደ ቅጥር ግቢው ስትገባ አብነት በቆመችበት መንቀጥቀጥ ጀመረች።

ከመኪናው ወርደው ወደ ቤት ሲያመሩ በረንዳው ላይ ለአፍታ ዐይን ለዐይን ገጠሙ። ጎላጎላ ባሉት ዐይኖቻቸው ውስጥ እልህ ይንቀለቀላል፤ ከንፈሮቻቸው በንዴት ይንቀጠቀጣሉ። ከእግር እስከ ራሷ በግልምጫ ከገረፏት በኋላ ጥለዋት ወደ ቤት ገቡ። የዘወትር ጠባያቸው ነው። የተቀየሙትን ሰው ፊት ለፊት አይጋፈጡትም። ያርቁታል፤ ይንቁታል፤ ይበድሉታል። እያንዳንዱ የቤት ሰው፤ እናቷንም ጨምሮ እርሳቸውን ባየ ጊዜ ፀድንጋጤ የሚርደው፣ በፍርሃት የሚሽማቀቀውም በዚሁ ጋግርት ጠባያቸው የተነሣ ነው። ከሁሉም በላይ ባየቻቸው ቁጥር በስጋት ነፍስና ስጋዋ የሚበጨቀው ደግሞ የአብነት ነው።

እናም አባቷ ጥርስ ውስጥ በመግባቷ ሊደርስ ስለሚችለው ችግር እያሰበች ከቆመችበት ሆና ትተክዝ ጀመር።

*** *** ***

አብነት የሥራ ልብሷን አውልቃ ፒጃማዋን ካጠለቀች በኋላ በረንዳው ላይ ነፋስ በመቀበል ላይ ነበረች። ሠልፉ ከተካሄደ ካንድ ሣምንት በኋላ።

መሠረቱ ከፍ ብሎ ከተሠራው ቪላ በረንዳ ላይ ቁልቁል ሲመለከቱት የግቢያቸው ልምላሜ አይታን ገዝቶ መንፈስን ይሰርቃል። የአጥሩን ግንብ ተንተርሰው የተተከሉት ረዣዥም የጥድ ዛፎች፣ መደብ ላይ የተተከሉት ባለ ልዩ ልዩ ቀለማት አበቦች፣ በግንቡ ላይ በደረታቸው የሚሣቡ ሰፋፊ ቅጠል ያላቸው የሀረግ ተክሎች፣ ለመናፈሻ በተተወው ክልል ላይ በየጊዜው እየተከረከመ አረንጓዴ ምንጣፍ መስሎ የተዘረጋው ሣር ግቢውን ምድራዊ ገነት አስመስለውታል።



ግራና ቀኝ መደዳውን ረጃጅም የግንብ አጥሮችን ተገን አድርገው የተሠሩ ትላልቅ ቤቶች የብረት በሮቻቸው እንደተከረቸሙ ናቸው። በግንቦቻቸው አናት ላይ የተሰኩትን ስሊታም የጠርሙስ ሰባሪዎችንና በሮቻቸው ላይ የተተከሉትን የጠር ቅርጽ ያላቸው ሹል የብረት ዘንጎች ስትመለከትኝ ውስጡ የሚኖሩት ነዋሪዎች ውጫዊውን ዓለም እንደሚፈሩ ገመተች።

የዚያ መንደር ጠባይ ይገርማታል። ጎረቤት ከጎረቤት አቦል ቡና አይቃመስም። የሰፈሩ ህፃናት ግቢያቸው ውስጥ ተገልለው እንጂ በጋራ ሆነው አይቦርቁም። እድር፣ እቁብ፣ ሰንበቴ፣ ዝክር የሚባሉት የማኅበራዊ ግንኙነቶች አይታወቁም። መንደሩ አብዛኛውን ጊዜ ጭር እንዳለ ነው። የሰው ዘር ባካባቢው ለመኖሩ የሚታወቀው ከቪላቤቶቹ ጀርባ ከተሠሩት የጭስ ቤቶች ሽቅብ የሚትጎለጎል ጥቁር ጭስና ጣፋጭ መአዛ ያለው የምግብ ሽታ በመኖሩ ብቻ ነው። ፀጥታው የመቃብር ያህል ይከብዳል። እንደ አባቷ አገላለጽ ግን ያ መንደር ከምድራዊው ሲኦል ያመለጡ ብልሆች የራሳቸውን ምድራዊ ገነት ፈጥረው የተሸሸጉበት አምባ ነው። በምድር ሲኦል የሚጠበሱ ጎስቋሎች የሚቃጠል ገላ እንዳይሸታቸው፣ ዋይታቸው እንዳያደነቁራቸው፤ እንደ ኪሩቤል ሰይፍ የሚቆጥሩትን ረጃጅም የግንብ አጥር ከለላ አድርገውታል።

ከመኖሪያ ቤቷ ትይዩ ባለው ሰፊ ሜዳ ላይ ደግሞ ብቻውን የቆመ ግዙፍ ባህር ዛፍ ከአናቱ ወደ ግራ አዘንብሏል። የግንቦት ፀሐይ ሳያደክመው እንዳልቀረ ገመተች።

ይህን ትልቅ ባህር ዛፍ ባየች ቁጥር ደመ - ነፍስ አንዳች እውነት የነገራት ያህል ዘወትር ልቧ በሀዘን ይወጋል። ዛፉ ቅርንጫፎች ላይ አሞሮች ማማ ሠርተውበታል፤ አእዋፍ ጎጆቸውን አንጠልጥለውበታል። አሞሮቹ ትላልቅ ክንፎቻቸውን እያራገቡ ሲነሱና ሲያርፉ መንፈሷን በነፃነትና በደስታ ስሜቶች እንደሚያመጥቁባት ሁሉ ጭንቅላታቸውን ክንፎቻቸው ውስጥ ሸጉጠው በዝናብ ሲቀጠቀጡ ማስተዋሉም በመንፈሷ ውስጥ አንዳች የሀዘን ድባብን ይጭኑባታል።

የዛለው ሰውነቷና የደከመው መንፈሷ እረፍት ቢፈልግም፣ ጀንበር እስክትጠልቅ ግን ካለችበት አልተንቀሳቀሰችም። መኪናዋ ለማሸሽ የምትፈልገው የቻርሊ ምስል ከፈኩት አበቦች መሀል ብቅ እያለ፣ ግዙፉ ባህር ዛፍ ቅርንጫፎች ላይ እየተንጠለጠለ እንዲሁም የበረንዳውን ጌጠኛ የብረት ማእዘኖች እየተደገፈ "... ቢሆንም የትግላችን አንድ አካል ነሽ..." እያለ በዐይኖቹ ሲያባብላት፣

በፈገግታው ሲያንሆልላት ይታያታል። ጭንቀትና ፍርሃት ያጠቆረው የሰዓሊው ገጽታ ደግሞ የቻርሊን ምስል እየሻረ "...አቢ፣ ወደ ህይወትና ወደ ሞት በሚያመራ መንታ መንገድ ላይ እንደቆምሽ ይሰማኛል" እያለ ሲማጸናትና ሲያስጠነቅቃት፤ ሣራ ጋዴም ዐይኖቿን እያርገበገበች፣ ከንፈሯን እያንሻፈፈች በምጸት ስትስቅበት መላ ቅጡ የጠፋ የሃሣብ ማዕበል ሲደፍቃትና ሲያንሳፍፋት አመሸች።

በውስጧ የተፈጠረውን ቅራኔ ማስታረቅ አለመቻሏና ገና ከልጅነቷ ዓመታት ጀምሮ እንደ አባት፣ እንደ ወንድምና እንደ አስተማሪ ሆኖ ያሳደጋትን የአጎቷን ማስጠንቀቂያ ከቁብ ሳትቆጥር ለቻርሊ ፈገግታ መረታቷ ራሷንም አስገርሟታል። ወንዶችን መራቅና ከፍቅር ጣጣ ነፃ ሆኖ መኖር የህይወቷ መሠረታዊ መርህ ከሆኑ ቁም ነገሮች አንዱ ነበር።

እናቷ ገና ትንሽ ልጅ ሣለች ከምትተኛበት ክፍል እየመጡ ከእንቅልፏ ይቀሰቅሷት ነበር። ያኔ ፀጉሯ የሸፈነውን ክብና ድንቡሼ ፊት በትናንሽ ጣቶቿ እየገላለጠች፣ እንቅልፍ ያልጠገቡ ዐይኖቿን በመዳፏ እያሻሸች አንድ ዐይኗን አጨናቁራ ሸቅብ ትመለከታቸዋለች። እናቷም ከአልጋው ውስጥ ታቅፈው ካወጧት በኋላ በውስጥ ልብሷ ላይ የራሳቸውን ጋቢ ደርበውና ነጠላ ጫማዋን አጫምተው እጆቿን እየጎተቱ ወደ መኝታ ቤታቸው ይወስዷታል።

አልጋቸው ላይ አስቀምጠው ግራ እጃቸውን ትከሻዋ ላይ ጣል ያደርጉና በቀኝ እጃቸው እምቡጥ ባቄላ የመሳሰሉትን ጣቶቿን እያፍተለተሉ "አብነቴ፣ ዛሬ ብቻዬን ነኝና ከኔ ጋር ነው የምታድሪው። ብቻዬን ስሆን እፈራለሁ" ይሏታል ሀዘን በሰበረው ድምጽ።

"አባባስ?" ብላ ትጠይቃለች፤ ዘወትር መልስ የማታገኝለትን ጥያቄ። እናቷ በወፍራሙና ለስላሳ ክንዳቸው እቅፍ አድርገዋት ሲተኙም ቢሆን እንቅልፍ አይወስዳትም። ትንሹ አይምሮዋ በሀሳብ ባህር ውስጥ እየዋኘ ዐይኖቿን እንዳፈጠጠች ለብዙ ጊዜ ትቆያለች።

ማንቀላፋቷን ለማረጋገጥ ቀና ቢሉ ዐይን ለዐይን ይጋጩና ተፋጠው ይቀራሉ። በጉንጫቸው ላይ መንታ መንታ ሆኖ ኩልል እያለ የሚወርደውን እንባቸውንና የደፈረሱ ዐይኖቻቸውን ስትመለከት ደግሞ ምክንያቱ ባይገባትም፣ የእርሷም እንባ አብሮ ይወርዳል። ዐይኗም አብሮ ይቀላል።

የዘወትሩ የእናቷ እንባ እንቆቅልሽ በትንሹም ቢሆን የተፈታላት ትንሽ ካደገች በኋላ ነበር። አንድ ጠዋት ከናቷ ጋር አድራ



በኋለኛው በር ላይ የማለዳ ፀሐይ ብመሞቅ ላይ ሣለች፣ በሠራተኞች ቤት ውስጥ የሰማችው ሣቅና ሹክሹክታ ይሰባትና እንደዋዛ ጆሮዎቿን ጣል ታደርጋለች።

"ጌቶችኮ ዛሬም እንደ ልማዳቸው ቤት አላደሩም" አለች አልጋ አንጣፊዋ።

"የታደሉ ሰውዬ፤ በሚስት ላይ ሚስት፣ በቅምጥ ላይ ቅምጥ አስልፈው ለቤታቸው አልጋ መች ጊዜ ይኖራቸዋል?!" አለ ወጥቤታቸው በሽሙጥ።

"ኧረ እኔስ የበሽታ ነው የሚመስለኝ... ሆሆሆይ! ሰውየውኮ በቁማቸው ማለቃቸው ነው!" አለች አልጋ አንጣፊዋ መልሳ።

ሳቃቸው ከጣራ በላይ ሲዘልቅ በብሽቀት ወደ መኝታ ክፍሏ ሮጣ ገባች።

"በቅምጥ ላይ ቅምጥ" የሚለው አማርኛ ባይገባትም "በሚስት ላይ ሚስት" የሚሉት ቃላት ግን ለእናቷ እንባ ምክንያቱ ምን እንደሆን ገለጹላት። በሀዘን ተውጣ በመስኮት በኩል ወደ ውጭ ስትመለከት፣ አባቷ ከመኪና ወርደው በድካም ዝሎ የጎበጠ ረዥም፣ ቀጭን ሰውነታቸውን እየጎተቱ ዐይናቸው አብጦና ቀልቶ ሲንጠራወዙ ስታይ ሰይጣን መሰሏት። ሳታስበው እንዳች የጥላቻ ስሜት ወረራት። ከዚያን ጊዜ ወዲህም አባቷን ትፈራቸው፣ ትሸሻቸውና በሆዷ ታንቋሽሻቸው ጀመር።

እያደገች ስትመጣም በየቤቱ ጣራ ሥር በትዳር ስም የተቀመጡ ሴቶች ሁሉ ባሎቻቸው በባርነት የገዟቸው ምስኪኖች መስለው ይታዩዋት ነበር። ሁሉም እንደናቷ በቅናት እየተንገበገቡ የሚቃጠሉ፣ ወንዶቻቸውም እንደአባቷ ባሮቻቸውን ዘወትር የሚያስለቅሱና ርህራሄ የሌላቸው ሀሊና ቢስ አውሬዎች እንደሆኑ አመነች።

በመሆኑም ትምህርት ቤት ለምታያቸው ወንዶች ሁሉ የነበራት አስተያየት ለአባቷ ከነበራት ግምት ያልተሻለና ፍራቻዋም የከፋ ሆነ። እናም አሁን እምነቱን በውል የማትረዳውና ማንነቱን በውል የማታውቀው ሰው ይህን አብሯት ያደገና ከደሟ የተዋሃደ ፍራቻ አስወግዶ እንደምን ሊፈታተናት እንደቻለ ይገርማታል። ምናልባት ለውብት ጣአት ተንበረከካ መስገድ መጀመሯ ይሆን?!

የደረበችውን ጋቢ አስተካክላ የዛለ ሰውነቷን እየጎተተች ወደ መኝታ ክፍሏ ገብታ በአበባ ምንጣፍ ባሸበረቀው የአልጋዋ ጠርዝ ላይ

አረፍ አለች። እንስተኛ ጠረጴዛ ላይ ራቷ በሣህን ተከድኖ ተቀምጧል፤ በስለቹ ዐይኖቿ ገረመመችው። የምግብ ፍላጎቷ ጠፍቷል። ከሰዓሊው የተዋሰቻቸው ሁለት የእንግሊዝኛ ልብ ወለድ መጽሀፍትም በመጽሀፍ መደርደሪያዋ ላይ እንደተቀመጡ ናቸው። በዚህ ሰዓት በልብ ወለድ ገፀ-ባህሪያት ተመስጣ ራሷን መርሳት አልፈለገችም። ምናልባትም የገሃዱን ዓለም እውነት ለመጋፈጥ ገና ዐይኖቿን እየገለጠች ይሆናል።

የለበሰችውን ጋቢ ጥላ መኝታ ክፍሏ ማእዘን ላይ ወደቆመው የቁም ሣጥን መስተዋት በማምራት ፊት ለፊት ቁማ የምታየውን ምስል ከቻርሊ ቁመና ጋር ማወዳደር ጀመረች።

አልረካችም። ከርሷ ይልቅ የቻርሊ ውበት ጎላባት፤ ከርሷ ቁመና ይልቅ የርሱ አካል ገዘፈባት። "ሰዓሊው... ተፈጥሮ አብዝታ ውበትን የገለጸችብሽ ልዩ የኪነጥበብ ሥራዋ ነሽ የሚለኝ ለየትኛው ውበቴ ነው?" ስትልም ራሷን አጣጥላ ጠየቀች።

ተከድኖ የተቀመጠው ሣህን የበግ ወጥ አልጫ ፍትፍት እንደያዘ ተከድኖአል። አብነት በጣቷ ቆንጠር አድርጋ ቀመሰችው። አላምጣ መዋጥ ግን አልቻለችም። ያኘከችውን የሣህን ክዳን ከነበረበት መልሳ የጎረሰችውን እንደ ምንም ታግላ ዋጠች።

ጥቅልል ብላ ለመተኛት ሞከረች። አልሆነላትም። ህሊናዋ ግድግዳ ላይ ከተለጠፈው የቻርሊ ምስል ጋር እንደ ተፋጠጠች የንጋት ወፍ በዝማሬዋ የምሽቱን ማብቃት አበሰረቻት።

በመጪዎቹ ተከታታይ ቀናትም ቢሆን የቆሰለ ልቧን ስታስታምምና ስታባብል ሰነበተች። የቻርሊ ምስል በሄደችበት ይከተላታል። ስትበላ፣ ስትጠጣ፣ ስትተኛ፣ ከቤተሰቦቿ ጋር ስትጫወት፣ በሥራ ቦታዋ የድርጅቱን የሂሣብ መዝገብ ስትገልጥ ሳይቀር ብቅ እያለ ይታያታል። ቤትም ውስጥ ሳለች ከንፏ እንደተሰበረ የፎግብ ጫጩት አንዱን ጥግ ተገን አድርጋ የምታሰላስለው ቻርሊን ነው፤ የምታየው፣ የምታዳምጠው በስመመን የምትዳስሰው ሁሉ ቻርሊን ነው። ለውጭውም ዓለም ፍጹም ባእድ እየሆነች መጣች። ከሰው እየራቀችና በብቸኝነት እየተኮራመተች በራሷ ዓለም ውስጥ ስትሰጥም ብቻ ነው ትንሽ እፎይታ የምታገኘው።

በዚያን ሰሞን ለምታደርገውም ሁሉ ምክንያት አልነበራትም። ሌላው ቀርቶ ለማፍቀሯም ይሁን ለመፈቀሯ እርግጠኛ አልነበረችም። ለረዥም ዓመታት ለወንድ ልጅ ያልተበገሩት የልቧ በሮች እንዲህ



ተበርግደው እርሱን በመናፈቃቸው ተደንቃም "ምንኛ ምትሀቱኛ ነው?" ስትል በገረሜታ ራስዋን ጠየቀች።

መንጋትና መምሸታቸውን በውል በማታስታውሳቸው በነዚያ ቀናት፣ እነኛ ሽፋሽፍቶቻቸውን ቀደው ሊወጡ የሚወራጩ ይመስሉ የነበሩት የቻርሊ ዐይኖች ለረዥም ዓመታት የምታውቃቸውን ያህል ይናፍቋት ጀመር።

ራሷን መቆጣጠር አልተቻላትም። በውስጧ የታመቀውን ሃይል አፍና መያዝ አቃታት። የልቧን ስቃይ ማስታመም እየተሳናትም ሳታስበው እንባዋ ኩልል ብሎ የሚወርድበት ጊዜ መጣ። "ማፍቀር ወይስ፤" "ማበድ መጀመሬ ይሆን?" እያለች ትጨነቃለች።

አንድ ቀን ቢሮዋ ተቀምጣ በተገለጠው የሂሣብ መዝገብ ላይ አቀርቅራ ስትተክዝ ሣራ ጋዴም በሩን አንኳኩታ ገባች። በፈገግታ ተቀበለቻት። የሣራ ዐይኖች ያረፉት ግን በአብነት ፈገግታ ላይ ሳይሆን በለበሰችው አዲስ ባለ ፉር ጃኬት ላይ ነበር።

"ጉድ አፍተር ኑን አቢ! በዚህ መዝገብ ላይ እንዳቀረቀርሽ አንድ ቀን ጭንቅላትሽ ተቀንጥሶ ሳይንከባለል አይቀርም ... ቂቂቂቂ ...." እያለች ዐይኗን ከአዲሱ ባለ ፉር ጃኬት ላይ ሳትነቅል እጇን ለሰላምታ ዘረጋችላት።

"ሥራ ህይወት ነው ያለው ማን ነበር?" አለቻት አብነት እጇን እየጨበጠች።

"ህይወትስ ዳንስ! ቂቂቂቂ ... ይሄ ሥራ የሚሉት ነገር ባይኖር ኖሮ የሰው ልጆች ስንትና ስንት የዳንስ አይነት መፍጠር በቻሉ ነበር ... ቂቂቂቂ ..." አብነትም ከልቧ ሣቀች።

"ውው አብነት! ነፍስ ጃኬት ገዝተሻል፤ የየት ሀገር ነው?" ስትል ገና መቀመጫዋ ወንበር ከመንካቱ ጠየቀቻት።

"የጣሊያን ነው" አለች አብነት ጃኬቱ ኮሌር ላይ የተለጠፈውን ምልክት እያሳየቻት ።

"ፖ! ነፍስ ነው። ምን ነበረበት አምላክ ጣሊያኖችን ብቻ ፈጥሮ እኛን ቢረሣን ኖሮ .... ቂቂቂቂ።"

አብነት አሁንም ሣቀች።

"እኔም እንድ ሣምንት እዘንጥበታለሁ፤ አይደል አቢ?"
"እንዴታ!" አለች አብነት ያለ ቅሬታ።

ሁለቱም በዝምታ ለአጭር ጊዜ ከተቀመጡ በኋላ አብነት ያላሰበችውን ጥያቄ ሣራ ድንገት ጠየቀቻት። "አቢ? እስኪ ሳትደብቂ ንገሪኝ፤ ሰሞኑን ምን ሆንሻል?!"

አብነት ደነገጠች "ይሄን ያህል ሰው እስኪያውቅብኝ ድረስ የባህርይ ለውጥ አሳይቻለሁ ማለት ነው?" ራሷን ጠየቀች።
"ንገሪኝ እንጂ አብነት?!"
"ምን ሆኛለሁ? ምንም!" አለች አብነት ከንፈሯን እንደማለች። ቀና ብላ የሣራን ዐይኖች ለማየት ግን አልደፈረችም።
"እርግጠኛ ነሽ አቢ?!"
አብነት አልመለሰችላትም። እንዳቀረቀረች ቀረች።
"አቢ፣ አብረን ማደጋችን ተረሳሽ? ባሳለፍናቸው ዓመታት ውስጥ እንዲህ ተለውጠሽ አታውቂም። ገጽሽም እየረገጣ እኮ ነው። አትደብቂኝ አንድ ነገር ሆነሻል" አለቻት በርህራሄ ዐይን እያየቻት።

ከረጅም ዝምታ በኋላ አብነት ካቀረቀረችበት ቀና ብላ "ሣራ፣ እስኪ ስለቻርሊ የምታውቂውን ያህል ንገሪኝ?" አለቻት እየፈራች።

ሣራም በቅብዝብዝ ዐይኖቿ ትክ ብላ ስትመለከታት ቆይታ "ቻርሊ?!" ስትል ስሙን ደግማ ጠራችው።
አብነት በአዎንታ ራሷን ነቀነቀች።

የሣራ አይኖች ፈጠጡ። "ስለ ቻርሊ ማወቅ የፈለግሽው ምንድን ነው?" ግራ ከመጋባቷ የተነሳ እንደበቷ መተሣሰር ጀምሯል።
"ስለ እሱ የምታውቂውን ሁሉ!"
"ግን ለምን አብነቴ? ለምን?!"
"ማወቅ ስለምፈልግ!"
"የጠየኩሽ እኮ ስለርሱ ማወቅ የፈለግሽበትን ምክንያት ነው" አለች ሣራ ግንባሯን ቅጭም አድርጋ።

አብነት በዝምታ ማሰብ ጀመረች። "ለምን ችግሬን ሁሉ ዘርዝሬ አልነግራትም" ስትል አሰበች። "ጭንቀትን ለሁለተኛ ሰው ሲያካፍሉት ይቀላል፤ ተራራ ያከለው ችግር ይናዳል" ሲሉ ሰምታለች። እናም በሜይ ዴይ እለት የሆነውን ሁሉ በዝርዝር አጫወተቻት።



ሣራ በርጋታ ካዳመጠቻት በኋላ በመጀመሪያ የግዛ ጆሮዋን፣ ቀጥሎ ደግሞ የጓደኛዋን ጤንነት ተጠራጠረች። ግንባሯን ቅጭም፣ ዐይኖቿን ፍጥጥ፣ ሽፋሎቿን እርግብግብ አደረገችና "አብነቴ፣ የምትናገሪው ሁሉ የምር ነው ወይንስ ትቀልጂለሽ?" አለቻት።

አብነት ሁሉም ነገር የቀልድ መሆኑን ተመኝታ የቅሬታ ፈገግታ ፈነጠቀችላት። ይኼኔ "ሊሆን አይችልም አብነት! ይሄ ፈፅሞ ሊሆን አይችልም!" እያለች ሣራ ሣታስበው ጮኸች።

አብነት የወንድ ጓደኛ እንድትይዝ ሣራ ያላደረገችው ጥረት አልነበረም። ከትምህርት ቤት ጀምሮ። ሁለቱም ሥራ ከያዙ በኋላ እንኳን ከብዙ ሰዎች ጋር አስተዋውቃታለች። አብነት ግን የወንድ ጥላቻዋ ጋግርት ሁሌ እያገረሸባት ቀልቧ እንዳቸውንም አልመረጠም።

አሁን ታዴ ልቅልቁ የሚተው ሰው ነበረ? የጠራ ብርጭቆ የሚመስል ዐይኑ ስንቷን እንዳልጣለ፣ የተሸለመ ዘንግ የመሰለ ቁመናው ስንቷን ፀጉር ለፀጉር እንዳላናጨ፤ ከአብነት ጋር ብታስተዋውቃት "ይሄ አሻንጉሊት የመሰለ ሰው፣ እንደ ሰው በደም ሥሩ ውስጥ ሞቃት ደም ይመላለሳል ብለሽ ነው? አይመስለኝም። ሞዳ ኖቫ ሱቅ ውስጥ ከቆሙት አሻንጉሊቶች በምን ይለያል?" ብላ የሣራን ወሽመጥ ቆርጣዋለች።

ጌራንስ ቢሆን "የዚህ ሉጫ ፀጉር ትንሽ ረዘም ብሎ ከዳሌው ለቀቅ ቢል ኖሮ እኔን ይመስል ነበር። የተቀባው ሽቶኮ ልክ እማዬ የምትቀባውን አይነት ነው"ስትል አፌዘባታለች።

ታየን ብታስተዋውቃት፤ የፈረጠመ ጡንቻውንና እንደ ኳስ ያበጠ ደረቱን አይታ "ይሄ ጥሩ ቦቅሰኛ እንጂ ጥሩ አፍቃሪ ሊሆን አይችልም" ስትል አጣጣለችው። ታየ የሚያሽከረክራት እንደ ውሃ የምትፈሰውና ለከተማው አዲስ የሆነችው መኪና እየቆጨቻት ሣራ አብነትን በሆዷ ረገመች።

ተስፋ ሳትቆርጥ የዐይን እሸትን ደግሞ አስተዋወቀቻት ። "ይሄ ቅንዝረኛ ይመስላል" ስትላት ግን ሣራ ብሽቅ ብላ "ላንች የሚሆን ቦይ ፍሬንድ በልዩ ትእዛዝ በጃፓን ፋብሪካዎች ባንዱ ተሠርቶ እስኪመጣልሽ አፍሽን ከፍተሽ ተቀመጭ። በሃያ አምስት ዓመት እድሜሽ ልጃገረድ ነኝ ብለሽ ማውራት የሚያሣፍር እንጂ የሚያስከብር እንዳይመስልሽ። ያለሽበት ዘመንኮ ሃያ አንደኛው ክፍለ

ዘመን ነው። ግባሽ!" ብላት አከርፋ ሄዳለች። አብነት ሣቀች እንጂ በዚህ ንግግሯ አልተቀየመችም።

ሣራ ይህን ሁሉ ስለምታውቅ አሁን አብነት የምትናገራትን አምና መቀበል አልተቻላትም።

"ሣራ፤ እውነቱን ንገሪኝ አላልሽም? እንግዲያውስ የነገርኩሽ ሁሉ እውነት ነው" አለች አብነት የሚተናነቃትን እንባ ለማቆም እየታገለች። አልሆነላትም። እንባዋ እየተንከባለለ ጉንጮቿን በማቋረጥ ወደ ደረቷ መውረድ ጀመረ።

ሣራ በሁኔታዋ ግራ ስለተጋባች ከትልቁ ቦርሳዋ ውስጥ መሀረብ አወጣችና እንባዋን ትጠራርግላት ጀመር። የአብነት እንባ ግን ግድቡን እንደጣሰ ውሀ ፍጥነቱን ጨምሮ መንዠቅዠቁን ቀጠለ።

"እኮ ምንድነው የሚያስለቅስሽ?!" አለች ሣራ ትዕግሥቷ አልቆ እየተቆጣች። "እኔ እንጃ!" ከንፈሮቿ ተፈልቅቀው ፈገግ አለች። ሣራ፤ እያለቀሰ የሚስቅ ፊት በማየቷ ይበልጥ ደንግጣ ተርበተበተች። "ግን ጤነኛ ነሽ እንዴ አብዬ?!" አለቻት የሚቁለጨለጩ ዐይኖቿን እንዳፈጠጠችባት።

"አዎን ጤነኛ ነኝ ሣርየ፤ ያለ ርሱም በሽታ የለኝ" አለች አብነት እንባዋን ከሣራ በወሰደችው መሀረብ እየጠራረገች።

"እንግዲያውስ ልንገርሽ አብነት፤ እንዲህ መሆንሽ ልክ አይደለም። ይሄ ሁሉ ችግር የደረሰብሽ የሕይወት ልምድ በማጣትሽ ነው፤ በዚህም አልወቅስሽም። ምናልባት አስተዳደግሽ ያመጣው ችግር ሊሆን ይችላል። ሁል ጊዜም እንደ ሃያ አንደኛው ክፍለ ዘመን ሴት ለመኖር ሞክሪ የምልሽ ያለ ምክንያት አልነበረም። ረዥም የግንብ አጥር ካለው እስር ቤት በጠዋት ትወጫለሽ። እዚህ መጥተሽ ደግሞ በዚህ ሰማይ በሚያክል መዝገብ ውስጥ አፍንጫሽን ትቀብሪያለሽ። ሲመሽ እዚያው እስር ቤትሽ ትገቢና ትተኛለሽ። በቃ! ላንቺ ሕይወት ማለት ይሄ ነው። እርግጠኛ ነኝ አውራ ዶሮ በዚህ ምድር ላይ ካንቺ የተሻለ ነፃነት አለው። ምን ተረፈሽ? ይሄው በመጨረሻው ከማይሆን ሰው ላይ ወደቅሽ! አንድ ነገር ልንገርሽ፤ አሁን ማድረግ ያለብሽ ሁሉን ረስተሽ እርፈሽ ሥራሽን መሥራት ብቻ ነው" ሣራ ዛር የተነሳበት ያህል ተንቀጠቀጠች። ·



"አብነት ድክም ባለ ድምጽ "የሚሠራ ሰው የሚያፈቅር ልብ የለውም ማለት ነው?" ስትል ጠየቀቻት።

"እንደሱ ማለቴ ሳይሆን... እ... አየሽ አንቺ እርሱን ማፍቀር አትችይም"

አብነት ቅስሟ ተሰብሮ ሆዷ በፍርሃት ሲሸበር ታወቃት። ሣራም ይህንኑ ስሜቷን ማንበብ ስለቻለች በሀዘኔታ ትመለከታት ጀመር።

"ለምን ሣራ? ለምን?!"

"እንዴት ብዬ ላስረዳሽ አብነት? አየሽ - አንቺና እርሱን ብዙ የሚለያዩዋችሁ ነገሮች አሉ"

"ግን ሁለታችንም ሰዎች ነን!"

"አዎን ሁለታችሁም ሰዎች ናችሁ። ግን ሰዎች ሁሉ ደግሞ እኩል አይደሉም"

"በምን ይለያያሉ?!"

"እንዴት! መልሱን የምታውቂውን ጥያቄ ለምን ትጠይቂኛለሽ አብነት? ሰዎች ከሰዎች የሚለዩበትን ሰንቱን ልንገርሽ?!"

"ንገሪኝ፤ በምን ይለያያሉ?"

"በእድሜ፤ በአስተሳሰብ፤ በሀብት፤ በእውቀት፤ በእምነት... እንዴ በብዙ በብዙ ነገር እንደሚለያዩ ጠፍቶሽ ነው?!"

"እኔና እሱን የሚለያየን ግን ምንድነው?!"

"አብነት! በእርግጥ ግን ጤነኛ ነሽ?!"

"ሣርየ- አልዋሸሽም፤ ተሸንፌያለሁ!"

"ቀድሞ ነገር አንቺ ስለፍቅር ምን ታውቂያለሽ?!" አለቻት ሣራ ግሳጼም ቁጣም በተቀላቀለበት አንደበት። እውነት ነበር። ከአብነት መሟገቱ ዋጋ እንደሌለው አውቃ ሣራ ወደ መስኮቱ በመሄድ ቁልቁል አስፋልቱን መመልከት ጀመረች። ከጥቂት ቆይታ በኋላም ፊቷን ወደ ኣብነት መልሳ "እሺ፤ አሁን ምን እንዳደርግልሽ ነው የምትፈልጊው" ስትል ጠየቀቻት።

"ስለ ቻርሊ የምታውቂውን ያህል ንገሪኝ!"

ሣራ ፊጥና አልመለሰችላትም። ጭንቀቷ ፊቷ ላይ እየተነበበባት ብዙ ከቆየች በኋላ "ስለ ፈጣሪ ይሁንብሽ አብነት፤ ስለ ቻርሊ አትጠይቂኝ። ቅስምሽ እንዳይሰበር፤ የማፍቀር ተስፋሽ ለዘለዓለሙ እንዳይጨልም፤ አፈቀርኩት ስለምትይኝ ሰው ማንነት አትጠይቂኝ!" ስትል ተማፀነቻት። "አንድ ነገር ልምከርሽ፤ በውብትሽ

አትቀልጅበት። ሮሚዮና ዡልዬት፣ ኦቴሎና ዴዝዴሞና /በመቶዎች ከሚቆጠሩ አመታት በፊት የኖሩ ሀሳብ ወለድ የፍቅር አርበኞች ናቸው። ሕይወት ደግሞ ልብ ወለድ አይደለችም!" አለቻት እጇጋን እያወናጨፈች።

አብነት ከዚያ በላይ አልጠየቀቻትም። የእጇን ጥፍሮች በጥርሷ እየከረከመች አንገቷን እንዳቀረቀረች ቀረች።

ግራ በቻርሊና በአብነት መካከል ያለው የሰማይና የመሬት ያህል ርቀት ሲታሰባት ከልቧ አዘነች። በሀሊናዋ የመጣው የመጀመሪያው ጥያቄም "ህይወት ደጋጎችን ለለምን አብዝታ ታስቃያለች?!" የሚል ነበር።



## ምዕራፍ ሁለት

የግንቦት ልደታ ዕለት ቻርሊ ሞቅ ብሎት ነበር ወደ ሰፈሩ የተመለሰው። ሜክሲኮ አደባባይ የተሣፈረበት ታክሲ በቄራ መንገድ ላይ ከሚገኘው በግ ተራ ስትደርስ እፀቁም ወረደ። ዛሬም ኮሌታው ላይ ሁል ጊዜ የምትጠይም ነጭ ሸሚዝና ከአፍንጫዋ ቀና የምትል ጥቁር ሜማውን አድርጓል።

"ሰይጣን ሰፈር" ተብሎ ወደሚጠራው መንደሩ ሲታጠፍ ቀኑ ማጨለም ጀምሯል። ቤቱ ከመግባቱ በፊት ወደ ትንሿ የሸቀጣሸቀጥ መሸጫ ሱቅ ጎራ ብሎ፤ ወሩን ሙሉ ሲወስድ የሰነበተውን የሲጋራ፣ የቢኖ፣ የሰርዲንና የአምቦ ውሃ ዱቤ መክፈል ነበረበት።

የመንደሩ ጎረምሶች እነ አሊባባ ሙሌው፣ እነ ታሪኩ ከራራው ከሱቅ አጠገብ የተተከለውን የስልክ ምሰሶ ከበው ያወራሉ። ሰላምታ ሰጥቷቸው አለፈና የሱቁን ባንኮኒ እየደበደበ "አሳላም አሊኩም ጀማል!" ሲል ተጣራ። ጀማል ከጫት መቃሚያው ካርቶን ላይ ፍንጥር ብሎ ተነሳና "ዋ አሊኩም ሰላም... ጋሽ ቻርሊ" አለው። በልደታ ቀን ቻርሊን በማየቱ ፊቱ በደስታ በርቷል።

"ታዲያስ፤ ሂሣቡን ደማመርከው? አብዛዛኸው?" ሲል ጠየቀው ቻርሊ፤ በፊቱ ላይ ስጋት እየተነበበበት።

"በሚገባ እንጂ ጋሽ ቻርሊ፣ ... በሚገባ" የነጋዴው ጉንጭ በጫት ተወጥሯል፤ ዐይኖቹ በምርቃና ፈጠዋል። ወደ ግራ ዘመም ያለችውን ነጯን ከብ ኮፍያውን ካስተካከለ በኋላ አንድ አሮጌ ደብተር በማገላበጥ ድምሩን አየ። "የዚህ ወር ሰማንያ አምስት ብር ብቻ ነው!"

ቻርሊ በመገረም አፏጨ "ሰማንያ አምስት ብር?!"
"ይኼው ነው ጋሽ ቻርሊ!"

ቻርሊ ሁል ጊዜም ደሞዝ በመጣ ቁጥር ገንዘቡን ሳይቀበል ይናደዳል። ምኑን ከምኑ እንደሚያደርገው፣ የትኛውን ቀዳዳ በምን ያህል ብር እንደሚደፍነው ሲያሰላስል፣ ሁሉም ነገር ዝብርቅርቅ ይልበትና ይበሳጫል። ሲጋራው በዱቤ፣ መጠጡ በዱቤ፣ ቀለብ በዱቤ፣ ሁሉም በዱቤ። "ከምሞቃት ፀሐይና ከምተነፍሰው አየር በስተቀር ያለ ዱቤ የማገኘው የህይወት መና ይኖር ይሆን?" እያለም ራሱን ይጠይቃል።

የጉሮን ውድነትና የርሱን አባካኝነት ሲያስበው ደግሞ "የዱቤ ክልል ባርኔጣ በዱቤ ገዝቼ አለመድፋቴም ሰውዬው እኔ ሆኜ ነው" በማለት በራሱ ላይ በምጸት ይስቃል።

"ይሁና መቼስ ምን ይደረጋል? ግማሹን አሁን ልክፈልህና ቀሪው ደግሞ በሞዴል ይጨመርልሃል" አለው ቻርሊ እጁን ወደ ጉያው እየሰደደ። ነጋዴው ፋታ አልሰጠውም "ኧረ አይሆንም ጋሽ ቻርሊ፣ እስኪ ሱቁን ይመልከቱት? ባዶውን እኮ ነው!" በጣቱ ወደ መደርደሪያው አመለከተው።

የጎደለ ዕቃ አልታየውም። መደርደሪያው እንደወትሮው በቅባት ጠርሙሶች፣ በጫማ ቀለም ቆርቆሮዎች፣ በሰንደል፣ በተንጠለጠሉ ማበጠሪያዎች፣ በሲጋራ ካርቶኖች፣ በቶኖ፣ በሳልሳና በሰርዲን ቆርቆሮዎች እንደተሞላ ነው። ዐይኖቹን መለስ ሲያደርግ የሰፈሩ ጎረምሶች ካርቶን ላይ ጽፈው በሰጡትና ሱቁ መደርደሪያ ላይ በተለጠፈው ማስታወቂያ ላይ አረፈ።

"ሳታጎብ አትፈርም፣
በጨለማ አትሳም፣
ሳታይ አትጠጣ፣
ለዱቤም አትምጣ!"

ቻርሊ ፈገግ ብሎ "አንተ ዕቃ ማውረጃ የምታጣው እኔ ገንዘብ ልከፍልህ ስመጣ ብቻ ነው?" አለው። ነጋዴው ቀልብ በሚሰርቅ ፈገግታ "ወላሂ አልኩዎ ጋሽ ቻርሊ፣ በጄ ላይ ሣንቲም የለም" ሲል በማግባባት መለሰለት? ቻርሊ ገንዘቡን አውጥቶ ቆጥሮ ከሰጠው በኋላ "አንድ ጠርሙስ አምቦውሃና አንድ ፓኮ ኒያላ ስጠኝ" ሲል አዘዘው ። ጀማል የተጠየቀውን ሁሉ አቅርቦ "ሂሣቡስ ጋሽ ቻርሊ?" ሲል ጠየቀው።

"ጻፈው!"

"ገና በልደታ ጋሼ?!" ነጋዴው አፉን በእጁ ያዘ።

"ጻፈው አልኩህ ጻፈው! ልደታም ሆነ ባዕታ ለኔ ለውጥ የለውም" አለ ቻርሊ በቁጭት ጥርሶቹን ነክሶ እያፋጨ።

ጀማል በዚያቹ ሳብ ባጠቆራት ደብተር ላይ አዲስ ገጽ ገልጦ ውልግድግድ ባለ የእጅ ፅሁፍ ያረጁ ዳክዬዎች የሚመስሉ ሶስት ፊደላት አሠፈረ ቻ ... ር... ሊ! የዱቤው ሕይወት እንደገና ጀመረ።



ሰይጣን ሰፈር ውስጥ ቻርሊ "ኋይት ሃውስ" የሚላት ሶስት ጠባብ ክፍሎች ያሏት ቤት አለችው። ውጭዋንና ውስጧን፣ ኮርኒስ የሌለው የቆርቆሮ ጣራዋን ሳይቀር ነጭ ኖራ የተቀባችና መንገድ ዳር የምትገኝ አጥር የለሽ ቤት ናት።

ቻርሊ ከመሰል ልጁ "ሊትል ቻርሊ"ና ከሴት ልጁ ሃረገወይን ጋር የሚኖረው በዚች ቤት ውስጥ ነው። ቻርሊና ሃረገወይን ግን ለስሙ እንጂ ብዙ ጊዜ ዋይት ሀውስ ውስጥ አይኖሩም።

በውስጥዋ የሚረባ ዕቃም የለም። የአፈር ወለል ባላት የመጀመሪያዋ ክፍል ውስጥ፣ አንድ ባህላዊ በርጩማ በአናቱ ተደፍቶ እሳት ያልነካው የሸክላ ምጣድ ተቀምጦበታል። ጠረጴዛ መሆኑ ነው። በስተቀኝ የሊትል ቻርሊ ታጣፊ አልጋና ከርሱ ትይዩ ደግሞ አንድ ያረጀ የሰፋ ወንበር ተቀምጧል። በሁለተኛው ክፍል ውስጥ የቻርሊ አልጋና የልብስ ማስቀመጫ ሳጥን፣ በሶስተኛው ደግሞ የሃረገወይን አልጋ፣ የምግብ ማብሰያና የመመገቢያ ቁሳቁሶች ይገኛሉ።

የመጀመሪያዋ ክፍል ግድግዳ ላይ ቻርሊ ለሃያ ዓመት በተዋናይነት በማገልገሉ የተሸለማት የምስክር ወረቀት ሌጣዋን በምስማር ተመትታ የቤቱ ብቸኛ የዐይን ማረፊያ ሆናለች።

ቻርሊ የኋይት ሀውስን በር ከፍቶ ሲገባ ጨለማው ዋጠው። ከሙያው ቀጥሎ ተስፋ የሚያስቆርጠው ከዋለበት ውሎ ሲመለስ ባዶና ጨለማ ቤቱን ከፍቶ መግባቱ ነው። "ሰው ከጨለማ ወጥቶ እንዴት ወደ ጨለማ ይገባል?!" እያለ ይበሳጫል። ልክ ጨለማን እንደሚፈራ ብላቴና እርሱም የኋይት ሀውስን በር ሲከፍት ይሰቀቃል፤ ይቀፈዋል። ይህ ጨለማ ቤቱ ደግሞ ሁሉ ጊዜ የሚያስታውሰው ሚስቱን ውቢትን ነው። ባንድ ወቅት የነበረውን የሞቀ ጎጆ፣ ጣፋጭ ትዳርና የማይጠገብ ሕይወት።

አሁንም የኋይት ሀውስ ጨለማ ስለቀፈፈው "ከቤቱ ጨለማ የውጭው ጨለማ ይሻላል"ብሎ የአምቦውሃውን ጠርሙስ መሬት አስቀምጦና የዱቤ ሲጋራውን ለኩሶ በሩ ደፍ ላይ ተቀመጠ።

ቻርሊ ገና ተማሪ ሳለ በቀልደኛነቱና በአስቂኝነቱ የታወቀ ወጣት ነበር። ዛሬ ድረስ የሚደንቀውም ነገር በህፃንነቱ ያሳለፈውን ጎምዛዛ ህይወት ከውስጡ አስወግዶ በቀልድ መተካት መቻሉ ነው። አውጥቶና አውርዶ ለዚህ የህይወት ጉራማይሌው የሰጠው

መደምደሚያ "ምናልባት ትንሿ ነፍሴ ከተዘፈቀችበት ሲኢል ውስጥ ዉ ለማምለጥ የምታደርገው መወራጨት ይሆን ይሆናል" የሚል ነው።

ዓለምነህ፣ ገና ትምህርት ቤት ሳለ ነበር ቻርሊ የሚለውን ቅፅል ያተረፈው። አስተማሪዎቹ ማስተማር ሲሰለቻቸው ቀልድ እንዲያወራ ያዙታል፣ ይቀልዳል። "ቻርሊ ባንድ ዐይንህ አልቅስ?" ይሉታል፣ ያለቅሳል። "ጆሮዎችህን አነቃንቃቸው!" ያነቃንቃቸዋል። "ቻርሊ እስኪ ፀጉርህን አቁመው"፣ ያቆመዋል። ምትሃት ይሁን ልዩ ተሰጥኦ ያልገባቸው ተማሪዎች በአድናቆት ያጨበጭባሉ፣ ይስቃሉ።

የትምህርት ቤቱ የበጎ አድራጎት ክበብ በሚያዘጋጀው ቲያትርም ላይ ቻርሊ ምንጊዜም መሪ ተዋናይ ነው። በወላጆች ቀንማ ቻርሊ የማይሳተፍበት የኪነት እንቅስቃሴ አልነበረም።

አስረኛ ክፍል እንደደረሰም ሙሴ የሚባል ጓደኛ አገኘ። እርሱም እንደቻርሊ እናትና አባት አልነበሩትም። ችግረኛ አክስቱ ዘንድ ተጠግቶ ነበር የሚኖረው። ቢሆንም ከቻርሊ ይሻላል። ቻርሊ ቃርሞ ኗሪ፣ በአገኘበት አዳሪ ነበር።

እንደ ቋንጣ ደርቆ ይታይ የነበረው ሙሴ ሁሌ የአክስቱን የዕለት ጉርስ ከአፋቸው በመካፈሉ ይሰቀቅ ነበር። ይህን ሃዘኑንም ዘወትር ለቻርሊ ያጫውተዋል። ቻርሊም በበኩሉ ኑሮውን ከርሱ ጋር በማስተያየት ህይወቱ የተሻለ መሆኑን በማሳየት ያጽናናዋል።

ሙሴ አንድ ቀን ቻርሊን ጠርቶ "ለምን ትምህርቱን ትተን ሥራ አንገባም? ቀለም እኮ ዳቦ አይደለም! አንድ ቀን ጠኔ እንደሚገድለን አታውቅም?" አለው። ቻርሊ አስቦበት የማያውቀው ነገር በመሆኑ አፉን ከፍቶ ያዳምጠው ጀመር።

"ሥራ ስንገባ ገንዘብ እናገኛለን። ገንዘብ ካገኘን ደግሞ ቢያንስ አንራብም። ግድ የለህም ቻርሊ፣ ሥራ እንግባ! እየሁ ፣ እኔን ጭንቀት ሊገድለኝ ነው። በየቀኑ ይርበኛል። ከአሮጊቷ ነጥቄ የምበላው እህል ደግሞ አፈር አፈር ነው የሚለኝ። ተመልከተኝ፣ በቁሜ ልሞት አይደለም?"አለና ያደፈ ሸሚዙን ከፍቶ ደረቱን አሳየው። አጥንቶቹ ፈጠዋል፣ ቆዳው መሸብሸብ ጀምሯል። ቻርሊም በቅሬታ ፈገግ ብሎ የራሱን ደረት ገልጦ ተመለከተ። የጎድን አጥንቶቹ ፈጠዋል፣ ቆዳው ወዝ የለውም። ጭንቅላቱን በሀዘኔታ እየነቀነቀ ሙሴን ቀና ብሎ ተመለከተው። ዐይኖቹ እንባ አርግዘዋል።



"ለመሆኑ ሥራ የት ነው የምናገኘው?! በፈለግከው ጊዜ ከሱቅ እንደምትገዛው ዳቦ በቀላሉ የሚገኝ መሰለህ!" ሲል ጠየቀ ቻርሊ።

"ቲያትር ቤት ማስታወቂያ ተለጥፎ አይቻለሁ። እንዲያውም ብዙ ተማሪዎች ተመዝግበዋል። ቲያትረኛ መሆን አትመኝም ቻርሊ?"

"እውነትህን ነው ሙሴ?!"

"ቻርሊ ሙት፣ እውነቴን ነው!" እጁን ስቦ መታው። አብረው ተመዘገቡ፣ አብረው ተፈተኑ። ቻርሊ አለፈ፣ ሙሴ ግን ወደቀ።

በቲያትር ቤቱ በር ላይ የተለጠፈውን ውጤት እንዳዩ ሙሴ የቻርሊን ቀኝ እጅ ይዞ "አንተ እድለኛ ነህ ቻርሊ፣ እኔ ግን መድረሻ የሌለኝ ከርታታ ፍጡር ነኝ። ምናልባት ነገ ተነገ ወዲያ ጠኔ አስፋልት ላይ ጥሎኝ ተደፍቼ የምቀር ምስኪን... ደህና ሁን ቻርሊ ይቅናህ!" አለው የጨበጠውን እጅ አጥብቆ እንደያዘ።

ቻርሊ ክልቡ አዘነ። "አይዞህ ሙሴ! ይህን ያህል ተስፋ አትቁረጥ። • እየህ አሁን እኔ ሥራ ከያዝኩ አንተም አትቸገርም። ያገኘኋትን አብረን እንበላለን" እያለም ሊያጽናናው ሞከረ።

ሙሴ ግን የተቋጠረ እንባውን እየጠራረገ "ቻርሊ! ዳግመኛ ወደዚያ ቤት ተመልሼ የአሮጊቷን ዐይን አላይም!" ብሎት ፊቱን አዙሮ ሄደ። ብዙም ሳይቆይ አንድ የከባድ መኪና ጋራዥ ውስጥ መፍቻ፣ አስትራቾና ግራሶ አቀባይ ሆኖ ተቀጠረ። ቻርሊም አርቲስት ተብሎ ተዋናይ ሆነ።

ይህ ከሆነ ሃያ ሁለት አመት ሆነው። የዛሬው ሙሴ ግን የድሮው ሙሴ አይደለም። የሁለት ከባድ መኪና ማደሻ ጋራዦች ባለቤት ነው። ልጆቹ ወደ ትምህርት ቤት የሚመላለሱባት ማርቸዲስ እንኳን ታይታ አትጠገብም።

ቻርሊ ሥራ በጀመረበት ዓመት "አርቲስት" የሚለው የፈረንጅኛ ቃል ተቀጥሎለት በወጣትነቱ፣ የተከበረ ሰው ሆነ። ደስተኛ ሕይወት ይመራ ጀመረ። ያኔ ቻርሊ ላይ ዐይኗን ያልጣለች ኮረዳ አልነበረችም። በመልክ መልካም ቁመናው ላይ የደረበው የ"አርቲስትነት" ካባ ሴቱን ሁሉ ወደ ቻርሊ ሳበው።

ሥራ በያዘ በዓመቱም ወብትን ከቤተቦቿ አስኮብልሎ አገባት። የናጠጠ የህንጻ ተቋራጭ ልጅ ነበረች። ባገባት በመጀመሪያው ዓመት

ሀረገወይንን፣ ባመቷ ደግሞ ዛሬ ሰው ሁሉ "ሊትል ቻርሊ" እያለ የሚጠራውን ሳምሶንን ወለደችለት።

ያን ጊዜ የኖረው ህይወት አሁን ድረስ ያጽናናዋል። "ተጨናብሰው ከሚኖሩት የመቶ ዓመት ህይወት የዚያ ዓይነቱ አጭርና ጣፋጭ ህይወት ይመረጣል" እያለም ዛሬ ድረስ ይፎክርበታል። ትዝታው አሁንም በዐይኑ ላይ እንደተንገዋለለ ነው። ከሥራው ሲመለስ የመኖሪያ ቤቱ ጸድቶ፣ ቄጠማ ተጎዝጉዞና ቡና ተፈልቶ፣ ምግቡ በወግ ተዘጋጅቶለት፣ ልብሶቹ ታጥበውና ተተኩሰው... የውቢትን ሒሲና የገንዘብ ፍቅር ሞራ ሆኖ ሳይጋርደው በፊት የቀኝ እጁ ነበረች። ወፈር ያለ ጥራዝ ያለውን ቃለ ተውኔቱን ገልጾ በቤቱ ውስጥ እየተንጎራደደ ሲያነበንብ፣ ሊትል ቻርሊን አስተኝታ ሀረገወይንን አቅፋ፣ ቡና የምታፈላበትን የከሰል ምድጃ እያርገበገበች ከትከት ብላ ትስቃለች። እንደ ቃጭል የሚንከለከለው ሳቋም የቻርሊን ጆሮ እየኮረኮረ ልቡን ሞቅ ያደርገዋል።

"ምን ያስቅሻል ውብዬ?!" ይላታል ጥራዙን ገልጾ እንደያዘ።

"አንተ ነሃ..." ትለዋለች እየተሽኮረመመች።

"እንዴት?" ሲል ይጠይቃል የደስ ደስ ያላቸውን ሣቂታ ዐይኖቿን እየተመለከተ።

"እኔ እንጃ፣ አንተን አይታወቅህም እንጂ ሁሉ ነገርህ ያስቃል። ልብ ብዬ የኑሯችንን ነገር ሳስበውማ፣ እኛ ራሳችን በመድረክ ላይ ተውኔት እየተጫወትን ያለን ነው የሚመስለኝ። ሕይወት ካንተ ጋር አትጠገብም። ሁሌ ራሴን እንደ አዲስ ሙሽራ ነው የምቆጥረው" ትለዋለች።

ቻርሊም "ህይወት እንዴት የማትጠገብና ጣፋጭ ነች?! በዚህ ምድር ላይ እንደ እኔ ደስተኛ ሆኖ የሚኖር ሰው የለም"ይላል በሀሳቡ።

ዓመት በዓመት በተተካ ቁጥር ግን ውቢት "አርቲስት" የሚለው መጠሪያ ዝናና ክብርን እንጂ ገንዘብን እንደማያፈራ ተገነዘበች። ኑሮዋን ስትመለከተው አድሮ ቃሪያ የሚባለው ዓይነት ሆነባት። ዘንድሮ ከአምና ለውጥ የለውም። ከርሞም አዲስ ነገር እንደማይፈጠር አወቀች። ጓደኞቿ መኪናና ቪላ ያሏቸውን አግብተዋል። አንዳንዶቹም ትምርታቸውን ጨርሰው ሥራ ይዘዋል። ስለዚህም ውቢት ተነሳቁላና ክስሳ መታየቱን ስላልወደደችው ከልጆቿ ጋር እቤት መዋልን አዘወተረች። ቻርሊንም ዘወትር በጭቅጭቅ ሸንታው፣ ግንባሯን እንደቋጠረች ትቀበለው ጀመረች። እንደ ወትሮው ቤት ውስጥ እየተንጎራደደ ቃለ ተውኔቱን ሲያነበንብ አልጋዋ ላይ



እንደተጋደመች "እባክህ ልተኛበት ቻርሊ፣ ልጆቹንም ከእንቅልፋቸው አትቀስቅሳቸው... አፍ ዘወትር እንደ ቁራ መጮህ አይሰለችህም?!" ትለዋለች። ይኸኔ የቻርሊ ቀሽት እርር ትልና ጥራዙን ወርውሮ ይተኛል።

ሌላ ጊዜ ደግሞ "ኤጭ፣ እኔስ እንዲያው ላንተ ስል የት ልድረስ? የኛ ቤት እንደ ሰው ቤት የሚመስለው መቼ ይሆን? ነጋ ጠባ እንደ ልክፍተኛ መጮህ፣ እንደ ታኅቀ ዶሮ ማንቋረር፣ እንደ እብድ መቀባጠር። እንዲያውስ ላለማበድህ ምን ማስረጃ አለህ? እንዲያውም የለየልህ እብድ ነህ!" ትለዋለች። ቻርሊም ጥራዙን ወርውሮ ይወጣና አፍንጫው ድረስ በአልኮል ተሞልቶ ይመለሳል። እንደ እርግብ የዋህ ትመስለው የነበረችው ሴት፣ እንደ እባብ መርዝ ስትተፋ ጆሮውን ማመን ያዳግተዋል። እናም በመገረም እየተመለከታት "ውቢት የምትናገሪውን አስተውይ!" ይላታል። ሆኖም ሰክሮ በመምጣቱ ጭርሱኑ አራስ ነብር ትሆንበታለች።

"ይልቅ አንተው ራስህ ምን እየሠራህ እንደሆን አስተውል! ለምን ሌላ ሥራ ፈልገህ አትቀጠርም? ገንዘብ የምታገኝበትን፣ ኑሯችን የሚቃናበትን መንገድ ለምን አትፈልግም?" ትለዋለች ከዐይኗ በሚወነጨፍ የጥላቻ ፍላፃ እየወጋችው።

"ሙያዬን እወደዋለሁ፣ አከብረዋለሁ። ውቢት ስለፈጣሪ ይሁንብሽ በሙያዬ አትምጭብኝ!?" እያለ ይማፀናታል።

"አዬ ሙያ እቴ! ነጋ ጠባ እንደ እንቁራሪት እየጮሁ ጉንጭ ማልፋትም ከሙያ ተቆጠረና 'እወደዋለሁ! አፈቅረዋለሁ!' ይባልልኛል፤ እፍ እቴ...! ሆድ የማይሞላ ሙያ በአፍንጫዬ ይውጣ!" ትለዋለች አፍንጫዋን በሁለት ጣቶቿ እንደሰነገች። ሲጋራውን ለኩሶ አቀርቅሮ ይወጣል።

የሚሰቱ ዘለፋና ሽሙጥ እየበረታበት በመምጣቱም የቃለ ተውኔት ጥናቱን ሌሊት ላይ ማካሄድ ጀመረ። ውቢት ግን አልለቀቀችውም። በውድቅት ለሊትም እንደ ብራቅ ጮሃ ቆሌውን ትገፈዋለች። "መብራት! መብራት! ለምን በከንቱ መብራት ታቃጥላለህ?! እስኪ ሰዓትህን ተመልከት? እኩለ ሌሊት አልፏል... ያለፈው ወር የመብራት ክፍያችን ስንት እንደሆነ ዘነጋህ? የምትሰጠኝ ገንዘብ ለልጆችህም ወተት መግዣ አልበቃ! ደግሞ መብራት እያቃጠልክ በረሃብ ልትፈጃቸው ነው?!"

"ነፍስ ሲጋሽን ያገኘም እጣት ያቃጥላት" ይላል በሆዱ ከንፈሩን በቁጭት እየነከሰ። ከዚያም ቃለ-ተውኔቱን ያጥፍና መብራቱን አጥፍቶ ይተኛል። ይህችን በሙያው የመጣች ሴት ኢጋንንትም በምን እንደሚቋቋማት ሴት ተቀን ያስባል፣ ያስባል። መፍትሔ ግን አላገኘም።

ብዙውን ጊዜ እርሷ የምትናገረው ትክክል መሆኑን ያውቃል። ከዚያ ከሞቀ ቤቷ ወጥታ እርሱ ዘንድ ስትጎላቀል፣ የሚፈርጡ ብርቱካኖች ይመስሉ የነበሩት ጉንጮቿ መሟሸሽ መጀመራቸውን ሲመለከት፣ በአለባበሷ ከትምህርት ቤት ጓደኞቿ ማነሷን ሲያስተውል "የፈለገችውን ብትል እውነት አላት።በእኔ ሀጢያት ስትጠበስ ለምን እንዲህ አትንጨረጨር?" እያለ በራሱ ላይ ይፈርዳል።

ሊትል ቻርሊ እግር ተክሎ ወዲያ ወዲህ መውተርተር ሲጀምር ውቢት ጭርሱኑ አውሬ ሆነች። ዱሮ የሚያውቃትና ፍቅርን ሰጥቶ ፍቅር የተጋራትን የኑሮን ጣእም ያየባትን ሴት አልመስልህ አለችው። ቆየት ብላም መብለጭለጭ፣ መቁለጭለጭ አዘወተረች። ለነዚያ ሁሉ ጌጦች መግዣ የሚውለውን ገንዘብ ከየት እንደምታመጣ መገመትም አልቻለም። ልጇን ጎረቤት እየተወች ውጭ መዋል፣ አመሻሽታ ቤት መግባቷ ግን ግራ አጋብቶታል።

አንድ ሰንበት ቻርሊ በጊዜ ቤቱ ገብቶ ሀረገወይንን ፊደል ሲያስቆጥር ሊትል ቻርሊ ደግሞ ከጓዳው ክፍል ተኝቶ ነበር። ውቢት ቀትር ላይ ተኳኩላ እንደወጣች አልተመለሰችም። ሀረገወይንን እንቅልፍ ስለተጫጫናት አባቷ አስተኝቷት አዲስ የተሰጠውን ቃለ ተውኔት ማንበብ ጀመረ።

ይሁንና የሚያስበው ስለ ውቢት ስለነበረ አዕምሮውም ሊሰበሰብለት አልቻለም። በዚያች ሰዓት ምን ልትሠራ እንደምትችል በሃሣቡ እያሰላሰለ ልቡ በቅናት ይኮማተራል። ቃለ - ተውኔቱን አሥር ጊዜ እየጣለ አሥር ጊዜ ያነሳል። በላይ በላዩ የሚለኩሰው ሲጋራ ጢስም ጠባቧን ክፍል አፍኗታል። ሠዓቱን ሲመለከት ከምሽቱ ሰስት ሰዓት ይላል። የትዳሩ ሞት መቃረቡን አወቀ።

ብዙም ሳይቆይ የቤቱ በር በሃይል ሲደበደብ ሰማና በርጋታ ሄዶ ከፈተው። ውቢት ገፍተር አድርጋው ስትገባ የጠጣችው አልኮል ሽታ ጭምር ወደ ጓላው ገፈተረው። ፀጉሯ ተበታትኗል፣ ቀዩ ፊቷ ሣንባ መስሏል። አልፋው ወደ መኝታ ክፍሏ ገባች። በሩን ዘጋና የእንጨት ወንበሩ ላይ ኩርምት ብሎ ተቀመጠ።



ወዲያው እየተረገረገች መጥታ ከፊቱ ሌላኛ ባለው ወንበር ላይ ተቀምጣ በፀጥታ ታስተውለው ጀመር። ምን ትበለው?! ምን ይበላት?! ያስተሳሠራቸው ፍቅር ውሉ ከተፈታ ውሎ አድሯል፤ የአንድነታቸው ማማ ተንዶ በመካከላቸው ሰፊ ገደል ተዘርግቷል፤ በአንድ ጣራ ሥር አብረው ይደሩ እንጂ አንዳቸው ለአንዳቸው ባእድ ናቸው።

"ወዴት ነበርሽ?!" አላላትም። የት እንደነበረች ከሁኔታዋ ይገምታል። "ምን ስትሠሪ አመሸሽ" አላላትም። ምን ስትሠራ እንዳመሸች ይገምታል። ሊቋቋመው የማይችል የንዋይ ጎርፍ ፍቅረኛውን ከቤቱ ጠርጎ ወስዷታል። አባሮ ሊይዘው በማይችል ፍጥነት የውቢት ልብ አፈትልኮ ሮጦ ወጥቷል።

"ትሰማኛለህ አርቲስት?" ምላሷ ይኮላተፋል።

"እምን ፣ እሰማሻለሁ ውዴ"

"ለማንኛውም ነገር መጀመሪያ እንዳለው ሁሉ መጨረሻ አለው? የለውም?"

ቻርሊ ትኩር ብሎ ይመለከታት ጀመር። ከጠየቀችው ጥያቄ ይልቅ ያሰላስል የነበረው ስለ ሰው ልጅ ባህርይ መለዋወጥ ነበር።

"እሃ ፣ ንቀት ነው? ተጀነን። ቀድሞም የአርቲስት ኪሱ ባዶ ቢሆንም ከወኔውና ከልቡ ጅንን ነው! ይሁንና ለጠየቅኩህ ጥያቄ መልስ እፈልጋለሁ። አሁኑኑ!" በሌባ ጣቷ መሬቱን እየጠነቆለች አሳየችው። በእርሷ እንደበት የርሱን ጩኸት ስትጮህበት ብሽቅ አለ።

"ምንድነው የምትይው?" ጥርሶቹ በቁጭት መፋጨት ጀመሩ።

"ቀላል ጥያቄ ነው የጠየኩህ። ለማንኛውም ነገር መነሻና መድረሻ አለው? የለውም" ወፈፍ አደረጋት።

ቻርሊ ጥቂት እንደማሰብ አለና "መቼም..." ንግግሩን ሳይጀምር አቋረጠችው። "መቼም ብለህ ነገር አትጀምር። የድለላ፣ የሸንገላ ነው የሚመስለኝ። የጠየኩህ ቀጥተኛ ጥያቄ ነው ቀጥተኛ መልሱን ስጠኝ!"

"ቢ ... ሎጂካል፣ ውቢት!"

"ከሎጂክህ ጋር እንጦርጦስ መውረድ ትችላለህ። አሁን ስለሎጂክ እንድታወራልኝ አልፈልግም። ለጥያቄዬ ብቻ መልስ ስጠኝ!።"

"እንግዲያውስ፣ 'እውነቱን' ማወቅ ከፈለግሽ 'መጀመሪያና መጨረሻ ያላቸው ነገሮችና ክስተቶች እንዲሁም የሌላቸው ደግሞ አሉ ለምሣሌ..."

"ለምሣሌ የኔና የአንተ እርባና የለሽ ትዳር መጨረሻው አሁን አይመስልህም?"

ቻርሊ ሁለት ጆሮዎቹን በሁለት እጆቹ ድፍን አድርጎ ያዘ። "ውቢት! እውነት አንቺ ነሽ ይህንን የምትናገሪው?!"

"አዎን እኔ ነኝ ቻርሊ!" ራሷን በአዎንታ ነቀነቀች። ቻርሊ በልቡ ቆራጥነቷን አደነቀው። ውቢት ቀጠለች። "ፍቅር የጊዜ ጉዳይ ነው። ተራሮች እንጂ ፍቅር ለዘላዓለም አይኖርም። እኛም በጊዜያችን ብዙ ሞከርን፣ ህይወትን ታገልን። አልሆነልንም። በግድ በእግረ ሙቅ አስሮ ያቆራኘን የለም። አዎን ማንም የለም"

አሁን ደሟ ቀዝቅዟል። ድምጿም ረጋ ያለ ነው። ድፍረት አጥታ የሰነበተችበትን ጉዳይ አፍረጥርጣ በመንገሯ በውስጧ ይታገላት የነበረው እልህ ቀዝቅዟል። የጥላቻ ጦር ሲያዘንብበት የነበረው ዐይኗም ረግቧል።

"የበደልኩሽ ነገር አለ?" አላት ቻርሊ በተቆራረጠ ድምጽ። የውቢት መልስ አጭር ነበር። "የለም!"።

"ታዲያ?"

"ቢቃኝ፤ በይሉኝታ ተተብትቤ ከዚህ በላይ በችግር ወህኒ ለመማቀቅ አልፈልግም።"

"ውቢት!"

"አዎን ቻርሊ፤ ዓለምን በጥፍሯ አቁሞ ሲያሽከረክራት የሚኖር፣ እያንዳንዱ ህያው ፍጡር በደም ስሩ የተከተበው የንዋይ ፍቅር መሆኑን ለማስተዋል በከንቱ ምትሃት የተጨፈኑት ዐይኖችህ ገና አሁንም አልተከፈቱም። ይህን አርቲስት የሚል ስም ይዘህ እርባን የለሽ ትዳር ከዚህ በላይ መኖር አልችልም!"

ቻርሊ የእልህ ሲቃ ተናነቀው። "ሙያዬን አከብረዋለሁ፤ አፈቅረዋለሁ" አላት ሳያስበው እየጮኸ።

"ይሄ እንኳን ሙሉ መብትህ ነው" ትከሻዋን ሰበቀች።

"እኮ አሁን ምን ይሁን ነው የምትይው" መልሱን ቢያውቀውም ትጨክናለች ብሎ ስላልገመተ ለመጨረሻ ጊዜ ጠየቃት።



"ፈትቼሃለሁ!" አለችው በቁርጠኝነት። ከዚያ በላይ እጠገቡ ተቀምጣ ዐይኖቹን ማየት አልደፈረችም። ፈጥና ተነሳችና ወደ መኝታ ክፍሏ ሄደች። ቻርሊ ሌሊቱን ሙሉ ሲጋራውን እያጨሰ በጠባቧ ክፍል ውስጥ ሲንጎራደድ፣ ሲቆም፣ ሲቀመጥ ነጋለት። ንጋትም ላይ ቢሆን የቀኝ እጁን እንደሚቆርጥ እያወቀ ዐይኖቹ ሊያንቀላፉላት አልቻሉም።

ጠዋት ላይ ሻይ አፍልታ፣ ቁርሱን አቀረበችለት። ሁለት የልብስ ሻንጣዎቿን አውጥታ በሩ ሥር አስቀምጣለች። ከቀረበለት ቁርስ በጣቱ ቆንጥሮ የጎረሰውን መዋጥ አቅቶት ከአንድ ጉንጩ ወደ ሌላው እያመላለሰ ሲያጉላላው ቆይቶ፤ አጥንት የዋጠ ያህል ፊቱን አኮፋትሮ እንደ ምንም ብሎ አስገባው።

ውቢት የክት ልብሷን ለብሣና ተጊያጊጣ ፀሐይ እንደመሰለች ከመኝታ ክፍሏ ወጥታ ልጆቿን ሳመች። ሻንጣዎቿን አንስታም በረቅ አድርጋ ተመለከተችውና ወደ በሩ አመራች።

ቻርሊ አላስችል ብሎት ተፈናጥሮ ተነሣና ክንዷን ያዝ አድርጎ አስቆማት። ሁሉም ነገር እውነት አልመስልህ ቢለው "እውነት አንቺ የኔዋ ውቢት ነሽ?" ሲል ጠየቃት። ዐይኑ ኩሬ መስሏል።

ውቢት ፈገግ አለች። ፈገግታዋ ከፀሐይ ድምቀት አሥር እጅ የደመቀ፣ ውበቷ ከጨረቃ ውበት አሥር እጅ የላቀ ነበር። "ቻርሊ፤ ፀሐይ በወጣችበት እንደማትጠልቅ አታውቅም? ሰውንም አስቀመጥከው ቦታ ፈልገህ አታገኘውም!" አለችው በደስታ የሚያበሩ ዐይኖቿን እያርገበገበች።

"ይህን መልከ ቀናነትህንና ሙያህን አፍቅሬ ትዳር በምትለው ወህኒ ውስጥ የምትማቅቅ ሌላ ምስኪን ፈልግ። እኔስ ከአዚም ከትብትብህ ተፈታሁ በቃኝ!" በርግጥም ቅር ያላት አትመስልም።

ቻርሊ አዘነ። ድሮ ድሮ ደስታው፣ ደስታዋ፣ ሀዘኑ ሀዘኗ ነበር። ዛሬ ግን ሁሉም ነገር ተገለባብጦ ሀዘኑ ደስታዋ፣ ደስታዋ ሀዘኑ ሆኖ ሲያገኘው ቀስ ብሎ የያዘውን እጅ ለቀቀ። እየራቀች ስትሄድ ግን እንባው መውረድ ጀመረ፤ ሀረገወይን ሱሪውን ጨምድዳ ይዛለች። ሊትል ቻርሊን ታቅፎ ከአይታው እስከተሰወር ድረስ በዐይኑ የኮረኮንቹን መንገድ አሻገራት። አንድ ቀን ትመለሳለች የሚል እምነት ነበረው። አልተመለሰችም። ከዚያች ቀን ወዲህ ትዳሩም፣ ህይወቱም ሙያው ብቻ ሆነ፤ ለሃያ ሁለት ዓመታት። ታዲያ አሁን በቅርብ የዛሬ ሁለት ዓመት ገደማ ኀት ሆቴል አጠገብ ከሚገኘው የአውቶብስ

ፈርጣታ ላይ ቆሞ የእውቶብሷን መምጣት እየተጠባበቀ፤ ያጠናውን ቃል ተውኔት በሀሊናው በማነብነብ ላይ ሳለ አንድ እንደ ውሃ የምትፈስ ነጭ ፒጆ የአስፋልቱን ጠርዝ ይዛ ቆመችና ጥሩንባዋን ፒፕ-ፒፕ አደረገችለት።

ቻርሊ ጎንበስ ብሎ በመኪናው የበር መስተዋት በኩል ሾፌሩን ተመለከተ። ከዚህ ቀደም የማያውቃት የፀሐይ መነጽር ያደረገች ሴት ናት። በእጇ እየጠቀሰች ጠራችውና ተንጠራርታ የመኪናውን በር ከፈተችለት። ቻርሊ ሳያቅማማ ዘው ብሎ ገባ። መኪናዋ ጉዞዋን ጀመረች። የመቀመጫዋ ምቾት ሰውነቱን ዘና አደረገው። ሴትዬዋ የተቀባችው ሽቶ መዓዛም ወደ ልቡ ሲሰርግ ታወቀው።

"ወዴት ነህ?" አለችው ሰረቅ አድርጋ እየተመለከተችው። የድምጿ ቄንጥ ቻርሊን ሳበው። እናም እየተኩራራ የቲያትር ቤቱን ስም ጠራ።

"አፈር በበላሁ፤ ዛሬም እዚያው መድረክ በምትለው የዶሮ መስፈሪያ ቆጥ ላይ ነህ?" አለችው በአንድ እጇ መሪውን፣ በሌላው እጇ ደግሞ አፏን እንደያዘች።

ቻርሊ ሽምቅቅ አለ። "ምን ለማለት ፈልገሽ ነው?" ድምጹ መንቀጥቀጥ፣ የዐይኑ ቆቦች መርገብገብ ጀመሩ።

"ተወው፣ ተወው፣ ለካስ ዛሬም ሙያህን ትወደዋለህ፤ ታከብረዋለህ" አለች ሴትየዋ ሽሙጧን በፈገግታ እያጀበች።

ገልመጥ ብሎ አስተዋላት "አንቺ ሴት ጤነኛ ነሽ?! ማነው በቀትር ሽቶ የተርከፈከፈባት አጋንንት ፈትቶ የለቀቀብኝ? በቃኝ እዚህ አውርጂኝ!" አላት የቆሰለ አንበሳ ሆኖ።

"አሄሄ ... አሄሄሄሄ ... እዬ ቻርሊ!"
"ሴትዬ እዚህ አውርጂኝ አልኩሽ እኮ! ምን በጠራራ ፀሐይ ትለክፊኛለሽ፣ ...ልክፍታም! እንዴ! ባገር አማን የሰው ሰው ጠርቶ መሳደብ ምን የሚሉት ፈሊጥ ነው? በቃኝ፣ እዚህ አውርጂን!"

"አሂሂ ... ሂሂሂሂሂ ..."
ሣቋ አበሸቀው፤ ራሱን መቆጣጠር አቅቶት ያን የወተት አረፋ የመሰለ ጥርሷን ሲያራግፍላት እጁን ለቡጢ ሲያመቻች "እዬ ቻርሊ ! ዛሬም ድሮ የማውቅህ ያው የጥንቱ ቻርሊ ነህ። ሳትነጠል፣



ሳትቃጠፍ፣ ሳትዛባ፣ ሳትሸነፍ ያው እንደ ነበርከው አለህ። እውነትም ፀሐይ በወጣችበት አትጠልቅም የሚለው አባባል ለአንተ አይሠራም። አየህ ቻርሊ፤ አንተ ብቻ ነህ ካስቀመጡበት ቦታ የማይንቀሳቀስ ተራራ ሆነህ የኖርከ፣ የዓለማችን ድንቅ ፍጥረት" በምፀት ትስቅበት ጀመረች።

"ውቢት!" ዐይኖቹ በመገረምና በድንጋጤ ፈጠጡ። መነጽሯን አውልቃ "ሃሎጋይ!" ስትል በቄንጥ ሰላም አለችው። አፍጥጦ ከመመልከት በቀር አንዳች ቃል አልተነፈሰም።

ከቲያትር ቤቱ በር ላይ አውርዳው መኪናዋን እያፈሰሰች ስትበር፣ ቆሞ ለዐይኑ እስክትሰወር ድረስ ለሁለተኛው ጊዜ ሸኛት። ለረዥም ጊዜ እጁ ከአፉ ላይ አልወረደም፤ በመገረም የፈጠጡ ዐይኖቹ አልረገቡም። ካዛንቺስ ትልቅ ቡና ቤት መክፈቷን ሰማ እንጂ እንዲህ ትለዋወጣለች ብሎ በውኑ ቀርቶ በህልሙም እንኳን አላሰበም።

የበሩ ደፍ ላይ ሆኖ ይህን ሁሉ ሲያሰላስል ቀየና ከሰመመኑ ሲነቃ ለምን ውቢትን እንዳስታወሳት ያስብ ጀመር። "አዎን! አዎን! የኋይት ሃውስ ጨለማ" አለ እየተጣደፈ። የኋይት ሃውስ ጨለማ ውቢትን እንዳስታወሰው ሁሉ ውቢት ደግሞ ብተራዋ በሚደይደይ ሰልፍ ውስጡ የተዋወቀችን ወጣት አስታወሰችውና በትረፊታ ረገግ አለ።

ልክ ውቢትን ሲያገኛት እንደነበረችው ወጣትና አዲስ ነች። "ደስ የምትል የውብት ቀንዶ" ሲል አሰበ። የተውኔት ጥበብን አፍቅሮ ለሴት ልጅ ፍቅር ለዘለዓለሙ የተቀረቀረው ልቡ አሁንም እንደተዘጋ ነው። ሙያውን እየጠላውና ተስፋ እየቆረጠ ቢሄድም፣ ቀልቡ ለሴት ልጅ ውበት አይሰረቅም ነበረ። የዚች የዛሬዋ ወጣት ልጅ ፈገግታና የሚንከባለሉ ዐይኖች ግን... ምን ዐይኖቿ ብቻ፣ መላ ሁኔታዋም የሆነ መስህብ አለው።

ቻርሊ አብነትን ከሀሳቡ ለማባረር እግሩ ሥር ያስቀመጠውን የአምቦ ውሃ አንስቶ ብብቱ ሥር ወሸቀና ፈጥኖ በመሄሳት የቤቱን መብራት አበራው። አናና፣ አና ይሸታል። በወለሉ ላይ የሲጋራ ቁርጥራጮች ተበታትነዋል።

የአምቦ ውሃውን ጠርሙስ በምጣድ ከተሠራው ጠረጴዛ ላይ አስቀመጠ በአሮጌው ሶፋ ላይ እግሮቹን በማጣመር ተቀመጠ። ግድግዳ ብቻ የሚለያያቸው ጎረቤቱ ሂትለር በጊዜ ገብቶ ልጁ ቡችን ማስቃየት ጀምሯል።

ሂትለር የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት መምህር ነው። ሰይጣን ሰፈር መጠጥ የማይጠጣና የማይሰክር ሰው በመብራት ፈልጎ ማግኘት ባይቻልም፤ ሂትለር ግን ወደር የማይገኝለት ጠጭ፣ ንትንቅ የማይል፤ ጠጥቶ በቃኝ የማያውቅ ሸንቁር ፍንቦ በመሆኑ ነው። ሚስቱ አንድ ልጁን ቡችን አስታቅፋው ከሄደች ወዲህ ደግሞ ብዙ ይጠጣል። እቤት ሲገባ ዋነኛ ተግባሩም ቡችን ማስቃየት ነው። በቀበቶ ይተለትለዋል፤ ቁልቁል አንጠልጥሎ በበርበሬ ያጥነዋል፤ እጅና እግሩን አስሮ ያስደርረዋል። ይሄን ሁሉ የሚያደርገው ሚስቱን ለመበቀል ነው።

"አንተ ተከላ! እናትህም በልታ የማትጠግብ የሰው አሳማ ነበረች። በቀን ሁለት ዳቦ በልተህ ራበኝ ብለህ ታለቅሣለህ!" ሂትለር ይጮሃል።

"አላለቅስም አባዬ፣ ሁለተኛ አላለቅስም!" ቡች ያላዝናል።

"አባቴ - አትበለኝ - አባት ይንሣህና! የናትህን ጉድ ያልሰማሁልህ መሰለህ? አንተ የኔ ልጅ ሣትሆን የጣልያኑ የሲኞር ፖውሎ ዘበኛ ልጅ ነህ። ይሄን የጥንቸል ጆሮ የመሰለ ሾጣጣ ጆሮህን ስመለከት ሁል ጊዜም ይደንቀኝ ነበር - ገና ልጅ ሣለህ ጀምሮ። የዚያ የመንደሩ አውደልዳይ ኮርማ፤ የሲኞር ፖውሎ ዘበኛም ጆሮው እንዳንተ ሾጣጣ ነበር። ቀበሮ ፣ የሰው ቀበሮ! ..." ግርፊያው ቀጥሏል፤ የልጁ ጀርባ ይጮሃል፤ አፉ ይለማመጣል።

"እናትህ የት እንዳለች ታውቃለህ?"

"አላውቅም፣ አባይዬ"

" አንድ ሸማኔ አግብታ ጥበብ ለብሳለች አሉ። ጣቷ ላይ ያጠለቀችው ጌጥ ቢሸጥ እኔና አንተን ይገዛል አሉ። አንተም እንደ እናትህ ብልጥ ነህ?"

"አይደለሁም አባዬ"

"እንግዲያው ባባትህ ወጥተህ ይሆናል። የሲኞር ፖውሎ ዘበኛም እንዳንተው ነጉላ ነበር። ለመሆኑ ከትምህርት ዓይነቶች የትኛውን ትመርጣለህ?"

"ሣይንስን ነው አባዬ"

"ውሸታም ልጅ ውሸታም ትምህርት ቢመርጥ አይደንቀኝም። ሣይንስ ውሸት ነው። ዝንብ የጤና ጠንቅ ነች ይላል። የዚህ የሰይጣን ሰፈር ሕዝብ በሚሊዮን ከሚቆጠሩ የዝንብ አብሮ አደግ ወዳጆቹ ጋር በመከባበርና በመተባበር ሲኖር እንጂ፣ ተቅማጥና ሞት ቀርቶ ቁርጠት ይዞት አይተሃል?!"

"አላየሁም አባዬ!"

"ታዲያስ? እንዳንተ ያለው ውሸታም ሣይንስ ግን 'ብርድ የኒሞኒያ መንስኤ ነው' ይላል። እስኪ በዚህ መንደር



እርቃናቸውን ከሚንጠለጠሉ ህፃናት አንድ እንኳን ታሞ የተኛ አይተሃል?!"

"አላየሁም አባየ"

"ሣይንስ ለዚህ ምን መልስ ይሰጥሃል? የህፃናቱ ቆዳ ከአይ የተሠራ ነው ሊልህ ነው? የሣይንስ ውሸት በዚህ ብቻ አያቆምም። 'ጉንፋን ከቆሻሻና ከመጥፎ ሽታ ይመጣል' ይልሃል። ለመሆኑ እዚሁ ሰይጣን ሰፈር ጠላ ቤቱ አጠገብ የተከመረው ቆሻሻና የሽንት ፍሳሽ ይታይሃል? ጠላ ነጋዴዋ እርጊት እንኳን ጉንፋን ሊይዛቸው ሲያስነጥሳቸው ሰምተሃል?!"

"አልሰማሁም አባዬ!" ይላል ቡች እየተንቀጠቀጠ

"ሣይንስ ውሸት ነው! አንተም ውሸታም ነህ! የፖውሎ ዘበኛም ውሸታም ነበር"

"ልክ ነህ አባዬ"

"ሌላ የምትወደው ትምህርት ምንድን ነው?" ግርፋቱን ቀጥሏል።

"ህብረት! አባዬ ህብረት!"

ሂትለር ከትከት ብሎ ይስቃል። "'ከድጡ ወደ ማጡ' አሉ። ህብረት? ይሄም ለኛ ሀገር አይሠራም። በወፈረ በቀጠነው ለሚጯጯህ፣ አጥንት ላይ እንደ ሰፈረ የውሻ መንጋ እርስ በእርሱ በሚናጭ ህዝብ መሃል ህብረት ብሎ ትምህርት ውሸት ነው! አንተም ውሸታም ነህ፤ ልክ እንደ ዘበኛው!ሌላ አምጣ!"

"እሽ - ታሪክ አባዬ"

ሂትለር ድምጹን ከፍ አድርጎ ከጣራ በላይ ይስቃል። "ታሪክም ውሸት ነው! እንደኔ፣ እንዳንተ፣ እንደ ሰይጣን ሰፈር ላሉ ነዋሪዎች አይሠራም። ቀድሞ ነገር ደሃ ምን ታሪክ አለው? የድሃ ታሪክ ቀን ከሌት የማይተኛ ሆዱን ለማሸነፍ የሚያደርገው ተጋድሎ ነው። ታሪክን ለባለ ታሪኮች ተውላቸው። የሰው አሳማ! ሥርተህ ሆድህን የምትሞላበት ትምህርት አትመርጥም?!'

"ሂሣብ!" አለ ቡች ሲፈራ ሲቸር። ሂትለር ይስቃል። "አሁን ገና ልክ እንደ እናትህ ጠጣ ሆንክ። ሂሣብ ምን ጊዜም ትክክል ነው። አንድ ብርና አንድ ብር ዘለዓለሙን ያው ሁለት ብር ነው። እንደ ሣይንስ አይዋሽም። እንደ ህብረት አያፌዝም፣ እንደታሪክ ጀንበር ስትጠልቅ አይለዋወጥም"

"ልክ ነህ አባየ"

"ብራቮ ቡች! አራቱን የሂሣብ መደቦች አጣርተህ ካወቅህ ይበቃሃል። እውነቱን ይዘሃል ማለት ነው። አራቱን የሂሣብ መደቦች አውቀህ ስትጨርስ ንገረኝ። ከዚያ በኋላ ወደ ትምህርት ቤት

አትሄድም። ተምረህ ከምታብድ፣ ደንቁረህ ብትራብ ይሻላል፣ እሺ ቡቺ?!"

"እሺ አባዬ"

ሂትለር ይኸኔ ልጁን አቅፎ ይስማል። ራሱንም እያሻሸና ከጉያው እያስገባው "ይሄ ሾጣጣ ጆሮህ ባይኖር እወድህ ነበር ቡቾ"ይለዋል።

"ታዲያ ለምን ሁልጊዜ እሱን እያየህ ከምትደበድበኝ በምላጭ ከርክመህ አታስተካክልልኝም? ያማቱን ሊመስሉ ይችሉ የለም ?!" የሚል ምላሽ ሲሰጠው ሂትለር ደረቱን ደግፎ ትንፋሽ እስኪያጥረው ይስቃል።

ከዚያ በኋላ ፀጥታ ይሰፍናል። ጥቂት ቆይቶ ሂትለር ማንኮራፋት ይጀምራል። ያን ሁሉ ጉድ ሲያዳምጥ ቻርሊንም እግሮቹን እንዳጣመረ በአሮጌው ሶፋ ላይ እንቅልፍ ይዞት ጭልጥ አለ። ሊትል ቻርሊና ሀረገወይን ቤታቸው አልገቡም ነበር።



# ምዕራፍ ሶስት

አብነት በአባቷ መኪና ወደ ሥራ ስትሄድ ልዩ እንደሰጋ ነበረች። ትላንት ምሽት አባቷ መኝታ ቤት ድረስ መጥተው "ነገ የምንነጋገረው ብርቱ ጉዳይ አለ" ብለዋታል።

መሀል ፒያሳ ከሚገኘው ትልቅ ሕንፃ ሥር ደርሰው መኪናዩቱ ስትቆም አባቷ ፈጥነው በመውረድ ወደ መግቢያው በር እየተጣደፉ አመሩ። አብነትም ቦርሳዋን አንግታ እጅጌ ጉርድ ሸሚዟን እያስተካከለች ተከተለቻቸው።

ዘወትር እንደምታደርገው ሁሉ ቀና ብላ አንደኛው ፎቅ ላይ በጥቁር መስተዋት ላይ በወርቃማ ቀለም የተፃፈውን ማስታወቂያ ተመለከተች፤ "አብነት አስመጭና ላኪ ድርጅት" ይላል። እንደወትሮው የኩራት ስሜት አልተሰማትም። ሃሳቧ ሁሉ ዛሬ ከአባቷ ጋር በሚፈጠረው ውዝግብ ላይ ያተኮረ ነበር።

ቢሮዋ በር ላይ ፀሐፊዋ ቅድስት በፈገግታ ተቀብላ አስገባቻት። ጠቡብ ያለችው ቢሮዋ በቆዳ የተለበጠ መጠነኛ ጠረጴዛና ወንበሮች፣ የፋይል ካቢኔትና የመፃህፍት መደርደሪያ ይዛለች። ስትገባ ቀዝቃዛ አየርና አና አና የሚል ሽታ ተቀበላት። በመስኮቱ ዘልቃ የምትገባው የጠዋት ፀሐይ ገና ሙቀቷን በመርጨት ለቢሮዋ ድምቀትንና ሙቀትን አልቸረቻትም። አብነት ቦርሳዋን ከጠረጴዛዋ ላይ አስቀምጣ የማሞቂያውን ሶኬት ተከለችና ሻይ አዝዛ ተቀመጠች።

የአብነት መደበኛ ተግባር የድርጅቱን ሂሣብ መከወን ነው። ትልቁን መዝገብ ጠረጴዛው ላይ ዘርግታ በማቀፊያ ካከማቸቻቸው ሰነዶች ላይ የወጪና የገቢውን ሂሣብ መመዝገብ ጀመረች። የምትሠራው ሂሣብ የተጭበረበረ መሆኑን ስለምታውቅ በዚያ ቢሮ ውስጥ የምታሳልፈው ጊዜ ሁሌም ይቆጫታል። እርሷ የምትሠራው ሂሣብ ብዙውን ጊዜ የሚያሳየው መጠነኛ ትርፍ፣ አንዳንድ ጊዜም ኪሣራ ሲሆን፣ የድርጅቱ ገቢ ግን ቁጥር ሥፍር እንደሌለው ታውቃለች። አባቷን ስለዚህ ጉዳይ ጠይቃ የተሰጣት መልስ "አንድ ቀን ትረጅዋለሽ!" የሚል ነበር። ያ "ቀን" ግን እጅግ ስለራቀባት የተጭበረበረ ሂሣብ ስታገላብጥ የምታቃጥለው ጊዜ ያንገበግባታል።

የዘረጋችውን መዝገብ በንዴት አጥፋ እጆቿን አጣምራ ተቀመጠች። ጠረጴዛዋ ላይ ያለው ካላንደር ሜይዴይን አስታወሳት። ሜይደይም ቻርሊን፤ ቻርሊም ዛሬ ከአባቷ ጋር የምታደርገውን

ውዝግብ። በሚይደይ ሰልፍ ላይ ከተካፈለች ወዲህ አባቷ እነጋግረዋት አያውቁም። ፊታቸውን በጥላቻ እንዳጠቆሩባት ነበሩ።

ስለ አባቷ ጭካኔ እንድታስብ የሚያደርጋት አንድ ድርጊት ምን ጊዜም ከህሊናዋ አይጠፋም።...

ከሁለት ዓመታት በፊት ፣ በድርጅቱ ውስጥ ሥራዋን የጀመረች ሰሞን ነው። አባቷ ቢሮ ውስጥ ተቀምጣ ስለ ሂሣብ መዝገብ እያያዝ ስትወያይ፣ የቢሮው በር ተንኳኩቶ አንድ ጎስቋላ ሰው ይገባል። የለበሰው ሰማያዊ ቱታ እላዩ ላይ ነትቧል፤ ጫማዎቹ ተበጣጥሰዋል፤ በተገለጠው ደረቱ ላይ አጥንቶቹ ፈጥጠዋል። ረዘም ያለ ከሲታ ፊቱ ላይ ዐይኖቹ በስጋትና በጥርጣሬ ይቁለጨለጫሉ። በራ ጭንቅላቱ ላይ ደግሞ የደም ሥሮቹ ትር ትር ትር ሲሉ ይታያሉ።

አብነት ድንግር ብሏት አንዴ አባቷን፤ መልሣ ጎስቋላውን ሰው ስትመለከት ቆየች። አባቷ ሰውየውን በዝምታ ከተመለከቱት በኋላ "ከዚህ በፊት ውሣኔየን አሳውቄሃለሁ? አላሳወቅኩህም?!" ሲሉ ተቆጥተው ጠየቁት።

ሰውየው እያንነበበ "ጌታዬ..." ከማለቱ የጀመረውን ሳያስጨርሱት "የጠየኩህ አጭር ጥያቄ ነው። አጭር መልስ ብቻ ስጠኝ!" ሲሉ አፈጠጡበት ።

"አሳውቀውኛል ጌታዬ ..." አለ በመርበትበት ።

"ታዲያስ? አሥራ አምስት ዓመት ሙሉ ድርጅቱ ውስጥ ስትሠራ፣ አንድ ቀን እንኳን ለቃሌ ሳልታመን፣ የተናገርኩትን ሳልፈጽም የቀረሁበት ጊዜ አለ?!" ሲሉ ግንባራቸውን ቋጥረው ጠየቁት።

"የለም ጌታዬ"

"እንግዲያ፣ ከሥራ ካሰናበትኩህ በኋላ ምን ልትፈጥር መጣህ?! ማሰብና መጨነቅ የነበረብህ'ኮ የድርጅቱን አሥር ብር እንኳን የማያወጣ ዕቃ ለመስረቅ እጆችህን ስትዘረጋ ነበር። በታታሪና በቅን ሠራተኛነትህ ያላደረኩልህ ነገር አልነበረም። አሥረኛ ክፍል ድረስ ልዩ ወጪ እየሰጠሁ አስተምሬሃለሁ... ቤተሰቦችህን እንደ ቤተሰቤ ቆጥሬ ረድቻቸዋለሁ።አንተ ግን አሥር ብር ለማያወጣ ንብረት ታማኝነትህን አጎደልክ። አሁን ልወቅስህ አልፈልግም፤ ሁሉን ነገር ጨርሰናል" አሉና ተሽከርካሪ ወንበራቸውን አዙረው ጀርባቸውን ሰጡት።

ሰውየው እንዳቀረቀረ "ጌታዬ ጥፋተኛ ነኝ" አለ። "ጥፋተኛነትህን ያወቅኸው ዛሬ በመሆኑ በራስህ ልታዝን ይገባል። ጥፋት ከፈፀሙ በኋላ በጥፋታቸው የሚያዝኑ የዋሆች ናቸው። የሰው



ልጅ አዕምሮ የተሰጠው ከፉውን ከደጉ አመዛዝኖ እንዲለይበት አይደለም?! ወዳጄ፤ በኔ ህይወትና በድርጅቴ ውስጥ ለየዋሆች የሚሆን ቦታ የለም!" አሉት ፊታቸውን እንዳዞሩ።

"ጌታዬ ምህረት ያድርጉልኝ?" አለ ሰውየው እንባ እየተናነቀው። አልመለሱለትም ። "ሚስቴ ወልዳ አራስ ቤት ነች፤ ሰባቱ ልጆቼ የሚልሱት የሚቀምሱት ርጋፊ ዱቄት እንኳን የላቸውም። ዐይኑ ሥውር እናቴ ዛሬ ጠዋት ጠኔ ይዟት ከተኛችበት የቦንዳ አልጋ ላይ አልተነሳችም። እኔም ራሴ እህል ከቀመስኩ ዛሬ ሶስተኛ ቀኔ ነው... ስድስት ወር ሙሉ ያለ ሥራ..." ንግግሩን ሣይጨርስ እንባ ቀደመው።

አብነት እንባዋን እየታገለች አቀረቀረች ። አባቷ ግን ጀርባቸውን ሳያዞሩ "እኔ መንገሻ ከደሙ ንፁህ ነኝ። መሣሣት አልነበረብህም፣ ከተሣሣትክ ደግሞ የስህተትህን ዋጋ በፀጋ መቀበል አለብህ። አሁን ሥራ ስለያዝኩ ቢሮዬን ለቀህ ውጣልኝ!" አሉት በቁጣ።

ሰውየው ፈዞ ባዶ ስሜት ባዘሉ ዐይኖቹ ጀርባቸውን ሲመለከት ከቆየ በኋላ እንባውን እያባበሰ የቢሮውን በር ከፍቶ ወጣ።

አብነት ራሷን መቆጣጠር አልቻለችም። "አባባ! ይህን ምስኪን ይቅርታ አድርገህለት የነዚያን ሁሉ ምስኪን ፍጥረታት ህይወት ብታድንስ?!" እያለች ማልቀስ ጀመረች።

አባቷም ፊታቸውን ወደርሷ መልሰው፣ "ይቅርታን ማድረግ የሚችል ርህሩህ ልብ ቢኖረኝ ኖሮ ዛሬ ከደረስኩበት መድረስ ባልቻልኩም ነበር። ምናልባትም ዕጣ ፋንታዬ ለቀን እንጀራቸው ከሚማስኑት ውስጥ በተራ ቁጥር አንድ መመዝገብ ነበረ" አሏት ሃዘን፣ ቅሬትና ድል አድራጊነት በተመላበት ትንሽ ፈገግታ።

አብነት በፍጥነት ወጥታ ደረጃውን እየተንደረደረች በመውረድ ሰውዬውን ህንፃው መውጫ በር ላይ አስቆመችው። ተስፋና ጥርጣሬ በተደባለቀባቸው ዐይኖቹ እየተመለከታት ኪሶቿን ሁሉ እያገላበጠች መፈተሽ ጀመረች። ኪሷ ውስጥ ያገኘችው ግን አንዲት የተጣጠፈች ብርና ሃያ ሳንቲሞች ብቻ ነበር። ቦርሣዋን ቢሮዋ ትታቀለች።

ምን እንደምትሰጠው ጨንቋት ስታስብ፣ የሃያ አንደኛውን አመት ልደቷን ስታከብር ከቤተሰቦቿ የተበረከተላትን የወርቅ አምባር እጇ ላይ ተመለከተችው። አስበች። ምርጫ አልነበራትም። ሳታመነታ

አምባሯን አውልቃ ሰጠችው። "ይህን ሽጠህ ቤተሰቦችህን መግባቸው። ሥራ እስከታገኝ ድረስ ምናልባት አትራቡም ይሆናል።"

ሰውየው እውነት አልመሰለውም። እየተንቀጠቀጠ የተቀበላትን የወርቅ አምባር እንደያዘ ፈዞ ቀረ። ሰባራ ሶልዲ ኪሱ ባልነበረበትና ቤተሰቦቹም በረሃብ ሊያልቁ ሰዓታትን በሚቆጥሩበት በዚያች ጊዜ የወርቅ አምባሯን የሰጠችው የኒያ የጨካኝ ሰው ልጅ መሆኗን ተጠራጥሮ ዐይኖቹን እየጨመቀ አጣርቶ ያያት ጀመር።

"ደህና ሁን!" ብላው ፎቁን መውጣት ስትጀምር ተከትሎ አስቆማትና "እመቤት! አንቺን የማመሰግንበት አንደበት የለኝም። ምን እንደምናገር እንኳን አላውቅም... እግዚአብሔርን የምለምነው ሰው ሆኜ ውለታሽን የምመልስበትን ቀን እዲሰጠኝ ብቻ ነው" አላት ሣግ ከሚያፍነው ልሣኑ ጋር እየታገለ።

"እግዚአብሔር ይርዳህ!" ብላው ደረጃውን መውጣት ስትጀምር ሰውየው ካለበት ሳይነቃነቅ ይመለከታት ነበር።

ንጽህና ቤት ገብታ ፊቷን ከታጠበችና ፀጉሯን ካስተካከለች በኋላ ወደ አባቷ ቢሮ ተመልሳ ገባች። ፊታቸውን ወደ መስኮቱ መልሰው ፒፓቸውን ለኩሰው ያጨሳሉ።

የበሩን መከፈት ሲሰሙ ፊታቸውን መልሰው አጠገባቸው በነበረው ወንበር ላይ እንድትቀመጥ በእንጫቸው አመለከቷት። በርጋታ እየተራመደች ሄዳ ተቀመጠች።

በእጇ ላይ የነበረውን የወርቅ አምባር አለመኖሩን ሲያዩ በቅሬታ ፈገግ ብለው "በድርጊትሽ ልታፍሪ ይገባል። ተግባርሽ ያረጋገጠልኝ ብኩን ሴት መሆንሽን ነው። ይህ ድርጅት ያለ ጠንካራ ወራሽ እንደሚቀርና ከህልፈቴ በኋላም በደምና በላብ ተጨማልቄ ያፈራሁት ሀብት ሰብሣቢ እንደሌለው እረዳለሁ። የዚህ ምክንያት ደግሞ ምናልባት እኔ እዚህ ቦታ ለመድረስ ከየት እንደተነሣሁ የማታውቂ ሥር ለቀቅ በመሆንሽ ይሆናል።" አሏት እንደ በረዶ በቀዘቀዙ ዐይኖች እያዩዋትና እንደ እሳት በሚለበልብ ምላሳቸው እያንገበገቧት። ወዲያው ዓይኖቻቸውን ቡዝዝ አርገው በሀሳባቸው ውስጥ ጠፉ።

***    ***    ***



መንገሻ የኔህ የእናትና የአባት ፍቅር አይቶ ያደገ ልጅ አልነበረም። አባትና እናቱ ጣልያን ኢትዮጵያን በወረረች ጊዜ ቤታቸው ውስጥ እንዳሉ ከአየር በተወነጨፈ ፈንጂ መሞታቸውንና እርሱም የስድስት ዓመት ልጅ እንዳለ በእሳት ነበልባል ከጋየው ጎጆ ውስጥ፣ ከሬሳ መሀል ተፈልፍሎ መውጣቱን የአገሬው ሰዎች ጉድ እያሉ እድሜ ከጨመረ በኋላ አጫውተውታል።

ከዚያ ለነፍሴ ያለ አንድ የንጋዴ ቤተሰብ ተጠግቶ በአሥር ዓመቱ በጎንደር ከተማ ውስጥ ለጣልያኖች እንቁላል እየገዛ የሚሸጥ፣ የሚላላክና መጠነኛ ሥራዎችን የሚሠራ ሽቃይ ሆነ። ጦርነቱ ከተፈፀመ ከአራት ዓመት በኋላ መንገሻ አንድ አሮጌ ካሚዮን ላይ ሲኖር ፖፒኖ ለሚባል ሽማግሌ ጣልያናዊ በአውታንቲነት ሊሠራ ተቀጠረ። ካሚዮኗ ከጎንደር ወረዳዎችና አውራጃዎች የሚሰበስብ የከብት ቆዳ ወደ አዲስ አበባ የምታመላልስ ነበረች። በዚያች የወላለቀች ካሚዮን ላይ የቆዳውን ቅርናት እንደ ውድ የፈረንሳይ ሽቶ ቆጥሮ፣ የሽማግሌውን ጭቅጭቅና ካልቾ እንደ ጉርሻና ምርቃት ተቀብሎ ለአሥር ዓመታት ያህል በትጋት፣ በቅንነትና በታማኝነት ሠራ። ጣልያናዊውም መቼም አንድ ጊዜ ሲፈጠር በዚህ ጥፉ ብሎታልና በኢትዮጵያ ውስጥ ቀረኝ የሚለው የሥጋ ዘመድ ስላልነበረው የወጣቱን ትጋት በማየት ሲሞት ካሚዮኗን አውርሶት እንደሚሞት ቃል ገባለት።

በአባትና በእናቱ ሞት በኢጣልያኖች ላይ ያቄመው መንገሻም፣ ሽማግሌውን በማግባባት "ሰውና እንጨት ድንገት ተሰባሪ ነውና መኪናዋን ለኔ ለማውረስህ በሕግ ሳታረጋግጥ ብትሞት ልፋቴ ሁሉ ከንቱ ይቀራል... መቼም በቃል ከተነገረ ነገር በጽሑፍና በውል የተቀመጠ ይሻላልና ውል ግባልኝ" በማለት ሌት ከቀን ይነተርከዋል።

ሽማግሌውም ንዝንዙ ሲሰለቻቸው ውርሱን በፍ/ቤት ያጸድቅለትና ሰነዱን በእጁ ይዞ "እንግዲህ እስከሞት ታገስ"ይለዋል። መንገሻ በትእግስት መጠባበቅ ጀመረ። አንድ አመት አለፈ። ሽማግሌው እንኳን ሊሞት አልታመመም። ሁለተኛው ዓመት ሄደ፤ ወይ ፍንክች! በእርጅና በገረጀፈው አካሉ ውስጥ ሲር፣ ሲር የምትል ነፍሱ እንደ ጅማት ክር ቀጥናና ጠንክራ አልበጠስ አለች። ሶስተኛው አመት ላይ ሽማግሌው ጭራሽ ቆዳውን እንደሚገለፍፍ እባብ እየታደሰና እያማረበት ሄደ። መንገሻ በገዛ እድሉ አዘነ።

በአምስተኛው ዓመት የሽማግሌው እድሜ እንደ ማቱሣላህ የተራዘመችለት ስለመሰለው ፍጹም ተስፋ ቆረጠ። መኪናዋ ከዓመት ዓመት እየወላለቀች ትሄዳለች። የጣልያኑ እድሜም እንደ መኪናዋ እየተንከራከሰች ታዘግማለች፤ የመንገሻ እድሜም ያለ ፋይዳ

ትባክናለች። በመጨረሻ አብረው በተኙበት አልቤርጎ በገዛ ፎጣው አፍኖ ገደለው፤ ለአንዱ መነሳት፣ ሌላው መውደቅ አለበት፤ ይህ በአዋጅ ያልተደነገገ ማኅበራዊ ሕግ ነው።

ምህረትን የሚለምኑና ይቅርታን የሚማጸኑት የሽማግሌው ዐይኖች እስከ ዛሬ ከህሊናው ሥሌዳ አልተፋቁም። ... ከተኛበት አልጋ ላይ አፍና አፍንጫውን አፍኖ ሲይዘው በሚቁለጨለጩት ዐይኖቹ ምህረትን ይለምኑው ነበር፤ አልማረውም።

የሽማግሌው ሞት በልብ ድካም ተመካኝቶ መንገሻ የወላለቀችዋ ካሚዮን ብቸኛ ወራሽ ሆነ። ከዚያች ዕለት ጀምሮ በወጣትነት ጉልበቱ የህይወትን ውጣ ውረድ በመጋፈጥ ከኑሮ ጋር ብቻውን ትግል ገጠመ። አሁን አሁን ከዚያች መኪና ጋር ያደረገውን ትግል ሲያስበው በመለኮት፣ አለበለዚያም በሰይጣን ድጋፍ እንጂ ያን ሁሉ ፈተና ብቻውን እንዳልተወጣው ይገምታል።

የእድሜ ኮንትራቷን ያገባደደችው ካሚዮን ጥቂት ኪሎሜትሮች ብቻ ሄዳ ካልሆነ ቦታ ትቆምና እልነቃንቅ ትላለች። መንገሽ ከጋቢናው ወርዶ ሞተሯ ሥር ይገባና አቧራና ጭቃ ላይ እየተንከባለለ አንዱን ብልሽት ይጠግናል። መኪናዋ ጥቂት ኪሎሜትሮች ብቻ በኤሊ ፍጥነት ትሄድና ደግሞ እሻፈረኝ ትላለች። ፀጉሩን እየነጩ፣ በግምባሩ ላይ እንደ ውሃ የሚወርደውን ላብ እየረጨ ይወርድና እንደገና ሞተሯ ሥር ይወተፋል። በመኪናዋ ብልሽት ሣቢያ ከአውሬ ጋር እየተፋጠጠ፣ እንደ እሳት የሚፋጀውን የቀን ሀሩርና እንደ በረዶ የቀዘቀዘውን የሌሊት ቁር "ተመስገን" ብሎ እየቻለ ሣምንት ያህል በረሃ ያድራል።

እንደ ሰው ከደም፣ ከሥጋና ከአጥንት ሣይሆን ከብረት የተገነባ "እቻዬ ዲፌር" ሆኖ ለመፈጠሩ ከራሱ ጋር የተማመነው ስድስት ቀን ያለበቂ ምግብና ውሃ በረሃ ውስጥ የተሰበረውን የመኪናዋን ሞተር ጠግኖ ካንቀሳቀሳት በኋላ ነበር።

በሰባተኛው ዓመት ላይ የኤሊዋን ሞተሮች አወላልቆ በመሸጥ፣ እንጀቱን አስሮ ካጠራቀመው ገንዘብ ጋር በማጣመር ትንሽ ፈጠን ያለች ሌላ ኤሊ ሲገዛ ሥጋው ከገላው ላይ ተፋቆ ነጭ አጥንቱ ፈጦ ሊወጣ ምንም አልቀረው ነበር። መኪናዋ ሥጋውን አላምጣ በልታ ደሙን ጠጥታዋለች። ያችን የቆርቆሮ ደመኛ ሳትቀድመው ግን ቀደማት።

በአሥራ ሶስተኛው ዓመት ላይ ፈጣኗን ኤሊ ሸጦ አንድ የኑዳጅ መጫኛ ቦቴ ገዛ። ከአምስት ዓመት በኋላ ደግሞ ሌላ፣ ደግሞ ሌላ፣ አሁንም ሌላ... በስቃይ ያስጨነቀችው፣ ቀና ቢል እንደጦር



እናት ሰንጥቆ የሚገባ ፀሐይ፣ ዥር ቢል ሞተሯ የተሰበረ አሮጌ ካሚዮን አይቶ እንደ ህፃን ልጅ ስቅስቅ ብሎ ሲያለቅስ ፊቷን ያጠቆረችበት ዓለም፣ እምስተኛውን የነዳጅ መጫኛ ቦቴ፣ የተንጣለለ የእንግዳ መቀበያና ሶስት መታጠብያ ክፍሎች ያሉት ትልቅ ቪላ ቤት ከነ ሙሉ ድርጅቱ ሲገዛ፣ እያጨበጨበች አብራው ሳቀች።

ከወደቀበት ትቢያ ላይ በጁና በእግሩ ተንፏቆ በትግሉ የቆመው መንገሻም፣ ዓለም ዳግመኛ ፊቷን እንዳታዞርበት ቀን ተሌት ጠንክሮ መሥራት ጀመረ። ማታ ማታ እየተማረም ዘጠነኛ ክፍል ድረስ ዘለቀ።

"በአንድ ሙያና በአንድ የህይወት መስመር ላይ ሙጭጭ ማለት ትርፉ እንደበሰበሰ እንቁላል ከውስጥ መሸተት ነው" የሚለው መንገሻ የነዳጅ መጫኛ ቦቴዎቹን ሁሉ ሸጦም መሬት በመግዛት በትራክተር የሚያርስ የናጠጠ ገበሬ ሆነ። ከአመታት በኋላ ደግሞ መሬቱንና ትራክተሩን ሸጦ የመለስተኛ ህንፃዎች ሥራ ተቋራጭ ሆነ።

ህይወት እንደሳቀችለት የወሎዋን ሸጋ አርያምን አግብቶ አንድ የአስመጭና ላኪ ድርጅት ከፈተ። በስተርጅና በወለዳት በአንድዬ ልጁ ስም ስይሞም "አብነት አስመጭና ላኪ ድርጅት" አሰኘው።

*** *** ***

መንገሻ ይህን ሁሉ ታሪክ በተመስጦ ሲያስቡ አብነት በዝግታ ክፍሉን ለቃ ወጣች።

ይህ የሆነው ከሁለት ዓመት በፊት ነበር።

እጆቿን አጣምራ ከተቀመጠችበት ወንበር ሳትነሣ ሻይ የሚያመላልሰው ልጅ ሰርቪሱን እንዳንጠለጠለ በሩን አንኳኩቶ ገባ። ሻዩን ሳትጠጣው ቀዝቅዟል። ልጁ ብርጭቆውን ይዞ ሲወጣ ፀሐፊዋ ገርበብ ባለው በር ጭንቅላቷን ብቅ አድርጋ "አቢ፣ አባትሽ ቢሮ ትፈለጊያለሽ" ብላት ሄደች።

አብነት በበሸቀት ጠረጴዛውን በቡጢ መታችው። እስከመቼ እንደ ህፃን እንቆቻብለው እንደሚይዟትና እስከመቼ ወድቆ እንደሚሰበር እንቁላል እንደሚጠነቀቁላት አይገባትም።

ስልችት እንዳላት ወደ አባቷ ቢሮ በመሄድ በሩን አንኳኩታ ገባች። ሰፊው ቢሮ ከግርማ ሞገሳቸው ጋር ተደምሮ ያስፈራል። አጠገባቸው ካለው ወንበር ላይ ለመቀመጥ ስትጠጋ ልብ ከሚያቀልጥ ፈገግታ ጋር ከመቀመጫቸው ተነስተው ጨበጧት። አብነት ደነገጠች።

ቦታ ቦታቸውን ይዘው ከተቀመጡ በኋላ እንኳን ፈገግታቸው ከገፃቸው አልጠፋም። ከወደትከሻቸው መጉበጥ ጀምረዋል። ጠይሙ የፊታቸው ቆዳ ዐይኖቻቸው ጠርዝና ጉንጫቸው አካባቢ መሸብሸብ ጀምሯል። ዐይኖቻቸው አልበገር ባይነትን ግንባራቸው ላይ የታረሱት የህይወት መስመሮች ደግሞ ጭካኔና አስፈሪ ሞገስን አላብሰዋቸዋል።

"በሠራተኞች አመጽ ላይ መሳተፍሽን ካወቅሁ በኋላ ያለ እንቅልፍ ነበር የሰነበትኩት። አንድ ነገር መወሰን ነበረብኝ"አሏት ፒፓቸውን ትምባሆ እየጠቀጠቁ። የአብነት ልብ በፍጥነት መምታት ጀመረ።

"ብዙ ካወጣሁና ካወረድሁ በኋላ በዚያን ዕለት ተማበርሽ ላዝን እንደማይገባኝ የወሰንኩት ገና ትላንትና ነበር። ድርጊትሽ ሁለት ነገሮችን አረጋግጦልኛል። አንደኛ ከእንግዲህ ህፃን ልጅ ያለመሆንሽን፤ ሁለተኛም ልበ ሙሉና ደፋር ሴት የወጣሽ መሆኑን ነው። የምንጊዜም ስጋቴና ጭንቀቴ በህጢያት እድፍ ጨቅይቼ፣ በላብ ተጨማልቄ ያፈራሁት ሀብትና ከምንም በላይ ደግሞ ይህ በስምሽ የሰየምኩት ድርጅት ያለ ጠንካራ ወራሽ ይቀራል የሚል ነበር።

"መቼስ ለወንድ ልጅ ፍሬ አላደለኝም። 'እያንዳንዳችን ገና ከእናታችን ማህጸን ስንወጣ የእድላችንን አሻራ በእጃችን መዳፍ ውስጥ ጨብጠናት እንወጣለን' የሚሉት የሰንበት መምህራችን እውነት አላቸው። የኔውም እድል በማታ እድሜዬ ባንድ እጄ ብዝቀው የማያልቅ ሀብት፤ በሌላው ደግሞ የወንድ ልጅ ፍሬ ማጣትን እርግማን ማፈሴን ከተገነዘብኩ ቆይቻለሁ።

"ከህልፈቴ በኋላ፣ በስንት ጥረት ያከማቸሁት የደለበ ሀብት እንደዋዛ ሲናድና ሲባክን፣ በደም ተጨማልቄ ያቋቋምኩት ድርጅት ሲዘጋ ይታሰበኝና ልፋቴ ሁሉ ከንቱ እንደነበረ በመገመት እሳቀቃለሁ። አንዳንዴም አምላክ በኃጢያቴ እየቀጣኝ ነው ስል እጨነቃለሁ።"

ፒፓቸውን ደጋግመው ከሳቡ በኋላ ገለፃቸውን ቀጠሉ። "ገና ከልጅነትሽ ድሆች የሚማሩበት ትምህርት ቤት ገብተሽ እንድትማሪ ያደረኩት ያለ ምክንያት አልነበረም። ድህነትን እንድታይና እንድታውቂ ነበር። ሰው ድህነትን ከፈራ ስንፍናንም ይጠላል የሚል እምነት ነበረኝ። ያሰብኩት የተሳካልኝ አልመሰለኝም። ከዚያ የፈረንጆች ጅምር እብድ ከሆነ ሰዓሊ አጎትሽ ጋር ያሳለፍሻቸውን ጊዜያቶች ሁሉ እንደባከኑ ነው የምቆጥራቸው። አየሽ፤ የሰው ልጅ



እያንዳንዷን የሰከንድ ሽራፊ ከቡ ለማስቀረት የማያውለው ጊዜ ሁሉ የባከነ ነው። አንዳንድ ጊዜ ሳስበው 'ነጮቹ በስልጣኔና በእድገት ዝናቸው እኛን ተቀጣይ የባህር ፍርጎ ያደረጉን በጊዜ አጠቃቀም ብልሃታቸው እንጂ ለአዕምሯቸው በተሰጠ ልዩ ፀጋ አይደለም' የሚሉት ሰዎች እውነት አላቸው እላለሁ።

"ያም ሆነ ይህ ከእንግዲህ እኔን ተክተሽ ስለምታስተዳድሪው ድርጅት ተግባርና ምስጢር ማወቅ እንዳለብሽ ወስኛለሁ። ቆሜያለሁ ማለት ዘበት ነውና ጊዜ ሳይቀድመኝ እንደቀደምኩት እገምታለሁ" አሏት በተሽከርካሪው ወንበር ላይ እየተቁነጠነጡ።

የአብነት ዐይኖች እንደፈጠጡ ነበሩ። የመጨረሻውን ሀረግ ሲናገሩ የምትመለከተው የአባቷ ገጽታ ደስተኛ አልነበረም። በድምፃቸው ውስጥ ቅሬታ ይሰማል። አማራጭ በማጣት ብቻ ያደረጉት ነገር ስለነበር ከልብ አዘነችላቸው።

"የድርጅቱ ሂሣብ በየዓመቱ ለምን ኪሣራ እንደሚያሳይ ደጋግመሽ እንደጠየቅሽኝ አስታውሳለሁ። ገቢያችንን የምንደብቅበት በቂ ምክንያት አለን። ምናልባት የመንግሥት ግብር ለማስቀነስ ወይም ለማስቀረት መስሎሽ ከነበር ተሳስተሻል" አሏት። በገፃቸው ላይ እየጎላ የሚሄደውን ጭንቀት እየችና ሀዘኔታዋ ወደ ፍርሃት አጋደለ "ያች ቀን ደረሰች!" ስትል አሰበች።

ከረጅም ዝምታ በኋላም "አቢይ ምክንያታችን የድርጅቱ ዋነኛ ገቢ ከኮንትሮባንድ ንግድ የሚገኝ በመሆኑ ነው!" አሏት ግንባራቸውን ቋጥር አድርገው። ንግግራቸው ያሳደረባትን ስሜት ለመረዳት ዐይኖቻቸው ለቅጽበት እንኳን ከዐይኗ ላይ አልተነቀሉም። አብነት በድንጋጤ ተሽማቀቀች።

"በሶሻሊስት የኢኮኖሚ ፖሊሲ በተተበተበ የንግድ ዓለም ውስጥ በሀቀኝነት ነግጄ አተርፋለሁ የሚል ነጋዴ ቢኖር፣ አንድም ደንቆሮ አለያም ገንዘቡን መጣያ ያጣ ምስኪን ነው። እለት ተለት የማደግና የመግዘፍ ፍላጎቱ እግር ከወርች የታሠረ ካፒታል፣ ህጋዊ በሆነ መንገድ መፈናፈኛ ካጣ፣ የህግን እግረ ሙቅ ሰብሮ ለመዳበርና ለመግዘፍ ቀዳዳ መፈለጉ የራሱ የካፒታል ጠባይ በመሆኑ በድርጅቱ የኮንትሮባንድ ንግድ ሥራ አላፍርበትም" አሏት ፍርጥም ብለው።

ፒፓው ውስጥ ጨሶ ያለቀውን የትምባሆ አመድ በሲጋራ መተርኮሻው ላይ እያራገፉ ከቆዩ በኋላም "ድርጅቱ በኮንትሮባንድ

ነጋዴኑቱ ወደ ሀገር በድብቅ ከሚያስገባቸው እቃዎች ውስጥ ልዩ ልዩ መሣሪያዎች፣ መለዋወጫዎች፣ የህትመትና የማባዣ መኪናዎች፣ ካሜራዎች፣ የፊልም ፕሮጀክተሮች፣ የነፍስ ወከፍ የጦር መሣሪያዎችና ፈንጂዎች ዋና ዋናዎቹ ሲሆኑ፤ ከሀገር ውስጥ እያሾለክን ከምንልካቸው ውስጥ ደግሞ አትራፊዎቹ ወርቅና የዱር አራዊት ቆዳ ናቸው" አሉ።

ሳታስበው ከንፈሮቿ መንቀጥቀጥ የእጅና የእግር መተጣጠፊያዎቿ መዛል ጀመሩ። አባቷ ፍርሃቷን እንዳያወቁባት ከራሷ ጋር መታገል ብትጀምርም አልቻለችም።

አባቷ ቀጠሉ ። "በንግድ ዓለም ውስጥ ዋነኛው ጥያቄ ትርፍ እንዴት ተገኘ የሚለው ሳይሆን ትርፉ ራሱ ነው። ኀብዝ ነጋዴ ቀን ተሌት የሚያልመው እንደተራራ ከቆለለው የካፒታል ክምር ላይ እንዴት የሳንቲም ሽራፊ እንዴት እንደሚያክልባት እንጂ ያቺ ሣንቲም ስትገኝ የተሠራው ኃጢያትና በዚያ ሳቢያ ሊደርስ የሚችለው የገዥም እሣት ቅጣት አይደለም።" ድንገት መሣቅ ሲጀመሩ አብነት የልቧ ምት ፈጠነ።

"ለገሀነመ እሣቱ ቅጣትማ ደሀውም ሀብታሙም እኩል ነው የሚሰለፉት ። ምክንያቱም ድሃ ሆኖ መፈጠርም በራሱ ኃጢያት ነው። የድሀ መነሻና መድረሻው ያው የሲጋና የነፍስ ሲኦል ነው። ምድራዊውን ሲኦል ገነት ለማድረግ የሚውተረተር ድሃ ግን ብልህ ነው። ቢያንስ ቢያንስ ከጋለ ብረት ድስት ወደ ጋለ ብረት ድስት እየተገላበጠ እንደሚጠበስ ሥጋ ከመሆን ያመልጣልና።

"እና አትደንግጭ፤ ይኼ የህይወት ጥያቄ ነው፤ የመኖር ወይም ያለመኖር ትግል። አንድ ሰው በህይወት ለመኖር ከወሰነ ደግሞ ከሰውነት ማእረጉና ክብሩ ጋር መኖር አለበት። አለያ የሚተነፍስ ሬሳ እንጂ ሰው አይደለም። እንደ ሰው ከሰው ተፈጥረው በሁለት እግራቸው መቆም አቅቷቸው ዘላለም እንደ እበት ልጅ በደረታቸው ሲንፏቀቁ የሚኖሩ ሰዎች ምን ጥሟቸው በዚህ ምድር ላይ እንደሚኖሩ አይገባኝም?! የህይወት ትርጉም መኖር ብቻ መስሏቸው ከሆነ ተሳስተዋል!!"

አባቷ ለምን በዚህ ዝርዝር የህይወት ጉዳይ ውስጥ ገብተው እንደሚነግሯት ያልገባት አብነት፣ በመገረም የፈጠጡ ዐይኖቿን እያርገበገበች ከማዳመጥ በቀር አንዲትም ቃል አልተነፈሰችም።



"ይህን የምነግርሽ ... በህይወቴ ካካበትኩት የእውቀት መዝገብ ላይ እየለቀምኩ ነው። በዚህ ምድር ላይ እውነትንና እውነተኞችን አገኛለሁ ብለሽ አንድ ሺ ዘመን ምድሪቱን በስንጥር፣ ሰማዩን በጭራሮ እያሰሽ ፈልጊ - አታገኚያቸውም። አሥር እንጀራ ለአንድ ሺ የምታሻማው ህይወት ራሷ፣ ሰብአዊውን ፍጡር ሰብአዊነቱን ገፎ የጣለ፣ ከራሱ በላይ የማያስብ አሳማ አድርጋዋለች። በአሳሞቹ ገበታ ላይ ከአሳሞች ጋር ለምግብ ቀርበሽ እንደወፍ ብትቆነጥሪ፣ ጠኔ አዙሮ ይደፋሽ እንደሆን እንጂ ድርሻሽን የሚተውልሽ የለም። ይህ የህይወት ፈተና ነው። አሥር እንጀራ ለአንድ ሺ ሰው ታሻማለች፣ ጠንካሮችና ብልሆች ጠግበው ያድራሉ፤ ደካሞችና የዋሆች ይራባሉ። በኔ ህይወት ውስጥ ይሉኝታ፣ ሥነ - ምግባርና ይቅርታ ቦታ የላቸውም። አንቺም እኔን መስለሽ እንድትበቅዪ እፈልጋለሁ!" አሏት ፒፓቸውን አዲስ ትምባሆ ለመጠቅጠቅ የፕላስቲክ ፖኬት ከኪሳቸው እያወጡ።

አብነት ስለ አባቷ ይህን ያክል አለማወቋ ገርሟት አፏን እንደከፈተች ቀረች። ትምባሆውን በርጋታ ከጠቀጠቁና ከብሪት ጭረው ከለኮሱ በኋላ "ይህን የምነግርሽ ያለምክንያት አይደለም። ድርጅታችን የኮንትሮባንድ እቃዎችን የሚያስገባበትንና የሚያስወጣበትን ዘዴዎች ስነግርሽ እንዳትደነግጪ ብዬ ነው። በዚህ ረገድ የምንጠቀምባቸው ሶስት መመሪያዎች አሉን። አንደኛው በተቻለ መጠን እቃዎቹ በምስጢር እንዲወጡና እንዲገቡ ማድረግ ነው። ይህ ሁልጊዜ የሚሳካ ነገር አይደለም። ... በኬላ ጠባቂዎች መያዝ፣ በፊናንስ ፖሊሶች እጅ መውደቅ አለ። እንዲህ ሲሆን ሁለተኛውን ስልት ለመጠቀም እንሞክራለን። የኬላ ጠባቂዎችንም ሆነ የፊናንስ ፖሊሶችን አፍ በብር ረብጣ ጠቅጥቀን ፀጥ እናሰኛቸዋለን። ለመንግሥት ባለሥልጣኖች በሶስተኛ እጅ በኩል በሚሰጥ መማለጃ ጉዳዩን በማድበስበስ ንብረቶቻችንን ለማስለቀቅ እንጥራለን። ይህ የማይሳካ ከሆነ ግን ሶስተኛውንና አደገኛውን መመሪያ ለመጠቀም እንገደዳለን። በዚህ የመጨረሻ አማራጭ፣ በሀይል ተዋግተንና ደም አፍስሰን፣ ራሳችንም መስዋእት በመሆን ከበባውን እንጥሳለን። የብዙ ንጹሀን ደም እንደሚፈስ ብናውቅም፣ የአንዱ ውድቀት ለሌላው ትንሳኤ ነውና አንጨነቅም።"

የትምባሆው ጭስ ቀጥ ብሎ ወደላይ ይትጎለጎላል፤ የአብነት የተበለጠጡ ዐይኖችና የተከፈተው አፏ አልገጠሙም። "እና እኔ ነኝ በንጹሀን ደም ለመጨማለቅና ይህን ሁሉ ጉድ ለመሸከም የታጨሁት?!" ስትልም ደጋግማ ራሷን ትጠይቃለች። "ለዚህ ድርጅት እንደ ዓይን ብሌን ሆነው የሚያገለግሉ ሁለት ሰዎችን ደግሞ ላስተዋውቅሽ..." አሉና የጠረጴዛውን መሳቢያ ከፍተው ሁለት ቢጫ ፋይሎችን

በማውጣት የመጀመሪያውን ፋይል አቀበሏት። "ስዩም አለሽኝ፤ የህግ ጠበቃ" የሚል ጽሑፍ አነበበችና ገለጠችው።

ጠበቃውን ታውቀዋለች። ወደ ድርጅቱ በመጣ ቁጥር ቢሮዋን ሳይሳለም ሄዶ አያውቅም። ብዙ ጊዜ ሻይ አብረው እንዲጠጡ ቢጠይቃትም ቀልቧ ስለማይወደው ግብዣውን አትቀበለውም።

በገለጠችው ፋይል ውስጥ በቅጥር ውል ስምምነቱ ላይ ፎቶግራፉን ተመለከተች። ከፊቱ ረዘም፣ ከአፍንጫው አጠር ያለ ኀልማሳ ነው። ከግምባሩ በራነት ጀማምሮታል፤ ትናንሽና በጥልቀት የሚያስተውሉት ዐይኖቹ ነገር አዋቂነቱን ይመስክሩለታል።

"ይህ ሰው የድርጅታችን የዐይን ብሌን ነው። የህግ ትምህርቱን የተማረው እንግሊዝ አገር ሲሆን፤ ድርጅቱ ከገባበት አዘቅት ውስጥ እየተከራከረ ነፃ ያወጣው ባለውለታችንም ነው። ድርጅቱ እሱን ይዞ የተረታበት ጊዜ የለም። ወተት ጥቁር ነው ብሎ የማሳመን ችሎታና ከሰይፍ የሣለ ምላስ ያለው ነው። ምናልባት ወይዘሮ ሁሉግርጌሽ የሚባሉትን የእናትሽን አብሮ አደግ ታውቂያቸው ከሆነ የርሳቸው የወንድም ልጅ ነው። ወደ ዋናው ቁም ነገር ልመለስና፣ እያንዳንዱ ሰው የየራሱ መጥፎ ባህርይ አለው። ይህም ሰው ድርጅቱን ሊጎዱ የሚችሉ መጥፎ ባህሪያት አሉት። ከመጠን በላይ ጠጪና አመንዝራ ስለሆነ የድርጅቱን ሚስጥር ይጠብቃል የሚል እምነት የለኝም።... ገንዘብን ከምንም በላይ አብልጦ የሚወድ በመሆኑም አንድ ቀን ይሸጠናል የሚል ጥርጣሬ አለኝ። ስለዚህ ዐይኖቼን ሳልሰብር ሁልጊዜም በንቃት እጠብቀዋለሁ" አሏት።

ከዚያም የመጀመሪያውን ፋይል ተቀብለው ሁለተኛውን አቀበሏት። "ናፖሊዮን አምባው፤ ሾፌር" የሚል ጽሁፍ ተጽፎበታል። ፋይሉን ገልጣ ስትመለከት ጢሙን ያሳደገና ግምባሩ ቅጭም ያለ ያንድ ኀልማሳ ፎቶግራፍ አየች። ለነፍስ ገዳይነቱ ቅንጣት ታህል አልተጠራጠረችም። እርሱንም እዚሁ ቢሮ ሲመላለስ ታውቀዋለች።

"ይህ ሰው የድርጅቱ ቀኝ እጅ ነው። የመጨረሻው እግራጭ የሚተገበረውም በርሱ አማካይነት ነው። ድርጅቱ ውስጥ ከመቀጠሩ በፊት የአየር ወለድ ሠራዊት አባል ነበረ። ኤርትራ ላይም ግራ እግሩን በጥይት ተመቷል። ድርጅቱ የቀጠረው በሾፌርነት ሽፋን ሲሆን ዋነኛው ተግባሩ ግን ድርጅቱ የሚያንጃብብበትን አደጋ የቀኝ ከንድ በመሆን ህልውናውን ማስጠበቅና መጠበቅ ነው" አሉ የጎሪጥ እየተመለከቷት።



አብሯት ጆሮዎቿ በትክክል የሚያዳምጡ ለመሆናቸው እርግጠኛ አልነበረችም። ድርጅቱ ውስጥ ሁለት ዓመት ያህል ስትሠራ ይህን ሁሉ ጉድ ባለማወቋ ራሷን እንደደደብ ቆጠረችው።

አባቷ ገለፃቸውን ቀጥለዋል። "ከነኝህ ለድርጅቱ ዐይን ከሆኑ ሠራተኞችና ከጥቂት ታማኞች በቀር፣ ማንኛውንም ሠራተኛ ከአንድ ዓመት በላይ በቋሚነት አንቀጥርም። አንድ ሠራተኛ በድርጅቱ ውስጥ ብዙ ቆየ ማለት ስለ ድርጅቱ ብዙ አወቀ ማለት ነው። ይህ ደግሞ የድርጅቱን ሚስጢር ለነፋስ መበተንና በአደጋ ቀለበት ውስጥ መግባት ስለሆነ ብዙ እንጠነቀቃለን" አሏት የሰጧትን ፋይል ለመቀበል እጃቸውን እንደዘረጉ።

ቀስ ብላ አቀበለቻቸው ። ፋይሉን በመያዟ ብቻ እጆቿ በደም የተጨማለቁ ስለመሰላት በቀሚሷ መጠራረግ ጀምራለች። ከተቀመጡበት ተሽከርካሪ ወንበር ላይ ተነስተው ከወንበሩ ጀርባ ቆሙና "የነገርኩሽን የድርጅቱን ሚስጥር እንድትጠብቂ አልጠይቅሽም። ከእንግዲህ ህፃን አይደለሽምና ራስሽን ለውድቀት አሳልፈሽ እንደማትሰጪ እገምታለሁ... ለወደፊቱ ተቀራርበን እንደምንሠራ ተስፋ አለኝ። ጨረስን!" አሏት ። እግሮቿ እየተወላገዱ ከፍሉን ለቃ ወጣች።

ቢሮዋ ገብታ ወንበሯ ላይ ስትቀመጥ ራሷን እንዳዞራት፣ ከንፈሯ፣ እጆቿና እግሮቿ እንደተንቀጠቀጡ ነበሩ። በደም ባህር ውስጥ የሚዋኘው የአባቷ ህይወት ታሰባት። ድርጅቱ በያንዳንዷ ሰከንድ ለአደጋ የተጋለጠ መሆኑንም ስታምን ሕይወቷ ጨለማ ሆኖ ታያት። የዚህ አደገኛ ድርጅት ወራሽና የወደፊቱ የሥራ መሪ እንድትሆን በመታጨቷም የአባቷን ህሊና ቢስነትና ጭካኔ ረገመች።

በአንድ ነገር ግን እርግጠኛ ነች። ህይወት ጨካኝ ደፋርና ቆራጥ አድርጋ አላበቀለቻትም። "እሣት አመድ ወለደ" እንዲሉ ከአባቷ ጋር ያላት የባህርይ ልዩነት በሰማይና በምድር ርቀት መጠን የተዘረጋ ነው። ደምና ሥጋቸውን እንጂ ከባህርያቸው ቅንጣት ታህል አልተጋራችም።

"ለወደፊቱ ተቀራርበን እንደምንሠራ ተስፋ አለኝ። ጨረስን!" የአባቷ ድምጽ ልክ በረሀ ውስጥ እንደሚጮህ ቁራ ህሊናዋ ውስጥ ይጮሃል፣ ይጮሃል፣ ይጮሃል። ፈራች። ብላቴና ጨለማን እንደሚፈራ እርሷም ህይወትን ፈራች።

ደንዝዛ በተቀመጠችበት ብዙ ከቆየች በኋላ ነበር ጠረጴዛዋ ላይ ያለውን የሣራ ጋዴም ማስታወሻ ያየችው። "አቢ! ግማሽ ሰዓት ቢሮሽ ውስጥ ተጎልቼ ብቆይም ከተቀረቀርሽበት የአባትሽ ቢሮ ባለመውጣትሽ

ብሽቅ ብዬ ሄጃለሁ። ከሥራ መልስ ቤት እመጣለሁና ጠብቂኝ። ጭፈራ ስለምወጣ አዲሱን ባለ ፈር ጃኬትሽን ታውሽኛለሽ። ቻዎ!"

አብነት በዚያ ጭንቀቷና ሀዘኗ ውስጥ የሣራ ጋዲምን ማስታወሻ እንብባ ስትጨርስ ፈገግ አለች። በሣራ ቀጠሮም ደስ አላት። ምናልባት ስለ ቻርሊ ጥቂት ነገሮችን መስማት ትችል ይሆናል።

*** *** ***

አብነት መኝታ ክፍል ውስጥ ሣራ ጋዲም ጫማዋን አውልቃ አልጋ ላይ ጋደም አለች። አብነትም አዲሱን ባለ ፈር ጃኬት በፌስታል ጠቅላላ መደርደሪያው ላይ ካስቀመጠችላት በኋላ ከአልጋው ትይዩ ባለው ወንበር ላይ ተቀመጠች።

"አብነቴ፣ ፍቅር ያዘኝ የምትል ሴት ስታጋጥመኝ እንደምን እንደምቆጥራት፣ እንደ ምስኪን እንደማዝንላት ታውቂያለሽ?!"

"ለምን?!"

"እንጃ። የቃሉ ትርጉም አይገባኝም። ከወንድ ጋር መቅበጥ፣ መዝናናት እንጂ ከዚያ በላይ ፍቅር እያሉ ሰዎች በራሳቸው ጭንቅላት ውስጥ የሚፈጥሩት ፈዝ አይጥመኝም" አለች ሣራ አጭር ፀጉሯን በጣቶቿ እያበጠረች። አብነት ይህችን ልዩ ፍጥረት በመገረም ታስተውላታለች - ያለመሰልቸት።

"ታዲያ አንዳንድ ቀን ሁሉም ነገር ስልችት ሲለኝ፤ የወንድን ልጅ ዐይን ማየቱ ሲያስጠላኝና የገዛ ነፍሴም የባዘች ስትመስለኝ፣ መኝታ ቤቴን ኢቆልፍና አልጋዬ ላይ ተጋድሜ አንጎሌ 360 ዲግሪ እስኪሽከረከር አስባለሁ። የበሽታ ይሆን እንዴ?! እያልኩም እጨነቃለሁ። ያኔ የገዛ ህሊናዬ መንፈሴን በወቀሳ ጦር ይሸቀሽቀዋል። 'ስስታም ነሽ ሣራ! በገዛ ህይወትሽ መስተዋትም የራስሽ ምስል እንጂ የሌላ ሰው አይታይሽም፣ መቀበልን ስታውቂበት መስጠት ግን አይሆንልሽም። ፍቅር እኮ ቸርነት ነው። አንቺ ግን ለራስሽ ፍላጎት ማነፍነፍ እንጂ ለሌላው የፍቅር ጥማት ቁብ የለሽም። ይህን የአሸንጉሊት የመሰለ ውብትሽን እንደ ጥሩር አጥልቀሽ ለማንበርከክ እንጂ ለመንበርከክ፣ ድል ለማድረግ እንጂ ድል ለመሆን ስለማታልሚ፣ የፍቅር ጦር ልብሽን ቀዶ ሊገባ አይችልም። አንቺ ምንም ቢሆን ማፍቀር አትችይም ' እያለ በነገር ወስፌ ጠቅ ሲያደርገኝ ደንግጬ ከአልጋዬ እነሳና ' ጎዶሎ ህይወት' እያልኩ ጨለማ ክፍል ውስጥ ብቻዬን ተንሰቅስቄ አለቅሳለሁ"



አብነት ልቧ በሀዘን ተሰብሮ ሁለቱን እጆቿን ደረቷ ላይ አመሳቅላ በርህራኄ ዐይን ትመለከታታለች። በሀዘን የጨፈገገው የሣራ ገፅታ ግን እፍታ ሣይቆይ በፈገግታ ተጥለቅልቆ ትቀጥላለች። "ግና ጉንጮቼን እያቃጠለ የሚወርደው ትኩስ እንባዬ ሳይደርቅ ግን ያው ህሊናዬ ይቀየርና 'የለም! የለም! አንቺ እንዳችም የህይወት ሣንካ የለብሽም ሣራ' እያለ ያጃጃኛል። 'ወንድን ልጅ ማዝናናት፣ ማቅበጥ አፈቀርኩ ብሎ ልቡን ሲጥል በቆመበት ገትሮ ማለፍ እንጂ፣ ፍቅር የሚሉት የሴትን ልጅ ወኔ ማምከኛ መተት ለአንቺ እጣ ክፍልሽ አይደለም' እያለም ያጽናናኛል። 'ለምን ከሌሎች ውድቀት አትማሪም ወዳጄ?!' እያለ እውነትን ይጠቁመኛል። 'ወደድኩ፣ አፈቀርኩ ብለሽ ስትንበረከኪ ጀርባሽን እረግጠ በሌላይቱ ሄዋን ላይ ለሚንጠለጠል የአዳም ዘር እንዲች ብለሽ ልብሽን እንዳትሰጭ!' እያለ ያስጠነቅቀኛል" አለቻት። አብነት ማስጠንቀቂያው ለእርሷ መሆኑ ገብቷታል። "አብነቴ፣ አንቺም ተጠንቀቂ። እንዶድ በገርነቷ ውሃ በላት እንዲሉ፣ አንቺንም የዋህነትሽ ጠልፎ እንዳይጥልሽ ዐይኖችሽን ገልጠሽ ተመልከች"

አብነት ለምን ታስፈራራኛለች በሚል ቁጭት ከውስጥ መንደድ ጀመረች። "አንቺ ማለት እኔ አይደለሁም ሣራ። ሁለት ሰዎች የግድ አንድ አይነት አመለካከት ሊኖራቸው አይችልም። እኔ ግን ስለ ፍቅር ሁሉን እቀበላለሁ!" አለቻት በቆራጥነት።

ሣራ ከተኛችበት በዝግታ ተነስታ ጠርዙ ላይ ተቀመጠችና በመገረም ትመለከታት ጀመር። "አብነት! ቀድሞ ነገር አንቺ ስለፍቅር ምን ታውቂያለሽ?!"

"ሁላችንም ከእናታችን ሆድ ስንወጣ ፍቅርን ተምረን የምንወጣ ይመስለኛል። ለማፍቀር ኮሌጅ መግባት ወይም የግድ በእድሜ መገርጀፍ አለብን?!"

ሣራ ለዚህ ጥያቄ መልስ አልነበራትም። ይልቁንም ጓደኛዋ በጥቂት ሣምንታት ውስጥ በአስተሳሰቧ በስላ፣ በባህርይዋ ተለውጣ ጭራሽ የፍቅርን አቡጊዳ ልታስቆጥራት ሽንጧን ገትራ ስትሞግታት ዐይኖቿን እያርገበገበች፣ ከንፈሯን እያንሻፈፈች "አቢ ቢያንስ ቻርሊን ያፈቀርሽበትን ምክንያት ንገሪኝ!" አለቻት በመረታቷ እልህ ይዟት።

አሁን ደግሞ ግራ መጋባቱ የአብነት ተራ ሆነ። ፀጥ ብላ ማሰብ ጀመረች። "እውነት ያፈቀርኩት ለምንድነው?! ለውብቱ መንበርከኬ ይሆን?! በጭራሽ! ውበት ሊደነቅ ቢችል እንጂ፣ የሚፈቀርስ የሰው

ልጅ ሙሉ ስብእና ነው። ሙሉ ስብእናውን በውል የማያውቀውን ሰው እሩን ሞልቼ አፍቅሬዋለሁ ማለት እንዴት ደፈርኩ?! ወድጄዋለሁ የሚለው ቃል ይሻል ይሆን?! ዳሩ ስልቻ ቀልቀሎ፣ ቀልቀሎ ስልቻ እንደተባለ ልዩነቱ ፀጉርን የመሰንጠቅ ያህል የቋንቋ ጨዋታ ብቻ ነው። ለመውደድ ተከፍቶ ለፍቅር የሚቀረቀር ልብ አሰቂኝ ነው የሚመስለኝ። ሆሆይ፤ ለነገሩ የሣራ ጥያቄ ፈታኝ ነው!" ከራሷ ጋር ስትነጋገር ቆየችና በመጨረሻ "እኔ እንጃ ሣራ፣ ሁላችንም ስንጠለ እንጂ ስናፈቅር ይህ ነው የምንለው ምክንያት የለንም። ቢኖረንም ደግሞ በውል አናውቀውም። አይደል?" አለቻት በሣራ ጥያቄ እንዳትረታ ይህን መልስ የሰጣትን አዕምሮዋን እያደነቀች።

"ሆሆሆይ!" ይሄው ነበረ የሣራ መልስ።

አብነት ያሳለፈቻቸውን የጭንቀት ቀናትና ያለ እንቅልፍ የገፋቻቸውን አሰልቺ ሌሊቶች ቁጥር ሣራ አታውቅም። ከሰው ሸሸታ በብቸኝነት ምን ያህል እንደተቆራመደችም ሣራ አላወቀችም። ፍቅር በነኛ ጥቂት ሣምንታት ብቻ ምን ያክል መንፈሷን እንዳደከመው አካሏን እንዳደቀቀውም አላወቀችም። አብነት ግን አልቻለችም፤ ተሸንፋለች።

ሣራ ከአልጋው ላይ በፍጥነት ወርዳ ጫማዋን አጠለቀችና ወደ ቁምሳጥኑ መስተዋት በመሄድ አጭሩን ፀጉሯን በጣቶቿ ማስተካከል ጀመረች። ተበሳጭታለች። አብነት አቀርቅራ ታስባለች። ሣራ ፀጉሯ መስተካከሉን ካረጋገጠች በኋላ ወደ አብነት በርጋታ በመቅረብ "ስለ ቻርሊ አንድ እውነት ማወቅ አለብሽ አብነት!" አለች ሀዘኔታና ጭካኔ በተመላበት ድምጽ።

"ምን?!" አለች አብነት እየተርበተበተች። "አ፣ ማለቴ..." ሣራ! የአብነትን በድንጋጤ የከሰለና በፍርሃት የተበለጠጡ ዐይኖች ስትመለከት ልትናገር ያሰበችውን ትታ ዐይኖቿን ማርገብገብ ጀመረች።

አብነት ስለ ቻርሊ ልትነግራት የፈለገችው መጥፎ ነገር በምላሷ ጫፍ ላይ መንጠልጠሉን ስለተረዳች መራራውን እውነት ለመስማት ደፍራ መቀመጥ አልቻለችም። ጉልበቷ ይብረከረክ አካሏ ይንቀጠቀጥ ጀመር።

ሣራም የአብነትን ሁኔታ ስትመለከት የመሸበርና የስጋት ስሜት አደረባት። 'አንድ እውነት' ያለችውን እውነት ለመናገር የከፈተችውን አፏን ስትገጥም ሁለት ፍሬ የእንባ ዘለላዎች የዐይኗን ሽፋሎች ዘለው ወደቁ። በጓደኝነት በቆዩባቸው ረጅም ዓመታት ውስጥ



ለመጀመሪያ ጊዜ በሣራ ዐይኖች ላይ እንባ ያየችው አብነትም ፍርሃትና ድንጋጤው ለቋት በመገረም አፍጥጣ ታያት ጀመረ።

ሣራ በፌስታል ተጠቅልሎ የተቀመጠውን ባለ ፊር ጃኬት እንስታ በርሳዋን ካነገተች በኋላ ዐይኖቿን በመሀረብ አደራረቀች። በሩን ከፍታ ልትወጣ ስትልም ዞር ብላ አብነትን በርህራሄ ዐይን እያየቻት "አቢ፣ እባክሽ ይህን ቻርሊ የምትይውን ሰው እርሺው፤ 'የማይበሉት እህል ከአፈር አንድ ነው'" ብላት ወጣች።

## ምዕራፍ አራት

ከዚያ በኋላ ስላሉት ጥቂት ቀናት የምታስታውሰው ነገር የለም። ጠባይዋ ሁሉ ተለዋውጦ አውሬ ሆናለች። ከቤተሰቦቿ ጋር በረባ ባልረባው መናቆር የየእለት ተግባሯ ሆነ። ከነዚህ ራሷን እንደ እብድ ከምትቆጥርባቸው ቀኖች በአንደኛው ምሽት፤ መኝታ ክፍሏ ውስጥ ልታነብ የምትታገለውን ልብ ወለድ መጽሐፍ አሽቀንጥራ አልጋዋ ላይ ወረወረችና በረዥሙ ፒጃማዋ ላይ ጋቢዋን ደርባ ከመኝታ ክፍሏ እየተጣደፈች ወጣች። መተላለፊያውን አቆራርጣ የጀርባውን በር ስትከፍትም ቀዝቀዝ ያለ የበጋ ነፋስ ዳበሷት አለፈ። ከዚያ በሩን በዝግታ ዘግታ ከጥርብ ድንጋይ በተሠራው ደረጃ ላይ ኩርምት ብላ ተቀመጠች።

የጨረቃ ብርሃን ሰፊውን ግቢ ወገግ አድርጎታል፤ ከዋክብትም በጠቆረው የሰማይ ሰሌዳ ላይ ተሰበጣጥረው ያንፀባርቃሉ፤ በቅጥር ግቢው ዙሪያ የታጠረውን ግንብ ተንተርሰው ያደጉት የጥድ ዛፎች በንፋሱ ኃይል እየተገፉ በሻልስ ስልት ይደንሳሉ። መላው ዓለም በእንቅልፍ ተውጦ ብቻዋን የቀረች እስኪመስላት ድረስ ፀጥታ ሰፍኗል።

በጋቢዋ እንደተጠቀለለች ሰማዩ ላይ አፈጠጠች። የጨረቃዋ ውበት አይታያትም። የከዋክብቱም ጥቅሻ አልሳባትም። የምታየው ሁሉ አልጣማትም። በአካልም በመንፈስም ደንዝዛ የጨው አምድ መስላ ተኀልታለች።

ዘግይታ የሰው ድምፅ የሰማች መሰላትና ጆሮዎቿን አንቅታ የድምጹን አቅጣጫ ማጣራት ጀመረች። መጀመሪያ ዝግ ብሎ የሚያጉረመርም የመሰላት ድምጽ እየቆየ ጥርት ብሎ ተሰማት። ከጀርባዋ ካለው የወላጆቿ መኝታ ቤት መስኮት እየዘለቀ የሚመጣ የእናትዋና የአባቷ ውይይት ነበር።

"ይቺ ልጅ ምነው ጠባይዋ ሁሉ እንዲህ ግራ ሆነብኝ?" ጎርናናው የአባቷ ድምጽ እንደ ነጎድጓድ አስገመገመ።

"የዘመኑ ልጆች ምን መላ አላቸው ብለህ ነው?! እንግዲህማ እድሜዋም እየገፋ፤ እየደረሰች እኮ ነው" ድክም ያለው የእናቷ ድምጽ የዜማ ስልቱን ጠብቆ ተንቆረቆረ።



"እስኪ እንደ ጠባይዋ ያገኙት። መቼስ ንብረቴን የሚሰበስብና በምሳሌዬ የምትከለው ወንድ ልጅ ለመውለድ አይገቡት ገብቼ፣ ወጥቼና ወርጄ እንዳልሆነልኝ ታውቂያለሽ"

"ኧረ እባክህ አርፈህ ተቀመጥ! በማምሻ እድሜህ የፈጣሪን ዐይን በእንጩት አትውጋ። ያለችንን አንድዬ ፍሬ እርሱ እንዲጠብቅልን ሌት ተቀን መለመን እንጂ፤ ... ደግሞ በርሱ ሥራ ገብቶ መቀባጠር ምንድነው?!"

"ይሁና! እስኪ ለሁሉም እንደ አመሏ ያግኙት... እጇን ካልሰጠችን ባዩም መግቢያ መውጫ አሳጥቶኛል" አለ የአባቷ ድምጽ ቅሬታን አዝሎ።

አብነት ልቧ በውስጧ ስትፈስ፣ የደም ሥሮቿ ለክፍልፋይ ሰከንዶች ቀጥ ብለው ሲቆሙ ታወቃት።

"ታዲያ በጊዜ ድረን ፍሬዋን ብናይ አይሻልም? ወይዘሮ ሁሉግርጌሽም ይሄው እግራቸው እስኪቀጥን ይመላለሱብኛል" አሉ እናቷ።

ሁሉግርጌሽ የሚለው ስም ዘወትር ጥቁር የሀዘን ልብስና ጥቁር ሻሽ ለማይለያቸው፣ አጭር ድብልብል ብስል ቀይ ሴትዬ መሰጠቱ አብነትን ይደንቃታል።

ቤታቸው በመጡ ቁጥር የመርፌ ቀዳዳ በሚያካክሉ ትናንሽ ዐይኖቻቸው ከላይ እስከታች እያጠኗት ለእርድ እንደሚቀርብ ሙክት "አሁንማ ደረሰች እኮ፣ ከዚህ በላይ መገርጀፍ ነው። ለሁሉም እኮ ጊዜ አለው... ለውበትና ለልጅነት ጊዜ አለው... ለወግና ለቁም ነገርም ጊዜ አለው። ሁሉንም በጊዜ ማድረግ ይበጃል ወይዘሮ አርያም" ይሏቸዋል እናቷን ያለመታከት።

"እሷ ደግሞ ምን ፍጠሩ ነው የምትለው?!" አለ ቆጣ ያለው የአባቷ ድምጽ። "ባለቤትሽን አግልጂኝ ነው የሚሉት" ፈራ ተባ የሚለውን የእናቷን ድምጽ ስትሰማ አብነት ሽምቅቅ አለች።

"ይሄ የርሶ ጠበቃ እኮ የታናሽ ወንድማቸው ልጅ ነው። እሳቸውም ሰውየውን ሲከቡት ከፈጣሪ ነው የሚያስተካክሉት። የጠባዩን ሽጋነት አውርተው አይጠግቡም። እዚሁ አዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ባለው የጥብቅና ቢሮው ብር በአካፋ ይዝቃል አሉ። የሟች አባቱ ውርስም ቁጥሩ በውል አይታወቅም እያሉ ሲያደርቁኝ ነው የሰነበቱት"

"እኮ ምን ፍጠሩ ነው የምትለው?!"

"አብሩቴን ካላገባሁ ሞቼ እገኛለሁ ብሏል አሉ። መተዋወቂያ ይሁነኝ ብሎ በርሳቸው እጅ የላከላትን የወርቅ አምባር፣ የጆሮ ጉትቻና የአንገት ሀብል አንተ ካልሰማህና ነገሩን ካልቆረጥከው አይሆንም ብዬ መለስኩት። ደግም አላደረኩ?"

አባቷ በምጸት ከጣራ በላይ ሲስቁ ሰማች። "ይሄ ቀጣፊ!... በፊት በር ማንኳኳት እንደማይሆንለት አውቆ በጓሮ በር መሹለኩ ነው?! ምነው አብረን ስንውል አንድ ቀን እንኳን ስሟን አላነሳብኝ? ሾላካ! ለነገሩ ደፋር ነው። አይ መማር ክንቱ! እነስ ፈረንጅ ሀገር ደርሰው በሻምፓኝ ታጥበው ሲመጡ የማስተዋያና የማመዛዘኛ ህሊናቸው ይመክናል ልበል?! እስኪ እኔ ልጄ ወርቅ ቸገራት አላልኩት፣ ወይስ ማን ያሳደጋት መሰለው?!"

"ዘመኑ ነው አሉ እቴ! የትላንትናው አለፈ፣ እንግዲህ ሰው እንደሆነው መሆን፣ ከዘመኑ ጋር መለወጥ እንጂ የወጉን ብቻ ይዞ መንገታገት ምን ይፈይዳል ብለህ ነው?"

"ይሄ 'ዘመኑ ነው' ሚል ፈሊጥ ለስንቱ ወሽካታ ዋቢ እየሆን እንደሚዘልቅ አላውቅም። ሁሉ በጊዜ ሲመካኝ የሰው ልጅ ክብር ረከሰ፣ ሥርዓት ቅጥ አንባሩ ጠፋው።"

"እኔስ ቶሎ ድረናት የልጃችንን ፍሬ ብናይ ይበጃል ባይነኝ ። እንደምታየው በእግዜር እጅ የተያዝኩ በሽተኛ... አንድ ቀን አልጋ፣ አንድ ቀን መሬት ነኝና የልጄን ፍሬ ሳላይ ክፉ እንዳያገኘኝ እፈራለሁ"

"የለም የለም! ምንም ችኮላ አያስፈልግም። ምነው ሁሉም ልጄን እንደ ችግር ቀን እህል ተሻማት?! አንዱ መጥቶ ቪላ ቤት፣ ጥሩ ደመወዝ፣ ጥሩ መኪና አለኝ ይላል። ሌላው ይከተልና በጀርባዬ ላይ ተንጠራርቶ የብር ረብጣ እየቆጠረ ሊያባብለኝ ይከጅላል። ሄሄሄሄሄ... 'ጭብጥ ቆሎ ይዘህ ካሻሮ ተጠጋ' መሆኑ ይገባሻል?!"

"ወይዘሮ ሁሉግርጌሽ እንዳሉት ይሄኛው በሀብቱ ከኛ የሚተናነስ አይደለም" ከአጭር ዝምታ በኋላ "ነገርኩሽኮ! በልጄ ላይ ማንም ጣቱን አያሳርፍም። እኔ የመረጥኩላት ሌላ የህይወት መስመር አላት!"

አብነት ከተቀመጠችበት በረንዳ ቀስ ብላ ተነስታ ወደ መኝታ ክፍኗ በመሄድ በአልጋዋ ላይ ተጋደመች። በዚያች ሰዓት



የምትጨነቅበት፣ የምትሰጋበት ጉዳይ እልክበረም… በየማእዘኑ የሚታያት ሁሉ ጨለማ ነበር። በዚያ ጨለማ ውስጥ ደግሞ ፍጹም ባዶነት!

## ምዕራፍ አምስት

በማግስቱ ፒያሳ ላይ የተሣፈረችበት ታክሲ ቸርችል ጎዳናን ቁልቁል እየተምዘገዘገ ብሄራዊ ቲአትር በር ላይ ሲያወርዳት ነበር ከቁም ቅዥት የነቃችው።

ከጥርብ ድንጋይ ተሠርቶ፣ አደባባዩ ላይ ጉብ በማለት ተሳላፊውን መንገደኛ እየገላመጠ ጫማውን የሚያስጠርግ የሚመስለውን አንበሳ ሽቅብ እያየች ማሰብ ጀመረች። ከፒያሣ እያንደረደረ ያመጣት ወኔዋ ከቲአትር ቤቱ ህንፃ ስትደርስ ተፍረከረከ "ቢንቁኝስ? እንደአልባሌ ሴት ቢቆጥረኝስ?" ራሷን ጠየቀች። መልሳ ደግሞ "አይዞሽ አቢ! ደፋርና ጭስ መውጫ አያጣም... ያበጠው ይፈንዳ እንጂ ከዚህ በላይስ ታፍነሽ መኖር አትችይም!" በማለት ልቧን አደነደነች።

እግሮቿ በጥርጣሬና በዝግታ ይራመዳሉ። "ወዴት ነው እህት?" ሰፊው የመስታወት በር ላይ የቆመ የደንብ ልብስ የለበሰ ሰው አስቆማት። የቁመቱ ማጠርና የሰውነቱ መቀጨጭ ህፃን ልጅ አስመስሎታል። በትርፍ ጊዜው ቲያትር ይሠራ ይሆን ስትል አሰበችና ፈገግ ብላ "እባክዎ ቻርሊን ፈልጌ ነበር" አለችው።

በጣቱ ወደ ደረጃዎቹ እያመለከታት "ሻይ ቤት ወይም ስድስት ቁጥር ታገኚዋለሽ" አለና መተላለፊያውን ለቀቀላት።

ወደ ደረጃው ስታመራ በስተግራ በኩል ከሻይ ቤቱ በረንዳ ላይ የተደረደሩት አርቲስቶች በዐይናቸው ጦር ቁልቁል ይወጓት ጀመር። "እምላኬ ሆይ! ግራ ጋዴም ከመካከላቸው እንዳትኖር እርዳኝ" ስትል አጉተመተመች። ቀና ብላ አላየቻቸውም። አንዱ ግን በአድናቆት ሲያፏጭ ሠምታለች።

ደረጃውን ወጥታ ስትጨርስ በረንዳው ላይ መጀመሪያ ያገኘቻትን አርቲስት "እባክሽ የኔ እህት፣ ቁጥር ስድስት ወዴት ነው?" ስትል ጠየቀቻት። አርቲስቷ ባንድ እጇ ሲጋራ፣ በሌላው ደግሞ የቡና ሲኒ ይዛለች። ከቡናዋ ጎንጨት፣ ከሲጋራው ማግ ማግ አድርጋ ጭሱን በአፍና በአፍንጫዋ ካትጎለጎለች በኋላ "በዚህ ሄደሽ ትልቁን በር አንኳኩተሽ ግቢ" አለቻት ሲጋራ በያዘው ጣቷ በስተግራ ወደሚገኘው መተላለፊያ እያመለከተቻት።



በጥንቃቄ እየተራመደች ደብዘዝ ያለ ብርሃን ከሚታይበት የቁጥር ስድስት በር ላይ ቆመች። ጨለማው ያስፈራል፣ ቢሮው ውስጥ ይኖራል ብላ የገመተችው ቻርሊም አስፈራት። በርቀት የሚሳመጁት አርቲስቶች ዐይንም እንዲሁ። በዚያች ወሳኝ ሰከንድ በሩን ለማንኳኳት እጆቿ ሊታዘዟት አልቻሉም። ወኔዋ እንደከዳት ባለችበት ቆመች።

ለጎሊያድ አስከሬን የተዘጋጀ የሬሳ ሣጥን በሚመስለው ቁጥር ስድስት ውስጥ ቻርሊ ጠረጴዛው ላይ በዘረጋው የስቴይን መጽሐፍ "ዘ ዳርክ ኮሜዲ" ላይ አቀርቅሯል። ይሁን እንጂ አንዲትም ሐረግ አላነበበም። መጽሀፉ ላይ እንዳፈጠጠ ያስባል።

አሁን አሁን ስለሙያው መጨነቅ ትቷል። እሱ አያድግ፣ ሙያው አያድግ፣ እሱም ሙያውም አድሮ ቃሪያ እየሆኑ እንደ ግመል ሽንት ከዓመት ዓመት ወደ ኋላ የሚጓዙ እየመሰለው በመምጣቱም በሙያው ላይ የቆየባቸውን ጊዜያት "ከንቱ ዓመታት!" ይላቸዋል።

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ አጥብቆ የሚያሰላስለው፣ የሚያወጣና የሚያወርደውም መረን የተለቀቁ ሁለት ልጆቹን አሰባስቦ ኋይት ሀውስን እንዴት ቤተሰባዊ ፍቅር የተመላባት፣ እንደ ሰው ቤት የሚሳቅባት፣ ጭስ የሚጨስባት ህይወት ያላት ቤት ማድረግ እንደሚችል ነው።

ይሁንና "አከብረዋለሁ፣ እወደዋለሁ" ይለው ለነበረው ሙያው ባሪያ ሆኖ እምነቱን ለመሰበክ የህይወቱን ተልእኮ ከግብ ለማድረስ ቀን ከሌት ሲሮጥ፤ በየከተማው በየገጠሩ ሲንከራተት፤ ወዴት ወደቃችሁ ያላላቸውን ልጆቹን ውልግድግ ባህርይ ለማቃናት ጊዜ እንደቀደመው አውቋል።

የመጀመሪያ ልጁ ሀረገወይን ገና የስምንተኛ ክፍል ተማሪ ሣለች ነበር ትምህርቷን አቋርጣ አባቱ የማይታወቅ ልጅ እናት የሆነችው። ቻርሊ አዘነላት እንጂ አላዘነባትም። ለብሳቢና ተቆጭ የሌላት ልጃገረድ ከዚህም የከፋ ጉድ ይዛ ወደ ቤቷ አለመምጣቷ ብርቱ በመሆኗ ነው። ግራም ነፈሰ ቀኝ ልጁ አሁን የት እንዳለ ቻርሊ አያውቅም። ምናልባትም ለእናቷ ለውቢት ሰጥታው ይሆናል የሚል ግምት ቢኖረውም አልጠየቃትም። ሀረገወይን ማታ ማታ እየተማረች አሥራ አንደኛ ክፍልን ካጠናቀቀች በኋላ የመንገድ ዳር ቃፊር /ስትሪት ገርል/ ሆናለች። እነሆ በመረጠችው ህይወት ጎዳናም ኑሮዋን ትገፋለች።

የቻርሊ የወር ደመወዝ ሀረገወይን በየቀኑ የምትቀያይራቸውን ጫማዎች ሊገዛ አይችልም። በበርሳዋ የታጨቀው የሽቱ፣ የቅባትና የሊፒስቲክና የጥፍር ቀለም ዋጋ የት የለሌ ነው። ሀረገወይን እንግዲህ በዚህ ዓይነት አስነዋሪ ህይወት ውስጥ ነው የራሷን ኑሮ ፈጥራ የምትኖረው። ቻርሊ ይህችን የበኩር ልጁን በርሱ ደሞዝ እንዴት ሊያስተዳድራት ይቻለዋል? የተወላገደ ባህሪይዋን ገርቶ እንዴት የርሱን ኑሮ እንድትኖር ማድረግ ይችላል? ይህን ሲያስብ ተስፋው ሁሉ ይጨልምበታል።

ሌላው የቻርሊ ራስ ምታት ሊትል ቻርሊ ነው። አባቱ በቲያትር እንደተለከፈው ሁሉ ሊትል ቻርሊም የዚሁ ጥበብ አምላኪ ከመሆን አላመለጠም።

ገና ተማሪ ሆኖ እንኳን ትምህርቱ ላይ ማተኮሩን ትቶ፣ ቻርሊ ወደ ቤት ከሚወስዳቸው የተውኔት ጥራዞች ላይ አባቱ የሚጫወታቸውን ገፀ-ባህሪያት ቃለ-ተውኔቶች እየተደበቀ ያጠና ነበር። ቻርሊ ማታ እያንዳንዱን ቃል እንዴት እንደሚጫወታት እንዴት እንደሚንቀሳቀስም ልቅም አድርጎ ያይና በጭንቅላቱ ቀርጾት ይቆያል።

አባቱ ጥናቱን ጨርሶ እሮጌው ሶፋ ላይ አረፍ በማለት ሲጋራውን ለኩሶ ዘና ሲል፣ ሊትል ቻርሊ ያጠናውንና ከአባቱ ያየውን መልሶ ያሳየዋል። ቻርሊ ይደነግጣል፣ ይበሳጫል። "ሰይጣን!" ይለዋል ጥርሶቹን እንደነከሰ። ብዙ ጊዜ ተቆጥቶታል፣ ገርፎታል። አልሆንለትም። ስለዚህም በምክር ሊለውጠው ሞከረ።

ጓይት ሃውስ በር ላይ አስቀምጦ ፀጉሩን እየደባበሰና ጉንጮቹን እየነተለ "ሊትል፣ ሞኝ አትሁን። 'ሞኝ ብቻ ነው ከራሱ ውድቀት የሚማር።' ስለምን ብልህ ልጅ አትሆንም?! ከኔ ከአባትህ ኑሮ መማር ስትችል፣ እኔ ከገባሁበት ሲኦል ገብተህ ለመንጨርጨር ለምን ትጣደፋለህ? እናትህ ለምን ጥላኝ እንደሄደች፣ አንተም ለምን የእናትህን ፍቅር ሳታይ እንዳደግክ ታውቃለህ? ድህ በመሆኔ ነው። እኔ እውቀት እንጂ፣ ሙያ እንጂ ገንዘብ የለኝም። ይሄ ሙያ ደግሞ በፍቅር ያጀልህና ሳታውቀው ባሪያው አድርጎ ይገዛሃል። በርግጥ ዝነኛ ያደርግሃል፣ ያስከብርሃልም። ኪስህ ግን ባዶውን እንደሆነ ይኖራል። እናትህ ትወደኝ ነበር። ገንዘብ ስለሌለኝ ግን ጥላኝ ሄደች። አልፈርድባትም፣ በምን ሃጢያቷ የኔን ቅጣት ትሸከማለች። ለምን ብላ ትሰቃይ?! ስለዚህ ሄደች። በሄደችበት ይቅናት። እናም ሊትል ፣ ከኔ ውድቀት ተማር። ዓለም እንዴት ሰፊ ነች መሰለህ። ስንትና ስንት ሙያ አላት መሰለህ?! አንዱን ምረጥ፣ ማን ያውቃል ነገ ታዋቂ



ሀኪም፣ ሃብዝ ነጋዴ፣ ታዋቂ መሀንዲስ ወይ ማን ያውቃል ታላቅ የጦር ጄኔራል ትሆን ይሆናል" በማለት እያስተዛዘነ ይማፀነዋል።

ይሄ ሁሉ ጥረቱ ግን በድንጋይ ላይ ውሃ እንደ ማፍሰስ ነበረ። ቻርሊ ዞር ሲል ልጅየው የቁምጣ ሱሪውን ማንገቻዎች እያጠባበቀ ይነሳና አንድ የተውኔት ጥራዝ መንትፎ ሥርቻ ውስጥ ይወሸቃል።

ሊትል አሁን የአሥራ ሁለተኛ ክፍል ትምህርቱን አጠናቆ ያለ ሥራ ተቀምጧል። እንደ አባቱ ታዋቂ አርቲስት የመሆን ፍላጎቱ ስላልበረደለትም ከቲያትር ቤቶች አካባቢ አይጠፋም። በተለይ አባቱ በሚሠራበት ቲያትር ቤት ብዙ ጓደኞችን ያፈራ በመሆኑም ጠፍቶ አያውቅም። አባቱን በሚያዩበት ዐይን የሚያዩት የቻርሊ የሥራ ባልደረቦችም ሊትልን ይወዱታል። አብዛኞቹ ዓላማውን ስለሚያውቁ ያበረታቱታል። ቻርሊ ግን የልጁን ቲያትር ቤቶች አካባቢ ማውደልደል አልወደደለትም። በአማተር የቲያትር ክበብ ውስጥ ገብቶ በማድረግ ላይ ያለውን እንቅስቃሴም አይደግፍም።

አንድ ጊዜ ቻርሊ በሚኖርበት አካባቢ የተቋቋመ የአማተር የቲያትር ክበብ፣ ቻርሊን ለወጣት አባሎች የሙያ ልምድ እንዲያካፍል ይጋብዘዋል። ቻርሊም ቀጠሮውን አክብሮ በተባለው ጊዜ ይደርሳል። የክበቡ ሊቀመንበርም አጀንዳውን ብብቱ ሥር እንደሸጎጠ ሞቅ ያለ አቀባበል አድርጎለት ወደ አዳራሹ ይዞት ገባ። በመምጣቱ የተደሰቱ ወጣቶች እየተሻሙ ሰላምታ አቀረቡለት። ሊቀመንበሩ ስለ ክበቡ አላማና ስላጋጠሙት ችግሮች አጠር ያለ ንግግር ካደረገ በኋላ ወጣቶቹ ያዘጋጁቸውን ሁለት አጫጭር ተውኔቶች እንዲመለከት ጋበዘው።

ቻርሊ ከተውኔቶቹ ይዘት ይልቅ በወጣቶቹ የአተዋወን ብስለት ከመጠን በላይ ተደነቀ። ከእድሜያቸው ሊጋነት በስተቀር አማተር መሆናቸው ያጠራጥራል። ስሜቱን እንዲያውቁበት ግን አልፈለገም። አፏራውን ሳይጠየፉ፣ ለልብሳቸውና ለሰውነታቸው ሳይጨነቁ መድረኩ ላይ ሲወድቁና ሲነሱ ሲያይ ከልቡ አዘነ።

ወጣቶቹ ትርኢታቸውን ካጠናቀቁ በኋላም የርሱን ንግግር ለማዳመጥ በታ በታቸውን ይዘው ተቀመጡ። ቻርሊ ፊት ለፊቱ ባለው ጠረጴዛ ላይ ክርኖቹን ተመርኩዞና በመዳፎቹ ጉንጮቹን ደግፎ አንድ በአንድ አስተዋላቸው። ከዚያም "ማነው እነዚህን ተውኔቶች ያዘጋጃቸው?" ሲል ጠየቀ። ወጣቶቹ እርስ በርሳቸው እየተያዩ ዝም አሉ። ይኸኔ የሊትል ቻርሊ ሥራ መሆኑ ገባውና በንዴት ጥርሶቹን ቅርጭም አድርጎ አፋጫቸው። ምስጋናን ናፍቀው የሚንከራተቱ የወጣቶቹ ዐይኖች አሳዘኑት። እናም ከቤቱ ሲወጣ ሊያደርገው

ያሰበውን ንግግር ሊለውጥ አሰበ። ከውሣኔው በፊት ግን ጦርሱ እድሜ ሳለ ያጋጠመው ትውስ ብሎት በሃሳብ ፈረስ የኋሊት ሸመጠጠ።

የተዋናይነት ሥራውን የጀመረ ሰሞን ነው። እርሱና ወጣት ጓደኞቹ የተሰጣቸውን ቃለ ተውኔት ቀን ተሌት አጥንተው፣ በቀከከር የሚሠሩበት ጊዜ ነበር። አንድ ቀን አንጋፋው ዳይሬክተር በሰዓቱ ባለመገኘታቸው ቻርሊና ጓደኞቹ ለልምምድ የተሰጠቻቸው የመድረክ ሰዓት እንዳትባክን የራሳቸውን ጊዚያዊ ዳይሬክተር ሾመው በአናው አዳራሽ መድረክ ላይ ይጫጫሃሉ፣ ይወድቃሉ ይነሳሉ። ልብሳቸው አቧራ ጠጥቷል፣ ጠጉራቸውና የዐይናቸው ሽፋል ሳይቀር አቧራ ለብሶ እህል አስፈጭዎች መስለዋል።

ይህ ሁሉ ሲሆን የቲያትሩ አዘጋጅ አዳራሹ ጥግ ጨለማ ውስጥ ቆመው ሁኔታቸውን ያስተውሉ ኖሮ የወጣቶቹን መዳከም አይተው እረፍት እንዲያደርጉ በማዘዝ መድረኩ ላይ ብቻቸውን መንጎራደድ ይጀምራሉ።

ቻርሊ ያልገባውን ሊጠይቃቸው ወደ መድረኩ ወጣና ከፊት ለፊታቸው ቆሞ ሲንተባተብ ዐይኖቻቸውን ፍጥጥ አድርገው ይመለከቱት ነበር። እነኛ የፈጠጡ ዐይኖች ግን ቻርሊን አይመለከቱም፣ ጆሮዎቻቸውም ቻርሊን አያዳምጡም። ይህን ያወቀው ዘግይቶ ነው። ዐይኖቻቸው የዛሬውን ሳይሆን የነገውን ቻርሊን ህይወት ለመቃኘት የጊዜን ኬላ ሰብረው ነጉደዋል። ጆሮዎቻቸውም የዛሬውን ሳይሆን የነገውን ቻርሊ ብሶት ለማዳመጥ ቆመዋል። ብዙም ሳይቆዩ አፍጥጠው ከሚያዩት ትናንሽ ዐይኖቻቸው የእንባ ዘለላዎች ዱብ... ዱብ... ሲሉ ተመለከተ። ያ እንባ ስለሱ የወደፊት ሕይወት የፈሰሰ እንባ መሆኑን ያን ጊዜ አልተረዳውም። "ምነው ጋሼ?" አላቸው በድንጋጤ ዐይኖቹን በልጥጦ። ሁለት እጃቸውን ትከሻዎቹ ላይ አሳረፉና ሳግ ከሚያፍነው ልሣናቸው ጋር እየታገሉ "በርቱ!" አሉት። አዕምሯቸውን የሳቱ መሰለውና እጃቸውን ከትከሻው ላይ መንጭቆ እየሮጠ ከመድረኩ ወረደ።

ወጣቶቹ ፊት ተቀምጦ ይህን ሲያስብ በርሱም ዐይኖች ላይ የእንባ ዘለላዎች ተንጠለጠሉ። ወጣቶቹ በመገረም እርስ በርሳቸው ይተያያሉ። ከተቀመጠበት ድንገት አፈፍ ብሎ ተነሳና ጉሮሮውን ሲጠራርግ የሚያደርገውን ረዥም ንግግር ለማዳመጥ ሁሉም በየመቀመጫቸው ተስተካከሉ።

"ወንድሞቼና እህቶቼ፣ በዚህች ሰዓት ላስተላልፍላችሁ የምፈልገው መልእክት አንድ ብቻ ነው። ተማሩ! ሰው መሆን



[illegible]
ከፈለጋችሁ ተምራችሁ በሙያው ወረቀት ያዙ፣ በርቱ!" አላቸውና የረጠቡትን ዐይኖቹን እያደራረቀ ከአዳራሹ ወጥቶ ሄደ። ወጣቶቹ ጤንነቱን ተጠራጥረው እርስ በርሳቸው ይተያዩ ጀመር። ማታውን ቻርሊ ከልጁ ጋር ቡጢ ቀረሽ ውዝግብ አካሄደ። ዘግይቶ እንደሰማውም ያ የአማተር ቲያትር ክበብ ወዲያውኑ ፈረሰ። የክበቡ ሊቀመንበርም ቻርሊን አሁን ድረስ መንገድ ላይ ሲያየው እየገላመጠው ያልፋል።

ስለዚህም ቻርሊ ልጁን እንደምን የለከፈውን የጥበብ አጋንንት አስለቅቆና ከደሙ የተዋሃደውን አሻፈረኝ ባይነት አርቆ ሰው ሊያደርገው እንደሚችል ገና ሲያስብ የተስፋው ብርሃን ይጨልማል። እናም ሁልጊዜም ጭንቅላቱ እስኪፈነዳ ድረስ ችግሩን ያብጠለጥላል። ከራሱ ጋር ይጨቃጨቃል። አውጥቶና አውርዶ የደረሰበት ድምዳሜም ከዚህ ከማይወጣው ችግር ውስጥ የተዘፈቀው በሙያው ምክንያት መሆኑን ነው። ከሃያ ሁለት ዓመት በፊት ውቢት ልትረዳው የቻለችውን እውነት ለመቀበል ይህን ያህል ጊዜ በመውሰዱም ራሱን እንደ ድንጋይ ራስ መቁጠር ጀምሯል።

ዘወትር ከራሱ ጋር ሲወያይም "ልጆቼን ሰው ለማድረግ በቅድሚያ እኔ ሰው ሆኜ መገኘት መቻል አለብኝ። ሌላውን ታግሎ ከመጣል ራስን ማሸነፍ ይከብዳል። እኔም ራሴን ማሸነፍ አለብኝ፣ ሥራዬን መተው አለብኝ!" እያለ ይምላል። በመሃላው የፀናበትና ራሱን ያሸነፈበት ጊዜ ግን አልነበረም። ትዳሩን ያፈረሰበትን፣ ቤቱን የበተነበትን ሙያ እንዲህ እንደዋዛ እንዴት ሊሠናበተው ይችላል?!

ያስባል። ቢሮው ውስጥ ከተቀመጠበት ወንበር ላይ ሆኖ የዘረጋው መጽሀፍ ላይ ዐይኖቹን አፍጥጦ ማሰቡን ቀጥሏል። በሩ የተንኳኳ መሰለውና "ይግቡ?!" አለ በጥርጣሬ።

በሩ ተከፈተ። ዐይኖቹን ግን ማመን አልቻለም። የውቢት መንፈስ በእብነት ተመስሎ "አሁንም መድረክ ከምትሰው የዶሮ መስፈሪያ ቆጥ ላይ ነህ?!" እያለ ሊያፈዝበት የመጣ እስኪመስለው ድረስ ዐይኖቹን አፍጥጦ ተመለከታት። "መንፈሱ" ፈገግ አለለት... ወደ እርሱም መራመድ ጀመረ... ቻርሊ ከመቀመጫው ፈጥኖ ተነሳ። "እንደምን አደርክ!" ልብን ከሚሰንጥቅ ፈገግታ ጋር "መንፈሱ" ለሠላምታ እጁን ዘረጋለት... ቻርሊ ደመ ነፍሱን የሚንቀጠቀጡ እጆቹን ዘረጋ። ተጨባበጡ። ሞቃት ደም "በመንፈሱ" እጆች ውስጥ ሲርመሰመስ ታወቀው። የጨበጠው አካል መንፈስ ሳይሆን ሥጋ ነው። የሞት ሞቱን ፈገግ ለማለት እየሞከረ "ጤና ይስጥልኝ፣ ... እንዴት ሰነበትሽ ወዳጄ?!" አላት። በፈገግታው ውስጥ ግን ጥርጣሬና ስጋት ነግሶበታል። የዐይኖቹን መሎኪዎች ኳጣበ ትኩር ብሎ ተመለከታት።

ጨምቆ የያዘው የእጇ መዳፍ እንደጋለ ብረት ስላቃጠለው በፍጥነት ለቆት "ተቀመጭ እመቤት.." አላት ከልቡ ያልመነጨ የድለላ ፈገግታ ተላብሶ በጣቱ ወንበር እያመለከታት። ፊት ለፊቱ ተቀመጠች ፀጥታም ሆነ።

በዚያ ፀጥታ ውስጥ አንዳቸው የአንዳቸውን ስሜት ለማወቅ፣ አንዳቸው በአንዳቸው ዐይን ውስጥ ጠልቀው ይበራበሩ ጀመር። ሲጋት፣ ጥርጣሬ፣ ፍርሃት በሁለቱም ዐይኖች ውስጥ ተመስገው በየልቦቻቸው የሚነደውን የፍቅር እሳት ለማዳፈን ቃተቱ። ቅጭም ካለው ገጽታቸው በደመነፍስ በመካከላቸው ያለውን ረዥም ርቀት እየለኩና የተጋረጡባቸውን አንድ ሺህ መሰናክሎች እየቆጠሩ ሊዘልቁት የማይችሉ መሆናቸውን ተረድተው ተስፋ የቆረጡ ይመስላሉ። ያለ እንደበት ቀላጤነት፣ ያለ ቃላት አጨብጫቢነት ጭንቀታቸውን ተወያዩ።

ብዙ ብዙ ዘግይቶ የእጇን ጣቶች እያንቋቋ "ያን እለት በደህና ገባሽ?!" አላት ። ፈገግ ብላ "እንደጠየቅከኝ" አለችውና አንገቷን አቀረቀረች። ከንፈሯ ላይ የሚጫወተውን ፈገግታ ሲመለከትና እንደ ሩቅ ምስራቅ ለስላሳ ሙዚቃ በጆሮ ገብቶ መቅኒ ውስጥ የሚቋጠረውን ለስላሳ ድምጿን ሲሰማ፣ ከውቢት ጋር የተፋጠጠ መሰለውና እንደገና ደግሞ መረበሽ ጀመረ። ስለ ውቢት ያለው ጥሩ ትዝታ ከመጨረሻዎቹ መጥፎ ትዝታዎች ጋር ተዘበራርቀው ታወሱት። ሊያሳያት ይጥር የነበረው የውሸት ፈገግታም ጭል... ጭል... ጭል ብላ ውድም እንደምትል የሻማ እሳቂ ከገጽታው ላይ እልም አለች።

ቀና ብላ ስታየው ፈገግታው ፊቱ ላይ የለም። ግንባሩን ቅጭም አድርጎ ያስተውላታል። ፀአዳ የተለወጠ ስሜቱን ስትመለከት ሣራ ጋዴም ታወሰቻትና ፈገግ አለች።

"ምን ያስቅሻል?!" አላት የተቋጠረ ግንባሩን ፈትቶ እንደገና ፈገግ ለማለት እየሞከረ።

"ምን እያሰብክ ነው?" አለችው በአድራጎቷ እንደ ማፈር እያለች።

"አንቺን ካገኘሁበት ጊዜ ጀምሮ የየእለቱ ዋናው ተግባሬ ማሰብ ብቻ መሆኑን ልደብቅሽ አልፈልግም። ካንቺ ሁኔታ ጋር የተያያዙ ብዙ ትዝታዎች አሉኝ። የሚያስጨንቀኝ ነገር ግን ማሰቤ ሳይሆን በህሊናዬ እንደ ጅረት ከሚፈሰው የሀሳብ ጎርፍ በእፍኝ ጨልፌ ስለማስበው ነገር ምንነት ለመገንዘብ አለመቻሌ ነው" አላት የውሸት ፈግግታው ጠፍቶ ትክዝ እንዳለ።



አብነት ግንባሯን ቅጭም አድርጋ በጥርጣሬ ዐይን ትመለከተው ጀመር። የተናገረውን በጆሮዋ እንጂ በልቧ አላዳመጠችውም። በመጨረሻ ግን "የፍቅር አባዜ አንተንም አንበርክኮህ ይሆን?" የሚል ጥያቄ በአዕምሮዋ አቃጨለ።

"ሣራ ጋዴም ስለ አንቺ ብዙ አጫውታኛለች። ስላንቺ በሰማሁ ቁጥር እጨነቃለሁ" አላት ፊቱ ላይ ያንጃበበውን ጭንቀት ለመደበቅ ሳይሞክር። አብነት የቻርሊ አንደበት ሊገልጸው ከቻለው በላይ ስጋቱን ከፊቱ ላይ አንብባለች።

በልቧ ያቺ እብድኮ ሚስጥሬን ሁሉ ዘክዝካለት ይሆናል ብላ ሰላሰበች። "ሣራ ስለኔ ምን ነገረችህ?" ስትል ጠየቀችው።

ትክሻውን ሰበቀና "እሷስ ሁሉን ነግራኛለች" በማለት መርዶውን በአደባባይ አረዳት።

"አንተን ታዲያ ይሄን ያህል የሚያስጨንቅህ ምንድነው?" ለረዥም ጊዜ በዝምታ ተውጠ ከቆየ ብኋላ "አብነት፣ ልናልፈው የማንችለው በመካከላችን የተጋረጠ ትልቅ ተራራ ይታይሻል?... በግልጽ ለመናገር የሀብታም ልጅ ነሽ!" አላት።

"የቤተሰቦቼ ሀብት በሁለታችን መካከል ጣልቃ የሚገባበት መንገድ እንደሌለ ላረጋግጥልህ እወዳለሁ" አለችው በእርግጠኝነት።

"እየሽ አብነት፣ የንዋይ ፈተና ከፈተናዎች ሁሉ የላቀና በዋዛ የማይታለፍ ነው። በሁለታችን መካከል ያለውን የአስተዳደግና የአኗኗር ልዩነት ስገምተው..."

የጀመረውን ሳይጨርስ አብነት አቋረጠችው። "እባክህን ይህንን ሀሳብ አትጨርሰው... ስለምትለው ሁሉ የማውቀው አንዳች ነገር የለም። ስለ አንተ አንድ ነገር ብቻ ማለት እሻለሁ።" ቻርሊ ደነገጠ። አብነት ቃሉን ከአፏ ለማውጣት ስትታገል ቆየችና "እወድሃለሁ!" አለችው በድፍረት።

ይህንን በማለቷ ሀፍረት አልተሰማትም። በዚያ ሰሞን ራሷን መግዛት እንደተሳናት፣ በባህሪይዋ ፍጹም እንደተለወጠችና ራሷን እንዳልነበረች ታውቃለች።

"ለምን እውነትን እንፈራዋለን አብነት?!"

"እኔ የማውቀው አንድ እውነት ነው ቻርሊ።" ቃሉን እንድደግመው ትፈልጋለህ? እወድሃለሁ!" ይህን ቃሏን በቴፕሪከርደር ቀርጾ በረጋ መንፈስ እንደገና እንድታዳምጠው የሚያደርጋት ቢኖር "አብጂ ነበር" እንደምትል እርግጥ ነው።

ቻርሊ አዘላት። "የወጣትነት መንፈስ የነገን ቀን ዛሬ ላይ ቆሞ ማየት አያስችልም። በስሜቱ እየተገፋ የፊት የፊቱን፣ የእለቱን እንጂ ዘግይቶ ሊደርስ የሚችለውን የችግር ቁልል ማየት የለምና። ያፈቀረ ወጣት የፈለገውን እስኪያገኝ፣ የተመኘውን እጁ እስኪያስገባ ሰማይ መቧጠጡ አይታበልም። ያ ግለት በርዶ አፍላ ጉልበቱ ተንጠፍጥፎ ሲያልቅ ግን ዐይኑን ገልጦ ማስተዋል ይጀምራል። ያኔ ተስፋ ቆርጦ የሌላውንም ተስፋ ያጨልማል- ልክ እንደ ውቢት!" እያለ ሲያስብ ቆይቶ በመጨረሻ "አብነትI ስለ ልዩነታችን ሳነሳልሽ ምን ለማለት እንደፈለግሁ ገብቶሻል? ከትኩቶ ያሳደገሽን ስርዓት የምጠላው መሆኑን እንድታውቂው ነው! በሚይዴይ ሰልፍ ላይ 'የትግላችን አንድ አካል ነሽ' ብዬሽ እንደነበር ታስታውሻለሽ? ዛሬ ስለአንቺ ከነገረችኝ በኋላ ግን መሳሳቴን ተረዳሁት። የምጠላው ሥርዓት አካል ነሽ! ፍቅር ደግሞ ከስጋዊ ግንኙነት በላይ የመንፈስና የዓላማ አንድነትን ግድ እንደሚል ይሰማኛል..."

አብነት ልትቆጣጠረው ያልቻለችው አንድ የእልህ ስሜት ደረቷ ላይ ሲተናነቃት ተሰማት። "እና?" አለችው እየተቁነጠነጠች።

"እና ይህን እንዴት እንደምናስታርቀው አላውቅም" አላትI በአነጋገሩ ጠንከር እንዳለባት ገምቶ ለመለሳለስ እየሞከረ።

"ግን አንድ ነገር ልንገርህ?!" አለች አብነት እሳት መትፋት በጀመሩት ዐይኖቿ እየለበለበችው ። ቻርሊ ሁኔታዋ ስላላማረው መቀመጫው ላይ እንዳለ ወደ ኋላው አፈገፈገ።

"እንደሚገባኝ ልዩነቶቻችን አንተ የጠቀስካቸው ብቻ አይደሉም። አንድ ሺ ልዩነቶች፣ አንድ ሺ መሰናክሎች፣ አንዷ ሺ ችግሮች እንደሚገጥሙን መገመት አላቃተኝም። ይሁን እንጂ በኔ እምነት ፍቅር ተራራ የሚያክለውን መሰናክል የሚያሻግር ጉልበት፣ የውቅያኖስ ስፋት ያህል የተዘረጋውን ልዩነት የሚያጠብ ምትሃት፣ ታላቅ የተባለውን ችግር የጉድፍ ያህል የሚያሰንቅ ትዕቢት፣ የማይቻለውን ሁሉ የሚያስችል የነፍስ ኃይል ነው" አለችወ ከሚተናነቃት እልህ ጋር እየታገለች።



ቻርሊ ከደረት ኪሱ ሲጋራ አውጥና ክብሪት ጭሮ ከለኮሰ በኋላ በረዥሙ ሳበው። አብነት የክብሪቱን ጭስ ሽታ ለመከላከል እጇን አራገበች።

"በንድፈ ሃሳብ ደረጃ የምትይው ሁሉ እውነት ነው" አላት ሰውነቱን ዘና አድርጎ።

"እንዲያ ከሆነ ታዲያ ወደፊት ስለሚሆነው ዛሬ የሚያስጨንቅህ ምንድነው? ባንድ ነገር እርግጠኛ ነኝ... ከነቢያት ልጆች አንዱን አይደለህምና ነገ በፈተናው ማን እንደሚደክም ልታውቅ አትችልም" አለችው።

"ልክ ነሽ..." አለ ራሱን በመነቅነቅ ። ውሸቱን ነበር። ህይወት ብዙ አስተምራዋለች። ከነብያት ልጆች እንደ አንዱም አድርጋዋለች። በፍቅር ፈተናም ማን እንደሚወድቅና ማን እንደሚያልፍ በትክክል መገመት ይችላል።

"አንድ ነገር ደግሞ ልለምንህ! ውደደኝ ብዬ አልለምንህም። የፍቅር ጉልበቱ ከሰው ሰው ይጠናልና ... የልቤ ስቃይ አንተን አልፎ ኢየምህም ይሆናል። ውደደኝ ብዬ አልልህም። እንድወድህ ብቻ ተወኝ!" አለችው በሚንቀጠቀጥ ድምጿ። አፏ ይህን ቢናገርም ቅስሟ ግን በውስጧ እንደ ሸክላ ሲንኮታኮት፣ የሴትነት ክብሯ እንደ እንቧይ ካብ ሲናድ ይታወቃታል። ሰውነቷ መንቀጥቀጥ፣ ፀጉሯ መቆም ሲጀምርም ከተቀመጠችበት ተፈናጥራ ተነሳችና ወደ በሩ ሮጠች።

ባለ ኃይሏ ሁሉ በሩን ከፍታ እየሮጠች የህንፃውን ደረጃ መውረድ ጀመረች። ሻይ ቤት በረንዳው ላይ የተደረደሩት አርቲስቶች እንደጉድ ይመለከቷታል። ግድ አልሰጣትም። በሩ ላይ የተጋረጠውን አጥሩን ዘበኛ ገፍትራ እየተንደረደረች አስፋልቱን ተሻገረች።

ላየን ባር ትይዩ ባለው የአስፋልት ጠርዝ ላይ ታክሲ ስትጠብቅ ነበር ቻርሊ የደረሰባት። ክንዷን ያዝ ሲያደርጋት "ከኔ የምትፈልገው ምንድነው?!" ስትል ጮኸችበት።

ቻርሊ የሚናገረው ጠፍቶት እየተንተባተበ "አብነት ምን እያደረግሽ እንደሆነ ታውቂያለሽ?" ሲል ጠየቃት።

"እምን አውቃለሁ። ፍቅርን ከረገጠ፣ ማንነቱን ሊረዳልኝ ካልቻለ ሀብና ቢስ ሰው እየሸሸሁ ነው። አውሬ!" አለችው፤ ለትሮጥ በንፋስ የተበታተነውን ረዥም ፀጉሯን እያስተካከለች።

ቻርሊ ተገርሞ "አብነት፤ እስኪ የምትናገሪውን ረጋ ብለሽ አስተውይ" አላት የልመና ዜማ ባለው ድምፀት።

"ውስጤን ገልጬ ባሳይህ፣ መውደድ እንዳሸነፈኝ ብነግርህ እንደ መንገድ ዳር አልባሌ ሴት ቆጠርከኝ..." የጀመረችውን ለመጨረስ አልቻለችም። ከንዴን መንጭቃ በማስለቀቅ እየሮጠች የቆመ ታክሲ ውስጥ ገባች። ቻርሊ አፉን በጁ ደፍና በመገረም ያስተውላታል። ምን ማድረግ እንደሚችል በውል አላወቀም።

ታክሲው ውስጥ አብነት ጭላቅላቷን ጭኖቿ ላይ ደፍታ ፀጉሯን እየነጨች ማልቀስ ጀመረች። በሁኔታዋ የተገረመው ታክሲ ነጂ "ምነው እመቤት?" አላት ጎርነን ባለ ድምጽ።

"እይመለከትህምና ዝጋ!" ስትል ጮኸችበት።

"መርሃባ! ባንቺው መጀን፤ እዘጋለሁ" አላት በትህትና። ቀና ብላ ስታየው ራሱን የተላጨ፣ አንገቱ ሙሉ ደረተ ሰፊ ወጠምሻ ነው። ቡጢ ቡጢ የሚያካክሉ የቀሉ ዓይኖቹን ማየት አስፈርቷት ጎንበስ አለች።

ከቀትር በኋላ አብነት ከህንፃው ላይ ሆና ቁልቁል መንገዱን ስትቃኝ ሣራ ጋዴም ወደ ህንፃው ስትገባ አየች። ልትረዳው ባልቻለችው ምክንያት ግን ሣራን ማነጋገርም ሆነ ማየት አልፈቀደችም። ስለቻርሊ እንዳትጠይቃት ሰግታ አሊያም የሣራ ማስጠንቀቂያ ስለሰለቻት ይሆናል።

የቢሮዋ በር ሲንኳኳ "እባክህ አምላኬ እፉን ያዝልኝ" ስትል አጉተመተመች። ሣራ ገና በሩን ከመክፈቷ ሳቋን ለቀቀችው። አብነት ደነገጠች።

"እሺ፤ ጉደኛይት። ለካስ እንዲህ አይነቷ ጀግና ኖረሻልና" ብላም መልስ ሳትጠብቅ ሣመቻት።

"ቁጭ በይ፣ ሣራ"

"ቅድምኮ ከቻርሊ ጋር ሌባና ፖሊስ እንደሚጫወቱ ህፃናት ስትባረሩ አይቻችኋለሁ"

"ቁጭ በይ፣ ሣራ።"



"ቂቂቂቂ... ቂቂቂቂ እውነተኛውን የህይወት ድራማ ስትጫወቱት ያ ሁሉ አርቲስት ህንፃው ላይ ካለው የቡና ቤቱ መስተዋት መስኮት ላይ ይመለከታችሁ ነበር። የተዋጣለት ድራማ በመሆኑ ያሳደነቀ አልነበረም ቂቂቂቂ..."

"ቁጭ በይ፣ ሣራ"

"አቢ፣ ቢሮው ገብተሽ ምን እንዳልሽው አልጠይቅሽም። ለመስማት የጓጓሁት እሱ ምን እንዳለሽ ብቻ ነው"

"ቁጭ በይ!" ሣራ ወንበሩን ስባ ተቀመጠች። አብነትም ወደ መቀመጫዋ ሄዳ በዝምታ ተከፈለች።

"ምነው አብነት? ምን እንዳለሽ ንገሪኝ እንጂ!" ጆሮዎቿ ቆመዋል "አብነት የጠየቀቻትን ከነገረቻት ቢያንስ ለሳምንት ሳቃ የምታስቅበት ትኩስ ወሬ ይኖራታል።

"ምንም" አለች አብነት ትከሻዋን እየሰበቀች።

"እንዴት ምንም አብነት? ከኔ የምትደብቂው ሚስጥር ሆነብሽ እንዴ?"

"እንደዚያ ሳይሆን፣ ምንም የሚሠራልሽ ነገር የለም"

"ይሠራልኛል፤ ንገሪኝ!"

ንዝንዟ ሲሰለቻት የሆነውን ሁሉ በዝርዝር አጫወተቻት። ሣራ መጀመሪያ በፀጥታ እየቆየች ግን ራሷን መቆጣጠር እስኪሳናት ድረስ በሣቅ ትንከተከት ጀመር። ስትስቅ ትናንሽ ዐይኖቿ ይጨፈናሉ፤ በቀጭን ሰውነቷ ላይ የተተከሉት ትልልቅ ጡቶቿም ላይና ታች ይዘላሉ። አንዴ ጎንበስ ሌላ ጊዜ ቀና እያለች ሰውነቷ እስኪዝለፈለፍ ሳቋን ቀጠለች።

አብነት በንዴትና በእልህ መጋል ጀምራለች። ግንባሯን ቋጥሮ፣ ቅንድቧን ሰብስባ፣ ዐይኖቿን ፍጥጥ አደረገችና "ምን ያስቅሻል?" ስትል ጠየቀቻት።

ሣራ እንደ ወባ በሽተኛ የሚያንዘፈዝፉትን ሳቅ እንደ ምንም ታግላ ካቆመች በኋላ ከዐይኗ የሚወርደውን እንባ በጣቶቿ እያደራረቀች "አይ አብነት!" አለች በመገረም።

"ማበድሽ ነው እንዴ ሴትዬ?" አብነት እንደበሸቀች ጠየቀች።

"ያበድሽስ አንቺ፤ ጨርቅሽን መጣል እንጂ አሁንማ ሌላ ምን ቀረሽ?"

አብነት ከመቀመጫዋ በፍጥነት ተነስታ እልህና ቁጭት ባፈነው አንደበት "አንቺ የውሻ ልጅ!፤ ይሄን ክፍል ለቀሽ ውጪ!" ስትል አንባረቀችባት።

ሣራ ለአጭር ጊዜ ባለችበት ደርቃ ቀረች። የጓደኛዋ ፀጉር ቀጥ ብሎ ቆሟል፤ ደም ሥሮቿ ግንባሯ ላይ ፈጠዋል፤ ከንፈሮቿ ይንቀጠቀጣሉ። በርጋታ ከመቀመጫዋ ተነሳችና ግንባሯን ቅጭም አድርጋ "ምን አልሽ?" ስትል ትናንሽ ዐይኖቿን እያቁለጨለጨች ጠየቀቻት።

"ውጭ! ሁለተኛ ዐይንሽን ማየት አልፈልግምና ውጭልኝ!"

ሣራ ጋዴም በፌስታል ይዛ የመጣችውን ባለ ፈር ጃኬት ከአብነት ጠረጴዛ ላይ በርጋታ ካስቀመጠች በኋላ ቦርሳዋን ይዛ ተነሳች። ለአብነት ብዙ ልትነግራት የምትፈልገው ነገር ነበር። ከአብነት ጋር ብዙ መጫወት የምትፈልገው ጉዳይ አላት፤ ከአብነት የምትፈልገው ብዙ ነገር አላት። በውስጧ የታፈነው ቁጣ ግን ከዚህ ሁሉ በላይ ነበር። "አመሰግናለሁ" አለቻትና ዐይኖቿ የቀጠሩት እንባ አብነት ፊት ከመዘርገፉ በፊት እየተጣደፈች ቢሮውን ለቃ ወጣች።

አብነት እየተንቀጠቀጠች መስኮቱ አጠገብ ሄዳ ቆመች። ቁልቁል ስትመለከት ሣራ ጋዴም አስፋልቱ ጠርዝ ላይ እንባዋን በመሀረብ እያደራረቀች ታክሲ ትጠብቃለች። የአብነት አንጀት በሀዘኔታ መንሰፍሰፍ ጀመረ። እንባዋ ግድቡን እንደጣሰ ቦይ ጉንጮቿ ላይ ይንዶለዶል ገባ። እዚያ ቦታ ላይ ቆማም ይህን ትርኢት ማየቱ አልተቻላትም። የቢሮዋን በር ከፍታ ደረጃውን እየተንደረደረች ወርዳ ወደአስፋልቱ ሮጠች። ሣራ ጋዴም ግን አልነበረችም። የሀንፃውን ምሰሶ ተደግፋ ዐይኖቿን በሁለት እጆቿ ሸፈነችና ተንሰቅስቃ ማልቀሷን ቀጠለች። በመጨረሻም ፀጉሯን እየነጨችና እየተወላገደች ወደ ህንፃው መጥታ መፀዳጃ ቤት ገባች። የእጅ መታጠቢያውን የባንቧ ውሃ ከፍታ በእፍኟ ውሃ ከዘገነችለት በኋላ ቀና ስትል፣ በመስተዋት ውስጥ ምስሏን አየች። የተበታተነው ፀጉሯ ግንባሯ ላይ ወርዷል። በደፈረሱት ዐይኖቿ ውስጥ ጭካኔና እልህ ይንቀለቀላሉ፤ ወዞማው የፊቷ ቆዳ ገርጥቷል፤ ከንፈሮቿም ደርቀዋል። "አምላኬ ምናለ ብትገድለኝ?!" ስትል ድንገት ከጣራ በላይ ጮኸች።

ከሣራ ጋር ያሳለፈቻቸውን የጓደኝነት ጊዜ ስታስታውስ ዳግም ተመልሰው የማይመጡት ድንቅ ዓመታት አንገበገቧትና ራሷ'



ረገመች። ሣራ መተኪያ የሌላት ጓደኛዋ ነበረች። ስለ ራሷ ስትናገርም "እኔ በፈቀድኩበት አቅጣጫ ያለከልካይ በነፃነት እንደምትበር ወፍ ነፃ የሆንኩ ሰው ነኝ" የምትለው ታወሳትና በቅሬታ ፈገግ አለች። አሁንም ከአብነት እቅፍ ወጥታ በነፃነት በረረች። ምናልባት ዛሬውኑ ሌላ የቤት ጓደኛ ትይዛለች፤ ዳግም በነፃነት እስክትበር።

አብነት እንደተከዘች ወደ ቢሮዋ አመራች። ሣራ የነበረችበት ወንበር ላይ አባቷ ተቀምጠው ጠበቋት።... ግር ብሏት የከፈተችውን በር እንደያዘች ባለችበት ቆመች።

"ግቢ" አሏት፣ ከፒፓቸው የሚትጎለጎለውን ጭስ ከፊታቸው ላይ በእጃቸው እያባረሩ። ኮታቸውን ቢሯቸው ትተው በሸሚዝ ብቻ ነበሩ። ጥቁር ሱፍ ሱሪያቸውን የታጠቁትም በማንገቻ ነው። እንደከበዳት በርጋታ ሄዳ ወንበሯ ላይ ተቀመጠች።

"ለአጭር ጉዳይ ነው የመጣሁት። ከዚህ ቀደም ስለድርጅቱ በተነጋገርንበት ወቅት፣ ተቀራርበን እንደምንሠራ ተስማምተን ነበር" አሉና በዝምታ ተመለከቷት።

ከዝምታቸው የአዎንታ ማረጋገጫ እንደሚጠብቁ ገመተችና "አዎን" አለች ራሷን እየነቀነቀች።

"ጥሩ፤ እ ... አዲሱን ሥራሽን ለድርጅቱ አንድ ውለታ በመፈፀም ትጀምሪያለሽ" አሏት።

የአብነት ልብ በፍጥነት መምታት ጀመረ።

"አዲሱ ሥራሽ... እ.. የዚህን ድርጅት ጠበቃ አቶ ሰዩምን ይመለከታል። ባለፈው ጊዜ እንደነገርኩሽ ይህ ድርጅት ያለርሱ ምንም ማለት አይደለም። ሰውየው ተዓምር መሥራት የሚችል ችሎታና አቅም አለው። ይህ ድርጅት ደግሞ ይሄንን ምትሃታዊ ችሎታውን መጠቀም ይፈልጋል። በየሳምንቱና በየወሩ እየተከሰሰ ሕግ ፊት የሚቀርበው ድርጅታችን በጠበቃችን ብርታት ባይሆን ኖሮ ይቅር ያለፉትን በርካታ ዓመታት፣ አንድ ቀን እንኳን ተከፍቶ መቆየት ባልቻለም ነበር። ይሁንና ይህ ድርጅት ጠበቃውን እንደሚፈልግ ሁሉ ጠበቃው ደግሞ ከኔ የሚፈልገው ነገር አለ" አሉና በለበጣ መሣቅ ጀመሩ።

አብነት ትንፋሿን ሰብስብ አድርጋ በመገረም ትመለከታቸዋለች።

"ይህን ፍላጎቱን እንደ ህልም አድርገሽ ቁጠሪው። ልጁን እንደርሱ ላለ ፈንጭና አባካኝ ሰው የማይሰጥ ጠንቃቃ አባት ስላለሽ ልትኮሪ ይገባል። በቀጥተኛ አነጋገር ጠብቃው አንቺን ማግባት ይፈልጋል!"

አብነት ትንፋሿ መቆራረጥ ጀመረ።

"ረጋ በይI ጠበቃው ምን እንደሚፈልግ አስቀድሜ አውቅ ስለነበረ በጥያቄው አልተደነቅኩም። ይሁንና በዚህ ጉዳይ መቃቃርና ሰውዬውን ማራቅ የለብንም። ሰዎች እንጂ ፊጋ በሬዎች ስላይደለን እንዲህ ዓይነቱ አደጋ በድርጅታችን ላይ ሲያንዣብብ ግምባራችንን ሰትረን መላተም አይገባንም። ይህን ችግር እንዴት እንደምንወጣው ማሰብ አለብን። 'ላምን ሲያልቡ ጨው እያላሱ ነው' ሲባል እንደሰማሽ እገምታለሁ። ትክክለኛ አባባል ነው" አሉ ፈገግታቸውን እያጠገቧት ። በትምባሆ ጭስ የጠቆሩና ውልግድግድ ያሉ ረገዥም ጥርሶቻቸውን ማየት አስጠላት። ከአንደበታቸው የሚወጣውን ቃል ማድመጡም ሰቀጣት።

"የተመኘው እንደሚሳካለት እንዲገምት ፈገግታሽን አትንፈጊውI ሊቀርብሽ መሞከሩ አይቀርምና ቅረቢው። ነገር ግን ምንጊዜም አንድ ነገር ከህሊናሽ መውጣት የለበትም። ከርሱ ጋር በሆንሽ ቁጥር ራስሽን ልክ ቲያትር እንደሚጫወት ሰው አድርገሽ ቁጠሪው። ሁሉ ነገር ልብ ወለድ መሆኑን አትዘንጊ።

"ሲያጫውትሽ ተጫወችለትI ልብሽ ግን እየደጋገመ ይርገመው። ሲያስቅሽ ገልፍጭለትI ልብሽ ግን በለበጣ ይሳቅበት። በእሣት እንደምትጫወቺ ግን አትርሺ። በመርዛሙ ልሣኑ እንዳያደነዝዝሽ ተጠንቀቂ። በነፍስም በስጋም ከርሱ መራራቅሽን ዘወትር አረጋግጪ። ያልተዋጣላት ተዋናይ ሆንሽ ያዘጋጀሽው ወጥመድ ውስጥ ራስሽ እንዳትወድቂና የድርጅቱን ህልውና ከአደጋ ላይ እንዳትጥይ ግን ተጠንቀቂ!!" አሏትና ፒፓቸውን እየመጠጡ ተነሱ።

አብነት ልትቃወማቸው አፏን ስትከፍት ስሜቷን ተረድተው ቆም አሉና "አንድ የማስጠነቅቅሽ ነገር ደግሞ አለ። የምንሠራው ሁሉ ለድርጅቱ ህልውና መሆኑን እንዳትዘነጊ። በዚህ ግንኙነታችንም እንደ አባትና እንደልጅ ሳይሆን እንደ አሠሪና ሠራተኛ ራሳችንን መቁጠር ይኖርብናል። አሁን የሰጡሽ ሥራ ትእዛዝ ነውና ያለ ጥያቄ፣ ያለ አንዳች ተቃውሞ መፈጸም ይኖርበታል!" ብለዋት እየተቆናጠሩ ከቢሮዋ ወጥተው ሄዱ።



የትምባሆው ጭስ ቢሮዋ ውስጥ ይንሳፈፋል። ዐይኖቿ ደመ-ነፍሳቸውን በወፍራሙ ጭስ ላይ ይማልላሉ። ማድረግ የምትችለው ነገር የለም። እሷ የሁኔታዎች ተገዥ እንጂ በፈለገችበት አቅጣጫ ያለከልካይ የምትበር ወፍ አይደለችም። እናም በወጥመድ ውስጥ ያለች ትንሽ ወፍ የሆነች መሰላትና ከትከት ብላ በምሬት ሣቀች።

# ምዕራፍ ሰድስት

ሰባቱ የስብሰባ ተካፋዮች ቡና የጠጡባቸው ፍንጃሎች ባዷቸውን ረጅሙ ጠረጴዛ ላይ ተኮልኩለዋል። ጠበብ ያለችው ክፍል በሲጋራ ጢስ ታፍናለች። በዚያች ቢሮ ውስጥ ከየቲያትር ቤቱ የተወከሉ ባለሙያዎች የሳንሱር ጣጣቸውን ጨርሰው የሚቀርቡላቸውን የቲያትር ጽሑፎች በመገምገም ብቃታቸውን ያረጋግጣሉ። በባህል ሚኒስቴር ህንፃ ውስጥ።

የዕለቱ ስብሰባ ረዘም ላለ ሰዓት ያለማቋረጥ በመካሄዱ ባለሙያዎቹ የተሰላቹ ይመስላሉ። አንዳንዶቹ ያዛጋሉ፤ ይንጠራራሉ፤ ከፊሎቹ ደግሞ የፈዘዙ ዐይኖቻቸውን በመዳፎቻቸው እያሻሹ ጆሮዎቻቸውን ወደ ተናጋሪው ደግነዋል።

"...ስብሰባውን ለማጠቃለል፣ በቀረበልን አንድ ተውኔት ላይ ለአምስት ጊዜ ተገናኝተን ቃለ ተውኔቱን በንባብ አዳምጠናል፣ ከተውኔት መመዘኛ ነጥቦችችን አኳያ በመመልከት የተለያዩ አስተያየቶችን በማቅረብ የተውኔቱን ደካማና ጠንካራ ጎኖች መርምረናል..." አለ ሰብሳቢው ዳንኤል እጅጉ። "በመሆኑም የማጠቃለያ ሀሳብ በመስጠት ስብሰባውን እንድንፈጽም እጠይቃለሁ።

የሚጽፍበትን ብእር ጭንቅላት በጥርሱ እየነከሰ ያዳምጥ የነበረው የስብሰባው ፀሐፊ ቀበል አድርጎ... "እንደ እውነቱ ከሆነ ...የግል አስተያየቴን ለመስጠት ነው፤ ይህ ተውኔት ከተውኔት መመዘኛ ነጥቦችችን አኳያ እንከን የሚወጣለት አይደለም። የሴራ አነዳደፉ፣ የቃላት አጠቃቀሙ፣ የገፀ-ባህርያት አሳሳሉ፣ የገፀ-ባህሪያቱን የኢኮኖሚ አቋም በማያሻማ ሁኔታ አገላለፁ፣ የመቼት ጥያቄ አመላለሱ... እንደ እውነቱ ከሆነ... የግል አስተያየቴን ለመስጠት ነው። ...ብስለት ያለው ሥራ ነው ብዬ እገምታለሁ" አለና ሰረቅ አድርጎ ቻርሊን በሀፍረት ተመለከተው። ቻርሊ ይህ ሰው የደራሲው የልብ ጓደኛ መሆኑን ያውቃል። ትላንትናም አንድ ቡና ቤት አብረው ሲጠጡ አይቷቸዋል።

"ባደረግናቸው ስብሰባዎች ላይ እንዲስተካከሉ ሃሣብ ያቀረብንባቸው ነጥቦች እንደተጠበቁ ሆነው ተውኔቱ ለህዝብ ቢቀርብ ብቃት ያለው ሥራ ነው ብዬ እገምታለሁ" አለ ወፍራሙ የስብሰባ ተሣታፊ ጢሙን በእጆቹ እያፍተለተለ።



ሥላላ ድምጽ ያለው አጭሩ ተሣታፊ በበኩሉ ጉሮሮውን ጠራረገና ቀጠለ፤ "የደራሲውን ጥበባዊ አቀራረብ እያደነቅኩ ተውኔቱ ለህዝብ ቢቀርብ እደግፋለሁ"

"የኔም ሀሳብ አሁን ከተሰማው የተለየ አይደለም" ራሰ በራው ተናገረ። ... ቀጣዩ ተሰብሳቢ ምንም አልተነቃነቀም። ወደ ጣሪያው የሚትጎለጎለውን የሲጋራ ጭስ እያስተዋለ በፀጥታ ተቀምጧል። ዳንኤል ጥቂት ቆይቶ "አበራ፤ አስተያየት የመስጠቱ ተራ ያንተ ነው" ሲል አሳሰበው። አበራ የሲጋራውን አመድ መተርኮሻው ላይ አራገፈና "የምሰጠው አስተያየት የለም" አለ በሰለቸ ድምጽ።

ሰብሳቢው ወደ መጨረሻው የኮሚቴ አባል ፊቱን መለሰ። ቻርሊ ግምባሩን እንደቋጠረ ባዶው ግድግዳ ላይ አፍጥጧል። ዳንኤልና ቻርሊ አንድ ቲያትር ቤት ውስጥ የሚሠሩ የማይጣጣሙ ባለሙያዎች ናቸው። እናም ተጠባብቀውና ተራርቀው ነው የሚኖሩት።

"ቻርሊ አስተያየትህን ብትሰጥ" አለ ሰብሳቢው በንቀት። ቻርሊ ዐይኖቹን ከተከለበት ግድግዳ ላይ ነቅሎ ሰብሳቢውንና ተሰብሳቢዎቹን ከገረመመ በኋላ፣ "ተውኔቱ ብቃት የለውም!" ሲል ባጭሩ አስተያየቱን ሰጠ።

"ምክንያትህን ብትገልጽ?" አለ ዳንኤል ግምባሩን ቅጭም እንዳደረገ። ፀሐፊው በበኩሉ ብእሩን በቃለ ጉባኤው መዝገብ ላይ እያነጣጠረ ተቁነጠነጠ።

"ምክንያቱማ ፀሐፊ ተውኔቱ የተውኔትን ዓላማና ግብ አለማወቁ ነው። ኧረ እስኪ እናንተን መልሼ ልጠይቃችሁ። ስለተውኔቱ ጥበባዊ አቀራረብ አብዝታችሁ ስትወተውቱ ምነዋ አንዳችሁ እንኳን ስለ ይዘት አለመተንፈሳችሁ?!" እያንዳንዳቸውን ተራ በተራ አስተዋላቸው፤ መልስ የሰጠው ግን አልነበረም።

ቻርሊ ቀጠለ "'ጥበብ በጥበብነቱ ብቻ ከተወሰደ ጥበብ የለሽ ነው' ያለውን ደራሲ ትክክለኝነት እንዷ ስሙን አሁን ማስታወስ አልቻልኩም። የማኅበረሰቡን ህይወት የማይዳስስ፣ የዘመኑን ሰው ማህበራዊ ህይወት መስተዋት ሆኖ የማያሳይ ጥበብ ጥበብነቱ ምኑ ላይ ነው?!" ዐይኖቹ ደም መልበስ ከንፈሮቹ መንቀጥቀጥ ጀምረዋል።

"መድረኮቻችን እስከ መቼ ነው 'የአንድ ሺ ከአንድ ሌሊት' ተረቶች መተረቻ የሚሆኑት? ጥበብስ መቼ ነው ለደራሲው የገንዘብ

ካዘናፕ ስተዋናዩ ደግሞ ዝና መሸመቻ ገበያ ከመሆን አልፋ ማኅበረሰቡን ሊታገለግል የምትበቃው?"

"የምትናገረውን ብታስተውል መልካም ነው!" አለ ሰብሳቢው፤ ጥላቻው እያገረሸበት።

"ይሄ ስብሰባ የፈለግከውን መናገር የምትችልበት መድረክ አለመሆኑንም ብትገነዘብ ይበጅሃል" አለ ፀሐፊው በበኩሉ በዐይኖቹ እያስፈራራው።

ቻርሊ ሁለቱንም ከቁብ አልቆጠራቸውም። "አሁንም እደግመዋለሁ! በማህበረሰቡ ዐይን የማያለቅስ፣ በማህበረሰቡ ጥርስ የማይስቅ፣ ከማህበረሰቡ ጋር ታሞ ከማህበረሰቡ ጋር የማይድን ጥበብ፤ ያለሙቀት፣ ያለ ድምቀት በግ ብሎ ድርግም የሚል የብርሃን አላቂ ነው። ...እንኳንስ ብርሃን ሆኖ ማህበረሰቡን ወደ እውነት ሊመራ፣ ለገዛ ጭንብሉ ዓይኑም ፍኖት አይሆንም። እንኳንስ ሙቀት ሆኖ ያዘነች፣ የተጨነቀችን ነፍስ ሊያጽናና፤ ቆፈን እንዳደነዘዘው ቡችላ ለሚያሳዝን አንደበቱ አለኝታ አይሆንም። እንኳንስ የሌላውን ዐይን ሊወጋና የሌላውን ቀልብ ሊስብ፣ ከራስ ፀጉር እስከ እግር ጥፍሩ ያጠለቀውን ከል አይገፍም። ጥበብ ያለይዘት ውጭውን በከበረ ድንጋዮች ያጌጠ መቃብር ማለት ነው፣ ውስጡ በድን!" የእልህ ሲቃ እያንቀው ሁሉንም አስተዋላቸው። አሥራ ሁለት ዐይኖች በጥላቻ፣ በመገረም፣ ግራ በመጋባት፣ በሀዘኔታና በግድ የለሽነት ያስተውሉታል።

"አጥጋቢ ባልሆነ ምክንያት የቀረቡልንን የተውኔት ጽሁፎች ብቃት የላቸውም እያልን የምንመልስ ከሆነ፣ በቲያትር ቤቶች የሚቀርብ ሥራ እንደማይኖር ለምን አታስተውልም? በዚህ ግቢያ ስንት ጉሮሮዎች እንደሚዘጉስ አትገምትም?" ፀሐፊው አፈጠጠበት።

ቻርሊ በምጸት ሣቀ። "ይቅርታ አድርግልኝና ጓድ ፀሐፊ፣ ቲያትር ቤቶች የተቋቋሙበት ዋነኛ ዓላማ የኛን ጉሮሮ ለመክፈት ከሆነ አዳራሾቻችንን ወደ ወፍጮቤትነት፣ ወደ ዳቦ ማምረቻ ድርጅትነት አለበለዚያም ወደ ከብት ማድለቢያ ግቢያነት ለውጠን የእለት ጉርሳችንን ማግኘት ባላዳገተን ነበር። በጥበብ ባንነግድባት፣ በእውነት ባንቀልድባት፣ በፍቅር ባናተርፍ ይበጃል ነው የምለው። በይሉኝታ፣ በጥቅምና በቸልተኝነት ገረፍ ገረፍ አድርገን ለህዝብ እንዲቀርቡ የምናደርጋቸው ጉንድሽ ሥራዎች ህዝብንና ሙያውን ማራራቅ፣ ህዝብንና ባለሙያውን ማናናቅ እንጂ የሚፈይዱት ነገር የለም። የኛ ጥብቅነት ጥበቡን እንደ ገበያ የቆጠሩ ፀሐፊ ተውኔቶችን የእንጀራ



ገመድ እንደሚበጥስ አውቃለሁ። እውነተኞቹን የጥበብ ረሃብተኞች ግን ያተጋል" ቻርሊ ሽንጡን ገትሮ መሟገቱን ቀጠለ።

ሰብሳቢው በብሽቀት ፈገግ እያለ "እንግዲህ ፍፁም የሆነ ሥራ እስክታቀርቡልን ድረስ በፀሐፊ ተውኔቶቻችን የብስለት ደረጃ የቀረቡልንን ሥራዎች ማሳለፍ ግዴታችን መሆኑን ብትረዳልኝ እወዳለሁ" አለ።

ከተሣታፊዎቹ ከፊሉ ፈገግ አሉ። ቻርሊ ላይ የተሰነዘረበት ሽሙጥ በውስጡ መቀጣጠል የጀመረውን ንዴት አጋጋመበት። "ተዋናይ የግድ ፀሐፊ ተውኔት መሆን የሚኖርበት አይመስለኝም። ፀሐፊ ተውኔት ባይሆንም ግን የተሰጠውን ቃለ ተውኔት አጥንቶ እንደ በቀቀን በመጮህ መወሰን የለበትም። ስሜቱ፣ የህይወት ግንዛቤውንና ፍልስፍናውን ያልተቀበለውን ገፀ ባህርይ፣ የተዋናዩን ቀልብ ገዝቶ ከመቅኔው ያልተዋሃደውን ቃለ ተውኔት በመድረክ ላይ ቆሞ ቢጋገር፣ እንደ አሮጌ ጅብ ደንቁሮ... ከማደናቆር በላይ አንዲትም እውነት ከአርሱ አንደበት ጠብ አትልም። እና ጓድ ሰብሳቢ ሽሙጡን ቢያቆዩት። ተዋናይም በጥበብ ሥራ ላይ መተቸት፣ መሄስ ይችላልና..."

የቻርሊ ንግግር ያሰለቸው ፀሐፊ አቋርጦት፣ "ተዋናይ በቀረበ የጥበብ ሥራ ላይ ትችት መስጠት አይችልም ያለ የለም። እንዲህ ቢሆንማ የኛም እዚህ መገኘት ባላስፈለገም ነበረ። ይቅርታ አድርግልኝና ቻርሊ፣ ከተኛህበት ነው የምትነቃው። በዚህ ቃለ ተውኔት ላይ ስንወያይ ዛሬ አምስተኛ ጊዜያችን ነው። በነዚህ ሁሉ ቀናት አንዲትም ቃል አልተነፈስክም። አሁን በውይይታችን ማብቂያ ላይ ይሄ ሁሉ ማቅራራት ለምን እንደሆነ አይገባኝም" በማለት አፈጠጠበት።

ሰብሳቢውም ቀጠለና "በተጨማሪ፣ ይሄ መድረክ የብሶት አደባባይ አይደለም። የህይወት ውድቀትህን እንጉርጉሮ ለማዳመጥ አልመጣንም" አለ፤ የቻርሊን ቁስል ፈልጎ በመደንቆሉ እርካታ እየተሰማው።

ቻርሊ ለአፍታ መላ ሰውነቱ ደነዘዘ። ብዙ ቆይቶ "ስለ ተደራቢ ብሶት እንጂ ስለ ግል ህይወቴ አላነሳሁም፤ ብናገርም አትሰሙኝም። በምድረበዳ ብቻውን እንደሚጮህ ቁራ የገዛ ድምጼ ለኔው ጆሮ እንጂ ለናንተ ሩቅ ነው..." ንዴቱን በትግሥት ለመቆጣጠር እየታገለ፣ በእልህ ሊታፈን ከተቃረበው ልሳኑ ቃላቱን በመከራ ወረወራቸው። "የህይወት...

ውድቀትህን እንጉርጉሮ ነው ያልከኝ?! ለመሆኑ የህይወቴ ውድቀት ምክንያት ምን እንደሆነ ታውቃለህ?" ብድግ ብሎ ቆመ። መናገሩን እንጂ ምን እንደሚል አያውቅም። የአዕምሮ ህመሙ ሲነሣበት እንደሚሆነው ሁሉ ዐይኖቹ ደም ለብሰዋል፤ ከንፈሮቹ መንቀጥቀጥ ጀምረዋል።" ከሞተው ጎጆዬ ይልቅ የጥበብ ሞት ነው የሚቆጨኝ! ባክነው ከቀሩት ልጆቼ ይልቅ ፍቅር ስትባክን ነው የሚያመኝ። ከባዶው እንጀራ ይልቅ የእውነት ጠኔ ነው የሚጥለኝ።አንተ ሳትሞቅ የፈላህ የምሁር ጅምር! አትናገረኝ!...አትና..." ከመጨረሱ በፊት በሁለት እጆቹ መዳፎች ጭንቅላቱን ግራና ቀኝ ግጥም አድርጎ በመያዝ "ራሴ ሊፈነዳ ነው!" ሲል አቃሰተ። አጠገቡ የነበሩት ሁለት የስብሰባ ተሣታፊዎች ደጋግፈው ከወንበር ላይ አስቀመጡት።

"ውሃ! ውሃ፤ እባካችሁ ትንሽ ውሃ"፤ ሌላኛው ሰው ቡና ከጠጡባቸው ፍንጃሎች አንዱን አንስቶ እየተጣደፈ ከክፍሉ ወጣ። ቻርሊ ጭንቅላቱን እንደያዘ ጠረጴዛው ላይ በግምባሩ ተደፍቶ በፍጥነት እየተነፈሰ ያቃስት ጀመር። ዳንኤል በድል አድራጊነት ገጹ ፈክቷል።...ተሣታፊዎቹ በድንጋጤ እርስ በርሳቸው ይተያያሉ። ክፍሉንም ሙሉ ፀጥታ ዋጠው።

ውሃ ሊያመጣ የሄደው ሰው በፍንጃል ሞልቶ ያመጣውን ውሃ ጠረጴዛው ላይ አስቀመጠና የቻርሊን ትከሻ እየነቀነቀ "ቻርሊ፣ ይሄው ውሃ" እያለ አነቃው። ቻርሊ ከጭንቅላቱ ቀና አለና ያለበት ቦታ የጠፋው ያህል ዙሪያውን ተመለከተ። ዘግይቶ ከኮቱ ኪስ ውስጥ ትንሽ ጥቅል አውጥቶ ሁለት እንክብሎችን በመጣለት ውሃ ዋጠ። ከዚያም በረዥሙ ተነፈሰና ቆመ። ከዳንኤል ጋር ዐይን ለዐይን ተፋጠጡ። በዳንኤል ዐይኖች ላይ ድል አድራጊነት፤ በቻርሊ ዐይኖች ውስጥ ደግሞ በቀል ይንቀለቀላል። "አንድ ቀን ይለይልናል!" አለና ጥርሶቹን በሀይል አፋጭቶ በመጠጥ ኃይል ሚዛኑን መጠበቅ እንደተሳነው ሰው እየተወላገደ ክፍሉን ለቆ ወጣ።

የባህል ሚኒስቴርን ህንፃ ጠምዛዛ ደረጃዎች ወርዶ፤ የግራና የቀኝ እግሩን እያማታና እጆቹን እያወናጨፈ የአስፋልቱን መንገድ በመሻገር መንደሩን አቋርጦ ሰንጋተራ ሲደርስ ፊት ለፊቱ ወዳየው የመጠጥ መቸርቸሪያ ግሮሠሪ እየተጣደፈ ገባ።

ኒቂሴኮ የሀበሻ ልብሷን እንደለበሰች መቀመጫዋን እያነጠረች "ምን ልታዘዝ?" ስትል ከፈገግታ ጋር ጠየቀችው።

"ደብል ቅጥር ነፍስ ገዳይ ቅጅልኝ!"



"የዚህ የጅን ቅጥል ስሙ ደግሞ አበዛዙ..." እያለች ስትውረገረግ ሄዳ አልኮሉን ቀድታ አመጣችለት። ቻርሊ ገና ከእጂ እንደተቀበለ በአንድ ትንፋሽ ጨለጠው። ሁለተኛውን ዙር ሲያስቀዳ ከጥቂት ደቂቃዎች በፊት የዋጣቸው እንክብሎች ትዝ አሉትና ክትክት ብሎ ብቻውን ሣቀ። "ያልታደልኩ፤ ያልታደሉ" ፊቱን አማተበና ሁለተኛውን ዙር መለኪያ ለመጨለጥ ከከንፈሩ ጋር አገናኘው።

"ብቻዎን ይስቃሉ እንዴ እንቴዬ?"

"ከሌሎች ጋር ለመሣቅ ሳልታደልስ ኒቂሲኮ..."

"ኧረ እኝህ! የሰው መድሃኒቱኮ ሰው ነው"

"እጥፌ መርዙም!"

"ቢሆንም ህልም ተፈርቶ ሣይተኛ አይታደርም። ሰው ያለ ሰው የደረቀ እንጨት ማለት ነው። ተቃጥሎ ከመክሰልና አመድ ከመሆን ሌላ ምን እጣ አለው?! ምንም"

አጋር የሌለው ከርታታ ፍጡር መሆኑን አሣየችው። ከዚህ ጥቁር ሰማይ በታች፣ ከዚች ጥቁር መሬት በላይ አንድ ራሱን፤ ብቻውን ቆሟል። ነፍሱ አጋሯን ፈለገች። በበድን ህይወቱ ውስጥ እስትንፋሿን እፍ ብላ የምትዘራብት አይዞህ የምትል ጓደኛ ፈቀደች። ሥጋው ግን በአልኮል ትነፍራለች፤ ይጠግል ያለማቋረጥ። ድንገት አብነት ከነለዛዋ በዐይኑ ላይ ተደቀነች። ከርሷ ሊቆራኝ ወሰነ። ህልም ተፈርቶ ሳይተኛ አይታደርም እማይደል ያለቻው ኒቂሴኮ?!

*** *** ***

አብነት ከሥራዋ ወጥታ ወደ ቤቷ ለመሄድ ታክሲ ፍለጋ ትጣደፋለች። አባቷ ቀደም ብለው መኪናዋን ይዘው ወጥተዋል። አንድ ሰው መንገዱን ዘግቶ ከፊት ለፊቷ በመቆም እንዳትራመድ አገዳት። ቀና ብላ አየችው - ቻርሊ! ቢሮው ባገኘችው ጊዜ ፊቱ ላይ ይነበብ የነበረው ንቃትና በራስ የመተማመን መንፈስ አይታይበትም። የሰለቸ፣ የደከመና ተስፋ የቆረጠ ይመስላል።

"ደህና ሰነበትሽ አብነት?" ብሎ ለሰላምታ እጁን ዘረጋላት።

"መንገዱን ልትለቅልኝ ትችላለህ?!" አለችው ግምባሯን ቋጥር አድርጋ እጆቿን እየሰበሰበች ። እልህ ይተናነቃት ጀምሯል።

"በቀደም እንዳሳዘንኩሽ ይገባኛል... ግን ምን ላድርግ?"

"መንገዱን ብቻ ልቀቅልኝ!" ገፍትራው ልታልፍ አሰበች።

"ይቅርታ ልታደርጊልኝና የሆነውን ሁሉ ልትረሺው አትችይም?"አላት ሀዘን በሰበረው ድምጽ። ተስፋ የቆረጡት ዐይኖቹ እየተንከራተቱ ሲማፀኗት ጨክና ረግጣው ልትሄድ አልቻለችም።

ለረዥም ጊዜ በዝምታ ስትመለከተው ይተናነቃት የነበረው እልህ እየቀለላት፣ በውስጧ መንተክተክ የጀመረው ደም መቀዝቀዝ ሲጀምር ታወቃት። ዐይኖቿም የእንባ ዘለላዎች መቋጠር ጀመሩ። የዘረጋውን እጁን በሚንቀጠቀጡት እጆቿ በዝግታ ጨበጠቻቸው።

የአስፋልቱን ጠርዝ በመያዝ ከመንገደኛው ጋር እየተርመሰመሱ በዝምታ መጓዝ ጀመሩ። ብዙ ከሄዱ በኋላ እየተርመሰመሱ "እንደሚገባኝ... አንቺን ልረዳሽ የቻልኩትን ያህል አንቺ እኔን ልትረጂኝ አልቻልሽም። ከልዩነታችን አንዱ..."የጀመረውን ሳይጨርስ አብነት አቋረጠችው።

"ኡህ... ቻርሊ! አሁንም ስለልዩነቶቻችን?!"

"ስለ ልዩነቶቻችን መነጋገሩና አንዳችን የአንዳችንን የህይወት ድክመት መገላለጡ፣ የስህተቶቻችንን ምክንያቶች በቅድሚያ ለመገንዘብና ልባችንንም ለይቅርታ... ለማንበርከክ እንደሚበጀን ታውቂያለሽ?" አላት የጎድን እያስተዋላት። "እና ስለ ልዩነታችን ማውሳቱ የሚጎዳን አይደለም። ቅድም ልነግርሽ የፈለግኩት አንቺ ለህይወት አዲስና ገና ጉልበትሽ ያልተነካ፣ ሁሉን መጋፈጥ የምትችይ ደፋር ሴት ስትሆኚ እኔ ግን ህይወትን እምፈራ መሆኔን ነው። ከህይወት ልምዴ ሁሉን እጠራጠራለሁ። ዛሬ ዛሬ ግን በአንድ ነገር እርግጠኛ ሆኛለሁ። ለዓመታት የተቆለፈውን ልቤን ፈልቅቀሽ ከፍተሽዋል..."

ከዚያ በኋላ የተናገረውን በውል ለማዳመጧ እርግጠኛ አይደለችም። የድል አድራጊነት፣ የደስታ፣ የቁጭት ስሜት ተደበላልቀው መላውን ሰውነቷን አሞቁት። ጆሮዎቿ ከዚያ በላይ መስማት አላስፈለጋቸውም። ነፍሷ በውስጧ ጨፈረች፣ ልቧ በሀሴት አጨበጨበች።

"ቡና ብንጠጣስ?!" አላት በዚያው የልመና ቃና ባለው ድምጽ። ቀና ብላ ዙሪያዋን አየች። አንድ ካፌቴርያ በር ላይ ደርሰው ነበር። እጅ ለእጅ ተያይዘው ወደዚያው በማምራት ቦታ ፈልገው በረንዳ ላይ ተቀመጡ።

ሁለቱም ቡና አዘው፣ አስተናጋጁ ይዞላቸው እስኪመጣ በፀጥታ ተፋጠጡ።

አብነት የቀረበላትን ቡና እያማሰለች "ቻርሊ፣ በዚያን ቀን ለምን እንደዚያ ጨከንክብኝ?" ስትል ጠየቀችው።

"ባለፈው ቀን ስለሆነው ሁሉ እንዳናነሳ ለምኜሽ አልነበረም?!"

"እሽ፣ ከዚያ በኋላስ የት ጠፋህ?"



"ታስሬ ነበር" አላትI ባሻገር መንገደኞቹን እየተመለከተ።

"ትቀልዳለህ?!" በድንጋጤ ከተቀመጠችበት ለመነሳት ቃጣት።

"የዲሞክራሲ መብቶች ትቢያ በለበሱበት አገር ጀንበር በወጣችና በጠለቀች ቁጥር እንደ ጥጃ መታሠሩና መፈታቱ ያስደንቅሻል? በተገናኘን ማግሥት ነበር የታሰርኩት!!"

የጀመረውን እስኪጨርስ አልታሠገችውምI "እኮ በምን ምክንያት?" ስትል በጥያቄ ወጥራ ያዘችው።

"ሰዎችን ለማሰር ምን ምክንያት ያስፈልጋል? ፀረ- አብዮተኛ ነው የሚለው ጥርጣሬ ብቻ እንጦርጦስ ለማውረድ በቂ ምክንያት ነው"

"እና እንዴት ለቀቁህ?"

"ማስረጃ አልነበራቸውም። ጎትተው ፖሊስ ጣቢያ እንደወረወሩኝ ገፍትረው ደግሞ አስወጡኝ" አለና በቅሬታ ፈገግ አለ።

"ግን አንተ እንደሚሉህ የአብዮቱ ጠላት ነህ?"

"እኔ እንጃ" አላት ትከሻውን እየሰበቀ። "እኔ ይህን አላውቅምI በአንድ ነገር ብቻ እርግጠኛ ነኝ። ሀገሬን እወዳለሁI ህዝቦቹን እመልካቸዋለሁ። ትከሻቸው ላይ የመርግ ያህል የተጫናቸውን ጭቆና አሽቀንጥረው ለመጣል የሚያደርጉትን ትግልም እደግፋለሁ"

"የእውነት ኮምኒስት ነህ?!"

"አዎን"

"የየትኛው ድርጅት አባል ነህ?!"

"እሱን ማንሳት ያስፈልጋል ብለሽ ነው?"

"ግን የምር ኮምኒስት ነህ?"

"አዎን ነኝ"

ውስጧ የተቀጣጠለው ድንጋጤ ፋታ እስኪሰጣት ጠብቃ "ቻርሊ! ለምን ኮሚኒስትነትህን እርግፍ አድርገህ አትተወውም?" ስትል የልመና ያህል ጠየቀችው።

"ከነፍሴ የተዋሃደውን እምነት፣ ከደሜ የተቀላቀለውን ዓላማ እንደምትይው በፈቀድኩት ጊዜ ልጥለውና ባሻኝ ጊዜ ላነሳው አይቻለኝም። የህዝቦችን ነፃነት እናፍቃለሁ። ለኔ ህይወት ያለዚህ ተስፋ ትርጉም የለሽና ባዶ ነች..."

አላስጨረሰችውም። "ተሳስተሃል ቻርሊ! የሰው ልጅ ህይወት ባዶ የምትሆነው ፍቅርን ስትነፈግ ብቻ ነው!" አለችው እየተጣደፈች።

"ልክ ነሽ" አላት ራሱን እየነቀነቀ። ያለ አንዳች ሙግት እጁን መስጠቱና ሀሳቧን መቀበሉ እየገረማት "ታዲያ ለምን ልመናዬን አትቀበልም?!" ብላ ልትጠይቀው ስትዘጋጅ "እኔም ልክ ነኝ!" አላት እየፈገገ።

"ሁለት ፍፁም የተለያዩ አመለካከቶች እንዴት ባንድነት ትክክል ይሆናሉ?! እርግጠኛ ነኝ ከሁለት አንዳችን በተሳሳተ የህይወት መስመር ላይ ነን!" አለችው ግራ በመጋባት ስሜቱን እየመረመረች።

"አይመስለኝም፤ በመደመር ስሌት አንድና ሶስት ወይም ሁለትና ሁለት ውጤታቸው ያው አራት ነው። ባንድ ጉዳይ ላይ እውነት ወደሆነው ውጤት ለመድረስም የግድ አንድ መስመር ብቻ መከተል የለብንም። እንደሚገባኝ ሰፊ ልዩነቶቻችንን ማቻቻል የምንችለው አንቺም የእኔን እውነት እኔም የአንቺን እምነት ስንቀበል ብቻ ነው" አላት እስተሳሰቡን ምን ያህል እንደተቀበለችው ለመገመት ዐይኖቿን ጠልቆ እየመረመረ። አልመለሰችለትም።

"እየሽ አብነት፣ በሁለት አካል ውስጥ ያለተቃርኖ የሚገዙ ሁለት ነፍሶች ቦታቸው ምናልባት በልብ ወለድ መጽሀፍ ብቻ ነው። የገሃዱ ዓለም ህይወት ግን… በየማእዘኑ በቅራኔ የተወጠረች፣ በልዩነቶች የታጠረች ነች። እንደምረዳው ፍቅር ህያው ሊሆን የሚችለው በነዚህ ልዩነቶችና ቅራኔዎች ውስጥ ሊፈጠር በሚችለው አንድነት ነው። እየተግባባን ነው?" አላት ፈገግ እያለ።

"ስለ ዲያሌክቲክስ እያስተማርከኝ ነው እንዴ?" አለችው በፌዝ። አንዳንዴ ግራ ሌላ ጊዜ ደግሞ ሠአሊው አጎቷ ሲሉ ሰምታ እንጂ የምታውቀው ነገር እንኳ የላትም።

"የለም… የለም…" መናገር እስኪሳነው ድረስ በሳቅ ይንፈቀፈቅ ጀመር። ሲስቅ እንደ ግራ ጋዴም ዐይኖቹ ይጨፈናሉ። በዐይኑ ጠርዝ ግራና ቀኝ ቆዳው ይሸበሸብና ውበቱን ያጎላዋል።

"ልክ ኮምኒዝምን የምታስጠናኝ ነው የመሰለኝ" አለች አብነት እየሳቀች። የሚያንፈቀፍቀውን ሳቅ እየታገለ አቆመና "እሽንፈሻል! እኔስ እንደበቀደም ዕለቱ ሮጠሽ ትሄጃለሽ ብዬ ሰግቼ ነበር" አላት። ሁለቱም ከግራ በላይ መሳቅ ጀመሩ። በካፌቴርያው በረንዳ ላይ የነበሩ ተስተናጋጆች ሁሉ ፊታቸውን እየጠመዘዙ በመገረም ተመለከቷቸው።



"ልዩነታችንን ማቻቻል ጀምረናል ማለት ነው። እምነትሽን ሳልጋፋ፤ እምነቴን ሳትቀበይ። ጥሩ ጅምር ነው" አለና የጠጡበትን ከፍሎ ብዙ ርቀት በእግራቸው ከተጓዙ በኋላ ተሰነባብተው ተለያዩ።

አብነት ከሄደች በኋላ ቻርሊ ብቻውን ቆሞ ማሰብ ጀመረ። አንድ ታላቅ በደል እየፈጸመባት እንዳለ ሁሉ ከልብ አዘነላት። ከብዙ ዓመታት በፊት ውቢት የተናገረችው ትዝ አለው። "ይህን መልክ ቀናነትህንና ሙያህን ወዳ ትዳር በምትለው ወህኒ ቤት የምትማቅቅልህ ሌላ ምስኪን ሴት ፈልግ። እኔስ ከትብትብህ ተፈታሁ!"

"ይችን ውብ ልጅ በማትዘልቀው የፍቅር ጎዳና እየመራሁ እግር ከወርች ወደምትታሰርበት ወህኒ የምነዳት ለምንድነው?" ሲል ራሱን ጠየቀ።

በአንድ ነገር እርግጠኛ ነው። የወጣትነት ስሜቷ ሲቀዘቅዝ፤ የፍቅሯ ግለት ሲበርድ፤ አንድ ቀን ልክ እንደ ውቢት "… ፍቅር የጊዜ ጉዳይ ነው!" ብላው በእድሜዋም በኑሮ ደረጃዋም አቻዋን ፈልጋ ትሄዳለች። በናፍቆቷ መዋለሉ፤ በትዝታዋ መንገብገቡ የእርሱ ፈንታ ነው። ቻርሊ ለራሱ አዘነ።

በውቢት የፍቅር ጦር ተወግቶ ገና ያላገገመው አመጸኛ ልቡ ግን ያጃግነው ጀመር። "ቻርሊ ፣ አብነት የህይወት ጨው ስለሆነች መራራውን ህይወትህን አጣፍጥባት። አዲስ እንደተወለደች የንጋት ጀንበር ብርሃንህ ናትና ጨለማውን ህይወትህን አድምቅባት። አብነት ከአልማዝ፤ ከእንቁና ከከበረ ሉል የምትበልጥ ናትና ለደረትህ ሊሻን አድርገህ ተዋብባት። እስከመቼ ህይወትን ፈርተህ? እስከመቼስ ከፍቅር ሸሽተህ ትኖራለህ?!" የቻርሊ ነፍስ መልሣ አንሰራራች። የሚፈራትን ህይወት ጨከነባት።

አብነት መንገሻ በዚያች እለት የወደቀችበትን ሳታውቅ የእፎይታ ምሽት አሳለፈች። በነኛ ጥቂት ሣምንታት ውስጥ ብቻ ስንቱን አየችው? ጭንቀት፤ ፍርሃት፤ ናፍቆት፤ የጨለመ ተስፋ፤ ራስን መጥላት፤ ፍቅር እንዴት ያለ ሃይል አለው?! በአንድ ጀንበር ብቻ ህይወት እንደ አደይ አበባ ፈክቶ በራላት። ራሳቸውን የሚያጠፉ ሰዎች ለአንዲት ጀንበር መታገስ ችለው ከአዲሷ ጀንበር ጋር የሚወለደው ቀን ምናልባት በህይወት ለመኖር የሚያጓጓ ገፀ-በረከትን ያመጣልናል ብለው አለማሰባቸው ደነቃት።

ለርሷ ግን ልቧ ውስጥ የተሰነቀረችው ትንሽ የፍቅር ትንታግ እለት ተለት እየጋመች መላ ህይወቷን አፈካችላት። "ህይወት" ማለት

ቅርጉሙ "ቻርሊ" ማለት ብቻ እስኪመስላት ድረስ ከአየሩ ጋር ተነፈሰችው፣ ከፀሐይዋ ጋር ሞቀችው።

ቻርሊና አብነት እንደ ሁለት ቀያይ ድንቢጦች የፍቅርን መዝሙር በየደረሱበት እየዘመሩ አንዳቸው ለአንዳቸው ብቻ የተፈጠሩ እስኪመስል በእረፍት ቀናትና ከሥራ በኋላ የማይነጣጠሉ ሆኑ። ከዋሉበት ውለው ሠፈሯ ድረስ ሸኝቷት ሲመለስ ከእርሱ መለየቱን ትጠላው ጀመር። ነጣጥሎ የሚያሳድራቸውን ፍቅር የማያውቅ ጨካኝ ጨለማ እየረገመች፣ ለእይታዋ እስኪሰወር ድረስ በዐይኖቿ መንገዱን አሻግራ ትሸኘዋለች።

በነዚያ ከማር በጣፈጡ ጥቂት ቀናት ውስጥ ያስጨንቃትና ያሰጋት የነበረ አንድ ነገር፣ የወ/ሮ ሁሉግርጌሽ አብዝቶ ወደ ወላጆቿ ቤት መመላለስ ነበር። ይህን በደስታዋ ውስጥ የተሰነቀረ ሳንካ ስታስብ ለአጭር ጊዜ ትሸበርና ወዲያው ደግሞ የሚመጣውን ሁሉ በቆራጥነት ለመጋፈጥ ከራሷ ጋር ትማማላለች።



# ምዕራፍ ስባት

አብነት ቻርሊን ከሰአሊው እኅቷ ጋር ልታስተዋውቀው ወሰነች። በርሷና በሰዓሊው መካከል ድብብቆሽ የለም። እናም የመጀመሪያውን ፍቅሯን ከርሱ የምትደብቅበት ምክንያት አልነበረም። "አብነትዬ ወደ ሞትና ወደ ህይወት በሚወስድ መንታ መንገድ ላይ መቆምሽ ይሰማኛል..." ያላትን እያስታወሰች፣ ወደ ህይወት የሚያመራውን ጎዳና መምረጧን ልታረጋግጥለት እጅግ ጓጉታለች።

የአንደኛ ደረጃ ተማሪ ሳለች ብዙውን ጊዜዋን የምታሳልፈው በሰአሊው ቤት ነበር። ነገረሥራው የሚያስገርም ፍጥረት ነው። አጭር ሆኖ ከሰውነቱ ደልደል ይላል። በራው ከመሀል ግምባሩ በመነሣት እናቱን አቋርጦ ማጅራቱ ደርሷል። ከጆሮው በላይ ግራና ቀኝ ሽበት የተዘራበት ጎፈሬው በወር አንድ ቀን እንኳን ለመበጠሩ ያጠራጥራል።

እቤቷ በመጣ ቁጥር ሁለት እጆቹን ካፖርት ኪሶቹ ውስጥ ሸጉጦ ትናንሽና አስተዋይ ዐይኖቹን እያርገበገበ አስቂኝ ቀልዶች በማውራት ቤተሰቡን ሁሉ በሣቅ ሲያንፈረፍር፣ ህይወት ያሸለበችበት የሚመስለውን ቀዝቃዛ ቤት እንዲያደምቅ ከሰማይ የወረደ ኮሚክ ይመስላት ነበር። ቤተሰቡ በሙሉ በሌለበት "ጅምር አብድ" ስለሚለው እናቷ የወንድማቸው መሰደብ ይቆረቁራቸው እንደነበር ታስታውሳለች።

እቤቱ በሄደች ቁጥር አንዳች የደስታ ስሜት እየፈነቀለው ትናንሽ ዐይኖቹን በደስታ እያቁለጨለጨ "ቀይዋ ድንቢጥ!" ብሎ በመጮህ ፣ በሁለቱም ብብቶቿ ስር እጆቹን አስገብቶ ወደላይ ያነሳትና ከደረቱ ላይ ለጥፎ በዝምታ ያስተውላታል። እሷ ግን በጆ ብላ ደረቱ ላይ አትረጋለትም። ባላት ሃይል ሁሉ በመንፈራገጥ ለማምለጥ ትታገላለች። ትግሉ ሲሰለቸው በርጋታ ከደረቱ አውርዶ ዘወትር እሚቀመጥበት ሶፋ ላይ ያስቀምጣትና እጆቹን ኪሱ ከቶ መንጎራደድ ይጀምራል።

ሰዓሊው የሚኖርበት ቤት ሰስት ክፍሎች ያሉት ሲሆን አንዱ የእንግዳ መቀበያ፣ አንዱ መኝታ ቤት፣ ሌላው ደግሞ የስእል መሳያ ስቱዲዮ ነው።

ስቱዲዮው ውስጥ ጠንካራ ሽፋን ያላቸው በርካታ መጻህፍት ተበታትነው፣ ስእል የተሠራባቸው የፋይዚት እንጨት ቁርጥራጮች እዚህም እዚያም የአቧራ ልብሳቸውን እንደለበሱ ወዳድቀው፣ ባዶ የቪኖ ጠርሙሶች በየስርቻው ተንከባለው ስትመለከት የሰዓሊው ህይወት

ምስቅልቅልነት ያሳዝናታል። የሲጋራው ጪስ፣ የቪኖው የአቧራውና የቀለሙ ሽታ በአንድነት ተቀላቅለውም ይህ ነው የማይባል ጠረን ስለሚፈጥሩ መተንፈስ እስኪሳናት ድረስ ትቸገር ነበር።

ሰዓሊው ወንበር ላይ ተቀምጣ፣ እርሱ ሲጋራውን በላይ በላዩ እየለኮሰና አቧራ የለበሱ ስእሎቹን እየጠረገ አንዴ ቀረብ ሌላ ጊዜም ደግሞ ራቅ በማድረግ በፍቅር ሲያስተውላቸው፣ በንቀት ሲያሾፍባቸውና በጥላቻ ሲወረውራቸው መመልከቱ ለርሷ ድንቅ ተውኔት የመመልከት ያክል ነበረ።

የሰዓሊው መንፈስ ውሉን ሊጨብጠው ባልቻለ ጥልቅ ሀሳብ እንደተወጠረ ትገምታለች። አንዳንዴም ተንበርክኮ ጭንቅላቱን ጭኖቹ ውስጥ በመቅበር ተንሰቅስቆ ያለቅሳል። እንደዚያ በሚሆንበት ጊዜ ልቧ ደረቷ ውስጥ ትወራጭና እንባዋ መፍሰስ ይጀምራል።

"... የህልውናችንን ምክንያት፣ የህይወታችንን ዓላማና ግብ፣ የከስመታችንን ምንነት እንኳን ለመለየት ያልታደልን ምስኪን ፍጡራን..." ይሄ ነበር የዘወትር እሮሮው። "...ለተፈጥሮ፣ ለህይወት፣ ለውብትና ለእውነት ትርጉም መስጠት ሳንችል፣ እድሜያችንን በከሲብ እየተንፏቀቅን የምንባክንበት ጎስቋሎች..." እልሁና በዐይኖቹ ውስጥ የሚነደው የቁጭት እሳት አሁን ድረስ ይታያታል።

የስእልን ጥበብ ፈረንሳይ ውስጥ በመማሩ "ይሄ የፈረንሳዮች ጅምር እብድ" እያሉ የሚዘልፉት አባቷ እንኳን ባያደንቁትም ያከብሩታል። ከሰዎች ጋር ያለውን ቅርበት ወስና የብቻውን ዓለም ፈጥሮ የሚኖር ጥበብ አምላኪ ሰው ነበር።

እያደገች በሄደች ቁጥር ከሰዓሊው ጋር የነበራት መቀራረብ እየጠበቀና ግንኙነታቸውም እየጠና ሄደ። በነዚያ ዓመታት ያነበባቸውን መጻህፍት ሲተርክላት፣ ስለ ሥነ-ጥበብ ሰዎች ሲነግራትና የእንግሊዝ ቋንቋ ሲያስጠናት እንዳችም የመሰልቸት መንፈስ አይታይበትም ነበር። ከመጻህፍት ጋር ያቀራኛትም እርሱ ነው። እርሷም በበኩሏ ቤቱን በማፅዳዳት፣ የስእል ሥራዎቹን በመልክ በመልካቸው በማደራጀት ኑሮው ሥርዓት እንዲይዝ ትጥር ነበር።

ሰዓሊው በአዲስ አበባ ሥነጥበብ ትምህርት ቤት መምህር ስለሆነ አብነትም እንደርሱ ሰዓሊ የመሆን ብርቱ ምኞት ስለነበራት ስእል ት/ቤት እንዲያስገባት ብዙ ትወተውተው ነበር። አንዴ በተለመደው ጥያቄዋ ስትወጥረው እንዲህ አላት። "... ገና ከልጅነትሽ ጀምሮ በዚህ የጥበብ መስመር ስላለሽ የተፈጥሮ ስጦታ ሳጠናሽ ነበር



የኖርኩት። እውነቱን ማወቅ ከፈለግሽ ሰዓሊ መሆን አትችይም። ቀልብሽ ለቀለም ትንግርት አይደነግጥም፣ ዐይንሽም በቀለም ውብት አይሳብም። ባጭሩ ሁለመናሽ ለቀለም ሚስጥር ደደብ ነው!" አላት። አብነት ደደብ በመባሏ ሲከፋት ሲያይ ግን "... የምትሞክሪያቸውን ግጥሞችና ድርሰቶችሽን ስመረምር ምናልባት ጥሪና ተልእኮሽ በሥነ ጽሑፍ መስክ ሊሆን እንደሚችል እገምታለሁ" በማለት አጽናናት።

አብነት አንድ ቅዳሜ ከቀትር በኋላ ቻርሊን ይዛ ወደ ሰዓሊው ቤት ሄደች። በቅሎ ቤት ተብሎ በሚጠራው ሰፈር አካባቢ ሲቃረቡ ነበር ከታክሲው ወርደው በስተግራ በኩል ቀጭኑን የአስፋልት መንገድ ይዘው ያሸቀለቀሉት። ሰዓሊው በተለመደው ቡላ ካፖርቱ ውስጥ ተጀቡኖ እጆቹን ኪሱ ውስጥ እንደሸጎጠ በግቢው ውስጥ ሲንጎራደድ አገኙት።

እንደ ቀድሞው "ቀይዋ ድንቢጥ!" እያለ ጮሆ አልተቀበላትም። በቀዘቀዙ ዐይኖቹ አንዴ አብነትን፣ ሌላ ጊዜ ቻርሊን በመገረም ሲመለከት ቆየና "እንኳን ደህና መጣችሁ!" በማለት ሁለቱንም ጨበጣቸው። ገጹ እንደጨፈገገ ነበር።

አብነት ነፍሷን እየተሻሙ ያሉትን ሁለት ተቃራኒዎች ካስተዋወቀች በኋላ አጎቷ ግንባር ላይ ደም በማየቷ "ጋሼ ግንባርህን ምን ሜረህ?!" ስትል በድንጋጤ ጮኸች።

እጆቹን ከኪሱ አውጥቶ "መኪናዬን አታያትም" አለና ወደ አሮጌዋ ቦክስዋገን በጣቱ አመለከታት። የፊት መስተዋቷ በሙሉ ረግፏል።" እንዴ?! ምንድነው ጉዱ ጋሼዬ? አደጋ ደረሰብህ እንዴ?!" በማለት እየጮኸች ጠየቀችው።

ሰዓሊው ትከሻውን ሰበቀና "ጊዜው በእያንዳንዱ ሰከንድ አደጋ ባናታችን ላይ የሚያንዣብብበት፣ እያንዳንዱ ሰው ሞትን አፍንጫው ላይ አንጠልጥሎ የሚዞርባት ጊዜ መሆኑን ዘነጋሽው?!" አለና ቻርሊን ሰረቅ አድርጎ ተመለከተው። ጥላቻው ፊቱ ላይ በግልፅ ይነበባል።

"እኮ መኪናህ ምን ሆነች?!"

"የጠዋቶቹ ተማሪ ሰልፈኞች በድንጋይ አደቀቋት። ህዝብ በአንድነት ያበደበትን ጊዜ በኔ እድሜ ከዚህ ቀደም አላየሁም። የኔ መኪና በድንጋይ በተወገረች፣ ሱቆች በተደበደቡ፣ የህንፃ መስታዋቶች በተሰበሩ የሚገኘው ጥቅም ምን እንደሆነ አይገባኝም" አብነት ከልቡ ማዘኑንና መበሳጨቱን አስተዋለች።

ወዲያው ግን ወደ ቤት እየመራ አስገባቸውና እንግዳ መቀበያው ክፍል ውስጥ በአረጀት የሶፋ ወንበሮች ላይ ተቀመጡ። ሰዓሊው ብስጭቱ አልበረደለትም ነበር። "በሀገሬ ሰማይ ላይ ሞት እንደዚህ ጥላውን ያጠላበትና ምድር ራሷ ደም ደም የተነፈገችበት ጊዜ አላየሁም፣ በየመአዘኑ ጨለማ!" አለ። የተናገረው ለነአብነት ይሁን ለራሱ በውል አላወቀውም።

"አትጨነቅ ወንድም፣ ከጨለማው ባሻገር የጭቁን ህዝቦች ብራ ቀን እንደሚወጣ ሞት ባረበበበት ሰማይ ላይ የህዝቦችን ብሩህ ተስፋ አንድ ቀን እንደምታይ አትጠርጥር" አለው ቻርሊ የአገጩን ጢም እያፍተለተለ።

ሰዓሊው በመገረም ሲመለከተው ቆየና "በደም ባህር ከተዘፈቁና ከእልቂት በኋላ የሚመጣ ብራ ቀን አይኖርም። ወንድም፣ ከፍጅት በኋላ የሚመጣው ቀን የፈራረሱ ጎጆዎችና ምድር ሙሉ የምስኪኖችን በድን የሚያስታቅፈን ጨለማ ቀን ነው። ይሄ የምትለው የማይጨበጥ ተስፋ የኮሚኒስቶች መሸንገያ ነው!" አለው የሶፋውን ጠረጴዛ እየደበደበ።

"ጦርነቱ ተጀመረ!" አለች አብነት በሃሳቧ። ሁለቱ ተቃራኒ አመለካከት ያላቸው ሰዎች ለፍልሚያ ሲዘጋጁ የሰነበቱ ይመስል ገና ከመገናኘታቸው ፍልሚያውን መጀመራቸው አስደነገጣት። ሰዓሊው ስለሚናገረው ነገር ግድ የሌለውና ቻርሊም ግትር መሆኑን ስለምታውቅ ንትርካቸው ወዴት እንደሚያመራ በመገመቷ ሰጋች።

"ኮምኒስቶች ከማንም ይበልጥ የሰው ልጅ ደህንነት ጠበቆች፣ የሽብርና የእልቂት ተቃዋሚዎች መሆናቸውን አታውቅም?!" አለ ቻርሊ በሰዓሊው ንግግር እየተቆጨ።

ሰዓሊው ፍቅፍቅ ብሎ መሳቅ ጀመረ። አብነት የምታደርገው ጠፍቷት ግራ ተጋባች። "አምላኬ፣ እባክህ እርዳኝ። ምን ሲያቀብጠኝ ነው እነዚህ ሰዎች እንዲገናኙ ያደረግኩት!" እያለችም ራሷን በጸጸት ጅራፍ መግረፍ ቀጠለች።

"... እኮ በስንተኛው ክፍለ ዘመን?! በየትኛው የዓለም ክፍል?! ከታሪክ እንዳነበብኩት ኮምኒስቶች ከረገጡት ምድር በላይና ቀይ ባንዲራቸው ከተውለበለበበት ሰማይ በታች የሚታይ ነገር ቢኖር የህያዋን ደም ብቻ ነው" አለ ሰዓሊው በርግጠኝነት።



"ጌታው ያለ መስዋእትነትክ የሚገኝ ድል የለም። ህዝቦችን በባርነት ከሚገዙና ደማቸውን ከሚጠጡ ጨቋኞች ደግሞ በልመና ነፃነትን መቀዳጀት ስለማይቻል ኮሚኒስቶች ደማቸውን በየትግሉ መስክ ማፍሰሳቸው እውነት ነው። ይሁን እንጂ ይህን እንደጠቦት ደም የሚረጭ የደጋጎች ደም አሸዋ ጠጥቶትና አየሩን አከርፍቶት የሚቀር እንዳይመስልህ። ለእልፍ አእላፍ ድሆች ነፃነት የተከፈለ ዋጋ በመሆኑ አንድ ቀን የህዝቦችን ብሩህ ቀን ይዞ ይመጣል። ይህን ደግሞ ታሪክ ደጋግሞ አሳይቶናል..."

ሰዓሊው አላስጨረሰውም። "ይህንን ታሪክ አትበለኝ! በጎሰቋሎች ደም የተጨማለቀ ታሪክ ታሪክነቱ የህዝቦችን ደም አንጠፍጥፈው እየላሱ ለደለቡ ኮሚኒስቶች እንጂ ለሌሎች ታሪክ አይደለም። እና ጀብድ ሆኖ አያስፎክርም" ሰዓሊው ይህን ሲናገር በቁጭት እየተንጨረጨረ ነበር።

"ኮምኒዝም ወፈፌነቱን የሚጀምረው ሰብአዊውን ፍጡር በመደብ በመሸንሸን ለአንድ ሀገር እድገት መሠረት የሆኑትን የምርት ማመንጫና መገልገያ መሣሪያዎችን በመዝረፍ በጋራ ባለቤትነት እንዲያዙ ሲያደርግ ነው። አስተውል! ይህ አስተሳሰብ በቅድሚያ የሚታገለው ግለኛ የሆነውን የሰው ልጅ ተፈጥሯዊ ባህሪ ነው። ኮምኒዝም ጨርቁን ጥሎ የሚያብደው ደግሞ ይሄን ጠንባራ ዓላማውን ከግብ ለማድረስ በአሸባሪነትና በወረራ የህዝቦችን ሰላም በማደፍረስ ክቡር የሆነውን ሰብአዊ ፍጡር መጨፍጨፍ ሲጀምር ነው" አለ ሰዓሊው እልህ እየተናነቀው።

"ወዳጄ፣ ስለ ኮምኒዝም ከዚህ የከፉ ዘለፋዎችና ትችቶች ተሰንዝረዋል። ከዚያም አልፎ እንደ ጥጃ ሲታሰሩና ሲፈቱኖረዋል፣ በፈላ ዘይት ተቀቅለው፣ በኤሌትሪክ ተጠብሰዋል። ይሁንና ኮምኒስቶች ይሄን ሁሉ መስዋእትነት መክፈል ቢገደዱም ግባቸውን መቀዳጀታቸው አይቀርም። ለምን? የያዙት ዓላማ የህዝብ አላማ ነውና! የያዙት እውነት የህዝብ እውነት ነውና!" ቻርሊ ሙግቱን ሲጀምር አሁንም ሰዓሊው ጣልቃ ገብቶ አቋረጠው።

"የህዝብ እውነት አትበለኝ! አንድ ነገር ላረጋግጥልህ። በምእራብም፣ በምሥራቁም ዓለም፤ በየትኛውም አገር ፖለቲካ ውስጥ "እውነት" የሚባል ነገር የለም። ቃሉን ለምን ታረክሰዋለህ?! ይህ "የህዝቦች እውነት" የምትለው ቀልድ የሚወለደው በፖለቲከኞች ጭንቅላት ውስጥ ብቻ ስለሆነ አልቀበለውም!..."

"ጋሼ፣ እንግዳ ቤትህ ሲመጣ የምታስተናግደው በዚህ ዓይነት ነው?!" አለች አብነት የንትርኩን ውጥረት ለማርገብ።

ሰዓሊው መደናገጡ ፊቱ ላይ እየታወቀበት "አ! ትልቅ ይቅርታ አብነት፣ ትልቅ ይቅርታ! አንተም ይቅርታ የኔ ወንድም። ከአብነት ጋር በመምጣትህ እንግዳ መሆንህም ተዘንጋኝ። ስህተቱ እንኳን የኔ ብቻ ሳይሆን እንግዳ ይመስል እጅና እግርሽን አጣጥፈሽ የተቀመጥሽው ያንችም ነው"። አላት ግሳጼ በተቀላቀለበት አንደበት። "የኤሌትሪኩን ምድጃ ለኩሰሽ መክሰስ ብጤ አዘጋጂልን። የምትፈልጊው ሁሉ እዚያው አለልሽ። እኔ ደግሞ የሚጠጣ ነገር ልግዛ። ተጫወቱ" አለና ሰፋው ሥር ተቀምጦ የነበረ አነስተኛ የመንገድ ቦርሳ አንጠልጥሎ እያፏጨ ወጣ።

አብነት ቻርሊን ቀና ብላ ስታየው በሃሳብ ጭልጥ ብሎ ሄዷል። ሀሳቡ ከሰዓሊው ጋር ሲያደርግ በነበረው ክርክር መመሰጡን ገመተች። "ቻርሊ፣ ጋሼ በተናገረው ተቀየምክ እንዴ?" ስትልም ጠየቀችው። ከሃሳቡ እንደነቃ ራሱን ነቀነቀና "ለምን?! ኮምኒዝምን የሚነቅፉ ሰዎች ከሚናገሩት ከአሥር አንዱ'ኮ እውነት ነው።... ነቀፌታቸውን ማዳመጡ ደግሞ የኮምኒዝምን ድክመቶች እንድንረዳና ተግባራችንን እንድንመረምር ይረዳናል" አላት በፈገግታ።

"ቻርሊ፣ አንተ ግን ለምን ኮምኒስት ሆንክ?"

"አየሽ በሰዎች ሁሉ ገጽታ ላይ ብሩህ ፈገግታ ማየትን እመኛለሁ። ስለዚህም ለሰዎች ያለኝ ፍቅር ነው ኮምኒዝምን እንድወድ ያስገደደኝ"

"ኮምኒስቶችንና ተግባራቸውን ስትመለከትስ በሰዎች ላይ ማየት የምትመኘውን ፈገግታ ሊያመጡ እንደሚችሉ ታምናለህ?"

"አብነት፣ እውነቱን ለማወቅ ከፈለግሽ ሁሉም ነገር ተመሰቃቅሎብኛል። ኮምኒዝም'ኮ የብዙ ጨካኝ ገዥዎች መጠቀሚያ ርዕዮተ ዓለም ሆኗል። ሁሉም በበጎ ዓላማ ላይ ያነጣጠረ እምነት መሆኑን በማየት ያጭበረብርበታል። ይሄ ግራ ያጋባኛል። በርዕዮተ ዓለምነቱ ግን አሁንም የማልፍለት ዓለማ ነው።"

አብነት ግራ የተጋባ ስሜቱን ተመልክታ ከልቧ አዘነችለት። "ቻርሊ እኔ የሚቀመስ ነገር እስከዘጋጅ ድረስ ለምን የስእል ሥራዎቹን አትመለከትም?!" በማለት የአጎቷን ሥራዎች እንዲመለከት ጋበዘችው።

ቻርሊ በማጨስ ላይ የነበረውን ሲጋራ መተርኮሻው ውስጥ ደፈጠጠና አብነትን ተከትሎ ወደ ሚቀጥለው ክፍል ሄደ። ጠቢብ



ያለችው ስቱድዮ ያልያዘችው ቅራቅንቦ የለም። መጻህፍት፣ የወዳደቁ ፋይዚቶች፣ መለስተኛ ጠረጴዛ፣ በየማእዘኑ የተወጠሩ ጨርቆች፣ የቀለም ብልቃጦችና ቡርሾች...

መስኮቶቹን በርግዳ ንጹህ አየርና ብርሃን እንዲገባ ካደረገች በኋላ በሥርዓት የደረደረቻቸውን በፋይዚት፣ በካርድና በወረቀቶች ላይ የተሠሩ በርካታ የስእል ሥራዎች ወደ ጠረጴዛው በማምጣት እንዲመለከታቸው ሰጠችው። ቻርሊ ስእሎቹን አንድ በአንድ እያነሳ መመልከት ሲጀምርም አብነት ጥላው ሄደች።

ይሁንና ሥራዎቹን እያገላበጠ ቢያፈጥባቸውም ቅርጻቸውንም ሆነ ማስተላለፍ የሚፈልጉትን መልእክት ሊገነዘብ አልቻለም። ሁልጊዜም በአብስትራክት ሥራዎች ተልእኮ እንደተገረመ ነው።

ጥቂት እንደቆየ አብነት ተመልሳ መጣችና "ሥራዎቹ እንዴት ናቸው?" ስትል ጠየቀችው፤ በጀርባው ላይ ተንጠራርታ በጁ የያዘውን ስእል እየተመለከተች።

"አብዛኞቹን ሥራዎች በየትኛው አቅጣጫ መመልከት እንዳለብኝ እንኳን አልተረዳሁም" አላት በራሱ ላይ እየሳቀ። በግልጽነቱና አሳዋቂነቱን ለመሸፈን ባለመሞከሩ ከልቧ እያደነቀችው ቀደም ሲል ከሰዓሊው ጋር የተወያየችባቸውን ሥራዎች አብራራችለት። ቀጥሎም "ዘር" የተሰኘውን ሥውር ያልሆነ ሥራ ለመመልከት ሲያነሳ የስእሉን ሃሣብ ራሱ እንዲመረምረው ትታው ወደ ሥራዋ ሄደች።

የእንቁላል ሳንድዊቾች አዘጋጅታ እንዳበቃችም እጇን ታጥባ በፎጣ እያደረቀች ወደ ስቱዲዮው አመራች። ቻርሊ በዚያው ስእል ላይ እንደተመሰጠ ስለአገኘችው ተገረመች "ቻርሊ፣ ይህንን ስእል ወደድከው እንዴ?" ስትልም ጠየቀችው። አልመለሰላትም።

ዐይኖቹ ስእሉ ላይ ቢያፈጡም እየተመለከተው እንዳልሆነ ተገነዘበች። አንዳች መንፈስ ነፍሱን እየተቆጣጠራት እንዳለ ሁሉ የፈጠጡት ዐይኖቹ እግረ ህሊናውን ተከትለው ኮብልለዋል። ትከሻውን እየነቀነቀች "ቻርሊ ምነው?" አለችው።

ከሄደበት ለመመለስ የፈጀበት ጊዜ ረዥም ነበረ። "ስለዚህ ስእል ልታብረጅኝ ትችያለሽ?" አላት ገና ከእንቅልፉ እንደነቃ ሰው ሆኖ። ከሰዓሊው ጋር ብዙ ጊዜ የተወያየችበት በመሆኑ ሃሳቡን ለማብራራት አልተቸገረችም። "እ... እዚህ ላይ ያው በሌጣ ትርጉሙ እንደምታየው ገበሬው ዘሩን በእጆቹ ዘግኖ ቁልቁል ሲበትን ዐይኑ ግን

ሽቅብ ደመናው ላይ ነው - ተስፋ! ዐይኖቹን ልብ ብለህ ብታስተውላቸው ተስፋን ብቻ የተማመኑ ባዶ ዐይኖች አይደሉም። እምነት ይጎላባቸዋል፤ ርግጠኝነት ያይልባቸዋል። ሰማዩ ላይ የተንጠለጠለው ደመና አንድ ቀን ዝናብ ሆኖ እንደሚወርድ፣ ከአጥንቶቹ ላቡን ጨምቆ ያለሰለሰውን ማሳና፣ ከጥሪቱ አጊጦ የዘራውን ዘር በቀለም እልባ ቀለሙ እንደሚያቀልመው፣ የበቀለውም እንደሚያሸት፣ ያሸተውም እንደሚያፈራ እምነት አለው። የወዙ ሙጣጭ እንደማይመክን፣ ድካሙ ከንቱ እንደማይቀር ተማምኗል"

በገለፃዋ የሰአሊው ፎቶ ኮፒ የሆነች ያህል እየተሰማት ቀጠለች። "እንደ ምታውቀው ዘር የትውልድ ምሳሌ ነው። አያቶቻችን ልጆቻቸው እነርሱኑ መስለው፤ እምነታቸውን፣ ባህላቸውን፣ አኗኗራቸውን፣ ቋንቋቸውን፣ ለተፈጥሮና ለህይወት ያላቸውን ከእድሜ የተካበተ ልምድ ይዘው እንደሚበቅሉ፣ እንደሚያሸቱና እንደሚያፈሩ ተስፋና እምነት አላቸው። አባቶቻችን በኛ ላይ፣ እኛም በልጆቻችን ላይ የሚኖረን ተስፋና እምነት ይሄው ነው። የህይወት ፈርጅ ሳይዛነፍ እንዲቀጥል" ስትል ገለፃዋን አጠናቀቀች።

ቻርሊ ፈዟል። ዐይኖቹን ተስፋ ባዘሉት የገበሬው ዐይኖች ውስጥ አስርጎ በውስጣቸው ጠፍቷል። ስእሉ በህይወቱ ውስጥ እንዳች ትርጉም እንዳለው የጠረጠረችው አብነት "ቻርሊ ደከመህ?" ስትል ጠየቀችው። ስእሉን በዘግታ ጠረጴዛው ላይ አስቀምጦ በረኛው ሲቆነፍስ ሰዓሊው ገርበብ ያለውን የሳሎን በር ከፍቶ ገባ። እነ ቻርሊም ከስቱዲዮው ወጥተው ተቀላቀሉት።

በቦርሳው ያመጣውን የቢራና የለስላሳ መጠጥ ጠርሙሶች ጠረጴዛ ላይ እየደረደረ "ብዙ እንዳልቆየሁ ተስፋ አለኝ... ከተማው አሁንም በአመጽኞችና በወታደሮች እየታመሰ መሆኑን ሰማሁ..." አላቸው። አብነት የጀመሩት አታካሮ ይቀጥላል ብላ ስለሰጋች ያዘጋጀችውን ሳንድዊች በፍጥነት አቀራርባ ለነርሱ ቢራ ለራሷ ለስላሳ ቀዳች።

የቀድሞውን ውይይት አቅጣጫ መቀየር ስለነበረባት "ቻርሊ ሥራዎችህን ሊረዳልህ አልቻለም። "ዘር" ከሚለው ሥራ በስተቀር ሌሎቹን በየትኛው አቅጣጫ እንኳን ማየት እንዳለበት አላወቀም" አለችው አጎቷን። ሰዓሊው ከትከት ብሎ ሲስቅ ቻርሊ ምግቡን እያላመጠ አቀርቅሮ ቀረ።



"አለመታደል ሆኖ ሥራዎቼን ሰዎች ሊረዱልኝ አይችሉም። ጓደኛሽም ሊረዳልኝ ባለመቻሉ አልደነቅም" አለ ሰዓሊው ቢራውን ተጎንጭቶ አፉን እየጠራረገ።

"የሥነ-ጥበብ ፋይዳም ዜሮ የሚሆነው እዚህ ላይ ነው። በጠቢቡና ጥበቡ በቀረበለት ሕዝብ መካከል ሊኖር የሚገባው የመግባቢያ ድልድይ ከተናደ የጠቢቡ ጥበብ ባከኗል። የጥበብ ሥራው ከማህበረሰቡ የአኗኗር ልምድ፣ ስነ-ልቦናዊ አመለካከትና ባህል ስለሚያፈነግጥ ተመልካች እንጂ ተርጓሚ፣ አፍጣጭ እንጂ አድናቂ አይኖረውም" አለ ቻርሊ ያለይሉኝታ። አብነት ሰዓሊው ይናደዳል ብላ ጠብቃ ነበር። የተገባቢጦሽ እግሩን እያነሳ ከጣራ በላይ መሳቅ ሲጀምር በሁፍረት ተሸማቀቀች።

"እንዴት ያለሽው ጡንቻ ራስ ነህ እባክህ?! ቀድሞ ነገር የከያኒ ድካም መች ተርጓሚና አድናቂ ማግኘት ሆነና?! አየህ የእውነተኛ ጠቢብ ህልሙ፤ ለሥራዎቹ ትርጉም የሚሰጡ ደቀመዛሙርት ወይም በቀለሙ ድምቀት የሚፈዙ አድናቂዎችን ማፍራት አይደለም።

"እንዲህ ዓይነቱ ከያኒ ብሩሹን ቀለም ባጠቀሰ ቁጥር የሚታየው የተፈጥሮ እውነታ፣ የህይወት ምንነት ሚስጥር ሳይሆን የአድናቂዎቹ በግርምት የፈጠጡ ዐይኖችና የተርጓሚዎቹ ምናብ አድማስ ብቻ ይሆናል። እዚህ ቦታ ላይ ጠቢቡ ከራሱ እምነት ይርቃል፤ ከእውነታ ይሸሻል። ከያኒ ከማህበረሰቡ ባህል፣ ስነልቦናዊ አመለካከትና ከፖለቲካዊ ተጽእኖ ውጭ በራሱ ዓለም ውስጥ ለእውነታ፣ ለህይወት ፣ ለራሱና ለብሩሹ ታማኝ ሆኖ መቆም አለበት" አለው ሰዓሊው በትናንሽና ብልጣብልጥ ዐይኖቹ እያሸሟጠጠው።

ቻርሊ ግንባሩን ቅጭም አድርጎ ሲያዳምጠው ቆየና በብርጭቆ ከሞላው ቢራ ተጎነጨለት። አብነት ብሽቀቱን እያጠበበት እንደሆነ ተረዳችና ፈገግ አለች።

ብርጭቆውን በሁለት እጆቹ መሀል እያሽከረከረም "የምትለው ሁሉ እውነት አይደለም። እኔ የሥነ-ጥበብን ዋጋ የምመዝነው ለማህበረሰቡ ንቃት በሚሰጠው ፋይዳ ብቻ ነው። የማኀበረሰቡን ጅሮ የማይኮረኩር፣ ቀልቡን የማይስብና ዐይኑን የማይወጋ ጥበብ፣ ጥበብ ነው ብትለኝ እንኳን ጥበብነቱ ለጠቢቡ ብቻ እንጂ የህዝብ ቁብ አይደለም" አለና ተጋፈጠው።

ጦርነቱ በዚህ መልክ ይዞቱን ለውጠ ቀጠለ። እነርሱ በእልህና በንዴት እየጦፉ በነገር ጥይት ሲጠዛጠዙ፣ አብነት በየትኛውም ደቂቃ በቡጢ ሊቀጣቀጡና በቢራ ጠርሙስ ሊፈራከሱ ይችላሉ እንዳለች የመሄጃቸው ሰዓት ስለተቃረበ ለመሰነባበት ተነሱ።

ሰዓሊው ውጭው በር ድረስ ሲሸኛቸው የቻርሊን እጅ እንደጨበጠ እንዲህ አለው። "በህዝቦቿ ደም ከቅኝ ገዢዎች መንጋጋ የተተፋችው አፍሪካ ገና የዲሞክራሲ ጀንበር ሲፈነጥቅባት፣ በኮምኒዝም ስም በየማእዘኑ በወታደራዊ አምባገነኖች ጫማ እየተረገጠች መድማቷ ያሳዝነኛል። የሀገሬ እጣም ከዚሁ አላለፈም። አዝናለሁ። ለዚህ ምስኪን ህዝብና ለዚች ላልታደለች ሀገር አዝናለሁ። ህዝቡ ለአንዲት ጀንበር የነፃነት አየር ለመተንፈስና ለአንዲት ቀን እንኳን ጠግቦ ለማደር አልታደለም። ሀገሪቱ የልጆቿን ደም እየጠጣች ወልዳ ለመብላት እንጂ አሳድጋ ለወግ ለማድረስ አልቻለችም። አንዳንድ ጊዜ ሳስበው ተረግማ ይሆን? እያልኩ እጨነቃለሁ።

"የህዝቡ እጅ አመድ አፋሽ ነው። የታሠረበትን የእጁን ገመድ በጥሶ አንዱን ሥርዓት ሲሰብር ቀጣዩ ሥርዓት የብረት ሰንሰለት ያጠልቅለታል። በትግሉና በደሙ የሰንሰለቱን ቀለበቶች ፈልቅቆ ነፃ ህዝብ ነኝ ብሎ ሲዘምር፣ ሌላኛው ሥርዓት የእግረሙቅ ገፀ-በረከቱን እንጠልጥሎ ከተፍ ይላል። የህዝባችን እጣ ይሄው ነው። ሲነጋ ሲል እየጨለመበት፣ ሊነሳ ሲል እየጠለፉት፣ ሊጎርስ ሲል እየነጠቁት፣ ከባርነት ወደ ባርነት ተቀባበሉት። ከጨለማ ወደ ጨለማ ነዱት።"

አብነት ሰዓሊው ሞቅ ሳይለው እንዳልቀረ ገመተች። ቻርሊ በመገረም ከማፍጠጥ ሌላ የሚናገረው አልነበረውም። ሰዓሊው ፍጹም ተስፋ የቆረጠ ይመስላል።

"እና አርቲስት ኮምኒስት፣ በኮምኒዝም የምትመኘውን ብሩህ ቀን በእድሜህ እንዳትጠብቀው" አለና እጁን እየወዘወዘ በመጨበጥ ተሰናበተው።

አብነት ወደ ኋላ ቀረት ብላ የሰዓሊውን እጅ እንደያዘች የኩክሹክታ ያህል "ጋሼዬ፤ ወደ ሞትና ወደ ህይወት ከሚያመራው መንታ መንገድ የህይወትን ጎዳና የመረጥኩ አይመስልህም?" አለችው ዐይን ዐይኑን በመመልከት።

በሰከንዶች ክፍልፋይ ፍጥነት ዐይኖቹ ውስጥ የመሸነፍ፣ ተስፋ የመቁረጥና የመታከት ስሜት ሲያንጸባርቅ ተመልክታ፣ ተስፋ እንደቆረጠባት ገመተችና ደነገጠች። ሰዓሊው እጇን እንደያዘ ጠልቀው



በሚያዩት ዐይኖቹ በርህራሄ ሲመለከታት ቆየና "ድንቢጥየ፣ እግዚአብሔር ከአንቺ ጋር ይሁን!" አላት። ዳግም በመንፈስ እንደ እንደማይሆን የተነበየ ያህል ዐይኖቹ ለአፍታ የእንባ ዘለላዎች አንጠለጠሉ። ...ዘለላዎቹ ከመውደቃቸው በፊትም ፎርባውን አዙሮ እየተጣደፈ ወደ ቤቱ ገባና በሩን በዝግታ ዘጋው።

ሰኔ ግም አለ። ሰማዩ በነጭ ወፍራም ደመና ተሸፍኗል። ክረምቱ ፊቱን ካጨፈገገው ሰማይ በታች እያፏጨ በሚያልፈው ቀዝቃዛ አየር "ገባሁ" እያለ ያስፈራራል። እንደ ቅዝቃዜውና እንደ ሰማዩ ኩርፊያ ግን ህይወት ደንግጣ አላሸለበችም - እንደወትሮዋ በጥይት ፍጥነት ትበራለች።

መተላለፊያው መንገድ በመንገደኛው ዝብርቅርቅ እንቅስቃሴ እንደተሞላ ነው። ሁሉም እየተጣደፉ ይሮጣሉ ... ይሄዳሉ፣ እርስ በርስ አይተያዩም ይሄዳሉ... ይሄዳሉ... ይሄዳሉ። ቆሞ ላስተዋላቸው ተማክረው ያበዱ እስኪመስሉ ድረስ በመሄድ ቀልባቸው ጠፍቷል።

አብነትና ቻርሊም ታክሲ ከመጠበቅ በእግራቸው መጓዙን ስለመረጡ የአስፋልቱን ጠርዝ በመያዝ ከትርምሱ ተቀላቅለዋል። ከበቅሎ ቤት እስከ ጎተራ ያለው መንገድ በሰው እንደተጨናነቀ ነው። ጎተራ ደርሰው በስተግራ በመታጠፍ መጓዝ ሲጀምሩ ግን ትርምሱ እየቀለለና ትፍግፍጉ እየዘረዘረ ሄደ።

አብነትን አንድ ነገር በህሊናዋ እየተመላለሰ ፋታ ነስቷታል። ቻርሊ "ዘር" የተሰኘውን ሥራ ሲመለከት ያን ያህል የተመሰጠውና መንፈሱ የተሸበረው ለምን ይሆን? ቀና ብላ አየችው። ቡዝዝ ባሉት ዐይኖቹ የሚጓዝበትን ጎዳና ባሻገር እየተመለከተ በርጋታ ይራመዳል።

"ቻርሊ፣ ቅድም 'ዘር' የሚለውን ሥራ ስትመለከት እንደዚያ የተመሰጥከው ለምንድነው?" እየፈራችና እየተባች ጠየቀችው። ለረዥም ጊዜ መልስ አልሰጣትም። በመጨረሻ ግን ለራሱ እንደሚነጋገር ዓይነት ከንፈሮቹ ሲንቃነቁ አስተዋለች "ዘር!"

ከፊቱ መጥቆርና ከሰውነቱ መወራጨት አንድ ነገር ሊነግራት እንደፈለገና መናገር የፈለገውን ነገር እንዳይናገር ግን ከውስጡ የሚታገለው ኃይል እንዳለ ስለተረዳች በፀጥታ መጓዝ ጀመረች። "አባቴ አገሬው ከእድሩ ታዛና ከሸንጎው የጥላ ስብሰብ ያራቀው የድሆች ድሃ የሆነ ምስኪን ፋቂ ነበረ..." አላት ትንፋሹን ሳግ እያፈነው።

"ትቀልዳለህ ?!" ልትለው አሰበችና ቀና ብላ ፊቱን ስታይ ገጹ በምሬትና በጥላቻ መጥቆሩን በማየቷ በዝምታ የጀመረውን እንዲጨርስ ተወችው።

"ፋቂ ታውቂያለሽ አብነት?"

"ፋቂ?! አይ አላውቅም፤ ሲባል ግን እሰማለሁ" አለች እየተጠራጠረች።

"ፋቂ የከብት ቆዳ በጨው እጅሎ፣ የቀርከሀውን ግንጣይ በጥቁር አለት ላይ ስሎ ....ከጠነባ ቆዳ ታግሎ፣ የሚኖር ፍጥረት ነው። እንደ አሳማ አለያም እንደጅብ ግልገል ጥንብ ለጥንብ ሲፍገመገም ህይወቱ የምታሽልብ የሰው አንድ አሰረኛ ሰው ነው" አላት በቁጭት እየተንጨረጨረ።

"እና አባትህ ፋቂ ነበሩ?"

"አዎን ነበረ...." በምጸት ሣቀ።

"ታድለህ!" አለችው በፍጹም ቅንነት ። ግምባሩ ቅጭም እንዳለ ዞር ብሎ ተመለከታትና "እያሾፍሽ ነው?!" ሲል ጠየቃት።

"ኧረ አላሾፍኩም.... ለምን?! የፋቂም ልጅ ሆንክ የፓይለት ለኔ ጉዳዬ አይደለም። የኔ ጉዳይ ሰው ሆነህ ከመፈጠርህ ላይ ብቻ ነው!" አለችው ፍርጥም ብላ።

ጥርጣሬ ባዘሉት ዐይኖቹ እያስተዋላት "ጆሮዎቼ የሚሰሙትን ማመን ይቸግራቸዋል አብነት... ከምን አይነት ቤተሰብ የተገኘሽ ሰው መሆንሽን ሳስበው አሁን የምትናገሪው የነፍስሽን እውነት መሆኑን መቀበል ያስቸግረኛል። ምክንያቱም 'ሰው እንደ አሰተዳደጉ ያስባል' ብዬ ስለምገምት ነው" አላት ጥርጣሬ በጎላበት ድምፅ።

"እንግዲህ ዝጋ ቻርሊ! ደግመህ ደጋግመህ የቤተሰቦቼን አስተሳሰብና እምነት በኔ ላይ አትለጥፍብኝ። የሀብታም ልጅ ስለሆንኩ ድሀንና ድህነትን መጥላት አለብኝ ማለት ነው?!"

እንደገና በዝምታ ሲዋጡ ቆዩና አሁንም ቆም ብሎ "አብነቴ? አንቺ ተርበሽ ታውቂያለሽ?" ሲል ጠየቃት።

"አልተራብኩም" አለችው በርግጠኝነት። የመንገሻ የኔነህ ልጅ ማለት ምን ማለት እንደሆን ስለማያውቅ አይፈረድበትም ስትል አሰበችና ፈገግ አለች።



"የምትለብሽው ነገር አጥተሽ በርዶሽስ ያውቃል ? ወይም ... የምትጫሚው ጫማ አጥተሽ እግሮችሽ በቀን ሀሩርና በምሽት ቁር ተቃጥለውና ተኮማትረው ያውቃሉ?"

"አይ ኧረ በጭራሽ!" አለችው የጥያቄው አቅጣጫ ወዴት እንደሚያመራ ለመገመት እየሞከረች።

በረዥሙ ተነፈሰና "ታድለሽ!" አላት። "አንቺ ድህነትን እንደጥሩ እድል ብትቆጥሪ አልፈርድብሽም። ከሰይፍ ስለት የሰላ ጥፍሩ አልቧጠጠሽም፤... ከጦር የሾሉ ጥርሶቹ አላነከሱሽም፤ ነዲድ እሳቱ አልፈጀሽም። እና አይፈረድብሽም አብነት። ተፈጥሮ ከለገሰችን በረከት ጣፋጭ ጣፋጩን እንጂ መራራዋን አልቀመስሽም። ግማሽ ህይወት እየኖርሽ በመሆኑም ድህነትን ብታሞካሺ አልፈርድብሽም" አላት። የተፀፀተም ፣ የቀናም፣ የተናደደም ፣ ተስፋ የቆረጠም ይመስላል።

"የብዙዎቻችን ችግር'ኮ ህይወትንእንዳለች መቀበል አለመቻላችን ፡ ነው። እንደሚገባኝ መንፈስ ሰባራና አልሸኞችም የምንሆነው የፍላጎታችን መጠን፣ ጣራና ድንበር ስለማይኖረው ብቻ ነው። አየህ፣ ድህነትም እንደ ሀብት ህይወት የጣለችልን እጣ ነው። ድንቁርናም እንደ እውቀት፣ በሽታም እንደ ጤንነት፣ መልከ ጥፉነትም እንደ ውበት የተፈጥሮ ድልድል ነው። ባለንና በሆነው ሁሉ ልንኮራበት እንጂ ልናማርር አይገባም" አለችው የበታችነት ስሜቱን አጥበው ሊወስዱ የሚችሉ ቃላትን በመምረጥ እየተጨነቀች።

የተጨማደደው ፊቱ በአፍታ ፈክቶ ክትክት ብሎ መሳቅ ጀመረ። እንዴት ያለው ድንቅ ፍጥረት ነው ስትል አሰበች አብነት። እለት ተለት ከነፍሷ የሚዋሃደው ነፍሱ መላ ህይወቷን ለውጦ ልዩ ፍጥረት አድርጓታል። ዐይኖቿ ጠልቀው እንኳን አያዩትም። እየሟሟ የሚያልቅባት ይመስላታል።

"አይ አብነት፣ የምትይው ቢጠፋሽ ድህነትና ድንቁርናም ሊኮራባቸው ይገባል አልሽኝ?! ሰፊው ልዩነታችን በመሀላችን ሲዘረጋ ይታይሻል?! አንቺ ህይወት የመለኮት ስጦታ ነች። እንደየ እጣ ፈንታችን ልንቀበላት እንጂ ልንታገላት አይገባም አይደልም የምትይው?! ላንቺ ድህነትና ድንቁርና፣ በሽታና ረሀብ የሚያኮሩ እንጂ የሚያሳፍሩ አይደሉም። የኔ እምነት ግን ከዚህ የተለየ ነው። ድሆችን ድሆች እንዲሆኑ የፈረዱባቸው ሰዎች እንጂ መለኮት አይደለም። የችግሮችም ሁሉ ምንጭ ሰዎች እንጂ መልስ ላጣንላቸውና ምክንያት ልንሰጥባቸው ላልቻልንባቸው ነገሮች ሁሉ በዋቢነት የምናሳልፈው

ፈጣሪ አይደለም..." ልትይዛቸው ያልቻለቻቸውን ብዙ ሃሳቦች ይተነትንላት ጀመር። እርሷ ማወቅ የፈለገችው ግን "ዘር" የሚለው ስእል የፈጠረበትን ስሜት ስለነበረ የጀመረውን አቋርጣ "ቻርሊ፣ የጀመርከው እኮ ዘር የሚለው ስእል..."

"እዎን... አዎን... ዘር የሚለው ስእል ... ለምን ወደዚህ ሀሳብ እንደገባሁ አላውቅም... አየሽ አብነት፣ እናቴ በወለደችኝ ባመቷ ነው አሉ ቀጥቅጠው የገደሏት... ቡዳ ብለው። ቀጥቅጠው ገድለው ፈፋ ጣሏት፣ ሞትን ራሱን የገደሉ ያህል፣ ከዚያ በኋላ ነው አሉ የአገሬው ሰዎች በሰላም ማንቀሳፋት የጀመሩት ... ሃ ሃ ሃ ሃ ... ሃ ሃ ሃ ..."

ቀና ብላ አየችው፤ ይስቃል። ሳቁ ግን የዋይታ ያህል የሚሰቀጥጥ ነበረ። ጥላቻና ምሬት እሾሃም ጥፍራቸውን ዘርግተው ሊቧጥጧት የተዘጋጁ ያህልም ገጽታው አስበረገጋት። እንደዚያም ሆኖ ግን ይስቅ ነበር። "ሃ ሃ ሃ ሃ ... ሃ ሃ ሃ ... ሞትን ገደልን ብለው ፎከሩ አሉ እንዲት እናቴን ገድለው..."

"ተወው ቻርሊ፣ ተወው፤ ከዚህ በላይ ምንም መስማት አልፈልግ" አለችው በፍርሃት እየተንቀጠቀጠች።

ጀንበሯ በምእራብ በኩል ጠልቃ የመንገድ መብራቶች በርተዋል። በአስፋልቱ መንገድ ላይ መኪኖች ረዥም መብራታቸውን ለቀው ያልፋሉ። መንገደኞች ወደ ቤታቸው ይጣደፋሉ።

"ምነው? ጠላሽኝ?!"አላት በትዝብት ዐይን እየገረመማት።

"የለም አልጠላሁህም ቻርሊ... ግን በቃ አሁን የምታወራውን ነገር ተወው..."

"ለምን አብነት? ለምን? የእውነት ግማሽ እኮ የለውም። እውነቱን እነግርሻለሁ። በእኔ ሕይወት ውስጥ አንቺ የማታውቂው ነገር እንዲኖር አልሻም። ብዙ ጊዜ እንደምትወጂኝ ነግረሽኛል። ምናልባት ያፈቀርሽው በሙያዬ ላይ ያለኝን ችሎታ ወይም ውጫዊውን እኔነቴን ሊሆን ይችላል። ውስጣዊ ማንነቴንስ?! መላውን ህይወቴንስ ታውቂዋለሽ? አታውቂውም - እና ልንገርሽ..."

"ቻርሊ....."

አላስጨረሳትም። "የዚያን የፋቂና የዚያችን የቡዳ ደምና ገጽታ ብቻ ሳይሆን የስም ስብራታቸውን፣ በወግ ቀበኞች የተነከተ ታሪካቸውንና እንደሞት መርዶ ነጋሪ አስፈሪ ድህነታቸውን ወርሼ ለተወለድኩት ህፃን ከዚያ ከምስኪን አባቴ በቀር የተረፈ ዘር አልነበረኝም። ገና እግር ተክዬ መውተርተር እንደጀመርኩ፣ ሮጨ



እንኳን ሳልጠግብ ነበር መማር የጀመርኩት። የአባቴን ዐይን የሸበበ ድንቁርና እኔንም እንዳይጋርደኝ፣ አባቴን ለጥንብ ሽታ እግር ከወርች ጠፍሮ ገፀ-ብረከት ያቀረበ ማይምነት፣ የእኔንም እጆች አጎልድፎ ለድንቁርና ግዳይ ሳይጥለኝ ገና ከጠዋቱ ነቃሁኝ!... በጆሮ ግንዴ የህሁ ጅራፍ ላሙህበት፣ በአንጎሌ ማሳ የፊደልን ዘር ልዘራበት፣ ከመንደሩ በጣም ርቄ፣ ስንቄን ባገልግል ሸክፌ ተረከዜ እስኪንሻፈፍ እየተንዘኩ እማር ነበር። አባቴም በርታልኝ ሲለኝ፣ ዓለም የነፈገችኝን ፍሰሀ ባንተ በልጄ ወግ ማዕረግ እካስበታለሁ ሲለኝ፣ የዐይኔ ተስፋ ነህ ሲለኝ፣ እሱንም በጥይት አረር ደብድበው አንድ ብቻዬን አስቀሩኝ! ሃ ሃ ሃ ሃ... ሃ ሃ ሃ ሃ... ውው!" ይስቃል፣ ይስቃል፣ ይስቃል። 'ሣቅ የደስታ ምንጭ ነው' የሚሉ ሰዎች ምንኛ ተሳስተዋል። ...ስረቅ አድርጋ ስታይ ዐይኖቹ የተከፈቱ የገሃነም ደጆች እስኪመስሉ ድረስ የበቀል እሳት በውስጣቸው ይንቀለቀላል። ሩጪ ሩጪ፣ ብረሪ ብረሪ የሚል ስሜት ከውስጥ ይታገላት ጀመር።

"አባቴን ለምን እንደገደሉት ታውቂያለሽ? የእናቴ መንፈስ በአባቴ ላይ አድሮ ልጆቻችንን ፈጀ ብለው ነው። አባቴን ገድለው 'ሞትን እንደገና ገደልነው' ብለው ፎከሩ። ትዝ ይለኛል፣ አርብ ቀን ነበር። እኔና አባቴ ገበያ ውለን አመሻሽ ላይ ወደ ጎጇችን ስንመለስ፣ በርቀት ጎጇችን በእሳት ተቃጥላ እንደ ጧፍ ስትንበለበል አየናት። ሁለታችንም ካለንበት ደርቀን ስንመለከት ከብቶቻችንም ሲነዱ አስተዋልን።

"አባቴ በዘንግ ያንገተውን ቋጠሮ መሬት አስቀመጠና እንዴ ወደሚቃጠለው ቤት አንዴ ወደ እኔ እየተመለከተ 'ልጄ ... ከእንግዲህ ይህን ጥቃት ቆሜ የምቀበልበት ትግስት የለኝም። ያለኝን ሁሉ ሸጬ አይገቡበት ገብቼ ይህን ጠመንጃ የገዛሁት፣ የእናትህ ደም እየጮኸ ለበቀል ስለቀሰቀሰኝ ነበር። 'የስራኤል አምላክ ይጠብቅህ!' አለና አንገቱ ላይ በማተቡ ክር ተንጠልጥላ ረጅም ዘመን ከርሱ ጋር የኖረችውን የኮከብ ቅርጽ ያላትን የብር ጌጥ በጥሶ በእጆቼ አስጨበጠኝ። 'ከአባቴ የወረስኩት ነው። አንተም ለልጅህ፤ ልጅህም ለልጅ ልጅህ ያስተላልፈው። ይች ሀብል የአያቶችህና የቅድመ አያቶችህ ላብና ደም በላይዋ ላይ የታተመባት የህያውነታችን ምስክር ናት። እንደ ህይወትህ ጠብቃት' አለና ግንባሬን ሳመኝ!!

"በፍርሃት የፈጠጡ ዐይኖቼ በጨበጥኩት የብር ጌጥ ላይ ሲቁለጨለጩ አባቴ አጭር ምንሽሩን ከእንግቱ አውርዶ አቀባበለና ቁልቁል ወደሚቃጠለው ቤት ገሰገሰ። እኔም ዱካውን ተከትዬ አብሬው ሮጥኩ።

"አባቴ ከቤታችን መዳረሻ ላይ ቁጥቋጦ የሸፈነውን አንድ ትልቅ ቋጥኝ ተገን አደረገና በደረቱ ለሽ ብሎ አደፈጠ። እኔም ከወደ ኋላው አንዲት አነስተኛ ቋጥኝ ተከልዬ በደረቴ ተኛሁና ዐይኖቼን አፍጥጬ የሚሆነውን አይጀመር።

"አባቴ የተኮሳቸው ሁለት ጥይቶች ጩኸት አስበርግገውኝ ጆሮዎቼን በጣቶቼ ድፍን አድርጌ እንደያዝኩ ከቤታችን ደጃፍ አንድ ሰው ተዝለፍልፎ ሲወድቅ አስተዋልኩ። ቤታችንን የሚበዘብዙት መንደረተኞችም የአፀፋ ተኩስ ለቀቁብን። ለሩብ ሰዓት ያህል በዚህ መልኩ ተኩሱ ቀጥሎ የአባቴ ጥይት ወደ መገባደዱ ሲቃረብ የባላጋራዎቻችን ተኩስ ማየል ጀመረ። ዙሪያችንን ሊከቡን መፈለጋቸውንም ከእንቅስቃሴያቸው ተረዳን።

"አባቴ ወደነበርኩበት አቅጣጫ ለአፍታ ያህል ዞር አለና 'ፈጥነህ ሽሽ!' አለኝ እንደተቆጣ። ...የአውሬ መንፈስ ዐይኑ ውስጥ ይንቀለቀላል፤ ፊቱ በላብ ተጠምቋል። ካለሁበት ንቅንቅ አላልኩም። ተነጣጥረው የተተኮሱ ጥይቶች ተገን ያደረገውን ቋጥኝ ሲሸራርፉት እንደገና ወደኔ መለስ አለና 'አምልጥ እኮ ነው የምልህ!' ሲል ጮኸብኝ። ምክንያቱ ባይገኝም ካለሁበት መንቀሳቀስ አልፈለኩም። የባለጋራዎቻችን ከበባ ግን እየጠበበ፣ ማምለጫ ቀዳዳዎቹም እየተደፈኑ ነበር።

"ለመጨረሻ ጊዜ አንገቱን ዘንበል አድርጎ 'እባክህ አምልጥ፣ እባክህ አንተ እንኳ ለዘር ትረፈኝ' ሲል ተማጸነኝ። በፊቱ ላይ ይንበለበል የነበረው የቁጣ እሳት ቀዝቅዟል፤ ዐይኖቹ ድክም ብለዋል፤ ድምጹም ለስላሳ ነበር። ከተጋደምኩበት ሆኜ አንዳች የእልህ ሲቃ ጉሮሮየን አነቀው። ሳላስበው እንባዬ በጉንጬ ላይ ይወርድ ጀመር። ወዲያውኑ ተገን አድርጌው የነበረው ቋጥኝ በሁለት ጥይቶች ተነደለ።

"አባቴ ወደነበርኩበት ዞር ብሎ ሲያይ እኔም እርሱን ስመለከት ዐይኖቻችን ለአፍታ ተጋጩ። በዚያ እንደ በረዶ የቀዘቀዘ ስሜት ባዘሉ ፀይኖቹ እየተማፀነኝ መሆኑን አላጣሁትም። 'እባክህ ለዘር ትረፈኝ!' ወደ ኋላዬ መለስ አልኩና እንደ ጥንቸል ቁጥቋጦውን እየዘለልኩ፣ ጋሬጣውን እየጣስኩ ተፈተለኩ። የባለጋራዎቹ ተኩስ ግን ከአይታቸው እስክሰወር ድረስ ተከተለኝ።

"በማግስቱ ካደርኩበት ዱር ወጥቼ በጥንቃቄ ወደ ቀያችን አዘገምኩ። አባቴ በጥይት ተደብድቦ ከተቃጠለው ጎጆ ጉበን ላይ ተሰቅሎ አገኘሁት። እዚያው ከባድማው ላይ ያለ እህል፣ ያለ ውሃ...



ቀኑን ሙሉ የአባቴን በድን ሽቅብ እያየሁ የእንባዬ ኩሬ ደርቆ ከዐይኖቼ ደም እስኪታለብ አለቀስኩ ... አለቀስኩ።

"አሁን ግን አስቃለሁ... በአሸዋ መጫኛ መኪና ላይ ተንጠልጥዬ ወደ አዲስ አበባ ስመጣ አንድ ቀን እንደምበቀላቸው ከራሴ ጋር እየተማማልኩ ነበረ። እያደር ግን... ብዙ እያወቅኩ ስሄድ ከልቤ ይቅር አልኳቸው። ልጆቻቸውን የሚገድለው ኩፍኝ፣ ትክትክ፣ ሣንባ ነቀርሳና ተቅማጥ እንጂ በእናትና በአባቴ ላይ ያደረ ክፉ መንፈስ አለመሆኑን ያስተማራቸው አልነበረም። እንደዚያ አውሬ ያደረጋቸው ማይምነት መሆኑን ስረዳ የበደል እድፍ ያጠቆረውን ልቤን በገዛ እንባዬ አጥቤ ይቅር አልኳቸው።

"አዲሳባም ብትሆን የተቀበለችኝ ፊቷን አጥቁራ ነበር። አትታዘቢኝና አብነት በረንዳ እያደርኩ ነበር ትምህርቴን መማር የቀጠልኩት። ከእሬት የመረረ ህይወት። የአባቴ ልመና ግን ዘወትር ከልቤ አይጠፋም ነበር። 'ዘር'...."

አብነት ስሜቷ ሁሉ ጆሮዋ ላይ ስለነበረ ጉንጮቿ ላይ እንደ ጅረት የሚፈሰውን እንባ አላስተዋለችም።

ድንገት ቀጥ ብሎ ቆመና "አብነት... ለመሆኑ ሁለት ልጆች እንዳሉኝ ታውቂያለሽ?!" ሲል ጠየቃት።

ጆሮዎቿ በትክክል ያዳመጡት አልመሰላትም። ምላሿን ከትናጋዋ በግድ አላቃ "ምን አልክ?" ስትል ጠየቀችው ድክም ባለ ድምጽ። የተናገረውን እንዳይደግም በልቧ አምላኳን እየተማፀነች።

የጎድን ተመለከታት። ገጽታዋ ጠቁሯል፤ አተነፋፈሷ በላይ በላዩ ነው። ይህ የስሜት መለዋወጥ ግን ማወቅ የሚገባትን ነገር እንዳታውቅ ምላሱን እንዲሰበስብ አላገደውም። "ሁለት ልጆች አሉኝ!" አላት ያለ አንዳች ማወላወል።

አብነት ራሷን እንደማዞር፣ የረገጠችው መሬት እንደመከዳት አላት። "ለምን እስከ አሁን አልነገርከኝም?!" አለችና ሳታስበው ጮኸችበት።

"አሁንም ብዙ የዘገየሁ አልመሰለኝም። ምነው ከፋሽ?"

አብነት አልመለሰችለትም። መሬት መሬት እያየች በዝምታ መኳዝ ጀመረች። ሣራ ጋዴም "የማፍቀር ስሜትሽ እስከዘለዓለሙ

በውስጥሽ እንዳይቀበር ስላፈቀርሽው ሰው ማንነት ከዚህ በላይ እንዳትጠይቂኝ" ያለቻትን አስታወሰችና በጥልቀት ማሰብ ጀመረች።

ዝናቡ ማካፋት ጀምሯል። አብነት ወደ መኖሪያ ቤቷ ተቃርባለች።

"እውነት እንደዚህ መራራ ነች አብነት... እንደአይስክሬም እየጣፈጠች አትላስም" አላት ግንባሩን እንደቋጠረ።

አብነት ከውስጧ መንደድ ጀመረች። "አሁን ምናለ ምላስህን ብትሰበስብልኝ!" አለችና ትላልቅ ዐይኖቿን አጉረጠረጠችበት። አልመለሰላትም። "እሽ፣ ለምን ቀድመህ አልነገርከኝም?"

"ለውጥ የለውም። እና ቅድም እንዳልኩሽ አሁንም የዘገየሁ አይመስለኝም። ለመወሰን በቂ ጊዜ አለሽ" አላት።

"ምን ለመወሰን?" እየተንቀጠቀጠች ጠየቀችው።

ትከሻውን ሰበቀና ዝም አላት።

ቻርሊ እንደሚለው ከእንግዲህ ምንም ጊዜ እንደሌላት አውቃለች። ከነፍሷ የተዋሃደ ነፍሱን እንዲህ እንደዘበት መንጭቃ ልታወጣና በልቧ ውስጥ ሥር የሰደደ ፍቅሩን በዋዛ ልትፈነቅል እንደማትችል ታውቃለች። ሁለት የእንባ ጠብታዎች ከዐይኖቿ ዘለው ጉንጮቿ ላይ ሲነጥሩ አልታወቃትም።

"አዝናለሁ። ልጆች ያሉኝ መሆኔን ስታውቂ ስለተከፋሽ በጣም አዝናለሁ" አላት ቅሬታ ባዘለ ድምጽ።

አብነት ማሰብ ጀመረች። "ግን ምን እንደዚህ አደረገኝ?" እያለች ራሷን ጠየቀች። ቅናት ነው? ጥላቻ ነው? ፍራቻ ነው? መልስ ልታገኝለት አልቻለችም።

"ጥፋተኛዋ አንቺ ነሽ፤ አብነት። ያፈቀርሽው ውጫዊውን ማንነቴን እንጂ እኔን አልነበረም። አሁን ግን እውነተኛ ማንነቴን አሳይቼሻለሁና መወሰን ያንቺ ድርሻ ነው" አላት። እንደበቱ ይህንን ቢናገርም ውስጡ ግን በመለያየት ስጋት እየተዝገዘገ ነበር።

ያለ አንዳች ቃላት ልውውጥ በፀጥታ ተጓዙ። ሰውነታቸው ቢዝልም አዕምሯቸው በውጥረት ላይ ነበረ። ሳያውቁት አብነት መኖሪያ ቤት ትይዩ ካለው ትልቅ ዛፍ ሥር ደርሰዋል። ከካፊያው ለመጠለል



ስሩ ሄደው ቆሙ። ከመንገድ መብራቶች የተፈነጠቀ ብርሃን አካባቢውን ደብዘዝ አድርጎታል። ፍጹም ፀጥታ ነግሷል።

ቡዝዝ ብለው መሬቱ ላይ የተተከሉትን የቻርሊን ዐይኖች ስትመለከት አንዳች የሀዘን ስሜት አንጀቷን አንሰፈሰፈው። መናገር ብትፈልግም ቃላቱ ጥርሶቿን ፈልቅቀው ሊወጡላት አልቻሉም። ምላሷ ከላንቃዋ ጋር በመርፌ የተሰፋ ያህል ፀጥ ብላ አየችው። ባሻገር የትልቁ ቤት መብራቶች ይበራሉ፤ ግቢውም ረጭ እንዳለ ነበር።

የቻርሊን ሁለት ክንዶች ጥብቅ አድርጋ ያዘችና ከፊት ለፊቱ ቆመች። የልብ ምቷ እየፈጠነ፣ የደም ስሮቿ እየተወጠሩ፣ ሰውነቷ እየጋለ ሲሄድ ይታወቃታል። ድምጿ ግን ደካማ ነበር። "ቻርሊ፣ ወስኛለሁ ። ካለአንተ መኖር አልችልም... እስከ መቃብር ከአንተው ጋር ነኝ!"አለችው በስሜት የሚቃጠሉ ዐይኖቿን እያንከራተተች።

ቻርሊ የጀመረችውን እንዳትጨርስ አፏን ይዞ ዝም ሊያሰኛት እጁን ለመሰንዘር ቢሞክርም አጥብቀው የያዙት የአብነት እጆች አላነቃነቁትም።

"አብነት፣ በስሜት ተገፋፍተሽ የገባሽው ቃል ኪዳን አንድ ቀን እንደሚጸጽትሽ አስተውይ ! ቃል ህይወት ነው። ያለ ቃሉ የሚኖር ሰውም በቁሙ እንደደረቀ ዛፍ በድን ነው። አቢ.... አንድ ቀን የገዛ ቃልሽ ጠልፎ እንደሚጥልሽ ታውቂያለሽ? ለምን ይህን ቃል ተነፈስሽው?" አላት በሚንቀጠቀጥ ድምጽ። በዚህ እርግጠኛ ነው፤ አንድ ቀን አብነት ልክ እንደውቢት "ፍቅር የጊዜ ጉዳይ ነውና በቃን!" እንደምትለው።

"ቻርሊ፣ ይህን ቃሌን ባጥፍ የቆምኩባት ምድር ትክዳኝ!"

"አብነት!" ቻርሊ ሳያውቀው ጮኸ። እጅግ እጅግ በመዘግየቱ አብነትን ዝም ሊያሰኛት አልቻለም።

እነኛን ቃላት ከዚያ በፊት ከሌላ ሰው ትስማቸው ወይ ራሷ ትፍጠራቸው በትክክል አታውቅም። በህይወት በኖረችባቸው ዓመታት ውስጥ ከተናገረቻቸው ቃላት ሁሉ የከበሩና ድንቅ ቃላት ግን ናቸው። እነኚህ ቃላት በመጪው ህይወቷ ውስጥ ሊያስከፍሏት ስለሚችሉት መስዋዕትነት ግን ለሰከንድ ታህል እንኳን አላሰበችም።

እጆቿን ስቦ ደረቱ ላይ ሲለጥፋትና ሲስማት ሁሉ በውል አታስታውስም። ወዲያው ሰማይና ምድሩን የሚያርገፈግፍ የነጎድጓድ

ድምጽ ሰማችና ከእቅፉ ውስጥ ተመንጭቃ ወደ ሰማይ አንጋጠጠች። የመብረቁ ብልጭታ ጥቁሩን ሰማይ ያርሰዋል። ከሀይለኛ ነፋስ ጋር የተቀላቀለ ከባድ ዝናብ እያጉረመረመ በአለው ኃይል ሁሉ ምድሪቱን ይቀጠቅጣል።

ዛፉ ሥር እንደቆሙ ውሽንፍሩና ጠፈጠፉ መላ አካላቸውን አራሰው። ከንፈሩን ሰማ ተሰናብታው ስትሄድ ዳግመኛ የምታገኘው አልመሰላትም ነበር። የትልቁን ቤት የውጭ በር አስከፍታ ስትገባ ዞር ብላ አየችው። አሻግሮ እየተመለከታት ከዛፉ ሥር እንደቆመ ነው።

መሀረቧን ከቦርሳዋ አውጥታ በጉንጯ ላይ ከዝናቡ ጋራ ተቀላቅሎ የሚወርደውን እንባዋን እየጠረገች ወደ መኝታ ከፍሏ ሮጠች።



## ምዕራፍ ስምንት

ሀምሌ ወር መግቢያ ላይ አብኔት ከቻርሊ ጋር የያዘችው ቀጠሮ እንዳያልፍባት ስትዘገጃጅ እናቷ የመኝታ ክፍሏን በር ከፍተው ገቡ። እርያም መከንን ከቁመታቸው አጠር፣ ከሰውነታቸው ደልደል ያሉና እንደ ፀሐይ የሚያበሩ ዐይኖች ያሏቸው ናቸው።

"ወዴት ለመሄድ ተነሳሽ ልጄ? ዛሬ እኮ እንግዳ ጋብዘናል" አሏት የአለባበሷን ድምቀትና የሰውነቷን ውበት በመደነቅ እያስተዋሉ።

"ዛሬ ብርቱ ጉዳይ አለኝ እማይ... የማልቀርበት" አለች አብኔት ማበጠሪያዋን ከቦርሳዋ ውስጥ ለማውጣት እየተጣደፈች።

"ተይ ተይ ልጄ... ዛሬ እንኳን የትም መሄድ አትችይም። የአባትሽ ትእዛዝ ነው። ይልቅ ፈጥነሽ ወደ ጭስ ቤቱ ሂጂና መሰናዶውን እርጂያቸው" ብለዋት መልስ ሳይጠብቁ ከክፍሏ ወጥተው ሄዱ።

አብኔት ቦርሳዋን አልጋዋ ላይ ወርውራ እጆቿን አጣመረችና ከአልጋዋ ትይዩ ባለው ወንበር ላይ ተቀመጠች። የሕይወት እስረኛ! ነፍሷን ለአንድ ቀን እንኳ ልታዝናና የማትችል የሕይወት እስረኛ። እንደ ሣራ ጋዴም ነፃ ወፍ ሆና የምትኖረው መች ይሆን?

ቀትር መቃረቢያ ላይ እናቷ ወደ ዋናው ቤት ስለአስጠሯት እየተጣደፈች ሄደች። ፍቅርና ርህራሄን ባዘሉ ዐይኖቻቸው እየደባበሷት "አብኔቴ፤ የእንግዳው መምጫ ሰዓት ተቃርቧል፣ ሰውነትሽን ተጣጥበሽ ልብሶችሽን ቀይሪያቸው።" አሏትና ለጥያቄ የተከፈተው አፏ ከመገጠሙ በፊት የለበሱትን ነጠላ መሬት ለመሬት እየጎተቱ ጥለዋት ሄዱ።

ሰውነቷን ታጥባ ወደ መኝታ ክፍሏ በመሄድ ቡና ዐይነት ቀሚስና ሣሣ ያለ ነጭ ሹራብ ለበሰች። ፀጉሯን አበጥራ ስትጨርስም ለመጨረሻ ጊዜ ወደ ቁምሳጥኑ መስተዋት ሄዳ ራሷን ተመለከተች።

ብዙም ሳይቆይ ከግቢው ውጭ የመኪና ጥሩንባ ሰማች። እናቷ ወደ ክፍሏ መጥተው "አብኔቴ ነይ ውጭና እንግዳውን ተቀበይው። ፍጠኝ እንጂ" እያሉ አጣደፏት። እየገፋፉ ወደ በረንዳው ሲወስዷትም የምታደርገው ጠፍቷት ግራ ተጋብታ ነበር።

ድምጽ ሰማችና ከእቅፉ ውስጥ ተመንጭቃ ወደ ሰማይ አንጋጠጠች። የመብረቁ ብልጭታ ጥቁሩን ሰማይ ያርሰዋል። ከሀይለኛ ነፋስ ጋር የተቀላቀለ ከባድ ዝናብ እያጉረመረመ በአለው ኃይል ሁሉ ምድሪቱን ይቀጠቅጣል።

ዛፉ ሥር እንደቆሙ ውሽንፍሩና ጠፈጠፉ መላ አካላቸውን አራሰው። ከንፈሩን ስማ ተሰናብታው ስትሄድ ዳግመኛ የምታገኘው አልመሰላትም ነበር። የትልቁን ቤት የውጭ በር አስከፍታ ስትገባ ዞር ብላ አየችው። አሻግሮ እየተመለከታት ከዛፉ ሥር እንደቆመ ነው።

መሀረቧን ከቦርሳዋ አውጥታ በጉንጯ ላይ ከዝናቡ ጋራ ተቀላቅሎ የሚወርደውን እንባዋን እየጠረገች ወደ መኝታ ክፍሏ ሮጠች።



## ምዕራፍ ስምንት

ሀምሌ ወር መግቢያ ላይ አብነት ከቻርሊ ጋር የያዘችው ቀጠሮ እንዳያልፍባት ስትዘገጃጅ እናቷ የመኝታ ክፍሏን በር ከፍተው ገቡ። አርያም መኮንን ከቁመታቸው አጠር፣ ከሰውነታቸው ደልደል ያሉና እንደ ፀሐይ የሚያበሩ ዐይኖች ያሏቸው ናቸው።

“ወዴት ለመሄድ ተነሳሽ ልጄ? ዛሬ እኮ እንግዳ ጋብዘናል” አሏት የአለባበሷን ድምቀትና የሰውነቷን ውበት በመደነቅ እያስተዋሉ።

“ዛሬ ብርቱ ጉዳይ አለኝ እማይ... የማልቀርበት” አለች አብነት ማበጠሪያዋን ከቦርሳዋ ውስጥ ለማውጣት እየተጣደፈች።

“ተይ ተይ ልጄ... ዛሬ እንኳን የትም መሄድ አትችይም። የአባትሽ ትእዛዝ ነው። ይልቅ ፈጥነሽ ወደ ጭስ ቤቱ ሂጂና መሰናዶውን እርጂያቸው” ብለዋት መልስ ሳይጠብቁ ከክፍሏ ወጥተው ሄዱ።

አብነት ቦርሳዋን አልጋዋ ላይ ወርውራ እጆቿን አጣመረችና ከአልጋዋ ትይዩ ባለው ወንበር ላይ ተቀመጠች። የሕይወት እስረኛ! ነፍሷን ለአንድ ቀን እንኳ ልታዝናና የማትችል የሕይወት እስረኛ። እንደ ሣራ ጋዴም ነፃ ወፍ ሆና የምትኖረው መቼ ይሆን?

ቀትር መቃረቢያ ላይ እናቷ ወደ ዋናው ቤት ስለአስጠሯት እየተጣደፈች ሄደች። ፍቅርና ርህራሄን ባዘሉ ዐይኖቻቸው እየደባበሷት “አብነቴ፣ የእንግዳው መምጫ ሰዓት ተቃርቧል፣ ሰውነትሽን ተጣጥበሽ ልብሶችሽን ቀይሪያቸው።” አሏትና ለጥያቄ የተከፈተው አፏ ከመገጠሙ በፊት የለበሱትን ነጠላ መሬት ለመሬት እየጎተቱ ጥለዋት ሄዱ።

ሰውነቷን ታጥባ ወደ መኝታ ክፍሏ በመሄድ ቡና ዐይነት ቀሚስና ሣሣ ያለ ነጭ ሹራብ ለበሰች። ፀጉሯን አበጥራ ስትጨርስም ለመጨረሻ ጊዜ ወደ ቁምሳጥኑ መስተዋት ሄዳ ራሷን ተመለከተች።

ብዙም ሳይቆይ ከግቢው ውጭ የመኪና ጥሩንባ ሰማች። እናቷ ወደ ክፍሏ መጥተው “አብነቴ ነይ ውጭና እንግዳውን ተቀበይው። ፍጠኚ እንጂ” እያሉ አጣደፏት። እየገፉፉ ወደ በረንዳው ሲወስዷትም የምታደርገው ጠፍቷት ግራ ተጋብታ ነበር።

አባቷ ሙሉ ጥቁር ሱፋቸውን እንደለበሱ ሽበት የወረረው ጠጉራቸውን በወጉ አበጥረው በረንዳው ላይ ቆመዋል። ዐይኖቻቸው ሲጋጩ በጥቅሻ "በርቺ" አሏት። ወዲያው ጥቁር ሲትሮይን መኪና እንደ ውሃ እየፈሰሰች የግቢውን በር አልፋ ከመኪናው ቤት በአንዱ ጥግ ቆመች።

ጠበቃው የመኪናዋን በር ከፈተና ወጣ። ሙሉ ጥቁር ሱፍ ለብሶ፣ ውሃ ሰማያዊ ቀለም ባለው ሸሚዝ ላይ ቀይ ክረባት አስሯል። ፀጉሩን በራነት የጀመረው ብስል ቀይ ነው። በላስቲክ የተጠቀለለ የጽጌረዳ አበባ ይዞ ወደ በረንዳው ሲያመራ ጥቁር ጫማው የፀሐዩን ብርሃን ያንፀባርቅ ነበር።

መጋረጃው ተከፍቶ ተውኔቱ ተጀመረ። ይህን እውነት ስታስታውስ በመገረም ፈዛ ቀረች። ወዲያው ደግሞ ገረሜታዋ ወደ መደናገር፣ መደናገሯ ወደ ፍርሃት ተለውጦ ሳታስበው እጆቿ ይንቀጠቀጡ ጀመር።

"ሃ ሃ ሃ ሃ. . . . ሃ ሃ ሃ ሃ ሃ. . . . እንኳን ደህና መጣህ ወዳጃችን" ብለው አባቷ እጃቸውን ለሰላምታ ዘረጉለት። እውነተኛው የሕይወት ድራማ ተዋናይ።

ጠበቃው ከአባትና ከእናቷ ጋር ሰላምታ ከተለዋወጠ በኋላ ወደአብነት አምርቶ "እንደምን ሰነበትሽ አብነቴ፣ እነሆ መተያያ፣ ጽጌረዳ ለጽጌረዳ!" አለና አበባውን አስታቀፋት። መልስ ሳትሰጠው አበባውን እንደታቀፈች ገጽታውን እንደ አዲስ ታጠና ገባች። ዘለግ ያለና ቀጭን ነው፤ አዲስ የተላጨው ጢሙ የፊቱን ከሲታማነት ያጋልጠዋል፤ አጠር ካለው አፍንጫው በታች ከንፈሮቹን ገጠጥ ያሉት ጥርሶቹ ይገልጧቸዋል። በአባቷ መሪነት ወደ እንግዳ መቀበያ ክፍል ገቡ።

አብነት ያልተዋጣላት ተዋናይ ስህተት ቁጥር አንድን ፈፀመች። "ጽጌረዳ ለጽገሬዳ!" ብሎ አበባውን ሲያስታቅፋት ቀልጠፍ ብላ እጁን በመጨበጥ "አመሰግናለሁ" ማለት ይገባት ነበር - ፈገግታዋን እየመዘነች።

ሳሎኑ ውስጥ በምግብ ጠረጴዛው ላይ ቦታ ሲይዙ ደግሞ ስህተት ቁጥር ሁለትን ፈፀመች። ጠበቃው አጠገብ ወንበር ስባ መቀመጥ ሲገባት ተፈናጥራ በርሱ ትይዩ መቀመጧ ለተውኔት ሥራ አመቺ አልነበረም።



ቀማሉ በረኛው ስፌ ጠረጴዛ ላይ ምሣ ቀረበ። የጠበቃው አበላል ለጉድ ነው፤ ውሲኪ አጠጣጡም እንደ ውሃ! ብዙም ሳይቆይ ደግሞ ሙግቱ እንደበቱ እየቀለጠ መፍሰስ ጀመረ። ጨዋታው መነሻ እንጂ መድረሻ የለውም። እዋቂነቱን ለመግለፅ ፖለቲካውን፣ ሣይንሱን፣ የማኅበረሰቡ ባህል መርከስ መንስኤዎችን እያነሳ ይተነትናል። በምድር ላይ የማያውቀው ነገር ያለ አይመስልም። ዓለምን በጣቱ ጫፍ ላይ አቁሞ የሚያሽከረክራት ይመስል ማንኛውም ታላቅ ድርጊት ሲፈጸም እርሱ እዚያ እንደነበር አድርጎ ያቀርበዋል።

አባቷ በበኩላቸው በማያስቀው ሁሉ እየሳቁ፣ በማያስገርመው ሁሉ የተገረሙ እየመሰሉ ተውኔቱን ያለ እንዳች እንከን ይጫወታሉ። አብነት ዐይኖቿን እያንከራተተች ዱዳ ይመስል ተቆልፋ ተቀምጣለች።

ግብዣው አልቆ ጠበቃው ተሰነባብቷቸው ሲወጣ ሞቅ ብሎት ነበር። አፉ ይኮላተፋል እግሮቹ ተሳስረዋል። እጇን ጨብጦ እያፍተለተለ "ጽጌረዳዬ ... ደህና እደሪልኝ ... ስለይሽ እያዘንኩ ነው" አላት። አልመለሰችለትም።

በረንዳው ድረስ ሸኝተውት ወደ ሳሎን ሲመለሱ አባቷ ክንዷን ያዝ አድርገው አቆሟትና "ያልተዋጣላት ተዋናይ ሆንሽ ነው የዋልሽው ... በእቅዳችን መሠረት እየተጫወትሽ አይደለም። ምናልባት መድረኩ ላይ ስትወጪ የመጀመሪያሽ በመሆኑ ተደናግጠሽ ይሆናል... በሚቀጥሉት ቀናት ግን ራስሽን አስተካክለሽ እንድትቀርቢ..." ብለዋት ተደናግጣ በቆመችበት ጥለዋት ሄዱ።

አባቷ ለምን በእሣት መጫወት እንደመረጡ ባይገባትም ጠበቃው በየሳምንቱ የቤታቸው ቋሚ እንግዳ መሆን አዘወተረ። አብነት ግን አልተሻሻለችም፤ እንደወትሮዋ ያልተዋጣላት ተዋናይ እንደሆነች አለች። ጭርሱኑ አንዳንድ ጊዜ በህመም እያመካኘች መኝታ ክፍሏን ቆልፋ ትቀመጣለች። ሌላ ጊዜ ደግሞ ቤቱን ጥላ ትሄዳለች። አባቷ በዚህ ይበሳጫሉ።

ጠበቃው በየሣምንቱ ለእርሷና ለቤተሰቦቿ አዳዲስ ስጦታዎችን ይዞ ነው የሚመጣው። ልብሶች፣ ጫማዎች፣ ሰዓት፣ የእጅ ቦርሳ፣ ልዩ ልዩ ሽቶዎች። እያንዳንዱን ስጦታ ባቀረበላት ቁጥርም "ይህ ስጦታ ክብርሽን ይመጥናል ብዬ ሳይሆን ከበሬታዬንና ያለኝን አድናቆት ሊገልጽልኝ ይችል ይሆናል በሚል እምነት ነው" ሳይላት አያልፍም። ከሳምንት ሳምንት ቃላቱን ሳይዛነፉ ስለሚደግማቸው "በቃሉ አጥንቶት ይሆን?" እያለች ትስቃለች።

ሳምንት አልፎ ሳምንት በተተካ ቁጥር እጠገቡ ተቀምጣ ርጥብ በሚያደርቅ ምላሱ እንደ እሞሌ ጨው ሲልሳት ትበሸቅ ነበር። ግብቂያ በሌለው የፈረንጅ ሀገር ታሪኩ ተሰላችታለች። መሸሽ ግን አልሆነላትም። የህይወት ጠንካራ ክንዶች ጠፍረው ይዘዋታል።

ወላጆቿ ቤት ባልነበሩበት አንድ ሰንበት በረንዳ ላይ ተቀምጣ መጽሐፍ ስታነብ የጠበቃው መኪና ግቢው ውስጥ ገብታ ስትቆም አየች። የመኪናዋን ቁልፍ እያሽከረከረ ወደ እርሷ ሲመጣም ድንጋጤና ፍርሃት ወረራት። "እንደምን ሰነበትሽልኝ ጽጌረዳ" አለና እጁን እየወዘወዘ ጨበጣት። እጆቹ ደረቅና እንደ ብረት የቀዘቀዙ ናቸው።

"ለምንድነው ስሜ ባልሆነ ቅፅል የምትጠራኝ?" ስትል ጠየቀችው። ሁል ጊዜም "ጽጌረዳ" ሲላት ያስጠላታል።

የበረንዳውን ማእዘን እንደተደገፈ "ለኔ የምትታይኝ ምንጊዜም ትኩስ ቀይ የጽጌሬዳ አበባ መስለሽ ነው" አላት በፈገግታ እያባበለ።

ወደቤት እንዲገባ ብትጠይቀውም በረንዳው ላይ መቆየት እንደሚፈለግ ስለገለጸላት ወንበርና አጭር ጠረጴዛ አስመጥታ የሚወደውን ውስኪ አስቀረበችለት።

ውስኪውን ደጋግሞ እስኪቸላልስ ድረስ፤ በፀጥታ ከቅጥር ግቢው ውጭ ያሉትን ለዐይን የሚማርኩ ቪላ ቤቶችና የአካባቢውን ልምላሜ ሲያስተውል ቆየ። ኋላም "አካባቢያችሁ ለማያዊውን ገነት ሊመስል የቀረው ምን እንደሆነ ታውቂያለሽ?! ነጫጭ ክንፎቻቸውን እያራገቡ የሚዘምሩ መልአክት ብቻ! ሃ ሃ ሃሃ ሃ ሃ..." አላት በራሱ ቀልድ ራሱን እያዝናና። አብነት ፈገግ እንኳን አላለችም። ያልተዋጣላት አርቲስት መሆኗን ስለተገነዘበች ያጠለቀችውን ጭንብል ጥላ ከመድረኩ ላይ ከወረደች ሰንበታለች።

"ፀጥታው ራሱ ህይወትን ያለምግብና ያለውሃ ለዘመናት የሚያቆይ ነው ሃ ሃ ሃ ሃ... መታደል ይሏል እኮ ይሄ ነው። እኔ የምልሽ ጽጌረዳ... ለምን ከውስኪው ትንሽ አትጠጪም?" አላት ያጋመሰውን የውስኪ ጠርሙስ አንስቶ እያስተዋለ። ሁኔታው ገርሟትና ፈገግ አለች።

"በውነቱ ውስኪ የሰውነትን ነርቮች ለማነቃቃትና ብርታት ለማግኘት በጣም አስፈላጊ ነው። ብዙዎቹ ሊቃውንት፣ የኪነጥበብ ሰዎች፣ በርካታ የሀገር መሪዎችና የፖለቲካ ሰዎች ከፍተኛ የውስኪ ሱስ እንደነበረባቸው ታሪክ ያስታውሰናል። ታዲያ ከውስኪም ውስኪ



ይመረጣል... ከቆንጆጆች መካከል ቆንጆዋ እንደምትመረጥ፣ ከጥሩ ውስኪዎች ውስጥም ብዙዎች ቺቫስን ይመርጣሉ! እና አብነት፤ ውስኪ ሊዘወተርና ሊወደድ የሚገባው መጠጥ ነው... በሞቴ አንዲት መለኪያ አትጎነጭም?" አላት ጠርሙሱን ወደሷ እያቀረበ።

ግምባሯን ቅጭም አድርጋ "ስለ ምክርህና ስለ ግብዣህ አመሰግንሃለሁ። ይሁንና እኔ አልኮል አልወድም" አለችው እንደተቆጣች። በውስጧ ግን ውስኪ ለመጋበዝ ይህን ሁሉ መቀባጠሩ እያስገረማት ትስቃለች። ትከሻውን ሰበቀና በጁ ከያዘው ውስኪ በመለኪያ ውስጥ ጨምሮ በአንድ ትንፋሽ ጭልጥ አደረገው።

"አቢ፤ በህይወትህ ምን ያስደስትሃል ብለሽ አትጠይቂኝም?!..." አላት የሲጋራ ፓኮና ክብሪት ለማውጣት ኪሶቹን እየፈተሸ። ካወጣው የዊንስተን ፓኮ አንድ ፍሬ ከለኮሰ በኋላም "ባትጠይቂኝም እነግርሻለሁ" አላት። ዝም በማለቷ የተቀየመ አይመስልም። "ሁለት ነገሮች ብቻ በህይወት ለመኖሬ ምክንያት ሆነውኛል ውስኪና የሴት ልጅ ውበት! ከውስኪ ቺቫስ ከሴት ልጅ ውበት ዐይኖቿ ይማርኩኛል። ብዙዎች የሴት ልጅ ውበት የተስተካከለ የሰውነት አቋምና ቅርጽ፣ የቆዳዋ ቀለም፣ ፀጉሯ፣ ጥርሷ፣ አፍንጫዋ ነው ይሉሻል - አፍንጫቸው ይውለቅና! አላዋቂዎች በያቸው። የሴት ልጅ ውበት ያለበትን ልንገርሽ ዐይኗ ላይ ነው!" አላት። ተፈጥሮ ከዓለም የሰወረችውን አንድ ታላቅ ሚስጥር ተጨንቆና ተጠቦ የደረሰበት ይመስል ገጽታው በድል አድራጊነት ፈካ።

"ዐይን ለማየት ብቻ የተፈጠረ የሚመስላቸው ሰዎች፣ ሣር ከሚግጥ በግ የማይለዩ እንስሶች መሆናቸውን አስተውለሽ ታውቂያለሽ?! ትልቁን የውበት ሚስጥር... እንቆቅልሹን መፍታት ተስኗቸዋል... ሃ ሃ ሃ ሃ..."

አብነት "እምላኬ ሆይ የዚህ መያዣ መጨበጫ የሌለው ዲስኩር ማብቂያ መች ይሆን?" እያለች በትግስት የሚሄድበትን ጊዜ ትጠብቃለች።

"...ኦክስፎርድ ዩኒቨርሲቲ ሳለሁ ልክ እንዳንቺ የውበት ቁንጮ የሆነች ውብ ዐይን የነበራት የሕግ መምህርት ነበረኝ። ክፍል ገብታ ስታስተምር እከታተል የነበረው የምትሰጠውን ትምህርት ሳይሆን፣ የዐይኖቿን እንቅስቃሴና ትንግርት ውበቱን ነበረ። ዐይኖቿ ተገልጠው በተሸፈኑ ቁጥር ነፍስን ከሥጋ የሚበጭቅ፣ ቀልብን ከነፍስ ውስጥ የሚሰርቅ ምትሃት ነበራቸው። የሰዓሊ ብሩሽ በውስጣቸው ከሚፈሰው

የሕይወት ጅረት ትንሽ እንኳን ጨልፎ በሸራ ላይ ሊነድፋቸው አይቻለውም። የባለቅኔ ብእር ዐይኖቿ የሚረጩትን ፀዳል ፈለግ ለመዳሰስ አይሞክረውም። የልቤ ጉልበት ለውብ ዐይኖቿ ጣእት ተንበርክኮ ይሰግድላት ነበረ። እነሆ ዛሬ ደግሞ ታሪኬ ራሱን ደገመ። የነፍሴን ቀልብ አብከንክና ሲያማልለኝ የኖረ የዐይን ውበት በዐይኖችሽ ውስጥ ተመስሎ..."

ትዕግስቷ ሁሉ ከውስጧ ተሟጦ በማለቁ ጥላቻዋን መቆጣጠር አልቻለችም። በእጇ የያዘችውን መጽሐፍ ወርውራ "የምትናገረውን እያስተዋልክ!" ስትል አፈጠጠችበት።

ያንኑ የሚስቅ ሬሳ የሚያስመስለውን ፈገግታውን እያሳያት "ግሩም ነው።" አለ በአድናቆት።

"እኮ ምኑ ነው ግሩም?" የተቋጠረ ግምባሯ ሳይፈታ የፈጠጡ ዐይኖቿ ሳይረግቡ ጠየቀችው።

"ድንቅ እንጂ! ከቆንጆ ልጅ ጠባይ ምን ያስደስተሃል አትይኝም! ባትጠይቂኝም እነግርሻለሁ። ከቆንጆ ልጅ ጠባይ የሚያስደስተኝ ቁጣዋ፣ አልኳና ግልፍተኝነቷ ብቻ ነው። ለምን በይኝ!? የጽጌሬዳ አበባ በሾህ ጥፍሩ ውብቱን መከላከሉ ተፈጥሯዊ ሕግ ነው። እስኪ አስተውይ! አንዲት አንኳር የወርቅ ፍሬ ለማግኘት የሰው ልጅ ስንቱን ተራራ ይቧጥጣል?! ስንቱን ገደል ይዘላል?! ስንቱን ሰርጣሰርጥ ይበጣጥሳል?! ተፈጥሮ ውቦቿን፣ ድንቅየዎቿን በቀላሉ ከብብቷ አታስነጥቅም። የቤት ልጅ ውበትም፣ እንደ ቆሰለ አንበሳ፣ እንደ እመጫት ነብር ባለ አሻፈረኝ ባይ ጠባይ መጠበቅ ካልቻለ ውበቷ የጅል ውበት ይሆናል። የጅል ውበት ደግሞ የጅል ሲሣይ ብቻ ነው። ሃ ሃ ሃ ሃ ሃ.... ሃ ሃ ሃ... አጠፋሁ እንዴ ወይዘሪት?!" አሳት እየተቁለጨለጨ።

ዐይኖቹን ላለማየት ፊቷን መለስ አድርጋ አሻግራ ትመለከት ጀመር። ዐይኖቿ ከቤቱ ትይዩ ባለው ትልቅ የባሕር ዛፍ ላይ አረፉ። ቅርንጫፎቹ ላይ የሰፈሩት አሞሮች ትናንሽ ጎጆ ይመስላሉ። ወፎቹ በተንጠለጠሉ ጎጆዎቻቸው ዙሪያ ይበራሉ፤ ያርፋሉ። ዛፉ ቀጥ ብሎ ቆሟል።

አብሯት ቻርሊ በዛፉ ሥር ቡዝዝ ያሉ ዐይኖቹን መሬት ላይ እንደተከለ፣ ካፊያው ልብሶቹን እንዳራሳቸው፣ የዝናብ ጠብታዎች ፀጉሩ ላይ እንደተንጠለጠሉ፣ እንደተጠራጠረና ከፍት እንዳለው በህሊናዋ ታያት። እናም ታወያየው ጀመር።

"ምነው ግንባርህን ቋጥረህ ትመለከተኛለህ ቻርሊ?"



"አንቺ ምን እየሠራሽ እንደሆነ ልታስረጂኝ ትችያለሽ?"

"እመነኝ ቻርሊ፣ በማንም አልለውጥህም!"

"እኮ እንዴት አድርጌ ልመንሽ አብሬት። እየሽ፣ ቢያንስ አንድ ነገር አይጠፋኝም ሴት ነሽ!"

"ውው... ቻርሊ! ለምን ተጠራጣሪ ትሆናለህ?"

"የማይጠራጠር ልብ አንድ ቀን በገዛ ጅልነቱ እንደሚፀፀት አታውቂም"

"እባክህ ቻርሊ ቀናተኛ አትሁን! ቅናት እኮ መሠረቱ የፀናን የፍቅር ካብ ሳይቀር የሚደረምስ፣ ጥርጣሬ የሚወልደው ግሬደር ነው"

"ሰው በሚወደው ነገር ያልቀና በምን ሊቀና ኖሯል? ፍቅር ስስት መሆኑን አታውቂም? ደግሞ አንድ እውነት ላረጋግጥልሽ፤ በቅናት የማይገለጽ ፍቅር እውነተኛ ፍቅር አይደለም!"

"ቻርሊ!"

"በወደፊቱ ህይወታችን ውስጥ ምድር ያፈራቻቸው ምርጥ ነገሮች ሁሉ ንብረቶችሽ ይሆናሉ... በለውጡም እነኝህ ዋጋ ሊተመንላቸው የማይችሉ ውብ ዐይኖችሽ የብቻዬ ይሆናሉ ! ሃ ሃ ሃ ሃ ሃ..." የጠቢቃው ጆሮ የሚቧጥጥ ሳቅ ከሰመመኗ ቀሰቀሳት።

"ምን አልክ?" አለችው ራሷን እየነቀነቀች። ያለውን ያለንዳች ሀፍረት ደገመላት።

ይህ ሰው ፍቅርን በገንዘብ ሊገዛት፣ ህይወቷን በንዋይ ሊመነዝራት የታጠቀ መሆኑ ገባትና "ገንዘብህ ብዙ ነገር ሊያደርግልህ ይችል ይሆናል፤ ፍቅርን ግን ሊገዛልህ አይችልምና አትድከም" አለችው ፍርጥም ብላ።

በትክክል ያዳመጣት መሆኑን እየተጠራጠረ በመገረም ሲመለከታት ቆየና "እባባልሽ... ቃላዊ ውበት እንጂ እውነትነት የለውም። ልብ ወለዳዊ ፈዝ ነው። በዚህ ምድር ላይ የገንዘብ እጅ የማይደርስበት ርቀት፣ የገንዘብ ሀይል የማያንበረክከው ጉልበት፣ የገንዘብ ጥበብ የማይሰርዘው እውነት የለም። ሌላው ቀርቶ ሞትን እንኳን የሚያሸንፍ የዘመናችን ታላቅ ኃይል ገንዘብ ብቻ ነው። አስተውይ ጽጌሬዳዬ... ደማችን እንኳን በደም ስራችን ውስጥ የሚፈሰው በገንዘብ ኃይል ነው። ይህን ሁሉ ማድረግ የሚችል የዓለማችን ገናና ኃይል እንደምን ፍቅርን መግዛት ያቅተዋል ... ሃ ሃ ሃ ... ሃ ሃ ሃ ..." ባላዋቂነቷ እየተሳለቀ ተመጻደቀባት።

አልተረታችለትም። "አትሳሳት ወዳጄ፤ ገንዘብ ስጋን ሊያጠግብ... የስጋን ፈቃድ ሊሞላ የሚያስችል ኃይል ሊኖረው ይችላል። ፍቅር ግን ከነፍስ ነው። ቁሳዊ በሆነ አርቴፊሻላዊ ኃይል ደግሞ የነፍስ ጉልበት አይሰበርም። ለብልጭልጭ ውበት የነፍስ ዐይን አይማረክም። እርግጠኛ ነኝ ይህ የምትመካበት ገንዘብ የሂዋንን ዘር ቀፎ ገላ እንጂ የልቧን እምነት፣ የልቧን እውነት አይገዛልህም!" አለችው።

ትክሻውን ሰበቀና የቀዳውን ውስኪ ደጋግሞ ተጎነጨ። ቀጠለናም "ልጅነት ነው ወይስ ጅልነት?!" ብሎ ጀርባውን ሰጣት።

"እአ... ስድቡ እንኳን ይቆይህ... የመጣሽው እኮ እኔን ለመሳደብ አይደለም" አለችው።

"ይሁን፤ የገንዘብን ምንነት አንድ ቀን ከገዛ ህይወትሽ ውድቀት ትማሪዋለሽ" አላት በሀዘኔታ ራሱን እየነቀነቀ። የብርጭቆውን ውስኪ ተጎንጭቶ አጣጣመናም "አክስፎርድ ዩኒቨርስቲ ሳለሁ..." የጀመረውን እስኪጨርስ ግን እድል አልሰጠችውም። ያስቀመጠችውን መጽሐፍ አንስታ ጥላው ወደመኝታ ክፍሏ ገባችና በሩን ቆልፋ ተቀመጠች።

ጥቂት ቆይታም የመኪና ሞተር ሲያጓራና በሩ ተከፍቶለት ሲወጣ ሰማች። ሣትፈልገው ከህይወቷ ጋር የተጣበቀ ይህ የሰው መዥገር እንዴት እንደሚነቀል አጥብቃ ማሰብ ጀመረች።



# ክፍል ሁለት

## ምዕራፍ ዘጠኝ

የቲያትር ቤቱ ሥራ አስኪያጅ እርጅና ያጎሳቆላትንና ቀለሟ በመላላጡም በቲያትር ቤቱ ሠራተኞች "ጭርቶ" የሚል ስም የተሰጣትን አሮጌ ኦፔል መኪናቸውን ቅጥር ግቢው ውስጥ አቁመው ወደ ቢሯቸው አመሩ።

አጠር ያሉና ድብልብል ራሳቸው ላይ የጠጉር ዘር የማይታይባቸው ናቸው ታፈሰ ጓንጉል። የመኪናቸውን ቁልፍ እያሽከረከሩ ወደ ቢሯቸው ከገቡ በኋላ ዘወትር እንደሚያደርጉት ሁሉ መስኮት ከፍተው ሲጋራቸውን እየሳቡ የግቢውን እንቅስቃሴ ይቃኙ ጀመር።

ወጣት ተወዛዋዦቹ ከብብ ሰርተው እየተሳሳቁና እየተጎሻሸሙ ይጫወታሉ "እነኚህን ልጆች መሬት ጠበበቻቸው አይደለም?" አሉ ሥራ አስኪያጁ በመገረም። በርሳቸው ዘመን የነበሩት ወጣት አርቲስቶች ጭምቶች፣ ታማኞች፣ የሙያ ፍቅር የሚያንገበግባቸውና ሰርተው ደከምን የማይሉ ነበሩ። እነኚህኞቹ ግን ከሥራ ይልቅ ቧልትና ፌዝ የሚቀናቸው፣ የማይጨበጡ እሳቶች በመሆናቸው "አይ ጊዜ! ጊዜ የማይወልደው ጉድ የለም። ይሄን ለማየት በቃሁ" እያሉ ዘወትር ይደመማሉ።

ከወጣቶቹ ራቅ ብሎ ደግሞ ስድስት ሠራተኞች አፍ ለአፍ ገጥመው ያወጋሉ። ከመካከላቸው ታደለች "ወፌን" በማየታቸው የግጦሽ ጉባኤ በጠዋት መሰየሙን አልተጠራጠሩም። የያንዳንዱ ሠራተኛ ህይወት እንደ ሣር የሚነጭበት፣ የያንዳንዱ ጓዳ የሚመረመርበት የሀሜት ጉባኤ ነው።

"የኔንስ ስም ከነጋ ስንቴ አንስተውት ይሆን?" ሲሉ ታፈ ራሳቸውን ጠየቁ።

ወዲያውኑ ረኸሙ "ከርከሮ" እና አጭሩ "ዱኩላ" እጅ ለእጅ ተያይዘው ከቢሮ ቢሮ ሲሯሯጡ ፈገግ አሉ። ዛሬ እንዴት ሊፋቀሩ እንደቻሉም ገረማቸው። ሁለቱ ሠራተኞች ቲያትር ቤቱ ውስጥ የሚታወቁት በትኩስ ዜና ምንጭነታቸው ነው። ዓለም አቀፋዊና አህጉራዊ ወሬዎችን እንደየክብደትና ቅለታቸው ሲተነትኑ፣ በመላው

[illegible] የተተከሉ ግደከር ቼኮችን ቁልፎች በእጃቸው እንደሚያሽከረክሩ አያጠራጥሩም። መንግስት በቅርቡ ሊያወጣቸው ያሰቡቸውን መመሪያዎችና አዋጆች ሲያስረዱም ከአርቃቂዎቹ መካከል ያሉበት ይመስላሉ። ከባህል ሚኒስቴር ተጽፈው ታፌ ቢሮ ያልደረሱትን መመሪያዎችና ደብዳቤዎችማ በቀላሉ ጠልፈው ነው በቅድሚያ የሚነዙት።

"የኔን ጡረታ በተመለከተ ሰሞኑን ምን ወሬ ሰምተው ይሆን?" ሲሉ አሰቡ ታፌ። መቼም የጡረታ ነገር ሞታቸው ነው። በሁለት ምክንያቶች።

ታፌ ስምንቱን ልጆቻቸውን የወለዱት ከአምስት ሴቶች በመሆኑ እምቡቱም ጎጆዎች የርሳቸውን እጅ አይተው ነው የሚያድሩት። ልጆቹ እያደጉ በሄዱ ቁጥር ደግሞ የልብሱ፣ የጫማው፣ የትምህርት ቤት ወጭው፣ የኪስ ገንዘብ ጥያቄው አብሮ እያደገ በመምጣቱ ኑሮ ከብዷቸዋል። ታዲያ ሙሉ ደሞዝ እያገኙ ያልሞላላቸውን ኑሮ በጡረታ ገቢ እንዴት ሊዘልቁት ይችላሉ? ሲያስቡት ዝግንን ይላቸውና ደጋግመው ያማትባሉ።

ሁለተኛው ምክንያታቸው ካቀኑት ቲያትር ቤት ያለመለየት ፍላጎት ነው። የማታ ትምህርት በመከታተል በአስተዳደር የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን አግኝተው አሁን ከያዙት ከፍተኛ ሥልጣን ከመብቃታቸው በፊት ሰው ለመሆን ያልፈነቀሉት ድንጋይ አልነበረም። ተዋናይ፣ ድምጻዊ፣ ሙዚቀኛ፣ ተወዛዋዥ፣ የመብራት ባለሙያ፣ የህዝብ ግንኙነት ... ኧረ ስንቱን?! ከዘበኝነት በቀር ያልሞከሩት ሥራ ይኖር?

"ከስንቱ ተጋጭቼ፣ ለስንቱ አጎብድጄ፣ በወጣትነት እድሜዬ ያቀናሁትን ቤት በጡረታ ስም ሊነጥቁኝ?" ይላሉ እንባ እየተናነቃቸው። ይሄን ሳይፈልጉት የሚሮጥ እድሜ በምን ጠፍረው ያቆሙታል?!

ዐይናቸው የእኑ ከርከሮን እንቅስቃሴ ሲከታተል፤ ግእም ያለው የአልቶ ሣክስፎን ድምጽ ከጆሮቻቸው ጥልቅ አለ። በቄ "መፍዙዝ" በጠዋቱ ሥራ ጀምሯል ማለት ነው። ታፌን አንዳንዴ በጣም የሚደንቃቸው የሌሎች መንግስት መሥሪያ ቤት ሠራተኞችም እንደ እርሳቸው ሰዎች ለቁጥር የሚታክት ችንጉርጉር ጠባይ ይኖራቸው ይሆን የሚለው ጥያቄ ነው።

በርሳቸው ግምት ፊፅሞ ሊኖር አይችልም። ስለዚህም በጥበብ ማስተዳደር እንደሚኖርባቸው ያምናሉ። የሚቀጣውን ቀጥተው፤



ከእንዱ ስቀው፤ ሌላኛውን አበሻቅጠው "ጥበባዊ አመራር" በሚሉት አስተዳደራቸው አርቀው ነው ሠራተኛውን ቀጥ አድርገው የያዙት። በዚህ የተነሣ እየተኩራሩ "እኔ ይህን ቤት የለቀቅኩ ቀን እያንዳንድሽን ጅብ ይበላሻል!" በማለት ሠራተኞቻቸው ላይ መዛባንን ከጀመሩ ከራርመዋል።

በርግጥ አንዳንዴም እውነት አላቸው። እስኪ አሁን እንደነ በቄ "መፍዙዝ" ያሉትን ሠራተኞች በምን መመሪያ ማስተዳደር ይቻላል?! በቄ ድሮ ድሮ ታታሪና ሙያውን አፍቃሪ ሠራተኛ እንደነበር ያውቃሉ። ያለ እናት ያሳደገው ልጁ ለእድገት በህብረት የዕውቀትና የሥራ ዘመቻ ገጠር ሂዶ ውሃ ከበላው ወዲህ ግን የአዕምሮው ትክክለኛነት አጠራጣሪ ሆኗል። ግቢ ውስጥ ካለው ድንጋይ ላይ ተቀምጦ ለረዥም ጊዜ መሬት ላይ ያፈጣል።

ሲለው ደግሞ ገና ወፍ ሳይንጫጫ ሥራው ገብቶ የሣክስፎኑን አፍ እንደ ጡጦ ጎርሶ ሲሠራ የሚገላግለው ምሽት ብቻ ነው። አንዳንዴም ብቻውን እዚያው ያድራል። የሚያጅባቸውን ዘፈኖች አጥንቶ መድረክ ላይ ከወጣ ወዲያ መጋረጃ ሊከፈት ጥቂት ደቂቃዎች ብቻ ሲቀሩ "ወይኔ ልጄ፣ ... እንዴት ትታዘበኝ ይሆን?! አንተ አፈር ሆነህ እኔ እዚህ እጨፍራለሁ..." እያለ ተንሰቅስቆ የሚያለቅስበትና መሣሪያውን ወርውሮ እብስ የሚልበትም ጊዜ አለ። በዚሁ ሳቢያ መድረኩ ላይ የወጡ የሥራ ባልደረቦቹ ሳይቀር ልባቸው በሀዘን ይሰበርና በሙሉ ስሜት ጨዋታዎቹን ማካሄድ ያቅታቸዋል። በቄም ከወር በላይ ወደ ቲያትር ቤቱ ብቅ ሳይል ይሰነብታል።

ታፌ የበቄ "መፍዙዝን" ዜማ እየሰሙ ዐይናቸውን ወደ ሌላ አቅጣጫ ሲወረውሩ ሠራተኛው "ኩላክ" /ሁብታም ዝቤ/ እያለ የሚጠራቸውን ሁለት ሠራተኞች ተመለከቱ። ሰዎቹ በአለባበሳቸው፣ በአረማመዳቸውና በአነጋገራቸው ሳይቀር ከሌሎች ሠራተኞች ለየት ያሉ ናቸው።

እሳት የላሱ ደላሎች በመሆናቸውም መኪና፣ የቤት እቃ፣ ሰዓት፣ የማያሻሽጡት ነገር የለም። እናም ወር መድረስ ላቃታቸው ሠራተኞች በድብቅ አራጣ ያበድራሉ፤ በበአላት ቀን ፍሪዳ ጥለው ቅርጫ በማውጣት ከደሞዝ ይሰበስባሉ፤ ጫማ፣ የኤሌክትሪክ ምጣድ ... በዱቤ በማቅረብ ሠራተኛውን "ጠቅመው" እነርሱም ይጠቀማሉ። የአብዛኛውን ሠራተኛ ኢኮኖሚያዊ ህይወት እየተቆጣጠሩት በመሆኑም ራሳቸውን ቢሮ እንደሌላቸው ባለስልጣኖች አድርገው ነው የሚቆጥሩት። ከብድሩ ጠበል ታፌም ብዙ ጊዜ ተጎንጭተዋል።

ሥራ አስኪያጁ ዘወር ሲሉ ግድግዳ ተደግፎ ሲጃራ የሚያጨሰውን ዳንኤል "ጅምርን" አዩና "እዩኝ እዩኝ" ያለ ደብቁኝ! ያበዛል" በማለት ተዛበቱበት።

ዳንኤል እጅጉ በቲያትር ጥበብ ሁለተኛ ዲግሪውን ይዞ ከውጭ እንደተመለሰ፣ "ጥበባዊ" አመራራቸውን የተፈታተነው መሆኑ ትዝ አላቸው። በሙያው ከኔ በላይ ለአሳር ባይነቱና ሞገደኛነቱም ብዙ አዳርሷቸዋል። ራሳቸው በቲያትር ቤቱ ያስቀጠሯትንና በወዳጅነት ይዘው የወጣትነት እድሚዋን የተጋሯትን ሣራ ጋዲምንም ከጃቸው ፈልቅቆ በመውሰድ የሠራተኛው መሳቂያ አድርጓቸዋል።

በዚህ ምክንያት ዳንኤልን የሚጥሉበት መላ ሌት ተቀን ሲያውጠነጥኑ ሳለ ባላሰቡት መንገድ የወጥመዳቸውን ጫፍ ረገጠላቸው ። ከዚያ ወዲህ በተራው የሠራተኛው መሳቂያ፣ የህዝብ መጠቃቀሻ ሆነ። ዛሬ ዳንኤል ብቻውን ቢሮ ቆልፎ ሲጋራውን በላይ በላዩ ሲያጨስ ነው የሚውለው። ታፌ ግን እንዲህ ሆኖ እያዩም አልተኙለትም። የቆሰለ እንበሳ ጊዜና አቅም አግኝቶ ከተነሳ ሊያደርስ የሚችለውን ጥፋት በመገመት ጅምራቸውን ለመጨረስ አሁንም እያደቡ ነው። "ጠላትህን ቀድመህ ቅስሙን ስበረው፤ የህይወት ተስፋውንም አጨልምበት፣ የእምነቱን መሠረት ናደው... ነፍሱ በቁም ይወድቃል። ያኔ የሥጋ ሞቱን እሱው በእጁ ይፈፅመዋል" የሚል ፍልስፍና አላቸው።

የዳንኤልንም ነፍስ ገዝግዘውታል። በዋዛ ልትቀነጠስላቸው ባለመቻሏ ግን አሁንም ትንንቁን ቀጥለዋል። ዐይናቸው ቀዝቃዛ የበቀል ጉም እንደለበሰ ሲመለከቱት ቆይተው "አንድ ቀን ያበቃልሃል!" ሲሉ ዛቱበት።

ወደ ሌላው አቅጣጫ ገልመጥ ሲሉ ደግሞ ባልተከፈተው የገንዘብ ቤት ቢሮ ላይ ብድር ለመውሰድ የሚተራመሱ በዛ ያሉ ሰዎችን ተመለከቱ። ቻርሊ ግንባር ቀደም በመሆን በሩን ተደግፎ ቆሟል። "ክይሲ!" አሉ ስራ አስኪያጁ በቁጣ።

ሌላው የታፌ አመራር ቀንደኛ ተቃዋሚ ዝነኛው ተዋናይ ቻርሊ ነው። ሥራ አስኪያጁ ስለ እርሱ ሲናገሩ "በችሎታማ ማን ደርሶበት? ታዲያ በየት የተጻረረው አጋንንት?! ጋግርት!" በማለት እያሞገሱ በዜሮ ያባዙታል።



ታፌ እንደ እንቅርት ተከምሮ ማንቁርታቸውን ያነቀውን ስጋ [illegible]ቸው ሲያባብሱ ቆዩና በብሽቀት ፈገግ አሉ። "እከክ ልበስና ይሆን 'ኩልኩልት' የሚሉ የስም እከክ እንዳለበስከኝ አትቀርም!" በማለት በቻርሊም ላይ ጥርሳቸውን ነከሱበት።

ቻርሊ "የተዋናይ መብት ይከበር!" እያለ ተዋናዩን በማሳደም አመራራቸውን ሲፈታተነው ቢሯቸው ጠርተው በዘለፋ ወረዱበት። አለቅነታቸውንና እድሜያቸውን በማመዛዘን በዝምታ የሚያልፉቸው መስሏቸው ነበር። ቻርሊ ግን በንዴት እየተንጨረጨረ "ጥበቡ ሊከበር የሚችለው'ኮ የተዋናዩ ሰብእና ሲከበር ነው። የሚያበራየውን በሬ ስለምን አፉን ሸበባችሁት? የአንተ የራስህ ኩልኩልት የሰባው በእኛ ላብ መሆኑን አታውቅም!" ሲል ጮኸባቸው። ቢሯቸው ቆሞ የነበረው ረዥሙ ክርክሮ ሳቁ ሳያመልጠው አፉን ሸፍኖ ሮጦ ወጣ። ሩብ ሰዓት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ዜናው ሠራተኛው ጆሮ ደረሰ። ከዚያች ቀን ጀምሮ ታፌ በተከበረው ስማቸው ላይ "ኩልኩልት" የሚል ቅጥያ አንጠልጥለው ቀሩ "አንተም ቀንህን ጠብቅ!" ብለው ዛቱና ያለቀ ሲጋራቸውን ወረወሩ።

ታፌ የቲያትር ቤቱን ሠራተኞች ሙያዊና ግለሰባዊ ባህርይ በነፍስ ወከፍ ደረጃ ያውቃሉ። በርሳቸው ግምት የአስተዳደር ሠራተኞች፣ ፀሐፊዎች፣ የሂሣብ ክፍል ሠራተኞች፣ የህዝብ ግንኙነትና የጥበቃ ሠራተኞች፣ ተላላኪዎች፣ አናፂዎችና የኤሌክትሪክ ቴክኒሽያኖች ደሞዛቸው በጊዜ ከተከፈላቸው፣ ጭማሪያቸው ወቅቷን ጠብቃ ከተጣለችላቸው እምብዛም ችግር የማይፈጥሩ ገራም በጎች ናቸው። ከአመራራቸው ውልፍት የሚል ቀበጥ ከተገኘም በጽሁፍ ማስጠንቀቂያና በአስር ብር ቅጣት ልክ ይገባል።

በሙዚቃና በውዝዋዜ ክፍል ያሉት ሠራተኞች ጠባይ ከነዚህ ለየት ያለ ነው። ድምፃውያኑ፣ የባህልና ዘመናዊ መሣሪያ ተጫዋቾች እንዲሁም ተወዛዋዦች ራሳቸውን ደስተኛ ለማድረግ የሚጣጣሩ ይመስላሉ። በአለባበሳቸው የፀጉና በአነጋገራቸው የዘመኑ፣ ፈገግታ ከገጻቸው ላይ የማይርቅ ናቸው። ጉስቁልናቸው በየጉዳቸው እንጂ በአካላቸው ላይ አይታይም። ጭንቀታቸው ከውስጥ እንጂ ገጻቸው ላይ አይነበብም። አብዛኞቹ በሙያው ፍቅር የናወዙ የመድረክ ረሀብተኞች በመሆናቸው ላባችውን አንጠፍጥፈው፣ ወገባቸው እስኪቀነጠስ ጨፍረው፤ ጉሮሯቸው እስኪተረተር ጮኸው የጥበብ ረሃባቸውን ይጠግባሉ፤ የሙዚቃ ጥማታቸውን ይወጣሉ። የዘወትር ጥረታቸው ሰዎችን አስደስተው ራሳቸው መደሰት ነው። ህልማቸውም በያዙት ሙያ ኮከብ ሆነው መገኘት ነው።

እነህ ሠራተኞች በታፈ አመራር ላይ ጠንከር ያለ ችግር አይፈጥሩም። ይልቁንም እርስ በእርሳቸው በሚያደርጉት ሽኩቻ በሥራው ላይ የሚፈጥሩት ችግር ይብሳል። ባለሙያዎቹ ከውጪ ሲያዩዋቸው ፍቅር ያላቸውና እንደ ድር አብረው አንበሳ መጥለፍ የሚያስችል ህብረት ያላቸው ቢመስሉም፤ ውስጣቸው ግን በአንድ ሺ አይነት ቅራኔ ተወጥሯል። ታፈ በዚህ በጣም ይደሰታሉ። "ሠራተኛ ቂጥ ለቂጥ ከገጠመ..." ይላሉ ዘወትር። ምንጊዜም የሚደንቃቸው ግን የሠራተኞቹ ጠብ ውሎ አለማደሩ ነው። ጠዋት ላይ "ሊጋደሉ ይፈላለጋሉ" የተባሉ ባለሙያዎች፣ ከቀትር በኋላ ትከሻ ለትከሻ ተቃቅፈው ሲስቁ ያያሉ። ስለዚህም ታፈ "በውሻ ሆድ ቅቤ፣ በአዝማሪ ሆድ ቂም ውሎ አያድርም" እያሉ ይተርታሉ።

የሙዚቃው ክፍል አርቲስቶች በገንዘብ ላይ በመጣ ነገር ቀልድ አያውቁም።

ለዚህም ነው ይላሉ ታፈ ሙዚቀኞቹ እንደ ረዳት ሾፌር "እንሂድ" ማለት የሚያዘወትሩት። የህዝብ ግንኙነቱን በየክፍለ ሀገሩ የጉዞ ፕሮግራም እንዲዘጋጅ የሚወተውቱት፣ አስተዳደሩን የውሎ አበሏ ጠቀም እንድትል የሚነተርኩት። ታፈ ከነኚህ ውስጥ የሚጎረብጥ አርቲስት ካጋጠማቸው ከክፍለ ሃገር ጉዞ እንዲሰረዝ በማድረግ ለወደፊት ሰጥ ለጥ ብሎ እንዲገዛ ያደርጋሉ።

የቲያትር ክፍል አርቲስቶች ግን ለታፈ የወገብ ላይ ቅማሎች ናቸው። አብዛኞቹ ለአለባበሳቸው እምብዛም የማይጨነቁ፣ ብዙ ከመናገር ይልቅ ማድመጥን የሚወዱ፣ ገጽታቸው ፈገግታ የሸሸውና የሀዘንተኝነት ድባብ ያጠላበት ነው።

አብዛኛውን ጊዜ የሚጋጩት ከራሳቸው ጋር ቢሆንም፤ ይህ ውስጣዊ የመንፈስ ሙግት ሲከር የአርቲስቱ ተጋፊነት ገደብ አይኖረውም።

ብዙዎቹ ለራሳቸው ያላቸው ግምትና ክብር ከፍተኛ መሆኑ ታፈን ይደንቃቸዋል። ሥራ አስኪያጁ ስለተውኔት ባለሙያዎች ሲናገሩ "... ዓለም ያለተውኔት ጨው እንደሌለው ወጥ ናት ብለው ስለሚገምቱ ኩሩዎችና ትምክህተኞች ሆነዋል። ጥበቡ ያለነርሱ ሊኖር ባይችልም ህዝቡ ግን ያለ ተውኔትም ሆነ ያለ እነርሱ መኖር እንደሚችል አይገነዘቡም" በማለት ይተቿቸዋል።



በታፈ ግንዛቤ ተዋንያኑ የሥራ ግዴታቸውን ለመወጣት የመጨረሻዎቹ ለመብታቸው ለመጮህ ግን የመጀመሪያዎቹ ናቸው። ከሥራ በመቅረት፣ በልምምድ ወቅት አካላዊም ሆነ መንፈሳዊ ቅድመ ዝግጅት አድርጎ ባለመገኘት፣ ከአዘጋጆች ጋር በመጋጨት፣ የመድረክ ሥነ-ሥርዓት በመስበር የሚደርስባቸው የለም። በተቃራኒው ለእድገት የሚጮሁ እነሱ፤ የሙያ ስልጠና የሚጠይቁ እነሱ፤ በውይይት ክበቦች ውስጥ አጀንዳ እየጣሱ ስለ መስሪያ ቤቱ የአስተዳደር ዝርክርክነት የሚወተውቱ እነሱ፤ የመንግስት ሀብት ያለ አግባብ ባከነ፣ አድልዎ ተስፋፋ እያሉ የሚጮሁ እነሱ በመሆናቸው የታፈ ዐይን ዘወትር እንደቀላባቸው ነው።

ተዋንያኑ ውስጣዊ አንድነት የላቸውም እንጂ እንደ እንደበተ ርቱዕነታቸው ጥበባዊ አመራራቸውን በቀላሉ ሊንዱት እንደሚችሉ ታፈ በሚገባ ያውቃሉ። ዳሩ ግን ከቅርብ ዓመታት ወዲህ በተዋኒያኑ መካከል የሚታየው ልዩነት እየሰፋ በመምጣቱ ታፈ ፈንጥዘዋል።

ሙያውን በዩኒቨርሲቲ ደረጃ ባጠኑ አርቲስቶችና ሙያውን በተፈጥሮ ችሎታና በረዥም ጊዜ የመድረክ ልምድ በተካኑት አርቲስቶች መካከል በተፈጠረው ከረር ያለ ሽኩቻ ሣቢያ፣ የተዋንያኑ የጋራ ጩኸት ታፍኗል ። በዚህም ታፈ ደስተኛ ናቸው።

በዳንኤል ዙሪያ የተሰለፉት የተማሩት አርቲስቶች "ተውኔት ህይወትን በመድረክ የሚተረጉም የጥበብ ሳይንስ ነው። በመሆኑም በማህበረሰቡ ታሪክ፣ ባህል፣ ቋንቋ፣ ስነ ልቦናዊ አመለካከት፣ ፖለቲካና ኢኮኖሚያዊ ህይወት ላይ ተመስርቶ የገሃዱን ዓለም ህይወት ጥበባዊ ኩል በመኳል አሳምሮና አስውቦ፤ ማህበረሰቡ ራሱን በመድረክ እያስተዋለ እንዲያደንቅ፣ እንዲታዘብ፣ እንዲያዝንና እንዲጠላ የሚያስችለው መስተዋት ነው" የሚል እምነት አላቸው።

በነርሱ እምነት ይህ ጥንታዊ ጥበብ ታሪክ ያለው እንደመሆኑ መጠን፣ እንዴትና መቼ እንደተጀመረ መታወቅ አለበት። ጥበቡ ባሳለፋቸው ረዥም ዘመናት በየሃገሩ ምን መልክ ነበረው? እድገቱስ ከየት ተነስቶ የት ደረሰ? በየዘመኑ የጥበቡ ቁንጮ የነበሩ ጠቢባን እነማን ናቸው? ግላዊ ባህሪያቸውና አኗኗራቸውስ ምን ይመስል ነበር? ይህ ሁሉ መጠናት አለበት።

"የተውኔት ጥበብ ታዳጊ ነው። እለት ተለት እያደገና እየተወሳሰበ በሚሄደው የሰው ልጅ ማህበራዊ ኑሮ ውስጥ የሰዎች ባህል፣ የአኗኗር ዘይቤና ስነ-ልቡናዊ አመለካከት ይበለጽጋል፣ ይለወጣል። ከአዲሱ ዘመን ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ችግር ጋር የአዲሱ

ሰው ማህበራዊ ችግርም ይወለዳል። በአዲስ ማህበራዊ ቅራኔዎች የተወጠረውን አዲስ ሰው አዲስ ስነ-ልቡናዊ አመለካከት ከሰው ልጅ መሠረታዊ ባህርያት ጋር እያገናዘቡ ለመቅረጽ ደግሞ ዘመናዊውን የመድረክ ዝግጅትና የአተዋወን ጥበብ መማር ግድ ነው። ሥነ-ተውኔት በተማረ፣ በተመራመረና በሰላ ህሊና ካልተመራ እንደተከተረ ውሃ ካለበት ፈቀቅ የማይል፣ እየቆየም የሚበሰብስ ጥበብ ነው" በማለት የሠላ ሂሳቸውን በልምድ ተዋንያኑ ላይ ይሠነዝራሉ።

በቻርሊ ሥር የተሰባሰቡት የልምድ አርቲስቶችም የነዳንኤልን በትር ለመመከት አይሰንፉም። "ተዋናይ ለተውኔት ይፈጠራል፤ የእናቱን ጡት እንደጎረሰ የሰዎችን ገጽ ያጠናል፤ ፊደሉን እንደጨበጠ የሰዎችን ባህሪይ ይመረምራል። የተዋናይ ዩኒቨርስቲው መድረኩ፣ ዲግሪውም የህዝብ ድጋፍና ተቀባይነት ነው። ጭንቅላት እንጂ ወረቀት መድረክ ላይ ቆሞ አይተውንም!" በማለት የነዳንኤልን ትምክህት ይመክቱታል።

ታፈ ሁለቱንም ጎራዎች አብይና መለስተኛ ውጋቶች በማለት በደረጃ መድበዋቸዋል። ባለወረቀቶቹ አርቲስቶች የቲያትር ቤቱ አመራር በሙያው በሰለጠኑ ምሁራን መያዝ አለበት የሚል ክረር ያለ አቋም በመያዛቸውና በባህል ሚኒስቴር ውስጥና ከዚያም በላይ ስልጣን ባላቸው የሙያ ጓደኞቻቸውም የሚታገዙ በመሆናቸው "በነፍስ የመጡ!" ተብለው በቀይ ቀለም ተሰምሮባቸዋል።

ባለ ልምዶቹ ደግሞ ለሙብታቸው አብዝተው በመጮሃቸው፣ በማያገባቸው የአስተዳደር ጉዳይ ውስጥ የእርጎ ዝንብ እየሆኑ በማሳጣታቸው በመለስተኛ ውጋትነት በአረንጓዴ ቀለም ተይዘዋል።

ከሁለት ዓመት በፊት በዳንኤል አዘጋጅነት የተሠራው ተውኔት በህዝብ ዘንድ ተቀባይነት አጥቶ ከተነሣ ወዲህ በታፈ ነፍስ የመጡት ውጋቶች ጡጫ ረገብ ብሏል። ቻርሊም ቢሆን ተሰፋ የቆረጠና ሀሞቱ የፈሰሰ ስለሚመስል፣ ጩኸቱ እንደ ቀድሞው ጎልቶ አይሰማም። በመሆኑም ታፈ ላለፉት ሁለት ዓመታት ፋታ አግኝተዋል። ጨርሰው ግን አላንቀላፉም። እርስ በርስ ተቦጫጭቀው ያሸለቡት ሁለት አንበሶች እስኪጨራረሱ ድረስ በጥበባዊ አመራራቸው ከተኙበት እያነቁ እንዲፋጠጡ እያደረጉ ነው።

ታፈ ከባህል ሚኒስቴር ለቲያትር ግምገማ ኮሚቴ አባልነት ከቲያትር ቤቱ ባለሙያዎች ሁለት አርቲስቶችን መርጠው እንዲልኩ ሲጠየቁ፣ ቻርሊንና ዳንኤልን አቀራኝተው መላካቸው ያለ ምክንያት አልነበረም። በአንድ ጠረጴዛ ዙሪያ ተገናኝተው እንዲፋለሙ፣



እንዲቦጫጨቁና እንዲተናኮሉ በማሰብ ነበር። ኢላማቸው ውሉን አልሳተም፤ ያነጣጠሩት ቀስት ዝንፍ አላለም። ሁለቱ ባላጋራዎች በነገር እየተቋሰሉና በሽሙጥ እየተላሉ የኮሚቴውን የሥራ ሂደት ማሰናከላቸውን ሰምተዋል።

ሁለቱ አንድ ካልሆኑ የተዋናይ ህብረት የሚባል ነገር አይኖርም። የተዋናይ ህብረት ከሌለ ደግሞ ታፈ "ያለሳቸው ቤቱ ሙች ይቻልና" እየተባሉ በአመራር ችሎታና ብስለታቸው ተደንቀው ይኖራሉ። የጡረታ ጊዜያቸውም እንደሚራዘም እምነታቸው የጸና ነው።

ድጋሚ ለኩሰው ያጨሱትን ሲጋራ ወረወሩና ተሽከርካሪ ወንበራቸው ላይ ቂብ አሉ። ጠረጴዛቸውም ላይ ፊርማቸውን የሚጠብቅ ማስታወቂያ ተመለከቱ። ማስታወቂያው "የመከኑች ተስፋ" የተሰኘ አዲስ ተውኔት ለቲያትር ቤታችን ስለተላከ፣ ቲያትሩን ለማዘጋጀት መወዳደር የምትፈልጉ ተመዝገቡ" የሚል ነው። ታፈ ዳንኤልን ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ የሚመቱበት በትር ታያቸውና ብቻቸውን ከምከም ብለው መሳቅ ጀመሩ። ይህ አዲስ እቅድ እንደሚሰምርላቸውም አልተጠራጠሩም።

በጣታቸው የቆዳ ወንበራቸውን መደገፊያዎች እየጠበጠቡ "እኔ በምመራው ቤት ውስጥ ቻርሊና ዳንኤል የተሰኙ ሰይጣኖችን ዐይኖቹ ማየት አይሹም!" በማለት አጉተመተሙ። ፊጥነውም በማስታወቂያው ላይ ፈረሙ።

# ምዕራፍ አሥር

ራስ ሆቴል የተዘጋጀው የዳንስ ምሽት ከተጀመረ ሶስት ሰዓት ሊሞላው ነው። ቀዝቀዝ ብሎ የተጀመረው ጨዋታ በየደቂቃው እየጋለ ሄዶ ተሟሙቋል። መብራቱ የሙዚቃውን ሂደት ተከትሎ ብልጭ ድርግም ሲል፣ ሙዚቃው እንደ ነጎድጓድ ሲያስገመግም፣ አቀንቃኙ እንደ ብራቅ ሲጮህ፣ ደናሹ እንደ እንዝርት ሲሾር፣ የሰከረው እየወደቀ ሲነሳ፣ ሞቅ ያለው ከአቀንቃኙ እኩል እየጮኸ እጅና እግሩን ሲያወናጭፍ፣ ቤቱን ካፈነው የሲጋራ ጭስና እንደእሳት ከሚፋጀው የሞቀ አየር ጋር አዳራሹን የሃጥአን ነፍስ በጋለ ብረት ምጣድ ላይ የሚታመስበት ገሃነም አስመስሎታል።

ጥግ ላይ ሰታዎቹ በቡጢ መናረት ጀምረዋል። ሊገላግላቸው የሞከረ አልነበረም። በሌላኛው ማእዘን ጉብሉ የጉብሏን ከንፈር ይመጣል። ዞር ብሎ እንኳን የሚያስተውላቸው የለም። እልፍ ብሎ ከመፀዳጃ ቤቱ ትይዩ አንዱ ተንበርክኮ ያስመልሳል። የመጣው ሁሉ በፍጥነት እየተራመደው ያልፋል።

ዳንኤል እጅጉ ያጋባቸው የቢራ ጠርሙሶች ጠረጴዛውን ሞልተውታል። ሣራ ጋዲም አጠገቡ ተቀምጣለች። እርሱን የምታዳምጥ ብትመስልም ቀልቧ ግን ያለው ከዳንኪረኞቹ ጋር ነው። ላለፉት ሁለት ዓመታት ስትሰማቸው የነበሩትን የብሶት እንጉርጉሮዎች ዛሬም እንዲያቋዝንባት አልፈለገችም።

"የኔ ስህተት ወይም የኔ ድክመት ብቻ አልነበረም፣ ሣራ... እኔን ለመጣል ፣ የኔን ቅስም ለመስበር ሲሉ ከያለበት ተጠራርተው ተረባረቡብኝ። አልጣሉኝም ብየ አልዋሽሽም ሣራ... ጥለው ረግጠውኛል...ግን..." በሁለት እጆቹ ፊቱን ሸፈነና ፀጥ አለ።

"እቤቱ ፈጣሪዬ! የዚህ ጣር ማብቂያ መቼ ይሆን?" ስትል አሰላሰለች ሣራ ጋዲም።

እጆቹን ከፊቱ ላይ አንስቶ በፀጥታ ተመለከታት። የፊቱን አቀማመጥ ትወደዋለች። አጠር ባለው ጥቁር ፊቱ ላይ ጠልቀው የሚያዩት ጎላ ጎላ ያሉ ዐይኖቹ ይማርኳታል። ረዘም ፈርጠም ያለ ወንዳወንድ አቋሙንና ረዣዥም እጆቹን ትኩራባቸዋለች። ሁለመናው ያስደስታታል። ልቧ ግን ምንግዜም እንደሸሸው ነው። ሣራ ጋዲም ወንድን ልጅ ማቅበጥ፣ ማዝናናት እንጂ ማፍቀር እርሟ ነውና።



ከታሌ ኩልኩልት መንጋጋ ፈልቅቆ ሲያወጣት አብራ[illegible] ብዙ የምትቆይ አልመሰላትም ነበር። በሴሰኝነቱ ብዙ ይታማ [illegible]ረና እርሷም ወንድ አይበረክትልኝም የሚል እምነት ስለነበራት እንደ[illegible]ቹ ጊዜ ልታሳልፍበት ነበር የተጠጋችው። እየቀረበችው በመጣች ቁጥር ግን ብቸኝነቱና ደግነቱ ያሳዝናት ጀመር። ቁጥር ሰፍር ከሌላቸው የወንድ ጓደኞቿም ለየት ባለ ዐይን ልትመለከተው ያስቻላት ይሄው ነበር።

"ግን ለምን? ምን አደረኳቸው? እኔ ለሰው ክፉ ነኝ ሣራ?!" ዐይኖቹ ደፍርሰዋል፣ ግምባሩ ላይ ያሉት ስሮች መፍጠጥ ጀምረዋል። ሣራ አልመለሰችለትም። ይህን ጥያቄ ሺ ጊዜ ጠይቋት ሺ ጊዜ እንዳልሆነ ገልፃለታለች። አሁን ደግሞ ልቧ ያለው ዳንሱ ላይ ነው። ሮጠሽ ከዳንኪረኞች ጋር ተቀላቀይ የሚል ስሜት ከውስጧ እየታገላት ትቁነጠነጣለች።

ቀጭን ሰውነቷ ላይ ጥብቅ ያለው ደማቅ አረንጓዴ ቀሚሷ የብዙዎቹን ደናሾች ዐይን እየቀለበ ፊቷ ላይ ይከሰክሰዋል ። ወርቃማ ቀለም የተቀባው አጭሩ ፀጉሯ ይስባቸዋል፣ ትናንሽና ብልጣብልጥ ዐይኖቿ ያባብሏቸዋል፣ ፊት ለፊቷ የተቀመጠው የዳንኤል ግርማ ሞገስና የተቋጠረ ግምባሩ ደግሞ ሁሉንም ያሸሻቸዋል።

"በቲያትር ጥበብ ዲግሪዬን አግኝቼ ካባ ሳጠልቅ በጣም አዝኜ ነበር። ለምን ይሄን ሙያ መርጬ እንዳጠናሁ ምክንያቱ እንኳን አልገባኝም ነበረ። እንደ ጓደኞቼ የአስተዳደር፣ የህግ፣ የፍልስፍና፣ የሣይንስ ትምህርት አጥንቼ እነርሱ የደረሱበት መድረስ ስችል ለምን በእሳት መጫወት እንዳሰኘኝ አላውቅም። ምናልባት የልጅነቴ ዓመታት..." ፀጥ አለ። ይህን እንኳን ለሣራ ሲነግራት አልፈለገም።

ገና የአምስተኛ ክፍል ተማሪ ሣለ ነው ድርሰት መስረቅ የጀመረው። ከቆዩ ጋዜጦችና መፅሀፍት ላይ የሚቀዳቸውን ግጥሞች በአማርኛ የትምህርት ክፍለ ጊዜ መምህሩ ባሉበት ለተማሪዎች ያነብላቸዋል። አፋቸውን ከፍተው ያዳምጡታል። መምህሩ ተማሪዎቹ ፊት አቁመው ትከሻውን ያዝ ያደርጉና "ታዘቡኝ ይሄ ልጅ አንድ ቀን ታላቅ ባለቅኔ፣ ታላቅ ደራሲ ይሆናል" ይሏቸዋል። ተማሪዎቹ ያከብሩታል። እንደ ትምህርት ቤት ጓደኛቸው ሳይሆን እንደ አስተማሪያቸው ይቆጥሩታል። ...ገና ትንሽ ልጅ ሳለ እንኳን ስሙ ትልቅ ነበረ። መንፈሱ ግን ሁሉጊዜም እንደተሸበረ፣ እንደተቅበዘበዘ ነው። ምናልባት አንድ ቀን ሌብነቱ ቢታወቅ፣ እንደ ሸንበቆ የተመዘዘው ስሙ እንደሙቀጫ ሲንከባለል፣ የሚያከብሩት ሲንቁት፣ የሚወዱት ሲጠሉት ይታየውና በኩራት ያበጠች ልቡ በጥርጣሬና

በለጋት ጦር እየተወጋች ትተናፍሳለች። ከትልቅ ሰሙ ጀርባ ትንሹ እሱነቱ ይታየውና ማንነቱ ጠፍቶት በጭንቀት ይባዝናል።

በነዚያ ዓመታት ከጓደኞቹ በታች ያደርገው የነበረው የተቀዳደደ ቁምጣ ሱሪው፣ በላዩ ላይ የነተበ ሸሚዙ፣ ጫማ የማያውቀውና ውርጭ ያነቃው ተረከዙ ነበረ። በዚህ ግን አያፍርበትም። "ባለቅኔ" እያሉ የሚደርቡለት የስም ካባ ቀዳዳው ሸሚዙ፣ እንዳይታየው ዐይኑን ይጋርድለታል። "ደራሲ" እያሉ የሚያጠልቁለት የስም ቀሚስ የተረከዙን ንቃቃት ይሸፍንለታል። ስሙ እርዛቱን የሸፈነበት፣ የበታችነት ስሜቱን የጋረደበት ጋሻው ነበረ።

እያደገ ሲሄድ ከጋዜጦችና ከመጽሄፍት የሚቃርማቸውን የሰነ ጽሁፍ ሥራዎች ማቅረቡን እርግፍ አድርጎ ትቶ የራሱን የግጥም ስንኞች ለመቋጠር፣ የራሱን ድርሰቶች ለመጻፍ ቀን ከሌት መጣር ጀመረ። አልተዋጣለትም። ከውስጡ የሚጮህ የዝነኝነት ረሃብ ግን ነፍሱን እረፍት እንደነሳት ቀረ።

እናም የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱን በከፍተኛ ውጤት አጠናቆ የውጭ ትምህርት እድል እንዳገኘ የመረጠው የቲያትር ጥበባት ትምህርት ነበር። ከህዝብ ዐይን ላለመራቅ፣ የስምና የዝነኝነት ረሃቡን ለመጥገብ። ዳንኤል ከትዝታው ዓለም መለስ ብሎ ከቢራው ተጎነጨለት።

"የቲያትር ጥበባት ጥሪ ሣበኝ። ልቧን ከፍታ ሰጠችኝ፤ ገመናዋን ገልጣ አሳየችኝ። ወደድኳት ወደደችኝም። ትምህርቴን ጨርሼ የምረቃውን ካባ ለብሼ ስቆም የጥበቡን ሙሉ ሚስጥር አጣርቼ ያወቅኩ መስሎኝ ነበር። በራስ የመተማመን መንፈሴና ኩራቴም እንዲህ አልነበረም ሃ ሃ ሃ ሃ.... ውው" የምጸት ሳቁ ከሚጮኸው ሙዚቃ እኩል አስተጋባ። ሣራ ደንግጣ አስተዋለችው።

"ሃገሬ መጥቼ የመጀመሪያውን ትያትር ላዘጋጅ መድረክ ላይ ስወጣ ነበር የደነገጥኩት። ስድስት ዓመት ሙሉ ምንነቷን ለማወቅ የደከምኩላት፣ ቀን ከሌሊት አፍንጫዬን መጽሀፍ ውስጥ ቀብሬ የፈለኳት ጥበብ ያላገጠችብኝ መሆኑ ገባኝ። እንደ ውቅያኖስ ከጠለቀው ሚስጥሯ በእፍኝ እንኳን እንዳልጨለፈችልኝ፣ በጓዳዋ ከታመቀ ገመናዋ በእርቦ እንኳን እንዳልሰፈረችልኝ ተረዳሁ።

ሣራ "ይህን ሁሉ አጣርቼ አውቃለሁ" ብላ አፉን ልታሲዘው ፈለገችና ስላሳዘናት በትግስት አለፈችው።



"ያዘጋጀሁት ቲያትር ወደቀ! ገና የመክፈቻው ቀን [illegible] ቲያትሩ... ያላስደሰተው ተመልካች ከፊሉ ጥሎ ሲወጣ ይሉኝታ [illegible] ደግሞ በቅምጡ አንቀላፋ። ቲያትሩ መታየት ከጀመረ ወር [illegible] ሳይሞላው አዳራሹ ኦና ሆነ"

"ይህ ሁሉ ሲሆንኮ እዚያው ነበርኩ" ልትል አሰበች ሣራ። ዳንኤል ግን ጊዜ አልሰጣትም። "ቲያትሩ ለምን ወደቀ ብለሽ አትጠይቂኝም? ወይንስ አንቺም የኔ ድክመት በመሆኑ አምነሻል?" ሲል አፈጠጠባት። አሁንም መልስ እስክትሰጠው አልጠበቃትም። "የችግሩ ሁሉ ምክንያት እኔን አድርገው... ሂስ በሚሉት ቅስም መግደያ የሾህ ጅራፋቸው ገረፉኝ። ለቲያትሩ ውጤታማ አለመሆን ግን ተጠያቂው እኔ ብቻ አልነበርኩም። ደራሲውና ተዋንያኑም ጭምር እንጂ። ቱጋ! የርሱ ዱልዱም ብእር በጫረው ደካማ ድርሰት ምክንያት፤ ያ ሁሉ የሂስ ናዳ ቢቀጠቅጠኝ እርሱ ዳር ቆሞ ይስቅ ነበር። ጭራሽ ዐይኖቹን በጨው ታጥቦ 'እዘጋጁ ተጫወተበት እንጂ ድርሰቱ እንኳን ጮማ ነበር' እያለ ከጠላቶቼ ጎን ተሰልፎ ያወግዘኝ ጀመር። አሁን ባየሁት ቁጥር ጉሮሮውን አንቀህ ሲጥ አድርገው ነው የሚለኝ!" ዐይኖቹን አፍጥጦ የሁለት እጁን ጣቶች ጭፍርር አድርጎ እርስ በእርስ አጠላለፈና ጨመቃቸው። ሣራ በሀፍረት ተሸማቃ አካባቢውን ቃኘችና "ምን ማድረግህ ነው ዳንኤል?!" አለች ግምባሯን ቅጭም አድርጋ።

ዳንኤል ራሱን ወዝውዞ በረዥሙ ተነፈሰ። "እኔም አልተሳሳትኩም ብዬ አልዋሽም። ገና የተውኔቱ ጽሁፍ እጄ እንደገባ ወኔዬን ተፈታተኑት። አንዱ ተነስቶ 'ቲያትር ማዘጋጀት ሴት እንደማጫወት ቀላል መሰለው እንዴ?' እያለ ሲያቆስለኝ፣ ሌላው ደግሞ 'መጽሀፍ አንብቦ ቆብ የደፋ ሁሉ'ኮ ቲያትር ማዘጋጀት አይችልም' እያለ የቲያትር ጥበባት ጥናቴን ሲያጣጥልብኝ፣ እንቺን አልደብቅሽም ሣራ ፈራሁ... ራሴን ተጠራጠርኩት። ፈርተሽና ተጠራጥረሽ የምትሠሪው የመድረክ ሥራ ደግሞ ፋይዳ የለውም።" ድንገት ጠረጴዛውን በቡጢ ሲለው የተከላከሉት የቢራ ጠርሙሶች እርስ በእርሳቸው ተጋጩ። ሣራ ከፊሎቹን በእጇ በመደገፍ ከመሰበር አዳነቻቸው።

"ጎንትለው ጎንታትለው የማይሆን እልህ ውስጥ አስገቡኝ። ታዋቂዎቹንና ልምድ ያላቸውን አርቲስቶች ሁሉ ትቼ ብዙም ልምድ ያልነበራቸውን አርቲስቶች መልምዬ ሥራ ጀመርኩ። ከረጠበው ወደ ጨቀየው የዘቀጥኩትም ያኔ ነበር። እና... እንደዚያ ሆኖ... ደራሲው እጅ ላይ የተንሳቀለው ተውኔት እኔ እጅ ሲደርስ ታሞ ተዋንያኑ ደግሞ

መድረክ ላይ ገደሉት። ሃ ሃ ሃ ሃ ሃ… የተውኔት ታዳሚውም ኢምንትላጀ ቀበረው … ሃ ሃ ሃ ሃ … ውው!"

ሣራ ብሽቀቷን አፍና ጠረጴዛው ላይ ከተቀመጠው የሲጋራ ፓኮ አንድ ፍሬ አውጥታ ማጨስ ጀመረች። ቢራው ሆዷን ስለነፋት ቅታቀለች። ያልፈጠረባትን ይሉኝታ ለዳንኤል ስትል እስከ መቼ እንደምታስታምም አሰበች። ከተቀመጠችበት ወንበር ሶስት ሜትር በማይበልጥ ርቀት የዳንሱ ዛር ነግሶ፣ ህዝቡ እየተንዘፈዘፈ ሲያጓራ፣ ዓለም ያለፈች ያህል ሽብሩና ትርምሱ የአዳራሹን መሠረት ሲያንቀጠቅጠው እሷ የዳንኤልን ሙሾ ታዳምጣለች።

"እየሽ ሣራ፣ መሣሣትም ትክክል እንደመሥራት ሁሉ በየእለት ህይወታችን ውስጥ ሊፈጠር የሚችል በመሆኑ፣ የቲያትሩ መውደቅ አልነበረም ቅስሜን ሰብሮ መንፈሴን ያሽማቀቀው። ከዚያ በኋላ የሆነው ድርጊት ነው እድሜ ልክ የማይሽር ቁስል… የካንሰር ያህል የከፋ የውስጥ ደዌ ሰንቅሮብኝ ያለፈው። ተረባረቡብኝ እንጂ… እንደ ጎመን ከተፉኝ!"

በርግጥም በቲያትሩ ምክንያት ዳንኤልን ያላወገዘ አልነበረም። ለጥበቡ ተቆርቋሪ የሆኑና በግል የሚጠሉት ሁሉ የሠላ ሂስ አወረዱበት። በግጠሹ ጉባኤ ላይም ዳንኤል የረዥም ጊዜ ዜና ሆነ። የሚያከብሩት ናቁት፣ የሚቀርቡት ሁሉ ሸሹት፣ ዳንኤል መግቢያ ቀዳዳ ጠፋው።

በመጨረሻም ታፌ ኩልኩልት ወደ ቢሯቸው አስጠሩት። በሣራ ጋዴም ምክንያት ሊበቀሉት እንደፈለጉ በመጠርጠሩ ተዘጋጅቶ ነበር ቢሯቸው የገባው።

ታፌ ለአፍታ ቀና ብለው አዩትና ግምባራቸውን እንደቋጠሩ በሚጽፉበት ወረቀት ላይ አቀረቀሩ። ዳንኤል ለረዥም ጊዜ ቆሞ በትዕግስት ጠበቃቸው። ብዙ ዘግይተው እንዲቀመጥ በእጃቸው ምልክት አሳዩትና ተቀመጠ። ከጠረጴዛው መሳቢያ ውስጥ ሁለት ጋዜጦች አውጥተው እየወረወሩለት። "በቀይ ቀለም የተሰመረባቸውን ብቻ አንብባቸው!" አሉት በጥላቻ የጎሪጥ እያስተዋሉት።

ዐይኖቹ በመጀመሪያው ጋዜጣ ርዕስ ላይ አረፉ። "ጥበብ ወይስ ድንቁርና?" ይላል። ዐይኖቹን በቀይ ቀለም የተሰመረባቸው መስመሮች ላይ ቁልቁል ወረወራቸው። "… በህይወቴ ከተሞኘሁባቸው ቀኖች አንዱ ይሄ ነበር። የሰባ ዶሮ ከአምቦት እንቁላሎች ጋር ገዝቼ ማለፊያ እራት ሊያበላኝ የሚያስችል ገንዘብ ከፍዬ ትኬት ከቆረጥኩ በኋላ ወደ



ቲያትር ቤቱ የሄድሁበት እለት። የደራሲውን ድንቁርናና የአዘጋጁን ጅላጅልነት፣ የተዋንያኑን መደዴነት አይቼ ወጣሁ። በተቃጠለው ገንዘቤና ጊዜዬ እንደተቃጠልኩ… ሁለተኛ የትያትር ቤቱን ደጅ ላለመርገጥ ከራሴ ጋር እየተማማልኩ …"

ሁለተኛውን ጋዜጣ በፍጥነት አንስቶ ተመለከተው። "እንደ ግመል ሽንት ወደ ኋላ!" ይላል ርእሱ። በቀይ ቀለም በተሰመረባቸው መስመሮች ላይም "… እድሜ ምክንያት ሆኖ ልመለከተው እድል ባያጋጥመኝም የኢትዮጵያን የሥነ - ተውኔት ዐይን ገልጦ ለተመልካች ቀረበ የተባለው 'ፋቡላ' የተሰኘው ተውኔት በድርሰቱ፣ በዝግጅቱና በአተዋወን ጥበቡ ከዚህኛው የተሻለ እንደሚሆን በደመ ነፍስ እገምታለሁ። እድሜ በቲያትር ጥበባት ቀብ ለሜነው አዘጋጅ እንጂ ዳግመኛ እድሉ ቢሰጠው ከዚህ የከፋ የጥበብ ግም ያሸተናል…" ይላል።

የዳንኤል የጀርባ አጥንት በአፍታ ጎብጦ የማጅራቱ ጅማቶች ተሽማቀቁ። ጋዜጣ የያዘው እጁ ይንቀጠቀጣል፣ ዐይኖቹ ቀይ ቀለም በተሰመረባቸው ፊደላት ላይ እንደተተከሉ ብዥ ብለዋል። ቀሪዎቹን ሀረጎች ሊያነብብትም አልቻሉም።

"በጀ አርቲስት ዳንኤል፣ ቲያትር ቤቱ ለደረሰበት የገንዘብ ኪሳራና እስካሁን ጠብቆት ለኖረ ዝነኛ ስሙ መርከስ ተጠያቂው ማነው ትላለህ?" ሲሉ ጠየቁት። አንገቱን እንዳቀረቀረ ዝም አላቸው።

"መልስልኝ እንጂ! ስለ ሙያው ከኔ ወዲያ ላሳር እያልክ ጥሩምባህን ስትነፋብን የከረምከው አንተ አልነበርክም እንዴ?!" ዳንኤል ቀና ብሎ አያቸውና መልሶ አቀረቀረ።

"ወዳጄ፣ የቲያትር ጥበብ አንተ እንደገመትከው ወይዛዝርትን እንደማሽኮርመም የሚቀል ነገር አይደለም። በሙያው መብሰልን፣ ሌት ተቀን አፈር ግጦ መሥራትን ይጠይቃል…" ዳንኤል ተነስቶ ቆመ። ታፌም ብድግ አሉ። ለአጭር ጊዜ ተፋጠው እንደቆሙ ዳንኤል ክፍሉን ለቆ ሊወጣ መለስ ሲል "ከዚህ በኋላ በዚህ ቲያትር ቤት ውስጥ ለዘበኝነት እንኳን እንደማትፈለግ ታውቃለህ?!" አሉት ጣታቸውን ጀርባው ላይ እንደቀሰሩ።

አንገቱን ቀልበስ አድርጎ ለአፍታ አስተዋላቸው። በድል አድራጊነት ስሜት ፊታቸው ፈክቷል። የተናደዱ ቢመስሉም ውስጣቸው ግን ጮቤ እየረገጠ መሆኑን አላጣውም። እንዳቀረቀረ ቢሮውን ጥሎላቸው ወጣ።

በሳምንቱ፣ በወደቀው ቲያትር ላይ የሚወያይ በርሳቸው የተጠራ የቲያትር ቤቱ የተውኔት ባለሙያዎች ጉባኤ ተካሄደ ። ከሰብሳቢው ጀምሮ አብዛኞቹ የስብሰባው ተሳታፊዎች የሚችሉትን ያህል ዳንኤልን በሂሰና በዘለፋ ቀጠቀጡት። ዳንኤል ለመከላከል አንዳችም ሙከራ አላደረገም። በስብሰባው ማጠቃለያ ላይ ቻርሊ የሰነዘረበት ዘለፋ ግን ከሁሉም የከፋ ነበር። "... የደማንላትን ጥበብ አድምተሃታል። የሞትንላትን ጥበብ ገድለሃታል ... ያስከበርናትን ጥበብ አዋርደሀታል። ስለዚህም ማንኪያና ጭልፋ ሲያሻሽጡ ከርመው ከርታስ የሜኑ ጅምር ምሁራን ከእንግዲህ በመካከላችን ቦታ አይኖራቸውም!" በማለት አቅራራበት። አዳራሹ በሳቅ ተሞላ። ከዚያ ስብሰባ ወዲህም ዳንኤል "ጅምር" የሚል የቅፅል ስም ተሰጥቶት ይኖራል።

በዚህ ጊዜ ሁሉ ያጽናናችው ሣራ ጋዴም ብቻ ነበረች።

"ጅምር አለኝ?!... አንድ ቀን ጭላንቅላቱ ውስጥ የተጠመደውን ፈንጂ ባላፈነዳለት ሰውየው ዳንኤል አይደለሁም!" ጠረጴዛውን በቡጢ እየደበደበ ዛተ። ሁለት የቢራ ጠርሙሶች ወድቀው ተከሰከሱ። ድምጻቸው ግን በሚጮኸው ሙዚቃና በደናሾቹ ዳና እንደተዋጠ ቀረ።

አሁን ሣራ ጋዴም አጠገቡ የለችም። ገና ድሮ ከደናሾቹ ጋር ተቀላቅላለች። ከተቀመጠበት ሲነሳ ብዥ አለበት። እግሮቹም ተሳስረዋል። እየተወላገደና ደናሾቹን እየገፈታተረ ከአዳራሹ ወጥቶ ሄደ። ከጓደኛው የተዋሳትን ፊያት 124 እንደምንም ፈልጎ ካገኛት በኋላም እየተዝለፈለፈ ገብቶ ሞተሯን ቀሰቀሰ። የት እንዳለ፣ ለምን እንደመጣ፣ ከማን ጋር እንደመጣ እንኳን ትዝ አይለውም።

ማለዳ ላይ የቤቱ በር በሃይል ሲደበደብ ሰምቶ እየተነጫነጨ ከእንቅልፉ ነቃ። አልጋው እንደተነጠፈ ነው። የለበሰውን ጃኬትና ሱሪ፣ የተጫማውን ጫማ ሳይቀር ሳያወልቅ እንደተኛ ሲገነዘብ፣ ራሱን እየታዘበና ጭንቅላቱን እያወዛወዘ በቅሬታ ፈገግ አለ። እያዛጋ በሩን ሲከፍት ሣራ ጋዴም እሳት ጎርሳ በሩ ላይ ቆማለች።

ትላንት ማታ የሆነውን ለአፍታ አስታውሶ እንደማፈር አለና ዐይኖቹን ከዐይኗ አሸሻቸው። ገፍተር አድርጋው ወደ ውስጥ አለፈችና መስኮቱን ከፈተችው። የጠዋት ፀሐይ ብርሃን ቤቱን አጥለቀለቀው።

አንድ ክፍል በሆነችው ቤት ውስጥ ዕቃዎቹ ሥርዓት ይዘው ተቀምጠዋል። ሶስት ወንበሮች ያሏት አነስተኛ ጠረጴዛ፣ መለስተኛ



ባለመስተዋት ቁምሳጥንና የመጽሀፍ መደርደሪያው የሚገባቸውን ቦታ እንደያዙ ናቸው።

ሣራ አንዱን ወንበር ስባ ተቀመጠች። ዳንኤል አልጋው ላይ አረፍ አለና አንገቱን አቀርቅሮ ጣቶቹን ያፍተለትል ጀመር። የእሳት ፍላጻ እየወነጨፉ ያሉትን ዐይኖቿን ደፍሮ መመልከት አልቻለም።

"ንቀትህ ወሰኑን አላለፈም?" አለች ከእግር እስከ ራሱ በግልምጫ እየሸነቆጠችው። ዳንኤል አልመለሰላትም። አገጩ ላይ የጎፈረውን ጢም እያፍተለተለ ዝም አለ።

"የጥፍርህን ቆሻሻ ያክል እንኳን እንዳልቆጠርከኝ ተረድቻለሁ" አለች ጥፍሯን ከጥፍሯ ጋር እያጋጨች። ደረቷን እየፈነቀለ፣ ጉሮሮዋን እያነቀና መላ ሰውነቷን እያንዘፈዘፈ የሚታገላትን እልህ እንዳፈነች "በዚያ ውድቅት አምኜህ ወጥቼ አንተም ባለመኪና ሆነክና እኔን ሊፍት ሰጥተህ ቤትህ ገብተህ ተኛህ... ለምን እውነቱን አትነግረኝም? ለምን አልወድሽም አትለኝም?" ስትል በድፍረት ጠየቀችው።

ከተቀመጠበት ተነስቶ የመስኮቱን ደፍ በሁለት ክርኖቹ ተደገፈና ውጭ ውጭውን ያስተውል ጀመር። "እዎን እውነቱን ንገረኝ! እስከ መቼ እሽሩሩ ብየህ እኖራለሁ? ንገረኝ ...አልወድሽም በለኝ!" አለችው ከመቀመጫዋ ተነስታ ከበስተጀርባው እንደቆመች። ዛሬ ቁጥራቸውን ከማታውቃቸው የወንድ ጓደኞቿ ሁሉ የምታዝንለትን ሰው እንደምትለየው እርግጠኛ ነበረች።

ፊቱን አዙሮ ግምባሩን እንደቋጠረ በፀጥታ ተመለከታት። "ለመውደድም ሆነ ለመጥላት የሚያስችል አንዳችም ሰብአዊ ስሜት የሌለኝ ሰው የምመስል የሰው ጥላ ነኝ። በውስጤ ከሚጮኸው የበቀል ጥይታ በቀር ምንም የማይሰማኝ ባዶ ቀፎ ነኝ ...እባክሽ ደግመሽ ውደደኝ፣ ጥላኝ አትበይኝ!" በትክክልም ባዶነቱ፣ ጥላቻውና ግድየለሽነቱ በተሰባበረው ድምጹ ውስጥ በውል ይለያሉ።

ሣራ ለረዥም ጊዜ ስትመለከተው ቆይታ በረዥሙ ተነፈሰች። ቆይታም ፈገግ አለች። "እመሰግንሃለሁ" አለች ዐይኖቿን እያርገበገበች። "'እውነቱን ተናግሮ ከመሸበት ማደር' አይደል የሚሉት አበው? እንግዲያውስ ከመለያየታችን በፊት እኔም አንድ እውነት ልንገርህ። አንተ የባዶነት ቀፎ ብቻ ሣትሆን የጅልነትም፣ የድንቁርናም፣ የፍራቻም ቀፎ ነህ!"

ማምባሩን ከስትሮ፣ ዐይኖቹን ጠበብ አድርጎ በመገረም ተመለከታት። ሣራ ግን ቀጠለች "አንድ ቲያትር ተበላሸና፣ ሰዎች ተናገሩህና ዓለም በጭንቅላቷ ቆመች ህይወት አበቃላት ማለት አይደለም። ልብ ቢኖርህ፣ እውቀትና ችሎታው ካለህ፣ ሌላ ተውኔት አዘጋጅተህ ማንነትህን ባሳየሃቸው፣ በገዛ እንደበታቸው ባቅለልካቸው ነበረ። ግን ወኔ የለህም፤ አልጫ ነህ። በገዛ ጭንቅላትህ በፈጠርከው ሴኦል ውስጥ ተወሽቀህ እራስህን የምታሰቃይ የሰው በግ! የነገሮችን አመጣጥና አካሄድ በየአቅጣጫቸው ማየት የማታውቅ የደንቆሮች ደንቆሮ ነህ! ሁለት ዓመት ሙሉ ያስታመምኩህ፣ እሽሩሩ ብዬ ያንቀላጸስኩህ አንድ ቀን ሰው ትሆናለህ ብዬ ነበር። አንተ ግን የጨነገፍክ ሽል ነህ! የአካል እንጂ የአዕምሮ እድገትህን ያልጨረስክ ሞሮ!"

ከዳንኤል ጋር ባሳለፉቸቸው ዓመታት ውስጥ ያንለት ገና ሣራ ጋዴም እውነተኛዋን ሣራ ሆነች። በድንጋጤ አፉን ከፍቶ ያስተውላታል። ንግግሯ ከርሷ እንደበት የሚፈልቅ አልመሰለውም ነበር። ሳያስበው ከክፍሉ ቱር ብላ ወጣች። ውለው ሳያድሩ እንደሚታረቁ ስለሚያውቅ የመሄዱ ነገር እምብዛም አላስጨነቀውም። ህሊናውን ሸንቁራ የገባችው አንዲት ሃሳብ ግን ከነከነችው፤ "ልብ ካለህ ሌላ ተውኔት አዘጋጅተህ ማንነትህን አታሳያቸውምን?!" የመከነች ተስፋ የተሰኘውን ቲያትር ለማዘጋጀት የምትፈልጉ ተመዝገቡ። የሚለው የታፈ ኩሉኩሉት ማስታወቂያ ትዝ አለው። ለማግሽ ሰዓት ያህል ከቆመበት ሳይንቀሳቀስ በፀጥታ ሲያስብ ቆየና "ጅምር ምሁር" አለና ክትክት ብሎ ሳቀ።

በሁለተኛው ቀን ጠዋት ታፈ ኩልኩሉት ቢሯቸው ድረስ አስጠሩት። እንደገባም ከመቀመጫቸው ተነስተው በፈገግታ ተቀበሉት። ዳንኤል ጥርጣሬው እያየለ ሰላምታ ከሰጣቸው በኋላ ፊት ለፊታቸው ተቀመጠ።

"ዳንኤል፣ ስለ አዲሱ ተውኔት ላነጋግርህ ነው ያስጠራሁህ። ተውኔቱን ለማዘጋጀት መመዝገብህን ስመለከት በጣም ነው የተደሰትኩት። በአለቅነቴ ሣይሆን በአባትነቴ አንድ ነገር ልለምንህ። እባክህ ያለፈውን ሁሉ እንርሳው። ቲያትሩ የወደቀው ባንተ ጥፋት አለመሆኑን የተረዳሁት በጣም በጣም ዘግይቼ ነበር። ያን ጊዜ ስለተናገርኩህ እንዳዘንኩና እንደተፀፀትኩ እኖራለሁ። የማንም መሃይም መጨፈሪያ የሆንከው ግን በገዛ ጥፋትህ ነበር። ብቆጣህም፣ ብሰድብህም ልትጠላኝና ልትርቀኝ ባልተገባም ነበረ። አለቅነቴ ቀርቶ በእድሜ ብዙ ብዙ እበልጥሃለሁ። ይሁን፤ ያለፈውን ሁሉ አሁን እናንሳው። እኔም በጥፋቴ ተፀጽቻለሁና አንተም ይቅርታ አድርግልኝ። አሁን ማሰብ ያለብን ስለ ጥበቡ እድገትና ስለ ቲያትር ቤታችን ዝናና ክብር ብቻ ነው። ይህን ተውኔት አንተ እንድታዘጋጅ



የመረጥኩህ በሁለት ምክንያቶች ነው። አንደኛ አንተን የሚያህል የጥበቡ ሰው በዚህ ቲያትር ቤት ውስጥ ባለመኖሩ በሥራህ የቲያትር ቤቱን ዝና ታድሳለህ፤ ሁለተኛም ጥበቡን አያውቀውም እያሉ ለሚያሙህ ሁሉ አንተነትህን ታሳያቸዋለህ.... ቀዳሚው ግን የቲያትር ቤቱ ስም ነው..." አሉት ከመቀመጫቸው እየተቁነጠነጡ።

ዳንኤል ጆሮዎቹን ማመን አልቻለም። "ኩልኩሉት አንድ የተንኮል ሂሣብ ቀምሯል ማለት ነው" ሲል አሰበ። በነዚያ ደቂቃዎች ግን የታፈን ሃሳብ መርምሮ ሊደርስበት አልቻለም።

"እኛ ስንበሚጨቅ ጥበቡ ረክሶ የቲያትር ቤቱ ስም ጎደፈ። በርግጥ አሁንም ያለፈውን ስህተት መድገም የለብህም። ታዋቂዎቹ አርቲስቶች በዚህ ተውኔት ውስጥ በመሪነት መሳተፍ አለባቸው። መጀመሪያ በዚህ መስማማት አለብን...". አሉት ስሜቱን ለማንበብ እየታገሉ። ዳንኤል ሳያውቀው ራሱን በእሽታ ነቀነቀ። የታፈ ነፍስ ከውስጥ ማጨብጨብ ጀመረች። ባጠመዱለት መረብ ውስጥ እንዲህ በዋዛ ሰተት ብሎ ይገባል ብለው አልገመቱም ነበረ።

ዳንኤል በዚያን ሰዓት ይታየው የነበረው ይህን ተውኔት አዘጋጅቶ የተሰበረ ስሙን ሲያድስ፤ ጠላቶቹን ሲያሳፍር... በድል አድራጊነት ሲፎክርና ማንነቱን ለህዝብ ሲያሳይ፤ በህይወቱ ውስጥ የሚፈጠረው አዲስ ለውጥ ነበር።

የቃለ ተውኔቱን ጥራዝ ተቀብሎ ቢሯቸውን ለቆ ሲወጣም ድንጋጤ፤ ጥርጣሬና ደስታ የተመሰቃቀለበት ስሜት እንዳፈነው ነበር።

## ምዕራፍ አሥራ አንድ

ንጋት ላይ ቻርሊ ማልዶ ነቃና ከአልጋው እየተንጫነጨ ወረደ። የትላንቱ ስካር የዞረ ድምር አልለቀቀውም። ራሱን ይነዝረዋል፤ ዐይኑንም ከብዶታል። ለመንጠራራት ሲሞክር መተጣጠፊያዎቹ ቃ.ቃ . ቃቃቃቃ አሉና በጠዋቱ ዘመሩለት። ከመኝታ ክፍሉ ወጥቶ በሲጋራ ቁራጮች ላይ እየተረማመደ የጓይት ሀውስን በር ከፍቶ ደፉ ላይ ተቀመጠና ሲጋራውን ለኮሰ።

ምርጊታቸው ረግፎ ግድግዳዎቻቸው በካርቶኖችና በላስቲክ ቁርጥራጮች የተለበዱ፣ የቆርቆሮዎቻቸው ምስማሮች ተነቅለው ጣራዎቻቸው ላይ ቋጥኝ የተከመረባቸውና ግራና ቀኝ በተመቱ ካስማዎች ብርታት የቆሙት ደሣሣ ቤቶች የሰይጣን ሰፈር ልዩ ምልክቶች ናቸው።

ቤቶቹ መንደሩን ለሁለት ከፍሎ በሚያልፈው ጥርጊያ መንገድ ትይዩ ግራና ቀኝ ቆመው እንደሚዋደዱ ፍቅረኞች ወገብ ለወገብ ተያይዘው፣ ነፋስ በነፈሰ ቁጥር የሙዚቃ ድግሳቸውን ለነዋሪው ህዝብ ያቀርባሉ።

የማለዳ አዕዋፍ የሰይጣን ሠፈር ነዋሪዎችን ከእንቅልፋቸው ለማንቃትና ንጋትን ለማብሰር አይጨነቁም። የኩራት ይሁን የድካም፣ አለያም የትህትና፣ የሰይጣን ሰፈር አውራ ዶሮዎች ክንፎቻቸውን እያራገቡ በመጮህ መንደረተኛውን ከጠዋት እንቅልፉ አያናጥቡትም። የማለዳ ፀሐይ ራሷ ነች አድሜያቸውን ጨርሰው በተበጣጠሱት የቤቶቻቸው ቆርቆሮዎች ዘልቃ በነፍስ ወከፍ የምሥራች የምትላቸው።

ያኔ በር እንጂ መስኮት የሌሏቸው የመንደሯ ቤቶች መከፈት ይጀምራሉ። ህጻናቱ እርቃናቸውን ከየበሩ ብቅ ብቅ ብለው በየደጆቻቸው ላይ መጸዳዳት ይጀምራሉ። እናቶቻቸውም ጣሳዎቻቸውን አፈር በመሰለ ነጠላቸው ሸፈን አድርገው፣ እያዛጉና እየተንጠራሩ ከልጆቻቸው ፊንጠር ብለው እነርሱኑ ይመስላሉ።

አባወራዎቹ በበኩላቸው የማያቋርጥ ሳላቸውን ከቤት እቤት እየተቀባበሉ ማናፈር ይጀምራሉ። ከጥቂት ቆይታ በኋላም ከየበሩ የከሰል ጭስ ሽቅብ ሲትጎለጎል በየቤቱ የሚወቀጠው የቡና ሙቀጫም ድም! ድም! ድም! ድም! ይላል። የጥርጊያ መንገዱ ቅይጥ እንቅስቃሴም እንዲሁ መዘበራረቅ ይጀምራል።



ሽባው ለማኝ የከባድ መኪና ጎማ ላስቲክ መቀመጫው ላይ ለጥፎ ከሺ ዓይነት እራፊ ጨርቅ የተሰፋ ድሪቶውን እንዳጣፋ፣ ብርኩማውን ተመርኩዞ መሬት ለመሬት/ ይሳባል። ቆም ይልናም በብርኩማው መሬቱን እየደቃ "ዘር አይብቀልብሽ ሰይጣን ሰፈር! ሰው አይውጣብሽ!" ይላታል አድባሯን። ጥቂት ተንፏቆ ደግሞ በብርኩማው ወደ ቤቶቹ እያመላከተ "እንደኔ የማታ እራት ያሳጣችሁ!" እያለ ነዋሪዎቹን ይረግማቸዋል። እንዲያው ትንፋሹን ጨረሰ እንጂ አብዛኞቹ የሰይጣን ሰፈር መንደረተኞች እንኳን የማታ ራት የጠዋት ቁርስም የላቸውም።

ለማኙ እርግማኑን እያወረደ ከዐይን ሲርቅ "የማለዳዋ ንግስት" የተተለተለ ቀሚሷን እንዳጠለቀች፣ በተንጨባረረው ፀጉሯ ላይ የተለከከ ሰንደል እንደሰካች ኮሾ ሲጋራዋን እየማገች ድንጋይ ታቅፋ ብቅ ትላለች። "እኔ አንድ ጣሣ ውሃ አሮብኝ አንቺ አቦል ቡና ታንቃርሪያለሽ። የችጋር ዘር!..." የያዘችውን ድንጋይ በየቤቱ ጣሪያ ላይ ታነኳለች። ድምጿን ሰምተው በየበሩ ብቅ ብቅ ያሉ ህጻናት እየሮጡ እናቶቻቸው ጉያ ሥር ይሸጎጣሉ።

ልጆቹ ሮጠው ሲገቡ ኩስስ ያሉ፣ አጥንታቸው የፈጠጠ የመንደር ውሾች ከየስርቻው እየወጡ ሳል በመሰለ ድምጽ እየጮሁ ይከተሏታል። በእርሷና በጠውላጎቹ ውሾች መሀል ጦርነት ይፋፋማል። ግብግቡ ምንግዜም የሚደመደመው በርሷ አሸናፊነት ነው። ያን የከሳሳ መንጋ በሁለትና በሶስት የድንጋይ እሩምታ እንደጉም ትበትነዋለች። ከዚያ በኋላ ከመሬት ላይ በምታገኘው ድንጋይ፣ የበግ ጭንቅላት፣ የሰርዲን ቆርቆሮ ሁሉ የመንደሩን ቤቶች እያንኳኳች ሰፈሩን ለአፍታ አስጨንቃው ታልፋለች።

በተራቸው ጭቃ ለሳኙ አባ ኮሻና ወንደላጤው እህል አስፈጭ ጋሼ ቦና እንደተማከሩ ሁሉ ከየቤታቸው ይወጡና በመተላለፊያው መንገድ ላይ ሲተያዩ ተፋጠው ይቆማሉ። "ዐይንህን የሎስ ይንጉጠውና ምን ታየኛለህ?" ይላሉ አባ ኮሻ የጭቃ መለሰኛቸውን ጠበቅ አድርገው ይዘው።

ጋሼ ቦና እናቱ ሲሞቱ ሲገዛት ጥቁር የነበረችውንና አሁን ግን የዱቄት ብናኝ ጠጥታ ነጭ የሆነች ባርኔጣውን እያስተካከለ፣ ደም የለበሱ ዐይኖቹን እያጉረጠረጠ "ብትታይ ምን ትሆናለህ?! እንኳን እንዳንተ ያለው ነጉላ ሌላ ሌላውም ይታያል" ይልና መልስ ይሰጣል።

ጠባቸው ሰፈርተኛውን ያታከተ ነው። አፀ ኮሻ አፍ አውጥተው አይናገሩት እንጂ፣ የመንደሩ አስተማማኝ የዜና ምንጭና ፈጣን ቃል አቀባይ የሆኑት እማማ ደብሬ በየቡናው ላይ አዘውትረው እንደሚያወሩት አባ ኮሻ አስፈጭውን ከሸውራራዋ ሚስታቸው ብር አንገቴ ላይ ይዘውታል!

"ቆይ አንተ የወፍጮ ቤት በግ እንዲህ እንዳነጠነጥክ አትኖርም!" ጭቃ ረጋጩ ጥርሳቸውን ያፋጫሉ። አስፈጭውም በበኩሉ ጣቱን እያወዛወዘ መዛት ይጀምራል። "እንደዶሮ አንገትህን ጠምዝዤ ባልነቅልልህ ይሄው ይሄ ብርሃን አይጨልምልኝ!" ይላቸዋል። ሰንት ዓመት ሙሉ።

መንደረኛው ለግልግል ከየደጁ ብቅ ማለቱን ያስተውሉና ሁለቱም ለድብድብ ይጠጋጋሉ። " ነውርም አይደል እንዴ አባ ኮሻ?! ኧረ አንተም ተው ጋሽ ቦና ... ሃይ ... ሃይ ... ሃይ ..." ይባልና ሁለቱ ሲገላገሉ አባ ኮሻ ከገላጋዩ መሃል ሚስታቸውን በዐይናቸው ይፈልጓታል።

ሸውራራዋ ብርአንገቴ በገላገጋዩ ዙሪያ እጆቿን እያርገበገበች ትሽከረከርና "ስለ ሚካኤል ብላችሁ የዛሬን ብቻ ከጉድ አውጡኝ! የዛሬን ብቻ ገላግሉልኝ" እያለች ታሽቃብጣለች። ያን ጊዜ አባ ኮሻ እርሷን ማባረር ይጀምራሉ። ይኼኔ መንደረኛው ጋሽ ቦናን ወደ መንገዱ እየገፋ ገለል ያደርገዋል።

ይህ ትርኢት ሲጠናቀቅ፣ ካሳ ሽፎ የሞተ ውሻ በገመድ እየጎተተ ብቅ ይላል። "ለሰይጣን ሰፈር አድባር የሚቃጠል ጥቁር ውሻ ቀርቧልና ምእመናን ተሰብሰቡ!" በአዋጅ ነጋሪ ድምጽ ይጮሃል። ህፃናት ከያሉበት እየወጡ፣ እጆቻቸውን የኋሊት በማጣመር፣ ፊታቸውን ቅጭም አድርገው ከሚጎተተው ውሻ ኋላ ኋላ በርጋታ ይከተሉታል። የሞተ ውሻ፣ ድመትና ዶሮ ከየወንዙና ከየስርቻው እየሰበሰበ ለሰይጣን ሰፈር አድባር ማቃጠል የካሣ ሽፎ የዘወትር ተግባር ነው።

አወል ሻይ ቤት በራፍ ላይ ሲደርሱ ጉዞው ይገታና "ምእመናኑ" ህፃናት በውሻው ዙሪያ ክብ ሠርተው ይቆማሉ። ከመካከላቸው ጥቂቶቹ የካርቶን ቅዳጆችና የወረቀት ብጥስጣሾች ሰብስበው በውሻው ላይ ይከምሩበታል። ሽፎ በጣሳ የያዘውን ጋዝ አርከፍክፎ ክብሪት ሲጭር እሳቱ ይንቦገቦጋል። ጭሱም እየተጥመለመለ ሽቅብ ይንራል።



ዘወትር እንደሚያደርጉት ሁሉ በእልልታቸው ሰፈሩን ያደበላልቁታል። "ዘመቻ ባና ዴንዳ" /ወደ ዘመቻ እንሂድ/ የተባለውን የወላይታ ህገረሰብ ጨዋታ በጭብጨባ ሲዘምሩ፣ ሽፎ በሚቃጠለው ውሻ ዙሪያ እየተሽከረከረ የህገረሰቡን ጭፈራ ያስነካዋል።

ብዙም ሳይቆይ ግን ፓስቴ ነጋዴው አወል ቁመቱን የሚያክል መቀርቀሪያ ይዞ ይንደረደርባቸዋል። "ምእመናኑ" በያለበት ሲበተኑ፣ ካሳ ሽፎ ሽፈፍ እያለ በመሮጥ የማጅራት ገትርን ጠጅ ቤት አቅጣጫ ይዞ ይበራል።

አወል በፍጥነት ወደ ሻይ ቤቱ ተመልሶ በባልዲ ውሃ በማምጣት የሚቃጠለው "መስዋእት" ላይ ይቸልስበታል። ጭሱ በየአቅጣጫው ይበተንና መንደሩን ያፍነዋል የሰይጣን ሰፈር አድባርም በተቃጠለ ውሻ ጭስ ትታጠናለች።

በዚህ መልኩ ሰይጣን ሰፈር ለብሳው ያደረችውን የጨለማ ድሪቶ ሙሉ ለሙሉ ገፋ ከእንቅልፏ ትነቃለች። ቀኑን ሙሉ አቧራው ላይ አፍንጫውን ቀብሮ የሚያንቀላፋው ጠውላጋ ውሻ በቦታው ይሰየማል። የመንደሩ ሴቶች ባዩት ቁጥር በመቀርቀሪያና በድንጋይ የሚያሳድዱት ጅራተ ቆራጣው ሌባ ድመት እያነከሰ መንገዱን ያቋርጣል። የተሰጣ ልብስ የሚመነትፈው አንካሳ ሽማግሌ እንጥር - እንጥር እያለ ውሻ ገዳይ ጠጅ ቤት ደጃፍ ላይ ይቀመጥና ኮቱን እየቀመለ ፀሐይ ይሞቃል። "ማዘር ኢንዲያ" የሚሏት ሴት ስድስት ልጆቿን እንዳስከተለች ወደ ጉልት ትሮጣለች። ሂትለር "አንተ የአሳማ ልጅ ለቁርስ አንድ ዳቦ አነሰኝ ነው የምትለው?!" እያለ በቡችላይ ይጮሀል።

ቻርሊ ይህን ሁሉ ድራማ በመገረም ሲያስተውል ቆየና "እንደ ቆርቆሮ የሚንኳኳ አሰልቺ የህይወት ኡደት!" ብሎ የያዘውን ሲጋራ በንዴት ወርውሮ አፈር እስኪሆን አሸው።

ሰሞኑን ከእቅዶቹ ዋነኛ የሆነውን የህይወት ተሃድሶ እውን ለማድረግ ሲሯሯጥ ነው የሰነበተው። አብነትን ካገኘ ወዲህ ተስፋ የቆረጠች ነፍሱ ለትንሳኤዋ መዘመር ጀምራለች። ለዓመታት ለሴት ልጅ ፍቅር የተዘጉ የልቡ ደጆች ተከፍተው አብነት ጓዟን ጠቅልላ ሰፍራበታለች። የወጣትነቱ ዓመታትም ይታወሱት ጀምረዋል።

ባለፈው ሳምንት አንድ ከባድ ሸክም ከጫንቃው ላይ በማውረዱም ትንሽ ተንፈስ ብሏል። አርቲስት የመሆን ቅዠት ሌት

ተቀን እያጣነው ነፍሱ የባዘነች ልጁን ሊትል ቻርሊን አይገዙ ገብቶ አንድ ፋብሪካ ውስጥ ሥራ ካገኘለት ሳምንት ሆኗል። ሳሁኑ አንድ ሀሳብ ጥሏል። ቀጥሎ ደግሞ በሀረገወይን ላይ ይዘምታል… ከዚያ በኋይት ሀውስ ላይ። እንዲህ እንዲህ እያለም የአብነትን ከንድ ተመርኩዞ ከወደቃበት ይነሳል።

ዐይኖቹን እያሻሸና እየተንጠራራ ከተቀመጠበት ተነስቶ ወደ ጀማል ሱቅ ሄደ። ብዙ ሳይቆይም ሁለት ዳቦ፣ አንድ ሰርዲንና አንድ ጠርሙስ አምቦ ውሃ ይዞ ተመለሰ። ኋይት ሀውስ በር ላይ ሲደርስ ከውስጥ የሚወጣ ድምጽ ሰማና ቆም ብሎ ጆሮውን ጣል አደረገ። ሊትር ቻርሊ "ኤቭሪባዲ" የተሰኘውን የእንግሊዝኛ ዘፈን እያንጎራጎረ ይደንሳል። ቻርሊ በመገረም ራሱን ነቀነቀና ገርበብ ያለውን በር ገፍቶ ገባ።

"ኬፍ! ዳዲ! ሥራ የሄድክ መስሎኝ፣ አለህ እንዴ?!" አለው ሊትል ዳንሱን አቁሞ።

ተረከዘ ልጥፍ ቆዳ ጫማ፣ ነጭ ባጊ ሱሪ፣ እጅጌ ጉርድ ቀይ ሸሚዝ ለብሷል። በሁለቱም እጆቹ ላይ የተለያዩ አይነት አምባሮችን ደርድሮ ግምባሩን አግድም ከፍሎ የሚሄድ ቀይ ሪቫን አስሯል። የፀሐይ መነጽሩም የሸሚዙን ኪስ አበጥ አድርጎታል። እንደ ቻርሊ ፊቱ በህይወት ድካም አይደብዝዝ እንጂ በመልክ፣ በሰውነት አቋምና ቅርጽ አንዳቸውን ከአንዳቸው መለየት እጅግ አስቸጋሪ ነው። ልጅየው በሀያ አመት እድሜው በምኑም በምኑም መሳ ለመሳ ያባቱ አቻ ሆኗል ።

"ሥነ ሥርዓት ይኑርህ ብዬ ስንት ጊዜ ነገርኩህ አንተ ልጅ! ለአባትህ አክብሮት አሳይ አላልኩም?!" ቻርሊ በንቀት ገላመጠው።

"ይቅርታ አባዬ፣ እንደምን አደርክ?" ሊትል ቻርሊ ዐይኖቹን ከዳቦውና ከሰርዲኑ ላይ ሳይነቀል እጆቹን እያፍተለተለ ይቅርታ የሚጠይቅ መሰለ።

"ለመሆኑ የት አድረህ ነው ፊትህ እንዲህ ዱቄት የነፋበት ወንፊት የመሰለው?" ሲል ጠየቀው ቻርሊ ግምባሩን እንደቋጠረ።

"እኔን ነው?" ሊትል ግራ የተጋባ መሰለ።

"እስኪ ዙሪያህን ተመልከት፤ በዚህ ቤት ከኔና ካንተ በቀር ሌላ ሰው አለ?"

ሊትል ዙሪያውን ቃኘና "የለም" አለ።

"ታዲያስ?!"



"አለና!"

"ዩ ሺት! በማን ነው የምታሾፈው?!" ቻርሊ የያዘውን ዳቦና ሰርዲን መሬት ወርውሮ ወደ ሊትል ተወረወረ። የሸሚዙን ኮሌታዎች ጨምድዶ ይዞ በቡጢ ሊያደባየው ሲንጠራራ ሊትል በሚቁለጨለጩ ዐይኖቹ እያባበለው መንተባተቡን ቀጠለ "ኖኖኖ! ዳዲ፣… ምን መሥራትህ ነው?! ከፈለክ እውነቱን እነግርሃለሁ…"

ቻርሊ ልጁ ገጽ ላይ የሚታየውን የጭንቀት፣ የፍርሃትና የብልጠት ስሜት ሲመለከት ንዴቱ በአፍታ በርዶ ሳቅ ይተናነቀው ጀመር። የጨመደደውን ሸሚዝ ለቆ እጁን በእጁ እየጠራረገ "ሸምቃቃ!" አለው።

ሊትል በረዥሙ ተነፈሰና ሸሚዙን አስተካከለ። ዐይኖቹ ግን መሬት ከወደቀው ሰርዲንና ዳቦ ላይ አልተነቀሉም። "ልክ አይደለህም ዳዲ፣ ለምን በሥነ - ሥርዓት የት አደርክ ብለህ አትጠይቀኝም፤ እነግርሃለሁ። የት አደርክ ብሎ ለመጠየቅ ሁለተኛ ቡጢ መሰንዘር የሚያስፈልግህ አይመስለኝም"

"እሺ የት አደርክ?" ቻርሊ ከልቡ ባልመነጨ ቁጣ ጮኸበት።

"ጥሩ፤ እንደዚህ ሥርዓት ያለው አባት ሆነህ ስትጠይቀኝ ሥርዓት ያለው ልጅ ሆኜ እመልስልሃለሁ። ትላንትና ኦቨር ናይት ፓርቲ ነበረብኝ!" አለና ትክሻውን ሰበቀ።

ቻርሊ ትኩር ብሎ ሲመለከተው ቆየና ተስፋ ቆርጦ ራሱን ነቀነቀ። በርጋታ እየተራመደም የሰርዲኑን ቆርቆሮ፣ ዳቦዎቹንና የአምቦ ውሃውን ጠርሙስ ከወደቀበት ሰብስቦ ከምጣድ በተሠራው ጠረጴዛው ላይ አስቀመጠ። ሊትል ቻርሊ ከጀርባው ያነበንባል።

"… ዳዲ አንተ ዳንስ አትወድም እንጂ ስንትና ስንት የዳንስ አይነት አሳይህ ነበር። የድሮ የናንተ ጊዜ ዳንሶች ዛሬ አንዳቸውም የሉም። ትዊስት፣ ማሪንጌቻቻ፣ ካሊፕሶ… ጂኒ ቁልቋል፤ ዛሬ ስማቸው እንኳን ተረስቷል። 'ዳንስ የሰውነት ነጻ እንቅስቃሴ ነው' የሚለው የነጮቹ አባባል እውነት ሆኖ ተገኝቷል። ዛሬ እንደድሮው ለእግር አረጋገጥህ፣ ለእጅ አሰነዛዘር ፎርም መጨነቅ አያስፈልግም። ብትፈልግ እንደ ዶሮ መንደፋደፍ፣ ስትፈልግ እንደ እሞራ መወናጨፍ ትችላለህ። ዳዲ ሙት ዛሬ እንደፈለግህ ለመደነስ ሙሉ ነጻነት አለህ!" አለው ረጋ ብሎ እየደነሰ።

"አንተ ልጅ ጤነኛ ነህ?! ደግሞ ማነው ፀጉርህን እንዲህ አድርጎ የገጣጠበህ?" ቻርሊ የምር መብሸቅ ጀመረ።

ሊትል ፀጉሩን በጁ እየነካካ እስተካከለና "ጓደኞቼ ናቸው ፣ ጆንትራ የተሰኘው ቄንጠኛው የዘመኑ ዘመነኛ ቁርጥ ይሄ ነው። አያምርም?!"አለና እንደ ተዋጊ በሬ ጭንቅላቱን ወድሮ አባቱ ወደቆመበት ተንደረደረ። ቻርሊ ሰውነቱን ወደ ኋላ ሸሸት አድርጎ የልጁን ራስ ገፋ አደረገው። ለምን ሥራ እንዳልሄደ ሊጠይቀው አፉን ሲከፍት ሊትል መለስ ብሎ የሰርዲኑን ቆርቆሮ አነሳና ቀደደው። ዳቦውንም ቆራርሶ የአሣውን ሥጋና ዘይት እየጧጠጠ መብላት ጀመረ። "እንዴት ርቦኝ ነበር መሰለህ ዳዲ?! ለሆዳም ልጅ ሰርዲን ያዝለታል አሉ" አለ የዳቦውን ሩብ ያህል እንደጎረሰ።

ቻርሊ እሮጌው ሶፋ ላይ ኩርምት ብሎ ተቀመጠና ልጁን በርህራሄና በፍቅር ዐይን ይመለከተው ጀመረ። ሁል ጊዜም ራብኝ ሲለው ሆዱ በርህራሄ ይዘላል።

"ዳሩ ምን ያደርጋል ዳዲ?! የፀጉር አቆራረጥ ቄንጥ ብቻውን ምን ይፈይዳል? ከጫማዬ ጋር አብሮ አይሄድም። ጉራማይሌ ነው። ይልቅ የረሳሁትን አስታወስከኝ ... በቀደም እንደምንም ተቸግረህ ጫማ ግዛልኝ ብየህ ነበር፤ ተሳካልህ?! ከቻልክ እስኒከር ጫማ ብዬህ ነበር። ሞላልህና ገዛህልኝ?!"

ቻርሊ እንዳልሰማ ፊቱን ወደ በሩ መልሶ በፀጥታ ተቀመጠ። ጨለማውን ቤት ከፍቶ ከመግባት ቀጥሎ የኋይት ሃውሰን ደጅ መርገጥ የሚያስጠላው አንዱ የልጁ የገንዘብ ጥያቄ ጭቅጭቅ ነው። የአምቦ ውሃውን ኮርኪ በጥርሱ ከፈተና ሩብ ያህል ከጠጣለት በኋላ ከጠረጴዛው ላይ አስቀምጦ ጥያቄውን በዝምታ አለፈው።

"ምነው! አርቲስት አይደለህም እንዴ ዳዲ?!"

ቻርሊ ዐይኑን ከልጁ ዐይኖች እንዳሸሸ በፀጥታ ተቀመጠ። ሊትል ግን አልለቀቀውም።

"ንገረኝ እንጂ ዳዲ፣ ለልጅህ ጫማ መግዛት ታንሳለህ?" በትዝብት ቁልቁል ተመለከተው።

ቻርሊ ተጨነቀ። ያለውዴታው የአምቦ ውሃውን ጠርሙስ አንስቶ ተጎጨና በረዥሙ ተነፈሰ። "ለመሆኑ አርቲስት ገንዘብ ያትማል ያለህ ማነው?"



"ታዲያ አባቶነትህ ምኑ ላይ ነው? ሱሪም፣ ጫማም እንደሚያስፈልገኝ ታውቃለህ፤ በቅድሚያ ግን የጫማው ነገር ነው በርኒንግ ኢሹ የሆነብኝ"

"እኮ ለዳንስ እንዲያመችህ?!" ቻርሊ የብሽቀት ሳቅ ሳቀ።

"ኖ! ለእርሱ ብቻ አይደለም ዳዲ። አየህ የዘመኑ ሰው ዐይን የተለከፈው በሰው ጫማ ነው። ሱሪህ ከመቀመጫህ ባዶ ቢሆን፣ ኮትህ ከትከሻህ ቢነትብ የዘመኑ ሰው ኬረዳሽ ነው። ብቻ በዐይኑ ጦር ጫማ ጫማህን እየወጋ ጥፍርህን ሲነቅል ይውላል። ይገርምሃል እኮ ዳዲ፣ በኛ ቋንቋ ችስቶሶማይሲስ የምንለው የድህነት በሽታ ከሽሚዝ ኮሌታና ከጫማ ሶል እንደሚጀምር ማን እንዳስጠናቸው አላውቅም።

"ስንትና ስንት ዘመን የተለየኸውን ጓደኛህን አግኝተህ እቅፍ አድርገህ ስትስመው፣ በማጅራትህ ተንጠራርቶ የጫማህን ሞዴል ያነባል። ከመንገድ ላይ ያገኘሃትን ኮረዳ እንዲያው ልብህ ከጅኋት ጠቀስ ያደረካት እንደሁ፣ ብርጭቆ ዐይኗ ተወርውሮ ጫማህ ላይ ይከሰከሳል።

"ጅሎች! 'ሰው ማንን ይመስላል ቢሉ ጫማውን' ይሉልሃላ። እኔ ግን ብልጥ ነኝ ዳዲ፤ የሰውን ልጅ ማንነት የምለየው ገና በዐይኑ ውሃው ነው። ቀጣፊውን ከሀቀኛው፣ ችስታውን ከቱጃሩ፣ ምሁሩን ከመሀይሙ፣ አራዳውን ከነሁላላው... በዐይኑ ውሃ እየዋኘሁ፣ ዝርዝር ታሪኩን እንደ ፊደል ነው የምቆጥረው"

ሊትል ሰርዲኗን አጋምሿታል። ቻርሊ ፍዝዝ ብሎ እያየው "ሰው ሳይሆን፣ ጉድ እኮ ነው የወለድኩት" እያለ ይገረማል።

"ታውቃለህ ዳዲ?! ጓደኞቼ ሁሉ ባለ እስኒከር ጫማ ናቸው። ማ.ማ.ማ.ማ! እንዴት ይደንሱበታል መሰለህ?! ይሄ የኔ ቆዳ ጫማ ብቻ ነው ባልተፈለገበት ቦታ እየገባ፣ ያልተፈለገ ድምጽ እየሰጠ የሙዚቃውን ስልት የሚያፋልሰው። ታዲያ ደናሹ ሁሉ፣ ወንዱ ትላለህ ሴቱ፤ ዳንሱን አቁሞ ይገላምጠኛል። ደግሞ ሁልጊዜም ይጠይቁኛል። ለምን አርቲስቱ አባትህ እስኒከር ጫማ አይገዛልህም? ይሉኛል። ታዲያ አንድ ቀን እንኳን አንተን አስጠጥቼህ አላውቅም። ልክ ነኝ አይደል ዳዲ?! የኛ ድህነት እዚሁ እኛኑ እንደካንሰር ውስጥ ውስጣችንን እየበላ ይፍጀን እንጂ ገበናችን አደባባይ ወጥቶ ለምን ፀሐይ ይሞቀዋል?! ታዲያ ምን እንደምላቸው ታውቃለህ?" ሁለተኛውን ዳቦ ቆርሶ ቆርቆሮውን መጧጠጥ ያዘ።

"የራስህ ጉዳይ!" አለው ቻርሊ ከውስጥ መንደድ እየጀመረ።

"ምን እንደምላቸው ታውቃለህ?! አንተው ራስህ እንደ ውዳሴ ማርያም ያስጠናኸኝን መልሼ እደግምላቸዋለሁ። ያስታጠቅከኝን የነገር ጥይት አርከፈክፍባቸዋለሁ። ለምን ከልብሳችን፣ ከጫማችንና ከሆዳችን ባሻገር አርቀን አናስተውልም?! እላቸዋለሁ። እስከ መቼ ነው እንደ አሳማ ለሆዳችን ስንፍገመገም ነፍሳችንን የእውነት፣ የፍቅር፣ የጥበብ፣ የብርሃን ጠኔ የሚገድላት ?!እላቸዋለሁ። ለምን ዘላቂ የህይወት ግብ አይኖረንም?! እላቸዋለሁ። ይሄ ምክንያቱ ሲሰለቻቸው ደግሞ፤ እኔ ጋዴም ነኝ! እላቸዋለሁ" ድንገት ምግቡን ማላመጥ አቆመና ፍቅፍቅ ብሎ መሳቅ ጀመረ። ቻርሊ አፉን ከፍቶ ያስተውለዋል።

"አሁንማ እውነትም ጋዴም ነው ብለው ጭቅጭቃቸውን ትተውኛል። የኔ ዐይኖች ግን ለአፍታ እንኳን በምኞትና በጉጉት ከአስኪከር ጫማዎቻቸው ላይ አይነቀሉም" እንደገና ሆዱን ይዞ ፍቅፍቅ ብሎ መሳቅ ጀመረ። "ታዲያ አሁን አንተ አስኪከሩን ብትገዛልኝ የቃሌ እዳ አይከብደኝም ነበረ። እንደካራቲስት ተገለባብጬ የከረመ አቋሜን ባንድ ጀንበር እቀይራለሁ። ጋዴምነት ኋላቀርነት፣ ጅሊነት ዘመናዊ አስተሳሰብ ነው እላቸዋለሁ። ልክ አይደለሁም ዳዲ?"

ቻርሊ የልጁን አነጋገር ሲመለከት ባዶ አንጀቱ ሲላወስ "እህል" እያለ ሲጮህ ተሰማው። የልጁ ንግግር ስላንገሸገሸው ቤቱን ጥለህ ሽሽ፣ ብረር ብረር አለው። ግን ምን መድረሻ አለው? ከሥራ የቀረው አዕምሮውን ትንሽ ለማሳረፍ ፈልጎ ቢሆንም ከመስሪያ ቤቱ የሸሸው ጭቅጭቅና ነገር ዱካውን እያነፈነፈ እቤቱ ገብቶ ይዞታል። ብስጭት ብሎ "ለመሆኑ ለምንድነው ዛሬ ከሥራ የቀረኸው?" ሲል ጮኸበት።

ሊትል ግራ እንደተጋባ ሁሉ በመገረም አባቱን ሲመለከተው ቆየና ፈገግ አለ። "እስካሁን አልሰማህም ማለት ነው?"

"ምኑን" የቻርሊ ዐይኖች ፈጠጡ።
"ሥራውን እኮ ሁለት ቀን ብቻ ሠርቼ ተውኩት!"

ቻርሊ አናቱን በዱላ የተመታ ያህል ሽምቅቅ አለና እጆቹን አጣምሮ ልጁን በትዝብት ዐይን ይመለከተው ጀመር። ኀባሁት ያለው ሲናድ፣ ሻረ ያለው ቁስል ሲያመረቅዝ፣ ልጁን ሥራ ለማስያዝ ያደረገው ውጣ ውረድ ሁሉ ሲታሰበው ግደለው! ግደለው! የሚል ሀሳብ ከውስጥ ይቀሰቅሰው ጀመረ። ከተቀመጠበት ግን አልተንቀሳቀሰም ። በድን ሆኗል።



'ሊትል ቻርሊ የአባቱን ሁኔታ ሊመለከት እንደመደንገጥ አለ። "ከመቆጣትህ በፊት ለምን ሥራውን ተውከው ብለህ አትጠይቀኝም?" ሊትል ባዶዋን የሰርዲን ቆርቆሮ እጥፍጥፍ አድርጎ እንደ ኳስ በእግሩ ለጋና በተከፈተው በር ወደ ውጭ አሻገራት። ቻርሊ ቆርቆሮዋን በዐይኑ ሲከተላት ቆይቶ መሬት ስታርፍ ምራቁን ደጋግሞ ዋጠ። ሊትልም የአምቦ ውሃውን ጠርሙስ አንስቶ ከጨለጠው በኋላ ሆዱን እያሻሸ ደጋግሞ አገሳ።

"እኔ እኮ ሥራ አገኘሁልህ ስትለኝ ዳዲ፣ በፋብሪካ ውስጥ ለሚቋቋሙ የኪነት ቡድኖች ላብ አደሮቹን በዳንስ ወይም በቲያትር እንዳሰለጥን የምቀጠር ነበር የመሰለኝ።" ዘይት የነካውን እጁን ፀጉሩ ላይ እየጠረገ ገለጻውን ቀጠለ።

"ምን አይነት ሥራ እንደሰጡኝ ባለማወቅህ ብታዝንብኝ አልደነቅም። ሥራው ምን መሰለህ? ግምብ ግምብ የሚያካክል የታሸገ እቃ ከመጋዘን እያወጡ በካሚዮን ላይ መጫን ነው!" እንደገና ፍቅፍቅ ብሎ መሳቅ ጀመረ።

"የመጀመሪያው ቀን አንተ እንዳትጨቀጭቀኝ ብዬ አጋስስ ይመስል ስሸከምዋልኩ። በዚሁ ሳቢያ ወገቤን አመመኝና ጓደኞቼ ሌሊቱን ሙሉ ወገቤን በቅባት ሲያሹኝ አደሩ። ስሸከም ነው እንዲህ የሆንኩት ግን አላልኳቸውም። ዳንስ ስደንስ ተቀጭሁ አልኩና በድንቅ ፈጠራ እንደ ሬሳ ገነዙኝ።" እንደገና ሳቁን ቀጠለ።

ቻርሊ ደንዝዟል። ዐይኖቹ ፈዘው፣ አፉ ተከፍቶ የልጁን ዲስኩር በፀጥታ ይጠጣል።

"በማግስቱ ሄድኩ፤ እዚያው ቦታ ተሸከም ብለው መደቡኝ። ትንሽ ስሠራ ሰውነቴ ሁሉ በላብ ታጠበ፤ መተጣጠፊያዎቼ ዛሉ፤ ትንፋሼ እንኳን ቃተተ። ሀላፊው ዘንድ ስንደረደር ሄድኩና 'ለምን በሰው ነፍስ ትጫወታላችሁ?!' ብዬ አፈጠጥኩበት። 'እንዴት?!' አለኝ መነጽሩን አውልቆ። ዛሬ ዓለም በስልጣኔ ተራቆ የትና የት በደረሰበት ሰዓት እናንተ የሰውን ልጅ ሰብአዊ ክብር አዋርዳችሁ ከእህያ አመሳስላችሁ ጭነት ስትጭኑን፣ ትንሽ ህሊናችሁን አይቀፋችሁም?!" አልኩት። 'እንዴ፤ ለምን በፎርክሊፍት፣ በሙቪንግ ቤልት ወይንም በክሬን አትጠቀሙም?!' አልኩት። በአጀንዳው ላይ የሆነ ነገር ጻፈና 'ስለ ጥቆማህ እናመሰግናለን። ይሄንኑ ለበላይ አካል ሪፖርት እናደርጋለን' ብሎ ተሳለቀብኝ። 'ከሪፖርትህ ጋር ጀሃነብ ግባ!' አልኩት። በቃ ከዚያ ወደቤት መጣሁ። ሲፈልግ አጋሰስ ፈልጎ ይጫን።

ስዚያውም እኮ ለዚያች የሃምሣ ብር ደመወዙ ነው ሃ ቻ ሃ ሃ… ሃሃሃቻ… እኔ ከጓደኞቼ ጋር አንድ ሰዓት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ እመድ የማደርጋት ወረቀት እኮ ናት። ፍረደኝ እስኪ ዳዲ፤ ለሃምሣ ብር ብለህ ሠላሣ ቀን ላብህን አፍስ ትለኛለህ?" እጆቹን የኋሊት አጣምሮ እንደ አቤት ባይ ከወገቡ ጎንበስ አለ።

ቻርሊ ቆሽቱ ከውስጥ ሲነፍር፤ ደሙ ሲንተከተክ ይታወቀዋል። "አንተ ጥጃ! አንተ ከማን በልጠህ ነው?! በዚያ ፋብሪካ ውስጥ ሲሸከሙ ያየሃቸው ሰዎችኮ የሃገሪቱ የእንጀራ ልጆች አይደሉም። ኑሮን ለማሸነፍ፤ በሁለት እግራቸው ለመቆም ነው ላባቸውን ሲያንጠፈጥፉ የሚውሉት…" ድምጹ እየተቆራረጠ የጀመረውን መጨረስ አልቻለም።

ሊትል ቻርሊ በግድየለሽነት ትከሻውን ሰበቅና ፈገግ አለ። "ኧረ እነሱስ የሚገርሙ ፍጥረቶች ናቸው። ያን የሚያክል ከብደት ተሸክመው እንደ ነፋስ ሲበሩ ጭብጥ ገለባ የተጫነባቸው አይመስሉም። ላባቸው እንደ ውሃ ሲንጠፈጠፍ ደከመን ብለው አያርፉም። ይግረምህና በህብረት ሆነው ይዘፍናሉ። አጀብ የሰው ልጅ ብርታት! ደምና ሥጋ የለበሱ ብረቶች አይደሉም እንዴ?! ታዲያ እኔ እነሱን ልሆን አልችልም" አለና ታጣፊው አልጋ ላይ ቁጭ አለ። ቻርሊ ቃል አልተነፈሰም። እንኳን ዛሬ በሃያ አመት እድሜው ገና ልጅ ሆኖ እንኳን ተናግሮ አያሳምነውም፤ ተቆጥቶ አይመልሰውም።

ሊትል አሁንም መሳቅ ጀመረ። "እኔማ ሥራቸውና ሁኔታቸውን ስመለከት፤ ዳንስና ቲያትር ላስተምራቸው ባለመሄዴ ፈጣሪዬን አመሰገንኩ። መቶ አመት ባስተምራቸው እንኳን እንደማይገባቸው እርግጠኛ ነኝ። ኤልቪስ ፕሪስሊን አያውቁ። ቦብ ማርሌይን አያውቁ፤ ጂሚ ሄንድሪክስን አያውቁ… ገና እኮ የተነከሩ ጥሬ ገብሶች ናቸው። የሚያውቁት አንድ ጩኸት ነው። አንድ! ሁለት! ፎርሣ፤ አንድ! ሁለት! ፎርሣ!… በቃ ይሄው ነው። ፎርሣ ብቻ… ፍርሣ! ፎርሣ! ፎርሣ! ፎርሣ!!! ሁለት ቀን ሙሉ ጆሮዬን ቢያደነቁሩት በጥጥ ጠቀጠኩት። የሚያውቁት አንድ ዘፈን ነው 'ጎበዜ ና ጎበዜ፤ በአብዮት ጊዜ የለም ትካዜ!' ይሉልሃል። እኔማ ነገርኳቸው። 'እንደ ኑሯችሁ ቢሆን መተከዝ ብቻ ሳይሆን ስቅስቅ ብላችሁ ማልቀስ አለባችሁ!' አልኳቸው። ጭራሽ እንደ ጅል ቆጥረው አይስቁብኝም መሰለህ?! የህይወት ጉስቁልናቸውና የነፍሳቸው ስቃይ እንዳይሰማቸው ሃሽሽ ያስጨሷቸው ነው የመሰለኝ።" ሊትል እንዴ መተርተር ከጀመረ በቀላሉ አይቆምም። "ይግረምህና ቲያትር ማለት ምን ማለት እንደሆነ እንኳን አይውቁም። ሼክስፒርን እንዳቸው እንኳን አያውቁትም። እኔ



ስለ ሼክስፒር ታላቅነት ሳወራላቸው አንዱ ምን አለኝ መሰለህ 'ይሄ ሼክስፒር የምትለው የኛው አገር ታቦት ነው?' ብሎ በሳቅ ሆዴን ሲያስጨርሰኝ፤ አንዱ ደግሞ ተነስቶ ጓደኛውን ሲያርመው 'ሽክር ደግሞ ይጥፋህ እንዴ፤ የግብጾች ንጉስ እኮ ነው' አለልሃ። ኧረ የሚገርሙ ፍጥረቶች ናቸው። እኔ እኮ 'ላብ አደሩ ያቸንፋል፤ ጂኒ ቁልጳል' ስትለኝ በጉልቤነታቸው ነበር የመሰለኝ። አንድ ከስማና ካቦ ሲያንቀጠቅጣቸው ባየሁ ልኝ። 'ላብ አደሩ የአብዮቱ ግንባር ቀደም መሪ ነው' ሲባል ዓለምን በጣታቸው ጫፍ ላይ አቁመው የሚያሽከረክሯት ነበር የመሰለኝ። ዳንስ እንኳን የማይችሉ ምስኪኖች ናቸው። ባለቻቸው ትንሽ የእረፍት ጊዜ ደግሞ ቆሎቸውን እየቃሙ ምን እንደሚያወሩ ታውቃለህ?! አፍንጫቸው ሥር የተከመረው የካርቶን ቁልል ሳያስጨንቃቸው፤ ደግሞ ነገ ስንት ካሚዮን ካርቶን ወደ መጋዘን እንደሚያስገቡ ይተሳሰቡልሃላ። በመራራ ህይወት የሚያፌዙ፤ ጎስቋሎች። 'ፎርሣ! ፎርሣ! ፎርሣ! ጎበዜ ና ጎበዜ፤ በአብዮት ጊዜ የለም ትካዜ…' ሥራ ሳይሆን ሲኦል የገባሁ ነበር የመሰለኝ። ጭራሽ እነሱን መሆን አልችልም። የኔ ወገብ ዳንስ እንጂ ጭነት አይችልም። ለተዋናይነት እንጂ ለሸክም አልተፈጠርኩም"

ቻርሊ ድንገት ፍንጥር ብሎ የልጁን የሸሚዝ ኮሌታ ጨመደደና ከተቀመጠበት አልጋ ላይ አነሳው። ሊትል ለመከላከል እንዳችም ንቅናቄ አላደረገም። የግምባሩ ስሮች ተገታትረው፤ ዐይኖቹ ፈጠው የአባቱን ደም የለበሱ ዐይኖች በፍራቻ ያስተውል ጀመር።

አባትየው መናገር የፈለገውን ለማውጣት አቅም አልነበረውም። ከቁጥጥሩ ውጭ የሆነ ሀይል ልሳኑን አፍኖ ይዞታል። ያለውን ሃይል ሁሉ አጠራቅሞ በመገፍተር ከግድግዳ ጋር አጋጭቶ ከታጣፊው አልጋ ላይ ዘረረው።

ሊትል ከወደቀበት ሳይነሳ አባቱን በትዝብት ሽቅብ እያስተዋለ አልጋው ላይ እንደተዘረረ ቀረ።

ቻርሊ በንዴት የጦፈ አካሉ በረድ ሲልለት ክፍሉ ውስጥ እየተንጎራደደ ዘለፋውን አወረደበት። "ቅዠታም! እስከመቼ ነው የእውነታውን ዓለም እየፈራህ ህልምህን የምትኖረው?! የያዝከውን፤ የጨበጥከውን ለቀህ ልትደርስበት የማትችለውን ልትደርስበትም ብትችል አሳርከን የሚያስንጥህን ቅዠት የምትቃዠው?! 'ወገቤ ጭነት አይችልም' ይለኛል - ጭባ! ፈሪ ነህ። ፈሪ ሰው ደግሞ የህልሙ እንጂ የራሱ ገዥ አይደለም። የህይወትን ውጣ ውረድ ለመታገል፤ በጥረትህ ሰው ለመሆን ወኔ የለህም። ወኔህን በየአጥሩ ጥግ ሸንተኸዋል።

ሀሞትህን አስታውከኸዋል። "አሁን አንተም ቆሜያለሁ ብለህ ታምናለህ?!" አለው ድምጹ እየተንቀጠቀጠ።

ሊትል ከተዘረረበት ተነስቶ ሸሚዙን ካስተካከለ በኋላ የሱሪውን አቧራ አራገፈ። "ይሄው ቆሜያለሁ። ማንም ሰው እንደሚቆመው በሁለት እግሬ ቆሜያለሁ" አለ ተስፋ በቆረጠና በሰለቸ ስሜት።

"ለኔስ ሁለት ሞት ሞተህ፣ ወድቀህና በስብሰህ ነው የምትታየኝ። ሰው ራሱን መሆን አቅቶት ሌላውን መምሰል ሲከጅል፣ በፕሮቶኮሉ፣ በዲስኩሩ የሌላውን ፈሊጥ ሲገለብጥ... በሌላው ቄንጥ ሲዘንጥ፤ የሚሰጥር ሞቱን እርሱው በርሱው ውስጥ ይሞታል። እንደ እንቁላል ከውስጥ በስብሶ የገዛ በድኑን ከርፋት እዚያው ውስጥ ውስጡን ያሸታል። እና ቆሜያለሁ ብለህ አትበለኝ..." አለው። ቻርሊ በሚንቀጠቀጥ ድምጽ።

ሊትልም ግምባሩ ላይ ያሰረውን ሪቫን እያስተካከለ "በኔ ላይ ብቻ አትፍረድ ዳዲ። ውድቀት የሁላችንም እጣ ነው ። በኔ ላይ ያንጣጠርከውን መስተዋት ወደ ራስህ ብታዞረው ብዙ ብዙ ጉድ ያሳይሃል። ብቻ አንተስ ምን ታደርግ?! ዘንግተኸው እንደሆን እንጂ ገና በልጅነቴ 'በሰው ላይ ያያትን ጉድፍ ለመንቀስ የሚንጠራራ ሰው እድፋም ፊቱን ቢመለከተው ኖሮ ራሱን ይዞ በጮኸ ነበር' ትለኝ ነበረ። አንተም የኔ ጉድለትና ድክመት እንጂ የራስህ አይታይህም። ቢታይህም እንኳን ታዛቢና ተቆጭ ስለሌለህ ግድ የለህም.." አለና እጆቹን ሱሪው ኪሶች ውስጥ ከቶ በቁንጠኛ አረማመድ እየተቆናጠረ ጓይት ሀውስን ለቆ ወጣ።

ቻርሊ በሩ ላይ ቆሞ ልጁን ከአይኑ እስኪሰወር ድረስ በመገረም ሲመለከተው ቆየ። አዎን፣ ከቻርሊ ይልቅ ሊትል የሰውን ጉድፍ የመንቀስ፣ በሌላው ላይ የሚያየውን ጉድለት የማውጣት ጥሩ አይን አለው። "ጉድ! የሰው ጉድ!" ቻርሊ እየተገረመና እየተራገመ ተከትሎት ወጣ።

በማግስቱ ጠዋት ገና የቲያትር ቤቱን ቅጥር ግቢ እንደረገጠ፣ አንድ ዐይናው ተላላኪ እየሮጠ መጥቶ "ጋሽ ቻርሊ፣ ትላንት ቀኑን ሙሉ ፈልጌ አጣሁህ እኮ" አለው።

"ምነው በደህና?" አለ ቻርሊ ግምባሩን ቅጭም አድርጎ።

"ታፈ ይፈልጉሃል፤ በእግር በፈረስ.... ትላንት ያልደረስኩበት..." ቻርሊ ጥሎት ሄደ። ተላላኪው ግን እግር እግሩን



እየተከተለ "ጋሽ ቻርሊ፣ አደራ እንዳታስወቅሰኝ" እያለ ይወተውተው ገባ"

"ስውዬ፣ በጠዋት አትልከፈኝ" አለው ቻርሊ ተቆጥቶ።

"ምን ቸገረኝ! እኔ እንደሁ ውርድ ከራሴ ብያለሁ" ተላላኪውም በተራው ተቆጥቶ ሄደ።

ቻርሊ ህንጻው ላይ ወዳለው ሻይ ቤት ወጥቶ ቡና ካዘዘ በኋላ መስኮት አጠገብ ተቀምጦ አስፋልቱ ላይ የሚተላለፈውን መንገደኛ ያስተውል ጀመር። ህሊናው ግን ተላላኪውን በማመናጨቁ እየወቀሰው ነው።

ቡናውን ጠጥቶና ሲጋራውን አጭሶ ወደ ታፈ ቢሮ ሲያመራ ዳንኤል ጅምርንና ሣራ ጋዱምን እጅ ለእጅ ተያይዘው ወደ ሻይ ቤቱ ሲያመሩ ደረጃው ላይ አገኛቸው።

ሰላምታ ሊሰጡት በፈገግታ ሲቀርቡት ግን ግምባሩን እንደቋጠረ የእንገት ሰላምታ ሰጥቷቸው አለፈ። ብዙ ጊዜ የውስጥ ስሜቱን መደበቅ አይሆንለትም። ጥላቻውን በተቋጠረ ግምባሩ እንጂ በሞቀ ፈገግታ ሸፍኖ ሌላውን ማቄል አይችልም።

ታፈ ቢሮ ሲገባ ያጋጠመው ደግሞ ከወትሮው ለየት ያለ ሁኔታ ነው። ቻርሊ ገና በሩን ከፍቶ ሲገባ ከመቀመጫቸው ተነስተው በፈገግታ ተቀበሉት። የተቋጠረ ግምባሩ ሳይፈታ ሰላምታ ሰጣቸውና እየተጠራጠረ ወንበር ስቦ ተቀመጠ።

ታፈም ተንጠራርተው ግድግዳው ላይ ያለውን መጥሪያ በመጫን ተላላኪውን እየጠሩ "ታዲያ ምን ትወስዳለህ ቻርሊ፤ ቡና ወይስ ሻይ ልዘዝ?" ሲሉ ጠየቁት።

"የለም አሁን ጠጣሁ" አለ ቻርሊ ግራ እንደተጋባ።

"ተው! ተው! ያለቃ ግብዣ እምቢ አይባልም" ታፈ አግደረደሩት።

"የለም፣ አሁን ከበብ ነበርኩ" ሲል ተከላከለ ቻርሊ ። በሃሳቡ ግን "ይህ የሰው ከንቱ ዛሬ ደግሞ ምን የተንኮል ቁማር ሊጫወት አስቦ ይሆን?" እያለ ያሰላስላል።

ተላላኪው በሩን ከፍቶ ብቅ እንዳለ፣ ታፈ በስህተት መሆኑን ገልጸው አሰናበቱና "ታዲያስ ቻርሊ? ህይወት እንዴት ነች?" አሉ መላጣቸውን እያሻሹ።

"እንደ ክረምቱ ቆፈናም ናት" መለሰ ቻርሊ።

ታፈ ከምክም ብሰው ሲስቁ ቆዩና "አይ ቻርሊ! ህይወትንክ ቆፈናምም ማራኪም የሚያደርጋት ባለቤቱ ነው። ህይወትን ግምባርህን ጨፍግገህ ከተቀበልካት እርሷም ትፀየፍሃለች። ብድር በምድር ነዋ ነገሩ! ስቀህ ከተቀበልካት ደግሞ ታሞቅሃለች። ምነው ቢሉ ወርቅ ላበደረ ወርቅ ነዋ!" አሉት እየሳቁ። ቻርሊ አልመለሰላቸውም።

"አርቲስት በተፈጥሮው ተጫዋችና ደስተኛ ነው። አንተ ግን መቼ ይሆን ይህ የተቋጠረ ግምባርህ የሚፈታው?" የውሸት ሣቃቸው ክፍሉን ሞላው።

"አንድ ቀን!"

የቻርሊ መልስ እየገረማቸው ከኪሳቸው የሲጋራ ፓኮ አውጥተው ጋበዙት። አንድ ፍሬ አውጥቶ በታፈ ኩልኩልት ክብሪት ለኮሰ። ታፈም በፀጥታ ማጨስ ጀመሩ።

"ስማ ቻርሊ፣ ዛሬ እንኳን ያስጠራሁህ ለብርቱ ጉዳይ ነው። እንደምታውቀው የዚህ የተከበረ ቲያትር ቤት ስም ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጎደፈ፣ አድናቂዎቼንም እያጣ ነው። ከሁሉም በላይ ደግሞ ስንቱን ያየንባት ጥበብ እየተልከሰከሰች በማንም ምሁር ነን ባይ ጭንጋፍ ስትረገጥ ማየቴ እጅግ አሳስቦኛል። እናም በኔ ግምት ጥበቧን እንወዳታለን፤ ለጥበቧ ክብር እንቆማለን የምንል ሰዎች ተባብረን እጅና ጓንት በመሆን ከወደቀችበት ልናነሳት መሰለፍ የሚኖርብን ዛሬ ነው።"

ቻርሊ የሚሰማው ሁሉ ከታፈ ኩልኩልት አንደበት የሚመነጭ መሆኑን ተጠራጠረ። በያንዳንዱ አረፍተ ነገር መጨረሻ ላይ "ከመቼ ወዲህ?!" የሚል ጥያቄ በልቡ እያነሳም ነበር የሚያዳምጣቸው።

"ወደ ዋናው ጉዳይ ለመግባት፤ ሰሞኑን ማስታወቂያ ተመልክተህ እንደሆን 'የመከነች ተስፋ' የሚል አዲስ ተውኔት ለቲያትር ቤታችን ተልኳል። እና ይህን ተውኔት እንዲያዘጋጅ ያ ዳንኤል የሚሉት የምሁር ጀምር ተመድቧል። እኔ እንኳን እናንተ በሙያው የበሰላችሁትና ልምድ ያላችሁ ቲያትሩን ለማዘጋጀት ትመዘገባላችሁ ብዬ ነበር። የተመኘሁት ግን አልሆነም። ይሁን። እሱን እንተወውና ይህ ተውኔት መነሻው ወይ መውደቂያው እንደሆን አስጠንቅቄዋለሁ። እንደማይሳካለት ግን እርግጠኛ ነኝ።

"አንተንም በመሪ ተዋናይነት እንዲያጫውትህ ነግሬዋለሁ። ይህን ያደረኩት ለሙያው ባለኝ ፍቅርና ከማንም በላይ በችሎታህ ስለምተማመንብህ ነው። እየህ 'በደንባራ በቅሎ ቃጭል ተጨምሮ' እንደሚባለው በርሱ ድንቁርና ላይ ምሁር እያለ የሚጀነናቸው



አውሮች ይጨመሩበትና ሥራውን ሁሉ የጨረባ ተዝካር እንዳያስመስሉት ሰግቻለሁ። እንደገናም ደግሞ አልተማራችሁም፤ ጥበቡን አታውቁትም እያሉ የሚዘባበቱባችሁን ጀምር ምሁራን ሁሉ፣ በዚህ ተውኔት ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ትቀጧቸዋላችሁ። እናንተ እውነተኞቹ የጥበብ ልጆች፣ እነርሱ አስመሳዮች፤ እናንተ ብልሆች፣ እነርሱ ጅላጅሎች መሆናቸውን ታስመሰክሩበታላችሁ"

ቻርሊ በታፈ ኩልኩልት መላጣ ውስጥ የተጠነሰሰው መርዝ ምን እንደሆን ሊረዳ አልቻለም። በሚጠላው ሰው የመድረክ መሪነት በሚዘጋጅ ቲያትር ውስጥ ለመካፈል ደግሞ አንዳችም ስሜት አልነበረውም።

"ጥያቄውን ባልቀበልስ?" ሲል ግምባሩን እንደቋጠረ ጠየቀ።

ታፈ በቅሬታ ሲመለከቱት ቆዩና "የቲያትር ቤቱ ተቀጣሪ ሠራተኛ መሆንህንማ አትርሳ! እንጀራህ እኮ ነው" አሉት።

"በአዘጋጁ በኩል ይሄ ትእዛዝ ሊደርሰኝ ሲገባ እዚህ ቢሮ ድረስ በግል የተጠራሁበት ምክንያትስ ምንድነው?"

ታፈ እንደመደናገጥ አሉና "የአሁኑ ግንኙነታችንማ በኔና ባንተ መካከል የሚቀር ነው። እየህ ቻርሊ፣ ይሄ ጋግርት ጠባይህ እኮ ነው ከሰው በታች አድርጎ ያስቀረህ። ለምን እሺ ባይ አትሆንም? ከስንቱ ታግለህ የምትዘልቅ ይመስልሃል?!"

ታፈ ኩልኩልት ምንም ነገር ሊያደርጉለት እንዳላሰቡ ቻርሊ ያውቃል።

ስለዚህም ከመቀመጫው ተነሳና "እንጀራዬ በመሆኑ ትእዛዙን ተቀብያለሁ" ብሎ ክፍሉን ለቆ ወጣ።

ታፈ "ተንከከሰውና ተቦጫጭቀው ደክመው የተኙትን አንበሶች ከተኙበት በማንቃት ለመጨረሻው ፍልሚያ ወደ ሰገነቱ መንዳት!" የሚለው የጥበበኛው አመራራቸው አንድ መርህ፣ በቻርሊ የተነሣ አይሳካልኝ ይሆን የሚል ስጋት በአዕምሯቸው በመጫሩ በጥልቅት ስለጉዳዩ ማሰብ ጀመሩ።

## ምዕራፍ አሥራ ሁለት

መላው ዓለም ያደመባት እስኪመስላት ድረስ ግራ ተጋብታ ሰነበተች - አብነት መንገሻ። ዓለሙ ሁሉ ስለገባችው ቃል ኪዳን የሚፈታተናት እየመሰላት ተሸማቃለች። የልቧን ፍቅር ሊያይላት፣ የነፍሷን ጩኸት ሊያደምጥላት የቻለ ባለመኖሩ እርቃኗን አደባባይ የቆመች እስኪመስላት በሀፍረት ተኮራምታለች።

"ጠበቃውን የሚያክል ሰው ይቺ ምድር አላበቀለችም ... ልጄ አባክሽ ፍሬሽን እይቹ ልሙት" ነግቶ ሲመሽ፣ ደግሞ መሽቶ ሲነጋ የእናቷ ውትወታ ይሄው ነበር። አብነት ጆሮዎቿን ድፍን አድርጋ በመያዝ ከእናቷ ትሸሻለች።

"እስከመቼ መግባባት እንደማንችል አላውቅም። ከጠበቃው ጋር በሆንሽ ቁጥር መድረክ ላይ እንዳለሽ ተዋናይ ራስሽን ቁጠሪ ብዬ ስንት ጊዜ ልንገርሽ?! ደርሶ ግስላ መሆን... ግምባር መቋጠርን ምን አመጣው?"

"አልሆንልሽ ብሎኝ ነው አባየ..."

"የድርጅቱን ህልውና አደጋ ላይ እንደምትጥይው አታውቂም?!"

"ጭራሽ ተዋናይ መሆን አልቻልኩም'ኮ አባዬ"

"ቻርሊ ከሚባለው ቲያትረኛ ጋር ምን እንዳገናኘሽስ ልታስረጂኝ ትችያለሽ?"

"ምንም..."

"እንዴት ምንም?! ያለ ምክንያት ነው በየአደባባዩ አብረሽው ስትንከረፈፊ የምትውይው?"

አብነት መልስ አልሰጠችም።

"ለመሆኑ የሁለት ልጆች አባት መሆኑንና መንግስት በፀረ - ህዝብነት እንደሚከታተለውስ ታውቂ ኖሯል?!"

"ማን ነገረህ?!"

"አይመለከትሽም፤ ጥያቄዬን ብቻ መልሽ!"

"ኧረ ቻርሊ ፀረ- ህዝብ አይደለም"

"ምን አልሽ?"

"ምንም"

"ሁለተኛ ከርሱ ሰውዬ ጋር ታየሽ የሚሉ ነገር ብሰማ ውርድ ከራሴ። 'የአህያ ሥጋ አልጋ ሲሉት አመድ' አሉ። የድርጅቱ ብቸኛ ተስፋ አንቺ መሆንሽን ዘነጋሽው?!"



አብነት ትጨነቃለች።

ሰዓሊው ዘንድ ብቻዋን ስትሄድ ደግሞ "ያ ደደብ ጓደኛሽ ደህና ነው?" ይላታል የጎደን እየተመለከታት።

አብነት በሀፍረት ተሸማቅቃ ዝም ትላለች።

ብቸኝነቱ ቢጫጫናት ሣራ ጋዴምን ደቅርታ ልትጠይቅ ወሰነች። "ሃሎ፤ ሣራ?!"

"አዎን፣ ማን ልበል?"

"ሣራ፤ እባክሽ ሁሉን ረስተሽው እንደ ቀድሟችን እንሁን"

"ማን ልበል?"

"አንቺ ግን እንዴት ጨካኝ ነሽ ሣራ..."

"ይሄን ስልክ ልዘጋው ነው። ማንሽ?"

"አብነት ነኝ ሣ..." ስልኩ ጆሮዋ ላይ ተዘጋ። "ዓለም ሁሉ አንቅሮ ተፍቶኛል ማለት ነው?" አለች አብነት ለራሷ።

በዚህ ላይ ደግሞ እሁድ በመጣ ቁጥር "አክስፎርድ ዩኒቨርስቲ ሳለሁ...." የማያባራው የጠበቃው ንዝንዝ አለ።

ቻርሊ ግን ይህንን ሁሉ አያውቅም። የሚያውቀው አንድ ነገር ከርሷ ጋር ሲሆን ደስተኛነት የሚሰማው መሆኑን ነው። ቀኑን ሙሉ ተቋጥሮ የዋለው ግምባሩ አብነትን ሲያይ ይፈታል። ቀኑን ሙሉ ተዘግቶ የሚውል ልሳኑ አብነትን ሲያገኝ ይፍታታል።

ይሄ ደግሞ አብነትን ቀን ተሌት ያስጨንቃታል። "እስከ መቃብር ካንተው ጋር ነኝ" ብላ ቃል ኪዳን በገባችለት ሰው ጀርባ የምታሳግጥ ስለሚመስላት ነፍሷ ትሸበራለች። ስለዚህም ብዙ አውጥታ ካወረደች በኋላ ሁሉንም ነገር ዘርዝራ ልትነግረው ወሰነች።

ቻርሊ ቀናተኛና በርሷ በመጣ ነገር ሙት መሆኑን ታውቃለች። ሰሞኑን ያደረገውን ስታስታውስ ደግሞ ይደንቃታል።

ፒያሣ መሃል በሚያዘወትሩት ቡና ቤት ተቀምጠው ቡና እየጠጡ ያወጋሉ። አብነት ከሰዓሊው ጋር ያሳለፈቻቸውን ዓመታት ትዝታዎች እያጫወተችው ነበር። እነርሱ ከተቀመጡበት ትይዩ ደግሞ አንድ ሰው ፊቱ የተቀመጠውን ሙሉ ሻይ እያማሰለ አብነትን ለረዥም ጊዜ አፍጥጦ ያያታል። ቻርሊም በበኩሉ በሰውየው አስተያየት ተገርሞ አፍጥጦ ያስተውለዋል። ሰውየው ፈፅሞ አያየውም። የአብነት ሀሳብ ሙሉ በሙሉ ሰዓሊው ላይ ነበር።

ቻርሊ ማፍጠጡ ቢሰለቸው ዐይኑን ሰብሮ የአብነትን ጨዋታ ያዳምጥ ገባ። ብዙ ቆይቶ ቀና ሲል ግን የሰውየው ዐይን አብነት ላይ መሆኑን አየ። ጥንቀት ተሰማው። እየቆየ ሲሄድ ግን ንዴትና እልህ ይተናነቀው ጀመር።

"ያን ሰውዬ ታውቂዋለሽ?" ሲል በአገጩ እያመለከተ ጠየቃት።

አብነት መለስ ብላ ሰውየውን አየችው። የበረደውን ሻይ እያማሰለ አፍጥጦ ያያታል። "አላውቀውም... ምነው?" አለችው ግራ ተጋብታ።

ከተቀመጠበት ቱር ብሎ ሄደና ሰውየው አጠገብ ቆሞ ቁልቁል አፈጠጠበት። "ምነው ወንድም?"

ሰውየው ከእንቅልፉ እንደነቃ ሁሉ ጥንቅላቱን ደጋግሞ ወዘወዘና "ምነው?" አለ ቻርሊን በገረሜታ ሽቅብ እያስተዋለው።

"ለምን ታያታለህ?"

"ማንን?" የሰውየው ድፍርስ ዐይኖች ተበለጠጡ።

"በማን ላይ ነው የምታፈጠው?!" ቻርሊ አፈጠጠበት። ቤቱ ውስጥ የነበሩ ተስተናጋጆች ሁሉ በድንጋጤና በመገረም ያዩት ጀመር።

ሰውየው አብነት ወደነበረችበት አቅጣጫ ገልመጥ ብሎ ከተመለከተ በኋላ በገጹ ላይ ይነበብ የነበረው መገረምና ድንጋጤ ወደ ፈገግታ ተለወጠ። "ወላ'ኒ ለእዚም... ያንተን ቆንጆ አላየሁብህም። በጥልቅ ሃሳብ ውስጥ ተውጬ ነበር" አለ እየሳቀ። ቤቱ በሳቅ ታመሰ።

ቻርሊ በሠራው ስህተት ተደናግጦ ምን ማለት እንደሚገባው ተጨንቆ ከቆየ በኋላ "ለሁለተኛው ሰው እንደዚህ አይታይም!" አለውና ወደ ነበረበት ተመለሰ።

ሰውየው ሲስቅ ቆይቶ "አንተም መታረም አለብህ እኮ ወንድሜ፣ ይችን የመሰለች ሸጋ ይዘህ ስትዞር እንደኔው ከሌሎች ጋር እንዳትጣላ ምናለ 'ማየት ከልክል ነው!' የሚል መፈክር ብትለጥፍባት?!" አለና ሳቁን ቀጠለ። በቤቱ ውስጥ የነበሩ ሁሉ ከግራ በላይ ሳቁ።

ቻርሊ አልመለሰለትም። ሂሣቡን ከፍሎ በፍጥነት ወጡ። በዝግታ እየተራመዱ ታክሲ ወደሚይዙበት አቅጣጫ ሲያመሩ አብነት



የሚታገለትን ሣቅ እያፈነች ጠየቀችው። "ቻርሊ፣ ግን ምን መሥራትህ ነው?"

"ምን ሠራሁ?!"

"ሰውየውን እንዴት እንዴት ነው ያደረከው?"

"ታዲያ ሰው በሰው ላይ እንደዚያ ዐይኑን ያፈጣል?"

"ቀንተህ ነው፣ አይደል?!"

ቆም ብሎ ሲመለከታት ቆየና "እውነቱን ማወቅ ከፈለግሽ፣ አዎን!" አላት።

"አታምነኝም ማለት ነው?!"

"አለማመንንና መቅናትን ምን አገናኛቸው?"

"ሰዎች የሚቀኑት የሚወዷቸውን ስለሚጠራጠሩ አይደለም?!"

"አትሳሳች። የሌላውን ባላውቅም እኔ የምቀናው ስለማላምንሽ አይደለም። ለኔ ፍቅር ማለት ስስት እንደሆነ ደጋግሜ ነግሬሻለሁ። እስስትልሻለሁ አብዬ! እኔ እንኳን በሙሉ ዐይኔ ላይሽ አልደፍርም። እንጃ! ለአንዲት ሰከንድም ቢሆን የሌላው ሰው ቀልብ ሲያርፍብሽ፣ ለአንድም ቀን ቢሆን በሌላው ሰው ልብ ውስጥ ማደርሽን ሳስብ ነፍሴ እሪ ብላ ትጮሃለች። ከፉ ጠባይ! አይጣል አመል! የፈለግሽውን በይው። ላንቺ አይታወቅሽም እንጂ ህይወቴን ለውጠሽዋል። ከውስጤ ተንጠፍጥፎ ያለቀ የመሰለኝ ተስፋ ሲያንሰራራ ይታወቀኛል። ሬት ሬት ትለኝ የነበረች ህይወት ትጣፍጠኝ ጀምራለች። ጨለማ ትመስለኝ የነበረች ዓለም ብርሃን ስትፈነጥቅ ትታየኛለች። የመኖሬ ምክንያት ሆንሻል አቢ። ለጨለማው ህይወቴ ብርሃንን የሰጠሽኝ አለኝታዬ አንድ ቀን ከዐይኔ ብትሰወሪ፣ ህይወቴ ምን ሊመስል እንደሚችል ይታሰበኝና አንቺን ያየሁባትን ቀን እረግማለሁ። አንድ እውነት እነግርሻለሁ። በኔ ህይወት ውስጥ አብነት መንገሻ ማለት የህልውና ጥያቄ ነች። የመኖር ወይ ያለመኖር ፈተና!"

"ቻርሊ!"

"ይህ የነፍሴ እውነት ነው አቢ"

"እወድሃለሁ"

*** *** ***

ፍቅረኞቹ አዘውትረው ሰዓሊውን ይጎበኙታል። በእረፍት ሰዓቱ ሁሉ "የደም ጎርፍ" የተሰኘውን አብስትራክት ስእል ይሠራል። ከቻርሊ ጋር በተገናኙ ቁጥር የሚያነሱትን አታካሮ ስለለመደችው ውዝግባቸው ወደ ጸብ ያመራል የሚለው ስጋቷ ተወግዶላት እንዲያውም ደስተኝነት ይሰማታል - አብነት።

በሳሎኑ ውስጥ ሰዓሊው ሲጃራውን እንደነከሰ ይንጎራደዳል። ቻርሊ ከሶፋው ላይ ተቀምጦ መጽሄት ያገላብጣል። አብነት ሻይ የጠጡባቸውን ስኒዎች እያነሳሳች ሰረቅ እያረገች ቻርሊን ትመለከተዋለች። ዛሬ ገጹ ሁሉ ፈክቶአል። ስለዚህም በህይወቷ ውስጥ የደረሰውን ምስቅልቅል ለማስረዳት ከዚህ የተሻለ ቀን እንደሌላት ገመተች። ያለችበትን ሁኔታ ሲረዳ ሊፈጠርበት የሚችለው ሀዘን እየታሰባት ግን ልቧ እንደተጨነቀ ነበር።

ብርጭቆዎቹን አጣጥባ ከቦታቸው በማስቀመጥ ወደ ሳሎኑ ስትመለስ አርቲስቶቹ እሳትና ጭድ ሆነው አገኘቻቸው።

"... 'የደም ጎርፍ' አልከው በዚህ ስእል ላይ የምታጠፋው ጊዜ ግን የባከነ ጊዜ ነው የሚመስለኝ" አለ ቻርሊ ያገላብጠው የነበረውን መጽሔት ጠረጴዛው ላይ ወርውሮ ።

"እንዴት?!" ሰዓሊው በመገረም ተመለከተው።

"የህዝቦችን ተስፋ የሚያጨልም በመሆኑ"

"ያለሁብትን ዘመን እውነታ ነው የሠራሁት። የጽጌረዳ አበባ የምታሸት ቆንጆ ሴት መሳል ነበረብኝ?!"

"እንደዚያ ማለቴ ሳይሆን፣ አሁን ከምታየው ጨለማ ጀርባ ሊመጣ የሚችለውን ብሩህ ቀን ሊያሳይ የሚችል..."

ሰዓሊው የያዘውን ሲጋራ ጥሎ ትቢያ እስኪሆን አሽቶና "የዚህን ትርምስ ውጤት ልንገርህ?! በህዝብ ልጆች ደም በታጠበ ዙፋን ላይ የፋሽዝም መደላደል ነው። በድርጅትና በትጥቅ የማይመራ የህዝቦች አመጽ ትርፉ አንገትን ለገዥዎች ካራ አመቻችቶ መስጠት ብቻ ነው። ያኔ ማለቂያ የሌለው የደም ጎርፍ ይንገዋገዋል" አለው ጣቱን ወደ ቻርሊ እንደቀሰረ።

"ገዥዎች በዲሞክራሲያዊ መብቶች ላይ በሜኑት የአፈር ክምር ሳቢያ ህዝቦች ሊነቁ፣ ሊደራጁና ሊታጠቁ አለመታደላቸው እውነት ነው። ይሁን እንጂ እጅና እግሮቻቸውን አጣጥፈው አደራጅ ከሰማይ እንዲወርድላቸው፣ ገዥዎቻቸውን የሚፋለሙበት ትጥቅ እንዲዘንብላቸው አያልሙም። እየታገሉ ይደራጃሉ፣ እየተደራጁ ይታጠቃሉ" አለው ቻርሊ በርግጠኝነት።

ሰዓሊው ፍቅፍቅ ብሎ እየሳቀ፣ "አሁን በምትለኝ መንገድ፣ ያለውን የሃይል ሚዛን ሳትተውለው ምን እንደሚታየኝ ታውቃለህ?! ባንድ ማእዘን ትልቅ ዝሆን በሌላው ማእዘን ደግሞ ትንሽ ትንኝ" አለና ሳቁን ቀጠለ።



ቻርሊ ብሽቀቱ እያስታወቀበት "ይሆን ያህል የህዝብን ሃይል ትንቃለህ ማለት ነው?!" ሲል ጮሆ ጠየቀው።

የሰዓሊው መልስ ደግሞ ይበልጥ የሚያሳብደው ነበር። "ህዝብ የራሱ ሃይል የለውም! የህዝብ ሃይል፤ የህዝብን እውነት ይዘናል ብለው ማደንዘዣ በከተቡት መሪዎቹ መዳፍ ውስጥ ነው። ይህ በመዳፋቸው ያመቁት ሃይል ደግሞ ገዥዎች የራሳቸውን ዓላማና ጥቅም ለማስፈጸም በህዝቡ ላይ መልሰው በመጫን የሚያንበረክኩበት ሃይል ነው። በመዳፋቸው በገባው የህዝብ ሃይል መልሰው ህዝቡን ይገዙበታል። 'እሾህን በእሾህ' እንዲሉ የህዝብ ተቃውሞ ልሣን በህዝብ መዳፍ ይታፈናል። የህዝብ አዕምሮ የገዥዎቹ አዕምሮ ነው። መሪዎቹን ተከትሎ ለልማት ወይ ለጥፋት ይሰለፋል... ለሰላም ወይ ለጦርነት ይታጠቃል። 'ለምን?!' ብሎ አይጠይቅም፤ ግራ ቀኝ አይቶ ለድርጊቶቹ ምክንያቶች አይፈልግም። እንዲህ አይነት የራሱ አዕምሮ ያለው ከሽዎች ውስጥ አንድ ቢገኝ እምቢ ባይ ሆኖ ተወልዷልና በህዝብ ሰይፍ ይሰየፋል! መሪዎቹን ተከትየ ሲአል አልወርድም ያለ በህዝብ ክንድ ይወገራል! እና አትድከም ወዳጄ፤ የህዝብ ሃይል... ጂኒ ቁልቋል የምትለው ሁሉ ፌዝ ነው" አለው።

ሰዓሊው ከሚናገራቸው ቃላት ጋር የሚያወናጭፋቸውን እጆቹንና የሰውነት እንቅስቃሴውን አብነት ስትመለከት፣ በመድረክ ሂደት ላይ ያለ ተውኔት የምትከታተል እስኪመስላት ድረስ ያለችበትን ዘንግታለች። ቻርሊ አልመለሰለትም። በጁ የያዘውን መጽሔት እያገላበጠ ቀልቡን ሁሉ ጆሮው ላይ ሰብስቦ ያዳምጠዋል።

ሳይታሰብ "የህዝብ አዕምሮ የገዥዎች አዕምሮ ነው አልከኝ?!" ብሎ ቻርሊ የብሽቀት ሳቁን ለቀቀው። "የኛ ማኪያቬሊ! ከሰማየ ሰማያት ምጡቅ አዕምሮ ያላቸው ልዩ ገዢዎች ወርደው ለህዝቡ አዕምሮ ይሁኑለት ካልከማ በፈላጭ ቆራጮች የምታመልክ እንጂ በዴሞክራሲ የምታምን ስላልሆንክ ፋሺዝምን መከኑን ባልተገባህም ነበር። በዚህ አባባልህ'ኮ ሂትለር የህዝብ አዕምሮ ነው! ስለዚህም ህዝቡ እንደከበት ተነጂ ነው።"

"ወዳጄ፣ ሀቁ ግን ይሄ አይደለም። ህዝቡን በሃይል አንበርክከውና አሸማቀው ገዢዎች ለተወሰነ ጊዜ ብቻ ህዝቡን በመከፋፈል ሊገዙት ይችሉ ይሆናል። ህዝቡ ግን ብዙም ሳይቆይ ከደነዘዘበት ይነቃል። ዋ! ያን ቀን ገዢዎችን ምን ይውጣቸው ይሆን?!

ያኔ የህዝቡ የበላይነት ይሠፍናል፤ ዴሞክራሲም ይንሠራፋል። ለእኔ ህዝብ ማለትም የተገፋውና ብዙሀኑ የጭቁን መደብ ነው…

"አንተ ግን ወዳጄ ግራ የምታጋባ ፍጡር ነህ። ከገዥዎችና ከጨቋኞች እንደ አንዱ እንዳልቆጥርህ አኗኗርህና ለነርሱ ያለህ ጥላቻ ያሳስተኛል… የህዝቦች ወገን ነህ እንዳልል በህዝብ ላይ ያለህ ንቀት ያስበረግገኛል። ለምን ተስፉ እንደቆረጥክ፤ ለምን ራስህን ከዓለም እንዳገለልክ አይገባኝም። በውነት ስላንተ ምን እንደምል አላውቅም" አለ ራሱን በሀዘኔታ እየነቀነቀ።

"በዚህ እንኳን ልትጨነቅ አይገባም። የኔ ህይወት ምንም ሚስጥር የለውም። እኔ ከዚህ እናንተ ከምትኖሩበት ትልቅ ጨለማ ውስጥ የራሴን ውጋጋኗ የሚያጥበረብር ትንሽ ዓለም ፈጥሬ የምኖር የእኔነቴ ጥላ ነኝ። ይች ትንሽ ዓለም የምልህ ሥነ ጥበብ ናት። ታብራለች፤ ብርሃኗ ግን ከትልቁ ዓለም ጨለማ ጋር ሲነጻጸር የትንታግ ያህል ኢምንት ነው። እና ሁልጊዜም እጨነቃለሁ… ግዙፉ ጨለማ ትንሿን ብርሃን እንዳይውጣት እፈራለሁ። አትገረም፤ ከዓለም የምሸሸው በጨለማው ዓለም ውስጥ ስባዝን የትንሿ ዓለሜ አቅጣጫ እንዳይጠፉኝና ለዘለዓለሙ በጨለማው ተውጬ እንዳልቀር ስለምሰጋ ነው። ስለኔ ይሄ በቂ አይሆንም ትላለህ?!" አለው እየሳቀ። እብነት ሰዓሊው ስለራሱ ሲናገር የሰማችው በዚያን እለት ብቻ ነበር። እነኚህ ሁለት ሰዎች አንድ ቀን እንኳን በሃሳብ ሊግባቡ ባለመቻላቸውም ከመጣረም በቀር አንዱን ደግፉ ሌላውን ተቃውማ ሃሳብ ሰጥታ አታውቅም። ፍቅረኞቹ በመጨረሻ ሰዓሊውን ተሰናብተው ወጡ።

ከበቅሎ ቤት ወደ ጎተራ በሚወስደው የአስፋልት መንገድ ጠርዝ ላይ እጁን በእጁ ውስጥ አቆላልፉ ብዙ ከተጓዙ በኋላ "ቻርሊ ዛሬ ደስተኛ ትመስላለህ" አለችው።

"እንዴት?" አላት በገጹ ላይ የሚታየው ፈገግታ እየደመቀ።

"እንጃ … ዛሬ ልዩ ሰው ሆነህብኛል፤ ፊትህ የሚረጨው ፀዳል ራሱ የጨረቃን ያክል ነው" አለችው እየሳቀች።

"ለኔም ይታወቀኛል። እንዲህ ሲሆን ግን እፈራለሁ። በመከራና በታላቅ ፈተና ዋዜማ አንዳንድ ጊዜ የሰው ልጆች ደስታ ወሰን የለውም ይባላል። ብዙውን ጊዜ ቅጥ የሌለውንና ምንነቱ ያልታወቀን ደስታ ተከትሎ የሚመጣው ሃዘን ጥልቅ ነው" አላት በቁም ነገር።

እብነት ደነገጠች። ልቧ በፍጥነት ይመታ ጀመር። ልታረዳው የተዘጋጀችው መርዶ ዐይኖቹ የሚረጩትን ብርሃን አውድሞ፣



ገጽታውን ያፈካውን ፀዳል አክስሞ ሊያሸማቅቀው እንደሚችል ስታስብ ሆዷ በርህራሄ ዘለለ። አማራጭ ግን አልነበራትም።

"ስማ ቻርሊ …" ብላ በመጀመር የህይወቷን ምስቅልቅልና ፍቅራቸው ያለበትን አደገኛ ሁኔታ በዝርዝር ገለጸችለት።

እያንዳንዱን አረፍተ ነገር በጨረሰች ቁጥር ዐይኖቹ በድንጋጤ ይፈጡ፤ ከንፈሮቹ ይንቀጠቀጡና እግሮቹ እስኪዝሉ ድረስ ጉልበቶቹ ይብረከረኩ ነበር። ሆኖም ንግግሯን እስክትጨርስ ቃል አልተነፈሰም። ቀና ብላ ስታየው አፉን እንደከፈተ ቀርቷል። ክንዱን ይዛ እየነቀነቀች "ቻርሊ!" አለችው። የሚሰማት ግን አይመስልም።

ቆይቶ ድንጋይ መስሎ ከቆመበት የያዘችውን ክንድ መንጭቆ እየተወላገደ በፍጥነት በመራመድ ጥሏት ሄደ። "ቻርሊ! ቻርሊ፣ ምን መሥራትህ ነው?!" እያለች ልትከተለው ብትሞክርም ልትደርስበት አልቻለችም።

"ደደብ!" አለች ጉንጮቿ ላይ መውረድ የጀመረውን እንባ እየጠረገች። ሳታስበው ከንፈሯን ቅርጭም አድርጋ ነክሳዋለች።

"ከማን ነው የሚሸሸው? እኔ የበደልኩት ነገር አለ እንዴ?! የተጨነቀች ነፍሴን ዋይታ አድምጦ አይዞሽ ሲለኝ፣ አለሁልሽ ሲለኝ ሲገባ ፊቱን ጠምዝዞ ጥሎኝ የሚሄደው ለምንድነው?!" ስትል አሰበች መንገዱ ላይ እንደቆመች።

የገዛ እልኋ ጉሮሮዋን አንቆ ያንቀጠቅጣት ጀመር። "ወንዶች እንደምን ያሉ ይሉኝታ የማያውቁ ህሊና ቢሶች ናቸው?፣ ችግርና ፈተና በመጣ ቁጥር ከፍቅረኞቻቸው ጎን ከመቆም ይልቅ ለምንድነው መሸሽ የሚቀናቸው?! ለምንድነው የመከራን ቀንበር እንዲሸከሙ ፍቅረኞቻቸውን ብቻቸውን የሚተዋቸው?!" መልስ የሰጣት ግን አልነበረም።

በዚህች ምድር ላይ ያለ አይዞሽ ባይና ያለ ረዳት "… እስከመቃብር ከአንተው ጋር ነኝ፣ ብክዳህ የቆምኩባት ምድር ትክዳኝ" ከሚለው ቃሏ ጋር ብቻዋን የቀረች ስለመሰላት መላይቱን ዓለም ጠላች።

*** *** ***

ወይዘሮ ሁሉግርጌሽ በየዕለቱ እየተመላለሱ ከእናቷ ጋር ረዥም ቆይታ ያደርጋሉ። ጠበቃውም በስጦታ ወረቀት የተጠቀለለ መተያያ እየያዘ መምጣቱን ቀጥሏል፤ አባቷ በአጣዳፊ ሥራ ተወጥረዋል። ሰዓሊውም በ "ደም ጎርፍ" ላይ እንዳፈጠጠ ይውላል። ቻርሊ ግን የለም።

በየቀኑ ቲያትር ቤት ስትደውል የምታገኘው መልስም" ቻርሊ ሰሞኑን አልገባም" የሚል ነው። 'ምን ሊደርስበት እንደሚችል በመገመት ተሳቀቀች። በተለይ "አንቺ ለኔ የህልውና ጥያቄ ነሽ። የመኖር ወይንም ያለመኖር ፈተና" ያላትን ስታስታውስ ነፍስና ስጋዋ በስጋት ይቦጨቅ ጀመር። በርግጥ ከዚህ ቀደም የመኖሪያ ቤቱን አካባቢ በጨዋታ መሃል በምልክት ነግሯታል። ስለዚህም ብትፈልገው አይጠፋትም። ሆኖም ወንድን ልጅ ተከትሎ መንጦልጦሉ ትርፉ መናቅ ይሆናል ስትል ፈራች። በውስጧ ያለው የናፍቆት ጉልበት ግን ከፍራቻዋ በላይ ነበር።

የቻርሊን ቤት እንደገመተችው በቀላሉ አጠያይቃ ደረሰችበት። መንደሩን መሀል ለመሃል አቋርጦ በሚያልፈው መንገድ ጠርዝ ላይ ኖራ የተቀባችውን ጎይት ሃውስን ስትመለከት ሆዷ በርህራሄና በሀዘን ይዘል ጀመር። እስከመቃብር ቃል የገባችለት ፍቅረኛዋ የሚኖረው ራቧን ትከልልበት አጥር እንኳን በሌላት ቤት ውስጥ ነው። ግራ ጋዴም "በአንቺና በርሱ መካከል ያለው ርቀት በሰማይና በመሬት መካከል ያለውን ስፋት ያክል የተዘረጋ ነው" ያለቻትን አስታውሳ በቅሬታ ፈገግ አለች።

የምታደርገው ጠፍቷት ከጎይት ሃውስ ትይዩ ፈንጠር ብላ እንደ ቆመች አንድ ሰው ገርበብ ያለውን በር ከፍቶ ወጣ። ቀይ እጅጌ ጉርድ ሸሚዝና የፀሐይ መነጽር አድርጓል። አብነት ሮጣ ልትጠመጠምበት ምንም አልቀራትም። እንደዘበት አየት አድርጓት አለፈ። ቻርሊ አለመሆኑን አወቀች።

"እባክህ..." አለችው ፈራ ተባ እያለች የወጣቱ ከቻርሊ ጋር መመሳሰል አስገርሟት። ቆም ብሎ ካስተዋላት በኋላ ጥቂት ተራምዶ ቀረባትና "ማንን ፈለግሽ የኔ እህት?" አላት።

አብነት ደነገጠች። "እባክህን ቻርሊን ፈልጌ ነበር"

"ቻርሊ ታሟል" አላትና በጥርጣሬና በመገረም ይመለከታት ጀመር።

"ላገኘው ፈልጌ ነበር"



እንደቆመ ጥቂት አሰበ ወደ ጎይት ሃውስ እየተጣደፈ ገባ። ትንሽ ከቆየ በኋላም እየተጣደፈ ወጥቶ "ጠብቂው" አላትና ደጋግሞ እየተገላመጠ ሄደ - ሊትል ቻርሊ።

ፍዝዝ ብላ እንደ ቆመች፤ ቻርሊ ጋቢውን ትከሻው ላይ ጣል አድርጎ ገርበብ ያለውን በር ከፍቶ ወጣ። ያልተበጠረው ፀጉሩ ተንጨባርሯል - ሰውነቱ ገርጥቶ አጥንቶቹ ፈጠዋል፤ ጠይምፊቱም ከስል ብሷል። ዐይኖቿን ተጠራጥራ ደጋግማ አሸቻቸው። እየቀረባት ሲመጣ ግን ገደል አፋፍ ላይ የተንጠለጠሉ ሁለት የብር ኳሶች የሚመስሉ ዐይኖቹን አየችና እርሱነቱን አረጋገጠች። "ለካንስ የፍቅርን ቅጣት አብረን ነው የተቀጣነው። በመለያየት ስጋት እኩል ኖሯል የቆሰልነው" ስትል አሰበች።

ጥቂት ተፋጠው ቆሙ። ወዲያው እንባዋ አመለጣትና ሰውነቷ ሁሉ እየተንዘፈዘፈ ታለቅስ ጀመር። እርሱ ግን እንደተጠየፋት ሁሉ ፊቱን ጠምዝዞ ባሻገር እየተመለከተ ዝም አለ።

"ቻርሊ፣ ምነው እንዲህ ሆንክብኝ?"

አልመለሰላትም።

"...ምነው ተለወጥክብኝ? ጠላኸኝ?!" አንድ ጊዜ የገረጡ ጉንጮቹን፣ አንድ ጊዜ ያልተበጠረ ፀጉሩን፣ አንድ ጊዜ ደግሞ ጤዛ ላይ እንዳደረ ብረት የሚቀዘቅዙ ጣቶቹን እየዳበሰች ትወተውተው ጀመር።

"ንገረኝና የኔም አንጀት ይቁረጥልኝ። እባክህ የውሃ ላይ ኩበት አድርገህ አታዋለኝ። እኔ እኮ አሁንም በማንም አልለወጥሁም። የገባሁልህን ቃል ታስታውስ የለም... እስከ መቃብር ከአንተው ጋር ነኝ"

የለበሰውን ጋቢ ጠርዝ ጭምድድ አድርጋ በመያዝ ዐይን ዐይኑን በስጋት ስትመለከተው፣ የደረቁ ከንፈሮቹን ላመል ያህል አላቆ "ሞተኮ!" አላት። ድምጹ ከሸለቆ ሸለቆ አስተጋብቶ እንደደከመ የገደል ማሚቶ በርቀት የሚሰማትን ያህል በህሊናዋ ውስጥ ነጠረ።

"ማነው እሱ የሞተው?" አለችው በድንጋጤ እንደፈጠጠች።

"ምስኪን ቻርሊ ከፍቅርሽ ጋር ተቀበረ። አሁን የቀረው ነፍስ አልባ ቆዳውን ተሸክሞ የሚንጠራወዝ በድኑ ብቻ ነው። ማንን ልትፈልጊ መጣሽ?" አለና ፊቱን አዙሮ ወደ ጎይት ሃውስ አመራ።

ፊቷን ሸፈነችና "አይሞትም፤ ቻርሊ እኔን ለብቻኝነት ጥሎ አይሞትም! ከነፍሴ የተዋሃደች ነፍሱን ማንም ከኔ አይነጥቃትም… ከህይወቴ ጋር የተጣመረች ህይወቱን ማንም ፈልቅቆ አይነጥላትም። የኔው ቻርሊ አይሞትም!" እያለች ትንሰቀሰቅ ጀመር።

ድምጹ ስለጠፋባት ፊቷን ገለጥ አድርጋ ስትመለከት ቻርሊ የለም። አንዳች የድንጋጤ ስሜት ከራስ ፀጉሯ እስከ እግር ጥፍሯ ነዘሯት አለፈ። ገልመጥ ገልመጥ ብላ ድንጋጤ ባፈጠጣቸው ዐይኖቿ ዙሪያዋን ቃኘች። ልታየው አልቻለችም። ድው! ድው! ድው! የሚለው የገዛ ልቧ ምት ለጆሮዋ እስኪሰማት ድረስ ፈራች።

በዝግታ ገርበብ ብሎ ወደተከፈተው በር አመራች። መግባት ግን አልደፈረችም። ደጃፉ ላይ እንደቆመች "ቻርሊ፣ ቻርሊ!" ስትል ተጣራች። የመለሰላት አልነበረም። "እባክህ አታስጨንቀኝ፣ እባክህን አትበድለኝ…" ከቤቱ ውስጥ የሚያንተመትም ድምጽ የሰማች መሰላትና ገርበብ ያለውን በር ገፋ አድርጋው ገባች። ዐይኖቿ ደብዛዛ ያለውን ብርሃን እስኪለማመዱት ድረስ በድቅድቅ ጨለማ ዙሪያዋን የታጠረች ያህል ምንም ለማየት አልቻለችም።

ቀቂት በጥቂት ዐይኖቿ ጨለማውን አሸንፈው ሁሉን ማየት ሲችሉ፣ ቻርሊን ሁለተኛው ክፍል ውስጥ አልጋው ጠርዝ ላይ ኩርምት ብሎ ተቀምጦ አየችው። ከተቀመጠበት ሆኖ አንጋጦ ይመለከታታል። እንዳለውም ነፍስ ያለው ፍጡር መሆኑን የሚያስረዱለት የሚንከራተቱት ዐይኖቹ ብቻ በመሆናቸው "ሞቻለሁ" ቢል እውነት አለው።

ለምንስ ቆሚያለሁ ማለት ዘበት ኖሯል። የሰው ልጅ ለገዛ ገላው እንደዚህ ባዳ ይሆናል? ያ እንደማለዳ ጮራ ልብን የሚያቀልጥ ፈገግታው ከምን ገባ? በራስ የመተማመን መንፈሱን ምን እንዲህ ሰበረው? ያን ወንዳወንድ አቋሙን ውሃ እንደገባ አሞሌ ያሟሟው ምንድን ይሆን?! እዚያው እንደተቀመጠ የሚሞትባት መሰላትና ፈራች።

ጠጋ አለችና ጋቢውን ትከሻው ላይ አስተካከለችለት። ዞር ብሎ እንኳን አላያትም። ዐይኖቹን አፈሩ ወለል ላይ እያንከራተተ ዝም አለ።



"ቻርሊ፣ እባክህን ፍቅርህን እንጂ ጥላቻህን አታሳየኝ። አልበደልኩህም፣ እመነኝ… ከመሰለህም ይቅር በለኝ" ትከሻውን እንደያዘች ተማፀነችው።

"አንቺ የበደልሽኝ ነገር የለም አብነት፤ ራሴ እራሴን በደልኩት። በመካከላችን ያለው ገደል ሊዘለል የማይችል መሆኑን ማየት አቃተኝ። ፍቅር ዐይኔን ሰወረኝ፤ የማመዛዘኛ ህሊናዬን ቀማኝ። አብነት እባክሽ ተይኝ… እንደገዛ ጥላዬ በሄድኩበት እየተከተልሽ በፀፀት ጅራፍ አትግረፊኝ። በቃኝ! እወድሃለሁ አትበይኝ! የሾህ አክሊል በጭንቅላቴ ላይ ደፍተሽ መርዛም ጌጥ ሆንሽ አታድሚኝ!" አላት በሚንቀጠቀጥ ድምጽ።

"ቻርሊ…"

"ቀድሞም እኮ ነግሬሻለሁ። እኔ ላንቺ የምገባ ሰው አይደለሁም"

"እንደሱ አትበለኝ ቻርሊ…"

"ለምን እውነትን እንፈራዋለን? እንደ ግንባር ላይ ጠባሳ ልሸህ፣ ፈግፍጌ ላጥፋህ ቢሉት በጀ የማይለውን ሃቅ ለምን እንሸሽዋለን? አንቺ ዘረ ብዙኻ የሃብታም ልጅ ነሽ…"

"እመነኝ አልኩህ ቻርሊ፤ ንዋይ አይለውጠኝም… የሚያልፈውን ሀብት አምኜ ለዘለዓለሙ በውስጤ አብቦ የሚኖረውን ፍቅርህን ያህል ታላቅ ሀብት በገንዘብ አልለውጠውም።"

"አንቺ ወጣትና ውብ ነሽ አብነት!"

"ውብትም እኮ ጤዛ ነው ሆዴ! አደይ አደይን ሆኖ አይከርምም፤ ቀስተ ደመና በሰማይ ላይ እንደዋለበት አያድርም፤ አበባም አብቦ አይኖርም። ውበቱ የማይደበዝዝ ውበት የልብ ፍቅር ብቻ ነው። እባክህ ውብ ነሽ እያልክ አታንጠራራኝ?! ነገ በእድሜ ነቀርሳ ጉንጮቼ ሲሸበሸቡ፤ የዐይኔ ውሃዎች ሲሟሙ ወደቅሽ ወላለቅሽ ልትለኝ ፤ ዛሬ ውብ ነሽ አትበለኝ…"

እጁን ይዛ ተነሳና አንገቷ ላይ ጥምጥም ብሎ አቀፋት። ለተቅበዘበዘው መንፈሱ ተገን እንደሚፈልግ አላጣችውም። እጆቿን ወገቡ ዙሪያ አጠላልፋ ጭምቅ አድርጋ አቀፈችው።

በእቅፏ ውስጥ እያለ የቀዘቀዘው ደሙ ሲሞቅ፣ የደነዘዘው ሰውነቱ ሲፍታታ ታወቃት። እርሷም አንድ ደስ የሚል ስሜት ሰውነቷን ሲወረው… ልቧ ቅልል… ዐይኖቿ ስልምልም… ጉልበቶቿ ብርክርክ ሲሉ ተሰማት።

የአንዳቸው ሙቀት አንዳቸውን ሲፈጃቸው በገዛ ልባቸው ደወል እየደነበሩ፣ አንዳቸው በአንዳቸው እቅፍ ውስጥ ተሰለመለሙ።

ከንፈሮቹን ለአመል ያህል ከከንፈሯ አሳቆ "እወድሻለሁ አቢ" አላት።

የትንፋሽ ያህል ነበር ያዳመጠችው። ክዕምሮዋ ሥራውን ያቆመ፣ ልቧ ደም መርጨቱን የረሣ መሰላት። በነጭ ደመና መሰል ነገር ውስጥ እየተንሳፈፈች፣ ሰማየ ሰማያትን እያቋረጠች ሽቅብ ወደ አየር እንደምትመጥቅ፤ የምድርን ማህፀን ሰርስራ የውቅያኖስን ያህል ጥልቀት ቁልቁል እንደምትጠልቅ ገመተች። "ቻርሊ፣ እኔም እወድሃለሁ" ለማለት እያሰበች ሃይሏም ጉልበቷም ከድቷት ተዝለፈለፈች።

ከዚያ በኋላ የምታስታውሰው ምን ነበር? ምንም።

አብነት ቻርሊ አልጋ ላይ የሞት ያህል እንቅልፍ ወስዷታል። ቻርሊ ጋቢውን ደረብ እንዳደረገ ኋይት ሃውስ ሳሎን ውስጥ ይንጎራደዳል። ሲጋራ ማጨስ ስላሰኘው ከኪሱ ሳንቲም አውጥቶ ወደ ደጅ ብቅ አለ። ቡቾ በሩ ላይ ተቀምጦ ያንቀላፋል።

"ቡቾ!" ቡቾ ከእንቅልፉ ነቅቶ ቻርሊን ሽቅብ አስተዋለና ፈጥኖ ተነሳ።

"አቤት ጋሽ ቻርሊ"

"ሂድና ከጀማል ሱቅ ሁለት ሲጋራ ግዛልኝ... እንደ ልማድህ ሰብረህ እንዳታመጣ ደግሞ" ሣንቲሙን ሰጠው።

"ጋሽ ቻርሊ..."

"ምን ሆንክ?"

"ማንናት ቅድም ጓዳ ሆና የጮኸችው?"

"ማን ጮኸ?"

"ሃረገወይንን ገረዷት እንዴ?"

ቻርሊ ሳቅ አፈነው ። "ወስላታ !በል ቶሎ ሂድ!"

"ጋሽ ቻርሊ..."

"ቶሎ ሂድ እኮ ነው የምልህ!"

"እርሶ ግን ጨካኝ ሰዎት"

"ምን በደልኩህ?"

"አባዬ ሲገርፈኝ አንድም ቀን እንኳን ገላግለውኝ አያውቁም"

"አንተ ለምን በአንድ ዳቦ አትጠግብም?"



"እኔ እንጃ ይርበኛል። አባዬ አሣማ ነህ የሚለኝ እውነት ነው?!" ቻርሊ ሌላ ሣንቲም አውጥቶ ሰጠውና "በዚህ ደግሞ ለራስህ ዳቦ ግዛ" አለው። ቡቾ ፊቱ ጨረቃ መሰለ።

"ለምንድነው ትምህርት ቤት ያልሄድከው ቡቾ?"

"ሂሳብ ችያለሁ። አባዬ ይበቃሃል ብሎኛል። ከዚህ በላይ ካወቅህ ታብዳለህ ብሎኛል... ተምረህ ከምታብድ ደንቆሮ ሆነህ ብትራብ ይሻላል ብሎኛል። እውነቱን ነው ጋሽ ቻርሊ?..."

ቻርሊ ልቡ በጥልቅ ሀዘን ስለተወጋ አልመለሰለትም። ቡቾም እየሮጠ ወደ ተላከበት ገሰገሰ።

አብነት ከሰመመን ዓይነት እንቅልፏ ስትነቃ ቻርሊ አልጋ ውስጥ እንደሆነች ተረዳች። ወዲያውኑ የፍራቻና የድንጋጤ ስሜት ያንቀጠቅጣት ጀመር። "ለምን? ለምን እንደዚህ ሆን?!" እያለች ተንሰቅስቃ ማልቀስ ጀመረች። ለተደፈረው ክብሯ፣ ለወደፊቱ ህይወቷ፣ ለጠበቃው እድል ... ለማን እንደምታለቅስ ግን አታውቅም።

መጀመሪያ ላይ ክብሯ ያለወግና ማዕረግ፣ ውስኪ እንደ ውሃ ሳይፈስ፣ ጮማ ሳይቆረጥ፣ ከበሮ ሳይደለቅ በመሄዱ ራሷን እንደ ክብረ ቢስ ሴት አድርጋ በመቁጠሯ የቁጭት እሳት ከውስጥ እየፈጀ አቃጠላት።

እየቆየች ግን "ነፍሴ ለመረጠው ሰው የስጋና የልብ ክብሬን አሳልፌ ስለሰጠሁ 'ረከስሽ!' ብሎ የሚኮንነኝ ከቶ ማን ነው?!" እያለች ራሷን አጀገነች።

ተንጋላ ከተኛችበት አልጋ ላይ ለመነሳት ስትሞክር ጉልበቶቿ ይንቀጠቀጡባት፣ ከባድ የራስ ምታትና የአካል ድካም ይሰማት ጀመር። "ቻርሊ እባክህ ውሃ" ስትል ጠየቀችው።

ከአልጋው ትይዩ ባለው ወንበር ላይ ኩርምት ብሎ ተቀምጧል። የደነገጠ፣ ግራ የገባውና ተስፋ የቆረጠ ፊቱን ስትመለከት "አብነቴ፣ እንዶድ በገርነቷ ውሃ በላት የሚባለውን ተረት ታውቂያለሽ?! ወደድኩ፣ አፈቀርኩ ብለሽ ስትንበረከኪ ጀርባሽን ረግጦ በሌላይቱ ሄዋን ላይ ለሚንጠለጠል የአዳም ዘር እንዳች ብለሽ ልብሽን እንዳትሰጭ!" እያለች ሣራ ጋዴም ያስጠነቀቀቻትን አስታወሰችና ልቧ በፍጥነት ይመታ ጀመር።

በብርጭቆ ቀድቶ የሰጣትን ውሃ ጠጥታ ስትጨርስ በፍቅርና በርህራሄ ዐይን ቁልቁል እያስተዋላት "አቢ፣ ስለወደፊቱ ህይወታችን ምን ታስቢያለሽ?" ሲል ጠየቃት።

ለረዥም ጊዜ በፀጥታ ስትመለከተው ቆይታ "አገባሃለሁ!" አለችው ድክም ባለ ድምጽ።

"እርግጠኛ ነሽ አቢ?!"

"እንደገና ቃሌን በመሃላ ማረጋገጥ አለብኝ?" አለችው በቅሬታ ፈገግ ብላ።

"የለም!... ቃልሽንስ ራሴን የማምነውን ያህል አምነዋለሁ!"



# ክፍል ሦስት

## ምዕራፍ አሥራ ሶስት

መንገሻ የኔነህ ተጨንቀው ነው የሰነበቱት። የቀን እረፍት የለ የሌሊት። "እብነት አስመጭና ላኪ ድርጅት" ከዚህ በፊት ካጋጠሙት አደጋዎች ሁሉ የከፋ አደጋ ላይ ነው!

እብነት እንደወትሮዋ አታያቸውም። ማለዳ ከቤት ይወጣሉ፤ ቀትር ላይ ወደ ቢሯቸው ይመለሱና ሰፊውን ቢሮ ቆልፈው ከወዲያ ወዲህ እንደተንቆራጠጡ የስልኩን እጀታ ሲያነሱና ሲጥሉ እስከ ምሽት ይቆያሉ። ውድቅት ላይ ወደ ቤታቸው ይመለሳሉ። ምን እንደተፈጠረ ልታውቅ ግን አልቻለችም።

አንድ ጠዋት ካቀረቀረችበት የሂሣብ መዝገብ ላይ አስጠርተዋት እየተጣደፈች ወደ ቢሯቸው ገባች። አባቷ ፒፓቸውን እንደነከሱ፣ ጠበቃው ሲጋራውን እያጨሰ በፀጥታ ተቀምጠዋል። ከፍተኛ ችግር መፈጠሩን ከቢሮው ሁኔታ ተረዳች። ጠበቃው ከሞቀ ፈገግታ ጋር ሰላምታ ሲያቀርብላት፣ አባቷ የምትቀመጥበትን ወንበር በአገጫቸው አመለከቷት። ሆዷ እንደፈራ ወንበር ስባ ተቀመጠች።

አባቷ ግምባር ላይ በይ ሠርተው የሚታዩት የህይወት መስመሮች ተስፋ መቁረጣቸውንና ጭንቀታቸውን ገልጸው አሳዩዋት። የሚያጨሱትን ፒፓ መተርኮሻው ላይ አስቀምጠው ጉሮሯቸውን ከጠራረጉ በኋላ "በጣም አጣዳፊ ለሆነ ጥብቅ ጉዳይ ነው የጠራሁህ አቶ ሰዩም። በቅድሚያ ግን እብነት እዚህ የተገኘችበትን ምክንያት ማወቅ ከፈለግህ በሚቀጥሉት ጥቂት ዓመታት ውስጥ የድርጅቱን ሃላፊነት ተቀብላ እኔን በመተካት የምትሠራ ስለሆነ የድርጅቱን ሚስጥር ማወቅና ያጋጠመውን ችግር መካፈል ስላለባት ነው..."

ገና ንግግራቸውን ሳይጨርሱ ጠበቃው በመገረም የሚቁለጨለጩ ዐይኖቹን እያርገበገበ ከመቀመጫው ተነሳና "እንኳን ደስ ያለሽ ጽጌረዳ" በማለት ጨበጣት።

እብነት በዚህ ድርጊቱ በመደናገጧ የዘረጋላትን እጅ ከመጨበጥ በቀር የተናገረችው ነገር አልነበረም።

አባቷ በቅሬታ ፈገግ እያሉ "አትድከም አቶ ሰዩም፤ ድርጅቱ አሁን ከገባበት የችግር ማጥ ካልወጣ ከእንግዲህ 'እብነት አስመጭና ላኪ

ድርጅት የሚባል ታሪክ የለም። የኔም ህይወት በአደጋ ላይ ነው" አሉና ሁሉቱንም በፀጥታ ያስተውሏቸው ጀመር። የአብነት ዐይኖች በድንጋጤ ፈጠጡ፤ የጠበቃው አፍ በመገረም ተከፍቶ ቀረ።

ከጥቂት ቆይታ በኋላ ጠበቃው ከንፈሩን በምላሱ እያረጠበ "ከዚህ ቀደም ከደረሱት አደጋዎች እስከፊ የሆነ ችግር ደረሰ እንዴ?" ሲል ጠየቀ።

"የአሁኑ ከምን ጊዜውም የከፋ ነው። እንዴት ብዬ እንኳን እንደምገልጽላችሁ አላውቅም" አሉና ያበቀመጡትን ፒፓ አንስተው በፀጥታ ያጨሱ ጀመር።

"ይግለጹልና... ከዚህ ቀደም በዚህ ድርጅት ምክንያት ያልተጋፈጥነው ፈተና፣ ያላየነው አበሳ የለም። የአሁኑን ደግሞ እንዳመጣጡ እንደምንመልሰው እርግጠኛ ነኝ" አለ ጠበቃው። ከአፉ የጀገነ ቢመስልም ገጽታው ግን ስጋትና ጭንቀት እንዳንዣበበት ነበር።

"ወደ ሃገር ውስጥ በድብቅ ልናሾልከው የሞከርነው ብዛት ያለው የጦር መሣሪያ ተያዘ!" አሉ አባቷ በቁጭት ጥርሶቻቸውን እያፋጩ። አብነትና ጠበቃውም በድንጋጤ ድንጋይ መስለው ከመቀመጥ በቀር አንዲትም ቃል አልተነፈሱም።

ከብዙ ቆይታ በኋላ ጠበቃው የሚያጨሰውን ሲጋራ በመተርኮሻው ላይ አጠፋና "ታዲያ ከዚህ ቀደም እንደምናደርገው በመርሆዎቻችን ተጠቅመን ድርጅቱን ከወንጀሉ ነጻ የምናደርግበትን መንገድ ለምን አንጠቀምም?" ሲል ጠየቀ።

"ይሄኛው ችግር ከምን ጊዜውም የከፋ ነው። እንዳለመታደል ሆኖ ብዙ ውስብስብ ጉዳዮች ተፈጽመዋል። ለባለስልጣኖች መደለያ ሰጥተን፣ የፈናንስ ፖሊሶችን አፍ በብር ጠቅጥቀን፣ የህግ ሰዎችን አይምሮ በጉቦ ብዛት አደንዝዘን፣ ድርጅቱንም ሆነ የኔን ህይወት ከአደጋ የምናተርፍበት ቀዳዳዎች ሁሉ ተደፍነዋል" አሉ ራሳቸውን በቁጭት እየነቀነቁ።

"ደህና... ዝርዝር ጉዳዩን ቢያስረዱን" አለ ጠበቃው የማስታወሻ ደብተሩንና ብዕሩን አውጥቶ ለመጻፍ እየተመቻቸ።



"ተወው አቶ በዩም፤ ከእንግዲህ ምንም መጻፍ አያስፈልግም" አሉት እጃቸውን እያወናጨፉ። ጠበቃው በመገረም እየተመለከታቸው የማስታወሻ ደብተሩንና ብዕሩን ወደ ኪሱ መለሰ።

"ከዚህ በኋላ ማድረግ የምንችለው ብዙ ነገር ያለ አይመስለኝም። ምናልባት አንድ የመጨረሻ ሙከራ ብቻ ማድረግ የምንችል ይመስለኛል። ይቺ ቀዳዳ ደግሞ ዝሆንን በመርፌ ቀዳዳ የማሾለክ ያህል የጠበበች ነች። ለማንኛውም ዝርዝር ጉዳዩን ላስረዳችሁ" አሉና ከመቀመጫቸው ተስተካከሉ።

ድርጊቱ የተፈጸመው ከአንድ ሳምንት በፊት ነበር። "የአብነት አስመጭና ላኪ ድርጅት" ከአንድ አውሮፓዊ የግል ኩባንያ ጋር በመዋዋል በርካታ የጦር መሣሪያዎች ይገዛል። ከሱዳን መንግስት ባለስልጣኖች ጋር በመመሳጠርም መሣሪያዎቹ ካርቱም ላይ እንዲራገፉ ያደርጋል። የሱዳን መንግስት ባለስልጣኖች በሰጡት የይለፍ ፍቃድም መሣሪያዎቹ በአንድ መለስተኛ የጭነት መኪና ተጭነው ኩርሙክ ከተባለው የሱዳን የጠረፍ ከተማ ድረስ ይመጣሉ።

በናፖሊዮን እምባው የሚመራ ሰስት አባላት ያሉት የድርጅቱ ሠራተኞች ኩርሙክ ላይ መሣሪያዎቹን ተረክበው ሸራ በለበሰች ቶዮታ ፒክ አፕ መኪና በመጫን አሳቻ መንገድ ተጠቅመው ወደ አሶሳ ይበራሉ። ያ መሣሪያ በሀገር ውስጥ በህቡእ ለሚንቀሳቀስ አንድ የፖለቲካ ድርጅት በከፍተኛ ዋጋ የሚሸጥ ነበር።

የኮንትሮባንድ መሣሪያዎቹን የጫነችው ቶዮታ የአሶሳን ከተማ ለቃ ከመውጣቷ በፊት በፊናንስ ፖሊሶች እይታ ውስጥ ትገባና እንድትቆም ትጠየቃለች። መኪናዋን ሲያሽከረክር የነበረው ናፖሊዮን ከሁለቱ የሥራ ባልደረቦቹ ጋር በመመካከር የፖሊሶቹን ማስጠንቀቂያ ጥሶ በከፍተኛ ፍጥነት እየበረረ ያመልጣል።

የአካባቢው ፊናንስ ፖሊስ አዛዥ የሆነ ሻምበል ሁለት ፖሊሶችን በማስከተል በላንድሮቨር መኪና ቶዮታዋን እያባረረ ተኩስ ይከፍታል። እነ ናፖሊዮን ቶዮታዋ በጫነችው ከባድት ማቢያ ከሚያባርራት ላንድሮቨር እይታ ውጭ መሆን አለመቻሏን በመገመት መኪናዋን ዳር በማስያዝ በላንድሮቨሯ ላይ የአፀፋ ተኩስ ይመልሳሉ።

በዚህ ሁኔታ ሁሉም ከመኪናዎቻቸው ወርደው ከግማሽ ሰዓት ለበለጠ ጊዜ ይዋጋሉ። በዚሁ ውጊያ ላይ ሁለቱ የድርጅቱ ሠራተኞች ወዲያውኑ ሲሞቱ፣ ናፖሊዮን ከንዱ ላይ በጥይት ይጫርና መኪናዋን ጥሎ ያመልጣል።

ከፈናንስ ፖሊሶቹ ወገን ሻምበሉና አንድ ወታደር ሲሞቱ፣ ሶስተኛው ወታደር በተኩሱ ወቅት ወደ ቶሮንቶዋ በመጠጋት ጋቢናውን ከፍቶ ቁልፏን ሊነቅል ሲሞክር በናፖሊዮን እጅ ቆስሏል።

አባቷ ዝርዝር ታሪኩን ሳይጨርሱ ጠበቃው ጣልቃ በመግባት "እና መኪናዋ ተይዛለች ማለት ነው?" ሲል እየተቁነጠነጠ ጠየቀ።

መንገሻ በአዎንታ ራሳቸውን ነቀነቁ።

"ናፖሊዮን ከመሸሹ በፊት ታርጋዋን ነቅሎ ነበር?!"

"በዚያ በኩል ችግር የለም። ቀድሞውንም የተለጠፈላት የሃሰት ታርጋ ነበር። የሻሲ ቁጥሯም የተፋቀ ነው"

ጠበቃው በእፎይታ ተነፈሰና "በተገደሉት ሠራተኞች ኪስ ውስጥ ማንነታቸውን ሊለይ የሚችል መታወቂያ ነበር?"

"የመስክ ሠራተኞቻችን መታወቂያዎች ሁሉ የሀሰት መታወቂያዎች መሆናቸውን ታውቅ የለም?!"

"ታዲያ የተጫነው የጦር መሣሪያ የኛ ድርጅት ለመሆኑ ምን ማስረጃ ያገኛሉ?" ሲል ጠበቃው በፈገግታ ጠየቀ።

አባቷ በረዥሙ ተነፈሱና "አሁን የገጠመንን ችግር ከሌላው ጊዜ ችግራችን ሁሉ የከፋ የሚያደርገው ይሄው አይደል?!" አሉ።

"እንዴት?" አለ ጠበቃው አሁንም እየተቁነጠነጠ።

"መሣሪያዎቹን በድርጅቱ ስም የገዛንበት ሰነድ መኪናዋ ውስጥ ነበር!" አሉ ከንፈራቸው እየተንቀጠቀጠ።

ጠበቃው መቀመጫውን በመርፌ የተወጋ ያህል ፍንጥር ብሎ ተነሳና "እንዲህ ዓይነት ስህተት እንዴት ሊፈጠር ይችላል?!" ሲል ጮኸ።

"ተፈጥሯል። ሰነዱ ልክ ከሱዳኖቹ ጋር ርክክቡን እንደጨረስን እዚያው ጠረፉ ላይ መቃጠል ነበረበት። ናፖሊዮን እንዴት ይህን እንደዘነጋ አላውቅም። እንደሚለው በመጨረሻዋ ደቂቃ ሰነዱን ከመኪናዋ ውስጥ ለማውጣት ጊዜ አልነበረውም" አሉ በፀፀት።

"በጣም አሳሳቢ ጉዳይ ነው" አለ... ጠበቃው ተመልሶ እየተቀመጠ።

"ትልቁን አሳሳቢ ጉዳይ ደግሞ ልንገራችሁ?!"

"ከዚህ የከፋ?"

"ከዚህ በጣም የከፋ! በተኩሱ ልውውጥ የሞተው ሻምበል ማን እንደሆነ ለመገመት ትችላለህ?!"

ጠበቃው ራሱን በመወዝወዝ መገመት አለመቻሉን ገለጸ።



"ከፍተኛ ደረጃ ላይ ናቸው ከሚባሉ የሃገሪቱ ባለስልጣኖች ውስጥ የአንደኛው ታናሽ ወንድም ነው። ቀብሩ የተፈጸመውም በአዲስ አበባ ከተማ ዮሴፍ ቤተክርስቲያን ሲሆን፣ ባለስልጣኑ የወንድሙን ደም ለመበቀል እየማለ ዝቷል ሲሉ ሰማሁ። በዚሁ ሳቢያ የሃገሪቱ የደህንነት ሃይሎች ሁሉ በኛ ጉዳይ ዙሪያ መረባቸውን ዘርግተዋል። የፈናንስ ፖሊስ አባላት በበኩላቸው የአባሎቻቸውን ደም ለመበቀል ቀን ተሌት ጉዳዩን መከታተል ቀጥለዋል።

"ከኛ ወገን የሞቱት ሁለት ሰዎች እጅ አሻራዎች ጉዳይስ?" ጠበቃው መጠየቁን ቀጠለ።

"ሁለቱም ከዚህ ቀደም በማናቸውም ምክንያት አሻራ ያልሰጡ ናቸው። በመሆኑም ከአስከሬናቸው ላይ የሚነሳው አሻራ በፖሊስ ሪከርድ ውስጥ በሰነድነት ከተያዙ አሻራዎች ጋር ተመሳክሮ ማንነታቸው ሊለይ አይችልም" ሲሉ መለሱለት።

አብነት ዐይኖቿ እንደፈጠጡ የልቧ ምትም ከደቂቃ ደቂቃ እየጨመረ ነው።

"በጣም ያስደነቀኝን ነገር ደግሞ ልንገራችሁ ... ይህን ያህል ማስረጃ አግኝተው፣ ደህንነቶችም ይሁኑ ፖሊሶች እስከአሁን የድርጅቱን በር ማንኳኳት እንዴት እንዳቃታቸው ብቻ ነው። ይሄ ዝምታቸው ከማስገረም አልፎ እያስጨነቀኝ ነው" አሉ በፒፓቸው ጫፍ ጠረጴዛውን እየቆረቆሩ።

"ምናልባት ሰነዱ እስካሁን በጃቸው አልገባ እንደሆንስ?!" አለ ጠበቃው ገጽታው በተስፋ ፀዳል እየፈካ።

"ተአምር ነው! ይሄማ በጠራራ ፀሐይ ዝሆንን ከአንድ ሜትር ርቀት ላይ ማየት እንዳለመቻል ያለ እውርነት ነው" አሉ በቅሬታ እንደፈገጉ።

ሶስቱም ያለ ቃላት ልውውጥ ለረዥም ጊዜ በፀጥታ ተፋጠው ከቆዩ በኋላ አብነት በድንጋጤ የፈጠጡ ዐይኖቿን እያቁለጨለጨች "ቅድም 'ድርጅቱ ከተዘፈቀበት ችግር ውስጥ ለማምለጥ ከመርፌ ቀዳዳ የጠበበች መሹለኪያ አለች' ብለህ ነበር። መንገዱን ልታስረዳን ትችላለህ?" ስትል ጠየቀች ከአባቷ እንደበት ተአምር ለመስማት እየጠበቀች።

አባቷ ከእንቅልፋቸው እንደባነኑ አይነት በረገጉና "አዎን... አዎን... ለዚያም ቢሆን ከጊዜ አንጻር ሲታይ እጅግ ብዙ ብዙ

ዘግይተናል። ምናልባት ያ ሰነድ እስካአሁን በደህንነት ወይም በመንግስት ባለስልጣኖች እጅ ያልገባ ከሆነ... ምናልባት አሁንም በቆሰለው የፊናንስ ፖሊስ እጅ ውስጥ ያለ ከሆነ የጠየቀውን ዋጋ ከፍለን ለመግዛት መሞከር የመጨረሻው አማራጭ ነው። በኔ ግምት ይሄኛው አማራጭ የማይሠራ ከሆነ "አብነት አስመጪና ላኪ ድርጅት" አበቃለት ማለት ነው። የኔም እጣ በነፍስ ግዳይ ወንጀል ተከስሼ ሃያ አራት ሰዓት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ በጥይት መደብደብ ይሆናል። ከነዚያ ሁሉ የስቃይና የትግል አመታት በኋላ ወደ ትቢያ የምዘቅጥበት ሰዓት ቀርባለች" አሉ ሀዘን በሰበረው ድምጽ።

አብነት በተቀመጠችበት ትንቀጠቀጥ ጀመር። በጠበቃው ፊት ላለማልቀስ ከውስጥ የሚታገላትን እንባ ጥርሷን እንደነከሰች አግዳዋለች።

"እንዳሉት አሁንም የቀረችዋ ትንሽ የተስፋ ጭላንጭል ሳትወድም በጊዜ እያራገብን እንድትንቦገቦግ ለማድረግ ብንጥር የሚሻል ነው የሚመስለኝ" አለ ጠበቃው።

"እሱንማ መች አጣሁት?! ዋናው ጉዳይ እንዴት የሚለው ጥያቄ እኮ ነው አቶ ስዩም" አሉ። አኳኋናቸው ሁሉ ሞት ተፈርዶበት ፍጹም ተስፋ እንደቆረጠ ሰው ነው።

ጠበቃው በጣቱ ከያዘው ሲጋራ ቀጥ ብሎ የሚወጣውን ጢስ በፀጥታ ሲመለከት ቆይቶ ፈገግ አለ። ብዙ ሳይቆይ ያች የፈገግታ ፍንጣቂ ገጹን ሁሉ በፍስሃ አጥለቀለቀችው። አብነት በጠበቃው ጭንቅላት ውስጥ ምን እንደሚመላለስ ለመገመት እየሞከረች በመገረም አፍጥጣ ታየው ጀመር።

"ይሄኛው ችግር የተወሳሰበና በጣም አደገኛ በመሆኑ ከዚህ ቀደም ድርጅቱን አጋጥመውት ከነበሩት አደጋዎች እጅግ የከፋ ቢሆንም እስከመጨረሻዋ ደቂቃ ተስፋ መቁረጥና እጃችንን አጣጥፈን ፖሊስ በራችንን እስኪያንኳኳ መጠበቅ አይኖርብንም። ማን ያውቃል? ይሄኛውንም ችግር እንደሌሎች ሁሉ እንወጣው ይሆናል ... ውጤቱም ከዚህ በኋላ በምናደርገው ጥረት የሚወሰን ይመስለኛል..." አለ ጠበቃው ፊቱ ላይ የሚጫወተውን ፈገግታ ግምባሩን በመቋጠር ለመደበቅ እየሞከረ።

"ይሄማ እውነት ነው። ዋናው ጥያቄ ከቀረችን የቅጽበት ያህል ጊዜ ጋር እንዴት አብረን እንሩጥ የሚለው ነው። ከዚህ በኋላ



በማንኛውም ደቂቃ ፖሊስ ደጃችን ላይ ሊቆም ይችላል" አሉ አባቷ ተስፋ እንደቆረጡ።

"ከዚህ ቀደም ምን ያህል ጊዜ ይህን ድርጅት ከተከሰሰባቸው ከፍተኛ ወንጀሎችና ከገባበት እሳት ውስጥ መንጭቄ እንዳወጣሁት ያውቃሉ። አሁንም በቀረችን ጊዜ እንድሮጥባት እድሉን ብቻ ይስጡኝ። ማን ያውቃል? ተአምር ሠርተን ዳግመኛ የድርጅቱን ህልውና ልናጸናው እድል ከኛ ጎን ይቆም ይሆናል" አለ ጠበቃው አብነትን በስለታም ዓይኖቹ ሰረቅ አድርጎ እየጠረባት።

"የድርጅቱን ህልውና ብቻ አይደለም አቶ ስዩም፤ ... ዋናው የራሴ ህይወት ጉዳይ መሆኑን አትዘንጋ!" አሉ አባቷ።

"ከእንግዲህ ጊዜ ባናጠፋ ይሻላል፤ ነገውኑ ወደ አሶሳ እንቀሳቀሳለሁ" አለ ጠበቃው በቁርጠኝነት ።

አባቷ ከመቀመጫቸው ተነሱ፤ ጠበቃውም ፈጥኖ ከመቀመጫው ተነሳ። ሁለቱም ለአፍታ ተፋጠው ከቆዩ በኋላ የሚንቀጠቀጥ እጃቸውን ዘረጉለት። ጠበቃው ደንዝዛ የተቀመጠችው አብነትን የጎድን እያስተዋለ የዘረጉለትን እጅ ጨበጠ።

"አቶ ስዩም፣ እስካሁን ለድርጅቱ ለዋልክለት ውለታና አሁንም ህይወቴን ለማትረፍ ለምታደርገው ሩጫ ብድሩን በምን እንደምከፍልህ አላውቅም..."

የጠበቃው ዐይኖች ፈጥነው ወደ አብነት ሮጡ።

"... በርግጥ በምድር ላይ ውለታህን የምከፍልበት ምንም አቅም የለኝም። ከገባሁበት ወጥመድ ውስጥ አመልጣለሁ የሚል እምነት ባይኖረኝም እንዳልከው እስከመጨረሻዋ ደቂቃ ድረስ እጅና እግሬን አጣጥፌ በጭንቅላቴ ላይ ምላጭ እስኪሳብ መጠበቅ ስለሌለብኝ ሂድ ይቅናህ!" አሉ ድምጻቸው እየተቆራረጠ።

"ዋናው ጉዳይ የኔ ድካምና እርሶ የሚከፍሉኝ ወሮታ አይደለም። ህይወትዎ መትረፍ አለባት! የረዥም አመታት ድካምና ትግልዎ ውጤት የሆነው 'አብነት አስመጭና ላኪ ድርጅት' በሮቹ ለዘመናት ተከፍተው ለትውልድ የሚተላለፍ ቅርስ ሆኖ መቆየት አለበት" አለ ጠበቃው ግምባሩን ቅጭም እንዳደረገ።

"ይሄ ተአምር መሆን አለበት!" አሉ መንገሻ ፈገግ ለማለት እየሞከሩ።

"ማን ያውቃል?! ዝሆንን በመርፌ ቀዳዳ የማሾለክን ጥበብ ከ'ንግዲህ ዓለም ከኛ ይማር ይሆናል። ዛሬውኑ ናፖሊዮንን አነጋግሬ ነገ ጠዋት ወደ አሶሳ እበራለሁ" አለ ጠበቃው እየተጣደፈ።

"ወጪህ እጥፍ ሆኖ በኛ የሚሸፈን ይሆናል። ይቅናህ" አሉት አባቷ የጨበጡትን እጁን እየወዘወዙ። ጠበቃው ተሰናብቷቸው ወጣ።

በሰፊው ክፍል ውስጥ አብነትና አባቷ ብቻ ለረዥም ጊዜ በፀጥታ ተቀመጡ። ቆይቶ "ይሄውልሽ የመጨረሻዋ ሰዓት ቀረበች አብነት... ከ'ንግዲህ ቀኔ የተቆረጠች ሙት ነኝ" አሉ አባቷ ክብሪት ጭረው የፒፓውን ትምባሆ ካቀጣጠሉ በኋላ።

"ለምን አትሰወርም?" አብነት ዐይኗን በጉጉት አፍጥጣ ጠየቀቻቸው።

"ወዴትም መጥፋት አልችልም ልጄ። በኔ ምክንያት አንቺንና እርያምን እንዲያሰቃዩዋችሁ አልፈልግም። ከዚህ ይልቅ በጀግንነት ሞትን መጋፈጥን እመርጣለሁ" አሏት በቅሬታ ፈገግ እያሉ።

"ግድ የለህም አባዬ! እኛ ሁሉን እንችለዋለን!"

"አይሞከርም አልኩሽ እኮ!" ራሳቸውን እየወዘወዙ ቁርጡን ነገሯት።

"እሺ ቆይ፣ ጠበቃውን እንዴት አምነኸው የህይወትህን ጉዳይ አሳልፈህ ትሰጠዋለህ?" ስትል ጠየቀች አብነት።

" አላመንኩትም። አምኜውም አላውቅም። ወደፊትም አላምነውም። አሁን ግን አማራጭ የለኝም። የቀረችውን የመጨረሻ እድል እንዲሞክር የተውኩለት እንደማይሳካለት ስለማውቅ ነው። ዝሆን በመርፌ ቀዳዳ እንደማይሾልክ እርግጠኛ ነኝ። ከዚህ ችግር ውስጥ ለመውጣት እጣችን ከመቶ አንድ ብቻ ነው... እና እጅግም አልተጨነኩም"

"እኔ ግን ፈራሁ አባዬ... ይሄ ሰነድ በጠበቃው እጅ የገባ እለት እንደ ኳስ እያነጠረ እንደሚጫወትብን ታውቃለህ?! ከችግር ወደ ችግር እንደምንሮጥ ይሰማኛል"

"ምንም አማራጭ የለንም። ከነብር ቡጢ የድመት ንክሻ መቶ ጊዜ ይሻላል... ተይው አሁን የምንጨቃጨቀው በሞት ጉዳይ ላይ ነው" አሏት ከመቀመጫቸው እየተነሱ።

አብነትም ከመቀመጫዋ ተነስታ ቆመች። "አሁን የምረዳህ ነገር አለ?"



"ለጊዜው ምንም የለም... ፖሊስ ደጄን እስኪያንኳኳ ተዋናዩን ጓደኛሽን አጫውችልኝ" አሏትና ፈገግ አሉ።

አብነት በሀፍረት ተሸማቃ አንገቷን አቀርቅራ ከአባቷ ቢሮ ወጣች።

ጠበቃው ጊዜ አላጠፋም። ከድርጅቱ ቢሮ እንደወጣ የሲትሮይን መኪናውን ሞተር ቀስቅሶ ወደ ናፖሊዮን አምባው መኖሪያ ቤት ገሠገሠ። ዝሆን ሆኖ በመርፌ ቀዳዳ ለመሹለክ ከጊዜ ጋር መሮጥ እንዳለበት አምኗል። የዚህ ሩጫ ውጤት ከማንም በላይ የሚጠቅመው በርሱ ግምት እርሱን ብቻ ነው። "በመጀመሪያ ግን እድል ከኔ ጋር ትሁን!" እያለ እድልን ተማጸነ።

## ምዕራፍ አሥራ አራት

ከልጅነቱ ጀምሮ ችግር ምን እንደሆን ሳያውቅ በወላጆቹ ትከሻ ላይ ተሞላቆ ያደገ ቅምጥል ነበር። ብሩህና የሰላ አዕምሮው ቀለም የመቀበል ከፍተኛ ችሎታ ነበረው። ይሄ የተፈጥሮ ችሎታው ደግሞ ለትምህርት ከኔ በላይ ለአሣር የሚል ሀኬተኛ ባህሪይ ያለው ወጣት አድርጎ ቀረጸው። ብዙም ሳይርቅ የተፈጠረበት የትልቅነት ትምክህት በትከሻው ላይ የስንፍናን ካባ ደረበለት።

የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱን በከፍተኛ ውጤት አጠናቆ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በተፈጥሮ ሣይንስ ፋክሊቲ ፊዚክስ ለማጥናት ተመዘገበ። ከሁለት ዓመት በላይ ግን መማር አልቻለም። በዚያ እድሜው ቀልቡ የተሰረቀው በትምህርት ሳይሆን፤ የአባቱን መኪና እየተዋሰ በሚያምነሽንሻቸው ሴቶች ዳሌና ጭን፣ በመጠጥ ጣእምና በካርታ ቁማር ነበረ።

የተመኘውን አላጣም። በከተማው አለ የተባለ ሴሰኛ፣ የተሸነቆረ ገንቦ ነው የሚሰኝ ጠጭ፣ እሳት የላሰ ቁማርተኛ ወጣው። የትምህርቱም ነገር በዚያው አበቃለት።

ትምህርቱን ካቋረጠ በኋላ ለአራት አመታት ያህል የዘመድ ምክር ሳያግደው፣ የሰው እግዚአታ ሳይመክተው በዚያው አመሉ ገፋበት። በእድሜ እየሰከነ፣ የልጅነት ጉልበቱ እየደከመ ሲሄድ ግን ሁሉም ነገር ሰለቸው። እድሜው እየባከነ መሄዱን በማስተዋሉም ሁሉን በመጠኑ ለማድረግ ከራሱ ጋር ታገለ። ጉድ እስኪባል ድረስ አመሉን ሸሽጎ የተባረከ ለማስመሰልም ጣረ።

ይሁንና ውሎ ሲያድር ሃገሪቱም ሆነች ህዝቡ ሰለሰለቹት ወደ እንግሊዝ አገር በረረ። ቀደም ሲል ከፍተኛ የትምህርት ውጤት ስለነበረውና የዩኒቨርስቲውን የመግቢያ ፈተና በሚያኮራ ውጤት በማለፉም በኦክስፎርድ ዩኒቨርስቲ የህግ ትምህርት የመከታተል እድል አገኘ። በዚያ ዩኒቨርስቲ ግን ከሁለት ዓመት በላይ መማር አልቻለም።

አትብቱ ከተቀበረበት ሃገር በብብቱ ሸጉጦ ይዞት የወጣው አመል በነጮቹ ምድር አገርሸቶበት የለየለት ፈንጭ ሆነ። ትምህርቱን አቋርጦም በአውሮፓ ከተሞች ለአምስት ዓመት ያህል ሲያጨበጭብ ከረመ። በመጨረሻ የነጭን ፊት ማየትና የነጭን ምድር መርገጥ ቀፈፈው። ሁሉምነገር ሰልችቶትና ግራ ተጋብቶ ሲጨነቅ የአባቱን ሞትና ሀብታቸው ሰብሳቢ አጥቶ መዝረክረኩን የሚገልፅ ደብዳቤ ደረሰው። ውሎ ሳያድር የአየር ቲኬቱን ቆርጦ አዲስ አበባ ከች አለ።



ከዚያም በአፍላ ወረት፣ ያልወጣና ያልወረደበትን ሃብት እየረጨ በነጭ ምድር ላይ የሰለቸውን ጭፈራ በጥቁር መሬት ላይ በአዲስ ጉልበት ተያያዘው።

የ1966 አብዮት ሲፈነዳ በእጁ የቀረው ንብረት፣ የሚኖርበት ቪላ ቤትና አንድ ሲትሮይን መኪና ብቻ ነበር። ቀስ በቀስ ኪሱ እየተራቆተ በመምጣቱም ቤቱ ውስጥ ያሉትን ውድ ንብረቶች ሁሉ ሸጠ። መኪናዋም በቁማር እዳ ተያዘች። ሸሚዞቹ ጠየሙ፣ የጫማው ሶል እግሩ ሥር ሟሸሸ። በአና ቪላው ውስጥ እየተንጎራደደ የሚያጨሰው ሲጋራ አጥቶ እስኪያዛጋ ድረስ ድህነት ጉሮሮውን አንቆ ያዘው።

እንደንብ እውራ እየተከተሉ የሚያጅቡት ወይዛዝርት ከብሩ ጋር እንደ ጉም ተበተኑ። ጓደኞቹ ሁሉ ዐይንህን ለአፈር ብለው ሸሹት። ዓለም ከነባዶ ኪሱ አንትፍ ብላ ተፋችው። ድህነት ድህነት በሚሸተው ባዶ ቤት ውስጥ በወላለቀ የእንጨት ወንበር ላይ ተቀምጦ እያዛጋ፣ ከገዛ ህይወቱ ድክመት አንድ ቁም ነገር ተማረ። ብር የደም ሥር መሆኑን።

ቤቱን ሸጦ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ እድሉን ለመሞከር ከደላሎች ጋር ሲማከር ግን መቸም አንዴ ባለ እድላም ግምባር አድርጎ ፈጥሮታልና መካኗ አክስቱ ወ/ሮ ሁሉግርጌሽ አለሁልህ አሉት።

"እስከ ዛሬም እንባዬን እያፈሰስኩ ብለምንህ አሻፈረኝ ብለህ ይሄው እዚህ ደርሰሃል። አሁንም የወንድሜ የመጨረሻ ቅርስ የሆነው ይሄ ቤቱ አይሸጥም። ኧረ አገር ጉድ ይለናል!... አሁን የምለምንህ ካለፈው ስህተትህ ተምረህ ሰው ለመሆን እንድትጥር ነው። እኔስ ካለአንተ ማን አለኝ? ይህን ሁሉ ሀብትና ንብረት ጥዬው ልሞት አይደለም?! አንተ ተቸግረህ እኔ እጅና እግሬን ብሰበስብስ የአባትህ እጥንት እሾህ ሆኖ አይወጋኝም?! ከእንግዲህ ሀብቴ ሀብትህ ነው!" አሉት።

የጨለመችበት ዓለም ዳግመኛ ፀሐይ ሆና ሞቀችው። እንዳለፈው ግን ብርሃኗን ከሌሎች ጋር አልሞቀውም። በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ የጥብቅና ቢሮ ከፍቶ አንቱ የተባለ ጠበቃ ሆነ። ብሩህና የሰላ አዕምሮው ተሟግቶ የማይረታ ነገር አዋቂ አሰኘው። ሲበትን የከረመውን ሃብትም በአጭር ጊዜ ሰበሰበ። የገንዘብ ጥማቱ ግን ሊረካለት አልቻለም። ብር አምላኩ ሆኖ ቀረ። ከአባካኝነት በሽታ ሲፈወስ በስስት በሽታ ተለከፈ። ቢቻለው የዓለምን ሀብት ሁሉ ጠቅልሎ በደረት ኪሱ ቢያስቀምጥ ደስ ባለው።

ዛሬ መርሀ አድርጎ የያዘው ፈሊጥ "ገንዘብ መውጣት ያለበት፣ ገንዘብ ሊያስገኝ ለሚችል ጉዳይ ብቻ ነው። መርሬ እውጦ ማረሻ ማስተፋት!" የሚል ነው። አሁንም አፍንጫው ቀዳዳ ድረስ ይጠጣል። ይሁን እንጂ ብቻውን ነው ። አሁንም ሴት አምላኪ ነው። ሰባራ ሶልዲ ግን አይችራቸውም።

በኢኮኖሚያዊ አቋሙ እንደማይነቃነቅ አይነት ሆኖ በሁለት እግሩ ቀጥ ብሎ ቆሟል ። እረፍት ግን የለውም። እለት ተለት የጠኔ ያህል የሚርበው የብር ችጋር ቀን ተሌት ያሮጠዋል፤ አሁን እንኳን እየሮጠ ነው።

*** *** ***

ሰንጋተራ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት ፊት ለፊት መኪናውን አቁሞ ቁልፉን እያሽከረከረ ወደ ናፖሊዮን መኖሪያ ቤት ተጣደፈ። የቆርቆሮ አጥር ያለውን በር ገፋ አድርጎ ወደ ግቢው ከገባ በኋላም በሩን ደጋግሞ ቆረቆረ። ከውስጥ መልስ የሰጠው አልነበረም። ብዙ ዘግይቶ የቤቱ መስኮት በዝግታ ሲከፈት ተመለከተ።

ናፖሊዮን የተቀባበለውን መትረየስ ሽጉጥ ምላጭ እንደጨበጠ በጥንቃቄ በከፈተው መስኮት ጭላንጭል የእንግዳውን ማንነት ካረጋገጠ በኋላ ሽጉጡን ሽንጡ ስር ወሽቆ በለበሰው ሸሚዝ ሸፈነው።

ጠበቃው የናፖሊዮን በር ተከፍቶለት ሲገባ የተቀበለው አና አና የሚል አቧራ ያዘለ አየር፣ የሲጋራ ጭስና የጫማ ሽታ ነበር። ትንሽ ገርበብ ብሎ በተከፈተው መስኮት የሚገባው ብርሃን ክፍሉን ፍጹም ጨለማ ከመሆን አድኖታል።

በዚያ ክፍል ውስጥ ሥርዓት የያዘ አንዳችም ነገር የለም። ያረጁት የእንጨት ወንበሮች እዚያና እዚህ ተሰባጥረዋል። የሲጋራ ቁራጮች አፋ ድረስ የተጠቀጠቀበት መተርኮሻና ውሃ የተሞላበት የጆኒ ዋከር ዊስኪ ጠርሙስ የተቀመጡበት የእንጨት ጠረጴዛ ተንጋዶ ተቀምጧል። አቧራ የጠጡ ጋዜጦች የታጨቁበት መለስተኛ የመጽሐፍ መደርደሪያ ከወለሉ እምብርት ትንሽ ፈቀቅ ብሎ ቆሟል። የሰልክ ቀፎ የተቀመጠበት ብፌ ደግሞ ባዶውን ነው። ታዋቂው የፊልም ተዋናይ ቻርልስ ብሮንሰን የቶስካና ትምባሆውን እንደነከሰ የተነሳው ፎቶግራፍ ግድግዳው ላይ ተንጋዶ ተለጥፏል።



ጠበቃው እጁን ለሰላምታ እየዘረጋ "እንኳን እግዚአብሔር አተረፈህ ወዳጄ..." በማለት የሞቀ ሰላምታ ሰጠው።

ናፖሊዮን ግምባሩን እንደ ቋጠረ "አመሰግናለሁ" አለና የጠበቃውን እጅ እየወዘወዘ ጨበጠው።

ከቁመቱ ረዘም፣ ከሰውነቱ ፈርጠም ያለ ነው ናፖሊዮን እምባው። ኀፈሬውና ያደገ ጺሙ ጠቆር ያለውን የፊቱን ቀለም ይበልጥ አጨልሞታል። ፈርጣሞቹ የክንዱ ጡንቻዎች የለበሰውን እጅጌ ጉርድ ሸሚዝ ተርትረው ለመውጣት የሚታገሉ ይመስላሉ። በግራ እጁ ክንድ ላይ ደግሞ ፋሻ ጠቅሏል።

"ታዲያ አሁን ትንሽ ሻል አለህ?" አለ ጠበቃው በዐይኑ ወንበር እየፈለገ። ወንበሩ ላይ የተከመረውን አቧራ ሲመለከት ግን እንደማፈር አለ።

"ደህና ነኝ፤ መርፌ የወጋኝ ያህል እንኳን አልተሰማኝም" አለና በቀኝ እጁ ፋሻ የተጠመጠመበትን የግራ ክንዱን እየጠበጠበ ደህንነቱን አረጋገጠለት።

ጠበቃው ከኪሱ መሀረብ አውጥቶ ወንበሩ ላይ የተጋገረውን አቧራ ካፀዳ በኋላ በጥንቃቄ ጫፉ ላይ ተቀመጠ። ቤቱ ውስጥ የታመቀው የሚተነፍግ አየር ስለከረከረውም ደጋግሞ ሳለ። ቢጨንቀው "ለምን መስኮቷን ከፈት አድርገሃት ትንሽ ብርሃን አይገባም?" ሲል በደላሳ ፈገግታ እየሸነገለ ጠየቀው።

ናፖሊዮን በክፉ ዐይን ሲመለከተው ቆየና አቧራማው ወንበር ላይ ተስተካክሎ ተቀመጠ። "በህይወቴ ውስጥ በጣም ከምጠላው ብርሃን የምሸሸግበትን ይህችን የመጨረሻ ዋሻዬን ብርሃን እንዲያጥለቀልቃት አልፈልግም። እርቃኔን በአደባባይ የቆምኩ ያህል ይሰቅቀኛል" ሲል ግምባሩን ቋጥሮ መለሰለት።

ብርሃን የሚፈራ ሰው! የጠበቃው ልብ ፍጥነቱን ጨምሮ መምታት ጀመረ። እጁን በፍጥነት ወደ ኪሱ ሰዶ የሲጋራ ፓኮ አወጣና ተነስቶ እየጋበዘው "ይሁን፣ ብርሃን ከፈራህስ ይሁን..." እያለ ተንተባተበ።

ናፖሊዮን ጠበቃው የሰጠውን የሲጋራ ፓኮ ተቀብሎ አንድ ፍሬ በማውጣት ከለኮሰ በኋላ ፓኮውን ሸሚዙ ደረት ኪስ ውስጥ

ከተተው። ጠበቃው ሃፍረትም መገረምም የተቀላቀለበት ስሜት እንደተሚነው ወደ ወንበሩ ተመልሶ ተቀመጠ።

"የመጣህበትን ምክንያት ልትነግረኝ ትችላለህ?" አለ ናፖሊዮን በሲጋራው ጭስ በሠራቸው ሶስት ቀለበቶች ላይ ቡዝዝ ያሉ ዐይኖቹን እንደተከለ።

"የተፈጠረውን አደጋና ችግር ሁሉ ዛሬ ጠዋት አቶ መንገሻ ነገሩኝ... እና ይህን ከሰማሁ በኋላ ደህንነትህን ለመጠየቅ መምጣት የሚያስገርም ይሆናል?" አለ ጠበቃው ከንፈሮቹን የግድ አላቆ ፈገግ ለማለት እየሞከረ።

"ስለሱማ አመሰግንኩ! ቀን ተሌት ከአደጋ ጋር እየተጋፈጠ ለኖረ ሰው ይቺ የምላጭ ታክል ቁስል ቁጥር ውስጥ የምትገባ አይደለችም። ይልቅ ዋነኛ ምክንያትህን ንገረኝ?" ሳያውቀው እየጮኸ ነበረ። እያጣደፈ ከሚስበው ሲጋራ የሚወጣው ጭስም ጨለም ያለውን ክፍል ሞልቶታል።

"ዊል ... እ ... አሁን የመጣሁበት ዋናኛው ጉዳይ እንኳን የድርጅቱን ህልውናና የአንተንም ደህንነት ለማረጋገጥ ከእንግዲህ ወዲያ ማድረግ ስለሚገባን ጥረት እንድንመካከር ብዬ ነው" አለ ጠበቃው የመጣበት ጉዳይ እንዳይበላሽ ከአፉ የሚያወጣቸውን ቃላት በጥንቃቄ እየመረጠ።

"ከእንግዲህማ መመካከር፣ መወያየትና መነጋገር የሚል የቢሮ ፈሊጥ ሊሠራ አይችልም። ሁሉንም ነገር የሞተ ጉዳይ አድርገህ ቁጠረው። አሁን እኔ የማልመው እጄን ሊይዝ ወደ ቤቴ በሚመጣው የመጀመሪያው ፖሊስ የአፍንጫ ቀዳዳዎች ውስጥ እንደምን አድርጌ ሁለት ጥይቶች እንደማሾልክ ብቻ ነው" አለ ናፖሊዮን።

ጠበቃው የሚቀልድ መስሎት ገጽታው ላይ ፈገግታ ለማየት ቢሞክርም የናፖሊዮን ፊት ግን ኩስትር ያለ ነበር።

"እስከ መጨረሻዋ ደቂቃማ ተስፋ መቁረጥ የለብንም። ከገባንበት የችግር አዘቅት ለመውጣት ብዙ ጊዜ አለን" አለ ጠበቃው በሚቁለጨለጩ ዐይኖቹ ሊያጽናናው እየሞከረ።

"ጊዜም እድልም የሚባል ነገር የለም አልኩህ እኮ!" ናፖሊዮን ከተቀመጠበት ተነስቶ በደረት ኪሱ ካኖረው የጠበቃው ሲጋራ ላይ



አንድ ፍሬ በማውጣት እጁ ላይ ባለቀችው ሲጋራ አቀጣጠለና አላቂዋን ጣውላው ወለል ላይ ወረወራት። ጠበቃው ከመቀመጫው ተነስቶ በጫማው አሻት።

"መልካም! ለአንድ ጥያቄ ብቻ መልስ ስጠኝ... ሰነዱ በፖሊሶች ወይንም በደህንነቶች እጅ ገብቷል ብለህ የምታምን ከሆነ... እስካሁን እርምጃ ያልወሰዱበትን ምክንያት ልታስረዳኝ ትችላለህ?!" ሲል ጠየቀው ጠበቃው ወደ ነበረበት ወንበር እየተመለሰ።

ናፖሊዮን ምራቁን ጢቅ ብሎ ተፋና "እንጃ! እኔንም የደነቀኝ ይሄው ነው። እንኳን ይሄን ያህል ከባድ ወንጀልና የማያፈናፍን ማስረጃ አግኝተው፣ ለበነነ ለተነነው ሁሉ የሚሮጡ ሰዎች እስከ አሁን እግራቸውን ምን እንዳሠረው አላውቅም"

"ይሄ ዝምታ ምን ሊሆን እንደሚችል ትገምታለህ?"

"እንጃ"

"እንግዲያው እኔ የምገምተውን ልንገርህ?!"

"እህ..."

"ሰነዱን አላገኙትም!"

"ጨዋታ ጀመርክ ልበል?" ናፖሊዮን በክፍሉ ውስጥ መንጎራደዱን አቁሞ ከአንገቱ ዘንበል አለና ጠበቃውን በትዝብት ዐይን ተመለከተው።

"እመነኝ አልኩህ፣ ሰነዱ በጃቸው የለም!"

"ምንድነው የምታወራው? ሰነዱ እኮ ከመኪናው መሪ አጠገብ ከፍጥነት መቆጣጠሪያው በላይ ግልጽ ቦታ ነው የተቀመጠው!" ሲል ጮኸበት።

ጠበቃው ደነገጠና ዝም አለ። በሃሳቡ ናፖሊዮን እንደዚህ ያለ ዝርክርክ ሥራ እንዴት ሊሠራ እንደቻለ እየተገረመ ነበር።

"ይልቅ አንድ የሚያስገርም ነገር ልንገርህ አቶ ጠበቃ..." ናፖሊዮን በርጋታ እየተራመደ ወደ ጠበቃው ቀረበና ቁልቁል ተመለከተው። "በተኩሱ ልውውጥ ወቅት ሻምበሉ የሞተው በጀመሪያዎቹ ጥቂት ደቂቃዎች ውስጥ ነበር። ከዚያ ሁለቱ የኛ ሠራተኞች ተሰናበቱ። ሁለተኛውን ፖሊስ መትቼ ስጥለው የኔም ክንድ ቆስሎ ነበር። መድማት የጀመረውን ክንዴን አይቼ ቀና ስል ሶስተኛውና የመጨረሻው ፖሊስ ወደ መኪናዋ ሲሮጥ ስላየሁት ፈጥኜ ተኮስኩ። እግሩ አካባቢ ሳልጭረው የቀረሁ አልመሰለኝም ወደቀ። እንደገና ለጭንቅላቱ አነጣጥሬ በጥንቃቄ ምላጭ ሳብኩ... ሽጉጤ ግን ጥይት አልነበረውም! ከተኛበት ሆኖ ሽጉጡን ወደኔ አነጣጥሮ

ይመስለኝ ነበር። ባርኔጣው ከጭንቅላቱ ወልቆ መሬት ወድቆ ስለነበር የጭንቅላቱ በራ ታየኝ። ፊቱን አጣርቼ አየሁት ...ያንን ሰው አውቀዋለሁ!"

ጠበቃው ከመቀመጫው ተፈናጥሮ ተነሳና የናፖሊዮንን እጅ ጭምድድ አድርጎ ያዘው። ዐይኖቹ በተስፋ ፈጠው ድምጹም እየተቆራረጠ "እ ... እርግጠኛ ነህ?" ሲል ጠየቀው።

"አዎን እርግጠኛ ነኝ" አለ ጠበቃው አጥብቆ የያዘውን እጅ እያስለቀቀ።

"ማነው?"

"እንጃ... ሳምንቱን ሙሉ እዚህ ጨለማ ክፍል ውስጥ ተቀምጬ የማስበው የሰውየውን ማንነት ነው" አለና በረዥሙ መሳል ጀመረ።

"እንዴ ... ሰውየውን አውቀዋለሁ ካልክ .... እንዴት ማንነቱን ልትዘነጋ ቻልክ?" ሲል በመገረም ጠየቀው።

"የት እንደማውቀው ለማስታወስ አልቻልኩም። ባንድ ነገር ግን እርግጠኛ ነኝ። እርሱም ማንነቴን አውቋል። በዚያ በቀትር ፀሐይ፣ በዚያ አጭር ርቀት ላይ ዐይኑን ጨፍኖ ቢተኩስ እንኳን ሊመታኝ ይችል ነበረ። ይግረምህና አልተከሰም። ግራ እንደገባኝ በደረቴ ከተኛሁበት እንደ እሳት ከሚፋጀው መሬት ላይ ተነስቼ ወደ ኋላዬ ሮጥኩ አልተከተለኝም!"

የጠበቃው አፍ ባድናቆት ተከፍቷል። ዐይኖቹም እንደተበለጠጡ ናቸው። "ስለ እግዚአብሔር ብለህ የአዕምሮህን ጓዳ እየፈተሽክ የዚህን ሰው ማንነት አረጋግጥ ። እርግጠኛ ነኝ ሰነዱ አሁንም በርሱ እጅ ነው። ሊደርስ የሚችለው ጉዳት ደግሞ ከፍተኛ መሆኑን ከኔ ይልቅ አንተ የምትረዳው መሰለኝ" አለ በተስፋ እንዳፈጠጠ።

"አልቻልኩም። ቀንና ሌሊት በግምባሬ ላይ ላቤ እንደ ውሃ እስኪንቆረቆር ድረስ አዕምሮየን ጨምቄ አሰብኩ፣ አሰብኩ፣ አሰብኩ። ጭንቅላቴ ሊፈነዳ ትንሽ የቀረው ሲመስለኝ ተውኩት"

"ኖኖኖ! አሁንም እንደገና አስብ። ጭንቅላትህ በጥይት አረር ከመፈንዳቱ በፊት በራሱ ሃይል ፈንድቶ ብትገላገል የተሻለ ይመስለኛል ... ደግመህ አስብ ናፖሊዮን!"

ናፖሊዮን ትከሻውን ከፈሰና "ሁሉም ነገር ልክ እንደ ቅዠት ሆኖ ነው የሚታየኝ... አንድ ቀን ታክሲ ውስጥ ወይም ሲጋራ ስትገዛ



ሱቅ ውስጥ ያየኸውን ሰው ሌላ ጊዜ፣ በተለይ ከረዥም ጊዜ በኋላ፣ መንገድ ላይ ብታገኘው ገጽታው ይታወስሃል... ግን የት እንደምታውቀው እየመላለስክ ብታስብም ልትለየው አትችልም።

"ይሄኛውንም በዐይን እንደማውቀው እርግጠኛ ነኝ። የትና መቼ የሚሉትን ጥያቄዎች ግን አዕምሮዬ ፈጽሞ ሊመልስልኝ አልቻለም። ድሮ ድሮ ከማውቃቸው የትምህርት ቤት ጓደኞቼ ጀምሮ በአየር ወለድ ሠራዊት ውስጥ የማውቃቸውን ሰዎች አንድ በአንድ መቁጠር ምንም አልቀረኝ። ያንን ገጽታ የት እንደማውቀው ጭራሽ ማስታወስ አልቻልኩም።"

"ለምን እንዳልተኮሰብህ ለመገመት ትችላለህ?"

"አንድም ስለሚያውቀኝ ... አሊያም ጥይት በመጨረሱ ሊሆን ይችላል"

"የወደቁ ጓደኞቹን መሣሪያ መጠቀም አይችልም ነበር?"

"ይችላል። የሻምበሉ ሪቮልቨር ከርሱ አሥር ሜትር በማይሞላ ርቀት ላይ እንደወደቀ ነበር። ኧረ ቢፈልግ ላንድሮቨሩን አስነስቶ ገጭቶ ሊገድለኝም ይችላል"

ጠበቃው በደስታ ራሱን እየነቀነቀ "አሁን ሰነዱ በደህንነቶችም ይሁን በፖሊሶች እጅ እንዳልገባ ተስፋ ማድረግ እንችላለን። የፈናንስ ፖሊሱ ህይወትህን ለማትረፍ ሰነዱን አልሰጣቸውም ይሆናል" አለ።

ናፖሊዮን ለመጀመሪያ ጊዜ ፈገግ አለና "እንጃ! እኔ በዚህ ምድር ላይ በኖርኩባቸው ሰላሣ ዓመታት ውስጥ ለሰው ልጅ አደረኩት የምለው አንዳችም ደግ ነገር የለም። እና ሰውየው ቢያውቀኝም እንኳን ይህንን ያህል መስዋእትነት ለኔ ህይወት የሚከፍልበት ምክንያት የለም። ማን ያውቃል? ምናልባት እኮ አንድቀን በደህና ቡጢ መንጋጋውን ያወለኩለት ሰው ይሆናል..."

"ኖኖኖ...... ናፖሊዮን በዚች ደቂቃ ተስፋ የሚያስቆርጥ ነገር እንድትነግረኝ አልፈልግም"

"እውነቱ ግን ይሄው ነው!"

ጠበቃው በአንድ ቀን ውስጥ ብቻ የሰማው እጅግ የተመሰቃቀለ ጉዳይ እንዴት መልክ ሊይዝ እንደሚችል በፀጥታ ሲያስብ ቆየ። በተለይ ናፖሊዮንን ሊያምነው አልቻለም። ህሊናው በርካታ ጥያቄዎች እያነሳ ያስጨንቀው ጀመር።

"ፍቃድህ ቢሆን ሌላ አንድ ጥያቄ ልጠይቅህ?"

"ቀጥል!"

"ከዚህ ቀደም ድርጅቱ ተመሣሣይ ሥራዎችን በሚያካሂድበት ጊዜ እቃዎቹ የተገዙባቸው ሰነዶች እዚያው ጠረፍ ላይ ይቃጠሉ ነበር። ይህ ባሁኑ ወቅት ያልሆነበት ምክንያት ምንድነው?!"

ናፖሊዮን የዐይኑን መስኮቶች አጥበቦ ሲመለከተው ቆየና "ምክንያት እንኳን አለኝ። አየህ፣ እኛ ከኩባንያው በገዛናቸው መሣሪያዎችና ማለትም ሰነዱ በያዘው ዝርዝርና ሱዳኖቹ ባስረከቡን መሳሪያ መካከል የአይነትና የመጠን ልዩነት አለ። እንደሚገባኝ ሱዳኖቹ አጭበርብረውናል። እና የድርጅቱ ባለንብረት ደግሞ ይሄንን ማወቅ አለባቸው። መሣሪያዎቹ በህቡእ ለሚንቀሳቀሰው ድርጅት ሲሸጡ በሚፈጠረው ጉድለትና የአይነት ልዩነት ማን ተጠያቂ ይሆናል?! እና ከዚህ ነጻ ለመሆን ነበር ሰነዱን ያላቃጠልኩት"

ጠበቃው በተሰጠው መልስ ሙሉ በሙሉ ባይረካም አንገቱን በእምንታ እየነቀነቀ ዝም አለ። ናፖሊዮን የነገረው ታሪክ እውነት ከሆነ በመርፌ ቀዳዳ ለመሹለክ የእድሉ በር አሁንም ክፍት ነው። ይሁን እንጂ ልቡናው ናፖሊዮንን አላመነውም።

"ነገ ወደ አሰሳ እበራለሁ!" አለ ጠበቃው የናፖሊዮንን ስሜት ለመመርመር አፍጥጦ እየተመለከተው።

ናፖሊዮንም በተራው በጥርጣሬ ዐይን እየወጋው "ምን?" ሲል ጠየቀው።

ጠበቃው በናፖሊዮን ገጽ ላይ የድንጋጤ ስሜት ያነበበ መሰለው። "የምትለውን ሰው ፈልጌ አገኘዋለሁ!" አለ በልበ ሙሉነት።

"ጭራሽ ፈለጋችንን እያነፈነፉ ማጅራታችንን እንዲጨመድዱ ጊዜውን እንዳታፋጥንላቸው እሰጋለሁ!" አለ ናፖሊዮን በጥርጣሬ ዐይን ጠበቃውን የጎድን እያስተዋለ።

"አትጠራጠር፤ ፈለጋችንን ሊያገኙ የሚችሉበትን የመጨረሻ ቀዳዳ ደፍኜው እመለሳለሁ!" አለ ጠበቃው በእርግጠኝነት። አፉ ይህን ቢናገርም ህሊናው ግን የርሱ ወደ አሰሳ መሄድ ናፖሊዮንን ለምን እንዳስከፋው ምክንያት ይፈልግ ነበር።

"ባትሞክረው ይሻላል። ድርጊቱ በተፈጸመ አንድ ሳምንት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ፀጉረ ልውጥ የሆነ የአንድ አስመጭና ላኪ ድርጅት



ጠበቃ በዚያ አካባቢ መገኘት ለፖሊስ ትልቅ የጥርጣሬ ፍንጭ መሆኑን አታውቅም?"

"ጠበቃ መሆኔን አትዘንጋ፤ አንድ ሺ ምክንያት በመደርደር እዚያ የተገኘሁበትን ምክንያት ለማሳመን እችላለሁ። ይሄን እንተውና የመኪናዋን ታርጋ ቁጥር፣ የሰውየውን አቋምና ቅርጽ በደንብ እያስታወስክ ንገረኝ" በማለት ማስታወሻ ደብተሩንና ብዕሩን አውጥቶ ገርበብ ባለው መስኮት ወደሚገባው ብርሃን ተጠጋ። ናፖሊዮን እንደተከፋ ጠበቃው የሚጠይቀውን ሁሉ ነገረው።

"በተቻለ ፍጥነት ከአሰሳ እመለሳለሁ። እንደመጣሁም ውጤቱን አሳውቅሃለሁ" አለ ጠበቃው ማስታወሻ ደብተሩንና ብዕሩን ወደ ኪሱ እየከተተ። ናፖሊዮን አልመለሰለትም። ጠበቃው ተሰናብቶት እንደወጣ በሩን በሃይል ዘግቶ ጢቅ ብሎ ምራቁን ተፋ ።

በጨለማው ክፍል ውስጥ ወንበር ስቦ ተቀመጠናም ሁለት እግሮቹን አጠላልፎ ጠረጴዛው ላይ ሰቀላቸው። ከጠበቃው ሲጋራ አንድ ፍሬ በማውጣት ክብሪት ጭሮ ለኮሰና ብርሃኗ ቤቱን ከሙሉላ፤ በፊት ፈጥኖ ወደ መሬት በመወርወር አወደማት። "ሰው ከብርሃን ሸሽቶ የት ያመልጣል? እውር ሆነው የተፈጠሩቱ ምንኛ የታደሉ ናቸው?!" ሲል ዐይናማ ሆኖ በመፈጠሩ ተማረረ።

## ምዕራፍ አስራ አምስት

በጦር ሠራዊቱ ውስጥ የኮሎኔልነት ማዕረግ የነበረው አባቱ ለፈረንሣዩ መሪ ናፖሊዮን ቦናፓርት የነበረው ፍቅርና አክብሮት እጅግ የተለየ ነበረ። ለርሱ ናፖሊዮን ማለት ሁሉም ነገር ማለት ነው። ወደር የማይገኝለት ጀግና ከማንም በላይ ሀገር ወዳድ፣ ለተገፉት ቀን አውጭ፣ የህዝቦች ታማኝ ወታደር። ናፖሊዮን ሁሉም ነው።

ከሥራ መልስ አዲስ አበባ ከተማ በሚገኘው የጥናት ክፍሉ ውስጥ የናፖሊዮንን ታሪክና ገድል የሚያወሱ መፃህፍትና ቆየት ያሉ መጽሔቶችን በማንበብ አስተዳደጉን፣ ጠባዩንና የጦር ስልቱን በማጥናት ናፖሊዮንን የዓለማችን ታላቅ ሰው ያደረገው ሚስጥር ምን እንደሆነ ይመረምራል።

ይችን ሀገር በጎረቤቶቿ የታፈረች፣ በሌላው ሃገር ህዝብ የተከበረች ለማድረግ፤ ታላቅ ሃገርና ታላቅ ህዝብ ለመፍጠር የናፖሊዮንን መንፈስ የለበሰ፣ ዓላማውን ያነገበ፣ ወኔውን የታጠቀ ኢትዮጵያዊ ናፖሊዮን እንደሚያስፈልጋት ያስባል። ያም ሰው እርሱ ብቻ እንጂ ሌላ ሊሆን እንደማይችል ይገምታል።

ይህ ለረዥም ጊዜ በህሊናው የተጠነሰሰ ምኞት ለበላዮቹ የማይታዘዝ ትእቢተኛና መንፈሰ ግትር፣ በበታቾቹ ላይ ንቀትና ጭካኔ የሚያሳይ ክፉ ሰው እንዲሆን አስገደደው። ይህም ደግሞ በአለቆቹ ትእዛዝ እድሜ ልኩን በረሃ ለበረሃ የሚንከራተት ማዕረግ የጫኑ የሰው ግመል እንዲሆን አደረገው። በሄደባቸው የጦር ክፍሎች ሁሉ ክፉ ስሙ ቀድሞት የሚደርስ በመሆኑ የሚያቀርበውና የሚጠጋው ሰው አላገኘም። በዚሁ ሳቢያ ህልሙን እውን ለማድረግ የልቡን የሚያጫውተው፤ አብሮት የሚያሴርና የሚዶልት አላገኘም።የትልቅ ሀገር ዓላማና የትልቅ ህዝብ መሪነት ቅዠቱም አንድ ነፍስ እንኳን ሊማርከለት አልቻለም።

በዚህ እየተበሳጨ ከርሱ በቀር ሌላው ህዝብ ሁሉ ደንቆሮ፣ ራስ ወዳድና ፈሪ ይመስለው ጀመር። የበላይ አለቆቹ፣ የማዕረግ እኩዮቹና የበታቾቹ ትንኝ አክለው በዐይንህ አልሞላ እያሉት ንቀቱና ትእቢቱ እለት ተለት እየናረ ልቡን ተራራ ያህል አሳበጠው።

በሚሊዮን ህዝብ መሃል አንድ ራሱን በሀሳቡ የናፖሊዮንን ኒሻን በደረቱ ላይ ደርድሮ፣ ሻምላውን እንደጨበጠ በባህር ላይ ውጊያ ድል ሲያደርግ፣ በምድርና በአየር ጦርነት ሲያሸንፍ፣ የንጉስ ነገስቱን



ዙፋን ሰብሮ ስልጣን ሲቀዳጅ ይታየውና አንድ ቀን ህልሙ እውነት እንደሚሆን እየገመተ ራሱን ያጽናናል።

ህልሙን ከህልሙ በላይ እውን ለማድረግ አንዲት እርምጃ ከመራመዱ በፊት ግን ተቀደመ። በአጋጣሚ ይሁን ሆን ተብሎ በተቀነባበረ ሴራ፣ ባልታወቀ የመኪና አደጋ ሁለት እግሮቹ ተቆጥቅጠው ከጥቅም ውጭ ሆኑ። መከንኑም በጡረታ ተገልሎ እቤት ዋለ።

ህልሙ ግን ከደቀቁት የእግሮቹ አጥንቶች ጋር አብሮ አልደቀቀም። ሀሳቡ እንደ አካሉ ቤት አልዋለም። እንዲያም ሆኖ በአንድ ነገር እርግጠኛ ሆነ። ናፖሊዮን ቦናፓርት አካለ ስንኩል አልነበረም ... እና እርሱ ናፖሊዮንን መሆን አይችልም።

ይህም ቢሆን ጭራሽ ተስፋ ቆርጦ እጅና እግሩን አጣጥፎ እንዲቀመጥ አላደረገውም። በርሱ ኢትዮጵያዊ ናፖሊዮንነት ያላየውን የታላቅ ሃገር መሪነት ህልሙን፣ ከአደጋው በፊት አንድ ወር ቀደም ብሎ በተወለደው ልጁ ሲፈጸም ለማየት፣ በሞተ ተስፋው መቃብር ላይ ሌላ አዲስ ተስፋ ለመለመ። የጨቅላውን ህጻን ግምባር ደጋግሞ እየሳመ ስሙን ናፖሊዮን ሲል ሰየመው።

ልጁ እግር ተክሎ ግድግዳ ይዞ መቆም ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ የአባቱ ተስፋ ይበልጥ እያንሰራራ ሄደ። የሰውነት አቋሙንና ግርማ ሞገሱን እያስተዋለ "በዚህ አስፈሪ ግርማ ሞገስ ላይ የአዕምሮ ብስለት፣ ድፍረትና ቆራጥነት ቢጨመርበት እውነተኛውን ጥቁር ናፖሊዮን ከመሆን የሚያግደው አንዳችም ምድራዊ ሃይል አይኖርም!" እያለ በኩራትና በትምክህት ብቻውን ያገሳ ጀመር።

ጥቁሩ ናፖሊዮን እያደገ በሄደ ቁጥር ዐይን አፋር፣ ቀስስተኛና ከእናቱ እግር ሥር የማይጠፋ አውደልዳይ ሆኖ ሲመለከት ግን ተስፋውን ጥርጣሬ ገባው። አሥራ ሰስት ዓመት እድሜ ሲሞላው አባቱ ተሽከርካሪ ጎማ ባለው ወንበሩ ላይ ተቀምጦ ወደ በረንዳው ይወጣና፤ ከደረጃው ላይ በዝምታ የሚቀመጠውን የልጁን ፀጉር እየደባበሰ፤ ስለ ፈረንሣይ ሪቮሊሲዮን፣ ስለ ናፖሊዮን ቦናፓርት የትግል ታሪክ፣ ፈረንሳይንና ፈረንሳዮችን ትልቅ ለማድረግ ስላደረገው ተጋድሎ ያለመታከት ይተርክለታል።

ልጁ ግን አባቱ በሚነግረው ታሪክ አይመሰጥም። ፈረንሣዊ ስለሚባል ህዝብና ናፖሊዮን ስለሚባል መሪ መስማት አይጥመውም። በምትኩ ዐይኑን ኮትኩቶና ውሃ አጠጥቶ በአሳደጋቸው አበቦች ላይ

ተከሎ፣ አባቱ በሚነግረው ታሪክ መሃል እየገባ "አባዬ፣ እስቲ ተመልከታት ያችን ቀይዋን አበባ... ልትጠወልግ እኮ ነው... ተመልከት፣ ልትረግፍ ምንም ያህል አልቀራት ። ምነው እንዳማረባት በኖረች። አታሳዝንም?!" በማለት ይጠይቅና ታሪኩን ያቋርጠዋል።

ጡረተኛው አባቱ ግን ህልሙን እውን ለማድረግ የመጨረሻ እምነቱን የጣለበት ልጁ እንዲህ ልበ ሙቅ ሆኖ ሲያገኘው፣ ሸበ ከንፈሮቹን በጥርሱ ቅርጭም አድርጎ እየነከሰ በንዴት ይንጨረጨራል።

"ሰማህ ናፒ... የሰው ልጅ በዚህ ምድር ላይ ሲኖር ህይወቱ አንድ አላማ፣ አንድ ግብ፣ አንድ ተልእኮ ሊኖራት ይገባል። እንደ ናፖሊዮን ያለ ታላቅ ሰው ታላቅ አላማውን ከግብ ለማድረስ ምን ያህል ፈተና እንደተቀበለና ምን ያህል እንደተሰቃየ ብዙ ጊዜ ነግሬሃለሁ። ዛሬ ስሙ በመላው ዓለም የገነነውን ታላቅ ሰው ግን እነኚህ ችግሮችና ፈተናዎች አልገቱትም። ችግርን በትግሉ፣ ስቃይን በብልሃት እያሸነፈ ከአላማው ጫፍ ደርሶ ነበር። ናፒ እስኪ ሳትደብቅ ንገረኝ። ችግርና ፈተናን አልፈህ እንደ ናፖሊዮን ታላቅ መሪ ለመሆን አትመኝም?!" ይልና በጥልቀት በሚያዩ ዐይኖቹ ይመረምረዋል።

"እውነቱን ንገረኝ ካልከ አባዬ፣ እኔ ሳድግ አትክልተኛ ነው የምሆነው። አበባዎቼን እንዴት እወዳቸዋለሁ መሰለህ" ናፖሊዮን እንዳቀረቀረ የልቡን ሃሣብ ይገልጻል።

"ምን መሆን እፈልጋለሁ ነው ያልከው?" የጡረተኛው ደም ስሮች ግምባሩ ላይ መፍጠጥ ይጀምራሉ።

"አትክልተኛ ነው ያልኩህ አባዬ። የምወዳት ትንሿ ግልገሌ እስከ አሁን ውሃ አላገኘችም... ውው! ዛሬስ እንዴት በደልኳት!" ብሎ በስተጓሮ ትንሿን የበግ ግልገል ወዳሰረበት ጥግ ይሮጣል። የጡረተኛው መኮንን የፈጠጡ ዐይኖች ደም ያረግዛሉ።

አንድ ጠዋት በተሽከርካሪ ወንበሩ ላይ ተቀምጦ በግቢው ውስጥ ፀሐይ ሲሞቅ፣ ልጅ እግር ሚስቱ ከብስክሌቱ ጀርባ ቆማ ፀጉሩን ቅባት እየቀባች ታብጥርለት ነበር። መኮንኑ አካለ ስንኩል እስከሆነበት ጊዜ ድረስ ካገባቸው ሚስቶች አራተኛዋና የመጨረሻዋ ነች። በእድሜዋ ወጣት በባህሪዋ ግድ የለሽ ሴት በመሆኗ ለልጁ የነበራት ፍቅር ቀዝቃዛ ነበር።



ናፖሊዮንም አካፋ ይዞ አዲስ የአበባ መትከያ ቦታ ለማዘጋጀት ከግምቡ አጥር ሥር ሲቈርፕ ሁለቱም ባሻገር ይመለከቱታል።

አባትየው የልጁን የሰውነት አቋምና እንቅስቃሴ ሲመለከት ቆየና ድንገት ሰውነቱ በንዴት ጋለ፤ ዐይኖቹ በጥላቻ ደም ለበሱ። ከንፈሮቹ እየተንቀጠቀጡና ጥርሶቹ እየተንገጫገጩም ልጁን በጩኸት ጠራው።

ናፖሊዮን ፍርሃትና ድንጋጤ ያስፈጠጣቸውን ዐይኖቹን እያቁለጨለጨ አካፋውን ይዞ ከአባቱ ፊት ቆመ። "ትሰማኛለህ አንተ መደዴ?! እነዚህን አበቦች ሁሉ በያዝከው አካፋ ጨፍጭፈህ ግቢውን ንፁህ አድርግልኝ... ፍጠን! አሁን በዐይኔ እያየሁህ!" መኮንኑ ሰማይ መሬት በሚያርድ ነጎድጓዳማ ድምጽ ጮኸበት። ልጁ የሰማውን ሊያምን አልቻለም። በትክክል ያላዳመጠው መሆኑን ለመግለጽ አፉን ሲከፍት የአባቱን ዐይኖች አስተዋላቸው። የእሣት ማዕበል በውስጣቸው ይገላበጣል፤ የዐይኑ ቆቦች ይንቀጠቀጣሉ። አፉን መልሶ ገጠመና በፍርሃት ይናጥ ጀመር።

"ቂቂቂቂቂ... ... ፈራህ እንዴ?!.... ቂቂቂቂቂ.... አበባ መቁረጥ ፈራህ እንዴ?! ሂድና ጨፍጭፋቸው ... እርባና ቢስ ተክሎችኮ ናቸው ..... ቂቂቂቂ" አለችው ልጅ እግሯ እናቱ። የምታፌዝበት መሰለው። እንደ ቆርቆሮ የሚንኳኳው ሳቋ በጆሮው እየዘለቀ ሀሊናውን ደበደበው።

በአፍታ የልቡ ምት ሲንር፣ የደሙ ሙቀት ሲጨምር ታወቀው። የዐይኑ ብርሃን መጨለም፣ እንጎሉ በጭንቅላቱ ውስጥ መሽከርከር ሲጀምር ፊቱን አዙሮ፣ አካፋውን ወድሮ ወደሚወዳቸው አበቦች አመራ። የእናቱ ሳቅ ከጀርባው ያሳድደዋል ተንደርድሮ እንደሄደ ከፊት ለፊቱ ያገኘውን የአበባ ተክል በጥሶ ጣለው ...ቂቂቂቂ ....ቂቂቂቂ .....ሁለተኛውን .....ቂቂቂቂ ....ሶስተኛውን ....ቂቂቂቂ ...አሥረኛውን .... አሥራ አራተኛውን .... ለሩብ ሰዓት ያህል በአበባው ውስጥ እየተዘዋወረ ጨፈጨፋቸው። ትእዛዙን ሲያጠናቅቅ ክንዶቹ ዝለዋል፤ ሰውነቱ በላብ ተጠምቋል፤ እንባው በጉንጮቹ ላይ ይወርዳል። እንባው እንዲታይበት ስላልፈለገ ፊቱን ወደ ግምቡ አዙሮ በለበሰው ሹራብ እጅጌ ጠራረገና አካፋውን ጥሎ አባቱ ፊት ሂዶ ቆመ።

"አሁን ደስ አለህ?! አበቦቼ ሲጠፉ፣ የምወዳቸው ጽጌረዳዎቼ ሲወድሙ ማየት ደስ አለህ?!" ሳግ በሚያፍነው የተቆራረጠ ድምጽ በድፍረት ተናገረ። ወደ ውስጥ ሊውጠው ሲታገል የነበረው እንባው ግን አሸንፎት በመፍሰስ አሳጣው።

የአባቱ ግንባር እንደተቋጠረ፣ ዐይኖቹም የእሳት ኳሶች እንደመሰሉ ናቸው። የሚንቀጠቀጡ ከንፈሮቹን በግድ አላቆ "ተወልደህ ባደከባቸው ዓመታት ውስጥ ዛሬ ገና ወንድ ልጅ ሆነህ እንደገና ተፈጥረሃል። የህይወት ዋነኛ አላማ መኖር ነው! ትልቅ ሰው ሆኖ መኖር። ትልቅ ሰው ሆነህ ለመኖር በምትጀምረው የመጀመሪያ እርምጃ ትልቅ እንቅፋት ከሚሆኑብህ አንዱ ውበት ነው፤ የተፈጥሮ ውበት፣ የሴት ልጅ ውበት፣ የሁሉም ነገር ውበት። ሰው ሆነህ መኖር ከወሰንክ ነገ በወጥመዱ ጠልፎ ለሚጥልህ ውበት አትዘንለት። ናቀው! አጥፋው... ናፖሊዮን በናፖርት ታላቅ የሆነው..." የናፖሊዮን ጆሮ ማድመጥ ያቆማል።

"ሂድና ጠቦትህን ይዘሃት ና!" አለ መኮንኑ በጩኸት። ናፖሊዮን አንዳች የኤሌትሪክ ሞገድ ከእርግብግቢቱ እስከ እግር ጥፍሩ ነዝሮት አለፈ።

"ለምን?" ብሎ ሊጠይቅ አሰበና የአባቱን ፊት ቀና ብሎ ሲመለከት እንደ እሳት ለበለበው። ካለበት ቦታ ሳይንቀሳቀስ ሀውልት መስሎ ቆመ። "ግልገሏን አምጣት እኮ ነው ያልኩህ!" የኮሎኔሉ ጩኸት ናፖሊዮንን አንቀጠቀጠው።

"ቂቂቂቂ ..... ቂቂቂቂ .....ምን ይገትርሃል!..... ቂቂቂቂ.... ፈርቶ ነው" አለች እናቱ በአሽሟጣጭ ዐይኖቿ እየገሸላለጠችው። ናፖሊዮን ከዚያ በላይ መቆም አልቻለም። እንዳቀረቀረ ወደጠቦቷ መዋያ ሄደና በታሰረችበት ገመድ እየጎተተ አመጣት።

"እራሱንም እግሮቿን ጥፍር አድርግና እሠራት!" አለ መኮንኑ። ናፖሊዮን ቀና ብሎ አላየውም፤ የታዘዘውን ለመፈጸም ጠቦቷ እግር ሥር ተንበረከከ። እናቱ እየተጣደፈች ወደ ምግብ ማብሰያው ሮጠች።

ጠቦቷ ዐይኖቿን እያንከራተተች አንገቷን አንገቱ ሥር እየሸጎጠች ትታከከው ጀመር። ገና ባልጎረነነው፣ እንደ ጥጥ በሚለሰልሰው ድምጿ ባአአአአአ ..... እያለች የተሸበረውን መንፈሱን ጭራሽ ምስቅልቅሉን አወጣችው። አራት እግሮቿን ግጥም አድርጎ ሲያስራት ሚዛኗን መጠበቅ ባለመቻሏ ዘፍ ብላ ወደቀችና እግሮቿን እያንፈራገጠች መልሳ ለመቆም ተፍገመገመች - አልሆንላትም።

እየጮኸች እርዳታውን ተማፀነች። ከሚበላው እያበላ፣ ከሚጠጣው እያጠጣ ያሳደጋት የመጀመሪያ ጓደኛውን በዚህ አሳዛኝ



ሁኔታ ውስጥ ሲያያት ፈትቶ ሊለቃት አሰበና ቀና ብሎ የአባቱን ፊት አስተዋለ። የሰው ልጅ ጠይም ቆዳ እንደዚያ በአፍታ ጥቁር እንዣ መምሰል መቻሉን ያየው የዚያን እለት ነው። ሃሳቡን ትቶ ካጎነበሰበት ቀና አለ።

እናቱ ስለቱ የሚያብረቀርቅ ትልቅ ቢላዋ ይዛ አጠገቡ ቆማለች "ናፖሊዮን! የዚችን ጠቦት አንገት እንደ ጎመን ቀንጥሰህ ጣለው! አሁን!" የመኮንኑ ድምጽ እንደፈንጂ ጮኸ። ናፖሊዮን ግምባሩን ቋጥር አድርጎ በፀጥታ አስተዋለው።

"ቂቂቂቂ .... እንካ ቢላዋውን፣ ምን ገተረህ?... ቂቂቂ" ናፖሊዮን ቀና ብሎ አስተዋላት።

"ተቀበላት!"

ናፖሊዮን ከቆመበት አልተንቀሳቀሰም። "ምንድነው የምትጠብቀው?!" መኮንኑ የመቀመጫውን ጎማዎች በእጁ እየገፋ ጥቂት ተጠጋው።

"ቂቂቂቂ .... ፈራህ እንዴ?! የበግ ጠቦት እኮ ታርዳ እንድትበላ የተፈረደባት እንስሳ ነች.... ቂቂቂቂ...." አለች እናቱ ቢላዋውን እያስጠጋችለት።

"የለም.... በግ ጓደኛዬ ነች!" አለ ናፖሊዮን በጭንቅ ባፈናጠራቸው ቃላት።

"ናፖሊዮን!"

"ቂቂቂቂቂቂ ...."

"ናፖሊዮን!"

"ቂቂቂቂቂቂ ..."

ናፖሊዮን በጭንቅላቱ ውስጥ ፈንጂ ሲፈነዳ፣ ጉንዳን የመሰለ ነገር ሲርመሰመስበት ተሰማው። በዳበሳ እጁን ዘርግቶ ቢላዋውን ተቀበለና አባቱን አፍጥጦ ተመለከተው - የተራበ ተኩላ ይመስላል። እናቱን አስተዋላት፤ ትስቃለች - ላባዋን ነቅላ እርቃኗን የቀረች አሞራ መስላችው።

ቢላዋውን እንደያዘ በርከክ አለ። ከበጓ ዐይኖች ጋር ዐይኖቹ ሲጋጩ ሰውነቱ ሽምቅቅ አለና ዐይኖቹ ተጨፈኑ ባእእእእ... ባእእ... ባእእ ...ባእ። ጥቂት ዘግይቶ የእጁን መዳፍ ለብ ያለ ነገር ሞቀው። ዐይኖቹን ገልጦ መዳፉን ዘርግቶ አስተዋለ። ላቦቱ ሸቅብ የሚተን ትኩስ ደም! የጠቦቷ ጓደኛው ደም!.... ቢላዋውን ጥሎ ስቅስቅ ብሎ አለቀሰና ሲበቃው ተነስቶ ቆመ።

ዐይኖቹ ላይ ያረፈው ሃይለኛ የፀሐይ ብርሃን ያጥበረብረዋል "አሁን ደስ አለህ? በጓደኛዬ ሞት ደስ አለህ?!" አለው አባቱን። ጡረተኛው መኮንን አልመለሰለትም። ለረዥም ጊዜ በፀጥታ ሲመለከተው ቆይቶ ፈገግ አለ። ከጠቆረው የፊቱ ቆዳ ላይ የረጋው ደም ተገፏልI ዐይኖቹም እየጠሩ ነውI ከንፈሮቹም መንቀጥቀጣቸውን አቁመዋል።

"ጓደኛዬ ነው ያልከኝ ናፒ?! ትልቅ ሰው ለመሆን የመጀመሪያውን እርምጃ ስትራመድ መሰናክል የሚሆኑብህ ጠላቶችህ ብቻ ሣይሆኑ ከጎንህ ያሉ ወዳጆችህ ጓደኞችህም ጭምር ናቸው። ለማንም ለምንም እጆችህ እንዳይራሩ ተጠንቀቅ። ናፖሊዮን ቦናፖርት ታላቅ የሆነው..."

ናፖሊዮን ደንዝዞ ካለበት እንደቆመ አባቱ የብስክሌቱን ጎማ በእጆቹ እያሽከረከረ ቀረበውና ዝቅ ባለ ድምፅ "ናፒ..... አንድ ቀን ይች ሀገር ናፖሊዮንን የመሰለ ጀግና፣ ቆራጥና ብልህ ሰው ትፈልጋለች። ያ ጀግና ደግሞ አንተ ነህ! ይቅናህ!" አለው።

አላዳመጠውም። የአባቱን ዐይኖች ላለማየት፣ የእናቱን ድምጽ ላለመስማት፣ እግሮቿ ተጠፍረው ለዘለዓለሙ ያንቀላፉቻውን ጠቦት ላለማየት፣ የጨፈጨፋቸውን አበቦች ላለማየት ወዴት እንደሚሸሽ ያሰላስል ነበር።

እየሮጠ ወደ ቤቱ ጀርባ ሄደና ያረጁ እቃዎች የሚጠራቀሙበት አንድ ክፍል ውስጥ በመግባት ተደበቀ። ክፍሉ ውስጥ እንዲትም የብርሃን ፍንጣቂ አትገባም። በጨለማው ውስጥ ለረዥም ጊዜ እንዳፈጠጠ የተቅበዘበዘው መንፈሱ እፎይታ አገኘ። ከዚያች ቀን በኋላ ያችን ክፍል አዘውተራት። ብዙውን ጊዜውን የሚያሳልፈው በዚያ ጨለማ ውስጥ በማፍጠጥ ሆነ ። በጨለማ ፍቅር የተለከፈው ከዚያች እለት ጀምሮ ነው።

በሌላ ወቅት አባቱ የሚወዳትን ድመት በመጥረቢያ አንገቷን በጥሶ ጣላት። ተመስገኑ እንጂ አልተወቀሰም። ከዚያ በኋላ ባሉት ዓመታት የዶሮ አንገት ጠምዝዞ መግደል ተማረI የውሾችን ጭራ መቁረጥ፣ በወንጭፍ ጠጠር የወፎችንና የዋኖሶችን ደረት መንደል ለመደ። እየጎረመሰ ሲሄድም ከእኩዮቹ ጋር በቦቅስ መቀጣቀጡን ሥራዬ ብሎ ተያያዘው።



ጡረተኛው መኮንንም በልጁ ተግባር በመደሰትና በመኩራራት እንዲገፋበት ያበረታታው ጀመር። ጥርጣሬ ላይ የነበረ ተስፋውም እንሰራራ። የጥረቱን ውጤት ለማየት ግን አልታደለም። የልጁን "ታላቅ" ሰውነት ከማየቱ በፊት ሞት ቀደመው።

በትምክህት የተመረዘው የናፖሊዮን ጭንቅላትም ቀለም አልይዝ በማለቱ በየዓመቱ እየተንጠለጠለ ከክፍል ክፍል ማለፍ ልምዱ ሆነ። በየገባበት ክፍል ከተማሪዎች ጋር መጣላት፣ ከመምህራን ጋር መጋጨት የማይለወጥ ፀባዩ ስለሆነ የትምህርት ቤት ህይወቱን በብቸኝነት የታጠረ እንዲሆን አደረገው።

አሥረኛ ክፍል ሲደርስ የዓመቱ አጠቃላይ ትምህርት የፈተና ውጤት በተገለፀበት ቀንም ከሚጠላው ትምህርት እስከመጨረሻው ተሰያየ። ተማሪዎቹ መማሪያ ክፍላቸው ውስጥ ተቀምጠው የመምህራቸውን መምጣት ሲጠባበቁ መምህሩ ሪፖርት ካርዶቻቸውን ታቅፈው ገቡና ተማሪዎቹን "ሁላችሁም ለታላቁ ናፖሊዮን አንድ ጊዜ አጨብጭቡለት!" አሉ

ግራ የገባቸው ተማሪዎች ክፍሉን በጭብጨባ ነቀነቁት። መምህሩም የያዙዋቸውን የውጤት ካርዶች ጠረጴዛው ላይ አስቀምጠው የናፖሊዮንን ካርድ መዘው አወጡ። ካርዱን ከፍ አድርገው ለተማሪዎች እያሳዩም "ታላቁ ናፖሊዮን ከሀምሣ ሶስት ተማሪዎች ሀምሣ ሶስተኛ ወጥቷል!" አሉ። ክፍሉ በሳቅ ታመሰ።

ናፖሊዮን በዝግታ ተነሳና ወደ መምህሩ ተራመደ። የተማሪዎቹ ሳቅና ጭብጨባ አስታጋባ። ከመምህሩ እጅ ካርዱን ተቀበለና ብጥስጥሱን አውጥቶ አስተማሪው ፊት ላይ ወረወረው። መምህሩ ከተወረወረባቸው ወረቀት ለማምለጥ አንገታቸውን ቀና ሲያደርጉ የናፖሊዮን ፈጣን ቡጢ ደጋግሞ አገኛቸው። በሲጋራ የበሰበሱ ጥርሶቻቸውን አፍልሶና ደም በደም አድርጓቸው በሩን ከፍቶ በመውጣት በአጥር ዘሎ አመለጠ። እቤቱ እንደደረሰም ወደዚያች ጨለማ ክፍል ሂዶ ለረዥም ሰዓት ተቀመጠ። ከዚያች እለት በኋላ ወደ ትምህርት አለም ዳግመኛ አልተመለሰም።

በዓመቱ ውትድርና ተቀጠረ። ከዚያም በአየር ወለድ ሠራዊት ውስጥ ለአምስት ዓመት አገለገለ። በሥነ - ሥርዓት ጉድለት እንደተቀጣና እንደታሠረI በምግባረ ብልሹነቱ እንደተወቀሰI በኤርትራ ግንባር በተደረገ ጦርነት ቆሰለ። ህክምና ተደርጎለት ከጊዜም በኋላ እንደገና ወደ ግንባር ተላከ። ናፖሊዮን ግን ከረን ላይ በተደረገ አንድ ጦርነት ተካፍሎ ውጊያው ከማለቁ በፊት ወደ አስመራ ኮበለለ።

ከአስመራ ወደ አዲስ አበባ ገሥገሠ። የአየር ወለድ ሠራዊት ስለ ናፖሊዮን የሚያውቀው ነገር ቢኖር በከረን ግንባር መሞቱን ነው።

ሠራዊቱን ከድቶ ወደ ቤቱ ሲመለስም እናቱ መኖሪያ ቤታቸው የሆነውን ትልቅ ቪላ የመጠጥ መቸርቸሪያ አድርጋ ጠበቀችው። ከዚያ በኋላ በመካከላቸው የተፈጠረው ውዝግብ የከረረ ነበር። የዘመድ ሽማግሌዎች ጣልቃ ገብተው ነገሩን በጊዜ ባያበርዱትና ባያስማሟቸው ኖሮ፣ ምናልባትም የናፖሊዮን ጭካኔ ሰለባዎች ከሚሆኑት አንዷ የገዛ እናቱ ነበረች። በስምምነቱ መሠረት ናፖሊዮን ቤቱን ለቆ እንዲወጣላት እርሷም በየወሩ የተወሰነ ገንዘብ እንድትቆርጥለት ሆኖ በዚሁ ተለያዩ።

ሥራ-ፈት ሆኖ በቆየባቸው ዓመታት አብዛኛውን ጊዜውን የሚያሳልፈው ፊልም ቤቶች ውስጥ ነበር - በሁለት ምክንያቶች ። ጨለማዎቹ የፊልም ቤት አዳራሾች ከሚጠላውና ከሚፈራው ብርሃን ይገላግሉታል። እየመረጠ ከሚያያቸው ፊልሞች ደግሞ ከፍተኛ ወንጀሎች እንዴት እንደሚወጠኑ፣ እንደሚቀነባበሩና እንደሚፈጸሙ ያጠናባቸዋል። ቀልቡ ጀብድ በተሞላባቸው ወንጀሎች አፈጻጸም ተማረከ።

ምኞቱ እንዲሞላለትም እድል ከጎኑ ቆመች። በ "አብነት አስመጪና ላኪ ድርጅት" ውስጥ በሾፌርነት ተቀጠረ። ችሎታውንና ልበ-ሙሉነቱን ያረጋገጡት የድርጅቱ ባለንብረትም በትክክለኛው የሥራ ቦታ ላይ መደቡት። አሁንም በጨለማው ክፍል ውስጥ እንደተቀመጠ ያስባል። ሲያልመው የኖረው ታላቅ ጀብድ የሚሠራበት ጊዜ እየቀረበ መምጣቱን ደመ-ነፍስ እንደነገረው ሁሉ ከተቀመጠበት ተነስቶ የታጠቀውን ሽጉጥ በማውጣት ይወለውለው ጀመር፤ እያፏጨ።



## ምዕራፍ አሥራ ስድስት

ጠበቃው አቦሳ አንድ ሣምንት ከቆየ በኋላ ተመልሷል። ድል የሚያቀዳጀውን ቁልፍ ለመጨበጥ ግን ገና ብዙ ይቀረዋል። ሆኖም አሁንም ተስፋ አልቆረጠም - ገና ብዙ ሊሮጥ ወስኗል።

ከጉዞው ባገኘው አጠቃላይ ውጤት ናፖሊዮን ከነገረው ውስጥ አብዛኛው ድርጊት በትክክል መፈጸሙን፤ ቆዮ-ታዋ ለከፍተኛ ፖሊሳዊ የቴክኒክ ምርመራ ወደ አዲስ አበባ ተልካ ወንጀል ምርመራ ጽ/ቤት ቅጥር ግቢ ውስጥ መገኘቷን፤ የቆሰለው የፊናንስ ፖሊስም ለህክምና ወደ ዳግማዊ ምኒሊክ ሆስፒታል መምጣቱን አረጋግጧል።

ወደ አዲስ አበባ ተቻኩሎ የመጣውም ከማንም በፊት ቆሰለ የተባለውን ፖሊስ ለማግኘት ነው። በርግጥ ሰነዱ በእጁ ይኖር? የሚለው ጥያቄ ጭንቅላቱን ሊፈነዳ የተቃረበ እስኪመስለው ድረስ ሲበጠብጠው ቆይቷል።

ንጋት ላይ ማልዶ ነቃና መታጠቢያ ቤቱ ገብቶ ሰውነቱን ተለቃለቀ። በረዥሙ ፎጣው እንደተጠቀለለ መታጠቢያ ቤቱ መስተዋት ውስጥ ፊቱን ተመለከተ። በጥልቀት የሚያስተውሉት ብልጣ ብልጥ ዐይኖቹ የታከቱ ይመስላሉ፤ ያልተላጨው ጢሙ ፊቱን ይኮሰኩሰዋል፤ ወዛማ የነበረ የፊቱ ቆዳ ገርጥቷል። ጢሙን ለመላጨት አሰበና ዛሬ የሚሮጥበት ጉዳይ ምን ያህል አጣዳፊ እንደሆነ ሲያስታውስ የመታጠቢያ ቤቱን በር በፍጥነት ከፍቶ ወደ መኝታ ቤቱ ሮጠ።

ልብሱን ለባብሶ እንደጨረሰ ሠራተኛው ካቀረበችለት ቁርስ ጋር የተዘጋጀለትን ሻይ ጥቂት አልኮል ጨምሮ ጨለጠና የመኪናውን ቁልፍ እያሽከረከረ ተጣድፎ ወጣ።

የመኪናዋን ነዳጅ መስጫ በሀይል ረግጦ፤ በጥሩንባው መንገደኛውን እያስበረገገ ባለመኪናዎቹን እያሸማቀቀ፣ የትራፊክ መብራት እንዳያዘገየው እያቆራረጠ ንፋስ ስልክ ከሚገኘው መኖሪያ ቤቱ ዳግማዊ ምኒልክ ሆስፒታል ለመድረስ የፈጀበት ጊዜ በጣም አጭር ነበረ።

እንደደረሰ መኪናዋን ሆስፒታሉ በር ላይ አቁሞ ወደ ውስጥ ዘለቀ። በጠዋት የሰው አይነት ግቢው ውስጥ ይርመሰመሳል። በምርኩዝ ድጋፍ የሚሄዱ፣ በተሽከርካሪ ወንበሮች የሚገፉ ቁስለኞች፣

ያልግጸረዋ የሚለሉ በሽተኞች፣ በጋቢያቸው ተጠቅልለው ካርድ ለማውጣት የተኮለኮሉ ህሙማን፣ ስንቅ የያዙ ጠያቂዎች ፣ በየበሩ ላይ የቆሙ አስታማሚዎች ከወዲያ ወዲህ ውር ውር የሚሉ ነርሶች፣ በየመተላለፊያው ላይ አጭር ቆመጥ ይዘው ደረታቸውን እንደነፉ የቆሙ ዘቦች... ማንን ከማን እንደሚለይ፣ ማንን እንደሚያነጋገር ግራ ገብቶት ሲጋራውን ለኩሶ ማሰብ ጀመረ። የፖሊሱ ስም ተካልኝ ባልቻ ይባላል። የሰውነት አቋሙና የገጽታውን ምስል ከናፖሊዮን ተረድቷል። ግን ከዚህ ሁሉ ህዝብ መሃል እንዴት ፈልጎ ያገኘዋል?! ሆስፒታሎች ለምን የመረጃ ማዕከል እንደማይኖራቸው ራሱን ጠየቀና የሀገሪቱን ድህነትና ኋላ ቀርነት ረገመ። በሀሳቡ እንደተዋጠ ዐይኖቹን ከወዲህ ወዲያ እያማተረ አካባቢውን ሲያጠና፣ የተሸከርካሪ ወንበሩን ጎማ በገዛ እጆቹ የሚያሽከረክር አንድ ቁስለኛ ወደርሱ ቀርቦ በጣቱ የሚያሻትን ሲጋራ እያሳየ "እባክዎን እሳት ይሰጡኝ?" ሲል ጠየቀው።

ጠበቃው በፍጥነት ከኪሱ ላይተር አውጥቶ ሲጋራውን አቀጣጠለለትና በፈገግታ እያባበለው "እ ... እባክህን የኔ ወንድም ሰው ብጠይቅህ ልታፋልገኝ ትችላለህ?..." አለው።

"የማውቀው ከሆነ ምን ገዶኝ ጌታዬ" አለ ልጅ እግሩ ቁስለኛ የለኮሰውን ሲጋራ ደጋግሞ እየሳበ።

"ተካልኝ ባልቻ ይባላል....የፊናንስ ፖሊስ ነው። በጥይት ተመቶ ባለፈው ሳምንት ነው ለህክምና ወደዚህ የተላከው..."

ቁስለኛው ሲጋራውን እየማገ ዐይኖቹን ጠበቃው ላይ ተክሎ ሲያስብ ቆየና "ኧረ አላውቀውም... ስንቱ ይታወቃል ብለው ነው። በየቀኑ ከየግንባሩ የሚገባው ቁስለኛ ሥፍር ቁጥር የለውም... የሚሞተውም የዚያኑ ያህል ነው..."

"አአ... ኧረ ይሄ የሚሞት አይደለም"

"እንዴ?! ከብረት ነው እንዴ የተሠራው? ኧረ ዛሬስ ጉድ ሰማሁኝ! ምነው ጌታው? ደግሞ በእግዚአብሔር ሥራ ገቡተው"

"እግሩን ስለተመታ ለሞት አያደርሰውም ለማለት ፈልጌ እኮ ነው"

"ኧረ እንዲህ አይበሉ ጌታው! ሱፉን ለብሶ በከራባቱ እንደታነቀ ሲቆናጠር እዚህ ግቢ ገብቶ ሬሳው በወሳንሳ እየተጎተተ የሚወጣውን ስንቱን አይተናል"



ጠበቃው የራሱን አለባበስ ከታች ወደላይ በመቃኘት ቁስለኛው ሞት የተመኘለት ስለመሰለው ቅር ተሰኘ። "እና... አታውቀውም ማለት ነው?"

"አላውቀውም"

"ታዲያ እንዴት ላገኘው እችላለሁ?"

ቁስለኛው ሲያስብ ቆየና "ቆይ እስኪ.... እዚህ ግቢ አንድ ከተፎ አለ፣ መቼም እርሱ የማያውቀው ቁስለኛ አለ ማለት ዘበት ነው። ምናምን ካነረሱት መንጥቆ እንደሚያወጣው እርግጠኛ ነኝ" አለ በዐይኖቹ ከተፎውን እየፈለገ።

"ኧረ ችግር የለም። ይሄማ እዳው ገብስ ነው። እባክህ እርዳኝ የኔ ወንድም" አለና በኪሱ የያዘውን የሲጋራ ፓኮ አውጥቶ ጭኑ ላይ አስቀመጠለት።

ቁስለኛው በሰስት ዐይኑ ጭኑ ላይ የተቀመጠውን ፖኮ አየት አድርጎ ፒጃማው የደረት ኪስ ውስጥ ከተተ። "ይቆዩ... አንዴ፣ እዚህ ይቆዩ፣ ጌታዬ" ብሎት የተሽከርካሪውን ወንበር ጎማ በፍጥነት እያሽከረከረ ጥሎት ሄደ።

ብዙ ቆይቶ አንድ ልጅ እግር ቁስለኛ አስከትሎ ተመለሰ። ሉጫ ፀጉሩ ግምባሩ ላይ ወድቋል። የለበሰው የሆስፒታሉ ስም የተፃፈበት ሰፊ ፒጃማ ቀጭን ሰውነቱን ባዶ ጆንያ ውስጥ የቆመ ከዘራ አስመስሎታል። በብልጣብልጥ ዐይኖቹ ጠበቃውን ከላይ እስከታች እየደባበሰ ፈገግታ አሳየው።

"ልጁ ይሄ ነው፣ ጌታዬ። የቁስለኛውን ስም ማን ነበር ያሉኝ?" አለ የሲጋራ ዳረጎት የተጣለለት ቁስለኛ።

"ተካልኝ ባልቻ፣ የፊናንስ ፖሊስ ነው። እግሩን በጥይት ተመቶ ባለፈው ሳምንት ከአሰላ የመጣ..." እያለ ለአዲስ መጪው ያስተነትንለት ገባ ጠበቃው።

ፀጉረ ሉጫው ቁስለኛ ግምባሩን ቋጥሮ ዐይኖቹን መሬት ላይ ተክሎ ሲያስብ ቆየ። የጠበቃውም ልብ በፍጥነት መምታት ጀመረ።

"ትዝ አይለኝም፣ ከፊናንስ ፖሊስ?"

"አዎን አሰላ የነበረ..."

"እንጃ ትዝ አልልህ አለኝ። ፈቃደኛ ከሆኑ ቁስለኞች ባሉባቸው ክፍሎች እየተዘዋወርኩ ልጠይቅልዎ" አለ ሉጫው ።

"እባክሀ?"

"ይጠብቁኝ" አለና በምርኩዝ እንጥር እንጥር እያለ ከአጠገቡ ተሰወረ።

ከሩጫው እንደገመተው ይሄ ከምላጭ ስለት የተባ ቁስለኛ ፖሊሱ የተኛበትን ክፍል እንደማያጣው እርግጠኛ ነው። የሲጋራ ድርጎ ያገኘው ቁስለኛ ጠበቃውን አመስግኖ ተሽከርካሪ ወንበሩን እየገፋ ሄደ።

ጠበቃው እጆቹን ኪሶቹ ውስጥ ከቶ እየተንጎራደደ ለረዥም ጊዜ በትእግስት ጠበቀ። መታገስማ ግዴታው ነው። በምድር ላይ ከገንዘብ ቀጥሎ ነፍሱን የሚያማልሉት የአብነት ዐይኖች ሲንቦገቦጉ ታዩት። "የአብነት እስመጭና ላኪ ድርጅት" የመጨረሻዋ ሰባራ ሳንቲም ሳትቀር በእጁ ስትገባ እንደ ሰመመን ታየውና ምራቁን ደጋግሞ ዋጠ። ብቻ ይሄ መዘዘኛ ሰነድ እጁ ይግባ።

ከብዙ ቆይታ በኋላ ሉጫው ደግሞ ሌላ ቁስለኛ አስከትሎ መጣ። የጠበቃው ትንፋሽ ሊቆም ምንም አልቀረውም። የሰውየውን ቁመናና ገጽታ ናፖሊዮን ከሰጠው መረጃ ጋር ሲያመዛዝነው ግን በምንም አይገናኙም፤ ሉጫው አጠገቡ ከመድረሱ "አገኘኸው?" ሲል በጥያቄ አጣደፈው። "እርሱ ወንድሜ እንደሚነግረኝ ህክምናውን ጨርሶ ትላንትና ከሆስፒታል ወጥቷል" አለ ወደ አዲሱ ቁስለኛ በአገጩ እያመለከተ።

ጠበቃው የናቱን ሞት ያረዱት ያህል ገጽታው ጨፈገገ። የሰማውን ባለማመን ጆሮዎቹን እየተጠራጠረ "መቼ ወጣ አልከኝ?" አለው አዲስ መጪውን።

"ትላንት ጠዋት ተሰናብቶን ወጣ፤ ቁስሉ እጅግም ነበር። ሥጋው ውስጥ የቀረችው ጥይት ወጥታለት ቁስሉ መጥገግ እንደጀመረ እቤቴ ተኝቼ እገግማለሁ ብሎ በራሱ ጥያቄ ወጣ" አለ እንደተከዘ። "ዘመዱ - ነዎት?"

"አዎን፤ ሰውዬው እርሱ ለመሆን እርግጠኛ ነህ?"

"ተካልኝ ባልቻ አይደለም ያሉት? አሰሳ ላይ በጥይት የተመታው?! እዚሁ ተዋውቀን ጓደኞች ሆነን ነበር ... እንዴት ያለ ማለፊያ ሰው መሰለዎት። እዚሁ አዲስ አበባ ሚስትና ልጆችም አሉት"

የጠበቃው ልብ ፍጥነቱን ጨመረ። "አድራሻውን ሰጥቶሃል? እባክህን ለብዙ ጊዜ የተለየሁት ወንድሜ ስለሆነ ወደ ምድብ ሥራው ተመልሶ ከመሄዱ በፊት ዐይኑን እንዳየው ፈልጌ ነው..."



"እረ አልነገረኝም። ብቻ በጨዋታ የተነሳ የሚኖረው ራጉኤል ቤተክርስቲያን አካባቢ መሆኑን አጫውቶኛል" አለ እንደ መሰልቸት ብሉ።

የጠበቃው ተስፋ በውስጡ መሞት ጀመረ። ራጉኤል! በዚያ ሰው እንደ ቅጫጭ በሚርመሰመስበት መንደር ፖሊሱን ፈልጎ ማግኘት ዘበት መሆኑን ሲረዳ ጠማማ እድሉን እየረገመ በረዥሙ ተነፈሰ።

"በተመላላሽ ሊታከም ይመጣል ብለህ ትገምታለህ?"

"አይመስለኝም። ቁስሉ እኮ ሽሯል"

ጠበቃው ከደረት ኪሱ ብጣሽ ወረቀትና ብዕር አውጥቶ ስሙንና የስልክ ቁጥሩን ከጻፈ በኋላ አጣጠፈና ሰጠው። "ምናልባት ተመልሶ ከመጣ በዚህ አድራሻ እንዲደውልልኝ ንገረው"

"እሺ ምን ገዶኝ" አለ ቁስለኛው የጠበቃውን አድራሻ እያነበበ። ጠበቃው አሥር ብር አውጥቶ ከሉጫው ጋር ተካፍለው ሻይ እንዲጠጡበት ከሰጣቸው በኋላ ወደ መዝገብ ቤት አመራ። የጠበቃነት ሙያው ሁሉን የሚጠራጠር ቆቅ አድርጎ ቀርጾታል። ያገኘውን መረጃ ሙሉ በሙሉ አልተቀበለውም። ይሁንና የመዝገብ ቤቱ ቻርትም ፖሊሱ በትላንትናው ዕለት መውጣቱን አረዳው። ጠበቃው በጥልቅ ሃሣብ እንደተዋጠ የሆስፒታሉን ቅጥር ግቢ ለቆ ወጣ።

እያከነፈ የወሰዳትን መኪና ራጉኤል ቤተክርስቲያን አካባቢ አቆመና እግሩ ወዳመራው መንደር ቁልቁን እያሽከረከረ ገባ። የጠላ ቤት ማስታወቂያ ጣሳ ብዛት፤ የሻይ ቤት፤ የጠጅ ቤት ጋጋታ... ዝንብ የወረራቸው ህፃናት "አይ አዲስ አበባ!" ይላል እየደጋገመ።

በየደረሰበት ያገኘውን ሁሉ የሚጠይቀው ጥያቄ "ተካልኝ ባልቻ የተባለ ፖሊስ ... አሰሳ ላይ እግሩን በጥይት ተመቶ ወደ አዲስ አበባ የመጣ" በማለት ነበር። ሁሉም የሚሰጡት መልስ ደግሞ እንደተማከሩ ዐይነት አንድ ነው። የአለባበሱን ማራኪነትና የሚያንፀባርቀውን ጫማውን እያስተዋሉ "እረ እናውቅም" ይሉታል።

በየጉራንጉሩ እየተሹለከለከ ወዳገኘው ቀበሌ ጽ/ቤት ጎራ በማለት አጠያየቀ፤ እናውቃለን የሚል ግን የለም። ግምባሩ ላይ የሚንቆረቆረውን ላብ በመሀረቡ እየጠራረገ ቁና ቁና እየተነፈሰ መኪናውን ወዳቆመበት ተመለሰ። የመኪናዋ የፊትና የኋላ መብራት መስታዎቶችና የፍሬቻ መብራቶች ተሰርቀዋል።

በቁጣ እየነደደ ፀጉሩን መንጨት ጀመረ። "ጭራቅ ህዝብ!" እያለም የመኪናዋን ኮፈን በቡጢ ይቀጠቅጥ ገባ። ተላላፊ መንገደኞችም መኪናዋንና እርሱን ከበቧቸው። ጠብቃው ይለፈልፋል፤ አንዳንዱ ያዝናል ሌላው "ያጣ ካለው ቢነጥቅ ምን ሀጢያት አለው" እያለ ፍርዱን ይሰጣል። በመሀል አንድ ጎልማሳ ጠበቃውን ቀረብ ብሎ "የኔ ወንድም፣ እዚህ አካባቢ የሰው ዐይን የተገጠመው በብሎን ቢሆን ኖሮ ሰውዬው ሳያንቀላፉ ዐይኑን ፈተው የሚሸጡ ወረበሎች ያሉበት መንደር ስለሆነ ለተረፈው ንብረትህ እግዚአብሔርን አመስግነህ ብትሄድ ጥሩ ነው" ሲል መከረው።

ጠበቃው የመኪናዋን ሞተር ቀስቅሶ የከበበውን ህዝብ በጥሩንባው እያስበረገገ ያን የምድር ሲኦል የመሰለ አካባቢ ጥሎ ተፈተለከ። ከመጣበት አብይ ጉዳይ ጋር ሲያመዛዝነው የመኪናዋ መብራቶች መሰረቃቸው ከቁጥር ውስጥ የማይገባ በመሆኑ መልሶ ራሱን ማጽናናት ያዘ። እንዲያም ሆኖ እድል ለመጨረሻ ጊዜ በሩን የቀረቀረችበት መሰለው። ህሊናው ግን በርካታ የጥርጣሬ ጥያቄዎች እየወለደ ተስፋ እንዳይቆርጥ ያጃግነዋል። ሰነዱ በፖሊሱ እጅ ባይኖርስ? በደህንነቶች ወይም በወንጀል ምርመራ ፖሊሶች እጅ ገብቶ ቢሆንስ? ምናልባት በናፖሊዮን አምባው እጅ ቢሆንስ? ግን ለምን?

መሣሪያ ጭና የተያዘችው ቶዮታ ፒክ አፕ በአዲስ አበባ ወንጀል ምርመራ ፖሊስ ጽ/ቤት እንደምትገኝ አስታወሰና ማሰብ ጀመረ። የምርመራ ክፍል ሹም የሆነውን ሻምበል መብራቴን ያውቀዋል። ግን በዚህ ጉዳይ ላይ ምን ሊያነጋግረው ይችላል? ናፖሊዮን እንዳለው ጭራሽ ፖሊሶች ፈለጋቸውን እያነፈነፉ ማጅራታቸውን እንዲጨመድዱ ጊዜውን አያፋጥንም?

ጊዮርጊስ ላይ ከምኒሊክ አደባባይ ትይዩ መኪናዋን አቁሞ ከሱቅ በደረቴ ሙሉ ዊንስተን ሲጋራ ከገዛ በኋላ እያስጨሰ ማሰብ ጀመረ። የረሃብ ስሜት ይሰማዋል፤ በመንገድ የደከመ ሰውነቱ ጭራሹን ዝሏል፤ አዕምሮው ግን ሥራ አልፈታም። ብዙ ሲያወጣና ሲያወርድ ቆይቶ የመኪናውን ሞተር ቀሰቀሰና ወደ ወንጀል ምርመራ ጽ/ቤት ተፈተለከ።

መኪናውን ከቅጥር ግቢው አርቆ ካቆመ በኋላም ሻምበሉን ለማነጋገር እንደሚፈልግ አስረድቶና ተፈትሾ ገባ። ግቢው ውስጥ በአንድ ጥግ ቶዮታ ፒክ አፕ መኪና ቆማለች። ጠበቃው ትንፋሹን ውጦ ሰረቅ አድርጎ ታርጋዋን ተመለከተ - ናፖሊዮን የሰጠው ታርጋ ቁጥር ነው! አንዳች የሽብር ስሜት ሰውነቱን እየወረረው የሻምበሉ ቢሮ ወደሚገኝበት ባለ አንድ ፎቅ አሮጌ ህንፃ በጣውላ የተሠራውን ደረጃ



እያንሳጠጠ ወጣ። ልቡ በፍጥነት ይመታል፤ እጆቹ መንቀጥቀጥ ጀምረዋል። "ወዴት ነው ጓድ!" የሚል ድምፅ ሲሰማ ቀጥ ብሎ ቆመ። ሻምበሉ በር ላይ የቆመ ፖሊስ ነበር።

"ሻምበል መብራቴን ፈልጌ ነበር ጓድ"

"ለሥራ ጉዳይ ወጥተዋል። ቀጠሮ አለዎት?"

"የለኝም፤ ይመለስ ይሆን?"

"እስኪ ከሰዓት በኋላ ይሞክሩ"

ጠበቃው ሰዓቱን ተመለከተ። 5:30 ሰዓት ይላል። ፖሊሱን አመስግኖ እያንሳጠጠ በወጣበት ደረጃ ወረደ። ከግቢው ሲወጣ ዳግመኛ ቶዮታዋን ሰረቅ አድርጎ ተመለከታት፤ የፊት መስተዋቷ በጥይት ተበሳስቷል። በድካም የዛለ አካሉና ያለ እረፍት ሲያስብ የሰነበተ አእምሮው በመድከሙ ባለችው ትንሽ ሰዓት ለማንቀላፋት ወደ ቤቱ በረረ።

*** *** ***

ሻምበል መብራቴን የሚያውቀው ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በነበሩበት ጊዜ ነው። እንዲያውም አንድ አመት የቅርብ ጓደኞች ሆነው ነበር። ያ ጓደኝነታቸው ግን አልዘለቀም። ዐይናፋርና ሴቶችን ይፈራ የነበረው መብራቴ በስንት እበሳ ያገኛትን የከንፈር ወዳጅ ለስዩም ቢያስተዋውቀው ከተፎው ጉብሏ ማርካው ኖሮ ሦስት ቀን ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ከመብራቴ እጅ ላይ ሞጭልፎ ወሰዳት።

በዚህ ሳቢያ ጓደኛሞቹ ተጣልተው ብዙ ተዳርሰው ተለያዩ። የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን እንዳጠናቀቁም ስዩም አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣ መብራቴ ደግሞ ፖሊስ ኮሌጅ ገባ።

ዳግመኛ የተገናኙት ከሰባት ዓመት በኋላ ባንድ የራት ግብዣ ላይ ነበር። እንደተያዩ ሁሉን ነገር ረስተው ተቃቅፈው ተሳሳሙ። ያለፈውን የወጣትነት ትዝታቸውን እያስታወሱ ከጣራ በላይ ተሳሳቁ።

ከዚያ በኋላ አልፎ አልፎ እየተገናኙም ተግባብዘዋል። በመሃል ሻምበሉ ለልዩ ሙያዊ ስልጠና ወደ እስራኤል በመሄዱ ግንኙነታቸው ተቋረጠ። ጠበቃው ሻምበሉን ለመጨረሻ ጊዜ ያየው ከአንድ ዓመት በፊት ሚስቱን ፈቶ ትዳሩን ሲበትን የፍች ስምምነት ውል እንዲጽፍለት ቢሮው በመጣ ጊዜ ነበር። ከዚያ ወዲህ ስለ ሻምበሉ የሰማው ነገር የለም።

*** *** ***

ከሁለት ሰዓት መኝታ በኋላ ጠበቃው እንቅልፍ ያልጠገቡ ዐይኖቹን እያሻሸ ተነሳና መታጠቢያ ቤት ገብቶ ፊቱን ታጠበ። እየኮሰኮሰ የሚያሳክከውን ጢሙን ከተላጨ በኋላም መኪናውን ቀስቅሶ ወደ ወንጀል ምርመራ ጽ/ቤት ገሰገሰ።

ቢሮውን እንኳኩቶ ሲገባ፤ ሻምበሉ በመገረም የፈጠጡ ትናንሽ ዐይኖቹን እያርገበገበ ከመቀመጫው ተነስቶ ሰላምታ ሰጠው።

"ዐይኖቼን ማመን አልችልም .... እዚህ አገር አለህ እንዴ አቶ ስዩም?" አለ የጠበቃውን እጅ እየወዘወዘ።

"አለን! አለን!... አሁንማ የናት ሀገር ባንዲራ ጠባቂ ሆነን የት እንሄዳለን ብለህ ነው? አንተ ለጤናህ እንዴት ነህ ወዳጄ" ጠበቃው ወንበር ስቦ ተቀመጠ።

ሻምባል መብራቱ እንደ ስሙ ፊቱም የሚያበራ ብስል ቀይ ነው። ፊቱ ላይ ጢም የሚባል ነገር የለም። የለበሰው ደንብ ልብስ ወፍራም ሰውነቱ ላይ ተወጣጥሯል። ሁኔታውን ልብ ብሎ ላስተዋለ፤ የሉካንዳ ነጋዴ እንጂ የፖሊስ ሻምበል አይመስልም። የስራ ባልደረቦቹና አለቆቹ ግን በችሎታው የሚተማመኑበት ሰው ነው።

ጠበቃው ስለታም ዐይኖቹን ያወናጭፍ ጀመር። ቢሮ ውስጥ ግን ከአረጀ ጠረጴዛ፣ ወንበሮችና ከአንድ ቁምሳጥን በቀር ምንም የለም። የኮርኒሱ አቡጀዲ ተቀዳዷል፤ የግምቡ ቀለም ተፍቋል። የፖሊስ ጽህፈት ቤቶች መቼ ዘመናዊ መልክ እንደሚይዙ እየገረመው ዐይኖቹን ወደ መስኮቱ ወረወራቸው። መስተዋት የለሹ መስኮት ወደ ውጭ ተከፍቷል። ጠበቃው መስኮቱ አጠገብ ቆሞ ወደ ውጭ ለሚመለከት ሰው ቶዮታዋ ፊት ለፊት ልትታየው እንደምትችል ገመተ።

"ብጄ አቶ ስዩም፣ ዛሬ ልትመጣ የቻልክበትን ምክንያት አንድ ሺ ግምቶች ብደረድር እንኳን እንደማልደርስበት እርግጠኛ ነኝ። ችግር አለ እንዴ?" ሲል ጣቶቹን እያፍተለተለ ጠየቀው።

"በሦስተኛው ዓለም ከጭራቅ ህዝብ ጋር እየኖርክ ችግር ይጠፋል ብለህ ነው!" አለ ጠበቃው የተበሳጨ ለመምሰል እጆቹን እያወናጨፈ።

"ምን ተፈጠረ?" አለ ሻምበሉ ግምባሩን በቁምነገር ቋጥሮ እያደረገ።

"ነገሩ እንኳን ቀላል ነው። ግን መደፈሬ እያንገበገበኝ ነው ወዳንተ የመጣሁት። ዛሬ ጠዋት የመኪናዬን መብራቶች በሙሉ ፍሬቻ ሳይቀር አወላልቀው ወሰዱት" አለና ራሱን አወዛወዘ።

ሻምበሉ ፈገግ አለና "መኪናህን አሳውረዋታላ..." አለው።

"ያውልህ ሆሚርን መስላ ውጭ ቆማልሃለች። እኔ እንኳን የዕቃው ነገር ቆጭቶኝ የመጣሁ እንዳይመስልህ። እንዴት እደፈራለሁ? ህዝቡ እስከ መቼ ነው ቀን በቀን በጠራራ ፀሐይ እየተዘረፈ የሚኖረው?" አለ ግምባሩን እንደቋጠረ።

"ጭራቅ ህዝብ ብለህ መልሱን እኮ አግኝተኸዋል" አለ ሻምበሉ እየሳቀ። "የስራ አጡና ሥራ ፈቱ ቁጥር እንደ አሸን እለት ተለት እየፈላ ለቁጥር በታከተበት ከተማ ሰው እርስ በእርስ እየተበላላ አለማለቁም ራሱ የሚገርም ነው። የሚያሳዝነው ደግሞ ወንጀል የተፈጸመባቸው ሁሉ ድክመቱን በኛ ላይ ነው የሚጭኑት ። ይህን ከተማ ከወንጀልና ከወንጀለኞች ለመከላከል የሚያስፈልገውን ሃይልና አሁን እኛ የምንንቀሳቀስበትን የሃይል ብዛት ብነግርህ አፍህን ይዘህ ትገረማለህ። እየተወራጨን እንጂ ወንጀልን እየተከላከልን አለመሆኑን እናውቃለን። ችግራችንን የሚያውቅ ግን ከስንት አንድ ነው" ሻምበሉ በቁም ነገር ገለፃውን ቀጠለ።

"የወንጀል መንስኤዎች እለት ተለት እየጨመሩ፣ የወንጀል አይነቶች እየረቀቁና እየተወሳሰቡ በሚሄዱበት ከተማ ወንጀለኞችን እንዲያድኑና ህዝቡን እንዲጠብቁ ከተሰማሩ ፖሊሶች ውስጥ ሌቦች፣ ጉቦኞችና ቀማኞች መኖራቸው ደግሞ ወንጀልን እንከላከላለን የሚለውን ቋንቋ ቀልድ ያደርገዋል። ሁሌ የምሰጋውና የምጨነቀው ይህ አሁን ያለው ሁኔታ በዚሁ ከቀጠለ በመጪዎቹ ሃያና ሠላሣ ዓመታት ውስጥ ምን አይነት አስከፊ ሁኔታ ላይ እንደምንደርስ ስገምት ነው።

ሻምበሉ ንግግሩን ከመጨረሱ የቢሮው በር ተንኳኳና የሃምሣ አለቃ ማዕረግ ያንጠለጠለ አንዳች የሚያክል ሰው አጎንብሶ ገባና ለሻምበሉ ሰላምታ ሰጥቶ ቆመ።

"ምን ልታዘዝ ሳጅን?"

"ይሄ ትላንት ሌሊት የሴት አዳሪዋን ንብረት ዘርፎ ሲያመልጥ የተያዘው ሌባ በሰጠው ቃል ላይ ወንጀሉን ሊያምን አልቻለም" ሳጅን በነጎድጓድ ድምፅ ክፍሉን አንቀጠቀጠው።

"መቶ አለቃ የለም እንዴ?..."

"ለሥራ ጉዳይ ወጥቷል ... ጌታው ይፍቀዱልኝና ይህን ዐይን አውጣ ሌባ ላጨማልቀው። አምስት ደቂቃ ባልሞላ ጊዜ ውስጥ እናገዘዋለሁ" አለ ሳጅን እጅጌውን እየጠቀለለ።

ጠበቃው በዚህ ሰው እጅ የተጨማለቀ ሰው ከሰውነቱ ምን ሊተርፈው እንደሚችል ገመተና ተሳቀቀ።

"አታጨማልቀው... በተቻለ መጠን ፖሊሳዊ ምርመራ ዘዴዎችን ተጠቅመህ ትክክለኛ ቃሉን እንዲሰጥ አድርግ" አለ ሻምበሉ በሃምሳ አለቃው ሁኔታ እየፈገገ።

"ኧረ ዐይኑን በጨው ያሸ ደረቅ ነው። ወይኔ ሳጅን... ምናለ ባጨማልቀው?..."

"ጨርሰናል" አለና ሻምበሉ ሃምሣ አለቃውን አሰናበተው።

ሳጅን ወጥቶ ከሄደ በኋላ ጠበቃው ከመቀመጫው እየተቁነጠነጠ "አሁን በዚህ ሰው እጅ የገባ ሰው ይተርፋል?" ሲል በመገረም ጠየቀ።

ሻምበሉ ሲስቅ ቆየና "የቅጽል ስሙስ ማን እንደሆነ ታውቃለህ? 'ሚስቶ' ይሉታል። በሁለት በሦስት ቡጤና በጥቂት የጫማ እርግጫዎች ብቻ አንጀትን ከኩላሊት ጉበትን ከሳንባ ይቀላቅላል። ሰው ሁሉ ስለሚፈራው ራሱን የዚህ ግቢ አዛዥ አድርጎ መቁጠር ጀምሯል" አለ ራሱን በመገረም እየወዘወዘ።

የጠበቃው ሃሳብ ሳጅን ላይ እንዳለ "ለመሆኑ መኪናህ የት ነው የተሰረቀችው?" ሲል ሻምበሉ ድንገት ጠየቀው።

"ራጉኤል አካባቢ አቁሜያት..." አለ ጠበቃው ከእንቅልፉ እንደ ባነነ ሁሉ እየበረገገ።

ሻምበሉ ጥቂት ካሰበ በኋላ "እንዴት ልረዳህ እንደምችል አላውቅም። ለማንኛውም አራተኛ ፖሊስ ጣቢያ ልደውልና አዛዡን ላነጋግርልህ። በአጋጣሚ ዕቃው ሊያዝ ቢችል እንዲያሳውቁኝ ወይም



የተሰረቁ የመኪና ዕቃዎች በሚሸጡበት አካባቢ ሰው አሰማርተው እንዲያፈላልጉ እነግራቸዋለሁ" አለና የቴሌፎኑን እጀታ አነሳ።

ጠበቃው ፈጥኖ ከኪሱ ሲጋራ አወጣና "አንተ መቼም የጭስ ነገር አይሆንልህ። በጠረጴዛህ ላይም መተርኮሻ የለም" አለና ወደተከፈተው መስኮት ሄዶ ሲጋራውን ማጨስ ጀመረ።

ሻምበሉ ደጋግሞ ቁጥሩን መታና ጥቂት ከተነጋገረ በኋላ ስልኩን ዘጋ። "አዛዡ ስብሰባ ላይ ናቸው አሉ... ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ ወደ ቢሯቸው እንደሚመለሱ ስለተነገረኝ ቆይቼ እደውላለሁ" አለና ጠረጴዛው ላይ የተቀመጠውን መጥሪያ በጣቱ ሲጫን በር ላይ የቆመው ፖሊስ በፍጥነት ገብቶ ሰላምታ ሰጠ።

"ምን ትወስዳለህ አቶ ሰዩም" ባሻገር የቆመውን ጠበቃ ጠየቀው።

"ቡና ይሁንልኝ" አለ ጠበቃው እያዛጋ።

"ሁለት ቡና እዘዝልን" ፖሊሱ በፍጥነት ቢሮውን ለቆ ወጣ።

"የጠበቃው አዕምሮ ቁልቁል የሚመለከታት ቶዮታ ጉዳይ እንዴት እንደሚነሳ እያሰላሰለ ነበር።" ከዚች በጥይት ከተበሳሳች መኪና ሰው ይተርፍ ይሆን? በፖሊስ ጽ/ቤቶች ግቢ ውስጥ የማይታይ ነገር እኮ የለም" አለ በመገረም።

"ከየቷ?" አለ ሻምበሉ ከሀሳብ እንደነቃ አይነት በርግጎ።

"ከቶዮታዋ... ምን ተርፋለች ጃል?"

ሻምበሉ በቅሬታ ፈገግ አለ "ጉደኛ መኪና ነች። ከዚች መኪና ጀርባ የተጠላለፈው የወንጀል መረብ የዋዛ እንዳይመስልህ" አለና ከተቀመጠበት ተነስቶ ወደ መስኮት አመራ።

የጠበቃው ልብ በፍጥነት እየመታ ቀልቡን ሁሉ ጆሮዎቹ ላይ ሰብስቦ ያዳምጥ ጀመር። አሰሳ ድረስ የተንከራተተበት የሚስጥሩ ሰልቻ መቋጠሪያ እየተተረተረ ነው።

"ወንጀል የተሠራባት መኪና ነች?"

"ከወንጀልም ወንጀል! አራት ነፍስ የጠፋበትI አንድ ሰው የቆሰለባትI በሀገር በሕዝብና በአብዮት ላይ ከፍተኛ አደጋ ሊያስከትል የሚችል ደባ የተቀነባበረባት መኪና ነች..."

ሰማያዊ ሸርጥ የለበሰች አጭር ሴት ሁለት ስኒ ቡና በሰርቪስ አንጠልጥላ ገባችና አቀረበችላቸው። ጠበቃው በልቡ ረገማት። ሁለቱም

እዚያው እንደቆሙ ቡናቸውን እየጠጡ ቆዩ። ጠበቃው ከአቶ መንገሻና ከናፖሊዮን የሰማውን ታሪክ ሻምበሉ ደገመለት። እርሱ መስማት የሚፈልገው ግን የወንጀሉን አደገኛነትና የአፈፃጸሙን ድንቅነት ሳይሆን የተንከራተተበት ሰነድ የት እንደሚገኝ ነበር።

"ታዲያ የወንጀሉን ፈጻሚዎች ማግኘት እንዴት አልተቻለም?" ሲል ጠየቀ የያዛትን የሲጋራ እሳቂ ቁልቁል እየወረወረ።

ሻምበሉ በነገረው ታሪክ የተገረመውን ጠበቃ ይበልጥ ለማስገረም "ወንጀሉ በጥንቃቄ የተከናወነና ውስብስብ ነው ያልኩህም ለዚህ ነው። ለምሣሌ ታርጋ ቁጥሩን ውሰድ ከዚህ ስትመለከተው እውነተኛ ታርጋ ቁጥር ይመስላል። እንደዚያ ካሰብክ ተሳስተሃል። ረቂቅ በሆነ መንገድ ተሰርቶ የተለጠፈላት የተጭበረበረ ታርጋ ነው"

"ያንተ ያለህ!"

"የሞተር ቁጥሯም ተፍቆ ጠፍቷል"

"በዚህ በሦስተኛው ዓለም ይሄን ያህል የተቀነባበረ ወንጀል ሊፈጸም ይችላል ብዬ አልገምትም ነበር"

"በጣም የሚያስደንቅህ ደግሞ በሞቱት ሁለት ሰዎች ኪስ ውስጥ የተገኙት መታወቂያዎችም እንዲሁ የተጭበረበሩ ናቸው። አድራሻቸው፣ ማንነታቸውና ፎቶግራፋቸው ጭምር የነርሱ አይደለም። በዚህ ተስፋ ሳንቆርጥ ከአስከሬኖቻቸው ላይ የጣት አሻራ ወስደን ከፖሊስ የአሻራ ሪኮርድ መዛግብት ጋር አንላብጠን አገናዘብን። ከዚህ በፊት አሻራ ያልሰጡ ሰዎች ናቸው።

"ምን አይነት አጋጣሚ ነው?" አለ ጠበቃው በሚንቀጠቀጡ እጆቹ ሲጋራ አውጥቶ እያቀጣጠለ።

"በዚህም ተስፋ አልቆረጥንም፤ አመለጠ የተባለውን ሰው ማንነት ለማጣራት ከመኪናዋ የተለያዩ ክፍሎች ባነሳነው አሻራ ላይ በርካታ ጊዜ በመኪናዋ ላይ ያረፈ አንድ አሻራ አግኝተን አሁንም ከፖሊስ የአሻራ ሪከርድ መዝገቦች ጋር አገናዝበን ማንነቱን ደረስንበት፤ ግን..." የጠበቃው ትንፋሽ ለሰከንዶች ከፍልፋይ ቀጥ ብላ ቆመች ። "ግን ምን?!" አለ እንደማቃሰት ያለ ድምጽ እያወጣ።

ሻምበሉ ድንገት ፖሊስነቱን አስታወሰና ዝም አለ። ለምን ይህን ሁሉ ዝርዝር ታሪክ እንደሚያወራለት ለራሱም ቢሆን አልገባህ አለው።



"ልክ በፊልም የተሠራ ታሪክ የምትነግረኝ ነው የመሰለኝ። የሰውዬው ማንነት ከታወቀ ታዲያ ለምን እርምጃ መውሰድ አልተቻለም?" አለ ጠበቃው ድንጋጤውን በመገረም ለመሸፈን እየሞከረ።

"ተወው፣ ዝርዝር ጉዳዩ እጅግ ብዙ ነው" አለ ሻምበሉ በመሰልቸት። ጠበቃው ብዙ ለመስማት የነበረው ጉጉት በአጭር በመቀጨቱ በቁጭት የያዘውን ሲጋራ ደጋግሞ ለመጠጠው። ሻምበሉ የጀመረውን እንዲጨርስ የሚያግባባበትን ዘዴ ሲያሰላም ስልኩ መጮህ ጀመረ። ሻምበሉ እየተጣደፈ ሄዶ አነሳው። ጠበቃው ዐይኖቹን ወደ ቶዮታዋ ወርውሮ ጆሮዎቹን ወደ ሻምበሉ አቅጣጫ ደገናቸው።

"ሻምበል መብራቴ ነኝ፤ ጤና ይስጥልኝ ጌታዬ!... "ለረዥም ጊዜ ፊቱን አኮፋትሮ ሲያዳምጥ ቆየና" የኛ ስንፍና አይደለም እኮ ጌታዬ! በዚህ ወንጀል ዙሪያ ቀን ተሌት እየሮጥን ነው። አንዳንድ ግራ የሚያጋቡ ጉዳዮች ቢኖሩም ያን ያህል ተስፋ የሚያስቆርጥ አይደለም። ጥቂት ጊዜ ብቻ ይስጡን ጌታዬ... ያለንን ሃይል ሁሉ አሰማርተናል። ማንኛውንም ፍንጭ ሁሉ ሪፖርት አደርግልዎታለሁ... ግድ የለም አያፍሩብንም" ስልኩን ዘጋና በረዥሙ ተነፈሰ።

"ስቃይ፣ ስቃይ'ኮ ነው። የዚችን ቶዮታ ጉዳይ መች እንደምገላገል አላውቅም" አለ እየተበሳጨ።

"ማነው የደወለው?" አለ ጠበቃው እየቸኮለ። የተቋረጠውን የሚሰጥር ስልቻ አፍ ዳግም ለመፍታት ጊዜው ሳያመለጠው።

"የፖሊስ ጠቅላይ አዛዡ ናቸው" አለ ሻምበሉ በአገጩ ወደ ስልኩ ቀፎ እያመለከተ።

"ይህን ያህል በከፍተኛ ባለስልጣኖች ትኩረት የተሰጠው ወንጀል ሆኗል ማለት ነው? ደግሞ አንድ ነገር ሳልጠይቅህ ... ሊብሬ ወይም ሌላ የመኪናዋን ባለቤትነት ሊያስረዳ የሚችል ነገር በመኪናዋ ውስጥ አልተገኘም?" ጠበቃው ጥየቀ።

ሻምበሉ በሁለት እጆቹ ፊቱን እንደደገፈ ለረዥም ጊዜ በዝምታ ሲመለከተው ቆይቶ "ብጣሽ ወረቀት በመኪናዋ ውስጥ አልነበረም!" አለው።

የጠበቃው ነፍስ በውስጡ ቧረቀች፤ ፊቱ በደስታ መብራት ጀመረ። ሁኔታው ያስገረመው ሻምበል "ምነው?" አለው ግምባሩን ቅጭም፣ የዐይኑን መስኮቶች ጥብብ አድርጎ።

ጠበቃው ስሜቱን መቆጣጠር አለመቻሉ በሻምበሉ የጥርጣሬ ቀለበት ውስጥ እንደከተተው ለመገመት ጊዜ አልፈጀበትም። "የራሴ ነገር ነው ያስደነቀኝ። ይህን ልብ ወለድ የመሰለ ነገር እየነገርክ የመጣሁበትን ጉዳይ አዘናግተህ አጃጃልከኝ። በል ወዳጄ ስልኩን ደግመህ ደውልልኝ" አለና ሲጋራውን ወርውሮ ከቆመበት መስኮት ወደ ሻምበሉ ጠረጴዛ ተጣደፈ።

ሻምበሉ ግራ የተጋባ የሚመስለውን ፊቱን በቅሬታ ፈገግታ አፍክቶ የስልኩን እጀታ አነሳና ቁጥሩን አሽከረከረ። ዐይኖቹ ግን እየሰረቁ የጠበቃውን ገጽታ ያጠናሉ።

"ሃሎ፣ አሁንም አልጨረሱም? ጥሩ እንግዲያው እንደመጡ እንዲደውሉልኝ ይሁን..." ስልኩን ዘጋና እጆቹን አጣምሮ ጠበቃውን ይመለከተው ጀመር።

"አልተገኙም?" አለ ጠበቃው እየተጣደፈ።

"አሁንም ከስብሰባው አልወጡም"

ጠበቃው ሰዓቱን ተመለከተና "በቃ፣ ጠዋት እደውልልሃለሁ። ለጊዜው በር ላይ ያቆምኳትን ሆሜር ላሣይህ" አለ የሻምበሉን ጥርጣሬ ከአዕምሮው ውስጥ ለመፋቅ።

ሻምበሉ ፈጥኖ ተነሳና ተያይዘው የጠበቃው መኪና ወደቆመችበት አመሩ። መኪናዋን እየተዘዋወረ ከተመለከተ በኋላ ራሱን በሀዘኔታ እየነቀነቀ "አራቂተዋት የለም እንዴ? እንግዲህ እድል ከረዳህ የተቻለኝን ለማድረግ እሞክራለሁ... ነገ ደውልልኝ።" አለና እጁን ለስንብት ዘረጋለት።

ጠበቃው "እንደምትረዳኝ ተስፋ አደርጋለሁ... ደህና እምሽ" አለና ፈጥኖ ወደ መኪናው በመግባት ሞተሩን ቀስቅሶ ተፈተለከ። ሻምበሉ ግን ከቆመበት ሳይንቀሳቀስ ዐይኖቹን የጠበቃው መኪና ወደ ሄደችበት አቅጣጫ ቡዝዝ አድርጎ ማሰብ ጀመረ።

ጠበቃው የመኪናው መብራት በመሰረቁ ምክንያት ብቻ ነው የቢሮዬን በር ያንኳኳው? በቶዮታዋ ታሪክ ለምን ያን ያህል ተመሰጠ? የመኪናዋን ባለንብረትና ወንጀለኞቹ ሊገኙ አለመቻላቸውን ስነግረው



እንደዚያ ያስፈነደቀው ምንድነው? የሚሉ ጥያቄዎች በጭንቅላቱ ውስጥ እየዠጡሩ እረፍት ነሱት።

ሻምበሉ ከጠበቃው ሊደብቅ የቻለው አንድ ሚስጥር ብቻ ነበር። ከቶዮታዋ መኪና ላይ ከተወሰዱት አሻራዎች መካከል የአንድ ሰው አሻራ ከተለያዩ ቦታዎች ላይ በብዛት በመገኘቱ አሻራው ከፖሊስ የአሻራ መዛግብት ጋር ተገናዝቧል። ይህ ውጤት ደግሞ እጅግ ውስብስብ የሆነ ችግር ፈጠረ።

የተገኘው አሻራ ናፖሊዮን እምባው የተሰኘ ሰው በአየር ወለድ ሠራዊት ውስጥ ሲቀጠር ከሰጠው አሻራ ጋር ተመሳሳይ ሆኖ ተገኘ! ይኼኔ ሻምበሉ ጊዜ ሳይወስድ ወደ አየር ወለድ ጠቅላይ መምሪያ ይገሰግሳል። የመምሪያው ባለስልጣኖች ከአየር ወለድ አዛዦች ጋር በመነጋገር የተባለውን ሰው ማንነት ለማወቅ መዛግብት እንዲገላበጥ ያደርጋሉ። የተገኘው ውጤትም ሻምበሉን ራሱ እስከዞር ድረስ እንዲገረም ያደርገዋል። "ናፖሊዮን እምባው በኤርትራ ግንባር ከረን ላይ በግዳጅ ላይ ሳለ ተገድሏል!" ይላል መረጃው።

ሻምበሉ እየተጠራጠረና እየተገረመ ናፖሊዮን በሠራዊቱ ውስጥ ሲቀጠር የሰጠውን ፎቶግራፍና አድራሻ በመውሰድ ወደ ቢሮው ይመለሳል። አሻራው እንደገና እንዲገናዘብ ቢያስደርግም ውጤቱ ያው የመጀመሪያው ሆኖ ተገኘ። የሞተ ሰው መቃብር ፈንቅሎ ወንጀል ፈጸመ? ወይንስ ናፖሊዮን እምባው አሁንም በህይወት አለ? ሻምበሉ ግራ እንደተጋባ ናፖሊዮን በሠራዊቱ ውስጥ ሲቀጠር የሰጠውን አድራሻ መሠረት በማድረግ ፍለጋውን ቀጠለ።

በተጠቀሰው አድራሻ ሲሄድ ያጋጠመው ግን አንድ ትልቅ ቡና ቤት ነበር። የቡና ቤት ባለቤት ነኝ የተባለችውን ሴት አስጠርቶ ውስኪ እየጋበዘ አነጋገራት። አንድ ሺ ያህል ፖሊሳዊ የጥያቄ ዘዴዎችን ተጠቅሞ ስለ ናፖሊዮን የምታውቀውን ሁሉ እንድትነግረው ወተወታት።

"አልፎ አልፎ እንኳ አንቺ ዘንድ ብቅም አይል?"

"ከኔ ዘንድ... ቂቂቂ ... እኔ ዘንድማ ድርሽ ሳይል ስንት አመቱ! ገና አገጩ ላይ ጢም ማቆጥቆጥ ሲጀምር ነው ልቡ ተነፍቶ ረግጦኝ የወጣው..."

"በአየር ወለድ ሠራዊት ውስጥ ስለመቀጠሩ የምታውቂው ነገር የለም?..."

"ማ… ናፖሊዮን?… አይ ሻምበልዬ ኧረ ይሄንንስ ሰው አይሰማብዎ። ፈሪ እኮ ነው… ልቡ ከቡሽ የተሠራ ነው የሚመስለኝ … እና ይሄን አየር ወለድ ምናምን የሚል የሰው ወሬ አይስሙ። እርግጠኛ ነኝ ጭድ ተራ ወይም አከንባሎ ተራ ቢሄዱ አሁኑኑ ያገኙታል … እኔ መድረሻውን መች አጣሁት?! ቂቂቂ…"

ሻምበሉ ይበልጡን ግራ ተጋባ። በአንድ ሺ ጥያቄ ጭንቅላቷን እንዳዞረው፣ እርሷም በአንድ ሺ የማይረባ መልሷ ናላውን አሽከረከረችው። በመጨረሻም ሲፈልጋት ቢሮው ድረስ አስጠርቶ እንደሚያነጋግራት ገልጾ ጥሏት ወጣ።

በዚህ ግን ተስፋ አልቆረጠም። የዚህ ወንጀል ጉዳይ የእንጀራ ገመዱን የሚያስረዝም ወይ የሚያሳጥር መሆኑን ተረድቷል። ከአለቆቹና ከመንግስት ባለስልጣኖች በየቀኑ እየተወለደ የሚደርስበት የማስጠንቀቂያ የስልክ ጥሪ ቀንና ሌሊት እረፍት ነስቶ ያባንነዋል።

ከአየር ወለድ ሠራዊት ያገኘውን የናፖሊዮን እምባውን ፎቶግራፍ ይዞ በተኩስ ልውውጡ ወቅት ቆስሎ ለህክምና ወደ ዳግማዊ ምኒሊክ ሆስፒታል ተልኮ ወደተኛው የፈናንስ ፖሊስ አባል ደግሞ ሮጠ።

በማገገም ላይ ያለውን ቁስለኛ ያገኘው ከመኝታ ክፍሉ ወጥቶ በረንዳ ላይ ፀሐይ ሲሞቅ ነበር። ሰላምታ ከሰጠው፣ ማንነቱን ከገለጸለትና መታወቂያውንም ካሳየው በኋላ ስለተፈጸመው ወንጀል እንዲያጫውተው ጠየቀው። ቁስለኛው ሻምበሉ ከዚህ ቀደም የሰማውን ታሪክ ደገመለት።

ተካልኝ ባልቻ ንግግሩን ሲጨርስ ሻምበሉ "በተኩስ ልውውጡ ወቅት አምልጧል የተባለውን ወንጀለኛ አሁን ብታየው ልታስታውሰው ትችላለህ?" ሲል ጠየቀው።

ፖሊሱ በራ ጭንቅላቱን እያከከ ብዙ ሲያስብ ከቆየ በኋላ "ምናልባት" የሚል መልስ ሰጠው።

በብዛት እንዲታተሙና በፖሊሶች እጅ እንዲገቡ ካደረጋቸው የናፖሊዮን ፎቶግራፎች ውስጥ አንዱን አውጥቶ ከሌሎች ሁለት የተለያዩ ግለሰቦች ፎቶግራፎች ጋር በማቀላቀል ለቁስለኛው እየሰጠ "ከነዚህ ሦስት ፎትግራፎች ውስጥ ወንጀለኛው የቱ ነው ብለህ ትገምታለህ?" ሲል ጠየቀው። ቁስለኛው ፖሊስ ሦስቱንም ፎቶግራፎች እየደጋገመ ሲያያቸው ቆየና "ከነዚህ ውስጥ አይደለም" አለ



በርግጠኝነት። በሻምበሉ ልቡና ውስጥ የወንጀለኛውን ማንነት ለማወቅ ጭልጭል ትል የነበረች የመጨረሻዋ ተስፋ ወደመች።

"እስኪ እንደገና ተመልከታቸው" አለ ተስፋውን እንደቆረጠ። ፖሊሱ ዳግመኛ ፎቶግራፎችን መልከት መልከት አደረገና ራሱን በአሉታ ነቀነቀ። "በጭራሽ ከነዚህ መካከል አይደለም።"

"ያን ያህል እንዴት እርግጠኛ ሆንክ?" ሻምበሉ በብስጭት አፈጠጠበት።

"እንዴት ማለት?" ቁስለኛው ግምባሩን ቋጥሮ ጥያቄውን በጥያቄ መለሰለት።

"አንድ ቀን … ያውም ለተወሰኑ ደቂቃዎች በተፋፋመ የተኩስ ልውውጥ መሃል ያየኸውን ሰው በርግጠኝነት አስታውሰህ፣ በፎቶግራፉ ብቻ ነው አይደለም ለማለት እንዴት ደፈርክ?!"

"የጠየቁኝን ነው የመለስኩት ጌታዬ"

ሻምበሉ ከሦስቱ ፎትግራፎች ውስጥ የናፖሊዮንን መርጦ በማውጣት "እስኪ ይሄኛውን ተመልከተው፣ የአመለጠው ወንጀለኛ ይህ አይደለም?" አለው። ቁስለኛው በሰለቸ ስሜት ፎቶግራፉን ተቀብሎ ሲመለከተው ቆየና "አይደለም" በማለት መለሰለት።

ሻምበሉ ፎቶግራፉን መንጭቆ ወሰዶ ራሱን በንዴት እያወዛወዘ "ያልመለስክልኝ ጥያቄ አለ። እንዴት እርግጠኛ ሆንክ?" ሲል ዳግም ጮኸ።

"ለምን ያስጨንቁኛል ጌታዬ። በመለኮት ቸርነት ከሞት ተረፍኩ ብዬ እፎይ ስል እርሶ ደግሞ ምን ፍጠር ነው የሚሉኝ? ይህ ፎቶግራፍ የወንጀለኛው ፎቶግራፍ ነው ብልዎ 'እንዴት እርግጠኛ ሆንክ?' ብለው አይጠይቁኝም ነበር? የጠየቁኝ ግምቴን ነው… ትክክለኛውን ግምቴን ደግሞ ነግሬዎታለሁ" አለና እንደ ህፃን ልጅ ተነጫነጨ።

"ጥሩ፤ እዚህ ሆስፒታል ውስጥ ምን ያህል ጊዜ ትቆያለህ?"
"ቁስሉ ስላልጠገገ ገና ብዙ ጊዜ እቆያለሁ"

ሻምበሉ የማስታወሻ ደብተርና ብዕር አውጥቶ "አዲስ አበባ በምትቆይበት ጊዜ የምታርፈው የት ነው? የመኖሪያ ሰፈርህ ማለቴ ነው?" ሲል ጠየቀው።

“ራጉኤል!”

“ከፍተኛና ቀበሌ፣ የቤት ቁጥሩንም ንገረኝ ...”

ቁስለኛው በዐይኖቹ ላይ የስጋትና የጥርጣሬ ጥላ እንዳንዣበበ አድራሻውን ሰጠውና እያነከሰ ወደ ህክምና ክፍሉ ጥሎት ገባ።

የሻምበሉ አዕምሮ በበርካታ ጥያቄዎች እንደተወጠረ መኪናውን አስነስቶ የሆስፒታሉን ቅጥር ግቢ ለቆ ወጣ።

ይህ በሆነ በአራተኛው ቀን ወደ ሆስፒታሉ ቢሄድ ቀደም ሲል በተገናኙበት ዕለት ከሆስፒታሉ በራሱ ጥያቄና ውትወታ መውጣቱን ሰማ። በሰጠው አድራሻ መሠረት ሂዶ ቢጠይቅም በዚያ ስም የሚታወቅ ሰው የለም። የሻምበሉ ራስ በብስጭት ሲፈነዳ ምንም አልቀረውም።

ጠበቃውን ሸኝቶ ከቆመበት ቦታ እንዳለ ይህን ሁሉ ሲያሰላስል አንድ ሀሳብ በህሊናው ውስጥ ብልጭ አለና የኤሌትሪክ ሞገድ ያህል ሰውነቱን ነዘረው። ጠበቃው የመኪናዬ መብራቶች ተሰረቁ ያለው ራጉኤል አካባቢ ነው። ጠበቃውና ቁስለኛው ከወንጀሉ ጋር ግንኙነት ይኖራቸዋል? ወይንስ ያጋጣሚ ጉዳይ ነው?

የሻምበሉ አዕምሮ ባጋጣሚ ሊሆን ይችላል የሚለውን ሃሳብ አልተቀበለውም። የጠበቃው በቶዮታዋ ታሪክ መመሰጥና በመጨረሻ የወንጀለኞቹ ማንነት አለመታወቁን ሲነግረው የተሰማውን ደስታ ሲያስታውስ “አለ ነገር!” አለና ራሱን በእምንታ ነቀነቀ። ውሉ የጠፋበትን ምስቅልቅል ወንጀል ጫፍ ለመጨበጥ አሁን ትንሽ ጭላንጭል ታየችው። ካለበት ሳይንቀሳቀስ ደንዝዞ እንደቆመ፣

“እጨማለኩት እኮ ጌታዬ!’ የሚል ድምፅ ሰማ።” ወደ ኋላው ዞር ሲል ሳጅን ደረቱን እንደነፋ እጅጌውን እየጠቀለለ ቆሟል።

“ማንን?”

“ሴተኛ አዳሪዋን የዘረፋትን ዐይን አውጣ ሌባ...”

“እመነልህ?”

“ይችን ይወዳል የሰውዬው ልጅ!... በልጅነቱ ከእናቱ መቀነት የሰረቃትን ሳንቲም ሳይቀር ነው ያስቆጠርኩት”

ሻምበሉ ሳይወድ ፈገግ አለ። አሁን ስለ አንድ ተራ ሌባ ጉዳይ የሚያስብበት ሰዓት አይደለም። በእንጀራው ላይ በመጣ ከፍተኛ የወንጀል ጉዳይ እንደተመሰጠ ለሳጅን ማን በነገረው።

ሦስቱን የጥርጣሬ ነጥቦች፤ የናፖሊዮንን እናት፣ የቁስለኛውን ፖሊስና የጠበቃውን እንቅስቃሴ ለመከታተል የሚረዳውን አዲስ



ፕሮግራም ለመንደፍ ወደ ቢሮው ሮጠ። ሳጅን በመገረም አፉን እንደከፈተ ይመለከተው ነበር።

## ምዕራፍ አሥራ ሰባት

ጨለም ባለው ክፍል ውስጥ የሲጋራ፣ የጫማና የአቧራ ሽታ የጠበቃውን አፍንጫ እያፈነ ደጋግሞ ያስነጥሰዋል። ናፖሊዮን ከአቧራማው ወንበር ላይ በፀጥታ ተቀምጦ ሲጋራውን ያጨሳል።

"ናፖሊዮን!"

"እህ..."

"ተካልኝ ባልቻ የሚባል ስም ከዚህ ቀደም ሰምተህ ታውቃለህ?"

"አላውቅም"

"እስኪ ደጋግመህ አስብ"

"ማሰብ ትቻለሁ አልኩህ እኮ"

"ተካልኝ ባልቻ ማን እንደሆነ ታውቃለህ?"

"አላውቅም"

"ያቆሰልከው የፈናንስ ፖሊስ እኮ ነው!"

ናፖሊዮን በግዴለሽነት ትከሻውን ሰበቀ።

"ቁስለኛው ወደ አዲስ አበባ ለህክምና ተልኮ ዳግማዊ ሚኒሊክ ሆስፒታል ተኝቶ ነበር..."

"ነበር?"

"አዎን፣ ነበር"

"አገኘኸው?"

"አላገኘሁትም፤ እኔ አዲስ አበባ በገባሁበት ቀን እርሱ ከሆስፒታሉ ወጣ"

"አድራሻውን ማግኘት አልቻልክም?"

"አድራሻውን አግኝቼዋለሁ። ሰውዬውን ግን ማግኘት አልቻልኩም። በነገራችን ላይ የመኖሪያ ሰፈሩ ራጉኤል አካባቢ ነው። በዚያ አካባቢ ከምታውቃቸው ሰዎች አንዱ ይሆን?"

በባዶው ብፌ ላይ የተቀመጠው ስልክ መጮህ ጀመረ። ጠበቃው የናፖሊዮንን ዐይኖች እያየ ግራ በመጋባት ቢጠብቅም ናፖሊዮን ስልኩን ለማንሳት ምንም አይነት እንቅስቃሴ አላሳየም። ስልኩ አሁንም ደጋግሞ መጥራቱን ቀጠለ።

ጠበቃው ስልኩን ለማንሳት ከመቀመጫው ሲንቀሳቀስ ናፖሊዮን በአለበት ረግቶ እንዲቀመጥ በእጁ ምልክት አሳየው።

"ተወው!"

ጠበቃው ሽምቅቅ አለና ባለበት ረጋ።

"በጄ ምን ነበር ያልከው?"



ግራ የተጋባው ጠበቃ አንድ ጊዜ ወደ ስልኩ እንደገናም ወደ ናፖሊዮን ገልመጥ አለና "እ... አዎን በራጉኤል አካባቢ የምታውቀው ሰው አለ?" ሲል ጠየቀው።

"የለም"

ናፖሊዮን በሚያሳየው ግድ የለሽነት ጠበቃው በአንድ ጉዳይ እርግጠኛ ወደመሆን ተቃረበ። ሰነዱ በቆሰለው ፖሊስ እጅ የለም።

"ስማ ናፖሊዮን፣ በገዛ ህይወትህ በመጣ ጉዳይ እንዴት ግድየለሽ እንደሆንክ ሊገባኝ አልቻለም። ቀንና ሌሊት የምሮጠው፣ ከአዲስ አበባ አሰላ፣ ከአሰላ አዲስ አበባ... ራጉኤል ጂኒ ቁልቋል ለማን ስል ይመስልሃል?" ሲል እጆቹን እያወናጨፈ የተበሳጨ መሰለ።

ናፖሊዮን የዐይኑን መስኮቶች አጥብቦ በትዝብትና በንቀት ሲመለከተው ቆይቶ "ህ ... ለኔ ስትል ነው?" ሲል በምጸት ፈገግ አለ።

ጠበቃው ናፖሊዮን ሚስጥሩን ያወቀበት ስለመሰለው ደነገጠ። የተሰማውን የሀፍረት ስሜት ለመደበቅም ኪሶቹን እየደባበሰ ሲጋራና ክብሪት አውጥቶ ትምባሆውን ለኮሰ።

"በርግጥ ለኔ ስትል ነው?" ናፖሊዮን ፊቱን አጨፈገገና ደግሞ ጠየቀው።

ጠበቃው የናፖሊዮንን ገጽታ አልወደደውም። ክፍሉን በተጨነቁ ዐይኖቹ እያማተረ ከቶ ሊደርስ ቢችል የማምለጫ መንገድ ያመቻች ጀመር። ገርበብ ብላ ከተከፈተችው መስኮት በቀር በሩ ከውስጥ እንደተቀረቀረ ነው። "ማለቴ... በጥረቴና በሙያ ችሎታዬ ልታደጋቸው ከምሮጥላቸው ነፍሶች አንዷ የአንተም ነች። ልትተባበረኝ እኮ ይገባል ናፒ፤ በዚች የመጨረሻ ሰዓት እጅና ጓንት ሆነን ካልሰራን ውጤቱ ምን ሊሆን እንደሚችል መገመት መቻል አለብህ" አለ ገርበብ ያለችውን መስኮት ደጋግሞ እየቃኘ።

"ውጤቱ ምን ይሁን ምን አያገባኝም። የምትሮጠው የኔን ነፍስ ለማትረፍ ብለህ ከሆነ ደግሞ ጀሃነም መግባት ትችላለህ! ሞትን የምፈራ ሰው አይደለሁም። ሞት ለኔ ምን ማለት እንደሆነ ታውቃለህ? ከምጠላው ብርሃን መገላገል፤ በምወደው የጨለማ እቅፍ ውስጥ ለዘለዓለሙ ማንቀላፋት ማለት ነው"

"አትሳሳት ናፖሊዮን፤ ብርሃን እውነት፣ ብርሃን ፍቅር፣ ብርሃን ተስፋ ነው! እባክህን ተስፋ አትቁረጥ! በማንኛውም ጤነኛ አዕምሮ ባለው ሰው አስተሳሰብ ብርሃን ህይወት ነው ናፒ"

ናፖሊዮን በምጸት ፈገግ አለ። ብርሃን እውነትፕ ብርሃን ፍቅርፕ ብርሃን ተስፋ... ብርሃን ህይወት ነው ያልከኝ? ደላላ ነህ አቶ ጠበቃ! ይህን ካንተ አንደበት ስሰማ እንደምታላግጥብኝ እየተሰማኝ ነው። ደግሞ ጤነኛ አእምሮ የለህም ስትል ነው የሰማሁት? እንደጦር ሰንጥቆ በሚገባ ክፉ አስተያየት ተመለከተው።

"እንደዚያ ማለቴ ሳይሆን... ናፒ..."

"ሃ ሃ ሃ... ሃሃሃ... እም... ብርሃን ህይወት ነው አልከኝ እንጂ! ... ይሄን ሄደህ ላሳደከው በግ ንገረው... ብርሃን ሞት ነው!"

ጠበቃው በጁ የያዘውን ሲጋራ ወርውሮ ረገጠና ጣቶቹን ደጋግሞ አፋተጋቸው "ይሁን ናፒ ... የምትለው ሁሉ ትክክል ነው። ይሁንና አሁን ለውዝግብ ጊዜ የለንም"

"አውቃለሁI ከዚህ በኋላ ያለው ጉዳይ የሚፈታው በጥቂት የጥይት አረሮች ብቻ ነው! በዚህ ወንዶች ብቻ በሚፈቱት ችግር ውስጥ ላትህን አንጠልጥለህ የምትገባበት ምክንያት አልተገለጸልኝም"

ጠበቃው አገጩን በመዳፉ አስደግፎ ማሰብ ጀመረ። ሰነዱ ያለው በትክክል በናፖሊዮን እጅ ነው! ግን ለምን ዓላማ? አወጣ አወረደI ሊያጠግበው የሚችል መልስ አላገኘም። እናም ጭኩን አለና "ናፒ ሰነዱ ያለው በአንተ እጅ ነው!" አለው ።

ናፖሊዮን እጆቹን አጣምሮ በዝምታ ሲመለከተው ቆየና በቅሬታ ፈገግ አለ። "ይልቅ እኔ አንድ እውነት ልንገርህ የለየልህ እብድ አንተ ነህ!" አለው ፈገግታው ወደ ቁጣ እየተቀየረ። ጠበቃው ስሜቱን ለመረዳት ዐይኑን ሳያረግብ አፍጥጦ ተመለከተው። "ሰነዱ ያለው በእጅህ ነው?!" ናፖሊዮን በመገረምና ግራ በመጋባት የተበለጠጡ ዐይኖቹን ዐይኑ ላይ እንደተከለ ይመለከተው ጀመር።

"አልተሳሳትኩም ናፒ!"

"እንዴት ያለኸው የመንዝ በግ ነህ ጃል?"

ጠበቃው በያዘው መስመር ጸንቶ ለመግፋት ወሰነ። "ናፒI ይልቅ ባንድ ነገር እንስማማ ... ሰንት ልትሸጥልኝ ትችላለህ?!"

"ምኑን?"

"በእጅህ ያለውን ሰነድ! ድብብቆሹን ሁሉ ትተን በዋጋው ላይ ብቻ እንነጋገር።"

"በጭንቅላትህ ውስጥ ምን እንዳለ ሊገለጽልኝ አልቻለም... ወይንስ ልታሳብደኝ ትፈልጋለህ?"



"ሰነዱ በቆሰለው ፖሊስ እጅ እንደሌለ እርግጠኛ ነኝ። በደህንነቶችና በወንጀል ምርመራ ፖሊሶች እጅም አልገባም"

"ምን ማስረጃ አለህ?"

"ይህን ጉዳይ ለማጣራት አዲስ አበባ ወንጀል ምርመራ ቢሮ ሄጄ ነበር..." ናፖሊዮን እግሮቹን ከሰቀለበት ጠረጴዛ በፍጥነት አውርዶ በመቆም ጠበቃው ላይ ቁልቁል አፈጠጠበት "እብድ ነህ?"

ጠበቃው በድንጋጤ የተበለጠጡ ዐይኖቹን ሸቅብ ሰቅሎ "ናፒ ትዕግስት ይኑርህ..." እያለ ተንተባተበ።

"ይህን ብቻ ንገረኝ እብድ ነህ?"

ከፊት ለፊቱ ዛፍ አክሎ የቆመውን የናፖሊዮንን ግዝፈት ሲመለከት በርሱና በናፖሊዮን መካከል ያለው ልዩነት በጎልያድና በዳዊት መካከል የነበረውን ልዩነት አስታወሰው። "ኖኖ... ናፖሊዮን የኔ ወንጀል ምርመራ ጽ/ቤት መሄድ ከሰነዱ ጋር በተያያዘ ጉዳይ አይደለም ...የመኪናዬ መብራቶች ስለተሰረቁብኝ ለማመልከት ነበር እና ሲጋት አይግባህ..."

ናፖሊዮን በንዴት የተወጣጠረ ሰውነቱን ዘና አድርጎ በረዥሙ ተነፈሰ። ጠበቃው የተፈጠረው ውጥረት መርገቡን እንዳረጋገጠ ድፍረት ተሰማው። እናም "ናፒ... በእጅህ ለያዝከው ሰነድ ሃያ ሺ ብር ልክፈልህ!" አለው። የቀኝ እጁን ጣቶች ብር እንደሚቆጥር አይነት እርስ በእርስ እያፋተገ።

"ሃያ ሺ ብር?!" ናፖሊዮን በማድነቅ አፏጨ።

"አዎን ሃያ ሺ ብር ናፒ... በርግጥም ቀላል ገንዘብ አይደለም" የጠበቃው ተስፋ በውስጡ ማንሠራራት ጀመረች።

"ሃያ ሺ ብር? ሃሃሃሃ... አላነሰም?" አለው በምጸት እንደፈገገ።

"ጥሩ ሠላሳ ሺ..."

ናፖሊዮን አልመለሰለትም።

"ናፖሊዮን አጥብቀህ አስብ... መቼም መች ቢሆን በእጅህ ሊገባ የማይችል ገንዘብ ነው። ወጣትና ብሩህ የህይወት ተስፋ ያለህ ሰው ነህ። በእያንዳንዷ ደቂቃ ነፍስህን በጥርስህ አንጠልጥለህ ከአደጋ ጋር እንደተጋፈጥክ ከመኖር ይህ ገንዘብ ለዘለዓለሙ ነፃ ሊያወጣህ እንደሚችል አትዘንጋ" ጠበቃው የናፖሊዮንን ግትርነት ለመርታት ምላሱን እንደተልባ ያንጣጣ ጀመር። ናፖሊዮን ግን በምጸት እየፈገገ በመገረም ከመስማት በቀር ምንም አልተናገረም።

“መልካም፣ የመጨረሻውን ክፍያ ሳሳውቅህ ... ሃምሳ ሺ ብር! ዛሬውን ቼክ ልፈርምልህ እችላለሁ”

ናፖሊዮን ድንገት ክፍሉ እስኪንቀጠቀጥ ድረስ ይስቅ ጀመር። የጠበቃው ድንጋጤ እየጨመረ፣ የልብ ምቱ እየፈጠነ ሄደ። ከተቀመጠበት በፍጥነት ተነስቶም የናፖሊዮንን ክንድ ጭምድድ አድርጎ ያዘ። “ናፒ... አንድ እውነት ማወቅ አለብህ...” የወንጀል ምርመራ ፖሊሶች ማንነቱን እንዳወቁና የቀራቸው ነገር ቢኖር ያለበትን ቦታ መፈለግ ብቻ መሆኑን ሊነግረው አሰበ።

ናፖሊዮን ግን ቀድሞት ሳቁን አቁሞ ግምባሩን ቋጥሮ የዐይኑን መስኮቶች አጠበበና “ለመሆኑ አንተ ስንት ታገኝበታለህ?” ሲል ጠየቀው።

“ምናልባት እጥፍ!” ጠበቃው መልስ ለመስጠት ጊዜ አልወሰደበትም።

ናፖሊዮን በፍጥነት ሽጉጡን ከሽንጡ ሥር መዝዞ ካቀባበለ በኋላ የጠበቃውን የሸሚዝ ኮሌታዎች ጨምድዶ ዐይኑ ላይ አነጣጠረበት። “ውሻ! ለአንድ ቀን ታማኝነት እንኳን የማትበቃ የሰው ቁራ! አቶ መንገሻ አንድ ቀን እንደምትሸጠን ምንጊዜም እንደተጠራጠሩ ነበር .... ምክንያታቸው የገባኝ ግን ገና አሁን ነው ... አንተ አሳማ ! ሳታስበላኝ አበላሃለሁ!” አለ የሽጉጡን አፈሙዝ ወደ ዐይኑ እያስጠጋ። ዐይኖቹ ፈጠዋል ድምጹ ይንቀጠቀጣል።

“ኖ ...ናፒ የንጹህ ሰው ደም አታፍስስ...”

“ንጹህ ሰው? አንተ?”

“ናፒ... በቃ ሁሉንም ነገር እንዳልነበር አድርገህ እርሳው”

ናፖሊዮን ምራቁን ጢቅ ብሎ ፊቱ ላይ ተፋበትና አንገቱን ጨምድዶ በያዘው እጁ ገፍትሮ ከግድግዳ ጋር አላተመው። “ውጣ! ውጣ! አንተ የሰው ሽል!”

ጠበቃው እውነት አልመሰለውም። ከእጁ የወደቀውን የመኪና ቁልፍ በዳሰሳ ፈልጎ ካነሳ በኋላ በሩን ከፍቶ እየሮጠ ከግቢው ወጣ። ጫን ጫን እየተነፈሰ መኪናው ውስጥ ከገባ በኋላም ሞተሯን ቀስቅሶ ተፈተለከ። አይምሮው ግን ድንጋጤውን እያረጋጋ ያስብ ነበር። አሁን ባንድ ነገር ፍጹም እርግጠኛ ነው። ሰነዱ በናፖሊዮን እጅ አይደለም፣ በዚያ የተረገመ ቂሰለኛ ፖሊስ እጅ ነው። ምን ሊያደርግበት? የሚለውን የገዛ አዕምሮው የወለደውን ጥያቄ ግን አንድ ሺ ሌሊቶች ተጋድሞ ቢያስብና ቢያሰላስል እንኳን መመለስ እንደማይችል አምኗል።



የመጨረሻ እድሉን ለመሞከር የመኪናውን መሪ ወደ ቀኝ በማዞር በሰንጋተራ በኩል የተክለሀይማኖትን አቅጣጫ ይዞ ወደ ራጉኤል ተፈተለከ።

***   ***   ***

ሀይለኛ ዝናብ የህንፃውን መስተዋት እያጠበ ቁልቁል ይወርዳል። የእስመጪና ላኪ ድርጅቱን ቢሮ ቅዝቃዜ ለመከላከል የተለኮሰው ማሞቂያ ከጠረጴዛው እግር ሥር ተቀምጧል። መንገሻ የኔነህ በእጃቸው የያዙት ፒፓ ጭስ ሽቅብ ቀጥ ብሎ ይወጣል። በእድሜያቸው ላይ አሥር አመት ጨምረው የሰነበቱ ይመስል የፊታቸው ቆዳ ይበልጥ ተሸብሽቧል። በዐይኖቻቸው ውስጥ ያፈጥ የነበረው በራስ የመተማመንና ያልበገር ባይነት ስሜትም መክሰም ጀምሯል።

ጠበቃው ግምባሩን ቅጭም እንዳደረገ አጠገባቸው ካለ ወንበር ላይ ተቀምጧል። በአንጻሩ በርሱ ገጽ ላይ የድል አድራጊነትና የአሸናፊነት ስሜት ይታያል።ሁለቱም እንደተፋጠጡ ለረዥም ጊዜ በዝምታ በመቆየታቸው በቢሮው ውስጥ ሃይለኛ ውጥረት ተፈጥሯል።

“ሰነዱ በእጄ የገባው ገና ትላንትና ነው! ከአሥራ አምስት ቀን እልህ አስጨራሽና ፈታኝ ሩጫ በኋላ...” አለ ጠበቃው ያጠላለፋቸውን የሁለት እጆቹን አውራ ጣቶች እያሽከረከረ።

መንገሻ የመገረምም፣ የመደሰትም ይሁን የመደናገጥ ስሜት ሳያሳዩ ተስፋ የቆረጡ ዐይኖቻቸውን እያቁለጨለጩ በዝምታ ተመለከቱት።

“ምን ያህል ዋጋ እንዳወጣሁበት ብናገር በዚህ ምድር ላይ ሊያምነኝ የሚችል ሰው ቢኖር ሰነዱን የገዛሁት ሰው ብቻ ነው”

መንገሻ ራሳቸውን በአዎንታ ነቀነቁ። “በአንድ ሺ ስለታም ሰይፍ የታጠቁ ዘቦች ከሚጠበቅ የሳጥናኤል ዙፋን ላይ የወርቅ ዘውድ እንደመስረቅ የሚቆጠር ታላቅ ጀብድ ነው የፈጸምኩት ጌታዬ”

“ለዚህ ሁሉ ድካምህ ከኔ የምትፈልገው ወሮታ ምን ያህል ነው?” መንገሻ ጠበቃው ቢሯቸው ከገባበት ጊዜ ጀምሮ ለሁለተኛ ጊዜ ተናገሩ።

"ይሁ እንኳን በጣም አስቸጋሪ ጥያቄ ይመስለኛል ጌታዬ ... ያለ የሌለ ንብረቴ ሁሉ በዚህ ሰነድ ግዥ ላይ ውሏል። በከፍተኛ የወንጀል ጉዳይ ውስጥ እጆቼ ተነክረዋል። እርግጠኛ ነኝ ሰነዱን መለወጫ በማይገኝለት አንድ ህይወቴ ነው የገዛሁት። እና... ጥያቄዬ የሚከብድዎ ይመስለኛል" አለ ዐይኖቹን ከዐይኖቻቸው እያሸሸ።

መንገሻ ከውስጥ ያፈናቸው እልህና ንዴት ገንፍሎ እንዳይወጣ እየታገሉ "እኮ ምን ያህል እንደምትጠይቅ ንገረኝ!" አሉት።

ጠቢቃው ሁኔታቸውን ሲመለከት ከሞት ጋር የተፋጠጠ መሰለው። የተሸበሸበ ቆዳቸውን፣ በጎደጎዱት የዐይኖቻቸው ኩሬ አፋፍ ላይ የተንጠለጠሉትን ዐይኖቻቸውን፣ የደረቁ ከንፈሮቻቸውን ማየት ቀፈፈው። የሚንቀጠቀጠው ድምጻቸው መቃብር እየፈነቀለ እንደሚወጣ ድምጽ አሸበረው።

"በህይወቴ የገዛሁትን ሰነድ በምን ልለውጠው እንደምችል መገመት ያቅትዎታል?"

"በቀጥተኛ አማርኛ ምን እንደምትፈልግ አስረዳኝ!"

ጠበቃው ከኪሱ የሲጋራ ፓኮ አውጥቶ አንድ ፍሬ ወስደና አቀጣጠለ። በዐይኖቹ መንገሻን እየሰረቀ ያያቸዋል። በመጨረሻዋ ደቂቃ ድፍረት በማጣቱ የእጁ ጣቶች መንቀጥቀጥ ልቡ በፍጥነት መምታት ጀምሯል። ለረጅም ጊዜ በዝምታ ሲያሰብ ቆየና "ደህናI በህይወቴና በመላው ንብረቴ የገዛሁትን ሰንድ ለእርሶ በምን ያህል እንደምለቅልዎ ሰገምት እጅግም ብዙ እንዳልጠየኩዎት እገምታለሁ..."

"ምን ያህል ትፈልጋለህ?!" መንገሻ ድንገት ከጣራ በላይ ጮኹ።

"እ ... አብነትን ምን ያህል እንደምወዳት ያውቃሉ?"

"ይህ ለወደድካት ሴት አባት የሚቀርብ ጥያቄ አይደለም"

"ጥሩ... እንግዲያውስ በኔ ግምት በሁለት ጉዳዮች ላይ ብንስማማ ሁሉም ነገር መስተካከል የሚችል ይመስለኛል..."

"አንደኛ" አሉ መንገሻ እየተቁነጠነጡ።

"አንደኛI አብነትን እንዳገባ ሁኔታዎችን ሁሉ ያመቻቹሉ!"

"ሁለተኛስ?!"

"ሁለተኛም... ጋብቻችን ከመፈጸሙ በፊት ድርጅቱንና የድርጅቱ ንብረት የሆነውን የመጨረሻ ሽራፊ ሣንቲም ሳይቀር በስጦታ ያበረክቱልኛል!"



መንገሻ ከመቀመጫቸው ተፈናጥረው በመነሳት በጠበቃው ላይ ቁልቁል አፈጠጡበት። ፀጉራቸው ቀጥ ብሎ ቆሟል የተንጠለጠሉት ዐይኖቻቸው ደም አርግዘዋልI ከንፈራቸው ይንቀጠቀጣል። ከአንደበታቸው የወጣ ቃል ግን አልነበረም።

ጠበቃውም ፈጥኖ ተነሳና ቆመ። ከፊት ለፊቱ የቆመው ሞት ጉሮሮውን አንቆ እንዳይዘው የሰጋ ያህል ወደ ኋላው በማፈግፈግ በመካከላቸው ያለውን ርቀት አሰፋው።

"ይቀመጡ ጌታዬ..." እያለም በደነገጠ ገጹ ላይ አስቂኝ የሚያስመስለውን ፈገግታ ለማሳየት ሞከረ።

"አሳማ ነህ! ለሆድህ ታማኝነትህን የሸጥክ ከንቱ!" ጥርሶቻቸውን ደጋግመው አፋጩ።

"አይቆጡ ጌታዬ ስህተት የሠራሁ አልመሰለኝም። እዩ... አብረን በሠራንባቸው ዐመታት ውስጥ ስለራስዎ የህይወት ታሪክ አጫውተውኛል። እና በዚያ ታሪክዎ ውስጥ ምንጊዜም ከህሊናዬ የማይጠፋ አንድ ነገር ይታወሰኛል። ከሽማግሌው ባልያናዊ ጋር ያሳለፏቸው ትዕግስት አስጨራሽ የመጨረሻዎቹ አመታት! 'ህይወት የህይወት ጥያቄ ነች' ነበር ያሉኝ? 'ሰው ሆኖ የመኖር ወይም ያለመኖር ፈተና' ያንን ታሪክ ሲነግሩኝ ልቤ በሰሩት ስራ ፈረደልዎት እንጂ አልፈረደብዎትም። ለምን? እንዳሉትም ህይወት የህይወት ጥያቄ ነበረችና። እና ለምን ዛሬ በኔ ይበሳጫሉ? እኔም ዛሬ ልክ ያኔ እርሶ የነበረዎት የማደግና ትልቅ የመሆን ወኔ ነፍሴን ወጥሮ ያስጨንቃታል ...መተንፈስ መቻል አለብኝ ጌታዬ!" ገጹ በድል አድራጊነት ፈከቷል። መንገሻ የጠየቃቸውን ሁሉ ሰጥተው ነፍሳቸውን ማትረፍ እንደሚመርጡ ቅንጣት ያህል ባለመጠራጠሩ፣ የድርጅቱን በሚሊዮን ብሮች የሚገመት ሀብት ብዙም ሳይቆይ በደረት ኪሱ እንዳስቀመጠው የብር ቦርሳው የራሱ ያደርጋል።

"ክፍሉን ለቀህልኝ ልትወጣ ትችላለህ?!" መንገሻ ሀውልት መስለው ከቆሙበት ጮኹ።

"በሚገባ እንጂ ጌታዬ... መልስዎን የሚያሳውቁበትን ጊዜ ብቻ ይንገሩኝ"

"አንድ ወር!"

"አሥራ አምስት ቀን ይበቃል!"

መንገሻ ከብዙ ቆይታ በኋላ በእሽታ ራሳቸውን ወዘወዙ።

"ባንድ ሌላ ጉዳይ ላይ ደግሞ ባስጠነቅቅዎት እፈልጋለሁ። ሀይወቱን ለማስጠፋት ወይንም እኔን በማሳፈንና በማስገደድ ሰነዱን ከእጄ ለማግኘት እንዳይሞክሩ። በኔ ላይ ማንኛቸውም አይነት አደጋ በደረሰ በማግሸ ሰዓት ውስጥ ሰነዱ ፖሊሶች እጅ የሚገባበት መንገድ ሁሉ ተመቻችቷል። እና ሊደርስ የሚችለውን ችግር በቅድሚያ እንዲያውቁት ይሁን! ጤና ይስጥልኝ" አለና ጠረጴዛው ላይ አስቀምጦት የነበረውን ቦርሣ አንስቶ እየተቆናጠረ ክፍሉን ለቆ ወጣ።

"ከትቢያ ወደ ትቢያ!" ጠበቃው የቢሮውን በር ዘግቶ እንደወጣ ከአቶ መንገሻ አንደበት የወጣው ቃል ነበር ።መጀመሪያ ቀስ ብለው፣ እየቆዩ ግን ክፍሉ እስኪንቀጠቀጥ ድረስ መሳቅ ጀመሩ። በህይወታቸው ለመጨረሻ ጊዜ ያለቀሱት መች እንደሆን ትዝ አይላቸውም። አሁን ግን የእንባ ጠብታዎች ጉንጮቻቸው ላይ ነጠሩ። እየሳቀ የሚያለቅስ አረጋዊ ፊት! ከጥቂት ቆይታ በኋላ አዛውንቱ ንፅህና ቤት ሄደው ፊታቸውን ታጠቡ። ቁጣውና እልሁ ትንሽ በረድ ብሎላቸዋል። ወዲያውኑ መኪናቸውን አስነስተው በዝግታ ወደ መኖሪያ ቤታቸው አዘገሙ።

አብነት እናቷ ለጠበል ወደ ክፍለ ሀገር ስለሄዱ ለአባቷ ምግብ ለማዘጋጀት ማድቤት ውስጥ ተፍ ተፍ በማለት ላይ ሳለች አባቷ እንደሚፈልጓት ስለተነገራት ፒጃማዋን እየጎተተች ወደ ሰፊው ሳሎን አመራች።

መንገሻ ትልቁ ሶፋ ላይ ካፖርታቸውን እንደለበሱ እግራቸውን አጣምረው ኩርምት ብለው ተቀምጠዋል። ስትገባ በእጃቸው ምልክት ሰላሳዩዋት አጠገባቸው ካለው ሶፋ ላይ ተቀመጠች። ከገጽታቸው መከስል አንድ ክፉ ነገር እንደአጋጠማቸው ለመገመት ችላለች። ነፍስ አውቃ የአባቷን ማንነት ከለየችበት ጊዜ ጀምሮ እንደዚያ ተሸማቀው ያየችበት ጊዜ ትዝ አይላትም።

"አብነት..."

"አቤት"

"ተሸነፍን"

"አልገባኝም አባባ..."

"የፈራሽው ነገር ደርሷል። ሰነዱ በጠበቃው እጅ ገብቷል!"

ከበረዶ የቀዘቀዘ አንድ ነገር ሆዷ ውስጥ ሲሳወስ፣ አንጎሏ በጭንቅላቷ ውስጥ ማዕበል እንደሚንጠው ውቅያኖስ ሲተራመስ ታወቃት። ዐይኖቿ የሚያዩት ብርሃን ደበዘዘባት።



"ሰነዱ በእጁ እንደገባ እንደ ኳስ እየነጠረ ይጫወትብናል' ነበር ያልሽው? ትክክል ገምተሻል" የሚናገረው አፋቸው ብቻ እንጂ መላው ሰውነታቸው ከእንቅስቃሴ ውጭ ነው።

"በሰነዱ ልዋጭ የጠየቀው ምንድነው?" አለች አብነት ከንፈሯ እየተንቀጠቀጠ።

"መጠየቅ የሚችለውን የመጨረሻ ጥያቄ ነው የጠየቀው። አንቺንና ጠቅላላ የድርጅቱን ንብረት! በአንድ ጠጠር ሁለት ወፍ እንዲሉ ያለኝን ሁሉ ሊነጥቀኝ ታጥቋል።"

"ከመጀመሪያ ነበር የተሳሳትከው፣ በእሳት እየተጫወትክ እንደነበር ደጋግሜ ነግሬሃለሁ፣ አስጠንቅቄሃለሁ..."

"አብነት፣ አሁን ስላለፈው ስህተት የምንወቃቀስበት ጊዜ አይደለም። በዚያ ጊዜ የነበረኝ የመጨረሻው አማራጭ ጠበቃው ብቻ ነበር። ወጣም ወረደ ጠበቃው አሸንፏል። አሁን ምን ማድረግ እንደሚገባን ብንነጋገር ይሻላል"

"እንዴት አባባ?..." የአብነት ትንፋሽ መቆራረጥ ጀመረ።

"ጥያቄውን መቀበሌን ወይም አለመቀበሌን እንዳሳውቀው የሰጠኝ የአሥራ አምስት ቀን እድሜ ብቻ ነው"

"ጥያቄውን ባትቀበልስ?" አብነት መናገሯን እንጂ ምን እንደምትናገር እንኳን አታውቀውም፣ ሁሉም ነገር ተመሰቃቅሎባት ደንዝዛለች።

መንገሻ በቅሬታ ፈገግ አሉ "ሰነዱን ለፖሊሶች ያስተላልፋል፣ ያኔ ድርጅቱና የኔም ህይወት አበቃለት ማለት ነው"

"ጥያቄውን ብትቀበልስ?"

"አንቺን ያገባል፣ የአብነት አስመጭና ላኪ ድርጅት ቁልፍ ከመጨረሻዋ የሳንቲም ሽራፊ ጋር በስጦታ ይቀርብለታል"

"ባርባሪያን!" አለች የእልህ ሲቃ ጉሮሮዋን እያፈናት። ጥርሶቿን አፋጨችና ግንባሯን በምሬት ቋጠረች።

መንገሻ የፊቷን መለዋወጥና እልኋን ሲያስተውሉ ቆይተው በቅሬታ ፈገግ አሉ። ወንድ ሆና ተፈጥራ ቢሆን ከዚህ የችግር አዘቅት ውስጥ ባልገባሁም ነበር አሉ በልባቸው።

"እነዚህን ሁለት ምርጫዎች ልንዘል የምንችልበት ሌላ አማራጭ መንገድ የለም?"

"ምንም!"

"እና ምን አሰብሃል?"

"የጠየቀውን መፈጸም!"

ከመቀመጫዋ ተፈናጥራ ተነሳችና ቆመች። ሰውነቷ ይንቀጠቀጣል፤ ትላልቅ ዐይኖቿ ፈጠዋል። "ት... ትቀልዳለህ አባዬ!" አለች በመከራ ከአንደበቷ ባፈናጠረቻቸው ቃላት።

መንገሻ በቅሬታ ራሳቸውን እየወዘወዙ ዝም አሏት። "ለዚያ የሰው ጭራቅ አሳልፌህ ልትሰጠኝ? እጅና እግሬን ጠፍረህ ወደ ሲኦል እንደወረወርከኝ እወቅ"

"ምርጫ የለኝም አብነት... በተኩስ ልውውጡ ምክንያት የሞተው ሻምበል ወገን የሆኑ ባለስልጣኖች ስጋዬን በጫጭቀው ነፍሴን ሊቀራመቷት እየተቅበዘበዙ ነው። የሰነዱ በእጃቸው መግባት የሚያስከትለው ጣጣ የሚጠናቀቀው የኔን ህይወት በመሰዋት ብቻ መሆኑን አትዘንጊ"

"አባዬ..."

"አብነት፣ ህይወቴ በእጆችሽ መዳፍ ውስጥ ነች። የአባትነት ውለታዬን የምትከፍይበት ሰዓት ቀርባለች። ውሳኔሽን ባንድ ሳምንት ጊዜ ውስጥ እንድታሳውቂኝ ይሁን" አሏት ከመቀመጫቸው ተነስተው። ቁመታቸው ያጠረ መሰላት። ቀጠን ያለው ሰውነታቸው ጭራሽ ጠውልጎ ታያት። በለበሱት ሰፊ ስፖርት ውስጥ ብቅ ያለው ቀጭን አንገታቸው በሁለት እግሮቹ የቆመ ረዥም ኤሊ እንዳስመሰላቸው ታዘበች።

"አማራጭ የለም አልከኝ?!" ከፈጠጡት ዐይኖቿ እንባ መዝነብ ጀመረ። የደሟ ኡደትም እየፈጠነ ሄደ።

መንገሻ ራሳቸውን በአዎንታ ነቀነቁ።

"ብዙ ጊዜ ወንድ ልጅ ባለመውለድህ ስትፀፀት፣ ሴት ሆኜ በመፈጠሬ ስትማረር ሰምቻለሁ። አሁን ግን ሌላ አማራጭ እንዳለ አሳይሃለሁ ... ጠበቃውን እገድለዋለሁ!" አለች በሚንቀጠቀጥ ድምጽ።

መንገሻ በቅሬታ ፈገግ አሉ "አብነት!"

"ይህ ቃሌ ነው...እገድለዋለሁ! እገድለዋለሁ! ... እገድለዋለሁ!"

"አብነት..."

ረጅሙን ፒጃማዋን ሰብስባ የሳሎኑን በር በሃይል ዘግታ ወጣች። የመኝታ ክፍሏን በር ከውስጥ ቆለፈችና አልጋዋ ላይ ዘፍ ብላ በመውደቅ ሰውነቷ እየተንዘፈዘፈ ማልቀስ ጀመረች። "ቻርሊ ...እስከመቃብር ካንተው ጋር ነኝ፤ ብኩዳህ የቆምኩበት ምድር ይከዳኝ!" የሚለው የገዛ ቃሏ በምድረ-በዳ ብቻውን እንደሚጮህ ቁራ ጭንቅላቷ ውስጥ አንቋረረ።



አንደበቷ እየደጋገመ እገድለዋለሁ! እገድለዋለሁ! እገድለዋለሁ! ይላል። አዕምሮዋ ግን ማሰብ አቁሟል። ባራቱም ማእዘን ጨለማ! ባራቱም ማእዘን ሊዘለል የማይቻል አሾሃማ የብረት አጥር! በያቅጣጫው ካፈጠጠባት አደጋ ራሷን ለመሰወር ጭንቅላቷን በአሸዋ ውስጥ እንደምትቀብር ሰጎን የደረበችውን ጋቢ አንስታ ተከናነበችና ጮኸች "አምላኬ እባክህ እርዳኝ!"

## ምዕራፍ አሥራ ስምንት

እንቅልፍ ባይኗ ሳይዞር ስትወራጭ ያደረችበት ሌሊት በብርሃን ተሸንፎ ንጋት ሲገን የለበሰችውን ብርድ ልብስ ከላይዋ ወርውራ ተነሳች። ውሳኔዋን እንድታሳውቅ ከተሰጧት ሰባት ቀኖች አንደኛው አለፈ። ፊቷን ታጥባ ሻይ ከቀመሰች በኋላ ቦርሳዋን አንጠልጥላ ወጣች።

ቤት መዋል አልፈለገችም። ወደ ሥራ መሄድም አላሰኛትም። ሌሊቱን ሙሉ አንድ ሺ አንድ አይነት ውስብስብ የሃሣብ ድሮች ሲጠነጠኑበት ያደረውን አዕምሮዋን ለማሳረፍ ወደ ሰዓሊው ቤት መሄድ መረጠች።

ሠዓሊው ግቢው ውስጥ ይንጎራደድ ነበር። ዘወትር ይደርበው የነበረውን ካፖርት አልለበሰም። በምትኩ ወይን ጠጅ ቀለም ያለው አዲስ ሸሚዝ ለብሷል። ክራባትም አስሯል። የሚያንፍረው ጢሙን ተላጭቶም ፀጉሩን በወጉ ተስተካክሏል። እንዲህ አይነት ለውጥ በሰዓሊው ላይ ስታይ የመጀመሪያ ጊዜዋ ነው። በመገረም የፈጠጡ ዐይኖቿን እያንከባለለች ቆማ ታስተውለው ጀመር።

ገና ሲያያት "ምነው አቢ በጠዋት! ... ደህና?" አለና በስጋት በሚቁለጨለጩ ዐይኖቹ መረመራት ።

ሥራ መግባት እንዳላሰኛትና ከርሱ ጋር ለመዋል እንደመጣች ስትነግረው በደስታ እየተፍነከነከ "ብራቮ ቀይዋ ድንቢጥ! ዛሬ ቁርስ ከማዘጋጀት አዳንሽኝ" እያለ አጨበጨበ።

የሚወደውን ከእንቁላል ጋር የተጠበሰ ስጋ ከሠራችለትና አብረው ከተመገቡ በኋላ ከመጠጥ መያዣው ትልቅ ቦርሳ ውስጥ የቪኖ ጠርሙስ አውጥቶ በብርጭቆው እየቀዳ መጠጣት ጀመረ።

"ልክ እንደ ልጅነትሽ ዳግም በመንፈስ አንድ የሆንን መሰለኝ አቢ። ሉንቺን ሥራ መሄድ እንዳስጠላሽ ሁሉ እኔም ዛሬ ከቤት መውጣት ቀፎኛል" አላት በብርጭቆው ከቀዳው ቪኖ ውስጥ የምትንሳፈፈውን የቡሽ ሽራፊ በትንሽ ጣቱ ለማውጣት እየታገለ።

ትክ ብላ ተመለከተችው። ፊቱ መብለዝ ጀምሯል፤ ዐይኖቹ ደፍርሰዋል፤ ጣቶቹ ይንቀጠቀጣሉ። በዚህ ከቀጠለ በአልኮል የተነሳ በቅርቡ ጉበቱን እንደሚተፋ ገመተችና ከልቧ አዘነችለት።

"ስዕልህን አጠናቀቅህ እንዴ ጋሸዬ..."



"የቱን?"

"'የደም ጎርፍ' የሚለውን አብስትራክት?"

ግራ እንደገባው ዓይነት አፍጥጦ ሲመለከታት ቆየና "ስእል ላለመሥራት ከወሰንኩ ቆየሁ እኮ..." አላት የእጆቹን ጣቶች እያፍተለተለ።

"ምነው?" አለች አብሯት በቱራዋ ግራ የተጋቡ ዐይኖቿን እያቁለጨለጨች።

"የትንሿ ዓለሜ ብርሃን እየደበዘዘች ነው አቢ። በትልቁ ጨለማ ጽልመት ልትዋጥ ምንም አልቀራት። አንድ ቀን ስእል እሠራበት የነበረውን ቀለም የጠቀሰ ብሩሽ ወርውሬ ቁጭ አልኩና አሰብኩ። ከየት ተነስቼ የት እንደደረስኩ የገዛ ህይወቴን መመርመር ያዝኩ። በነዚያ ራሴን በረሳሁባቸው ዓመታት ውስጥ ለጥበቡ የጨመርኩት አዲስ ነገር፣ ለዓለም ያሳየሁት አዲስ ብርሃን ምን እንደሆነ መፈተሽ ጀመርኩ። ምንም የለም! ተራ ሰው ነኝ አቢ ..."

"ጋሼ!" በማለት አፏን እንደያዘች ጮኸች። ተስፋ የቆረጠ ገጽታውን ስታይ እንባዋ ከውስጥ ይተናነቃት ጀመረ።

"የኔ የምላት ትንሿ ዓለሜ ተረት ነበረች። የኖርኳቸውም ዓመታት በህፃናት ልብ ወለድ መጽሃፍት ውስጥ እንዳሉት ህይወት ተረት ተረት የተጫወትኩባቸው የባከኑ ዓመታት ናቸው። በስዕሎቼና በህዝብ ዐይኖች መካከል ያለው ርቀት በጣም ሰፊ ነው ... በዚህ እንኳን አልተከፋሁም። አሁን ግን የገዛ ሥራዎቼ ለራሴም ሚስጥር እየሆኑብኝ ተቸግሬ እንደነበር ልደብቅሽ አልፈልግም። ራሴን እያታለልኩ መሆኑን የተረዳሁት ዘግይቼ ነበር። አየሽ በህይወትሽ ራስሽን እያታለልሽ እንደመኖር ያለ የከፋ ወንጀል በራስሽ ላይ ለመፈፀም አትችይም። ከአንቺ የምደብቀው ሚስጥር የለኝም አቢ ... የገዛ ሥራዎቼ ሃሣብ እየተደበላለቀብኝ መንፈሴን ቢያመሳቅለው መላእክት ከሰማይ ወርደው እንዲያብራሩልኝ መጸለይ ብቻ ነበር የቀረኝ። የጥበቡን ሚስጥር አውቄ ጫፍ ደርሻለሁ ባልኩበት ሰዓት ምንም አለማወቄን አወኩት ... አሁን ይህን ጥያቄ ለምን ጠየቅሽኝ?!" አለና ጭንቅላቱን በሁለት እጆቹ እንደያዘ አቀረቀረ።

"ጋሼ ... ከነዚያ ሁሉ አድካሚና አሰልቺ ዓመታት በኋላ እንዴት ተሸንፋለህ?" ብስጭትና እልህ በተቀላቀለበት ስሜት ጮኸችበት።

"በዚያ ቀን የወረወርኩትን ብሩሽ ዛሬም እላነሳሁትም ... ባንድ ነገር ግን እርግጠኛ ነኝ አቢ ... አልተሸነፍኩም! እንደገና ወደ ፈረንሳይ ሄጄ የስእል ጥናቴን እጀምራለሁ" አላት አንገቱን እንዳቀረቀረ።

"እውነትህን ነው ጋሽዬ?"

"የምር። ራሴን እያታለልኩ መኖር አልችልም ... እስከዚያው ግን እጠጣለሁ"

በምፀት እየ..የ በብርጭቆ የሞላውን ቪኖ ባንድ ትንፋሽ አጋባው።

"ጋሽዬ... ግን ለምን ይህን መጠጥ የሚሉ ነገር እርግፍ አድርገህ አትተውም? እየጎዳህ እንደሆነ ይታወቅሃል?" አለች በልጅነቷ ዓመታት ታውቀው የነበረው ገጽታው በልዞ በማየቷ ከልቧ እያዘነች።

ካቀረቀረበት ቀና ብሎ የደፈረሱ ዐይኖቹን በመበልጠጥ ሲመለከታት ቆየና "ትቀልጃለሽ አብነት?! እኔ ሰዎች ሁሉ ለምን አይጠጡም እያልኩ ሲደንቀኝ መጠጥ ተው ትይኛለሽ?" አላት በሃዘኔታ ጭንቅላቱን እየወዘወዘ በንዴት እየተንጨረጨረ።

"ታዲያ እንዲህ የምትሆነው ለምን ትጠጣለህ ስላልኩህ ነው?" አለችና ለንቦጯን ጣል አደረገች።

"አዎን አቢ ... በዚህ ምድር ላይ በጣም የሚያናድዱኝ ሰዎች ሰዎችን እንምከር የሚሉ ሰዎች ናቸው። ግብዞች ነው የሚመስሉኝ፤ ጉረኞች። ራሳቸው ከእግር ጥፍር እስከ እፍንጫቸው ቀዳዳ ድረስ በችግር ባህር ተዘፍቀው በሌሎች ላይ የሚያዩትን ጉድፍ ለመንቀስ ሲንጠራሩ ያናድዱኛል"

"እንዴ! ታዲያ እዚህ ድረስ አይበቃም?" አለችው አብነት ብስጭት ብላ።

"ይበቃል አቢ፤ ዛሬ እኔን መጠጥ እንዳልጠጣ ለመምከር እንዳልመጣሽ እርግጠኛ ነኝ... አንድ ችግር እንዳጋጠመሽ ደግሞ አልጠራጠርም... ልትነግሪኝ የምትፈልጊው ነገር አለ..." አለና ድንገት አፈጠጠባት።

በውስጧ መቀጣጠል ጀምሮ የነበረውን ንዴት ለማብረድ በረዥሙ ተነፈሰችና ዝም አለች። ከሰዓሊው የምትደብቀው ሚስጥር የላትም። በተለይ አሁን ዓለም ፊቷን ባዞረችባት፣ እርቃኗን የቆመች ያህል ሀፍረትና ብቸኝነት በሚያሸማቅቃት ሰዓት የሰዓሊውን እለሁልሽ ባይነት ከምንም በላይ ትፈልገዋለች።



"እንዳልከውም በችግር ላይ ነኝ። ከየት እንደምጀምርልህ ደግሞ አላውቅም"

"ግድ የለም፣ ከመጨረሻው ጀምረሽ በመጀመሪያው ጨርሺው"

"ትቀልዳለህ ጋሽየ?"

"አቢ፣ ስለፈጠረሽ ምን እንደሆንሽ ንገሪኝ!"

"ህይወቴ ከፍተኛ አደጋ ላይ ነች..." ከመጨረሻው ጀመረችለት። የህይወቷን ምስቅልቅል አፍረጥርጣ አጫወተችው። ከአንድ አንገብጋቢ የግሏ ጉዳይ በቀር የደበቀችው ምንም የለም።

የያዘውን ሲጋራ ዘንግቶ እሳቱ እጁ ላይ እስኪጠፋ ድረስ በታሪኳ ተመስጦ ሲያዳምጣት ቆየ። ስትጨርስ ከእንቅልፉ እንደባነነ ዓይነት ራሱን ወዘወዘና የጠፋውን ሲጋራ እንደገና አቀጣጠለው። በጥልቅ በሚያስተውሉት ዐይኖቹ ለረዥም ጊዜ ሲመረምራት ቆይቶ "አንድ የደበቅሽኝ ሚስጥር አለ አብነት..." አላት።

በፍጥነት መምታት የጀመረ ልቧን ለማፈን በሁለት እጆቿ ደረቷን ተጭና ያዘች።

"ም ... ምንድ ነው?" አለችው በድንጋጤ የፈጠጡ ዐይኖቿን እያርገበገበች።

"እዝናለሁ አቢ፤ ትንሿን ቀይ ድንቢጥ በነበርሽ ጊዜ እንደምን ቅንና ንጹህ ልብ የነበረሽ ቅድስት ልጅ ነበርሽ?! አሁን ግን በመንፈስሽ አድፈሽ፣ በስጋሽ ረክሰሽ አየሁሽ ... ውው! በጣም ተራርቀናል ማለት ነው አቢ? ሚስጥርሽን እንኳን ደበቅሽኝ!" አለና ራሱን በሀዘኔታ ነቀነቀ።

"ምን እንደምታወራ እኮ አልገባኝም ጋሽዬ?"

"ሀ... የደበቅሽኝን እውነት ከእኔ አንደበት መስማት ትፈልጊያለሽ?"

አብነት አልመለሰችለትም።

"ከቻርሊ ፀንሰሻል!"

ከተቀመጠችበት ወንበር ላይ እንደ ኳስ ነጥራ ተነሳችና ወደ ኋላዋ አፈገፈገች። ልክ ከአንድ አይነት ክፉ መንፈስ ጋር የተፋጠጠች ያህል የሰዓሊውን ዐይኖች ማየት ቀፈፋት። ከርሷ በቀር ቻርሊ እንኳን የማያውቀውን የብቻዋን ሚስጥር ሰዓሊው እነፍንፎ ደረሰበት! ከፍሉን ጥላ ለመሮጥ ወደ በሩ ገልመጥ ስትል ከተቀመጠበት ተነስቶ ክንዷን ጨመደደና ባለችበት አቆማት።

"እ... እንዴት አወቅክ?" ሳታውቀው ጆሮ ግንዱ ላይ ሙኸችበት።

"ምን ጊዜም አስከፊውን ነገር እንምት ነበር አቢ.... ግና ከልጅነትሽ ጀምሮ ህይወትሽ ምስቅልቅል እንቆቅልሾች የሞሉበት እንደሚሆን ደመ-ነፍሴ ይነግረኝ ነበር" አለች ከንፈሯን አጥብቆ እንደያዘ።

ጨምድዶ የያዛትን እጇን መንጭቃ አላቅቃ ሶፋው ላይ ተቀምጣ ማልቀስ ጀመረች።

"ግና ከልጅነቴ ዓመታት ጀምሮ እጣ ፈንታየ ይሄ ነበር ማለት ነው?" በህሊናዋ ውስጥ የሚመላለሰው ጥያቄ ይህ ብቻ ነበር።

"ደምግባት ¸ እዳው ብዙ ነው አቢ! ውበትን ተከትሎ የሚመጣው ችግር ፈተናው እልህ ጨራሽ ነው። እና አብነት ... እንባሽ ወኔሽን ማምከኛሽ እንጂ መፍትሔ አይደለም። ጊዜው ከማለፉ በፊት ወስኚ!" አላት ሰዓሊው።

አብነት አንገቷን ከደፋችበት ጭኗ ላይ ቀና አድርጋ "በህይወትና በሞት መካከል ባለ መንታ መንገድ ላይ የቆምኩ መሆኔን ያስተዋልኩት አሁን ነው። ምን እንድወስን ትመክረኛለህ?" ስትል ተማጸነችው።

እጆቹን የኋሊት አጣምሮ ክፍሉ ውስጥ ሲንጎራደድ ቆየና በግድ የለሽነት ትከሻውን ሰበቀ። "በሰዎች ጉዳይ ውስጥ አፍንጫዬን መንከር እንደማልፈልግ ነግሬሻለሁ! አንቺስ ብትሆኝ በገዛ ህይወትሽ ውስጥ የሌሎችን ጣልቃ ገብነት ለምን ትጋብዣለሽ?... የገዛ ጭንቅላትሽን ተጠቅመሽ ሰው መሆንሽን ፈትኚበት" አላትና በርጋታ እየተራመደ ወደ ቀዳው ቪኖ በመሄድ ከጠረጴዛው ላይ አንስቶ ተጎነጨለት።

ከተቀመጠችበት ሶፋ ላይ ሆና አሰልቺ የሆነባትን ንግግር ስታዳምጥና እንቅስቃሴውን ስትመለከት ቆየች። በህይወቷ ለመጀመሪያ ጊዜ ሰዓሊውን ጠላችው። ከምንም በላይ አንድ የስነጥበብ ሰው ሊኖረው የሚገባው የሰብአዊነት ስሜት ከውስጡ ተንጠፍጥፎ ያለቀ ስለመሰላት ከልቧ አዘነችበት። "አሁን አንተን ስለሚያስደስትህና ስለሚያስጠላህ ነገር መስማት አልፈልግም። በከፍተኛ ችግር ውስጥ እንዳለሁ እያወቅህ አለሁልሽ ልትለኝ በሚገባ ሰዓት ብቻዬን ትተወኛለህ?" እያለች ተንጣጣችበት። ሠዓሊው ግን ምንም እንዳልተናገረችው ሁሉ ጭላጭ



ታህል የቀራትን የቪኖ ጠርሙስ ከቆዳ ቦርሳው ውስጥ ከከተተና ብርጭቆውን ቦታው ከመለሰ በኋላ "አዝናለሁ አብነት፤ ዘግይተሻል በቤ አቅም ልረዳሽ የምችልበት ሰዓት አልፏል" አላት ተስፋ በቆረጠና በሰለቸ ድምጹ። ብዙ ሳይቆይም ክፍሉን ጥሎላት ወጣ።

የቪኖ፣ የሲጋራና የአቧራ ሽታ ተቀላቅሎ አፍንጫን በሚተናፍግበት ክፍል ውስጥ ብቻዋን ቀረች። የእንባዋን ኩሬ ተንጠፍጥፎ ዐይኖቿ ኳ ብለው የደረቁ እስኪመስላት ድረስ ጭኖቿ ላይ ተደፍታ አለቀሰች። ብዙ ቆይታም ከሶፋው ላይ ተነሳችና ሰዓሊው እንደሚያደርገው እጆቿን የኋሊት አጣምራ ክፍሉ ውስጥ መንጎራደድ ያዘች። ቁጥር ስፍር የሌለው ሃሳብ በህሊናዋ ውስጥ ይንጫጫል። ከግድግዳው ወለል ላይ እያረፈ የሚነሳው የኮቴዋ ድምጽ "ተጠንቀቂ፤ ተጠንቀቂ! ተጠንቀቂ!" እያለ ያስፈራራታል። የአባቷ የአቶ መንገሻ ገጽ ደግሞ ኩስትር እንዳለ ብቅ ይልና "ወልዶ ለዚህ ያበቃ አባት ውለታ ይህ ነው?" እያለ ያፈጥባታል። የቻርሊ ገጽታ በተራው ብቅ ይልና "አይ ሰው ከንቱ! ቀድሞም እኮ ብዬሻለሁ አብነት። ለዚህ ዘመን ሰው የቃል ዕዳ ገብስ ነው። አንቺ እኔን በፀፀት ጅራፍ ለመግረፍ የተፈጠርሽ አጥፊዬ መሆንሽን ያየሁሽ ቀን ደመ-ነፍስ በጆሮዬ ሹክ ብሎኛል፤ ከህዲ! ከህዲ!" ይላታል።

ይኸኔ ጆሮዎቿን በእጇ ደፍና "ቻርሊ!" ብላ ሙኸች። የሰማት ግን አልነበረም። እየተወላገደች ሄዳ ተቀምጣበት በነበረው ሶፋ ላይ ዘፍ አለች። የዛለው ሰውነቷና የተዳከመው አዕምሮዋ በእንቅልፍ ለመረታት ጊዜ አልወሰደበትም።

የሞት ያህል ጭልጥ አድርጎ ከወሰዳት እንቅልፏ ስትነቃ ሰዓሊው ፊት ለፊቷ ባለው ሶፋ ላይ እግሮቹን አጣምሮ ጉንጩን በእጁ ደግፎ በርህራኄ ዐይን ይመለከታታል። እንቅልፍ ያልጠገቡ ዐይኖቿን እሻሸችና ሰዓቷን ተመለከተች። 9:00 ይላል። ልቧ በፍጥነት መምታት ጀመረ።

ፈጥና ተነሳችና ልብሷን አስተካከለች፤ ፀጉሯን አበጠረች። ሰዓሊው ከተቀመጠበት ሳይንቀሳቀስ እያንዳንዷን እንቅስቃሴ በንቃት ይከታተላል። ቦርሳዋን ካስቀመጠችበት አንስታ ወደ በሩ እየተራመደች "አመሰግናለሁ፤ ደህና ሁን" አለችው።

"አቢ ... የኔ ውድ ቀይ ድንቢጥ... ለምን ትፈርጂብኛለሽ? አየሽ እኔ እኮ ራሴን እንኳን መርዳት የማልችል ከአንቺ ያልተሻልኩ ምስኪን ሰው ነኝ፤ ተራ ሰው ነኝ!"

በሩ ላይ ቆም ብላ በትዝብት ዐይን ስትመለከተው ቆየችና ፀጉን በሀይል ዘግታበት እየፈጠነች በመራመድ ግቢውን ለቃ ወጣች። በዓሊው የዘጋችበትን በር ከፍቶ ተመለከታት። በጣም ርቃ ሄዳለች አልተከተላትም። ምንም ሊያደርግላት እንደማይችል ያውቃል። ዳግመኛ እንደማይገናኙ ደመ-ነፍስ ሹክ ያለውን ያህል ከርሱ በጣም ርቃ የምትታየውን አብነትን ላለማየት ዐይኖቹን ሸፈናቸው። "እግዚአብሔር ካንቺ ጋር ይሁን አቢ" ሲል አጉተመተመ።

በርሱና 'ትልቅ ጨለማ' ብሎ በሚጠራው ዓለም መካከል ለብዙ ዓመታት ተዘርግቶ የቆየው ድልድይም በዚህ ሁኔታ ተሰበረ።



## ምዕራፍ አሥራ ዘጠኝ

ጀንበር ወጥታ በጠለቀችና በሌላይቱ በተተካች ቁጥር ነዊ ከሥጋዋ እየተሟገተች ትንሽ ትንሽ መሞት ጀመረች። ጨቢጣ ከጨረቃ ላይ ጠጠር ሲዘግኑ፣ ዓለምን በእፍታ የአመድ ክምር የሚያደርጋት መሣሪያ ሠራን ሲሉ፣ እንደምን የጊዜን ሂደት የሚያግት ልጓም መፈልሰፍ ተሳናቸው?! ምን ነበር ነገ የሚሉት ቀን ባይፈጠር? እሷስ ጀንበርስ ባትወለድ? ቀኑ ለምን ፈጥኖ ይመሻል? ሌቱስ ለመንጋት ምን አጣደፈው? ቻርሊን ከእቅፏ ሊነጥቃት?! በጠቢቃው መዳፍ ውስጥ ሊወረውራት?! ተኝታ ትወራጫለች፣ ተቀምጣ ትበረግጋለች። የሰው ልጅ አእምሮ ብዙ ሃሣብ በማጀሉ የሚፈነዳ ቢሆን እለት ተለት በጭንቅላቷ ውስጥ የሚታመቀው ጭንቀት እናቷን ቀዶ ይወጣ እንደነበር አልተጠራጠረችም።

ውሳኔዋን እንድታሳውቃቸው አባቷ የሰጧት ሰባተኛው ቀን አለፈ። ምሽት ላይ መንገሻ ሙሉ የሌሊት ልብሳቸውን ለብሰው መኝታ ክፍሏ ገቡ። ከአልጋዋ ትይዩ በነበረው ወንበር ላይ ሲቀመጡም ከተጋደመችበት ተነስታ በረዥሙ የሌሊት ልብስዋ ላይ ጋቢ ደረበችና አልጋዋ ጠርዝ ላይ ተቀመጠች። ፈገግታ ሊያሳዩዋትና በውሳኔዋ ነፍሳቸውን እንደምትታደግ እርግጠኛነታቸውን ሊያስተማምኗት ቢፈልጉም ከፈገግታቸው ጀርባ ጥርጣሬ እንዳፈጠጠ ተመለከተች። ውሳኔዋን እንድታሳውቃቸው የተሰጣት ሰባት ቀን የሰባት ሰከንድ ያህል ሮጦ አልፏል። መንገሻ የመኝታ ክፍሏን በር ከፍተው እስከ ገቡባት ደቂቃ እንኳን ውሳኔዋን አታውቅም።

አባቷም ስጋት ባጠላባቸው ዐይኖች ሲመለከቷት ቆይተው አንዳች ሳይናገሩ ከሌሊት ልብሳቸው ኪስ ውስጥ ፒፓቸውንና የትምባሆ ፓኬታቸውን አውጥተው በፀጥታ ፒፓቸውን በትምባሆ ይጠቀጥቁ ጀመር። ከሞት ጋር ፊት ለፊት የተፋጠጡ ያህል ቅጭም ያለ ግምባራቸውን ስትመለከት ኢምንትነት ተሰማትና መንፈሷ ተበተነ። ሰዓሊው ከልጅነቷ ጀምሮ በውስጧ ሲኮተኩት የኖረው በራስ የመተማመን መንፈስና እውነትን ይዞ በጽናት መቆም የሚለው እምነት በእፍታ ሲናድ ታወቃት። መተጣጠፊያዎቿ ሁሉ መብረክረክ እጆቿ መንቀጥቀጥ ጀመሩ። በግንባሯ ላይ ለብ ያለ ሙቀት ሲሰማት እያላባት መሆኑን አወቀች።

መንገሻ የትምባሆውን ፓኬት ከኪሳቸው መልሱና ክብሪት ጭረው ትምባሆውን አቀጣጠሉ። ጥያቄያቸውን ለመጀመር ከመቀመጫቸው ሲመቻቹም ባለቻት የመጨረሻ ሰከንድ "አምላኬ

እባክህን እርዳኝ" ስትል የጣር ጩኸቷን በውስጧ አቀለጠችው። በውስጧ የተቀጣጠለው ሽብር መላ ሰውነቷን ሲያንዘፈዝፈው ራሷን መታዘብ ጀመረች። አንድ ጊዜ ለቻርሊ ምን እንዳለችው ስታስታውስ በድንጋጤዋ ላይ ሃፍረት ተጨመረና ከሰውነቷ ሽምቅቅ አለች። በቴያትር ቤቱ ውስጥ ለቻርሊ የተናገረችው የገዛ ቃሏ ነቃሽ ሆኖ ሊያስፈርድባት ቃል በቃል በጆሮ ግንዷ ላይ ጮኸ።

"አንድ ነገር ልንገርህ? እንደሚገባኝ ልዩነታችን አንተ የጠቀስካቸው ብቻ አይደሉም። አንድ ሺ ልዩነቶች፣ አንድ ሺ መሰናክሎች፣ አንዲ ሺ ችግሮች እንደሚገጥሙን መገመት አላቃተኝም። ይሁን እንጂ፤ በኔ እምነት ፍቅር ጋራ የሚያክለውን መሰናክል የሚያሻግር ጉልበት፣ ፍቅር በውቅያኖስ ስፋት የተዘረጋውን ልዩነት የሚያጠብ ምትሃት፣ ፍቅር ታላቅ የተባለውን ችግር የጉድፍ ያህል የሚያስንቅ የልብ ትእቢት፣ ፍቅር የማይቻለውን ሁሉ የሚያስችል የነፍስ ሃይል ነው!" እሳት መትፋት በጀመሩ ዐይኖቿ እየለበለበች ያፈጠጠችበት ታወሳት። መስዋዕትነት የሚያስከፍል የቃል እዳ!

"ውሳኔሽን ልታሳውቂኝ ትችያለሽ?" መንገሻ የርሳቸው ባልሆነ ቀጭንና ሻካራ ድምጽ በክፍሉ ውስጥ ፀጥታው አስፍኖት የነበረውን ውጥረት ሰበሩት።

"ቻርሊ፤ እስከ መቃብር ከአንተ ጋር ነኝ። ብክዳህ የቆምኩበት ምድር ይክዳኝ!" በዚያች ዝናብ በሚያካፋባት ምሽት ከቻርሊ ጋር ትልቁን ዛፍ ተጠልለው እንደቆሙ የገባችው ቃል ዛሬም ለአንድ ሺ አንደኛ ጊዜ ትዝ አላት። የገዛ ቃሏን ከፊት ለፊቷ ከተቀመጡት አባቷ ህይወት ጋር መዘነችው።

"የምናገረውን አድምጠሽኛል?" የመንገሻ ድምጽ ይንቀጠቀጣል። ህይወት ዛሬም የህይወት ጥያቄ ነች። ዛሬ ለርሳቸው የመኖር ዋናው ቁም ነገር እንደ ሰው ከሰብአዊ ክብሩ መኖር ሳይሆን እስትንፋስን ማቆየት ነው። ዛሬ እስትንፋስ መኖር ከቻለች ሰውን ሰው ስለሚያደርገው ሰብአዊ ክብሩ ደግሞ ነገ ይታሰብበታል። ለዛሬ ብቻ አብነት ነፍሳቸውን ትታደጋት።

ቀና ብላ አየቻቸው። ከርሷ ባልተሻለ ሁኔታ ተደናግጠው አስተዋለች። በነኛ የሰከንድ ክፍልፋዮች ፍርሃታቸውን ማየቷ አጀገናት፣ ጥርጣሬያቸው ልብ አስገዛት። ከፊት ለፊቷ የተፋጠጠችው ከሞት ጋር ሳይሆን ከአባቷ ጋር መሆኑን አረጋገጠች።



"ጠበቃውን አላገባም!" አለች በሚንቀጠቀጥ ድምጽ። ስጋና ነፍሷ የደም ላብ እስኪያልባቸው ታግለው ከመቅኔዋ ጨምቃ የተፋችው ቃል እንደሆነ ሁሉ በእፎይታ ተነፈሰች።

መንገሻ በስለት የተወጉ ያህል ከሰውነታቸው ለአፍታ ሽምቅቅ አሉ። ዐይኖቻቸው አስፈሪ ቅርጽ ይዘው ተበለጠጡ። ከንፈሮቻቸው ይንቀጠቀጣሉ፤ በጥርሳቸው ነክሰው የያዙት ፒፓ ወድቋል። እንዲህ እንደሚሆኑ ገምታ ነበርና መጭውን ከተቀመጠችበት ሆና በቆራጥነት መጠባበቅ ጀመረች።

"እብድ ... ነሽ?"
"አይደለሁም!"
"እንግዲያውስ አረመኔ ነሽ?"
"አይደለሁም!"
"ታዲያማ ምን ልትሰኚ?!"

ከአብነት ዐይኖች እንባ መዝነብ ጀመረ። አባቷ በህይወታቸው በመጣ ነገር የምትሰጣቸውን ምክንያት እንዴት ብለው እንደሚቀበሉ ጨነቃት "አባዬ ..."
"እባክሽ ከእንግዲህ አባቴ አትበይኝ?"
"ለተዋናዩ ፍቅረኛዬ ቃል ኪዳን አለኝ"

ግራ የተጋቡ ዐይኖቻቸውን አፍጥጠው በአስፈሪ ሁኔታ ሲመለከቷት ቆዩና የወደቀውን ፒፓ አንስተው በዝምታ ማጨስ ጀመሩ። "እርግጠኛ ነኝ አብደሻል" አሉ ራሳቸውን በቅሬታ እየወዘወዙ።

"አላበድኩም" ራሷን እየወዘወዘች ጮኸች።
"ባታብጂማ እንድ አባትሽን ለወንድ አትለውጭኝም ነበር"
"በማንም አልለውጥህም። ቃሌን ግን አጠብቃለሁ"
"ለአንድ ተራ ተዋናይ ለወጥሽኝ ነገ ረግጦሽ ለሚያልፍ ሰው ሸጥሽኝ"
"ሃሰት ነው፤ በማንም አልለውጥህም"

እንደገና በዝምታ ተውጠው ማሰብ ጀመሩ። ቆይቶ አንድ ነገር የወሰኑ ይመስል ፈገግ አሉ። አብነት ምን እንዳሰቡ ለመንተበይ አልቻለችም። በዚያ ጥቁር ፈገግታ ውስጥ ግን አደጋ ታያት! ከአደጋም የከፋ አደጋ፣ ሞት እንደተደገሰ ደመ-ነፍሷ ጮሆ ነገራት።

በእርጋታ ከመቀመጫቸው ተነሱና እንደ ጦር ዐይን በሚወጋ የጥላቻ አስተያየት ተመለከቷት። እርጋታቸው ደግሞ ይበልጥ አብረከረካት ይበልጥ አንዘፈዘፋት።

"ሰይጣናዊውን አማራጭ እንድጠቀም አስገድደሽኛልና በውጤቱ አትፀፀች" አሉ ገጽታቸውን እንዳጨፈገጉ።

አብነት ሀውልት መስላ ደርቃ እንደተቀመጠች የመኝታ ክፍሏን በር በሃይል ዘግተው ጥለዋት ወጡ።

ሰይጣናዊው አማራጭ ማለት ምን እንደሆነ መገመት አላዳገታትም። ቻርሊ ሞት ተፈርዶበታል ማለት ነው!

መንገሻ ቻርሊን ያለ አንዳች ማስረጃ ማስወገድ የሚችሉ መሆኑን አልተጠራጠረችምና ከተቀመጠችበት ሆና ትንቀጠቀጥ ጀመር። ጊዜ ሳትፈጅ የመኝታ ቤቷን በር በጥንቃቄ ከፍታ በኮሪደሩ በማቋረጥ ወደ ሳሎኑ አመራች።

በሩ ገርበብ ብሎ ተከፍቷል። ጎንበስ ብላ በተከፈተው በርና በግድግዳው መሃል በተፈጠረው ክፍተት አጮልቃ ተመለከተች። አባቷ ጀርባቸውን ለበሩ ሰጥተው ስልኩን ይዘው ቆመዋል። ወዴት እንደሚደውሉ አልተጠራጠረችም። ናፖሊዮን አምባው ድርጅቱ ከሚገባበት አዘቅት ውስጥ መንጥቆ ለማውጣት የሰይጣናዊ አማራጭ የቀኝ እጅ መሆኑን ነግረዋታል!

በደረቷ ውስጥ የሚወራጨው ልቧ በጉሮሮዋ አፈትልኮ እንዳይወጣ የሰጋች ይመስል በሁለት እጆቿ ደረቷን ተጭና በመያዝ አባቷ የሚሠሩትን በጥንቃቄ መከታተል ቀጠለች። የስልኩን ቁጥር ደጋግመው ይሞክራሉ... ይሞክራሉ፤ ከወዲያኛው ጫፍ ግን መልስ የሚሰጣቸው አልነበረም። ሲሰለቻቸው የስልኩን እጀታ ወርውረው ወደ ሳሎን በር አመሩ። አብነትም ወደ መኝታ ክፍሏ ሮጣ በሩን ዘጋችና ከውስጥ ቆለፈችው።

ሰዓቷን ተመለከተች። ከምሽቱ 3 ሰዓት። የናፖሊዮን አምባው ገጽታ በአፍታ በህሊናዋ ተስሎ አሸበራትና "ነፍሰ ገዳይ!... ነፍሰ ገዳይ!... ነፍስ ገዳይ!" እያለች ጮኸች። አባቷ እንዳሉት አብዳ ይሆን?

በተከታዩ ቀን ረፋዱ ላይ ከቤቷ ሆና ቻርሊ ወደሚሰራበት ቲያትር ቤት ደወለች። አላገኘችውም። ከሰዓት በኋላም ሞከረች - ቻርሊ ሥራ እንዳልገባ ተነገራት። ዘጠኝ ሰዓት ላይ ልብሷን ለባብሳ



ወደ መኖሪያ ቤቱ ገሰገሰች፤ ከዚያ ነፍሰ ገዳይ እንዲጠነቀቅ መንገር ነበረባት።

ታክሲ ውስጥ ሆና የምታሰላስለው እንዴት ብላ እንደምትነግረው ነበር። እውነቱን አፍረጥርጣ ብትነግረው ሊደርስበት የሚችለውን የመንፈስ ስቃይ ገመተች። ጭራሽ የማይሞከር ነገር ነው። ስቃዩንና ውድቀቱን ከማየቷ በፊት በርሷ ላይ ሊደርስ የሚችለውን ማንኛውንም አይነት መከራ ለመቀበል ተዘጋጀች "በኔ ስቃይ የሚሰቀቅበት፣ የኔን የመከራ መከር የሚያጭድበት ምክንያት የለም ... ስለፍቅራችን እሰዋለሁ!" ስትል ወሰነች ።

ሰይጣን ሰፈር ደርሳ ኳይት ሀውስ ደጃፍ ላይ ስትቆም በሩ ተቆልፎ አገኘችው። ቡቾ ከቤቱ በር ላይ ተቀምጦ ግድግዳውን ተደግፎ ያንጎላጃል።

"ማሙሽ... ማሙሽ... አንተ..." ትከሻውን እየነቀነቀች አነቃችው። ቡቾ እየተንጠራራና እያዛጋ ተነስቶ ቆመ።

"ቻርሊ የት እንደሚገኝ ታውቃለህ?" አለችው ትከሻውን ያዝ እንዳደረገች።

"ጋሽ ቻርሊ ጠዋት የወጡ ናቸው። ቁልፍ ከፈለጉ ግን ልሰጥዎት" አላት የደፈረሱ ዐይኖቹን አጨናቁሮ ሽቅብ እያስተዋላት።

"እሽ ስጠኝ..." ንግግሯን ከመጨረሷ በፊት ቡቾ ቱር ብሎ ቤቱ ገባና ሰንሰለት የተንጠለጠለበት ቁልፍ አምጥቶ ሰጣት። አብነት የኳይት ሃውስን በር ከፍታ ስትገባ ቡቾ እንደ ቤት ውሻ በሩ ላይ ቁጭ አለ።

ቦርሳዋን ከምጣዱ ጠረጴዛ ላይ አስቀምጣ ከአሮጌው ሶፋ ላይ አረፍ አለች። ኳይት ሃውስ ምስቅልቅሏ ወጥቶ ፈረስ ሲጋለብባት የዋለችና ያደረች መስላለች። በሀዘኔታ ራሷን ነቅንቃችና ፈጥና ተነሳች።

ያለምንም መሰልቸት ክፍሉን መጥረግ፣ ግድግዳው መገናኛዎች ላይ መድራት የጀመረውን የሸረሪት ድር ማጽዳት፣ ታጣፊውን አልጋ ማንጠፍ ያዘች። ከብዙ ድካም በኋላ ሁሉም ነገር ከዚህ በፊት እንዳስተካከለችው ሆኖ አገኘችው። መጠነኛ ድካም ስለተሰማት በአሮጌው ሶፋ ላይ እግሮቿን አጣምራ ተቀመጠችና ቻርሊን መጠባበቅ ጀመረች።

አሥራ አንድ ሰዓት አካባቢ ቻርሊ ወደቤት መጣ። የኳይት ሃውስን በር እንደረገጠ ቤቱን በዐይኖቹ ሲያማትር ቆየና አብነትን የቅሬታ ፈገግታ እያሳየ ተመለከታት።

"ግባ ቻርሊ..." አለችው ከተቀመጠችበት ተነስታ።

"ቻርሊ ፈጥኖ ወደ ውስጥ በመግባት በእጁ የያዘውን ዳጎስ ያለ የቃለ ተውኔት ጥራዝ ምጣዱ ጠረጴዛ ላይ ወርውሮ አንገቷ ላይ ተጠምጥሞ ሳማት።

"አቢ፣ ዛሬ ቀኑን ሙሉ መሥሪያ ቤት ደውዬ አጣሁሽ እኮ" አላት በደስታ በሚቁለጨለጩ ዐይኖቹ ከላይ እስከታች እየደባበሳት።

"ዛሬ ስራ አልገባሁም..." አለችው ዐይኖቿን ከዐይኖቹ እያሸሸች።

"ቁጭ በይ አቢ... ግን በደህናሽ ነው?" ገጽታው በአፍታ ስጋት አረበበበት።

"ደህና" አለችና ከነበረችበት ተቀመጠች። ከሁኔታዋ ደህና እንዳልሆነች ተረዳ።

"እኔም እኮ ሁለት ጊዜ ደውዬ አጣሁህ"

"አው!... ልክ ነሽ፤ ዛሬ ቲያትር ቤት ሳይሆን ባህል ሚኒስቴር ነበር የዋልኩት" በዐይኖቹ እየሰረቀ ይመለከታት ጀመር። ሁኔታዋ ሁሉ አላማረውም ቆይቶ "አቢ... ምነው ተለወጥሽብኝ? ገጽታሽ ከስሟል፤ ዐይኖችሽም ደፍርሰዋል..." ጭንቀቱ እያስታወቀበት ጠየቃት።

"ምስኪን" አለች በሃሳቧ። "ደህና ነኝ ቻርሊ... እስኪ አረፍ በል። አይታወቅህም እንጂ አንተም እኮ በአካልም በመንፈስም ተዳክመሃል። ለጥቂት ቀናት ለምን እረፍት አታደርግም?" ስትል የከሳት ዐይኖቿን ላዩ ላይ እያንከባለለች ጥያቄውን በጥያቄ ሸፈነችው።

ቻርሊ ታጣፊው አልጋ ላይ አረፍ አለና በረዥሙ ተነፈሰ "የኔስ ድካም እዳው ገብስ ነው አቢ። እስኪ አሁን ያንቺን አጫውቺኝ?" አለና በዐይኖቹ አባበላት።

ሁሌ የሚገርማት ይህ ጠባዩ ነው። ስሜቷን ፈጥኖ መረዳት ይችላል። ለአፍታ ያህል ዐይኖቿን አየት አድርጎ መከፋቷን ወይ ደስተኛነቷን ያውቃል። ፈጥኖም ያዘነችበትን ወይም የተደሰተችበትን ምክንያት ይጠይቃታል። ዛሬ ግን ሰማይ ከፍ ምድር ዝቅ ትላለች እንጂ የፍቅራቸው ሞት መቃረቡን አትነግረውም።



"ደህና ነኝ፣ ካንተ ጋር ለማምሸት ስለፈለኩ መጣሁ፤ መምጣት አልነበረብኝም ነበር?!" አለች ኩርፍ ብላ።

ስጋት ያረበበበት ገጽታው በፈገግታ ፈካና ከኪሱ ሲጋራና ክብሪት አውጥቶ በመለኮስ በዝምታ ማጨስ ጀመረ። እርሷ ደግሞ ትክ ብለው በሚያስተውሏት ዐይኖቹ ሀሊናዋን እየመረመረ ሚስጢሯን የሚደርስበት ስለመሰላት ተጨነቀች። ዝምታውም ቀፈፋት። ብዙ ቆይታ "ሥራ እንዴት ነው ቻርሊ?" አለችው የተፈጠረውን ውጥረት ለማርገብ ያህል።

"ይሄው ቀን ተሌት እንሮጣለን። ሲሰፍሩት ውለው የሚጎድል፣ ሲቀዱት ውለው የማይሞላ ሙያ ያከንፈናል። በነገራችን ላይ ይህ የመጨረሻው የመድረክ ሥራዬ መሆኑን ነግሬሻለሁ? በመድረክ ስንብት ሥራዬ ላይ የክብር እንግዳዬ ደግሞ አንቺ ነሽ ... ግብዣዬን አትቀበይም?" ሲል እንደፈገገ ጠየቃት።

"ግብዣህን እቀበላለሁ፣ መድረክን እስከመጨረሻው እሰናበታለሁ •የምትለውን ቀልድ ግን አልቀበልም። ይቅርታ አድርግልኝና ቻርሊ አሣ ከባህሩ ወጥቶ መኖር እንደማይችል አንተም ከመድረክ ተለይተህ የምትኖር አይመስለኝም" አለችው ቅር እንደተሰኘች።

"አሁን በምጫወተው ተውኔት ውስጥ ደግሞ ታላቅ የመንፈስ ፈተና ውስጥ ገብቻለሁ።"

"እንዴት?!"

"በመሪነት የምጫወተው ገፀ - ባህሪ ጎራዴ የሚታጠቅ ነው። በመድረኩ ላይ በምሆንበት ጊዜ ሁሉ፤ አንድ ሰይጣናዊ ድምጽ በዚያ ጎራዴ የትያትሩን አዘጋጅ አንገት አሽክርክሬ እንድጥለው ይቀሰቅሰኛል..."

"ቻርሊ!" አብነት በድንጋጤ ተነስታ ቆመች

"እውነቱን እነግርሻለሁ አብነት ያንን ድምጽ ማስቆም አልቻልኩም ... ከትያትሩ አዘጋጅ ጋር ወትሮም እሳትና ጭድ ነን፤ መድረክ ላይ ባየሁት ጊዜ ደግሞ ደሜ እየፈላ ጎራዴ የጨበጠ እጄ መንቀጥቀጥ ይጀምራል።"

አብነት ከቻርሊ አጠገብ ተቀምጣ ፀጉሩን፣ ጢሙን እየደባበሰች ልታፅናናው ሞከረች" ቻርሊ... እባክህን ረጋ በል... እባክህ እንዲህ እልሽኛና ግትር አትሁን..."

"አቢ..."

"አቤት?"

"በአካልም በመንፈስም ትንሽ በትንሽ እየሞትኩ ወደ ፍፃሜዬ እየሮጥኩ መሆኑን አታውቂ ይሆን? እያለቅኩኝ ነው። እንደሻማ ያውም ያለ ሙቀት፣ ያለ ድምቀት፣ ያለ ብርሃን። አቢ አልዋሽሽም፤ ሁሉም ነገር ሰልችቶኛል። ነፍሴም እየተቅበዘበዘች እረፍት አጥታለች። ለመኖር ምክንያት የሆንሺኝ አንቺ ብቻ ነሽ..." የጀመረውን ሳይጨርስ ጥርሶቹን እያፋጨ አፋጫቸው።

የመንፈስ ስቃዩ እርሷን ዘልቆ ያማት ጀመር። በአፍታ የተጨማደደ ገጽታው ህይወት ምን ያህል እንዳሰለቸው ሲነግራት አንጀቷ በርህራሄ ተንሰፈሰፈ። እና አሁን የተፈጠረውን ችግር ብትነግረው ደግሞ ...

"አቢ ... እባክሽን የሙያዬን ነገር አታንሺው። በሙያው ላይ የራሴ እቅድ ስላለኝ ወደፊት በሰፊው ተወያይተን አብረን እንወስናለን።" አላት የልመና ያህል።

"ወደፊት?" አሰበች አብነት፤ ዳግም ሁለቱ ተገናኝተው የሚወስኑበት "ወደፊት" የሚባል ቀን ይኖራል? አልመሰላትም፤ እንደማይኖርም እርግጠኛ ነች። ከእንግዲህ ዛሬን ብቻ እንጂ ነገ የምትባልን ቀን አታምናትም መንፈሷ ተሸበረባት፤ አልቅሽ አልቅሽ፣ ጩኺ ጩኺ የሚል ስሜት ከውስጥ ይተናነቃት ጀመር። "ቻርሊ ደክሞኛልና ማረፍ እፈልጋለሁ!" አለችው እየጮኸች።

ግራ በተጋቡ ዐይኖቹ ፍዝዝ ብሎ እየተመለከታት ባለበት ደንዝዞ ቀረ። አብነት አንድ ነገር እንደሆነች ያደረበትን ግምት ሁኔታዋ አረጋገጠለት።

"ቻርሊ!"

"ምነው አቢ..."

"የተናገርኩትን ሰምተሸኛል ወይንስ እንድደግመው ትፈልጋለህ?"

ቻርሊ ሃሳብ እንደገባውና እንደተጠራጠረ ከመቀመጫው ተነስቶ ከተቀመጠችበት ሶፋ ላይ እጇን ይዞ አነሳትና ወደ መኝታ ክፍሉ ይዟት ገባ። የክፍሉን መብራት አብርቶም የኋይት ሃውስን በር ሊዘጋ ወጣ። በሩን ዘግቶ ሲመለስ አብነት ልብሶቿን አወላልቃ በውስጥ ሱሪና በጡት መያዣ ብቻ አልጋው ጠርዝ ላይ ኩርምት ብላ ተቀምጣለች። ደስ የሚል የሽቶ ጠረን ትንፏን ክፍል አውዷታል። ሆዱ እየፈራና እየተጠራጠረ አጠገቧ ተቀመጠና ፀጉሯን ይደባብሳት ጀመር። አንገቱን አቀፈችና ደረቱ ሥር ሽጉጥ አለች።



የገሃዱን ዓለም መራራ እውነት ሸሽታ በመንፈሷም በስጋዋም የምትሸሸግበት ጥግ እንደምትፈልግ ከሁኔታዋ ተረዳ "በርግጥ አንድ ስህተት ተፈጽሟል" ሲል አሰበ። የአብነት ችግር ምክንያት ደግሞ የርሱንም መንፈስ አቁስሎ በስቃይ ላይ ስቃይ እንደሚጨምርበት አልተጠራጠረም። እና ፈራ፤ ማንም ሰው እውነትን እንደሚፈራ እርሱም ፈራ። ምን እንደተፈጠረ ሊጠይቃት አልደፈረም።

ድንገት ያቀፈው ራቁት ገላዋ ሙቀት የለበሰውን ጃኬትና ሸሚዝ ዘልቆ ሲፈጀውና፣ ፀጉሯን ከተቀባችው ቅባትና ከሰውነቷ የሚመነጨው ድንቅ መአዛ ልቡን ቅልል ሲያደርገው ታወቀው። ዐይኖቹም በእቅፉ ውስጥ ከሚወራጨው ወጣትና ራቁት ገላዋ ላይ ለአፍታ ሳይነቀሉ እንደፈዘዘ ቀረ፤ አደንዛዥ እጽ የተወጋ ይመስል።

"አቢ..."

"ቻርሊ፣ እባክህን ሳመኝ"

ደረቱ ላይ የተሸጎጠ ራሷን ቀና አድርጎ ተመለከታት። ዐይኖቿ ግርበብ ብለው ተጨፍነዋል፤ ገጽታዋ እንዳች የብርሃን ፀዳል ይረጫል፣ ከንፈሮቿ ለአመል ያህል ተላቀው አፏ ተከፍቷል። በስሜት በጋሉ ከንፈሮቹ ከንፈሮቿን ዳሰሳቸው የእሳት ያህል ይፋጃሉ።

"ቻርሊ ... በሃይል ሳመኝ..." ስትል ቃተተች። ሳማት።

"ቻርሊ ... ን ... ንከሰኝ"

"ለምን አቢ ? ለምን?"

"በድዬሃለሁና ተበቀለኝ!"

ቻርሊ በመርፌ የተወጋ ያህል ሽምቅቅ ብሎ ቀና አለና አስተዋላት። ትኩስ የእንባ ዛላዎች ጉንጮቿ ላይ ይንከባለላሉ።

"ምን... ምንድነው የምታወሪው አቢ?"

"ሳመኝ፣ ሳመኝ ... ሳ ... መኝ!" በጩኸት አስደነበረችው።

እናም ሳማት... ።

ቻርሊ በኋይት ሃውስ ሳሎን ውስጥ ሲጋራውን እያጨሰ ሲንጎራደድ ቆይቶ ሰዓቱን ተመለከተ ከምሽቱ አንድ ሰዓት ሆኗል። ወደ መኝታው ክፍል ገባና አልጋው ላይ የተኛችውን ፍቅረኛውን ለአሥረኛ ጊዜ ያህል ተመለከታት። ሁለት እጆቿን እንደተንተራሰች በጀርባዋ ተንጋላ እንቅላፍ ታለች። የተበታተነው ረዥም ፀጉሯ ፊቷን በከፊል ሸፍኖታል። ከጥቂት ደቂቃዎች በፊት ጭልጥ አድርጎ በወሰዳት እንቅልፍ መሃል ትቃዥና ትወራጭ ነበር። አተነፋፈሷም የጤንነት አልመሰለውም።

ካለበት እንደቆመ በተጨነቁ ዐይኖቹ ለረጅም ጊዜ ሲመለከታት ቆየ። የህይወቱን ጨለማ ገፉ የተሰፋ ጭላንጭል ያሳየችው፣ እሬት

ኑሮውን ጨው ሆና ያጣፈጠችለት፣ የመኖሩ ምክንያት የሆነችው ሴት በሰላም አሸልባለች። ወደ አልጋው ተጠግቶ በከንፈሮቹ ዐይኖቿን፣ አፍንጫዋን፣ ከንፈሯን፣ አንገቷን እየሳመ ቀሰቀሳት። ዐይኖቿን በዝግታ ገልጣ በቀዘቀዘ ስሜት አስተዋለችው።

ሰዓቷን ተመለከተችናም ተነሳች። ልብሶቿን ለመልበስና ፀጉሯን ለማስተካከል የፈጀባት ጊዜ አጭር ነበር። በርጋታ ወደ ጓይት ሀውስ ሳሎን በመሄድ ቦርሳዋን ከፈተችና የፊት መስታወት አውጥታ ፊቷን ተመለከተች። እንደገናም ቀለል ያለ ሻርፕ አውጥታ አንገቷ ዙሪያ ጣል አደረገችና ቦርሳዋን አነገተች።

ይህ ሁሉ ሲሆን በመካከላቸው አንዳችም የቃላት ልውውጥ አልነበረም። ቻርሊ ከጀርባዋ ቆሞ ያስተውላታል። ልክ ውቢት ተለይታው ስትሄድ ተሰምቶት የነበረውን አይነት ስሜት ስለተሰማው አዕምሮው እንደ መደንዘዝ አለ።

ወደ'ርሱ ዞር አለችና በፀጥታ ተመለከተችው። እንደፀነሰች ልትነግረው አሰበችና አፏን ከከፈተች በኋላ ምክንያቱን ባልተረዳችው ምክንያት ከምላሷ ጫፍ መለሰችው። "እ-አትሸኘኝም?" አለችው አንገቷን ዘንበል አድርጋ።

ግራ እንደገባው እግሮቹን በደመነፍስ አንቀሳቀሳቸው። አብነት ድንገት አንገቱ ላይ ተጠመጠመችና ትንፋሽ እስኪያጥረው ድረስ ትስመው ጀመር። ጉንጮቹን ለብ የሚል እንባ ስላረጠባቸው ከንፈሩን ከከንፈሮቿ ላይ አላቆ አያት። የደፈረሱት ዐይኖቿ እንባ ያዘንባሉ። "አቢ... ለምን እንዲህ ትስሚኛለሽ?" ድምጹ እየተንቀጠቀጠ የእንባ ዘለላ የቋጠሩ ዐይኖቹን እንደበለጠጠ ጠየቃት። አልመለሰችለትም። ዐይኖቿን ቡዝዝ አድርጋ ተመለከተችው።

"ስንብት ነው?" ሳያውቀው ከንዴን ጨምድዶ ያዛት።

" ምናልባት፣ ቻርሊ!"

"ለምን አቢ?... ለምን?"

"ምክንያቱ አስፈላጊ አይደለም ቻርሊ፣ ትርፉ መንፈስን በፀፀት ጅራፍ እየገረፉ ዘለአለም ራስን ማሰቃየት ነው። አንዳንድ ጊዜ ከማወቅ አለማወቅ ይሻላል። ዝም ብለን አንድን እውነት እንቀበል ሆዴ! ፍቅራችን ከንግዲህ ሞቷል! አንድ ነገር ግን እንድታውቅልኝ። ቃሉ ምን ያህል ቀላል ቢመስልም እወድህ ነበር!"

"አቢ... ም..."



"ስማ ቻርሊ፣ አንድ ነገር ላስጠንቅቅህ ። ሊገድልህ የሚፈልግ ሰው ያላድድሃልና ተጠንቀቅ"

"ምን አጠፋሁ?"

"በዚህ ምድር ላይ ያለወንጀላቸው የሚሞቱ ንጹሀን ቁጥር ብዙ መሆኑን ከኔ ይልቅ አንተ ታውቃለህ ቻርሊ። ልትቋቋመው የምትችል ሃይል አይደለምና አንድ ነገር አድርግ ... እስከ ዘለዓለሙ ደህና ሁን!"

"በቃ?"

"አዎን ቻርሊ... አየህ ለሁሉም ነገር መጀመሪያ እንዳለው ሁሉ መጨረሻም ደግሞ አለው። እባክህ ትወደኝ የነበረውን ያህል ልትጠላኝ ሞክር..."

ይህን አባባል መቼ ነበር የሰማው? ማን ሲለው ነበር ያዳመጠው? የአዕምሮውን ጓዳ እየፈተሸ ለረዥም ጊዜ እንደደነዘዘ ቆመ። "ፍቅር... የጊዜ ጉዳይ ነው... ለሁሉም ነገር መጀመሪያ እንዳለው ሁሉ መጨረሻም አለው" ውቢት! እና አሁን ደግሞ አብነት! ያልታደለ... ያልታደሉ።

አብነት ጥላው ስትወጣ ቆሞ አስተዋላት አልተከተላትም። እየተወላገደ ሄዶ መብራቱን አጠፋና በዳበሳ አሮጌው ሶፋ ላይ ኩርምት ብሎ ተቀመጠ። ዋይት ሀውስ ጨለመች። የነፍሱ ጨለማ ደግሞ ከዚያ የጠቀረ ነበር። የህይወቱም ብርሃን ከአብነት ጋር ለዘለዓለሙ ጨለመች። ተስፋው በእንጭጩ ተረመረመች። ሰው ያለ ተስፋው የሚተነፍስ ሬሳ እንጂ ህያውነቱ ምኑ ላይ ነው?

አብነት የሰይጣን ሰፈርን ጠጠራማ መንገድ እየተደናቀፈች ስትሮጥ ለራሷ ያህል እየጮኸች ነበር። እንባዋን ከጉንጮቿ ላይ "እያፈሰሰች ደግማ ደጋግማ የምትጮኸው እገድለዋለሁ! እገድለዋለሁ! እገድለዋለሁ!" የሚለውን ቃል ብቻ ነበር።

የወፍ ጫጩት ህይወት በጁ አልፎ የማያውቅ ሴት ሰውን ያህል ፍጥረት ለመግደል ልቧ ይታጠቅ እንጂ ተግባሩ ምን ያህል እንደሚቸገር ለሰከንድ ያህል ቆም ብላ አላስተዋለችም።

## ምዕራፍ ሀያ

ከቀኑ ስምንት ሰዓት ላይ ወደ ቢሮዋ ስትገባ ቦርሳዋን ጠረጴዛው ላይ ወረወረችና የስልኩን እጀታ አነሳች። ዐይኖቿ ደፍርሰዋል፣ ፀጉሯ በወጉ አልተበጠረም፣ እረፍት ያላገኘው ሰውነቷ ዝሎ ከጀርባዋ እንደመጉበጥ ብላለች። ቁጥሮቹን አሽከርክራ ስልኩ መጥራት ሲጀምር ልቧም በፍጥነት መታ። ዛሬ እንደሌላው ጊዜ ያልተቀጣላት ተቀናይ ሆና መገኘት አልፈለገችም። እቅዱ እንዳይሰናከል የሣራ ጋዴምን መንፈስ ተላብሳዋለች ያልሆነችውን ሁሉ ለመሆን።

"ሃሎ... እባክዎን አቶ ስዩምን..." ገጿ በፈገግታ ፈካ፣ ድምጿም የደስ ደስ አለው።

"አብነት ነኝ አቶ ስዩም..."

የደፈረሱ ትላልቅ ዐይኖቿን በባዶው ግድግዳ ላይ እያንከባለለች ከወዲኛው ጫፍ ያለማቋረጥ የሚኾነደነደውን ዲስኩር በፀጥታ ማዳመጧን ቀጠለች።

"እምን፣ ከአሶሳ ከተመለስክ ወዲህ አልተገናኘንም። ... በሰላም መመለስህን እንኳን ሳታሳውቀኝ በመቅረትህ አዝኘብሃለሁ ... አዎ አባባ ሁሉን ነግሮኛል። ለማንኛውም እኔና አንተ ተገናኝተን መነጋገር ያለብን ጉዳይ አለ። አሥር ሰዓት ላይ ቢሮ መጥተህ ልትወስደኝ ትችላለህ? ... ደስ ያለህ ቦታ ልትጋብዘኝ ትችላለህ ... አባባ ደህና ነው ምንም አታስብ፣ እጠብቅሃለሁ ... ደህና ዋልልኝ" የስልኩን እጀታ ከቀፎው ላይ እንዳስቀመጠች በፈገግታ ፈክቶ የነበረው ገጽታዋ በአፍታ ጠቆረ። ስልኩን በጥላቻና በንቀት ስታፈጥበት ቆይታ ምራቋን ጢቅ ብላ ተፋችበት።

ወዲያው ጠረጴዛው ላይ የወረወረችውን ቦርሳ ከፈተችና እጀታው ከቀንድ የተሠራ ጩቤ መዛ አወጣች። ዐይኗ ስር አቅርባ ተመለከተችው ስለቱ ያንፀባርቃል። በአባቷ መኝታ ቤት ለጌጥ የተንጠለጠለ ነበር። ዛሬ ጠዋት ፍትህን ልታስከብርበት ለብዙ ዓመት ተሰቅሎ ከኖረበት ግድግዳ ላይ አወረደችው። ጩቤውን የጨበጠችበት እጇ ይንቀጠቀጥ ጀመር። በርካታ ዝብርቅርቅ ስሜቶች የተመሰቃቀሉበት ገጽታዋ በአፍታ የተሸበረች ከተማ መሰለ።

ዐይን እያየ እግርና እጅን አጣምሮ ፍትህ በማይዳኛቸው ህጋዊ ወንጀለኞች መታረድ። ይህንን መከላከልም ወንጀል ነው?! ህጋዊ ወንጀለኞቹ የመጣሪያ ምላጭ ስበው የሰው ጭንቅላት አልፈጠረቁምና፣ ስለት መዘው አንጀት አልዘረገፉምና ማስረጃ ሆኖ በህግ ፊት የሚያስቀጣቸው ወንጀል የለም። ታዲያ የሌላውን የህይወት ተስፋ አጨልመው፣ አንዲት የደም ጠብታ ጠብ ሳትልባቸው የሰውን ነፍስ ከስጋው በመለያየት ህያውን ፍጡር በድን የሚያደርጉ ወንጀለኞች፣ ፍትህን የሚቀበሉት ከየትኛው ህግ፣ ከየትኛው ዳኛ ነው።

ወደ ማንም ሄዳ አቤት የማትልበት ወንጀል ነው የተፈፀመባት። ስለዚህም ራሷ ከሳሽ፣ ራሷ ዳኛ ሆና ፍትህን ልታገኝ ወሰናለች። ቢያንስ ወላጆቿ በወንድ እንዳልለወጠቻቸው አምነው መጭ ዘመናቸውን ከድርጅታቸው ጋር ይቆያሉ። ምናልባትም ቻርሊ ታማኝነቷን ያምንላት፣ ከሃዲ ያለመሆኗን ያውቅላት ይሆናል። ጠበቃውን አግብታ በማየቱ እድሜ ዘመኑን የሄዋንን ዘር እየረገመ እንዳይኖር፣ ራሱን በፀፀት ጅራፍ እየገረፈ እንዳይሰቃይ ባንድ ነፍሷ ውለታ ትውልለት ይሆናል። ማን ያውቃል? ጠበቃውንም ቢሆን ምን ጊዜም እውነት እንደምትረታ እርሱ በሚገባው ቋንቋ ታስተምረው ይሆናል።

ጩቤውን ከቦርሳዋ ውስጥ መልሳ ዚፑን ሸምቀቃ ዘጋች። ወዲያውኑ ቢሮዋን ማጽዳዳት ያዘች። ሁለት ዓመታት ያህል የሠራችባቸውን የሂሳብ መዛግብትና ሰነዶች በመልክ በመልካቸው አደራጀች። አላስፈላጊ የሆኑ የግል ወረቀቶቿን እየቀዳደደች ከቆሻሻ መጣያው ቅርጫት ውስጥ ከመረቻቸው። ዳግመኛ ወደዚህ ቢሮ እንደማትመለስ ስታስብ የእልህ ሲቃ እያነቃት በዐይኖቿ ላይ የእንባ ጠብታዎች መቋጠር ጀመሩ።

አንድ ጊዜ ስትቀመጥ፣ ሌላ ጊዜ ከመቀመጫዋ ተነስታ ክፍሉ ውስጥ ስትንቆራጠጥ፣ ጊዜ በእንፉቅቁ እየዳኸች አሥር ሰዓት ላይ ደረሰች። አብነት በመስተዋቱ መስኮት ላይ ቆማ ለመጨረሻ ጊዜ ቁልቁል መመልከት ጀመረች።

ገና ከቀትር ጀምሮ ሲያሊቃቅስ የዋለው ሰማይ ፈገግ ብሏል። ፀሐይዋ ከበታቿ እየታጠፈና እየተዘረጋ በጋረዳት የዳመና ምንጣፍ መሃል ብቅ እያለች ትጫወታለች። ከአስፋልቱ መንገድ ላይ እንፋሎት ሽቅብ ይተናል። የተላላፊው መንገደኛ ጥድፊያም ጨምሯል።

የጠበቃው ሲትሮይን መኪና ካለችበት ህንፃ ሥር ስትቆም ተመለከተች። ለለውጥ በሱፍ ኮትና ክራቫት ምትክ ውሃ ሰማያዊ ጃኬትና ነጭ ጅንስ ሱሪ ለብሷል። የመኪናውን በር ከቆለፈ በኋላ ቁልፏን እያሽከረከረ ወደ ህንፃው መግቢያ አመራ። አለባበሱና

የአረማመዱ ቅልጥፍና ገና ሮጦ ያልጠገበ ጎረምሳ አስመስሎታል። ወደ ወንበሯ ተመለሰችና ራሷን እያረጋጋች ጠበቀችው።

የቢሮዋን በር ከፍቶ ሲገባ በእጁ ላይ አንዲት ቀይ የጽጌረዳ አበባ ከነቅጠሏ መያዙን አስተዋለች። ሁለት እጆቹን በሰፊው ዘርግቶ ትከሻዋን አቀፈና ጉንጮቿን ሳማት። ፈጥኖም "ጽጌረዳ" አለና ቀይዋን አበባ አበረከተላት።

"አመሰግናለሁ" አለችና ፊቷን በፈገግታ አፍከታ ተቀበለችው። ያለፈውን ስህተት ባለመድገሟ በልቧ እምላኳን አመሰገነች።

"ናፍቀሽኝ ነበር አቢ... ደህና ነሽ?" በእጁ የያዘውን ቁልፍ እያሽከረከረ በዐይኖቹ ከላይ እስከ ታች ይደባብሳት ጀመር። ቡና ቀለም ያለው ባለፈር ጃኬቷ ጡቶቿን ቢደብቅበትም አጭሩ ቀይ ቀሚሷ ሞንዳላ ገላዋን አጋልጦ ሰጥቶታል። ዐይኖቹ የወሲብ ረሃባቸውን ሲያዛጉ ተመለከተች።

"ደህና ነኝ... ዳግመኛ በመገናኘታችን ፍጹም ደስተኝነት ይሰማኛል... ለምን አረፍ አትልም?..." እያለች ወደ እንግዳ ማረፊያው ወንበር አመለከተችው። "የለም የለም... መሄድ አለብን... አባትሽን ሰላም ብያቸው እስከመለስ ተዘጋጅተሽ ጠብቂኝ" አለና መልሷን ሳይጠብቅ እየተጣደፈ ወደ ቢሯቸው አመራ።

ጥድፊያው የት ለመድረስ እንደሆነ ገመተችና በምጸት ፈገግ አለች። በእጇ የያዘችውን የጽጌሬዳ አበባ ስትመለከት እባብ የጨበጠች ያህል ቀፈፋት። ቦጫጭቃ ግን አልጣለችውም። ዛሬ እውነተኛዋን ተዋናይ ለመሆን ታጥቃለች። ጥላቻን እንደ ማለዳ ጀንበር ለስስ ብሎ ልብ በሚያቀልጥ ፈገግታ አስታማ፣ የበቀልን እሳት እንደ እርጎ በቀዘቀዙ ቃላት አጣፍጣ በመቅረብ ልትፈታተነው ቆርጣለች።

ብዙም ሳይቆይ እንደ ኳስ እየነጠረ ተመለሰና "እንንቀሳቀስ አቢ" አላት ከቢሮዋ በር ላይ ቆሞ።

የሰጣትን የጽጌረዳ አበባ እያሽተተች ቆየችና ቦርሳዋን ከጠረጴዛው ላይ አንስታ ወደ በሩ አመራች። እጁን ክንዷ ውስጥ አስገብቶ ደረጃውን መውረድ ሲጀምሩ የቢሮዋ ስልክ አንቃጨለ። ዞር ብላ ስትመለከት ፀሐፊዋ ወደ ቢሮዋ እየገባች ነው። በጠበቃው እቅፍ ውስጥ እንደሆነች ተያይዘው ቁልቁል ወረዱ። ደረጃውን ወርደው ከህንፃው እንደወጡ ፀሐፊዋ እየተንደረደረች ደረጃውን በመውረድ



ደረሰችባቸውና "አቢ ... አሁን ይጠራ የነበረው ስልክ ያንቺ ነው..." አለች በላይ በላዩ እየተነፈሰች።

"ከየት ነው?" አብነት ግንባሯን ቅጭም አድርጋ ጠየቀች። ጠበቃው ተመልሳ እንዳትሄድበት እጇን አጥብቆ ይዟል።

"ተካልኝ ባልቻ እባላለሁ ይላል..."

"ማን?!" አብነት በመገረም ዐይኖቿን እያርገበገበች ተካልኝ ባልቻ ማን እንደሆነ ለማወቅ የአዕምሮዋን ጓዳ ማተራመስ ጀመረች። የጠበቃው ዐይኖች ተበልጥጠው ትንፋሹ መቆራረጥ ያዘ።

"ተካልኝ ባልቻ ነው ያለኝ... ሰሞኑን በየቀኑ እየደወለ ለጥብቅ ጉዳይ እፈልጋታለሁ ይላል... አንቺ ደግሞ..."

የጀመረችውን ሳትጨርስ አብነት አቋረጠቻት "እንደዚህ የሚባል ሰው አላውቅም... ምናልባትም በስም ስህተት ይሆናል አላውቅህም ብለሽ ስልኩን ዝጊው።"

"በጣም የተጨነቀ ይመስላል ... ነገ ደውል ልበለው?..."

ነገ የሚባል ቀን በቢሮዋ እንደማታሳልፍ ገመተችና በቅሬታ ራሷን ወዘወዘች። "እማርኛ እኮ ነው የምናገረው ቅድስት... ተካልኝ ባልቻ የሚባል ሰው አላውቅም። መሳሳቱን ነግረሽ ዝጊው።" ድንገት ዞር ብላ በፀሐፊዋ ላይ ጮኸችባት። ቅድስት ትከሻዋን በምንቸገረኝ አይነት ሰበቀችና በእርጋታ ደረጃውን መውጣት ጀመረች።

ጠበቃው ትንፋሹን ውጦ እንደበቱ ተሳስሮ እንደደነዘዘ ቆሟል። አብነት ሁኔታውን በመገረም ስትመለከት ቆየችና "እንሂድ እንጂ ጌታዬ..." አለችው ፈገግታ ለማሳየት እየሞከረች።

ክንዷን ጨምድዶ እንደያዘ በደመነፍስ እየተወላገደ መኪናው ወደቆመችበት ይዟት ሄደ። ሁኔታው አላማራትም። ደቂቃ ባልሞላ ጊዜ ውስጥ በአካልም በመንፈስም የደነዘዘበት ምክንያት አልተገለፀላትም። ይህን እያሰላሰለች ቀና ስትል የተመለከተችው ትርኢት ድንጋጤ ደግሞ ሰውነቷን እኩል ለእኩል ተረተረው። የጠበቃው መኪና ከቆመችበት ትይዩ አስፋልቱን ተሻግሮ ቻርሊ ሀውልት መስሎ እንደቆመ እያንዳንዷን ድርጊታቸውን ያስተውላል። አብነት በጠበቃው እቅፍ ውስጥ፣ ቀይ ጽጌሬዳ አበባ ግንባይ እንደያዘች!

ጠበቃው የመኪናውን በር ከፍቶ እንድትገባ ሲጋብዛት እንኳን ዐይኖቿ ባሻገር ከቻርሊ ጋር ተፋጠው ነበር። ያያታል! ታየዋለች። ለረዥም ጊዜ ዐይኖቻቸው አልረገቡም።

"ግቢ እንጂ ጽጌረዳዬ..." አለ ጠበቃው ጭራሽ ግራ ተጋብቶ። ፈጥና ወደ መኪናው ውስጥ ገባችና የበሩን መስተዋት አወረደችው። ቻርሊን ለመጨረሻ ጊዜ በዚህ ሁኔታ ልትሰናበተው ነው። እንባና እልህ በአንድ አብረው ይተናነቋት ጀመር። አላለቀሰችም። ከእንግዲህ እየሳቀች ብትወድቅ እንጂ ዘለላ እንባ ከደረቀው የዐይኗ ኩሬ ጠብ አይልም።

ጠበቃው የመኪናውን ሞተር አስጓራና ተሳሳፊ መኪና አለመኖሩን አረጋግጦ በከፍተኛ ፍጥነት ወደ ግራ ታጠፈ። ከፊት ለፊቱ ከአስፋልቱ ጠርዝ ወጣ ብሎ አንድ ሰው ጅብራ መስሎ ቆሟል! መንገዱን ለመልቀቅ አንዳችም እንቅስቃሴ አላሳየም። ጠበቃው ከሰከንድ ከፍልፋዮች ላነሰ ጊዜ በፈጣን ዐይኖቹ አትኩሮ ተመለከተው። ሰውዬው ጭራሽ ጥቂት እርምጃዎች ተራምዶ ወደ መሃል መንገድ ገባ። ጠበቃው ደነገጠ። በዚያ ፍጥነት ጨፍልቆት እንደሚያልፍ አልተጠራጠረም። የደምስሩ ቱቦዎች ፈጠጡ፤ ጡንቻዎቹ ተወጣጠሩ፤ ግምባሩም ላብ አመነጨ።

ጊዜ ሳያጠፋ ያለውን ሃይል ሁሉ ተጠቅሞ በሁለቱም እጆቹ መሪውን ወደ ግራ አጠፈው። መኪናዋ ጆሮ የሚሰቀጥጥ ድምጽ አሰማችና ተሽከርክራ ቆመች። ከፊት ለፊቱ ጋኔል መስሎ የተጋረጠበትን ሰው ጠርጎት እንዳለፈ አልተጠራጠረም። ፈጥኖ የመኪናውን በር ከፍቶ ባሻገር ተመለከተ። ተአምር ነው! ቻርሊ አሁንም ከነበረበት ቦታ ደንዝዞ ቆሟል። ጠበቃው ድንጋጤና ንዴት ያንቀጠቅጠው ጀመር። "አንተ የውሻ ልጅ... የመኪናየን ጎማ ዋጋ እንኳን አታወጣም!" ቻርሊ የሚሰማው አልመሰለውም መሃል አስፋልት ላይ ዐይኖቹን አፍጥጦ ቆሟል። ራሱን በብስጭት እያወዛወዘ መኪናው ውስጥ ገባና በሩን በሃይል ዘግቶ የጠፋውን የመኪናውን ሞተር ቀሰቀሰ።

የቻርሊ ዐይኖች ያያሉ እንጂ አይመለከቱም፤ ጆሮዎቹ ይሰማሉ እንጂ አያዳምጡም - ደንዝዟል። አብሹት ትንፋሿ ቀጥ ብሎ ሊቆም ምንም ያህል አልቀረው። በዚያች አጭር ቅጽበት ውስጥ የተፈጸመውን ድርጊት ሁሉ እውነት ነው ብላ ለመቀበል የአዕምሮዋ ጉልበት ደክሟል። መኪናዋ የደነሽ አደባባይን እቅጣጫ ይዛ ከመጣዟ በፊት ለመጨረሻ ጊዜ አንገቷን በመኪናው መስኮት ብቅ አድርጋ ተመለከተችው። በዐይኖቹ ውስጥ የሚንቀለቀለው የበቀልና የቁጭት እሳት ወላፈኑ ለበለባት። የተናነቃትን እንባ ዋጥ አድርጋ በእጇ የያዘችውን ቀይ ጽጌሬዳ አበባ በርሱ አቅጣጫ ወረወረችለት። ጠበቃው ሰረቅ አድርጎ አያትና የመኪናውን ፍጥነት ጨምሮ ተፈተለከ።



ቻርሊ ሜካኒካዊ በሆነ እንቅስቃሴ ወደ አበባዋ ቀረበና አነሳት። አንድ ጊዜ ቀረብ አንዴ ደግሞ ራቅ እያደረገ ሲመለከታት ቆየና ራሱን በሀዘኔታ እያወዛወዘ ፈገግ በማለት ከመኪናው መተላለፊያ ወደ መንገደኞች መተላለፊያው አስፋልት አመራና ቆመ።

ድንገትም "አባብ! አባብ!" እያለ ጮኸ። ተሳላፊ መንገደኞች ቆም እያሉ ያስተውሉት ጀመር።

ልክ የአባብ ጭራ የጨበጠ አይነት የአበባውን ግንጣይ ከጫፍ ይዞ እንዳይንድፈው በርቀት አንጠለጠለው "አባብ! አባብ! አባብ! አሳሳች ውበት ... አስመሳይ እውነት ... አባብ! አባብ!" ፍቅፍቅ ብሎ መሳቅ ቀጠለ።

የአበባውን ግንጣይ በርቀት እንዳንጠለጠለ "ውበት የሸፈነው ኩሶ! ... ውበት የጋረደው እሳት! እሳት! አባብ!" ሲል ጮኸ። አስፋልቱ ላይ ጣለናም በጫማው ሰል ረግጦ አሸው። የአብሹትን ጭንቅላት ረግጦ የደፈጠጠው ያህል እርደታ ሲሰማው የረገፉትን የአበባ ቅጠሎች በእግሩ በታተነና "አባብ! አባብ! አባብ!" እያለ በመጮህ መኪናዋ በሄደችበት አቅጣጫ በሩጫ እርምጃ ተፈተለከ። ከመንገዳቸው ተዘናግተው ቆመው ከሚያዩት ሰዎች መሃል የሚስቁ፤ በቅሬታ ፈገግ ያሉ፤ በሀዘኔታ ከንፈራቸውን የሚመጡ ነበሩ።

መንገሻ የኒህ አንደኛ ፎቅ ላይ ከሚገኘው ቢሮቸው የሆነውን ሁሉ በቀዘቀዙ ዐይኖቻቸው ቁልቁል ተመልክተዋል። ጠበቃው ቻርሊን በመኪናው ጨፍልቆት ቢያልፍ በወደዱ ነበር። የአተራረፉን ትንግርት ተአምር ብለው ከንፈራቸውን በቁጭት ነክሰዋል። አብሹት አበባውን ለቻርሊ ስትወረውር ሲመለከቱም በንዴት ተንጨርጭረዋል።

ልጅ ውሳኔዋን ለውጣ ህይወቷን አትረፈች እንዲሉ ያሰኛቸውን ትርኢት ከማየታቸው የቻርሊ ጣልቃ መግባት በጠበቃውና በልጃቸው መካከል የተፈጠረውን መልካም ጅምር የሚያጨልም መሆኑን አልተጠራጠሩም። በንዴት ጥርሶቻቸውን አፋጩና ዛቱ። ዛሬም ህይወት የህይወት ጥያቄ ነችና በአንድ ራሳቸው በመጣ ነገር ዋዛ የለም።

ወደ ጠረጴዛው ተመልሰው የስልኩን እጀታ አነሱና ቁጥሮቹን አሽከረከሩ። ከብዙ ቆይታ በኋላም ስልኩ ከወዲያኛው ጫፍ ሲነሳ ፊታቸውን እንደጨፈገጉ "ናፖሊዮን? መንገሻ ነኝ... ማታ አንድ ሰዓት ላይ ዋቢ ሸበሌ ሆቴል በሩ ላይ እንድንገናኝ ይሁን!... መኪናዬ ውስጥ

ሆኜ እጠብቅሃለሁ" አሉና ስልኩን ዘጉ። ቀጥለው ኪሳቸውን ደባብሰው ፒፓቸውንና የትምባሆ ጥቅል አወጡ።

ጠበቃው መኪናውን እያሽከረከረ አብነትን የወሰዳት ወደ ሆቴል ዲአፍሪክ ነበር። ከሆቴሉ ቅጥር ግቢ ውስጥ ከጀርባ በኩል ባለው የመኪና ማቆሚያ ሲትሮይኗን አቆመና ወደ ሆቴሉ ይዟት ገባ። በምግብ መመገቢያው አዳራሽ ውስጥ ብዙ ሰው የለም። ጥንድ ጥንድ የሆኑ ወንድና ሴት በየማእዘኑ ተቀምጠው ይመገባሉ። አብነትንም ወደ አንድ ጥግ እየመራ ወሰደና ሶፋ ወንበር ላይ አስቀመጣት።

ጠረጴዛው ላይ ያለውን የምግብ መምረጫ ካርድ ወደፊቷ እየገፋ "ለመክሰስ ምን ትወስጂለሽ አቢ?" ሲል ጠየቃት። አብነት ካርዱን መልከት አድርጋ ከለብ ሳንድዊች እንደምትወስድ ገለጸችለት።

አስተናጋጁ ገጽታውን አድምቆ እጆቹን የኋሊት አጣመረና ታዘዛቸው። ጠበቃው የሲጋራ ፓኮውን ከኪሱ ውስጥ እየፈለገ "አንድ ክለብ ሳንድዊችና አንድ ጉላሽ ይዘጋጅልን... ሁለት ሸሻሰ ውስኪም ጨምረህ አምጣ..." በማለት አዘዘው ።
አብነት ጣልቃ ገብታ ተቃወመች "እእ ... እኔ ለስላሳ"
"ተይ፣ ተይ!... ባይሆን ቀዝቃዛ ቢራ አምጣላት ... የሀፃናቱን መጫወቻ ለምን ትሻሚያቸዋለሽ" አለ እየሳቀ።
"እንዴ?! ተው እንጂ ስዩም!..."
"ከአንድ በላይ እንድትጠጭ አላስገድድሽም..." ንግግሩን ከመጨረሱ በፊት አስተናጋጁ ከአጠገባቸው ሄዷል።

የቀረበላቸውን ምግብ የተመገቡት በፍጹም ፀጥታ ነበር። ጠበቃው ቀልቡ በሦስት አብይ ጉዳዮች ተሰርቋል። በተካልኝ ባልቻ ስልክ መደወል፣ በመኪና ሊገጨው በነበረው ሰው ላይና አብነት ላነጋግርህ እፈልጋለሁ ባለችው ጉዳይ ዙሪያ ሃሳቡ ይሽከረከራል።
የጠበቃው ፊጣን የባህርይ ለውጥ ማሳየት ደግሞ አብነትን ክፉኛ አሳስቧታል። በተለይ ከሀንፃው ሲወርዱ የተካልኝ ባልቻን የስልክ ጥሪ ላለመቀበል ወስና ፀሐፊዋ ስልኩን እንድትዘጋው ካደረገችበት ቅፅበት ወዲህ አንዳች ኃግርት ልሳኑን የዘጋው ያህል ንግግሩ ቁጥብ ነበር።

ምግብ የተመገቡባቸው ሣህኖች ተነስተው ከውስኪው መደጋገም ያዘ። አብነት በብርጭቆ የተቀዳላትን ቢራ በትንሽ በትንሹ ፉት ትላለች። ጠበቃው ድንገት "ጭቃ የሰው ጭቃ!" አለ ከታፈነ ልሳን በሚወጣ ድምፅ። አብነት ግራ ተጋብታ አስተዋለችው።



"እንገቱ ላይ በወጣሁበት እጸድቅ ነበር... ደግሞ እኮ ሲያዩት ደህና ሰው ይመስላል... ዐይኑ እያየ ከሰው መኪና ጎማ ሥር ይወተፋል?!"

ስለ ቻርሊ እንደሚያወራ ገባት። በቅሬታ ፈገግ ብላ በፀጥታ ማዳመጧን ቀጠለች።

"እብድ መሆን አለበት!" አለ ራሱን እየወዘወዘ።
"ሰውዬው እኔ ሆኜ እንጂ የዚያ ሰው አጥንት መለቀሚያው ዛሬ ነበር ...ሃሃሃሃ" ውስኪውን በጥንድ እያስቀዳ ሲደጋግም አንደበቱ መፍታታት፣ ምላሱ መንጣጣት ጀመረ። አብነት "እብድ መሆን አለበት" የሚለውን አባባል ስትሰማ በስለት የተወጋች ያህል ሽምቅቅ አለች። ጠበቃው ስሜቷን አላጤነውም፤ ዐይኖቹ አሁንም የለበሰችውን ጃኬትና ቀሚስ በስሜት አውልቀው ወጣት ገላዋን ይደባብሷታል።

"ያን ሰው አታውቀውም?" አለች የሚተናነቃትን እልህ ለመዋጥ ከንፈሮቿን በጥርሷ እያኘከች።

"እንጃ... አይመስለኝም... መኪናው ውስጥ ተመልሼ ከገባሁ በኋላ የማሰላስለው አንድ ነገር ምን እንደነበር ታውቂያለሽ?... የሰውዬው ገጽታ ለኔ አዲስ ባለመሆኑ የት እንደማውቀው እያሰብኩ ነበር። ላስታውሰው ግን አልቻልኩም።" አላት ሲያቀጣጥለው አፉ ላይ ያደረገውን ሲጋራ መለኮሱን ትቶ።

"ቻርሊ የሚባል ተዋናይ ታውቃለህ?"
"እንዴ... እንዴ... ልክ ነሽ! አሁን በትክክል አስታወስኩት... ማይ ሎርድ! ይህችን ምስኪን ሀገር ዳግም ልታፈራው የማትችል አንድ ታላቅ ሰው አሳጥቻት ነበር... ሃሃሃ! የአርቲስቱን ህይወት ለማዳን የፈጸምኩት ታላቅ ጀብድ በሬድዮ መነገር፣ በጋዜጣ መታተም መቻል አለበት። ነገውኑ ለባህል ሚኒስቴር ማመልከቻ አስገባለሁ ሃሃሃ" እያለ በራሱ ቀልድ ራሱ ሳቀ።

አብነት ዘለሽ ጉሮሮውን አንቂው የሚል ስሜት ከውስጥ ይተናነቃት ጀመር። "የሰው ገብስ!" አለች በሀሳቧ። ወዲያውኑ የመጣችበትን ጉዳይ አስታወሰችና ራሷን ለማረጋጋት እየሞከረች ከረኸሙ ሳቅ ጋር አብራው ሳቀች።

ጠበቃው ቀጠለ፤ "ርግጠኛ ነኝ ሰክሮ፣ አለበለዚያም አብዶ መሆን አለበት።... ይገርመኛል፣ ከነዚህ አርቲስት ከሚባሉ ፍጥረቶች

አንድ እንኳን ደህና ሰው አይበቅልባቸውም? ሁሉ ጠጭ፣ ሁሉ ፈንጭ፣ ሁሉ የአእምሮው ብሎን የላላ ወፈፌ ነው። ... ለመሃሉ እንኳን አንድ ደህና ሰው የለባቸውም... ከንቱዎች" አስተናጋጁን ጠርቶ ከውስኪው እንዲደጋግም አዘዘ።

"እ - አልሰከረም" አለች አብነት ትንፋሿ እየተቆራረጠ።

"እንዴት ይህን ልታውቂ ቻልሽ?" የጠቢቃው ግንባር ተቋጠረ።

"አልሰማህም ማለት ነው?"

"ምኑን?"

"ከተማው ሁሉ የሚያወራውን የአርቲስቱን ታሪክ?"

"አልሰማሁም"

"አርቲስቱ በጣም የሚወዳት፣ በቃል ኪዳን የተሳሰረችው ፍቅረኛ ነበረችው..."

"በጀ!" አለ ጠበቃው ታሪኩን ለመስማት ባለመፈለጉ ገና በጅምሩ እየሰለቸ።

"እና በጣም የትልቅ ሰው ልጅ ነች። እነርሱ ተዋደውና ተፈቃቅደው ሊጋቡ አቅደው ሳለ... ቤተሰቦቿ ለሌላ ሰው ሊድሯት ወሰኑ፣ ያለፈቃዷ። እና ይሄው እርሱም እንዲህ ሆኖ ቀረ ... አያሳዝኑም?" አለችው።

ጠበቃው ትንሽ እንደማሰብ አለና "ለምን ያሳዝናሉ? መገናኘት እንዳለ ሁሉ መለያየት መኖሩንም አስቀድመው መተንበይ ነበረባቸው... በነርሱ ሁኔታ መለያየታቸው ቢያስደስት እንጂ አያሳዝንም። ለምን አትይም?... ውጥናቸው ያላቻ ጋብቻ ነበርና። እንደምትይኝ እርሷ የሀብታም ልጅ ከሆነች በአርቲስት ደመወዙ ምን ሊያበላት?! ቆሎ ሊያስቆረጥማት ወይንስ በኮንጎ ጫማ ሊያስኬዳት? አፈቀርን የሚሉ ሴቶች የማይገነዘቡት አንድ ቁም ነገር፣ ፍቅር ቀለብ አለመሆኑን፣ ፍቅር ራሱ ኑሮ፣ ፍቅር በራሱ ህይወት ሊሆን ያለመቻሉን እውነታ ነው። የፍቅርን ሙሽ ሲያላዝኑ ከርመው፣ ባዶ ኪሳቸውን ትዳር የሚሉትን የመቃጠያቸውን ሲኦል ይመሠርቱና መራራዋን ጽዋ ሲጎነጯት በሳምንቱ ሆድ ይብሳቸዋል። በወሩ በየአቅጣጫው ፊታቸውን ያዞሩታል። በሶስተኛው ወር ንዝንዝ በአራተኛው ወር ቡጢ፣ ግፋ ቢል በስድስተኛው ወር ደግሞ የፍች ፋይሎቻቸውን እያንጠለጠሉ የፍርድ ቤቶችን የሥራ ጊዜ ያጣብባሉ። ማጣፈጫው ከሌለ ፍቅር ሁሉ ውሸት ነው። ሃሃሃ-ሃሃሃ" አለ ማጣፈጫ የሚለው ቃል ብር መሆኑን ለማሳየት የቀኝ እጁቹን ጣቶች እያፋተገ።

አብነት አልመለሰችለትም።

ጠበቃው ቀጠለ፣ "ኦክስፎርድ ዩኒቨርሲቲ ሳለሁ... የእንግሊዝ ዳኞችን ራስ ያዞረ ዋናው ጉዳይ ይሄው የባልና ሚስት ፍች ጉዳይ ነበር



... ያላቻ ጋብቻ ለልብ ወለድ ድርሰት ጥሩ ጭብጥ ሊሆን ቢችል እንጂ በገሃዱ ዓለም ህይወት ውስጥ ከሬት የመረረ ነው" በዐይኖቹ አስተናጋጇን ፈልጎ በጥቅሻ ከውስኪው እንዲጨምርለት አዘዘው።

አብነት በአጠጣጡ ፍጥነት ጉድ እያለች "ይህ ሰው እንደ ከብት ይበላል፣ እንደ ከብት ይጠጣል፣ እንደ ከብት ያስባል፣ ዛሬ ደግሞ እንደ ከብት ታርዶ ይሞታል" ስትል አሰበች። ቆይታም "በጣም የሚያሳዝነው ነገር ደግሞ ልጅቷ ፀንሳለች አሉ... ምን አይነት መጥፎ አጋጣሚ ነው?" አለች ስሜቱን ለመረዳት ገጽታውን እያጠናች።

ጠበቃው በምንቸገረኝነት ትከሻውን ሰብቆ፣ የታችኛውን ከንፈሩን ልጥጥ አደረገና "ይሄ እንኳ ከቁጥር የሚገባ ችግር አይደለም። ተደብቆ የገባ የሰው ቆሻሻ ተደብቆ ይፈናጠርና በቆሻሻ መጣያ ቱቦ ውስጥ ይወረወራል። ይሄ ያለንበት ዘመን እኮ ሃያ አንደኛው ክፍለ ዘመን ነው። እንኳን ሳይፈለግ ለተወለደ ከንቱ ተፈልጎ ተወልዶ በእንክብካቤ ከተያዘው ቦታ የሚያገኘው ከሺ አንድ ነው። በተለይ ሶስተኛው ዓለም በሚባለው ጨለማ የዓለም ክፍል ሳይፈለግ የተወለደ ህፃን እጣ አይጎንም ያው ጨለማ ነው። ዐይኑን ገልጾ ወደ ጨለማ ከሚወረወር፣ ዐይኑን ሳይገልጥ እዚያው ከጨለማ ውስጥ እንደጨለመበት መቅጨት፣ እንደ ውለታ ይቆጠራል... ሃሃሃ ... አጠፋሁ?"

በገጹ ላይ የሚታየውን ጭካኔ ስትመለከት የተሸከመችውን ጽንስ ጎትቶ ያወጣባትን ያህል ሰውነቷ ጭብጥ አለ። ልቧም እየደጋገመ ይረግመው ጀመር "አራዊት!! አራዊት!! አራዊት!!"

ጠቢቃው ሁኔታዋን እያስተዋለ "ምነው? ፈራሽ?" አላት ትከሻዋን እየደባበሰ።

"እ... አልፈራሁም... ግን እንዲያው... ሃይማኖታዊ፣ ሞራላዊና ሰብአዊ ጉዳዮችን ሁሉ ትተን፣ ይህ ጉዳይ በህግ ፊት አያስጠይቅም?" ስትል ጠየቀችው።

ከትከት ብሎ ሲስቅ ቆየና "በህግ ፊትማ ምን የማያስጠይቅ ነገር አለ? የሰው ሚስት መሳም በህግ ፊት ሳሚውንም ተሳሚዋንም ያስጠይቃል። ያች ምስኪን ሴት ያለባሏ ለምን በሌላ ሰው እንደተሳመች የምትሰጠው ምክንያት ዋጋ አይኖረውም። ህግ አታድርጊ ያላትን አድርጋለችና ትቀጣለች። የሰው አጥር ዘሎ ሲሰርቅ የተያዘ ሌባም በህግ ይጠየቃል። ለምን? ህጉ የሰረቀ ወንጀለኛ ነው ብሎ ደንግጓልና። ምናልባት ያ ሌባ በርሃብ ሊሞት የቀረው የአንድ ሰዓት እድሜ ሊሆን

ይችላል። ምናልባትም በቤቱ ውስጥ እንደ አባግ ግልገል እየተንሚጨ ራብን እያሉ የሚጮሁበትን ስድስት ህፃናት ልጆቹን ህይወት ለማትረፍ እጥር ዘሎ ይሆናል። ምናልባትም የቀን ሥራ እንኳን አጥቶ አመት ሙሉ የተንከራተተ ምስኪን ይሆናል። ይሄ ምክንያት ግን በህግ ፊት ኢምንት ነው። እና ህጉ-ወጥ ውርጃም እንደዚሁ ነው። ሆኖም ማህበረሰቡም ህገወጥ ውርጃን ይቃወማሉ። ውርጃን ስታከናውን የተገኘች ምስኪን ሴትም በህግ ትቀጣለች። በማህበረሰቡም ዐይንሽ ለአፈር ትባላለች። ምናልባትም እኮ ያች ሴት የፀነሰችለትን ሰው እንኳን አታውቅ ይሆናል። ምናልባትም ልጁን የምታሳድግበት ጥሪት ቀርቶ ለራሷም ትልሰው ትቀምሰው ቁራሽ የሌላት ምስኪን ትሆናለች። ለህጉ ግን ይህ ምክንያቷ የንብስ ያህል ቀላል ነው። አስተውይ... ሆኖም ሆነ ማህበረሰቡ ልጁን ከነህይወቱ ብትወልድ ለአንድ ወር የወተት ሂሣብ ሳንቲም አይወረውርላትም፣ ስቃይዋን አይሰቃይም፤ ከመከራዋ አይካፈልም። ብቻ ደረቱን ነፍቶ... ሁሉም ግምባሩን ቋጥሮ "የፀነስሽውን ውለጂ!" ይላታል ወገቧን አጥብቆ ይዞ። ህግ ምክንያታዊ አይደለም። አንዳንዶች እንደሚሉት በእውነትም እውር ነው። ... እውር ህግ ... እውር ዓለም ... ሃሃሃ .... በህግና በህዝብ ፊትማ ምን የማያስቀጣ፣ ምን የማያስወግዝ፣ ምን የማያስኮንን ነገር አለ?! በራስሽ ገላ ለማዘዝ እንኳን ፈተና አለብሽ ሃሃሃ..."

የውሲኪው ብርጭቆ አሁን አሁን እየተሞላ ይፈራረቃል፣ የጠበቃው ቀይ ፊት ሣምባ እየመሰለ ሄዷል። ከአንድ የህግ ሰው በህግ ላይ ይሄን የመሰለ ውግዘት ስትሰማ ተገረመች። እንደገመተችው የሚናገረው ሁሉ ከልቡ አይደለም። ለጠየቀችው ጥያቄ ለእርሱ የነገር አካሄድ እንዲያመቸው ብቻ የሚለፈልፈው ተረት ነው። "አረመኔያዊ ሰብአዊነት!" አለች በሀሳቧ።

"እርሱስ ይሁን... ሌላው የገረመኝ ነገር ደሞ የሰው ፍቅረኛ ነጥቆ ካሳገባሁ እያለ የሚባትለው ባርባሪያን ነው... ከሌላ ወንድ መጸነሷን እያወቀ። እ... ለእርሱ አንዳችም ፍቅር እንደሌላት እየተረዳ?! እንዴት ትዳርን በሚያክል ክቡር ነገር ይቀልዳል?! ያለ መንፈሳዊና አካላዊ የፍቃድ አንድነት የሚመሠረተውን ትዳር ከቶ. ስሙን ማን ሊለው ነው?! ደባልነት?! ወይንስ ሲኦል?! ለህሊናው አይቀፈውም?! መንፈሱን ትንሽ አይሰቀጥጠውም?!" አለች እጆቿን እያወናጨፈች፣ ጠረጴዛውን በቡጢ እየቀጠቀጠች።

ጠበቃው ግምባሩን ቅጭም አድርጎ ሲመለከታት ከምትጫወተው ተውኔት ወጥታ ወደ እውነታው ዓለምና ወደ ገዛ ባህርይዋ እንደተመለሰች ስለገባት ፈጥና ገጽታዋን አፈካችው "ሆሆሆይ!.... በእውነቱ የአንዳንድ ወንዶች ጠባይ ይገርመኛል...



እንተገስ አይደንቅህም? እስኪ በርሱ ቦታ ብትሆን ምን ይሰማሀል?" ስትል ጠየቀችው።

ዛሬ ግራ ጋዴምን ልታከል ምንም ያህል አልቀራት። "ግን ምንድነው እንዲህ የለወጠኝ?" ጠበቃው ለጠየቀችው ጥያቄ መልስ ለመስጠት በመጠጥ የደነዘዘ አዕምሮውን ለማንቃትና መጎልደፍ የጀመረ ምላሱን እስኪስል ድረስ ባለችው ቅጽበት ራሷን ጠየቀች። መልሱ አልከበዳትም። ተስፋ መቁረጥ ነው። ቻርሊን አጥታለች፤ አባቷንና ቤተሰቧን ታጣለች፤ በጠበቃው ምክንያት ምን ያላጣችው አለ? ምንም። ያለፉት መልካም ቀኖች ዳግም ተመልሰው እንዳይመጡ ከፊት ለፊቷ የተጋረጠው የሰው አጋንንት ጥቁር መጋረጃ ሆኖ ተስፋዋን አጨልሞታል። ሰው ተስፋውን ከቀበረ፤ ይሉኝታ፣ ስነ-ምግባር፣ ሀዘኔታ፣ ፍርሃት... በውስጡ ቦታ አይኖረውም። ያልሆኑትን መምሰልማ በጣም ቀላሉ ጉዳይ ነው።

"በእርሱ ቦታ ብትሆን ምን ይሰማሃል ነው ያልሽኝ? ምንም አይሰማኝም። ምናልባትም ያ ሰው ከነፍሱ በላይ ልጅቱን ወዷት ይሆናል..."

"እርሷ ካልወደደችውስ?"

"የራሷ ጉዳይ ነው። እርሱ ከወደዳት ይበቃል። አየሽ ዘመኑ የውድድር ዘመን ነው... የጥሎ ማለፍ ትንንቅ። በዚህ ትግል ውስጥ ልብ የተመኘውን ጨብጦ የመንፈስ እርይታን ማግኘት ዋነኛው የህይወት ግብ ነው። ዋናው ጉዳይ የርሷ ፍቃደኛ መሆን ወይም አለመሆን አይደለም። የርሱ ፍላጎት ብቻ ነው። እዚህ ላይ መርሳት የሌለብሽ ዋነኛ ጉዳይ ሴት ልጅ ለማዳ እንስሳ መሆኗን ነው። እምን፣ ...ይህን እውነት በድፍረት እናገራለሁ፤ ሴት ልጅ አዲሱን ፍቅረኛዋን ባገኘች ወር ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ነባሩን ፍቅር ከልቧ ውስጥ አጥባ ትደፋለች። ዋናው ጉዳይ የሴትን ልጅ አያያዝ ከማወቁ ወይም ካለማወቁ ላይ ነው። ጆጌሬዳዬ... እኔ አንድ ክፉ አመል አለኝ፣ እውነቱን ፊት ለፊት እናገራለሁ ያለ ይሉኝታ። እና አሁንም ብዙዎች የማይቀበሉትን አንድ እውነት እነግርሻለሁ... ሴት ልጅ ምንጊዜም የገንዘብ ባሪያ ነች! ገንዘብ የማይገዛው የሴት ልጅ ገላ የለም!"

አብነት ከውስጥ መንደድ ጀመረች። ለባርነት ህይወት ከአጫት ሰው እንደበት ይህን ቀረርቶ ስትሰማ እልኳ ጉሮሮዋን አንቆ በዝግታ አንቀጠቀጣት። አንዳች ተቃውሞ ከመተንፈሷ በፊት ግን መድረክ ላይ እንዳለች ምናልባትም ለአሥረኛ ጊዜ እስታወሰችና በረኝርሙ ተንፍሳ ራሷን አቀዘቀዘች።

ጠበቃው ድንገት ስዓቱን ተመለከተና አለተናጋጁን ጠርቶ ሂሣብ ጠየቀው። ከፍያውን አጠናቀው ሆቴሉን ለቀው ሲወጡ እግሩ እንደተሳሰረ ተረዳች። መኪናው ውስጥ ገብተው ሞተሩን ሲቀሰቅስም ዐይኖቹ መፍዘዝ ጀምረው ስለነበር አደጋ ሊያጋጥማቸው እንደሚችል ገመተች። ይሁን እንጂ አልተጨነቀችም። ከሞት የተሻለ ህይወት አይጠብቃትምና መኖርም ይሁን አለመኖር ለርሷ ትርጉም የለውም።

መኪናዋ ከሆቴሉ ወጥታ ጉዞዋን ስትጀምር ወዴት እንደሚሄዱ አልጠየቀችውም። ወደ ሲኦል ይዟት ቢወርድ እንኳን ግድ አይሰጣትም። በዚያች ቅጽበት ለርሷ የህይወት ዋጋ ኢምንት ታክል ቀላል ነበረች። ምናልባትም "ህይወት ክቡር ነው" የሚባለው የተለምዶ ፈሊጥ ሁልጊዜም ለሁሉም እኩል እንደማይሰራ የተገነዘበችው በዚያ ጊዜ ነበር። እስከ ተስፋዋ የጨለመ ህይወት ክብሯ ምን ላይ ነው። ሞትን ርካሽና ተራ ለማድረግ የተፈዘ እንጂ ይህስ አባባል ሁሌም እውነት አይሆንም። መኪናዋ የቄራን አቅጣጫ ይዛ ቁልቁል እየተምዘገዘች በጎተራ አቋርጣ የንፋስ ስልክን አቅጣጫ ስትይዝ ሁሉ የምታሰላስለው ይህንኑ ብቻ ነበር።

ከሀሳቧ ስትነቃ ምናልባት ወደ ቤቱ እየወሰዳት ሳይሆን እንዳልቀረ ገመተች። በምትመለከተው የጠበቃው ሁኔታ በአካልም በመንፈስ ጥንካሬም የበላይነቱ የርሷ ነው። እንደ ኳስ እንዳነጠራት እንደጢብጢብ ቅጠል ልትጫወትበት ትችላለች። ስለዚህ ወደ ፈቀደው እንዲወስዳት ፈቀደችለት።

መምሸት ጀምሯል። የመንገድ መብራቶችም በርተዋል። የቅዱስ ዮሴፍን ቤተክርስቲያን አለፍ እንዳሉ መኪናዋ በሁተቀኝ በኩል ታጥፋ ጥቂት ከሄደች በኋላ ከአንድ ቪላ ቤት በር ላይ ቆመች። አንዲት ልጅ እግር ሴት የውጭውን በር ከፍታ አስገባቻቸው። እብነት የጠበቃው ሠራተኛ እንደሆነች ገመተች።

በቤቱ የውጭ መብራት እንደተመለከተችው ግቢው በልዩ ልዩ አበቦች የደመቀና ረጃጅም የጥላ ዛፎች ያሉት ነው። በጠበቃው መሪነት ወደ እንግዳ መቀበያው ክፍል ስትገባ የተመለከተችውም ዘመናዊ የቤት እያያዝ ነበር። እንድትቀመጥ እንኳን ሳይጋብዛት እየተወላገደ ወደ ሶፋው በመሄድ ዘጭ አለና ተቀመጠ። ሠራተኛዋ የእንግዳ መቀበያውን በር ዘግታ ስትመለስ እንደቆመች በማየቷ በጠበቃው ትይዩ ባለው ሶፋ ወንበር ላይ እንድትቀመጥ ጋበዘቻትና ወደ ውስጥ ዘለቀች። እብነት በርሳዋን ጠረጴዛው ላይ አኑራ እግሮቿን አጣምራ ተቀመጠች።



የፈዘዙ ዐይኖቹ ያረፉት በተጣመሩት ባቶች ላይ ነበር። በከፊል መጨፈን የጀመሩ ዐይኖቹን በልጥጦ አጎረጠባት። እነኛ ዐይኖች አሁንም የወሲብ ርሃባቸውን እያዛጉ መሆኑን ስትመለከት የእቅዱ መሳካት እየተቃረበ መሆኑን ገመተች። ወዲያው በሙቀት አመካኝታ የለበሰችውን ባለፈር ጃኬት አወለቀችና ጠረጴዛው ላይ አስቀመጠችው። እጅጌ ጉርዱ ስስ ሹራቧ ጡቶቿን አፍጥጦ አወጣቸው፤ ራቁት ከንዱን አጋለጠው።

ጠበቃው ከስካሩ ዓለም ለመንቃት ራሱን ደጋግሞ ነቀነቀ። ከፊት ለፊቱ የሚመለከተውን እውነት ዐይኖቹ ሊያምኑ አልቻሉም። ስንቱን ሌሊት ሲያልመው የኖረ ገላ እነሆ ከፊት ለፊቱ ሊፈነዳ የደረሰ የጽጌሬዳ አበባ መስሎ ደምቋል። በየደቂቃው ሊያያቸው የሚናፍቁት ኮከብ ዐይኖች ሽፋላቸውን ቀደው ሊወጡ የሚታገሉ እንደመሰሉ ይንቦገቦጋሉ። ምራቁን ደጋግሞ ሲውጥ ማንቁርቱ ሲወድቅና ሲነሳ ተመለከተች።

"ተጫወት እንጂ..." ያፈረች ባስመሰላት ፈገግታዋ ጭራሽ አነሆለለችው።

የሶፋውን መደገፊያ ተመርኩዞ ተነሳና ከተቀመጠችበት ሶፋ ጀርባ በመዞር ትከሻዋን እየደባበሰ ያልገመተችውን ጥያቄ ጠየቃት።

"አባትሽ ... በጣም አዝነዋል - አይደል?"

"ለምን? በምን ምክንያት?"

"ስለሆነው ነገር ሁሉ..."

"የራሱ ጉዳይ። በራሱ ጊዜና እድሜ የራሱን የደስታ ህይወት አሳልፏል። በማምሻ እድሜ ማዘን ምናልባት እጣ ፈንታው ሆኖ ይሆናል... የአባባን ነገር እርሳው... ምናልባት አሮጊት ሚስቱ ብቻ ስለእርሱ ትጨነቅ... ልክ አይደለሁም?" አለችው ትላልቅ ዐይኖቿን እያጉረጠረጠችበት።

ከፊት ለፊቷ በመዞር ግምባሩን ቅጭም አድርጎ በጥርጣሬ ዐይን ይመለከታት ጀመር። እብነት ተገረመች እንደዚያ ሰክሮ እንኳን የተጠራጣሪ አዕምሮው ጉልበት ገና አልደከመም።

"እንደዚያ የምታስቢ ከሆነ ደስተኛ ነኝ... ግን በምንም ነገር በኔ እንዳትፈርጂ... የሆነው ሁሉ መሆን የሚገባው ነገር ነው። ይህንን ያደረኩት ደግሞ ለሁለታችንም የጋራ እድገት ስል ነው። ልትፈርጅልኝ እንጂ ልትፈርጅብኝ አይገባም። ...ለምን አፈቀርከኝ ብለሽም አትውቀሽኝ። ይህ ጉዳይ ከኔ አቅም በላይ ነው። አንድ እውነት ብቻ እውነት ነው... ጽጌሬዳዬ እፍቅሬሻለሁ... የእኔ መሆን የሚገባውን

ደግሞ መሬት ቧጥጨና ለማይንም ቢሆን ረግጬ የኔ ማድረግ አለብኝ 'ህይወት የህይወት ጥያቄ ነች' እይደል የሚሉት አባትሽ?" እንጉቱ ጭንቅላቱን ተሸክሞ መቆም ያቃተው ያህል ራሱ ግራና ቀኝ መዝመም ጀምሯል።

ሠራተኛዋ ሁለት ውስኪ የተቀዳባቸው ብርጭቆዎች በማቅረቢያ ይዛ መጣች። አንዳንድ የበረዶ አንኳር በብርጭቆዎቹ ውስጥ ከጨመረች በኋላ እየተጣደፈች እንደገባች እየተጣደፈች ወጣች። ጠበቃው እየተወላገደ ወደ ክፍሉ አንድ ማእዘን በመሄድ የዘመናዊውን ቴፕ ሪከርደር መጫወቻ ተጫነው። ክፍሉ በሙዚቃ መሣሪያ ብቻ በተቀነባበረ የባህር ማዶ ሙዚቃ ተሞላ።

ወደ ነበረበት በመመለስ የውስኪ ብርጭቆውን ሲያነሳ አብነትም ብርጭቆዋን አንስታ ቆመች። "አንድ ብለን ስለጀመርነው ፍቅራችን!" ብርጭቆውን ከብርጭቆዋ ጋር አጋጨ።

"እስከ ዘለዓለሙ ለምንሰናበታት ዓለም!" አብነት በውስጧ አሰበች።

ከውስኪው ደጋግመው ተጎነጩለት። ሙዚቃው ይጮሃል፣ ጠበቃው የባጥ የቆጡን እየዘላበደ ይስቃል፣ አብነት መንፈሷ መሸበር፣ ልቧ በፍጥነት መምታት ጀምሯል።

ድንገት መለፍለፉን አቆመና ትክ ብሎ ይመለከታት ጀመር። በአዕምሮዋ የሚመላለሰውን ጉዳይ ገጿን አንብቦ የደረሰበት ስለመሰላት ደነገጠች። በእፍታ ግምባሯ ላብ ማመንጨት፣ ጣቶቿ መንቀጥቀጥ ጀመሩ። ዐይኖቿን ከዐይኖቹ አሸሸቻቸው። ከተቀመጡበት ተነስቶ ከጀርባዋ ዞረና ረዥሙን ፀጉሯን ይደባብሰው፣ ማጅራቷን ይዳስሰው ጀመር። እንደ ብረት የቀዘቀዙ እጆቹ በውስጣቸው ደም የሚመላለስባቸው አልመሰላትም።
"አብ - ነት..."
"አቤት..."
"ለምን ስታሰቃይኝ ኖርሽ?"

ከትከት ብላ ከጣራ በላይ መሳቅ ፈለገች። አልሳቀችም። ለጠየቃት ጥያቄም አልመለሰችለትም እርሱም መልሷን አልጠበቀም። የግራ ክንዷን ጨምድዶ ከተቀመጠችበት አስነሳት - አልተከላከለችውም። ቦርሳዋንና ጃኬቷን ከጠረጴዛው ላይ አንስታ ተከተለችው። በመኝታ ክፍሉ በር ላይ ከሠራተኛዋ ጋር ተላለፉ። ዐይኖቿ ፈጥነው የመኝታ ክፍሉን መፈታተሽ ጀመሩ። በሰፊው ክፍል ውስጥ የአባባ ምንጣፍ የተጣለበት ያማረ ሰፊ አልጋ በአንድ ማእዘን፣



ባለሶስት ተከፋች ቁምሳጥን በሌላ ማእዘን፣ የራስጌ መብራት የተቀመጠበት ኮሞዲኖ፣ አንድ የሶፋ ወንበርና መለስተኛ ጠረጴዛ ሥርአት ይዘው ተቀምጠዋል። ቢጫ ፈር ያለው የወለል ምንጣፍ የመብራቱን ብርሃን አፍኖ ክፍሉን አድምቆታል።

ፈዛ እንደቆመች ቀረብ ብሎ ጉንጯን ሳመና እጇን ይዞ ከሶፋው ወንበር ላይ አስቀመጣት። ብዙም ሳይቆይ እግሩን እያማታ ከክፍሉ ወጣ። አብነትም ፈጥና ቦርሳዋን ከፈተችና ማበጠሪያዋን አውጥታ ወደ ቁምሳጥኑ መስተዋት በመጠጋት ረዥሙን ፀጉሯን ማበጠር ጀመረች። በጆሮዋ ውስጥ የገዛ ቃሏ መደወል ጀምሯል። "... ቻርሊ እስከ መቃብር ከአንተው ጋር ነኝ፣ ብክዳህ የቆምኩባት ምድር ትክዳኝ!" የገዛ ቃሏ ለመንፈሷ ብርታትን ሰጣት። እንደሌላው ጊዜ ሁሉ አልከበሳትም፣ አልወቀሳትም በርቺ አላት።

ብዙም ሳይቆይ በመስተዋቱ ውስጥ ጠበቃው ከጀርባዋ ሀውልት መስሎ ሲመለከታት አየች። ባንድ ትሪ ላይ ሁለት ብርጭቆዎችና የውስኪ ጠርሙስ ይዟል። ማበጠሪያውን ፀጉሯ ላይ እንደተወች የያዘውን ትሪ ተቀበለችውና በመለስተኛው ጠረጴዛ ላይ በማኖር ለሁለቱም ውስኪ ቀዳች "ለፍቅራችን!" ብርጭቆዎቻቸው ዳግመኛ ተጋጩ። ከያዘው ብርጭቆ አልኮሉን ተጎነጨለትና የረሳውን ነገር እንዳስታወሰ ሰው አይነት ድንገት ብሎ "አ - አብነት ስልክ ይፈልግሻል ... እዚህ እንደሆንሽ አድራሻ የሰጠሽው ሰው አለ እንዴ?" ሲል ጠየቃት።

ግምባሯን ቋጥር አድርጋ በመገረም ስትመለከተው ቆየችና "ትቀልዳለህ? ማን ነኝ ይላል?" ስትል ጠየቀችው። በግዴየለሽነት ትከሻው ሰበቀና "እንጃ!... ተካልኝ ባልቻ ነው ያለኝ?... እንደዚያ ዓይነት ስም..." ከውስኪው እንደገና ተጎነጨለት። ይህን ስም ዛሬ ለሁለተኛ ጊዜ መስማቷ ነው። ግራ እንደተጋባች፣ እንደተገረመችና አፏን እንደከፈተች ለአጭር ጊዜ ፈዛ ቀረች። "ተካልኝ ባልቻ? ይህ ሰው ማነው? ከኔ ምን ይፈልጋል ? በዚህ ሰዓት እዚህ መሆኔን በምን አወቀ?" መልስ ያላገኘችላቸው ጥያቄዎች በጭንቅላቷ ውስጥ ተንጫጩ።

"ይቅርታ አድርግልኝ የስልኩን ጥሪ ልመልስ..." አለችና መልሱን ሳትጠብቅ እየተጣደፈች ከመኝታ ክፍሉ ወጥታ ወደ ሳሎን አመራች።

ስልኩ የተቀመጠበትን ቦታ ለማግኘት ጊዜ አልወሰደባትም። ከትልቁ ሶፋ አጠገብ ከአንድ አነስተኛ ጠረጴዛ ላይ አየችው። እጀታው ከቀፎው ላይ ተነስቶ አጠገቡ ተቀምጧል። እየፈራች እጀታውን እንስታ ከጆሮዋ ላይ አደረገች። ስልኩ የመያዝ ድምጽ አሰማት። ይበልጥ ግራ ተጋብታ እጀታውን መልሳ ከቀፎው ላይ አስቀመጠችና ቆመች።

"ይህ ሰው ማን ነው? ከኔ ምን ይፈልጋል?" የተቋረጠው ስልክ እንደገና ሊደውል ይችራል በሚል እምነት እጇቿን አጣምራ ጠበቀች - ስልኩ አልጠራም።

ግራ ተጋብታ እንደቆመች አንድ ነገር አስታወሰች። ጠበቃው ውስኪ ሊያመጣ ከነበሩበት መኝታ ክፍል በወጣበት ጊዜ የስልክ ጥሪ ድምጽ አልተሰማትም። የመኝታ ክፍሉ ስልኩ ካለበት ብዙም ስለማይርቅ የስልኩን ጥሪ ድምፅ መስማት ነበረባት። ጠበቃው ምን እንዳሰበ ሳላገባት ፈጥና ወደ መኝታ ክፍሉ ሮጠች።

አልጋው ጠርዝ ላይ ተቀምጦ ግምባሩን ቋጥሮ ጠበቃት። በገጹ ላይ ይታይ የነበረው የስካር መንፈስ ጠፍቷል፤ ዐይኖቹም መፍዘዛቸው ቀርቶ በንቃት ያስተውላሉ።

"ስልኩ ተዘግቷል ... ያልከውን ሰው ላገኝ አልቻልኩም..." አለች ጠበቃው በአፍታ ባሳየው ለውጥ እንደተገረመች። "ተይው... ምናልባት የለየለት እብድ ወይም ተራ ሰካራም ይሆናል" አላት በተጣራ አማርኛ። የተሳሰረ እንደበቱ ተፈቷል። የአብነት ጠንካራ መንፈስ መፈታት ጀመረ፤ ልቧም ተሸበረባት። በአፍታ እንዲህ ሀይልና ጉልበት ያገኘበት ሚስጥር ምንድነው? በጥንቃቄ እየተራመደች ወደ ሶፋው ሄደችና ተቀመጠች።

"ለመሆኑ ይሄ ተካልኝ ባልቻ የሚባል ሰው ማነው?"

"እንጃ!... ፈጽሞ አላውቀውም። ከኔ ምን እንደሚፈልግ አልገባኝም።" በጠበቃው ገጽታ ላይ ሥጋትና ጥርጣሬ ሲያጠላበት ተመለከተች። በእርሱና በዚህ ተካልኝ ባልቻ በሚባል ሰው መካከል ሊኖር ስለሚችለው ግንኙነት መገመት አልቻለችም።

"አንተም ታውቀዋለህ?" እየተጠራጠረች ጠየቀችው።

"አላውቀውም" በርግጠኝነት መለሰላት።

ትይዩ ሆነው እንደተፋጠጡ ጥቂት ደቂቃዎች ሮጡ። "ለነገሩ... አንቺም እንደ አባትሽ እልኸኛ ነሽ..." የጠበቃው የምጸት ሳቅ በአፍታ ክፍሉን ሞላው።



ምን ለማለት እንደፈለገ ስላልገባት የተጨነቁ ዐይኖቿን እያርገበገበች በፀጥታ ትመለከተው ጀመር።

"አባትሽ ድርጅታቸውን በየጊዜው ከሚዘፈቅበት የችግር አዘቅት ውስጥ ለማውጣት ለማንም ህይወት እንደማይሳሱ ታውቂያለሽ። በዚህ ድርጅት ሳቢያ ብዙ ደም እንደፈሰሰም ሳያስጠኑሽ እንዳልቀሩ ርግጠኛ ነኝ። እኔ እንኳን በቅርብ ጊዜ ... 'ይሀ ድርጅት እንደቦረንትቻ ደም ለምዷል...' ሲሉ ሰምቻቸዋለሁ። አዎን ለምዷል። ታዲያ አሁን እኔን ጭዳ ለማድረግ ምን እጅና እግራቸውን እንዳሰራቸው ታውቂያለሽ?" ሲል እየጮኸ ጠየቃት።

"አላውቅም" ስትል ፈጥና መለሰች። በእውነትም የምታውቀው ነገር አልነበረም። ሳምንቱን ሙሉ አባቷ ለምን ጠበቃውን ፀጥ ማሰኘት እንዳልቻሉ እየደጋገመች ራሷን ትጠይቅ ነበር።

"በዚህ እንኳን አምንሻለሁ... በርግጥም አታውቂም ነበር ማለት ነው። አየሽ በእኔ ህይወት ላይ ማንኛውም ዐይነት አደጋ በተቃጣ ወይም በደረሰ በሰላሣ ደቂቃዎች ውስጥ ሰነዱ በፖሊሶቹ እጅ የሚገባበት መንገድ ሁሉ ተመቻችቷል፤ ይህንንም አሳውቄያለሁ"

አብነት ደነዘዘች። ለካስ ጠበቃውን መግደል ለተፈጠረው ችግር ሁሉ የመፍትሔ ቁልፍ አይደለም?! የአባቷ እጅና እግር የታሰረበት ምክንያት ገባት። በራስ የመተማመን ትምክህታቸው የተናደበት፣ በህይወት ፍጹም ተስፋ የቆረጡበት ምክንያት ተገለጸላት። በእርግጥም ብቸኛ ተስፋቸው እርሷ ብቻ ነበረች።

በርሷና በርሳቸው መሃል የተዘረጋው መጋረጃ ቻርሊ ነው። ይህንን መጋረጃ መተርተር ደግሞ ከምንም ነገር ይልቅ ቀላል ነው። እና ቻርሊ... ምስኪን... ቻርሊ... እንደ ቦረንትቻ ደም ለለመደው ድርጅት የዘንድሮው ጭዳ ነው። አሁን ሁሉም ነገር ወለል ብሎ ታያት። የዚህ ሁሉ ውስብስብ ችግር ፍፃሜ ቻርሊን ሰውቶ የሚጠናቀቅ መሆኑን ተረዳች። ዝግ እያለ ይንቀጠቀጥ የነበረው ሰውነቷ ፍጥነቱን ጨምሮ ይንዘፈዘፍ ጀመር።

"አንቺ ግን ይህንን ሁሉ አታውቂም ነበር... ይህን ብታውቂ ኖሮ የኔን ህይወት ለማጥፋት ታጥቀሽ ባልመጣሽ ነበር!" አላት።

ካቀረቀረችበት ቀና አለችና በመገረም ዐይኖቿን አፍጥጣ አስተዋለችው፤ በምፀት ፈገግ አለ። ይሀ ሰው ነብይ ነው ወይንስ ጠንቋይ ሲቀልብ ኖሯል?!

"የማዝነው በራሴ እንጂ ባንቺ አይደለም ... ፍቅርን ስጋብዝሽ ሞት ደገስሽልኝ" ራሱን በሀዘኔታ ወዘወዘው። ተስፋ መቁረጥ፣ ጥላቻና ንቀት ባንድነት ተዋህደው ገጽታውን አመሰቃቅለውታል።

"አንተ ሰው የምትናገረውን የምታውቅ አልመሰለኝም..."
ከለበሰው ጃኬት ኪስ ውስጥ በቦርሳዋ ይዛው የነበረውን ባለ ቀንድ እጀታ ጩቤ አውጥቶ አሳያት!

ትንፋሿ እንደመቆም፣ ጭንቅላቷ እንደመዞር አለባትና ዐይኖቿ ተበለጠጡ። ዐይኖቿ የሚያዩትን አዕምሮዋ አምኖ ሊቀበል አልቻለም። ስልክ እንደሚፈልጋት አስረድቶ ወደ ሳሎን እንድትሄድ ባደረጋት ደቂቃዎች ውስጥ ቦርሳዋን ይፈትሽ እንደነበር አወቀች።

"በጣም ተራ ሰው ነህ፣ ከተራም ተራ... የሰው አተላ የሆንክ ሰው ነህ! ቦርሳዬን እንድትፈትሽ ማን ፈቀደልህ?" ድምጿ እየተንቀጠቀጠ የስድቡን መአት አወረደችበት።

"ስርዐት ስለጎደለው አድራጎቴ ይቅርታን እጠይቅሻለሁ... ያን ባላደርግ ደግሞ ሊደርስ የሚችለውን ጥፋት ገምተሽ ይቅርታ እንደምታደርጊልኝ አምናለሁ። 'ተራ ሰው ነህ' ነው ያልሽኝ?! አንቺ ደግሞ ፍቅር የማይገባሽ ተራ ነፍሰ ገዳይ መሆንሽን የምገልጸው በፍጹም አክብሮትና ትህትና ነው ...ሃሃሃሃ" አሁንም በምፀት ሳቀ። አባቷ "ጠብቃው አሸንፎናል" ያሏት ትዝ አላት።

"በርግጥም ተሸንፌአለሁ" ስትል አሰበች፣ ሽንፈቷን አምና ለመቀበልና እጅ ለመስጠት ግን አልከጀለችም። ከውስጧ ሆኖ የሚያጸናት የገዛ ቃሏ ምንጊዜም የመንፈሷ ብርታት፣ የልቧ ሁሉ ጉልበት ነው። "ቻርሊ... እስከ መቃብር ከአንተው ጋር ነኝ... ብከዳ..."

ስውነቷን የሚያንዘፈዝፈው እልህ ሊበርድላት አልቻለም። ዛሬም ያልተዋጣላት ተዋናይ ሆነች። በርግጥም ሙያው ለሙያው መፈጠርን የግድ ይላል። ሣራ ጋዴምን በሆነች እንደምን በታደለች ነበር?!

ጠብቃው የገዛ ጩቤዋን በእጆቹ እያቀባበለ ይጫወትባታል፣ አንገቱን አቀርቅሮ የጎሪጥ እያስተዋለ በምጸት ይስቅባታል። ቁጭት አንገበገባት ከዚህ በኋላ ተዋናይ ሆና ያልሆነችውን መሆን አላስፈለጋትም። በእጇ የያዘችውን ማበጠሪያ ወርውራ ፀጉሯን በወፍራሙ መጎንጎን ጀመረች።



"እውነተኛዋ የአባትሽ ልጅ፣ እልኸኛና ጀግና ነሽ። የቤት ልጅ ውብት እንደ እመሜት ነበር ቁጡና አሻፈረኝ ባይ በሆነ ጠባይ ካልተጠበቀ ውበቷ ተራና ርካሽ ይሆናል። እየጠላሽኝ በሄድሽ ቁጥር እየወደድኩሽ እንደምሄድ ታውቂያለሽ?! የተመኘሁትን ካላገኘሁ እንቅልፍ የማይወስደኝ ብርቱ ሰው ነኝ... ሃሃሃ"

የሚናገረው የልቡን እውነት ይሁን ሊያበሽቃት፣ ልትረዳ አልቻለችም። ፀጉሯን በፍጥነት እየጎነጎነች ተንጣጣችበት "እውነቱን ማወቅ ከፈለግህ አንተ ሰው ሳትሆን በሃያ አንደኛው ክፍለ ዘመን የምትኖር ሰው የምትመስል አውሬ ነህ... ለመሆኑ የቃል ኪዳን ፍቅረኛ እንዳለኝ ታውቃለህ?"
"አዎን አውቃለሁ"
"ማንነቱንስ ታውቃለህ?"
"አንድ የሰው ገለባ የሆነ ተዋናይ መሆኑን ሰምቻለሁ"
"እንደ ፀነሰኩለትስ ታውቃለህ?"

ፈጥኖ አልመለሰላትም። ለረዥም ጊዜ በዝምታ ሲመለከታት ቆየና "አዎንÞ የፀነስሽለት መሆኑን ቅድም ነገርሽኝ... ማር የምግጥ በግ መሰልኩሽ?" በተራው ከውስጥ መንደድ ጀምሯል።

"እና ይህን ሁሉ ካወቅህ በኋላ እንኳን..."
"አዎን ይህን ሁሉ ካወቅሁ በኋላ እንኳን እወድሻለሁ... አገባሻለሁም"

ፀጉሯን መጎንጎኗን አቁማ በተራዋ ለረዥም ጊዜ በዝምታ ተመለከተችው። የሰው አውሬ ከሆነ ሰው ጋር ባንድ ክፍል ውስጥ መቀመጧን አስታወሰችና ዳግም መሸበር ጀመረች። ፀጉሯን እንደነገሩ አስተካክላ ከተቀመጠችበት በጥንቃቄ ተነስታ ጃኬቷን ለበሰች። የወረወረችውን ማበጠሪያ አንስታ ቦርሳዋ ውስጥ ከተተችና ለመሄድ ተዘጋጀች። ጠብቃው እንዳችም እንቅስቃሴ ሳያሳይ በዐይኖቹ እንቅስቃሴዋን ይከታተላል። በዚህ ድርጊቱ ደግሞ ይበልጥ ተገረመች። በቀላሉ ይለቀኛል ብላ አልገመተችም ነበር።

መኝታ ክፍሉን ለቃ ስትወጣ ከኋላዋ ተከትሎ ከፊቷ በመቅደም የሳሎኑን በር ከፈተላት። የውጭው በር ላይ ሲደርሱ ክንዷን ያዝ አድርጎ አቆማትና "የሰው አውሬ አለመሆኔን በዚህ ድርጊቴ እንደምታረጋግጭልኝ አምናለሁ፣ ልትገድይኝ መጣሽ በስህተት ለቀቅኩሽ። ባንድ ነገር እርግጠኛ ሁኚ ጽጌረዳ ... እስከ ዘለዓለሙ የኔው ነሽ" አላት።

በእጁ ጨምድዶ የያዙትን ክንዷን መንጭቃ ለቀቀችና እፊጠጠችበት "አንተም ባንድ ነገር እርግጠኛ ሁን አቶ ጠቢቃ... እሱ ዘለዓለሙ አታገኘኝም! በማህ... ቢያንስ ቢያንስ አንድ ነገር አያቅተኝም። ነፍሴ በገዛ እጄ ውስጥ ናት!"

የጠቢቃው ዐይኖች በድንጋጤ እንደተበለጠጡና አፉም እንደተከፈተ እየተጣደፈች የግቢውን በር ከፍታ ሄደች። ጠቢቃው ሃሳብ እንደገባው በጨለማው ውስጥ ለረጅም ጊዜ ቆመ። እልኸኛና ሃሣብ ግትር እንደሆነች ስለተረዳ የተናገረችውን አታደርገውም ብሎ አልተጠራጠረም። ለምን ያን ያህል እንደጠላችው ሲያስብ ደግሞ በቁጭት ተንጨረጨረ። ያ ቻርሊ የሚባል የሰው ሽል ፈጥኖ መወገድ አለበት! ለዚህ ቀላል መንገድ በሰነዱ አመካኝቶ አቶ መንገሻን ማስፈራራት ነው።. ጨለማው ውስጥ ቆሞ እንዳፈጠጠ በምጸት ፈገግ አለ።

ወዲያው እብነት ቀስቅሳበት የሄደችው የወሲብ ርሃብ ተሰማውና አራዳ ወጥቶ ለማምሸት በመወሰን ወደ መኪናው አመራ።



## ምዕራፍ ሃያ አንድ

ጥቁሯ ማርቸዲስ በዋቢ ሸበሌ ሆቴል ህንፃ ትይዩ ቆማለች። ናፖሊዮን አምባው በለበሰው ረዥም ጥቁር ካፖርት ኪሶች ውስጥ እጆቹን ከቶ ጥቁር መነጽሩን እንዳደረገ ግራና ቀኝ ተገላምጦ ወደ መኪናዋ ተጠጋ። መንገሻ ተንጠራርተው በሩን ከፈቱለትና ገብቶ ካጠገባቸው ተቀመጠ።

"ጤና ይስጥልኝ ጌታዬ!"
"እንደምን ሰንብተሃል ወዳጄ?"

ከድምጻቸው መሰልቸታቸውንና ተስፋ መቁረጣቸውን ለመገንዘብ ጊዜ አልወሰደበትም። ሲያጨሱት የቆዩት ትምባሆ መኪናዋን አፍኗታል። ናፖሊዮንም ከካፖርት ኪሱ ሲጋራ አወጣ። ክብሪት አቀበሉት።

"ድርጅቱ ለአስቸኳይ ተልዕኮ ይፈልግሃል..." አሉ በመኪናው መስኮቶች ግራና ቀኝ ተመልክተው በቅርብ ሰው ያለመኖሩን ካጣሩ በኋላ።

ናፖሊዮን መልሱን ወዲያው ሰጣቸው "ዝግጁ ነኝ ጌታዬ። ይህ ተልዕኮ ከጠቢቃው ህይወት ጋር የተያያዘ ቢሆን እንደምን ግሩም ነበር..." አለ ሲጋራውን እንደነከሰ፤ በድምጹ ውስጥ ጥላቻና ጭካኔ ነግሶበታል።

መንገሻ ፈጥነው አልመለሱለትም። ዐይኖቻቸውን ቡዝዝ አድርገው ከፊት ለፊታቸው ጨለማው ውስጥ በሚታዩዋቸው ትልልቅ የዘንባባ ዛፎች ላይ ተክለው ሲያስቡ ከቆዩ በኋላ በቅሬታ ፈገግ አሉ። "እንዳለመታደል ሆኖ የጠቢቃው ብልጥ ነፍስ ገና የወጥመዳችንን ጫፍ አልረገጠችም። በርሱ ህይወት ጣታችንን እንዳናነሳ እጅና እግራችን ሁሉ ታስሯል"
"አልገባኝም ጌታዩ..."

መንገሻ ዝርዝር ጉዳዩን አስረዱት። ናፖሊዮን በፀጥታ ሲያዳምጣቸው ከቆየ በኋላ በመገረም ራሱን ወዘወዘ። "እና የዚህ እንደቦረንትቻ ደም የለመደ ድርጅት የዘንድሮ ጭዳ የሚሆነው አንድ ባልተፈለገበት ቦታ የገባ ምስኪን የእግት እሬት ነው"

ናፖሊዮን መነጽሩን አውልቆ በመገረም ሲመለከታቸው ከቆየ በኋላ "በምን ምክንያት ጌታዬ?" ሲል ጠየቀ። መንገሻ አሁንም ዝርዝር ምክንያቱን አስረዱት። ናፖሊዮን በመገረም ራሱን እየወዘወዘ ፈገግ አለና መነጽሩን መልሶ አደረገ።

"ይህ የእማት እራት ቻርሊ የሚባል ቲያትረኛ ነው... ታስታውስ እንደሆን ከጥቂት ወራቶች በፊት ይህ ሰው ከአብነት ጋር ያለው ግንኙነት ምን እንደሆነና ዝርዝር የህይወት ታሪኩን አጣርተህ እንድታቀርብልኝ አዝዤህ ብዙ መረጃዎችን ሰጥተኸኛል"

"አስታውሳለሁ ጌታዬ... አኗኗሩ ሳይቀር የተመሰቃቀለ ምስኪን ሰው ነው"

መንገሻ ራሳቸውን በአዎንታ ነቅንቁና በረዥሙ ተነፈሱ። "አዎን! ምስኪን ነው። ቢሆንም..." የጀመሩትን ለመጨረስ ቃላት ሲመርጡ ናፖሊዮን ተቀበላቸው "እያለቀስን እንበላዋለን!"

መንገሻ ለመጀመሪያ ጊዜ ፈገግ አሉ። "ደግ ብለሃል!... ልክ እንደ እሱ!..." ናፖሊዮንም በምጸት ሳቀ።

"ይህ ጉዳይ መከናወን ያለበት በጣም በአጣዳፊ ነው። እጅግ ቢዘገይ የአንድ ሳምንት እድሜ ብቻ" መንገሻ ግምባራቸውን ቋጥር አድርገው ትእዛዝ ሰጡ።

"አይጨነቁ ጌታዬ"

"ጨረስን!"

ከለበሱት ካፖርት ሥር እጃቸውን አስገቡና አንድ የተጣጠፈች የባንክ ቼክ አውጥተው በእጁ አስጨበጡት።

"አመሰግናለሁ ጌታዬ..." በፍጥነት የመኪናውን በር ከፍቶ ወጣና ከዐይናቸው ተሰወረ። መንገሻም የመኪናዋን ሞተር ቀሰቀሱ።



## ምዕራፍ ሀያ ሁለት

ደመናማ ጠዋት ነው። ንቂሲኮ የመጠጥ መቸርቸሪያ ግሮሰሪዋን የሲሚንቶ ወለል በመጥረጊያ ስታፀዳ ቆይታ ጥራጊውን ወደ አስፋልቱ ጠርዝ በተነችና እጆቿን አራገፈች። ጠዋት ላይ እንዲህ ደመና ሲሆን አትወድም። ቀኑን ሙሉ ደብቷት ነው የሚውለው። ተሳላፊውን መንገደኛ ቆም ብላ ተመለከተች። ሁሉም ዝናብ የመታቸው ቡችላዎች መስለው ታዩዋት። የለበሰችውን ቡናማ ቀለም ያለው ድርያ ሰብሰብ አደረገችና እየተጣደፈች ወደ ግሮሰሪዋ ገባች።

የመጠጥ መቸርቸሪያዋንና የመኝታ ክፍሏን በሚለየው መዝጊያ በሌለው በር ላይ የተጣለውን መጋረጃ ገለጥ አድርጋ ወደ አልጋዋ ተመለከተች። ትላንት አብሯት ያደረው ሰው አሁንም እንዳንቀላፋ ነው - አልቀሰቀሰችውም። በዝግታ ወደ መጠጥ መሸጫው ክፍል ተመለሰች።

በተከፈተው መስኮት ደፍ ላይ ክንዶቿን ጣል አድርጋ ውጭ ውጭውን እያየች ማሰብ ጀመረች። "የሚያሳዝን ፍጥረት ነው... ሌሊቱን ሙሉ ሲቃዥና ሲወራጭ ነው ያደረው... ደግሞ የአንዲት ሴት ስም እየደጋገመ ይጠራል... ምኑ ትሆን? ምናልባት ሚስቱ፣ ምናልባት ደግሞ ወዳጁ ትሆናለች። ምስኪን፤ ፊቷን አዙራበት ይሆናል። ከዚህ በፊት አንድ ቀን ብቻ ቤቴ መጥቶ ጠጥቷል ... ሃሣብ ያለበት ሰው ይመስላል። ትላንት ታዲያ በምን አስታወሰኝና መጣ? ደግሞ ብቻውን መሳቅ ያበዛል ... ለምን ብቻህን ትስቃለህ? ብዬ ስጠይቀው ምን ነበር ማታ ያለኝ? አዎን... አዎን 'ከሰዎች ጋር የምስቀው ሳቅ እራት እራት ስላለኝ ነው' ነው ያለኝ፤ በሰዎች ተስፋ የቆረጠና ኑሮ የጨለመችበት ሰው ይመስላል። እንዲያም ሆኖ ተጫዋች ነው... መልከ መልካም ነው። በእንዲህ አይነቱ ወንድ ላይ ፊቷን የምታዞር እንዴት ያለች ህሊና ቢስ ሴት ናት?! በጠዋት ቀስቅሽኝ ነበር ያለኝ? አስተኛኘቱ ግን ያሳዝናል። ልክ አራስ ልጇን አልጋዋ ላይ እንዳስተኛች እናት ለዚህ ሰው ሩህሩህነት ይሰማኛል። ምነው እዚሁ ተኝቶ በዋለ! ምነው የኔው ሆኖ በቀረ!" ድንገት ማሰቧን አቁማ ከት ብላ ብቻዋን ሳቀች።

"ኧረ አሁንስ አበዛሁት... ወጥ ረገጥኩ... ደግሞ እኔን ለውሎ ወይ ለአዳር እንጂ ለመሰንበቻ ለመከረሚያው ማን ይሻኛል? ለአዳሩና ለውሎውም ቢሆን ሰክረው ጥንቢራቸው የዞረለት። ቀድሞ እኔን ማን ሰው እንደሰው ቆጥሮኝ!..."

ግድግዳ ላይ ወደአንጠለጠለችው የፊት መስተዋት ጠጋ ብላ ፊቷን ተመለከተች። ንቅሳቷ ፊቷ ላይ ህሞት መስሏል። ፈግፍጋ

ልታጠፋው የምትችል ይመስል በሌባ ጣቷ ደጋግማ አሸችው። "ወይ ልጅነት!... ወይ ገጠሬነት!... በገዛ ፊቴ ላይ እንዲጫወቱ የተንጋለልኩላቸው ዕለት ምነው ሞቼ በቀረሁ!" የዘወትር ቁጭቷ ዛሬ ደግሞ ገና በጠዋቱ መጣባት።

እንደገናም ግራ እጇ ላይ ያሰረችውን የግድግዳ ሊያክል ምንም ያልቀረው ሰዓት መልከት አደረገችና ስጋት አጠላባት። ማታ ራሱን ስቶ አልጋ ላይ ከመውደቁ በፊት ማለዳ እንድትቀሰቅሰው ነግሯት ነበር። ልትቀሰቅሰው ወስና ወደ መኝታ ክፍሏ ገባችና መብራቱን አበራች። እጆቹን ተንተርሶ የሞት ያህል እንቅልፍ ወስዶታል።

"አንተ... ሰማህ? ማን ነበር ያለኝ ስሙን? አንተ፤ አፈር በበላሁ! አንተዬ..." አንድ ጊዜ ትከሻውን አንድ ጊዜ ጭንቅላቱን እየወዘወዘች አነቃችው።ቻርሊ ሲንጠራራ ቆየና ዐይኑን ገለጠ።

መጀመሪያ ግምባሩን ቁጥር አድርጎ አልጋው ጠርዝ ላይ አጠገቡ የተቀመጠችውን ሴት በመገረም ሲመለከታት ቆየና ቀና ብሎ ዙሪያውን ቃኘ። "እንዴ... የት?... የት... ነው ያለሁት?" ፈጠን ብሎ ከጆርባው ቀና አለና አፈጠጠባት።

"በአዳዲ ማርያም! ትላንት አብደህ ነበር ማለት ነው?" ንቂሴክ የተገረሙ ዐይኖቿን ታርገበግብበት ጀመር። "ሆሆሆይ!... 'ንቂሴክ' እያልክ ጉንጬን ስትደባብሰኝ ሁሉ አታስታውስም ነበር? ኧረ አንተስ ጉደኛ ነህ ጋሼ..."

ቻርሊ ትክዝ እንዳለ በተቀመጠበት ደንዝዞ ቀረ። ለምን ሰንጋተራ እንደመጣ፣ እንዴት ንቂሴክ ቤት እንዳደረ ትዝ አላለውም። ትዝ ያለው ነገር ገና ከቀን ጀምሮ መጠጣት መጀመሩ ብቻ ነው። ቆይቶ "ለምን እንዲህ ሆንኩ?" ሲል ራሱን ጠየቀና ጥልቅ ሀዘን ልቡን ወጋው። "ምነው ክፋህ... እዚህ በማደርህ ቅር አለህ እንዴ" አለችው ድምጿ ውስጥ ቅሬታ እንደጎላባት።

"ለምን?" ቡዝዝ ያሉት ዐይኖቹ ያዩዋታል እንጂ አይመለከቷትም። ጆሮዎቹ ይሰሟታል እንጂ አያዳምጧትም - በመንፈስ ርቋት ሄዷል።

"እንጃ!" አለች ትከሻዋን ሰብቅ አድርጋ። "ለብዙዎቹ ትንኝ አክለን፣ ውሻ መስለን ነው የምንታያቸው። አንተም ከብዙዎቹ አንዱ እንዳትሆን ብዬ ነዋ"



"ምን አልሽኝ?" ሀሊናውን ለማንቃት ራሱን ደጋግሞ ወዘወዘና ጠየቃት። ያለችውን ቃል በቃል ደገመችለት።

የሰማውን አዳምጦ በዝምታ ሲያስብ ቆየና "አንቺ እንዲያውም ከብዙዎቹ ትሻያለሽ... በአካል ገዝፈው ልእልት መስለው ተብለጭልጨው፣ ትንኝ የሆኑስ ባሉበት አሉ። በስምና በዝና ተኮፍሰው የሳባ ያህል ከቀለሉ የሰው እባቦች ትሻያለሽ" አላት።

ቡዝዝ ያሉት ዓይኖቹ በዐይኖቿ ላይ ቢተከሉም እርሷን እንደማያዩዋትና ርቀው እንደሄዱ ገመተች። የሚናገረው ሁሉ ከልቡ አልመሰላትም።

"ትቀልዳለህ ጋሼ? እውነት ከአብነትም እሻላለሁ?" በመገረም የደፈረሱ ዐይኖቻን በልጥጦ አፈጠጠባት። እንዴት አወቅሽ ማለቱን አላጣቸውም። ቀ ብላ በፍንጭቷ ቀለደችበትና "ምነው ደነገጥክ? ሌሊቱን ሙሉ ስሟን ስትጠራና ስትረግማት እኮ ነው ያደርከው። እርሷን ያገኘህ መስሎህ የኔን ጉሮሮ አንቀህ ይችት የደሃ ትንፋሼን ፀጥ ልታደርጋት ሽትታገለኝ እኮ ነው ያደርከው... እንዲሁ የቁም ስቅሌን ስታሳየኝ። እና አሁን ከአብነት ተሽዬ ታየሁህ?" በዐይኖቿ እያባበለች በጥያቄ ወጥራ ያዘችው።

ለረዥም ጊዜ ሲያስብ ቆየና "አዎን!" አላት ጭክን ብሎ "ከብዙዎች ትሻያለሽ ንቂሴክ ... የአንቺ ጉድ በአደባባይ ይፋ ተጋለጠ እንጂ ... ከመጋረጃ ጀርባ ኧረ ስንቱ ጉድ አለ መሰለሽ! ስሙ እንጂ ለናንተ የተረፋችሁ ለግብሩማ... ምነው ብትተይኝ ንቂሴክ? ምነው የልቤን ቁስል እየነካካሽ ስቃዬን ባታብሽብኝ?" አላት ሰውነቱን አስቆጥቶ።

"እንዴት ያለህ ጥሩ ሰው ነህ ጋሼ!... ብዙዎች ግን እንዳንተ አይደሉም። የሚጥሉልንን ሳንቲም ከቁም ነገር ቆጥረውት እንድንሰግድላቸው ይመኛሉ። እኛነታችንን አዋርደው ውሻ አሳክለው። አንተ ግን ሌላው ቢቀር ለአፍህ እንኳን ከሰው አስተካክልከኝ..."

ቻርሊ በተናገረው ነገር ህሊናው አልወቀሰውም። አብነትን ከንቂሴክ በማስተካከሉ የተበቀላት መሰለው።

"ኧረ ፈጥነህ ተነሳ ጋሼ" ቻርሊ ግራ በተጋቡ ዐይኖቹ አያት። "ትላንት እኮ ማልደሽ ቀስቅሽኝ ብለኸኝ ነበር። ሥራ አለብኝ ስትለኝ ነበር"

ፈጥኖ ሰዓቱን ተመለከተና በረኸመ ተንጠራራ። ራስ ምታት እንደ መጥረቢያ ይፈልጠዋል። አንድ ስኒ ጥቁር ቡና ናፈቀው። ከአልጋው አጠገብ ባለ የእንጨት ወንበር ላይ በሥርዓት ተጣጥፎ የተቀመጠ ልብሱን አንድ በአንድ እያነሳ ለበሰና ከመኝታ ክፍሏ ወጣ።

በመጠጥ መቸርቸሪያው ክፍል ውስጥ ወደ ተንጠለጠለው መስተዋት ጠጋ ብሎ፣ ፊቱን ተመለከተ። ገርጥቷል፤ ዐይኖቹ ደፍርሰው ቆባቸው አብጧል፤ የደረቀው ከንፈሩ ጠቁሯል፣ ፀጉሩ ተቆጣጥሯል። በመንፈሱ የሞተና ተስፋውን የቀበረ የገዛ ገጹ የማያውቀው ሰው መሰለው። በዚያ ገጽ ውስጥ የሚያነበው ባዶነትን ብቻ ነበር።

"ቁርስ ብጤ አፍህ ላይ እንዳታደርግ የኛ ቤት እንደምታውቀው ወይም እንደሰማኸው ነው" አለች ንቂቤክ ትክዝ እንዳለች።

በሥርዓት ቁጭ ብሎ ከቤቱ የተዘጋጀ ቁርስ የበላው መቼ ነበር? ው ... ው! በጣም በጣም ሩቅ ጊዜ ነው። የደረቁ ከንፈሮቹን የግድ አላቆ በአነጋገሯ ፈገግ አለ።

"ደሞ እንዴት ነው የምትስቀው?"

"እንዴት?"

"ጥርስህ ሲስቅ ፊትህ የሚያለቅስ እኮ ነው የሚመስለው"

"ከሰዎች ጋር የምስቀው ሳቅ ሁል ጊዜም እንደዚሁ ነው" አላትና ጥሏት ሊወጣ ወደ በሩ ፊቱን መለስ አደረገ።

"ስማ እንጂ!..."

ቻርሊ ቆም ብሎ ተመለከታት። ትኩር ብሎ ሲያያት እንደማፈር አለችና አንገቷን አቀረቀረች።

"ምን አልሽኝ ንቂቤክ?"

"ከሥራ ስትመለስ ከመጣህ... እ... ውስኪ የሆነች ቡና አፍልቼ... እጠብቅሃለሁ"

ትላንትናም ወደዚህ ለምን እንደመጣ ሲያስብ ቆየና አሁንም ምክንያት አጣለት። ምናልባት ለአብነት የሚመኘውን ስቃይ ሊያስቃያት ይሆናል። ምናልባት በሴት ልጅ ላይ ያደረበትን ጥላቻ ሊገልጽባት ይሆናል። ምናልባትም አብነትን የጎዳት መስሎት ይሆናል። የተቅበዘበዘች ነፍሱን የሚያሳርፍበት ጥግ ፍለጋ ይሆናል። ምናልባት ራሱን ለመርሳት። ከፊት ለፊቱ ለቆመችው ሴት አዘነላት። ራሷን አዳክማ ለሌሎች እረፍት የምትሰጥ አሻንጉሊት። ጠጋ ብሎ የጉንጯን



ንቅሳት በጣቶቹ ደባበሰና "እመጣለሁ" አላት። እንደማይመጣ ግን ልቡናው ያውቃል።

"የማይሆን ተስፋ እንዳልሰጠኸኝ ርግጠኛ ነህ?" በተስፋ የሚያበሩ ዐይኖቿን እያርገበገበች ጠየቀችው።

የማይሆን ተስፋ? በርሱ ላይ የተዋለበትን ግፍ በዚች ምስኪን ሴት ላይ ሊውልባት አልፈለገም። ትከሻውን ሰበቀና "እንሻ!" ብሎ ጀርባውን ሰጥቷት ወጣ።

ወደ ቲያትር ቤቱ ሲሄድ የእግሮቹ መተጣጠፊያዎች እየተንቋቁ ነበር። ዕለቱ "የመከነች ተስፋ" የተሰኘው ተውኔት ዝግጅት የሚጠናቀቅበትና ለባለሙያዎች የመጨረሻ ግምገማ የሚቀርብበት ዕለት ነው። ማስታወቂያው በትልቅ ሸራ ላይ ተሠርቶ ከቲያትር ቤቱ ህንፃ ላይ ከተለጠፈ ሰንብቷል። የመሪ ተዋናዩ የቻርሊ ስም ከተውኔቱ ደራሲና ከአዘጋጁ ስም ጋር በጉልህ ተጽፏል። ቲያትሩ በመጭው እሁድ የሚከፈት ሲሆን በመክፈቻው ዕለት ለሚገኙ ተጋባዥ እንግዶች የተዘጋጀው ካርድ ተበትኗል።

የቲያትር ቤቱ ህንፃ በርቀት ይታየዋል። ለምን እንደሚሄድ ባያውቅም እንኳን እግሮቹ ወደ ቲያትር ቤቱ ይራመዳሉ። በጀርባው በር አኩል የአጥር ግቢውን በር እንዳለፈ እየተጣደፈች የተቀበለችው ማራ ጋዴም ነበረች። አሁን በሚጫወተው ተውኔት ውስጥ በመሪ ተዋናይነት አብራው ትጫወታለች።

በሚርገበገቡት ዐይኖቿ ከላይ እስከታች ስትመለከተው ያበደ ውሻ መሰላትና ፈራችው። ያልተበጠረ ፀጉሩ፣ የደፈረሱና ያበጡ ዐይኖቹ፣ የደረቁና የጠቆሩ ከንፈሮቹ፤ መጨራመት የጀመረ ረዥም ቁመናው... በዐይኖቹ ላይ ያጠላውን እንደ በረዶ የቀዘቀዘ ስሜት ስታስተውል፣ የህይወት ተስፋው እንደገል እንክትክት ብሎ እንደተሰበረ አወቀች።

እየፈራችና እየተጠራጠረች ጠጋ ብላ "ጋሼ ቻርሊ ... ምነው ዘገየህ? የቲያትሩ ገምጋሚዎች ... ታፌ ኩልኩልትን ጨምሮ አዳራሹ ውስጥ ገብተው የተውኔቱን መጀመር ሲጠባበቁ ሰንት ጊዜያቸው። ተዋንያኑ ሁሉ መድረክ ላይ ከወጡ ቆይተዋል ... አዘጋጁ ዳንኤልም አንተን ጥበቃ እየተንቆራጠጠ ነበር... ግን በደህናህ ነው ጋሼ?" እያለች ተንተባተበችበት።

በግድ የለሽነት ትከሻውን ሰበቀና በህንፃው ጀርባ ወደ መድረኩ መልበሻ ክፍል አመራ። መልበሻው አካባቢ የነበሩ ተዋንያን ሁሉ ሁኔታውን ተመልከተው በድንጋጤና በፍርሃት ፈጥነው መንገድ በመልቀቅ አሳለፉት። ለእንዳቸውም ሰላምታ አልሰጣቸውም።

መልበሻው ክፍል ላይ ከዳንኤል ጅምር ጋር ተፋጠጡ። ዳንኤል እሳት በሚተፉ ዐይኖቹ ቻርሊን ከላይ እስከታች እየገላመጠ "ምን መሥራትህ ነው? በዚህ ወሳኝ ቀን እንዴት ይህን ያህል ሰዓት ትዘገያለህ?! አንተን ተክቶ የሚሠራው ተዋናይ አፕሪሲዮን ሆኖ ሆስፒታል መተኛቱን እያወቅህ እንዴት ትዘገያለህ? ይሄ ሁሉ ሰው ሥራ ፈቶ አንተን መጠበቅ አለበት? ይህ ከአንተ የሚጠበቅ አይደለም!" በማለት እየጮኸ በወቀሳ ይለበልበው ጀመር።

ቻርሊ የደፈረሱ ትላልቅ ዐይኖቹን እያጉረጠረጠ "የራሳቸው ጉዳይ!" አለ የራሱ ባልሆነ ጎርናና ድምጽ። ወደመ ልበሻው ክፍል ሊገባ መለስ ሲል ግን ዳንኤል ክንዱን ጨምድዶ አቆመው፣ "ሰዓት ማክበር ከመድረክ ሥነ-ሥርዓቶች ሁሉ በፊት ቅድሚያ የሚሰጠውና መከበር ያለበት ጉዳይ መሆኑን አታውቅም?"

ቻርሊ እየሳቀ የማያለቅስ የሚያስመስለውን ፈገግታ አሳይቶት "ገና ይሄንን ተውኔት ማዘጋጀት ስትጀምርና እኔም በመሪ ተዋናይነት ለመጫወት ስስማማ የተዋዋልነውን ላስታውስህ? በዚህ መድረክ ላይ አንተ አስተማሪ እኔ ደግሞ ተማሪ አለመሆናችንን ተማምነን ነበር። እና ከዚህ በኋላ አንዲት ቃል እንዳትናገረኝ!" አለና የያዘውን ክንዱን መንጭቆ ወደ መልበሻው ክፍል ገባ።

አዳራሹ ውስጥ ሰብሰብ ብለው በመጀመሪያዎቹ ረድፎች የተቀመጡት ገምጋሚዎች ለረዥም ጊዜ ያለሥራ በመቀመጣቸው የተሰላቹ ይመስላሉ። ከፊሎቹ ሲጋራቸውን እያጤሱ በዝግታ ያወጋሉ። ከፊሎቹ ደጋግመው እያዛጉና እየተንጠራሩ ትዕግስታቸውን ጨርሰው የተውኔቱን መጀመር ይጠባበቃሉ።

ታፌ ኩልኩልትም በመጀመሪያ ረድፍ ላይ ሲጋራቸውን እንደነከሱ ያስባሉ። ሰሞኑን የሰሙት የጡረታ ወሬ አደንዝዟቸዋል። በባህል ሚኒስቴር ያሉ አንዳንድ ወዳጆቻቸው የጡረታቸው ጊዜ እንዲራዘም እየታገሉላቸው መሆኑን ቢገልጹላቸውም በጡረታ በመጣ ነገር ሊያምኗቸው ግን አልቻሉም። በሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ውስጥ በስልጣን ኮርቻ ላይ መፈናጠጥ የጀመሩት የዳንኤል ጅምር ጓደኞች በጡረታ እንዲወገዱ አጥብቀው እየወተወቱና እየተሟገቱ መሆኑን አረጋግጠዋል። ዓላማቸውም ዳንኤል ጅምርን በቦታቸው ለማስቀመጥ መሆኑን አጣርተዋል።



ያየሰው ሰይጣን ሊያንበረክካቸው ምንም ያህል አልቀረውም። ጥበበኛው አመራራቸውም አልይዝ ብሏል። ቻርሊና ዳንኤል እንዲበሻጨቁ ለማድረግና ሁለቱንም በአንድ ጠጠር ለመጣል የነበራቸው እቅድ አልሠራም። ቻርሊን ምን አደንዝዞት ወኔውን እንደተሰለበ ሊገባቸው አልቻለም።

ልምምድ በሚደረግበት አዳራሽ ውስጥ አልፎ አልፎ እየገቡ ቃኝተዋቸዋል። ቻርሊ የታጠቀውን ጎራዴ በወገቡ ላይ በተመለከቱ ቁጥር የዳንኤል ጅምርን አንገት በመድረኩ ላይ ሲንከባለል አልመዋል። የተመኙት ግን ሆኖ አያውቅም። እርሳቸው ብቻ ሳይሆኑ አብዛኞቹ የቲያትር ቤቱ ሠራተኞች ይህ እንደሚሆን ቢገምቱም የተፈራው ሳይደርስ እነሆ ዝግጅቱ ሊጠናቀቅ ነው። ዳንኤል ጅምርም ሆነ ቻርሊ ተከባብረውና ተጠባብቀው ሥራቸውን ይሠራሉ። ታፌ ግን አሁንም ተስፋ አልቆረጡም። በያንዳንዳቸው ህሊና ውስጥ የታመቀው የጥላቻና የበቀል በምብ አንድ ቀን ፈንድቶ ይለይለታል በማለት በትዕግስት ይጠብቃሉ።

ወድቀው ከመላላጣቸው በፊት መሸነፋቸውን እንደማይቀበሉ ብዙ ሰዎች ሁሉ፣ ታፌም ሽንፈታቸውን መቀበል አልሆነላቸውም። በዳንኤል ጅምር ጥንካሬ ድክመታቸው ወለል ብሎ ታይቷል። ቢሆንም ለበርካታ ዓመታት ከለፉበት ቲያትር ቤት በጡረታ መገለላቸውን አሜን ብለው አልተቀበሉትም። ታፌ ፊት ለፊታቸው በተደቀነ ድቅድቅ ጨለማ ውስጥ እንኳን የተስፋ ጭላንጭል የሚያዩ ናቸው። ዛሬ ጥዋት ዳንኤል ጅምርን መድረኩ ላይ እንደ አንበሳ ሲጎማለል አይተውታል። ውድቀታቸውን አርድቷቸዋል። ታፌ ግን እየቆሰሉ አንገታቸውን አቀርቅረው በትዕግስት አለፉት።

የመድረኩ መጋረጃ በዝግታ መከፈት ሲጀምር ሥራ አስኪያጁ ሲጋራቸውን ጥለው መቀመጫቸው ላይ ተስተካከሉ። ልዩ ልዩ ቀለማት ያላቸው የብርሃን ጨረሮች በመድረኩ የተለያዩ ማእዘኖች ላይ ተረጩ። የመድረክ ገጽ ዝግጅቱም የታፌን ቀልብ ሳበው። ይህ የዳንኤል ድል የርሳቸው ውድቀት የመጀመሪያው መግለጫ ነው። ተውኔቱ ቀጠለ።

ዳንኤል ጅምር በጨለመው አዳራሽ ውስጥ ጥግ ቆሞ የተውኔቱን ሂደት ይቆጣጠራል። የመብራት ሠራተኞቹ ሥራቸውን በሚገባ እያቀላጠፉት ነው። የመድረክ ገጽ ዝግጅቱን እንደ አዲስ ተመልካች አደነቀው። ተዋንያኑ ከጠበቀው በላይ መድረኩን ተቆጣጥረውት በመንቀሳቀስ ላይ ናቸው። ማንም ባልገመተው መንገድ ተውኔቱ ተዋጥቶለታል። ከእንግዲህ "የምሁር ጅምር" እያለ

የሚያላግጥበት ማነው? "ተውኔት ማዘጋጀት ሴት እንደማጫወት አይቀልም" እያለ የሚያፌዝበትስ ማነው? "የጥበብ ግም አሸተተን" እያለ ጋዜጣ ላይ የሚሞነጫጭረውስ ማን ሊሆን? ወደር የማይገኝለት የጥበቡ ሰው መሆኑን በጣት ለሚቆጥራቸው ወዳጆቹ፣ ከፀጉሩ እኩል ለበዙ ጠላቶቹ እነሆ በዚህ ተውኔት እየገለፀ ነው።

ሣራ ጋዲምን መድረኩ ላይ ተመለከታት። ለዚህ ትንግሌ ያበቃችው እርሷ ናት። አገር አንቅሮ ሲተፋው አይዞህ ያለችው፣ ተስፋ ቆርጦ ራሱን ሲረግም ማንነቱን እንዲፈትን አቅጣጫውን የመራችው እርሷ ነች። እነሆ አሁን ደግሞ የሰጣትን ገፀ-ባህርይ ተላብሳ በመድረኩ ላይ እንደ እንዝርት ትሾራለች። በፍቅር ዐይን አስተዋላት።

የዛሬውን የቻርሊ እንቅስቃሴ ግን አልወደደውም። በመንፈሱም ሆነ በአካሉ ደንዝዟል። ተውኔቱን ማዘጋጀት ሲጀምር አብረን እንዝለቃለን የሚል ግምት አልነበረውም። ሆኖም የቻርሊን ልዩ ችሎታ ሊጠቀምበት በመፈለጉ እንደሚሰበር እንቁላል ተንከባክቦ እዚህ መድረስ በመቻሉ የገዛ ትዕግስቱን አድንቋል።

ቻርሊ የሚጫወተውን ገፀ-ባህሪይ በተለዋጭነት የሚጫወተው ተዋናይ ቲያትር ቤቱ ውስጥ አሉ ከሚባሉት እውቅ ተዋንያን አንዱ ቢሆንም የቻርሊን ያህል ለመጫወት ገና ብዙ ይቀረዋል። ቻርሊ በእውነትም የመድረክ ዋርካ፣ የተውኔት እስትንፋስ ነው። ዳንኤል ጅምር ይህንን እየመረረው ውጦታል።

የዛሬው የቻርሊ እንቅስቃሴ ግን ልክ አይደለም። ይህን ደግሞ ዳንኤል በበጎ መልኩ አልተረጎመውም። ተውኔቱ ለገምጋሚዎች በሚቀርብበት ወሳኝ ዕለት፣ በባህል ሚኒስቴር የሚገኙ ባለስልጣን ጓዳኞቹ በተገኙበት ዕለት እንዲህ መደንዘዙ ዝግጅቱን ለማበላሸት በመፈልጉ መሆኑን ገመተ። በግምቱ ትክክለኛነት ደግሞ አልተጠራጠረም። ቻርሊ መድረኩ ላይ በወጣ ቁጥር ተውኔቱ ሲሞት እያየ ነበርና ተቁነጠነጠ። መድረኩ ላይ ዘሎ ወጥቶ ጉሮሮውን ሊያንቀው ወደደ።

ቻርሊ በበኩሉ የሚንቀሳቀሰው ደመ-ነፍሱን ነበር። ከባድ የራስ ምታት እናቱን ይፈልጠዋል፤ ባዶ አንጀቱ የእህል ያለህ እያለ ይጮሀል። ከሰውነቱ መሃል የተነሳ እንደ ልቡ መንቀሳቀስ፣ እንደፈቀደው ትንፋሽ ማውጣት አልቻለም። በወገቡ ላይ የታጠቀው ጎራዴ ኩንታል የተጫነ ያህል ከብዶታል። በአካልም በመንፈስም ፍጹም በመድከሙ ሲያጠና የሰነበተው ቃለ-ተውኔት በተደጋጋሚ እየተሳተው የተውኔቱን ሂደት ብዙ ጊዜ አሰናከሎታል። እንዲያም ሆኖ ከራሱ ጋር እየታገለ ጥርሱን ነክሶ ትወናውን ቀጠለ።

ወደ መጨረሻው ላይ ግን ተውኔቱ ውስጥ ከዚህ በፊት በጣም የሚወደውን አንድ ክፍል መጫወት ቀፈፈው። ቃለ-ተውኔቱን ማውጣቱ አስጠላው። እናም ወገቡ ላይ የታጠቀውን የጎራዴ እጀታ እንደጨበጠ ዲዳ ሆኖ መድረኩ ላይ ቆመ። ሣራ ጋዲም ግራ ገብቷት እንዳፈጠጠች ቀረች። ቃላት ጠቋሚው ቃለ-ተውኔቱ የተሳተው መስሎት ከመጋረጃው ጀርባ ይወተውታል "ቻርሊ ቀጥል... እንዲህ በል 'አልሞትኩም እኮ ገና ነኝ... ትንፋሼን ጨርሼ አልዋጥኩም... አሸለብኩ እንጂ አልሞትኩም! ወድቋል ብለው ደስ እንዳይላቸው... ይሄው ትንፋሼን ላስደምጣቸው... ይሄው የተስፋን ፀዳል ከገጼ ላይ ላሳያቸ... ይሄው!' በል... ቀጥል... ቻርሊ... ቀጥል... እንዴ ሰውዬው ምን ነካው ዛሬ?"

ቻርሊ አይሰማውም። ከደምና ከሥጋ የተገነባ ሀውልት ሆኖ መድረኩ መሃል ተገትሯል። በአካል እንጂ በመንፈስ መድረኩ ላይ የለም። የትኛውን የተስፋ ፀዳል ነው ገጹ ላይ የሚያሳያቸው?! የህይወትን ውጣ ውረድ ከብዙዎች በላይ ሮጦታል። ራሱን እስኪጠላ፣ መፈጠሩን እስኪረግም ድረስ። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ደግሞ የመኖር ምክንያቴ፣ የህልውና ጥያቄ ነች የሚላት ሴት ከዳዋለች። ከወጣትነት እስከ ጎልማሳነት የለፋላት የቲያትር ጥበብም ሰልችታዋለች። የሙያው ሰዎች አስጠልተውታል። በገዛ ልጆቹ ሳይቀር ተስፋ ቆርጧል። አንድ ቀን የህዝቦች አመጽ የሚወልደውን ብሩህ ቀን እያለሁ የሚለው እምነቱም በወታደራዊ መንግሥት መጠናከር ተመናምኗል። በዚህ ላይ የአዕምሮ በሽታው ፋታ እሳጥቶ ያስቃየዋል። በዚህች ምድር ላይ ያለ ምክንያትና ያለ አላማ መኖር ድንጋይ ከሚኖረው ኑሮ ጋር አንድ እስኪመስለው ድረስ እርሱነቱን ንቋል። እና የምን አልሞትኩም?! የምን ትንፋሼን ጨርሼ አልዋጥኩም ነው?! ተስፋ ቆርጦ ከከሰመ ገጹ ላይ የምን የተስፋ ፀዳል ነው የሚያሳያቸው?!

ድንገት ከሰመመኑ ነቅቶ ግራ ቀኙን አስተዋለና መድረክ ላይ መሆኑን ተገነዘበ። ቃላት ጠቋሚው አሁንም ከጀርባው ይወተውታል "ቀጥል ቻርሊ... እንዲህ በል' አልሞትኩም እኮ ገና ነኝ..... ትንፋሼን ጨርሼ አልዋጥኩም..."

ቻርሊ ከታፈነው ልሳኑ ጋር ታግሎ ቃላቱን ከአንደበቱ አፈናጠራቸው። በዚያው ቅፅበት የተውኔቱን እስትንፋስ አንቆ ገደለው። ሁለቱንም እጆቹን ወደላይ ሰቅሎ በመንጠራራት ገጽታው የተስፋን ፀዳል እየረጨ ጨርሶ አለመውደቁን አለመሸነፉን ማብሰር

ቢገባው ፊቱን አጨፍግጎና ግምባሩን ከስክሶ በግድ የለሸነት ኸበር ቃላቱን የቃተታቸው።

ይኸኔ ከየት መጣ ሳይባል ዳንኤል ጅምር መድረኩ ላይ እመር ብሎ ወጣ። የግምባሩ ላይ ስሮች ፈጠው ፊቱ በላብ ተጠምቋል። ረጃጅም ጣቶቹ እየተንቀጠቀጡ በላይ በላዩ ይተነፍሳል። "እስ አሳየና.. እስ አሳየና.... ከዚህ በፊት እንደምትጫወተው ፈገግ ብለህ .... ስቀህ .... የተስፋን ፀዳል ከገጽህ ላይ አሳየን!" ሲል አዳራሹ እስኪንቀጠቀጥ ጮኸ።

ታፈ መቁነጥነጥ ጀመሩ ህልማቸው እውን ሊሆን ነው። ጥበባዊ አመራራቸውም እጅግ እጅግ ብዙ ዘግይቶ ሊሠራ ነው።

ቻርሊ ቃለ ተውኔቱን ደገመና ፈገግ ሊል ሞከረ። ሆኖም ዳንኤል ፀጉሩን ነጨ። "ይሄ የተስፋ ሣቅ ሳይሆን የምጸት ነው!" በማለትም ጮኸበት። ቻርሊ እንደገና ሞከረ።

"ይሄኛውም የቁጭት ነው!" የዳንኤል ጩኸት አሁንም በአዳራሹ ውስጥ አስተጋባ።

ቻርሊ ግራ እንደተጋባ ደንዝዞ ቀረ። የተስፋን ሳቅ ከየት ያምጣው? እና እዚያው እንደቆመ ሃያ ሁለት ዓመት ሙሉ በቁም ካሸለበበት መድረክ ላይ ድንገት ነቃ! ከሰመመኑ ባነነ! የባከኑ ዓመታት በሚላቸው ረጅም ኅመታት ውስጥ ያን ቀን ለመጀመሪያ ጊዜ ራሱን ሆነ! ውስጣዊው እርስነቱ፣ እውነተኛ ማንነቱ ታግሎ ጣለው! ሃያ ሁለት ዓመት ሙሉ የተከናነበውን የመምሰል ካባ ከላዩ ላይ ገፎ ጣለ! መስሎ መገኘት አቃተው።

"እስ በል ተስፋን አሳየኝ?!" ዳንኤል አሁንም ላንቃው እስኪተረተር ጮኸበት። ቻርሊ እንደመበርገግ አለና ቀና አለ። "እስ የማንን ተስፋ ነው ከገጼ ላይ የማሳይህ?" እሳት መትፋት የጀመሩ ድፍርስ ዐይኖቹን በዳንኤል ዐይኖች ላይ አሳረፋቸው። "የማንን ተስፋ? ከቲያትሩ ፍጻሜ በኋላ የደራሲውንና የአዘጋጁን የብር ተስፋ?! ወይንስ የገፀባህሪዩን የህይወት ተስፋ?!" ከንፈሮቹ መንቀጥቀጥ ፀጉሩ መቆም ጀመረ።

ዳንኤል ግራ ተጋብቶ በተራው ፈዝዞ ቆመ። ታፈ አንገት ላይ ከግምባራቸው የሚወርደው ላብ መንጠፍጠፍ ጀምሯል። የዐይናቸውን ቅንድብ ለአንድ አፍታ እንኳን ሳይሰብሩ መድረኩ ላይ አፍጠዋል።



አንዱ ቻርሊ ወገብ ላይ ያለውን ጎራዴ አንድ ጊዜ የዳንዴል ጅምርን ረዥም አንገት እያስተዋሉ በላይ በላዩ ይተነፍሳሉ። አዳራሹ ውስጥ ያሉ ገምጋሚዎችና የቲያትር ቤቱ ሙያተኞች እየተጠራሩ ተጠራቅመው የዚህን ተአምር መጨረሻ ለማየት ጨለማው ውስጥ አፍጥጠው ይጠባበቃሉ። ትንፍሽ ያለ ሰው አልነበረም።

ቻርሊ ቀጠለ፤ "ተስፋው የደራሲው፣ የአዘጋጁ፣ ምናልባትም የገፀ-ባህሪው ቢሆን እንጂ ለእኔ ምኔ ነው? እኔ ማን የሚሉኝ አሽቃባጭ፣ የማን አትርሱኝ ባይ ነኝ? እና የማንን ተስፋ ነው ያለውድ በግድ የምፈልገው? ከእንግዲህ ውስጤ እያለቀሰ፣ ጥርሴ የውሸት ሳቅ መሳቅ አይችልም! ገጼ ላይ የሚታየው የሃሰት የተስፋ ፀዳል በውስጤ የሞተውን ተስፋ አይደለም! እና ተወኝ.... እባክህ... አንተ ሰው.... ተወኝ!" ሲል እየተንቀጠቀጠ ከዳንኤል እኩል ጮኸ። በአካልም በመንፈስም የደነዘዘው ቻርሊ ያን ያህል ትንፋሽ፣ ያን ያህል የመንፈስ ጉልበት ከየት እንዳመጣ ለራሱም ጭምር ገርሞታል።

"የተስፋን ሳቅ ስቀህ አሳየኝ ነው የምልህ አንተ የሰው ከንቱ!" ዳንኤል የሚንቀጠቀጡ ሁለት ረጃጅም እጆቹን አንጨፍርሮ የቻርሊን ጉሮሮ ሊያንቅ በዝግታ ቀረበው። ቻርሊ የገዛነም ደጆች መስለው የተበለጠጡትን የዳንኤል ዐይኖች፣ የሚንቀጠቀጡ ከንፈሮቹን፣ የጣር ጩኸቱንና የተንጨፈረሩ ረጅም እጆቹን ሲመለከት መልአከ ሞት እስትንፋሱን ሊያፍን የሚጠጋው መሰለውና ጥቂት እርምጃዎች ወደ ኋላው አፈገፈገ።

ዳንኤል አሁንም እየጮኸ ቀረበው "የተስፋ ሳቅ! የተስፋ ፀዳል" ቻርሊ አሁንም ያፈገፍጋል። "የምን ተስፋ?! የምን የተስፋ ፀዳል?! እንዳች ተስፋ በውስጤ የለም... በየማእዘኑ የሚታየኝ የጠቆረ ጨለማ ነው... በዚያ ጥቁር ጨለማ ውስጥ ደግሞ መልአከ ሞት! ሞት ብቻ ነው ጥርሱን አግጥጦ የሚታየኝ! የምን የተስፋ ፀዳል? የምን የህይወት ተስፋ ነው የምትለኝ? ሞት! ጨለማ! መልአከ ሞት!..." በማለት ወደ ኋላው እየሸሸ መድረኩን በጩኸት አንቀጠቀጠው።

ዳንኤል የተንጨፈረሩ እጆቹን አውርዶ በረጅሙ ተነፈሰና "መሃይም!" ብሎ ምራቁን መድረኩ ላይ ጢቅ አለ። ይቺ ቃል ከቻርሊ ጆሮ ተወርውራ ገባችና እንደ ኤሌክትሪክ ሞገድ መላ አካሉን ነዘረችው፤ የህይወት ቁስሉን ጨፍልቃ አሸችው። ረዥም ሰውነቱ ሲንዘፈዘፍና ከውስጥ የወጣ የጣር ጩኸት በአዳራሹ ውስጥ ሲያስተጋባ አንድ ሆነ። ማንም በማይገምተው ቅልጥፍናና ፍጥነት የታጠቀውን ጎራዴ ከወገቡ ላይ መዞና ወደ ዳንኤል ተንደረደረ።

ዳንኤል የፈጠጡ ዐይኖቹን በልጥጦ በድን እንደሆነ ቆሞ ቀረ። በቻርሊ እጅ ላይ የሚያየው ስለታም ጉራዴ በሰከንድ ክፍልፋዮች ፍጥነት አንገቱን እንደጎመን ቀንጥሶ እንደሚያሽከረክራት ቅንጣት ታህል አልተጠራጠረም።

የቻርሊ ዐይኖች መጨለም ጀምረዋል። በዚያ መድረክ ላይ የሚታየው በመልአከ ሞት የመሰለው የዳንኤል ረኸርም አንገት፣ በጆሮዎቹ የሚሰማው "መሃይም! መሃይም! መሃይም!" የሚል ድምጽ ብቻ ነው።

ስለታም ጉራዴ የያዘው እጁ ከመዘርጋቱ በፊት፣ የመጀመሪያዋ የደም ጠብታ በመድረኩ ወለል ላይ ከመፈንጠቋ በፊት፣ የጆሮ ታንቡር የሚተረትር ቀጭን የጭንቀትና የዋይታ ድምጽ አዳራሹን አናወጸው! ሣራ ጋዴም እንደ ቀስት ተፈናጥራ በዳንኤልና በቻርሊ መሃል ቆመች!

የቻርሊ እጅ በአየር ላይ እንደተንጠለጠለ ሌላ ድምጽ ደግሞ በአዳራሹ ውስጥ አስተጋባ። ስሜት የፈነቀለው የታመቀ ምኞቱ ያፈነዳው ድምጽ "በለው ቻርሊ!" ሲል ተሰማ።

ቻርሊ ድምጹን ወደሰማበት አቅጣጫ ለአፍታ ያህል ጭንቅላቱን ዘንበል አድርጎ ተመለከተ። ከመድረኩ ላይ ወደ አዳራሹ ደብዘዝ ብሎ በተረጨው ብርሃን በጀመሪያው ረድፍ ታፈ ኩልኩልትን በስሜት ተውጠው ጅማቶቻቸው ተወጣጥረው ሲቁነጠነጡ አስተዋላቸው።

"ኩልኩልታም!" አለ ቻርሊ ጥርሶቹን እንደነከሰ። በዚያች ቅጽበት የተወጣጠረ ጡንቻው ሲዝል፣ እንደ እሳት ከውስጥ የሚያቃጥለው የገዛ ደሙ ሲቀዘቅዝ ተሰማው። በረኸርሙ እየተነፈሰ ጎራዴ ጨብጦ በዳንኤል አንገት ላይ የተዘረጋ እጁን በዝግታ አወረደው። መላ ሰውነቱን እንደ ፈላ ውሃ የሚፈጀው ላብ ከግንባሩ ላይ እየተንከባለለ በመድረኩ ወለል ላይ ይንጥር ጀመር።

ከእንቅልፉ እንደነቃና ምን ይሰራ እንደነበር እንደጠፋው ሰው ዙሪያውን ቃኘ። አሁን ዐይኑን ጋርዶት የነበረው ጨለማ ተገፎለታል። "መሃይም! መሃይም!" እያለ የጆሮውን ታምቡር እየነረተ ህሊናውን የወቀረው ድምጽ አይሰማውም። ሣራ ጋዴም በዳንኤል አንገት ላይ እንደተጠመጠመች ቆማለች። ከቲያትር ቤቱ ተዋንያን አብዛኞቹን በአዳራሹ ውስጥ፣ ጥቂቶቹን ደግሞ በመድረኩ ላይ የተውኔቱን አልባሳት እንደለበሱ አስተዋላቸው። ታፈ ኩልኩልት፣ የቲያትሩ



ገምጋሚዎች፣ የባህል ሚኒስቴር ባለስልጣናት ባሉበት ደርቀው ተቀምጠዋል። አንዲት ቃል የሚተነፍስ፣ አንዲት ሰንዝር ካለበት የሚንቀሳቀስ የለም። ቻርሊ ጎራዴውን እንደጨበጠ ጥቂት ርምጃዎች ተንጎራደደ።

የደፈረሱት ትልልቅ ዐይኖቹ የቁጭት እሳት ይተፋሉ። ገጽታው በተስፋ መቁረጥ ጥላ ጨልሟል። ወደ መድረኩ መሀል በዝግታ እየተራመደ በመሄድ በወለሉ ላይ በርከክ አለና ከወጣትነት እስከ ጉልምስና የሠራባትን፣ ክፉና ደግ ያየባትን መድረክ ሳማት። ከተንበረከከበት ቀና ሲል የእንባ ዘለላዎች ከዐይኖቹ ላይ ረገፉ።

"ሰለቸሁ... ደከምኩ.... ይሄው እናቴ ኪነት፣ ቃል ለምድር ለሰማይ፣ ሁለተኛ ሳንተያይ!" ቀኝ እጁን በመድረኩ ላይ አኑሮ ማለላት "ከረፈደ ብነቃም.... እኔ እኔን ሆኜ የምኖርባት ትንሽም ብትሆን እድሜ አላጣም..." በግራ እጁ የያዘውን ጉራዴ ተመርኩዞ ተነሳና ቆመ።

"ስንቱን መስዬ ኖርኩት?!" ማንን እንደሚጠይቅ ግራ ገብቶት አንድ ጊዜ አዘጋጁን፣ አንድ ጊዜ ገምጋሚዎቹን፣ አንድ ጊዜ የሙያ ባልደረቦቹን፣ በመጨረሻም መድረኩን በደፈረሱ ዐይኖቹ ገረመማቸው።

"ስንቱን መስዬ ኖርኩት? በስንቱ ቁንጥ ዘነጥኩት? የስንቱን ዲስኩር ደሰኮርኩት? በስንቱ ሃዘን አለቀስኩ? የስንቱን ደስታ ሳቅኩት? እበድ ሲሉኝ እንዳበድኩ፣ ሙት ሲሉኝ የውሸት ሞት እንደሞትኩ፣ ምስኪን ሁን ሲሉኝ ደባደቦ... ቱጃር ነህ ሲሉኝ በከረባት እንደታነቅኩ... ፀጉሬን ቀለም ሲቀቡኝ፣ ፊቴን ሲያሽጎረጉሩኝ፣ እንደ ፈለጉ ሲያደርጉኝ እኔነቴንም አሰረሱኝ። እኔ እኔን ሆኜ የምኖርበትን እድሜ ቀሙኝ!"

ማንን እንደሚከስ፣ ማን ላይ አቤት እንደሚል እንኳን አያውቅም። በመድረኩ ላይ ያሉት የሙያ ጓደኞቹ ናቸው። የረገጣት መድረክ ጆሮ የሌላት ግዑዝ ነች። እናም እንዲሁ ግራ እንደገባው ተጠለ።

"እነዚህ የእድሜ ነቀርሶች... ኪነት ባንቺ አሳበው ነው.... ኪነት አንቺን አሳይተው ነው... ሳቤ አንቧቸው ነፍሴን ከሥጋዬ ጨምቀው ያለቡኝ ። ኪነት አንቺን ቢሉኝ ነው... ስጋና ነፍሴን አስገዝቼ ለስንቱ ባሪያ የሆንኩት ... እንጂማ ለማን እበለጥ ነበር?" ጥርሶቹን በቁጭት ሲያፋጭ ብዙዎቹን በትኩረት አሳቸው።

ዞር ሲል ዳንኤል ጆምርን አየው። እንዳሸነፈው ቢያውቅም ውድቀቱን በአደባባይ አሜን ብሎ ሊቀበል አልፈቀደም። እናም የዘሰፋውን መአት አወረደበት። “አንተ በወረቀት የምትኮራ የምሁር ጆምር፣ አንተ ዲግሪ ብርቁ! ጉራ ስንቁ! አዲስ ሰማይና አዲስ ምድርን ፈጥረህ እንደምታቀርብ ታላቅ ጠቢብ አድርገህ ራስህን በመቁጠርህ ልታፍር ይገባሃል። አቤት ጉራህ!... አቤት ጥሩንባህ!... በእኛ ትከሻ ተንጠላጥለህ የገዛ ጎንህን ልታስባ? የኛን ስም ቀብረህ የገዛ ስምህን በወርቅ ቀለም ልትቀባ?.... አይሟል ጉራህ!.... እኔማ በአንተ ቤት የምተነፍስ አሻንጉሊት እኮ ነኝ... በገዛ ወረቀትህ እንጂ እኔ ከህይወት ልምድ በገበየሁት፣ ከእድሜ ፊደል በቆጠርኩት፣ በተፈጥሮዬ በወረስኩት እውቀት አታምንም። እውቀትን ፈርጅ ለማስያዝ መማር አስፈላጊ ቢሆንም ለሙያው መወለድንና በልምድ መብሰልን ያህል ታላቅ እውቀት እንዴት አሜን ብለህ አትቀበልም ?!”

ዳንኤል እንዳቀረቀረ ቀረ። ድንጋጤው አሁንም አልለቀቀውም። ቻርሊ ቀጠለ “...ጉረኛ! ሸክስፒርን ያህል ታላቅ ሰው የትኛው ኮሌጅ መረቀው?! ቴስፒስን ማን ካባ አለበሰው?! ኤስኪለስንስ ማን ቀባው?! ይህን ማየት የማትችል ጭፍን... ተማርኩ ብለህ ብትራቀቅ በራስህ እንደሳቅክ እወቅ!” የዳንኤልን ዐይን ማየት የቀፈፈው ይመስል ዐይኖቹን ፈጥኖ ከዐይኑ አሸሻቸው።

የረገጣትን መድረክ በፍቅር ዐይን ሲመለከታት ቆየ። የሃያ ሁለት ዓመት እንጀራውን፣ የሃያሁለት ዓመት ፍቅረኛውን፣ የሃያ ሁለት ዓመት እናቱን፣ የሃያ ሁለት ዓመት ቤቱን ሲሰናበታት እንባ በዐይኖቹ ላይ ግጥም እንዳለ ነበር። “እና እናቴ ኪነት... እስከዛሬ በስምሽ እድሜዬን፣ ላቤን፣ ነፍሴን ጭምር ተዘረፍኩልሽ... እኔ ነኝ ያለ ባለተራ ደግሞ አዲስ ትውልድ ይደግፍሽ ... የፋንታውን ይድከምልሽ ። እኔማ ምን ረባሁሽ? ሃያ ሁለት ዓመት ሙሉ መሆንን ሳይሆን መምሰልን ስለጠንኩብሽ። እንጂማ ምን አዲስ ነገር ፈጠርኩልሽ? እስኪ ምን አዲስ ነገር ፈጠርንልሽ?!”

የሙያ ጓደኞቹን አንድ በአንድ አስተዋላቸው። በብዙዎቹ ዐይኖች ላይ የእንባ ዘለላዎች ተንጠልጥለዋል። ቻርሊ መስተዋት ሆኖ በገዛ ህይወቱ ውድቀት በመጭዎቹ ዓመታት የራሳቸውን ህይወት ምስል ሲያሳያቸው ብዙዎቹ በመንፈስ መውደቅ ጀመሩ።

“ምንም አልጨመርንልሽ... ምንም። እኛ እርስ በእርሳችን ለመጋጋጥ፣ ለመቦጫጨቅ፣ ለመነጫጨት እንጂ ለፈጠራ ጊዜ የለንም። ከመካከላችን አንዱ እንኳን ነፍስ ዘርቶ አዲስ ነገር ያሳየን እንደሁ ተጠቃቅሰን እንገጠዋለን። ከነፈጠራው፣ ከነቅስሙ፣ ከነተሰፋው



እንቀን በቁም እንቀብረዋለን። እንዳችን ከእንዳችን ተሽለን ማታየቱን አንወደውም። እኩል መደንቆር፣ እኩል መደህየት፣ እኩል መንጭቀቅ፣ ይሄ ነው የኛ ህልማችን... ይሄ ነው የኛ ተስፋችን። አዲስ ነገርማ እንዴት በዐይናችን አይተን! ዐይነ ውሃችን ደም ይለብሳል፤ ምቀኝነት አንቀጥቅጠን የቅናት ዛር በላያችን ላይ ይነግሳል...” በእጁ የያዘውን ጎራዴ በዝግታ ወደ መሬት ለቀቀው።

“እና በቃሽኝ እምዬ... አንቺንም እኔ በቃሁሽ፤ እርም ይሁንብኝ እማይ!.... አንቺ የሃያ ሁለት ዓመት ትዳሬ... አንቺ የሃያ ሁለት ዓመት እንጀራዬ በቃኝ በቃሁሽ... እንግዲህ እርም!.... እርም ይሁንብኝ... እኔውም ለአንቺ እርም ነኝ!” በዝግታ ተንበርክኮ ለመጨረሻ ጊዜ መድረኳን ሳማት። ቀና ለማለት ሲሞክር ግን ሁሉም ነገር ጨለመበት። ከተንበረከከበት ለመነሳት አቅም አጠረው። አንጎሉ በጭንቅላቱ ውስጥ የሚሽከረከር መሰለው። በሁለት እጆቹ ጭንቅላቱን ያዘና “ራሴ... ራሴ... ራሴ ሊፈነዳ ነው” ሲል ቃተተ። አፍታም ሳይቆይ በግምባሩ ተደፋና ሃያ ሁለት ዓመት ሙሉ ላቡን እንጠፍጥፎ በሠራበት መድረክ ላይ ማንንም ሳይመስል ራሱን ቻርሊን ሆኖ ተዘረረ።

***   ***   ***

ናፖሊዮን አምባው ቲያትር ቤቱ በር አካባቢ ያንዣብባል። ሁለት ቀን ሙሉ የቻርሊን ፈለግ አነፍንፎ ሊደርስበት አልቻለም። መኖሪያ ቤቱ አካባቢ በተደጋጋሚ እየተመላለሰ አስሶታል፤ የውሃ ሽታ ሆነበት። ቲያትር ቤቱ በር ላይ ቆሞ ስረኸም ሰዓታት አድብቷል፤ ቻርሊ ግን ወጥመዱ ውስጥ ሊገባ አልቻለም። ከዚህ ቀደም ከአቶ መንግሻ በደረሰው ትእዛዝ መሠረት ስለ ቻርሊ ማንነት ለማወቅ ላይና ታች ባለበት ወቅት፤ ቻርሊ መጠጥ የሚያዘወትርባቸውን ሥፍራዎች ያውቅ ስለነበረም በየተራ አሰሳቸው። የቻርሊን ጭራ ግን ሊይዘው አልቻለም “ይሄን ሰው ምን በላው? መሬት ተቀዳ ዋጠችው? ወይንስ ሰማይ ሰንጥቆ ሾለከ?” እያለ ከመገረም በቀር ለቻርሊ መሰወር ምክንያት መስጠት አልቻለም።

አሁንም ቲያትር ቤቱ በር አካባቢ የህንፃውን ግድግዳ ተደግፎ ቆሟል። ጥቁር የቆዳ ጃኬትና ሰማያዊ ጅንስ ሱሪ እንዲሁም ጥቁር መነጽር እንዳደረገ ሲጋራውን በላይ በላዩ ይስባል።

ስለሚገድለው ሰው ማንነት ያውቃል። ለምን እንደሚገድለውም ጠንቅቆ ተረድቷል። ግድያው ፍትሃዊ በመሆኑ ግን እያምንም፤ ይሁንና ለምን ብሎ ሳይጠይቅ ሙያዊ ግዴታውን መወጣት አለበት።

ለናፖሊዮን እምባው በቻርሊ የጆሮ ቀዳዳዎች ውስጥ ሁለት የጥይት አረሮችን በማፈለክ ከአስፋልት ላይ መዘረር በጣም ቀላል ተግባር ነው ። ጨለማን ተገን ማድረግ፣ ከምስክሮች ዐይን መሰወር አያስፈልገውም። የአየር ወለድ ሠራዊት አባልነት መታወቂያው አሁንም ሸሚዝ ኪሱ ውስጥ ነው። ቀን በቀን እንደ ሽር እሀል አስጥቶት እጁን ኪሱ ውስጥ ከቶ ወደ ፈለገበት መሄድ ይችላል። አስቂም የሚጠይቀው ቢገኝ እንኳን ሬሳ ጣቱን በተዘረረው አስከሬን ላይ ጠቁሞ "ይህ ሰው የለየለት አናርኪስት ነው?!" ማለት ብቻ ነው። ከዚያ በላይ ዝርዝር ታሪኩን የሚጠይቀው እንደሌለ እርግጠኛ ነው።

ቻርሊን የበላ ጅብ ግን አልጮህ አለ። ናፖሊዮን ከቲያትር ቤቱ የሚወጡና የሚገቡትን ሠራተኞች ሲቃኝ ለረዥም ጊዜ ቢቆይም ቻርሊ ዝር አላለም። ሲሰለቸው ከሰዓት በኋላ ለመመለስ ወስኖና ወደ ቤቱ ጉዞ ጀመረ።

ብዙም ሳይርቅ ግን ቲያትር ቤቱ ህንፃ ላይ የተለጠፈውን በትልቅ ሸራ ላይ የተሠራ ማስታወቂያ ተመለከተና ቆም አለ። "የመከነች ተስፋ" ይላል የተውኔቱ ርዕስ። የመሪ ተዋንያን የስም ዝርዝር በተፃፈበት ማእዘን የቻርሊን ስም በመጀመሪያው ረድፍ ላይ በጉልህ ቲጽፎ ተመለከተው። ተውኔቱ የሚከፈትበትን ቀን አየ። ጥቂት ቀናት ብቻ ቀርተውታል።

ካለበት ሳይንቀሳቀስ ዐይኖቹን በማስታወቂያው ሰሌዳ ላይ እንደተከለ ማሰብ ጀመረ። ከአሶሳ ከተመለሰበት ጊዜ ጀምሮ የመንፈስ እረፍት የለውም። አሶሳ ላይ በፈፀመው ግድያ ሳቢያ ፖሊሶች ተከታትለው ሊይዙት እንደሚችሉ ገምቷል። በተለይም የሰነዱን ጠባቂው እጅ መግባት ከሰማ ወዲያ ለህይወቱ ዋስትና እንደሌለው አውቋል። ይሁን እንጂ አልፈራም፤ አልደነገጠም። ለእርሱ ሞት ማለት ከሚጠላው ብርሃን ተነጥቆ በሚናፍቀው የጨለማ እቅፍ ውስጥ ለዘላዓለም ማረፍ ነው። "እናም እየቀረበ ከመጣው ሞት ጋር መገናኘት ሳይቀር በህይወቴ ዝነኛ የሚያደርገኝን ታላቁን ጀብድ ለምን አልፈጽምም?!" ሲል አሰበ።

"ሰዎችን መግደል ቀላል ነው። ገዳዩን ሊያረካና ዝነኛ ሊያደርገው የሚችለው የአገዳደሉ አይነትና ብልሃት ነው" አለ ናፖልዮን ከራሱ ጋር ሲመካከር። ቻርሊም ዝነኛና ታላቅ የሃገር ሃብት እንደመሆኑ እንደ መንገደኛ ተራ ሞት መሞት የለበትም። ገዳዩንም ሟቹንም ዝነኛና ታላቅ የሚያደርግ የክብር ሞት መሞት አለበት።



ስለዚህም "በቲያትሩ መክፈቻ እለት በሚጫወትበት መድረክ ላይ እደፋዋለሁ!" ሲል ወሰነ።

የተናገረውን እንደሚፈጽመውም ቅንጣት ታክል አልተጠራጠረም። በማድያው ማግስት ጋዜጦች ይዘው የሚወጡት አስገራሚ ዜና፣ የወንጀል ምርመራ ፖሊሶች ግራ መጋባት፣ በአይነቱ በሀገሪቱ የመጀመሪያው ስለሆነው የመድረክ ላይ ግድያ በህዝብ ዘንድ የሚፈጠረው መደነቅ ታሰበውና ፈገግ አለ።

ብዙም ሳይቆይ በእጁ የያዘውን ሲጋራ ረገጠና የፀሐይ መነጽሩን አስተካክሎ ስለአስገራሚው ወንጀል አፈፃፀም እቅድ ለማውጣት ወደ ጨለማው መኖሪያ ቤቱ እየተጣደፈ ሄደ።

## ምዕራፍ ሃያ ሦስት

ሀንፃው ሥር ቆም ብሎ "አብነት እስመጭና ላኪ ድርጅት" የሚለውን ማስታወቂያ ሲመለከት ልቡ ደረቱ ውስጥ በደስታ ስትዘል ተሰማው። "አብነት" የሚለው ስም ለእርሱ ቅዱስ ነው። አንከስ የሚል የግራ እግሩን እየጎተተ ወደ ሀንፃው ገብና ደረጃውን በዝግታ መውጣት ጀመረ።

ድርጅቱ ውስጥ በፀሐፊነት ተቀጥራ የምትሠራው ቅድስት መኮንን ደግሞ ከታይፕራይተሩ ጀርባ ተቀምጣ ማስቲካዋን እያኘከች ታስባለች። ሰሞኑን የምትመለከተው ትርምስ እንቆቅልሽ ሆኖባታል። የድርጅቱ ባለንብረት የአቶ መንገሻ ጠባይ ተለውጦና በአካልና በመንፈስ ጠውልገው ሲታይ አንድ ችግር እንደተፈጠረ ገምታለች። እንደ ቀድሞው በጊዜ ሥራቸው አይገቡም አረፋፍደው ሲመጡም ፒፖቻቸውን ነክሰው ቢሮው ውስጥ እየተንጎራደዱ ብቻቸውን ከመለፍለፍ በቀር ሥራ አይሠሩም። አብነትም ብትሆን ሥራ ሳትገባ ቀናት አልፈዋል። የድርጅቱ ንብረት እየተቆጠረና እየተመዘገበ ሲሆን ጉለሌ አካባቢ የሚገኘው የድርጅቱ የእቃ መጋዘን ሠራኞችም አብዛኞቹ ከሥራ መሰናበታቸውን ሰምታለች። የድርጅቱ ጠበቃ አቶ ስዩም ብቻ በየቀኑ ይመላለሳል። የተፈጠረው ችግር ምን እንደሆነ እንቆቅልሹ ሊፈታላት አልቻለም።

የቢሮዋ በር ሲንኳኳ አልሰማችም። ቆይታ ከእንቅልፏ እንደባነነች ሁሉ ብርግግ ብላ "ይግቡ" አለች። በሩ በዝግታ ሲከፈት እድሜው በሠላሣዎቹ መጨረሻ የሚገመት ራሰ በራ፣ መካከለኛ ቁመትና ቀጭን ሰውነት ያለው ሰው ከፊት ለፊቷ ቆመ። "ይግቡ፣ ምን ልርዳዎት?" አለች ግምባሯን ቅጭም እንዳደረገች። የሰውየው ገጽታ አዲስ አይደለም።

የከፈተውን በር በጥንቃቄ ከዘጋ በኋላ አጠገቧ ወዳለው የእንግዳ መቀበያ ወንበር ተጠግቶ አረፍ አለ።

"ምን ልርዳዎት?" አለችና ማስቲካ ማላመጧን ቀጠለች።
"አብነትን ፈልጌ ነበር የኔ እህት..."

ፀሐፊዋ ማስቲካ ማኘኳን አቁማ ማሰብ ጀመረች። እንዲህ አይነት ሰው ከአብነት ጋር ምን ጉዳይ ይኖረዋል? ሲያዩት በኑሮ ብርቱ ክንድ የታሸ ምስኪን ይመስላል። ግምባሩ ላይ የሚታዩት የህይወት መስመሮች የህይወትን መራራ ጽዋ ተጎንጭቶ ፊቱን ያኮፈተረ የምድር



ጎስቋላ መሆኑን ይመሰክሩበታል። ማስቲካዋን አስጮኸችና "ለምን ነበር የፈለጓት?" ስትል ጠየቀችው።

"በጣም አስቸኳይ ለሆነ... ለዚሀ ድርጅት ጉዳይ ነበር። ሳምንቱን ሙሉ ስልክ እየደወልኩ ብፈልጋትም ላገኛት አልቻልኩም ... ለመሆኑ በደግ ነው?" ሲል ስጋቱ እያስታወቀበት ጥያቄዋን በጥያቄ መለሰላት።

"አሃ... ተካልኝ ባልቻ ማለት እርስዎ ነዎት?" ፀሐፊዋ ማስቲካ ማኘኳን አቁማ በመገረም አስተዋለችው።
"አዎን እመቤት፣ እባክሽን እርጂኝ?"
"አብነት ሰሞኑን ሥራ አልገባችም" ፀሐፊዋ መልስ ለመስጠት ጊዜ አልፈጀችም።
"እሱስ ይሁን... ግን በደህና ነው?" በተካልኝ ዐይኖች ውስጥ ስጋትና ጥርጣሬ አፈጠጡ።

"አይ ... በደህና ነው። ድርጅቱን የሚመለከት ጉዳይ ከሆነና እንደሚሉትም አስቸኳይ ከሆነ የድርጅቱ ባለንብረት ከሆኑት ከአባቷ ከአቶ መንገሻ ጋር ለምን አይነጋገሩም?" አለች ፀሐፊዋ ለተካልኝ አስቸኳይ ጉዳይ መፍትሔ ያገኘች ስለመሰላት። ተካልኝ "መንገሻ" የሚለውን ስም ሲሰማ ግምባሩን ቋጥር አደረገና የጥላቻና የምሬት ስሜት በአፍታ ገጽታውን አጨለመው። ቆይቶም "የለም... የለም ማግኘት የምፈልገው አብነትን ብቻ ነው። ልትረጂኝ የምትችይበት መንገድ ካለ እባክሽን እርጂኝ" ሲል ተማጸናት።

ፀሐፊዋ ግራ ተጋብታ ከእግር እስከ ራሱ ስትመለከተው ቆየችና "እንጃ፣ ልረዳዎ የምችል አይመስለኝም። እንደሚያስታውሱት ባለፈው ጊዜ ስልክ ደውለው ከነስምዎ ነግረውኝ እኔም ይህንኑ ነግሬያት የማታውቅዎ በመሆኑ ልታነጋግርዎ ፈቃደኛ አልነበረችም" አለችው ሥራ የሚፈልግ ሰው መሆኑን እየገመተች።

"አሁን የት እንደምትገኝ ታውቂያለሽ?... እባክሽ የኔ እመቤት እንዳልኩሽ የምፈልጋት እጅግ ላጣዳፊ ጉዳይ ነው"

ፀሐፊዋ የሰውየው ሁኔታ ስላላማራት ፈጥና መልስ አልሰጠችውም። የመኖሪያ አድራሻዋንም ልትነግረው አልፈቀደችም። ዛሬ ጊዜ ማን ማንን ያምናል? ሰው የገዛ ጥላውን እየሸሸ የሚኖርበት ጊዜ ነው። የሚፈልጋት ለክፉ ይሁን ለደግ ፣ በምን ታውቃለች?!

"እንጃ... የት እንደምትገኝ አላውቅም" አለችው ፍርጥም ብላ።

ተካልኝ አብነት የት እንደምትገኝ ፀሐፊዋ እንደምታውቅ ገምቷል። እናም በዋዛ አልለቀቃትም። "ስራሷ ጉዳይ ነው የምፈልጋት አልኩሽ እኮ የኔ እመቤት ... የውለታ ጉዳይ ሆኖብኝ ነው እንዲህ ያስቸገርኩሽ። ደግሞ ወደ ምድብ ሥራዬ የመመለሻዬ ጊዜ ካለፈ ሶስት ቀን ሆኖታል። ከዚህ በላይ አዲስ አበባ መቆየት አልችልም... አየሽ በጣም አጣዳፊና ብርቱ ጉዳይ ነው" አላት ተስፋ የቆረጠና የተሰላቸ ገጽታውን እንዳጨፈገገ።

"ጉዳይዎን ሊገልጹልኝ ይችላሉ?"

"ኧረ ብርቱ ሚስጥር ነው..."

"እንግዲያውስ ይቅርታ ያድርጉልኝና ልረዳዎ የምችልበት ምንም መንገድ የለም"

"ካልሆነ የቤቷን ስልክ ቁጥር ስጭኝ"

"አልችልም የኔ ወንድም ... ጊዜው እንደሚያዩት የከፋ ነው፤ ሰዎች ሰዎችን የሚያምኑበት ጊዜ አይደለም"

"ግድ የለሽም፣ እኔን እመኚኝ"

"እርሰዎ' ኮ እንደ እኔና እንደሌሎች ያው ሰው ነዎት" ፈገግ ብላ ፍንጭት ጥርሷን አሳየችውና ማስቲካዋን ማኘክ ቀጠለች።

"አየሽ... ለማንም የማልናገረው ጉዳይ በመሆኑ እኮ ነው..."

ፀሐፊዋ ይህ ሰው ከአብነት ጋር ሊኖረው ስለሚችለው ሚስጥር ለማወቅ በጣም ጓጓች "ምንም ቢሆን ጉዳይዎን ካልገለጹልኝ አድራሻዋን ልሰጥዎት አልችልም። እዩ የአለቆችን የግል አድራሻ ለማይታወቅ እንግዳ ሰው መስጠት የአንዲት ሙያዋን የምታከብር ፀሐፊ ሥነ-ምግባር አይደለም... እና ግድ የለዎትም፣ የርሷ የተባለ ሚስጥር ሁሉ የኔ ነውና ጉዳይዎን ይንገሩኝ..." አለች በፈገግታዋ እያግባባችው።

ተካልኝ ባልቻ በቅሬታ ፈገግ አለና ራሱን በአሉታ ወዘወዘ። "ይህ እንኳን የሚቻል ነገር አይደለም እመቤት..."

"እንግዲያው እኔም ልረዳዎት አልችልም"

በዝግታ ከመቀመጫው ተነሳና "አመሰግናለሁ" አላት። ፀሐፊዋ ማስቲካ ማላመጧን ትታ በጥርጣሬ ዐይን ስትመለከተው የሚያነክስ እግሩን እየጎተተ የቢሮዋን በር ከፍቶ ወጣ።

ከፊት ለፊቱ የመንገሻ የኔነህን ቢሮ የተዘጋ በር ተመለከተ። አንዳች መጥፎ ትዝታ የተቀሰቀሰበት ያህል ቆም ብሎ ግዑዙን እንጨት በጥላቻ ዐይን አፈጠጠበት። በሃሳቡ ያንን በር አልፎ በሰፊው ቢሮ



ውስጥ በተሽከርካሪ ወንበር ላይ የተቀመጠ ሥጋና አጥንት የለበሰ የሰው ሰይጣን መኖሩን አሰበና ፊጠን ብሎ ደረጃውን መውረድ ጀመረ።

ከሆንየው ወለል ላይ ሲደርስ እንደገና ገጹን በቅሬታ ፈገግታ አፍክቶ መተከዝ ያዘ። አዎን ከዚህ ቦታ ላይ ቆሞ ነው አብነት እስከ መቃብር የማይዘነጋውን ውለታ የዋለችለት! አባቷ አቶ መንገሻ አሥር ብር የማያወጣ የድርጅቱን ንብረት በመሰረቁ ከሥራ አሰናብተውት ስድስት ወር ሙሉ ሥራ አጥቶ ሲንከራተትን፣ ልጆቹ ራብን እያሉ ሲንጫጩበትን፣ አራስ ሚስቱ ጡቷ ደርቆባትን፣ ዐይኑ ስውር እናቱ በተኙበት የቦንዳ አልጋ ላይ ጤኔ ጥሎ በስል ጥርሱ ሲያኝካቸው... በነፍስ የደረሰችለት እዚህ ቦታ ቆሞ ነበር።

የሚያየውንና የሚሰማውን እስኪጠራጠር ድረስ በእጁ ላይ ያጠለቀችውን የወርቅ አምባር አውጥታ... 'ይህን ሸጠህ ለልጆችህ የሚቀምሱት ነገር ግዛላቸው... ምናልባት ሥራ እስከታገኝ አትራቡም ይሆናል...' ነበር ያለችው።

ከሁለት ዓመታት በፊት አብነት ባደረገችለት ውለታ የቤተሰቡን ህይወት ማትረፍ ከቻለ በኋላ ሥራ ፍለጋውን በርትቶ ቀጠለ። እንዳሰበው ግን አልሆነለትም። ዘመድ የለውም፣ ረዳት የለውም ። እናም ሰጥ ባለ ሜዳ ላይ ብቻውን እንደቆመና በየማእዘኑ የሚያስገመግም ንፋስ በየአቅጣጫው እንደሚያላጋው ዛፍ በህይወት ብርቱ ቡጢ ግራና ቀኝ እየተላጋ ተንከራተተ።

አብነት የቸረችው እርዳታ ከመሟጠጡ በፊት፣ እርሱና ቤተሰቦቹ ዳግም በረሃብ ስለታም ጥፍር ከመቧጠጣቸው በፊት ሊያገኝ የቻለው በፌናንስ ፖሊስ ውስጥ በውትድርና መቀጠር ነበር። እየቀረበ ከመጣው ሲኦል እንዲያመልጥ ሕይወት የከፈተችለት ቀዳዳ ያ ብቻ ሆነ። ሳያቅማማም ተቀጠረ።

የውትድርና ስልጠናውን እንደጨረሰም ለኮንትሮባንድ ቁጥጥር ሥራ ወደ አሶሳ ተላከ። አዲሱ ሥራውን በታማኝነትና በትጋት ለማከናወን ጣረ። የአብነት ውለታ ግን ለአንዲት ቀን እንኳን ተዘንግቶት አያውቅም። ልጆቹ፣ ሚስቱና አሮጊት እናቱ በታወሱት ቁጥር አብነትም ከፊቱ ላይ ድቅን ትልበታለች። ሰው ሆኜ ውለታዋን እመልሳለሁ የሚል እምነት ግን አልነበረውም።

ይሁንና ባለፈው ወር መጀመሪያ ላይ አንድ እንግዳ ጉዳይ አጋጠመው። የኮንትሮባንድ እቃ ጭናለች የተባለች አንዲት ቶዮታ ክሩዛን ኩምሩክ ተነስታ በአሶሳ አቋርጣ ለማለፍ ስትሞክር እንድትቆም

ትእዛዝ ይሰጣታል። ቶዮታዋን ያሽከረክር የነበረው ሰው ትእዛዙን በመጣስ መኪናዋን በከፍተኛ ፍጥነት እያሽከረከረ ያመልጣል። የአካባቢውን የፊናንስ ፖሊስ አዛዥ ሻምበልና እርሱን ጨምሮ ሶስት ሆነው በላንድሮቨር መኪና ቶዮታዋን ይከተሏታል።

ከብዙ ክትትል በኋላ ቶዮታዋ በጫነችው ዕቃ ከብደት ምክንያት የፖሊሶቹን ክትትል ማምለጥ ባለመቻሏ በውስጧ የነበሩ ሶስት ሰዎች ከመኪናዋ ወጥተው ተኩስ ይከፍታሉ።

ከኮንትሮባንድ ሠራተኞች ሁለቱ ሲሞቱ ከፖሊሶቹ ወገንም ሁለቱ ይወድቃሉ። ተካልኝ ባልቻም ግራ እግሩን በአንድ ጥይት ተመትቶ ከናፖሊዮን አምባው ጋር ይፋጠጣሉ። ናፖሊዮንን የት እንደሚያውቀው ያስባል "የአብነት አስመጪና ላኪ ድርጅት" ሠራተኛ መሆኑን ይጠራጠራል። በዚያች ቅጽበት አብነት ትታወሰውና በናፖሊዮን ላይ ያነጣጠረውን አፈሙዝ አውርዶ እንዲያመልጥ ይተወዋል።

ከዚያም በጥይት የተመታ እግሩን በጨርቅ አስሮ እያነከሰ ቶዮታዋ የድርጅቱ ንብረት መሆኗን ለማረጋገጥ ውስጧን መፈተሽ ይጀምራል። መኪናዋ ውስጥ ያገኘው ሰነድ ከፉኛ አስደነገጠው። በርግጥም ቶዮታዋ "የአብነት አስመጪና ላኪ ድርጅት" ንብረት ነች። መኪናዋ የጫነችውን የነፍስ ወከፍ የጦር መሣሪያ ዝርዝር ሲመለከት ደግሞ ባለበት ደርቆ ቀረ።

በያዘው ሰነድ ላይ የአብነትን ስም ሲመለከት ለእርሱና ለቤተሰቡ የዋለችው ውለታ ትዝ ብሎት አይኖቹ እንባ ማቅረር ይጀምራሉ። አሁን ደግሞ በርሷ ቤተሰብ ህይወት፣ ደህንነትና ንብረት ላይ በመጣ ከባድ ጉዳይ ውለታዋን የሚከፍልበት ቀን ስለመጣለት ተንበርክኮ የቆመበትን መሬት ሳመ። በእጁ የያዘውን ሰነድ አጣጥፎ ኪሱ በመክተት ወደ ካምፑ ተመለሰ።

ለህክምና ወደ ዳግማዊ ምኒሊክ ሆስፒታል መጥቶ በተኛበት ወቅት የገጠመው የመጀመሪያ ፈተና በአዲስ አበባ ወንጀል ምርመራ ፖሊስ ሻምበል በኩል የቀረቡለትን መሰቀለኛ ጥያቄዎች መመለስ ነበር። ሻምበሉ ስለ ሰነዱ የሚያውቀው ነገር እንደሌለ ቢያውቅም በኮንትሮባንድ ሠራተኞችና በፊናንስ ፖሊሶቹ መካከል በተደረገው የተኩስ ልውውጥ ወቅት ስላመለጠው ወንጀለኛ የሚያውቀው ነገር ሊኖር እንደሚችል ጠርጥሯል።



ሁለተኛውን ብርቱ ትግል የገጠመው ደግሞ ከጠበቃው ጋር ነበር። ያለበትን አድራሻ አነፍንፎ ያገኘው ጠበቃ የአብነት አስመጪና ላኪ ድርጅት የህግ ጠበቃ መሆኑን በመግለጽ ስለ ሰነዱ ጠየቀው። ተጠራጣሪው ፖሊስ ግን ስለሚያወራለት ሰነድ የሚያውቀው ነገር እንደሌለ በማስረዳት አፉን ይሰበስባል።

ጠበቃው ሊያምነው አልቻለም። ሰነዱ በእጁ ይገኛል ብሎ የገመተው የመጨረሻው ሰው እርሱ ነው። ስለዚህም ገንዘብ የማይከፍተው የሚስጥር ቁልፍ የለም ብሎ የሚያምነው ጠበቃ የአሥር ሺህ ብር የባንክ ቼክ በጎስቋላው ፖሊስ ፊት በመጻፍ ሰነዱን የሚሰጠው ከሆነ በዚያች ደቂቃ ውስጥ የአሥር ሺህ ብር ባለንብረት መሆኑን በመግለጽ ይፈታተነዋል።

ይህ ድርጊቱ ግን የተካልኝ ባልቻን ጥርጣሬ አባባሰው። ሰውዬው የወንጀል ምርምራ ፖሊስ ባልደረባ መሆን አለበት ወደሚል መደምደሚያ ደረሰ። በመሆኑም ስለ ሰነዱ የሚያውቀው ጉዳይ እንደሌለና በዚህ ዐይነቱ የወጀል ጉዳይ ውስጥ እጁን መክተት የማይፈልግ ምስኪን የልጆች አባት መሆኑን በማስረዳት፣ ሰነዱ በእጁ እንደሌለ በርግጠኝነት አሳመነው።

ግራ የተጋባው ጠበቃ ሲጋራውን እንደነከሰ እጆቹን ኪሶቹ ውስጥ ከቶ ማሰብ ጀመረ። ያ በደም ያደፈ ሰነድ በወንጀል ምርመራ ፖሊሶችና በደህንነቶች፣ በናፖሊዮን አምባውና በዚህ የፊናንስ ፖሊስ እጅ ካልገባ የት ደረሰ?

ይሄን ውስብስብ ጉዳይ መፍታት አልቻለም። ያም ሆኖ ግን ድል የርሱ ነች። ዋናው ነገር ሰነዱ ማንም እጅ አለመግባቱ ነው። በተስፋ እየፈገገ "ሰነዱ በኔ እጅ ነው!" አለ። ማን ከልካይ አለበት? በሥጋት የደነዘዘው የመንገሻ የኔነህ ጭንቅላት ለአፍታም እንደማይጠራጠረው አመነ። አብነትም ብትሆን ትቀበለዋለች። ስለዚህ የሚፈልገውን ለማግኘት ከጊዜ ጋር መሮጥ አለበት። የመንገሻም ይሁን የአብነት ጭንቅላት ረጋ ብሎ ለማሰብ ጊዜ ከማግኘቱ በፊት፣ የሰነዱ በማንም ሰው እጅ ያለመኖሩ እውነት ከጆሯቸው ከመድረሱ በፊት፣ ሰነዱ በእጁ መሆኑን አሳምኖ የአብነትን እጅና የድርጅቱን ቁልፍ ፈጥኖ መረከብ አለበት። ከዚያ በኋላ ሚስጥር ሆኖ ስለሚቀረው ጉዳይ የሚጨነቅ ይጨነቅበት ። ገጽታው በተስፋና በድል አድራጊነት እየፈካ ፖሊሱን ተሰናብቶት ወጣ።

ተካልኝ ባልቻ ከቆመበት የሆንጻው ወለል ላይ ሆኖ ሲያስብ ቆየና ከህንፃው ወጥቶ የአስፋልቱን ጠርዝ በመያዝ መንገዱን ቀጠለ።

ሳምንት ሙሉ አብሯትን ፈልጎ ማጣቱ ገርሞታል። አሁን ደግሞ ቢሮዋ ድረስ መጥቶ አጣት። ሃኪም የሰጠው ፈቃድ በመጠናቀቁ ሳያገኛት ወደ ምድብ ሥራው እንዳይመለስ ነበር ስጋቱ።



## ምዕራፍ ሃያ አራት

ኋይት ሃውስ ጓዳ ውስጥ ቻርሊ ተዘርሮ ከተኛበት ነቃ። ጭንቅላቱ ውስጥ የተጠመደው ፈንጂ ሊፈነዳ የተቃረበ እስኪመስለው ድረስ ውጥረት ይሰማዋል፤ ሰውነቱ እንደ እሳት በሚፋጅ ትኩሳት ይቃጠላል፤ መላ አካሉ በላብ ተጠምቋል።

የሃያ ሁለት ዓመት የትዳር ጓደኛው የሆነችውን የቲያትር ጥበብ ፈትቶ፣ የሃያ ሁለት ዓመት ልጁ የሆነችውን ኪነት ቀብሮ እርም አውጥቶ በመድረክ ላይ ከተዘፈረ በኋላ ተከታታዮቹን ሶስት ቀናት ያሳለፈው በንቂሴኮ አልጋ ላይ ነበር። መድረኩ ላይ ሲፈጠፈጥ ያበጠ ግምባሩን በመሀረብ አስሮ፣ በድካምና በህመም ስሜት የዛለ ሰውነቱን እየጎተተ ወደ ቤቱ የተመለሰውም ዛሬ ጠዋት ላይ ነበር።

ሊትል ቻርሊ ሁኔታውን ሲያይ ተደናገጠ። ቲያትር ቤቱ ውስጥ ተፈጥሮ ስለነበረው ትርምስ ሰምቶ ስለነበረ አባቴ በሰላም ወደቤቱ ይመለሳል የሚል ግምት አልነበረውም። ቻርሊ ውጭ በቆየባቸው ሶስት ቀናትም ውስጥ በጭንቀት እንደተሰቃየ በሃሳብ እንደተብከነከነ ነበር የሰነበተው። ስለዚህም የአባቱን ወደቤት መመለስ ሲያይ ከጭንቀቱ ተገላገለ።

ቻርሊ ከእንቅልፉ ነቅቶ አልጋ ላይ ተንጋልሎ ሳለ ከሌላኛው ክፍል ድምጽ የሰማ ስለመሰለው ከተኛበት ሆኖ ጆሮውን አቀና።

"...አንተ ግን ሊትል ለምን አባትህን አትመክረውም?" የሣራ ጋዴም ድምጽ ነበር።

"አባቴ የቃሉ ሰው ነው። የተናገረውን ከመፈጸም ወደ ኋላ የሚል አይደለም..." መለሰላት ሊትል ቻርሊ።

"እንደዚያ አትበል እንጂ ሊትል... ቲያትር ቤቱ እኮ ጠቅላላውን ተደናግጧል። እኛ ሆንን... የቲያትሩ አዘጋጅ ትላለህ፤ ደራሲውና አስተዳደሩ ጭምር ያልተረበሸ ማንም የለም። ሶስት ወር ሙሉ የመሪ ገፀ-ባህሪዩን ድርሻ ሲያጠና ሰንብቶ ተውኔቱ ሊታይ ጥቂት ጊዜ ሲቀረው አልሠራም ይላል! ፖስተሩ በስሙ ከተለጠፈ ስንት ጊዜው ... ማስታወቂያው በራዲዮና በቴሌቪዥን ተላልፎ፣ የጥሪ ካርዶች ታድለው አሁን በመጨረሻው አልሠራም ማለት ልክ ነው?! ደግሞ የሚገርመኝ የነገሩ መዘበራረቅ። ደብል ካስቱ አፕራሲዮን ሆኖ ሆስፒታል ከተኛ ሳምንት ሆነው... እና ለምን አትመክረውም ? ከሥራ

ያባርሩሃል... የሃያ ሁለት ዓመት አገልግሎትህ ከንቱ ይቀራል አትለውም? 'አይጥ ወልዳ ወልዳ ጅራት ሲቀራት ሲጥ' አሉ"

"በጃ"

"አይ ቻርሊ - 'ሲያልቅ አያምር' አሉ! ከነዚያ ሁሉ ዓመታት አገልግሎት በኋላ አሁን በመጨረሻው እንዲህ አድርጎ ተስፋ ይቁረጥ? በሆነ ባልሆነው መበሳጨት፣ በረባ ባልረባው ማኩረፍ፣ ሰውን ትንኝ አሳክሎ መናቅ ደግ ነው? ... ከተውኔቱ አዘጋጅ ጋር በምን እንደተጣሉ ታውቃለህ? አንተ እንኳን ቅድም የመሪ ገፀ-ባህሪዩን ቃለ ተውኔት ስትጫወትልኝ አንድ ቦታ ላይ ስለ ተስፋ የሚያወራው አንድ አባባል አለ አይደል? ቆይ ምንድነው..."

"...'አልሞትኩም እኮ! ገና ነኝ! ትንፋሼን ጨርሼ አልዋጥኩም! ... ወድቋል ብለው ደስ እንዳይላቸው..... ትንፋሼን ላስደምጣቸው!... ይሄው የተስፋን ፀዳል ከገጼ ላይ ላሳያቸው!..... ይሄው' የሚለውን ነው?"

"ልክ ነህ ሊትል!... ይሄው አንተ እንኳን በደንብ ትጫወተዋለህ። ቃለ-ተውኔቱን በደንብ አጥንተኸዋል.... በቃ፣ በዚህ ነው ከአዘጋጁ ጋር የተጣሉት። አዘጋጁ የተስፋን ሳቅ ስቀህ አሳየኝ ሲለው ቻርሊ አንድ ጊዜ የቁጭት፣ አንድ ጊዜ የምጸት፣ አንድ ጊዜ የትዝብት፣ አንድ ጊዜ ደግሞ የንቀት እያደረገ አዘበራረቀው። ይቅር እንቅስቃሴውንና የገጽ ገለፃውን ቃለ-ተውኔቱን ማለት ቀፈፈው። እንዴ ቻርሊ ግን ምን ነካው? በእውነት ጤነኛ ነው? ግን አንተ ምነው ብትመክረው ሊትል..."

"ዳዲ ከኔ ይልቅ ራሱ ለራሱ ያውቃል..... እየኮረኮመ ፊደል ያስቆጠረኝን፣ ህይወትን ያስተማረኝን ሽቅብ ተንጠራርቼ እንዲህ አድርግ ልለው አልችልም... እዝናለሁ ሣራ"

"ስማ ሊትል..... አንተ ግን አላማህ ምን ለመሆን ነው?"

"ተዋናይ"

"እውነት?"

"ሹር!....."

"ታድለህ"

"ሣራ፣ አንቺ ጎበዝ ተዋናይ ነሽ..... ግን ሙያውን ትወጅዋለሽ?"

"በደንብ ነዋ! በዚህ ዓለም ላይ የምኖረው ለሁለት ነገር ስል ብቻ ነው - ለቲያትር - ሥነ-ጥበብና ለዳንስ! ምናልባት ቻርሊ ነገሮህ ይሆናል ሊትል.... አባቴ ሀብታም ነጋዴ ነው። ዘመዶቼ ሁሉ ብር አፍንጫቸው ድረስ ብፍ ነው። እኔ ተቀጥሬ የምሠራበትን የወር ደሞዝ



ብነግርህ ግን ትስቃለህ ። ይህንን ሥራ ስጀምር ከአባቴ ተጣላሁ። ... ዘመዶቼ ሁሉ ጠሉኝ .... ናቁኝ። የራሳቸው ጉዳይ! እኔ የእኔን እንጂ የእነርሱን ህይወት አልኖርም። ነጋ ጠባ ጭቅጭቃቸው ሲሰለቸኝ ከነቤቱም ጥየላቸው ወጣሁና ብቻዬን ትንሽ ቤት ተከራየሁ። እየህ እኔ አሁን ወደፈለገችበት አቅጣጫ ያለ ከልካይ እንደምትበር ወፍ ነፃነት ያለኝ ሰው ነኝ። ሙያውን እፈቅረዋለሁ.... እናም ደስተኛ ነኝ"

"አባቴ ግን በሙያው ተስፋ የቆረጠ ይመስላል..."

"ቻርሊ የድሮው ቻርሊ እንዳይመስልህ። እኔ ሥራ እንደጀመርኩ ጊዜ በትዕግስቱና በታታሪነቱ የማደንቀው ለወጣቶቹ ተዋንያን ሁሉ አርአያ የሆነ አርቲስት ነበር። አሁን ግን ምን እንደነካው አላውቅም"

"እኔ ደግሞ ይገርምሻል እርሱ እንዲህ ተስፋ የቆረጠበትን ሙያ የነፍሴን ያህል እወደዋለሁ። ከልጅነቴ ጀምሮ ምኞቴ ሁሉ አርቲስት ሆኖ ለመኖር ነው..."

ቻርሊ ከተኛበት እንደምንም ያለ ሃይሉን አጠራቅሞ ተነሳና የበሩን ጉበን በሁለት እጁ ይዞ ሊትል ቻርሊ ላይ አፈጠጠበት። ላቡ በግንባሩ ላይ ይወርዳል፤ የአበጠው ግምባሩ ቆዳ በልዞ ጠቋሯል፤ ሰውነቱ በዝግታ ይንቀጠቀጣል። "ምን ስትል ነው የሰማሁህ ሊትል?!"

"እንደምን ሰነበትክ ጋሼ.... ተሻለህ?" አለችው ሣራ እጥፍጥፍ ብላ ከተቀመጠችበት አሮጌ ሶፋ ላይ ፈጥና በመነሳት። ቻርሊ ግን ዞር ብሎ እንኳን አላያትም።

"አንተን እኮ ነው የምጠይቅህ..." በልጁ ላይ ያፈጠጡት ዐይኖቹ አልረገቡም። ሊትል ቻርሊም አልመለሰለትም። ከሲጋራው ጭስ በሚያወጣቸው ቀለበቶች ላይ ዐይኖቹን እንደተከለ ዝም አለው።

"እሺ እኔ ምን አደረኩህና ታኮርፈኛለህ ቻርሊ ....እኔና የሙያ ባልደረቦችህ ምን በደልንህ?" ሣራ ጋዴም ጣቶቿን እያፍተለተለች በሚማጸኑ ዐይኖቿ ትደባብሰው ጀመር።

"ሁለተኛ ቅድም ያልኩውን ደግመህ ስትል ብሰማህ አንገትህን አንቄ ነው የምገድልህ... ገባህ?! እንደ ቋንጣ ነው ዘልዝዬ የምሰቅልህ!" የቻርሊ ድፍርስ ዐይኖች ከአፎታቸው መውጣት ከንፈሮቹ መንቀጥቀጥ ጀመሩ።

ሊትል ቻርሊ ሲጋራውን መሬት ወርውሮ ረገጠና በፍጥነት ተነስቶ ቆመ። "ምን አድርግ ነው የምትለኝ ዳዲ? ራስህን ካድ ነው

የምትለኝ? በውስጡ የሚነደውን እሳት በረዶ ነው ብለህ ሸፍኖ ነው የምትለኝ? አልችልም! አልችልም! ተዋናይ መሆን እፈልጋለሁ! ሙያውን እወደዋለሁ። እና ይህንን እውነት መካድ አልችልም ዳዲ.... የፈቀድከውን አድርገኝ.... ይሄው በትፈልግ ግደለኝ!" ዐይኑን አፍጥጦ ፊት ለፊት ተጋፈጠው።

ቻርሊ በውስጡ መፍላት የጀመረ ደሙ በአፍታ ቀዘቀዘና እንደፈዘዘ ቀረ። ቆይቶ በእንቅልፍ ልቡ እንደሚቃዥ ሰው ሆኖ ለራሱ ያሀል አጉተመተመ "ይህንን ቃል ከሃያ ሁለት ዓመት በፊት እኔው ራሴ ብየው ነበር፤ ዛሬ ደግሞ አንተ ደገምከው። እኔ በገባሁበት ሲኦል አንተ እንድትገባ አልፈልግም.... እኔ ያባከንኳቸውን ዓመታት.... አንተ እንድታጠፋቸው አልፈቅድም ሊትል!"

"ዳዲ...."

"ሊትል.... ነጮች ምን እንደሚሉ ታውቃለህ? 'ከወጣት ብልጣብልጥ ይልቅ የሽማግሌ ሞኝ ብልህ ነው' ይላሉ። እና እባክህ ልብና ጆሮህን ሰጥተህ ስማኝ። እባክህ ለአንድ ጊዜና ለመጨረሻ ብቻ እሺ ብለህ አድምጠኝ.... በመጨረሻው እድሜዬ አንተው ብቻ ነህ የቀረኸኝ.... እና ስማኝ። ተዋናይነት የባህሪይ ዘማዊነት ነው፤ ራስን ረስቶ ሁሉን መምሰል ነው። እቋም የለሽነት ነው፤ ነፃ ድህነት ነው፤ የእድሜ ኪሳራ ነው፤ 'ቀን በቬሎ ማታ ቆሎ' ኑሮ ነው ሰማኸኝ ሊትል?"

"ጋሼ ቻርሊ..."

"ይቅርታ ሣራ፤ አንቺ ቆይኝ.... አንተ የኔው ጉድ ሰማኸኝ? ተዋናይ ሆነህ በራስህ ጭንቅላት የገዛ ሃሣብህን አታስብም፤ በገዛ ልብህ የገዛ እምነትህን አታምንም፤ ማንነትህን ምንነትህን እንደረሳህ የእድሜ ሸማህ ሰትነትብ፤ እስትንፋስህ ስትደክም ቀንህ የመሸ ቀን ድንገት እንደ እኔ ትነቃለህ.... ከጨለመ ትባንናለህ.... እድሜህን ምን ስትሠራ እንዳሳለፍከው እያሳቀህ፤ እያስጨነቀህ፤ እያስቆጨህ ትነሳለህ።"

ሣራ ጋዴም ይህን ንግግር በትዕግስት ማስጨረስ አልሆነላትም። ቻርሊ ራሱ በአንገቱ ውስጥ ሸምቀቆ ጠልቆለት እስትንፋሱ ከመሰናበቷ በፊት የመጨረሻውን የሙት ዲስኩር የሚያሰማ ሰው መሰላት።

"ተው እንጂ ጋሼ ቻርሊ... ይሄ እኮ የራስህ አስተሳሰብ ነው። ለምንድነው የሊትልን ስሜት የምትጫነው? የራሱን የህይወት አቅጣጫ ፈለግ ራሱ አነፍንፎ እንዳይፈልጋት ለምንድነው ይህን ሁሉ መሰናከል



ከፊቱ የምታኖረው ? ልክ አይደለህም ቻርሊ..... ይሄ የምትለው ሁሉ ሀሰት ነው!" ሸንቧን ገትራ ሞገተችው።

ቻርሊ በምጸት ፈገግ አለ። "አውቃለሁ ሣራ፤ አንቺ ምን ያህል ሙያውን ከልብሽ እንደምታፈቅሪው አውቃለሁ። በአንቺው ደርሶ እስኪታይው ምን ብልሽ የህይወት ልምዴን እንደማታምኚው፤ ምክሬን እንደማትሰሚው አውቃለሁ። 'ቲያትር የሞኝ ፍቅር ነው'፤ ያጃጅላል.... ራስ ያስረሳል። አንተ ግን ተጠንቀቅ ሊትል... ይህን እያዳመጥክ እምቢ ካልክ..." ንግግሩን ሳይጨርስ አንጠልጥሎ ተወው። ምንም እንደማያደርገው ያውቃል። ከልጅነቱ ጀምሮ አብሮ ያደገውን በሽታ በጠበል ብቻ ነው ያልሞከረው። በቁጣ፤ በምክር፤ በዱላ ሊነቀልለት አልቻለም። ምን እንደሚለው ግራ ገብቶት አፉን እንደከፈተ ቀረ።

ሣራ ክንዱን ያዝ አድርጋ ሶፋው ላይ አስቀመጠችው። ሊትል ቻርሊና እርሷ ከታጣፊው አልጋ ጠርዝ ላይ ተቀመጡ።

"እስኪ አሁን የሊትል ነገር ይቆይና የአንተን እንነጋገር ቻርሊ። ያንተን ጉዳይ እንዴት አደረከ? ሁሉም እኮ ግራ ገብቶትና ተስፋ ቆርጦ የሚጠባበቀው የአንተን ውሳኔ ብቻ ነው" አለች ሣራ በስጋት ዐይኖቹን እያስተዋለች።

የቻርሊ መልስ ቁርጥ ያለ ነው "ሊቃሌ ሳልታመን፤ ስዋሽና ስቀጥፍ አይተሽኝ ታውቂያለሽ ሣራ? በቃኝ ብያለሁ፤ በቃኝ!"

"ጋሼ.... እባክህ ደጋግምና ረጋ ብለህ አስበው። የተውኔቱ መክፈቻ ጥቂት ጊዜ ሲቀረው? የኛን የሙያ ጓደኞችህን ድካምና... የሌሎች ባለሙያዎችን ብርቱ ጥረት ሁሉ እንዴት ዋጋ ታሳጣዋለህ?"

"አዘጋጁ ልከሽ ነው የመጣሽው ሣራ?"

"ተው እንጂ እንደሱ አትበል..."

"አዎን እንደሚያወጣሽ አውቃለሁ... እና አማላጅ ሆነሽ ነው የመጣሽው? ለግልግል ነው የመጣሽው?"

"ጋሽ ቻርሊ ደግሞ ታበዛዋለህ.... በእውነት ታበዛዋለህ...." ሣራ ለንቦጯን ጣል አደረገች።

"ራስህ ሥራው በይው። እርሱ ባለዲግሪ፤ ባለወረቀት፤ እንኳን ተውኔት አዲስ ሰማይና አዲስ ምድርን ፈጣሪ አይደለም? ራሱ ይሥራው" በመጨረሻው የመድረክ ሥራው ላይ የሆነውን ሲያስታውስ ሰሞኑን ደጋግሞ በጆሮው ላይ እየጮኸ ጭንቅላቱን ሲፈልጠው የቆየ ድምጽ በህሊናው ያስተጋባ ጀመር "መሃይም! መሃይም! መሃይም!"

"ራሱ ይሥራው... በቀደም መድረኩ ላይ እንደቆምኩ ግራ ገብቶኝ.... ሃያ ሁለት ዓመት የተካንኩበት የመምሰል ጥበብ ጠፍቶኝ... በተስፋ መሳቅ አቅቶኝ... ሰማይ ምድሩ ሲዞርብኝ... ምን ብሎ እንደሰደበኝ ሰምተሽ የለም?" ቻርሊ በቁጭት ከንፈሩን ነከሰ።

"ደግሞ ምን አለኝ ልትል ነው?" ሣራ ቅንድቧን ሽቅብ ሰብስባ አፈጠጠችበት። "ሰምተሻል ሣራ.... እንድደግመው ትፈልጊያለሽ? እኔ አዕምሮዬ ዞሮ ስንገዳገድ መሃይም አለኝ... ይሄ የምሁር ጅምር.... ጥራዝ ነጠቅ እውቀት የታጀለበት እንኩላ ራስ... ሃያ ሁለት ዓመት በሠራሁበት መድረክ ላይ ቆሞ... መሃይም አለኝ..."

"እኔ ይህንን አልሰማሁም... ይልቅ ይህን ተወውና ውሳኔህን አሳውቀኝ"

"ቻርሊ ለቃሉ ታማኝ ነው በይው... ንገሪው.... በቃኝ!"

የሣራ ዐይኖች እንባ አቀረሩ። ለቻርሊ ከልቧ አዘነችለት። እንደ ህይወቷ ዋነኛ ግብ አድርጋ በመረጠችው ሙያ ትልቅ ስምና ዝና ያተረፈ የሙያ ባልደረባዋ ከረዥም ጊዜ አገልግሎቱ በኋላ ተስፋ ቆርጦና ግራ ገብቶት አሮጌው ሶፋ ላይ ዝናብ የመታው ዶሮ መስሎ ስታስተውለው አንጀቷ በሀዘኔታ ተላወሰ።

"ጋሼ በመጨረሻ... በመጨ..." ንግግሯን ሳግ አፍኖ በውስጧ አነቀው። እንባዋ ግን ኩልል ብሎ ወረደ።

"አዎን ሣራ.... በመጨረሻው እንዲህ ሆንኩ። የሃያ ሁለት ዓመት ትዳሬን ፈታሁ። ልጄን ቀበርኩ። ስንቱን ዘመን ሳስታምማት የኖረች ጥበብ በውስጤ ሞተች። እኔ ነኝ ያለ ባለተራ ደግሞ ከወደቀችበት ያንሳት፣ እስትንፋሱን እፍ ብሎ ደግሞ በተራው ነፍስ ይዝራባት። በቃኝ ሣራ.... በቃኝ!"

ሣራ እንባዋን በሹራቧ እጅጌ እየጠራረገች ጫማዋን አድርጋ፣ ቦርሳዋን ይዛ ተነሳች።

"ሊትል እባክህ ሸኘኝ..." እሪ ብለሽ ጮኸሽ አልቅሽ የሚል ስሜት ታገላት። ከዚያ በላይ እዚያ ቆማ የቻርሊን ጣር ማየት አልፈለገችም።

"ደህና ሁኝ ሣራ.... ሁላችሁም ደህና ሁኑ.... በርቱ..." ሊሰናበታት ብድግ አለ።



"ቻርሊ!" ድንገት ተወረወረችና አንገቱ ላይ ተጠምጥማ ስቅስቅ ብላ ታለቅስ ጀመር። "ጋሼ፣ በመጨረሻው... እንዲህ ሆንክ?" እንባ ባቀረሩ ዐይኖቹ ትኩር ብሎ ተመለከታት። የዛሬዋን ሳይሆን የነገዪቱን ሣራ። ወዟ ተመጦ፣ የፊቷ ቆዳ ተሸብሽቦ፣ የተካነችበት የመምሰል እውቀት ጠፍቷት ...ግራ ገብቷት..."

"በርቺ ሣራ፣ በርቱ!" እሁድ መጥቼ ዝግጅታችሁን እመለከታለሁ። ሃያ ሁለት ዓመት ሙሉ በተሳቀብኝ መድረክ ላይ የጥበብን ሞት እያየሁ .... የፍቅርን ሞት እያየሁ... የውብትን ሞት እያየሁ መሳቅ እፈልጋለሁ። እኔም ለአንድ ቀን እያለቀስኩ እስቃለሁ" ለስንብት የዘረጋችለትን እጇን ጨብጦ ወዘወዘው።

ሣራ ድንገት የረሳችውን ነገር አስታውሳ "ቻርሊ.... ታፔ ኩልኩልት በጡረታ መሰናበታቸውን ሰምተሃል?" አለችው እንባዋን እየጠራረገች፣ ከቻርሊ ገጽ ላይ የደስታን ስሜት ለማንበብ እየጓጓች።

ቻርሊ ፈጥኖ አልመለሰላትም። በታፔ ኩልኩልት ጡረታ መገለል አልተደሰተም። የዘወትር ጭንቀታቸው ታሰበውና በሀዘኔታ ራሱን ወዘወዘ። "አልሰማሁም ሣራ... በኪነት ትከሻ ላይ የተጫኑ ጋን የሚያህል ጭነት ወረደ፣ በርሜል የሚያህለው እንዳይተካ ደግሞ ቀን ከሌሊት ፀልዩ" አላት በምጸት ፈገግ እንዳለ።

ሣራ የቻርሊን ሽሙጥ አልወደደችውም። ፈጥና ካለችበት በመንቀሳቀስ "ሊትል እባክህ ሸኘኝ...." አለችና በሩን አልፋ ወጣች።

ሊትል ቻርሊ ከተቀመጠበት ታጣፊ አልጋ ላይ ተነስቶ ወደ በሩ ሲያመራ ቻርሊ ክንዱን ያዝ አድርጎ አቆመውና ትክ ብሎ በስስት ይመለከተው ጀመር። ሊትል ለብቻው ሊነግረው ያሰበው ነገር እንዳለ ስለገመተ ወደ ሣራ ዞር አለና "እየሄድሽ ጠብቂኝ....." አላት።

አባትና ልጅ አንዳቸው በአንዳቸው ዐይን ውስጥ ጠልቀው ገብተው እርስ በርስ ይመራመሩ ጀመር። በሰውነት አቋምና በፊታቸው ገጽታ ፍጹም ተመሳሳይ ናቸው። በቅርብ ርቀት ካልሆነ በርቀት እንዳቸውን ከአንዳቸው መለየት ያስቸግራል።

ቻርሊ በዝግታ የሸሚዙን ቁልፎች ፈታና አንገቱ ላይ ለረዥም ዓመታት እስሮት የኖረውን ባለ ኮከብ የብር ጌጥ ከአንገቱ ላይ አውልቆ ለሊትል ቻርሊ አስጨበጠው። ሊትል ግራ ተጋብቶ ዐይኖቹን

እያንከራተተ አንድ ጊዜ የብሩን ጌጥ አንድ ጊዜ አባቱን ይመለከት ጀመረ።

"ስለዚህ ጌጥ ብዙ ጊዜ ጠይቀኸኝ ብዙ ጊዜ ብዙ ነገር አስጠንቸሃለሁ። አይደለም ሊትል?"

"አዎን ዳዲ.... ግን እኮ...."

"ይህን ጌጥ... ይህን የማንነትህን ማስታወሻ ... በአንገትህ ላይ የማጥለቂያው ጊዜ አሁን ነው...."

"ዳዲ...." ሊትል አንድ ሺ ጥያቄዎች ለመጠየቅ አፉን ከመከፈቱ ቻርሊ አቋረጠው።

"ሊትል፤ አሁንም ዘወትር የምነግርህን እደግመዋለሁ .... ሰው ሁን! እወድሃለሁ።" ትከሻውን አቅፎ ግምባሩን ሳመው።

ሊትል በእጁ የያዘውን ጌጥ እያስተዋለ ፊዞ እንደቆመ ቻርሊ ትከሻውን ገፋ አድርጎ "ሂድ ሊትል፣ ሣራ ትጠብቅሃለች" አለው።

ሊትል ከሰመመኑ ነቅቶ ራሱን ወዘወዘና በፍጥነት እየተራመደ ወደ ሣራ አመራ።

ቻርሊ በሩ ላይ እንደቆመ ሊትል ቻርሊና ሣራ ጋዴም ከነድ ለከነድ ተቆላልፈው በኮረኮንቹ መንገድ ላይ በዝግታ እየተራመዱ ለዐይን እስኪርቁ ድረስ አስተዋላቸው። ለራሱ ብቻ በሚሰማው ድምጽም "ሊትል... አንተ የመጨረሻ ንብረቴ፣ እወድሃለሁ!" ሲል አጉተመተመ።



# ምዕራፍ ሃያ አምስት

በአዲስ አበባ ወንጀል ምርመራ ፖሊስ ጽ/ቤት ቅጥር ግቢ ውስጥ ባለው ቢሮው ውስጥ ተቀምጦ አንድ ፋይል ያገላብጣል - ሻምበል መብራቴ። የእጅ ሰዓቱን ተመለከተ፤ ከጠዋቱ 3:30 ሰዓት ጠረጴዛው ላይ የተቀመጠውን መጥሪያ እንደተጫነ ቢሮው በር ላይ የነበረው ፖሊስ ፈጥኖ ወደ ውስጥ በመግባት ሰላምታ ሰጥቶ በተጠንቀቅ ቆመ።

"ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ የሚመጣውን እንግዳ ያለ ምንም ጥያቄ ፈጥነህ እንድታስገባው!"

"እሺ ጌታዬ" ወታደሩ በሩን ዘጋና ወጣ።

በአሶሳ አካባቢ በፈናንስ ፖሊሶችና በኮንትሮባንዲስቶች መካከል በተፈጠረው ግጭት ህይወቱ የጠፋችውን የፈናንስ ፖሊስ ደም ለመበቀል ከየአቅጣጫው የሚደረግበት ግፊት በመጨመሩ ተወጥሯል።

ጉዳዩ እስከዛሬ ያለአንዳች አጥጋቢ ውጤት በመጓተቱ በሀገሪቱ የወንጀል ምርመራ ሥራ ላይ እምነት እንዳይኖራቸው ያደረገ መሆኑን በመግለጽ ታላላቅ ከተባሉት ባለስልጣኖች ውስጥ ብዙዎቹ አለቆቹን አውግዘዋቸዋል። ለርሱም በተዋረድ ያለቆቹ ወቀሳና ዘለፋ እንዲሁ ደርሶታል።

ሻምበል መብራቴ ይህን በእንጀራው የመጣ መሰናክል አልፎ የፖሊሳዊ ሙያውን ውጤታማነት ለማሳየት ወንጀሉ ተፈጸመ ከተባለበት ጊዜ ጀምሮ ቀን ተሌት እንደሮጠ ነው። ስለወንጀሉ አፈጻፀም ቴክኒካዊ መረጃዎችን ሰብስቧል፣ ከወንጀሉ ጋር ግንኙነት ሊኖራቸው ይችላሉ ያላቸውን ሰዎች በጥብቅ ተከታትሏል - ተጨባጭ ፍንጭ ማግኘት ግን አልቻለም።

ወንጀሉን ፈጽሟል ብሎ የሚገምተው ናፖሊዮን አምባውን ነው። ከብዙ ውጣ ውረድና አስቸጋሪ ትንታኔ በኋላም ናፖሊዮን አምባው ከረን ላይ በተደረገ ጦርነት አልሞተም ወደሚል ድምዳሜ ደርሷል። ከዚህ አንጻር ደግሞ ናፖሊዮንን በህይወት አይተነዋል የሚሉ ሰዎች ግን አላጋጠሙትም።

የወንጀለኛው እናት ነች የተባለችው ሴት ስለ ልጇ በህይወት መኖርም ይሁን መሞት የምታውቀው ነገር እንደሌለ እየማለችና እየተገዘተች ቃሏን ሰጥታለች። በተከሉ ልውውጥ ወቅት በህይወት

የተረፈው የፈናንስ ፖሊስ በበኩሉ ከአየር ወለድ መዝገብ ቤት የተገኘውን የናፖሊዮንን ፎቶግራፍ ተመልክቶ ያመለጠው ወንጀለኛ ይህ አይደለም ሲል በርግጠኝነት ተናግሯል።

ከእነኚህ መረጃዎች በተፃራሪ ደግሞ ከፖሊስ ጠቅላይ መምሪያ በአሻራ ኤክስፐርቶች የተሰጠው ማረጋገጫ፣ ከመኪናዋ ልዩ ልዩ ክፍሎች ላይ የተወሰደው አሻራ ናፖሊዮን አምባው በአየር ወለድ ሠራዊት ውስጥ ሲቀጠር ከሰጠው አሻራ ጋር አንድ መሆኑን በማረጋገጥ፣ ናፖሊዮን አምባው ከሁለት ዓመት በፊት በጦር ግንባር ሞቷል የሚለውን እምነት ውድቅ ያደርገዋል።

ሻምበል መብራቴ የናፖሊዮንን ፈለግ ለማነፍነፍ ሦስት የትኩረት ነጥቦች ሊሆኑ ይገባል ብሎ ባመነባቸው ሰዎች ማለትም በናፖሊዮን እናት በተካልኝ ባልቻና በጠበቃው ህይወት ዙሪያ የመረጃ ሰዎቹን በማሰማራት ክትትሉን የቀጠለ ቢሆንም ከአንዳቸውም ላይ ከወንጀለኛው ጋር ግንኙነት ሊኖራቸው ይችላል የሚያሰኝ ፍንጭ ሊያገኝባቸው አልቻለም። የወንጀለኛውን ማንነት ለማወቅ ያደረጋቸው ሙከራዎች ሁሉ ውጤት አልባ በመሆናቸውም ተስፋ ወደመቁረጡና ራሱንና ፖሊሳዊ ሙያውን ወደመጥላት ተቃርቧል። በተለይ እለት ተለት ስልክ እየደወሉ የሚዘልፉትንና የሚያስጠነቅቁትን ባለስልጣኖች ስድብና ዛቻ መስማት እንገሽግሾታል። አሁን የመጨረሻውን ሙከራ ለማድረግ በዝግጅት ላይ ነው። ይህ እቅዱ የማይሳካለት ከሆነ ግን የርሱ ነገር አበቃለት።

ከፊት ለፊቱ የተዘረጋውን ፋይል አጠፈና ጠረጴዛው መሳቢያ ውስጥ ከተተው። ብዙም ሳይቆይ ጠበቃው አቶ ሰዩም የቢሮውን በር አንኳኩቶ ገባ። በገጹ ላይ የወትሮው ንቃትና ፈገግታ አይታይበትም። ሻምበሉ ይህን ያስተዋለው ጠበቃው ገና የቢሮውን በር እንደረገጠ ነው። 'አሶሳ ላይ ከተፈጸመው ወንጀል ጋር ግንኙት አለው፤ የወንጀለኛውን ማንነትና ወንጀለኛው ያለበትን ቦታ ሊያውቅ ይችል ይሆናል' የሚለው የሻምበሉ ግምት ከቀን ወደ ቀን እየጨመረ ቢሄድም ማስረጃ በማጣቱ ግራ ተጋብቶ ሰንብቷል።

ሻምበሉ ፈጥኖ ከመቀመጫው በመነሳት የሞቀ ሰላምታ ሰጠው። ጠበቃውም የውሸት ፈገግታ ለማሳየት እየሞከረ የሻምበሉን ሰላምታ ከመለሰለት በኋላ ግምባሩን ቅጭም እንዳደረገ ወንበር ስቦ ተቀመጠ።

የጠበቃው ጭንቀት ገጹ ላይ በጉልህ ይነበባል። ሻምበሉ ትላንትና ስልክ ደውሎ ሊያነጋግረው እንደሚፈልግና ጠዋት ቢሮው እንዲመጣ ከጠየቀው በኋላ መንፈሱ ተረብሿል። ፖሊሶች



ስለተፈጸመው ወንጀል የተጨበጠ ማስረጃ ያገኙ ስለመሰለውና የእርሱም እጅ በጉዳዩ ውስጥ ያለበት መሆኑ ስለተደረሰበት ሊያስሩት እንደፈለጉ በመገመቱ ሙሉውን ሌሊት እንቅልፍ በዐይኑ ሳይዞር ሲወራጭ ነው ያደረው።

ሳምንቱን ሙሉ የመንፈስ እረፍት አልነበረውም። ተካልኝ ባልቻ አብነትን ለማግኘት ያደረገው ሙከራ ሚስጥር ምን እንደሆን ሊያውቅ ባለመቻሉ የምኞቱን መፈጸም ተጠራጥሯል። አሁን ደግሞ ሻምበሉ ይፈልገዋል። ለምን ጉዳይ እንደፈለገው እስኪገልጽለት ድረስ ዘና ብሎ መቀመጥም ይሁን ዐይኖቹን ማየት አልደፈረም። ይህ የባህሪይ ለውጥ ደግሞ የሻምበሉን ጥርጣሬ በማጉላት የመጨረሻ ሙከራውን እንዲገፋበት ሀሊናውን እያነቃ አጃገነው።

ስለ ሥራ፣ ስለጤንነቱና የተለያዩ ቀላል ጉዳዮች ሲያጫውተው ቆይቶም "ዛሬ የጠራሁህ እንኳን ደስ ያለህ ልልህ ነው..." አለ ሻምበሉ ፈገግታውን በገጹ ላይ እያሞቀ።

"በአምላክህ፣ ምን ተፈጠረ ልትለኝ ነው?" አለ ጠበቃው በተጠራጣሪ ዐይኖቹ ሻምበሉን እየመረመረ።

"የመኪናህ መብራቶች ወላልቀው በመወሰዳቸው እጅግ አዝነህ ፖሊሳዊ ሙያችንንም ስታንኳስስብን ነበር..." የሻምበሉ ፈገግታ አሁንም በገጹ ላይ ይጫወታል።

"እና.... ምን አዲስ ነገር ተፈጠረ?" ጠበቃው በመገረም ይመለከተው ጀመር።

"የመኪናህን ዕቃ የሰረቁት ሌቦች ሊያሻሽጡ ላይ ታች ሲሉ በፖሊሶቻችን እጅ ወድቀዋል... የምስራች!"

ጠበቃው ፈጥኖ አልመለሰለትም። የተጠራበትን ምክንያት ሲረዳ ሌሊቱን ሙሉ እንቅልፍ አሳጥቶ ሲያስጨንቀው ያደረ ሃሳብ ቀስ በቀስ እንደ ጉም እየተበተነ ከውስጡ ተኖ ሲወጣ ታወቀው። "እናንተ ፖሊሶች እኮ ተአምረኞች ናችሁ። ከነዚህ ሁሉ ቀናት በኋላ እንዴት ተሳካላችሁ? እኔማ ተስፋ ቆርጬ የተሰረቁትን ዕቃዎች በሙሉ በአዲስ ከተካኋቸው ሳምንት አለፈ" በማለት መገረሙን ገለጸለት።

"እና የጠራሁህም የምርጥ ፖሊሶቻችንን የሥራ ውጤት እያደነቅክ ንብረቶችህን እንድትረከብ ነው"

"አመሰግናለሁ ሻምበል" የጠበቃው ገጽታ ፈካ። የመኪና ዕቃዎቹ ጉዳይ ከቁም ነገር የሚጻፍ አይደለም። እንዲያውም ሲያስጨንቀው ያደረው ሃሳብ እውነት አልሆነ። "ትዕግስት ግሩም ነገር ነው ጃል!..... በችኩልነት ተግባራችሁን በመንቀፌ ባይሆን ጠርሙስ ውስኪ እቀጣለሁ።" የታሰረ እንደበቱ እየተፍታታ በራሱ ፌዝ ራሱ ሲስቅ ሻምበሉም ተከተለው።

"እየሀ በፖሊሳዊ ሥራ ዋናው ነገር ትዕግስት ነው... የጊዜ ጉዳይ እንጂ ማንኛውም ወንጀል እንደተቀበረ አይቀርም። አሁን በቀደም ያጫወትኩህ የዚች ግቢያችን ውስጥ የቆመች ቶዮታ ጉዳይ ትዝ አይልህም?"

ሻምበሉ አሰሳ ላይ ወደ ተፈጠረው ወንጀል ጉዳይ ገብቶ ውይይት የሚከፍትበት ቀዳዳ በማግኘቱ ፈጥኖ ተጠቀመበት።

"የ... የቷ ቶዮታ?" የጠበቃው ገጽታ በአፍታ ጽልመት ለበሰ፤ አንደበቱም እንደመተሳሰር አለ።

"ምነው እንዲን አሰሳ አካባቢ ወንጀል የተፈጸመበት" አለ ሻምበሉ ጉዳዩን በሁለት ጓደኞች መካከል የሚደረግ ተራ ጨዋታ ለማስመሰል ያለውን ፖሊሳዊ ጥበብ እየተጠቀመ።

"እምን፣ ልክ ነው። አራት ሰው ሞተ ነው ምናምን ያልከኝ..."

"በትክክል አስታውሰሃል.... እንደዚያ የተወሳሰበውን የወንጀል መረብ እንኳን ከጊዜ ጋር ልንበጣጥሰው ችለናል ። የወንጀለኛውም ማንነት ታውቋል።"

ጠበቃው አንዲት ቃል መተንፈስ አቅቶት ከተቀመጠበት እንደደነዘዘ ቀረ። ትናንሽ ዐይኖቹ ብቻ ሻምበሉ ፊት ላይ እየተንከባለሉ ይቅለጨለጫሉ። ድካሙ ሁሉ ምኞቱ ሁሉ እንደ እንቧይ ካብ ሲደረባ ታየው። የአብነት አስመጭና ላኪ ድርጅት ባለቤትነቱ፣ የአብነትን እጅ የመጨበጥ ህልሙ ቅዠት መሆኑ ታየው።.. በወንጀሉ ቀጥተኛ ተጠያቂም ባይሆን በተዘዋዋሪ መንገድ አፍንጫው ድረስ የተነከረ በመሆኑ የራሱም ደህንነት አጠራጠረው። እጅግ ብዙ ዘግይቶ "ወንጀለኛው ተያዘ ማለት ነው?" ሲል የራሱ ባልሆነ ድምፅ ጠየቀው።

ሻምበሉ የጠበቃው እጅ በወንጀሉ ውስጥ መነከሩን ገጽታውንና እንቅስቃሴውን በመመልከት አረጋገጠ። "አልተያዘም፤ በቅርቡ ግን እጃችን እንደሚገባ ፍጹም እርግጠኞች ነን"



የጠበቃው አንደበት እንደ ተቆለፈ ቀረ። የገዛ ልቡን ፈጣን ምት እያዳመጠም በፀጥታ ተቀመጠ።

"... እና እንዳልኩህ.... ለፖሊሳዊ ሙያ ዋናው ጉዳይ ጊዜና ትዕግስት ነው። ይህ አሰሳ ላይ ተፈጸመ የምልህ ወንጀል መያዣ መጨበጫ የሌለው በመሆኑ የወንጀለኛውን ፈለግ ብዙዎቻችን እንደርስበታለን የሚል እምነት አልነበረንም... ጊዜና ትዕግስት ግን ሁሉን እንደ መስተዋት ወለል አድርገው አሳዩን - የዚህ ወንጀል ፈፃሚ ናፖሊዮን ይባላል!"

ጠበቃው እንዳች የኤሌክትሪክ ሞገድ በአካሉ ያለፈ ያህል ከመቀመጫው ብድግ ብሎ ተመልሶ ተቀመጠ። ለሻምበሉ ይህ አንድ ታላቅ ድል ነበር።

"ምነው አቶ ስዩም... ደህና?" አለ ሻምበሉ ግምባሩን ቅጭም አድርጎ። የጠበቃው የተቆለፈ አንደበት ለመፈታት ጥቂት ጊዜ ወሰደበት።

"አይ...ይ.... ይህ የምትለኝ ሰው ነጭ መሆን አለበት"

አለ ፈጥኖ እጆቹን ወደ ኪሱ በመላክ ሲጋራና ክብሪት እየፈለገ።

ሻምበሉ የውሸት ሳቅ እየሳቀ "መደንገጥህ አያስደንቀኝም። እኔም ይህንን ስም ስሰማ እንዳንተው በድንጋጤ ከመቀመጫዬ ተነስቻለሁ። ባይገርምህ ይህ ሰው ኢትዮጵያዊ ነው... የአየር ወለድ ሠራዊት አባል የነበረ ወታደር..."

የጀመረውን ሳይጨርስ ጠበቃው ፈጥኖ አቋረጠው "ታዲያ ለምን አልተያዘም?"

ሻምበሉ ፈገግ እያለ "አሁንም ትንሽ የጊዜና የትዕግስት መስዋእትነትን እንድንከፍል ፖሊሳዊ ሙያችን ግድ ይለናል። እየሀ፣ የሰውየውን ማንነት ብናውቅም እስከአሁን አድራሻውን ልናገኝ አልቻልንም..."

ጠበቃው ይህን የምሥራች ሲሰማ በውስጡ እየሞተ ያለው ተስፋ እንሰራርቶ ነፍስ ሲዘራ ታወቀው። "አድራሻውን ማግኘት አልተቻለም ነው ያልከው?"

ሻምበሉ ፈጥኖ መልስ አልሰጠውም። በረጅሙ ሲተነፍስ ቆየና "እምን፣ አዲስ አበባ ውስጥ ለመኖሩ እርግጠኞች ብንሆንም... ቀን

ሌሊት በመብራት ፈልገን ልናገኘው አልቻልንም። በየኬላውና በየክፍለ ሃገሩ ለሚገኙ የፖሊስ ሃይሎች ሁሉ ፎቶግራፉን በትነናል። አሁን ዋነኛው ችግራችን ምን እንደሆነ ገብቶሃል? ወንጀለኛው አዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ከተደበቀ እስከ ምጽአት ልናገኘው አንችልም"

"ታዲያ ምን አሰባችሁ?"

"ምንም። ወንጀለኛው ከተደበቀበት ጎሬ ወጥቶ እንዲንቀሳቀስ ሱባኤ ገብተን እንጸልያለን" አለ ሻምበሉ።

"አምላክ ይርዳችሁ" አለ ጠበቃው የውሸት ፈገግታ እየሞከረ።

"አሜን።" ሻምበሉ እየተንከተከተ ከጣራ በላይ ሳቀ። ጠበቃው ግን በዚህ ቀልድ አብሮ መሳቅ አልሆነለትም። በሀሳብ እንደዋለለ፣ በጭንቀት እንደተሽማቀቀ ሲጋራውን ሲያጨስ ቆየና ሰዓቱን መልከት አድርጎ "አመሰግናለሁ ሻምበል፣ ዕቃውን መረከብ እችላለሁ?" ሲል ጠየቀ።

"በሚገባ እንጂ። ለሁለተኛ ግን መኪናህን አጉል ቦታ አቁመህ ብዙ እንዳትርቅና ዳግመኛ ፖሊሳዊ ተግባራችንን እንዳታወግዝ..." አሁንም ከጣራ በላይ ሳቀ።

"ኧረ አይለምደኝም ሻምበል፣ ሳጠፋሁትም እከሳለሁ" ጠበቃው አፉ ቢንተባተብም በሀሳብ ከፖሊሱ ርቆ ከናፖሊዮን አምባው ጋር ይወያያል።

ሻምበሉ አነስተኛ ወረቀት ላይ ማስታወሻ ጽፎ ጠረጴዛው ላይ ያለውን መጥሪያ ሲጫን በር ላይ የቆመው ፖሊስ ፈጥኖ ገባ። ሻምበሉ ማስታወሻውን እያቀበለው "ይህን ማስታወሻ ይዘህ ግምጃ ቤት ሂድና ንብረታቸውን አስረክባቸው" በማለት ትዕዛዝ ሰጥቶ ጠበቃውን ከሞቀ ሰላምታ ጋር የቢሮውን በር አሳልፎ ሸኘው። ፈጥኖም ወደ መስኮቱ በመጠጋትና ቁልቁል በማየት የጠበቃውን እንቅስቃሴ ይከታተል ጀመር።

ጠበቃው የተረከበውን ንብረት ከመኪናው ዕቃ መጫኛ ውስጥ አስገብቶ ከቆለፈ በኋላ የመኪናውን ሞተር አስነስቶ በፍጥነት ተፈተለከ። ከዚያ ግቢ በሰላም መውጣቱን ያረጋገጠው የምንሊክ አደባባይን አቋርጦ የቸርችል ጎዳናን ቁልቁለት ሲያያዝ ነው።

አሁንም እቅዱን ለማሳካት ትንሽ እድል ያለው ለመሆኑ ተስፋ አድርጓል። ናፖሊዮን በጨለማው ክፍል ውስጥ አርፎ ከተቀመጠ ሻምበሉ እንዳለው እስከ ምጽአት ፈልጉን ሊያሸቱ እንደማይችሉና ምጽአት ደግሞ ለጠበቃው መቼም የማይደርስ ቀን መሆኑን አምኗል። ያ የሰው ጭራቅ እግሩን ሰብስቦ ይቀመጣል? ያም ሆነ ይህ ትልቅ ሰው



የመሆን ህልሙን እውን ለማድረግ በቀረችው ዕድል ለመጠቀም ናፖሊዮን አምባውን ማግኘት ይኖርበታል። ጊዜ ሳያጠፋ ፖሊሶች ወንጀለኛ መሆኑን እንደደረሱበትና ማንነቱን እንዳወቁም በማስረዳት ካለበት እንዳይንቀሳቀስ ማስጠንቀቅ አለበት።

ቤሔራዊ ባንክ ደርሶ የመኪናውን መሪ ወደ ቀኝ በማጠፍ የሰንጋተራን አቅጣጫ ሲይዝ፤ የአብነት አስመጭና ላኪ ድርጅትን ቁልፍና የአብነትን እጅ ለመጨበጥ ካቀደ ወዲህ ያጋጠመውን ችግርና ፈተና ሁሉ እስታውሶ በቅሬታ ፈገግ አለ። መሰናክሎችን ሁሉ አልፎ አሸንፍኩ ሲል አሁን ደግሞ የፖሊሶቹ ወደ ወንጀሉ ፈፃሚ መቃረብ አስደነቀው። በእቅዱ መሠረት ከሦስት ቀናት በኋላ "የአብነት አስመጭና ላኪ ድርጅት" ባለንብረት የሆኑት አቶ መንገሻ ድርጅቱን ለጠበቃው በስጦታ ማስተላለፋቸውን የሚያረጋግጠውን ሰነድ በሶስት እማኞች ፊት ይፈርማሉ - እሁድ! በመጭው ሳምንት ውስጥ የስጦታው ውል በፍርድ ቤት ይጸድቃል። ከዚያ የአብነትን እጅ ሳትወድ በግድ ይጨብጣል። የዚህ እቅድ ፍጻሜ በጣት የሚቆጠሩ ቀናት ብቻ ሲቀረው የፖሊሶቹ ዘራፍ ማለት ምንድነው?!

መኪናውን አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት በር ላይ አቁሞ በእግሩ መንደር ውስጥ ገባና ግራ ቀኝ ተገላምጦ ናፖሊዮን የሚኖርበትን የአጥር ግቢ በር ገፋ አድርጎ ወደ ውስጥ ገባ።

ሻምበል መብራቴ ጠበቃው ከፖሊስ ጣቢያው መኪናውን አስነስቶ ከወጣበት ቅጽበት ጀምሮ የሲቪል ታርጋ በተለጠፈባት ቮልስዋገን መኪና ከኋላው ተከትሎታል! ስለዚህም ጠበቃው የናፖሊዮንን የአጥር በር ከፍቶ ሲገባ በርቀት ይመለከተው ነበር።

## ምዕራፍ ሃያ ስድስት

ዘወትር በፈገግታ ያጌጥ የነበረው ገጽታዋ በፍርሃትና በሽብር ደብዝዟል። ፈርጠም ያለው አካሏ ውሃ እንደገባው አሞሌ እለት ተለት እየሟሸሸ መንምኗል። መንጋትና መምሸታቸውን በውል በማትለያቸው የመጨረሻዎቹ ቀናት የመኝታ ክፍሏን ቆልፋ አልጋዋ ውስጥ እንደተወሸቀች ሰነበተች። ከሰዎች በመራቅና ጠረናቸውን በመሸሽ የመንፈስ ሰላም የምታገኝ መስሏት ነበር። ያሰበችው አልተሳካም። በያንዳንዷ ሰከንድ ዐይናቸውን አፍጥጠው ከሚታገሏት እውነታዎች ጋር መጋፈጧ የግድ ነበር። የራስ ቅሏ የፈነዳ እስኪመስላት ድረስ የሃሳብ ናዳ ህሊናዋን እየፈለጠ የእፍታ እፎይታና ሰላም ነሳት። ፀጉሯን እየነጨች "ሰው ከገዛ ህሊናው ሸሽቶ የት ይደርሳል?" እያለች ብቻዋን በመጮህ ሁለት የእንቅልፍ እንክብሎች ትውጥና ከጥቂት ደቂቃዎች ቆይታ በኋላ በእንቅልፍ ትወሰዳለች። ይህ ግን መፍትሔ አልሆናትም። ከእንቅልፏ በነቃች በጥቂት ደቂቃዎች ውስጥ ደግሞ ወደ ቀድሞው ሃሳብና ጭንቀት ተመልሳ ትገባለች - እብነት መንገሻ።

የየዕለቱ ግጭቷ ውጫዊውን ዓለም፣ ሰዎችን፣ ህይወትንና ተፈጥሮን በመጥላት በምሬት መንገፍገፍ፤ ውስጣዊ የስሜትና የሃሳብ ተቃርኖዎቿን መዳኘት ነው።

"… አቤ… ዳግም እንደማትነሽ ሆነሽ መውደቅሽን ታውቂያለሽ? እንደሻማ እየቀለጥሽ ማለቅሽስ ይሰማሻል? ለምን ብለሽ ራስሽን እንዳትጠይቂ ህሊናሽን ምን አደነዘዘው? ዐይኖችሽን ገልጠሽ እንዳታይ ምን የምትሀት በርኖስ ጀቦነው?" የገዛ ህሊናዋ በወቀሳ ይለበልባታል። "… ፍቅር ከህይወት በላይ ነው? ወይንስ ራሱ ፍቅር ህይወት ነው?… ቃልስ ቢሆን ምንድነው? ከትናጋችን አፈትልኮ በአየር ውስጥ አየር የሚሆን ትንፋሽ አይደለም? ቃል ከህይወትና ከህልውና በላይ ነው? ወይስ ቃል ለህይወት ነው? የማይጨበጥ ተስፋስ ምንድነው? ተስፋ የህይወት ነዳጅ እንጂ እራሱ የህይወት ግብ ነው? እዚ. ለምን እንደ ሃያ አንደኛው ክፍለ ዘመን ሰው አታስቢም?" በቁጭት ያንዘበዝባታል።

ይህ ሁሉ ሆኖ አንድ ሺህ ያህል ዐይኖቻቸውን ያፈጠጡና ጥርሳቸውን ያገጠጡ እውነታዎች የልቧን ፍቅር አጥበው ሊያጠሩት አልቻሉም። አንድ ሺህ አጥጋቢ ምክንያቶች የነፍሷን እምነት ሰብረው ቃሏን ሊያስክዷት አልሆኑላቸውም። የፍቅር ጉልበት ሃይሉ በምን ይለካ ይሆን?!



ለዚህ ህይወቷ ምንነት ትርጉም መስጠት ባትችልና በተከናነበችው የጨለማ በርኖስ ውስጥ ቅንጣት ታህል የተስፋ ፍንጣቂ ባይታያትም፣ ያለፉትን ጥቂት ቀናት በጨለማ ውስጥ አሳልፋቸዋለች። ምናልባትም መኖር ማለት መተንፈስ ከሆነ አሁንም ትንፋሿ አልቆመም፣ ትተነፍሳለች።

የመኝታ ክፍሏ በር ሲደበደብ ስማችና ከተኛችበት ተፈናጥራ በመነሳት መብራት አበራች። ሰዓቷን ስትመለከት ከምሽቱ አንድ ሰዓት ይላል። በለበሰችው ረዥም ፒጃማ ላይ ጋቢዋን ደረብ አደረገችና በሩን ከፈተች። የቤት ሰራተኛዋ ዘረቱ ሻይ የያዘ ብርጭቆና ጣፋጭ ይዛ ቆማለች።

"ተሻለሽ አብዬ…"

"ደህና ነኝ…"

"እስኪ ይችን እንኳን ቅመሽ…" አለችና የሻዩን ብርጭቆና ጣፋጩን ትንሿ ጠረጴዛ ላይ ካኖረችላት በኋላ "አባትሽ ሊያነጋግሩሽ የሚፈልጉ ይመስለኛል" ብላት እየተጣደፈች ክፍሉን ለቃ ወጣች።

እፍታም ሳይቆዩ መንገሻ የኔክ ጥቁር ካፖርታቸውን እንደለበሱ ፒጃቸውን ነክሰው በሩን ገፋ በማድረግ ወደ መኝታ ክፍሏ ገቡ። ዐይናቸውን ማየት ስለቀፈፋት ፊቷን ወደ ግድግዳው አዙራ አልጋው ጠርዝ ላይ ተቀመጠች። የቻርሊን ፍፃሜ ሊያረዷት እንደመጡ አልተጠራጠረችም።

መንገሻ ትምባሆውን እያጨሱ ክፍሏ ውስጥ ጥቂት ከተንጎራደዱ በኋላ "የኔ ልጅ ፣ እባክሽ ህይወቴንና የራስሽንም እድል ጉድጓድ ቆፍረሽ ለመቅበር አትወራጪ። ስለ መጭው እንጂ ስላለፈው ጊዜም አትጨነቂ… አየሽ የረገጥናት ምድር ሰፊ ነች። ህይወትም በሚሊዮን የሚቆጠሩ መስመሮች አሏት… የሰው ልጅ ብልህነትም ይሁን ጅልነት የሚፈተነው ባለችው አጭር እድሜ ውስጥ እነኝህን የህይወት መስመሮች እንዴት እየለዋወጠ እንደሚጠቀምባቸው ከማወቁ ወይንም ካለማወቁ ላይ ነው፤ አንድ የህይወት አማራጭ መጭጭ ብሎ በመያዝ ከሚመጣው እርጋታ የሚገኝ ነገር ቢኖር መበስበስና መሽተት ብቻ ነው። እና ያለፈውን ረስተሽ የመጭውን ቀን አስተውይ…" አሏት።

የዚህ ገለፃ ትክክለኛ ግልባጭ የቻርሊን ፍጻሜ የሚያረዳ መሆኑን ስለገመተች ያቀረቀረውን አንገቷን ወደ አባቷ መልሳ "ቻ… ቻርሊ ሞቷል ? ቻርሊ ሞቷል ማለት ነው?" ስትል ጠየቀቻቸው። ድምጿ ይቆራረጣል፣ ከንፈሯ ይንቀጠቀጣል።

የለበጣና የምጸት ፈገግታቸውን ፈገግ ብለው "ስለምትይው ሰው የማውቀው ነገር የለም" በማለት አፌዙባት። እንደሚያውቁ ግን ጥርጣሬ አልነበራትም።

"ዳግም ቻርሊን አታገኘውም!" እንደሚሏት አልተጠራጠረችም። ከተቀመጠችበት አልጋ ላይ ተፈናጥራ ተነሳችና ድንጋጤና እልህ በሚያንቀጠቅጣቸው እጆቿ የካፖርታቸውን ኮሌታዎች ጨምድዳ በመያዝ "ንገረኝ ቻርሊ ሞቷል!" በማለት እየጮኸች ዐይናቸው ሥር ተጠግታ አፈጠጠችባቸው።

መንገሻ የልጃቸው እብደት ድንበር ጥሶ መሄዱን አልተጠራጠሩም። በገፃቸው ላይ ይጫወት የነበረው የምጸት ፈገግታ ከስሞ ዐይኖቻቸው በንዴት ተበለጠጡ። ካፖርታቸውን ጨምድዶ የያዘውን እጇን መንጭቀው እንደ ብረት በቀዘቀዘ አጥንታማ መዳፋቸው በጥፊ መተው ወለሉ ላይ ዘረሯት።

የገረጣ የጉንጯ ቆዳ የጣት ያህል ለበለባት። ከወደቀችበት አበባ ምንጣፍ ላይ እየተፍገመገመች ተነሳችና አልጋዋ ጠርዝ ላይ ተቀመጠች። የተመታውን ጉንጯን በጣቷ ስትዳብሰው ሰንበር አውጥቷል። በድካም የዛለው ሰውነቷ ተሸክሟት ሊቆም አልቻለም። በእልህና በቁጭት የጋለው መንፈሷ ግን አዲስ እንደተወለደች ጀንበር ጉልበቱ ገና አፍላ ነበር።

"ቻርሊ ሞቷል?" ራሷን እንጂ አባቷን የጠየቀችው ጥያቄ አልነበረም። የተጨማደደውን የካፖርታቸውን ኮሌታ አስተካክለው የጠፋውን ፒፓ ክብሪት ጭረው ከቀጣጠሉ ሁለት ሶስት ጊዜ ከሳቡ በኋላ "የምትይው ሰው ህይወት በእጄ መዳፍ ውስጥና በእጅሽ መዳፍ ውስጥ ነው" አሏት መንቀጥቀጥ በጀመረ ድምጻቸው።

በትክክል ያዳመጠቻቸው ስላልመሰላት ጭንቅላቷን ደጋግማ በመወዝወዝ ራሷን ለማንቃት ሞከረችና ከተቀመጠችበት በዝግታ ተነስታ ቆመች። ደም የለበሱ ዐይኖቿን ማየት ያስጠላቸውን ያህል ፊታቸውን ወደ ግድግዳው ጠመዘዙና "የምናገረውን አድምጠሻል?" በማለት ጮኹ። "ቢያንስ እስከ አሁን ቻርሊ አልሞተም። አምላኬ እባክህ እርዳኝ" ስትል ለራሷ ያህል አጉተመተመች።

ዝምታዋ አጠራጥሯቸው ወደ ግድግዳው ያዞሩትን ፊታቸውን መለሱና "የምትይው ሰው ህይወት እንድትቆይ ትፈልጊያለሽ?" ሲሉ



ደግመው ጠየቋት። መልሱ እንደ ጥያቄው ቀላል ነበር የአዎንታ መልሷን ተከትሎ የሚመጣው ሌላ ጥያቄ ግን ምን እንደሚሆን አላጣችውም።

"የእርሱን ህይወት እኔ ብቻ ሳልሆን ምናልባት አንተም ትፈልጋት ይሆናል" አለችና በረዥሙ ተነፈሰች። በዚያች ቅጽበት ፍርሃት፣ ሀፍረትና ይሉኝታ ቦታ አልነበራቸውም። ምን ለማለት እንደፈለገች ግራ ስለገባቸው የዐይኖቻቸውን መስከቶች አጥብበው በመገረም ይመለከቷት ጀመር።

"እርግጠኛ ነኝ... በሆዴ የተሸከምኩት ህፃን ያለአባት እንዲቀር አትፈልግም!" ስትል ያበጠውን እውነት አፈረጠችላቸው። ሰው ታሞ እንጂ መቶ ፈርቶና ሰግቶ ይሞታል?!

እሬት እሬት የሚለው እውነት ከአንደበቷ ተወንጭፎ ጆሯቸው ላይ ሲነጥር የተበለጠጡ ዐይኖቻቸው ሳይረግቡ የተከፈተው አፋቸው ሳይገጠም በቆሙበት ደርቀው ቀሩ። የደነዘዘ አዕምሯቸውን ለማንቃት የፈጀባቸው ጊዜ ረዥም ነበር። የያዙትን ፒፓ ወርውረው እጆቻቸውን ወደ ኋላ በማጣመር በክፍሉ ውስጥ በፀጥታ ይንጎራደዱ ጀመር። ቆይቶ የሚራመዱበት ፍጥነት ዝግ እያለ፣ ገፃቸውን ያለበሰው የቁጭትና የተስፋ መቁረጥ ጥላ እየተገለጠ ዐይኖቻቸው የወትሮ ቅርፃቸውን ያዙ። በክፍሉ ውስጥ በተንቆራጠጡበት ጊዜ ውስጥ ፈጣኑ አዕምሯቸው የገጠመውን ችግር ለመፍታት ምን ስልት እንደነደፈ ለመገመት አልቻለችም።

በአልጋው ትይዩ ባለው ወንበር ላይ ተቀመጡና እጃቸውን አጣምረው እንደ ጉድ ተመለከቷት። በዚያ ዝምታ ውስጥ የሚያሳዩዋትን ያን የምትጠላውን የምጸት ፈገግታቸውን አልወደደችውም።

"ጥሩ....." አሉና የተዘጋ አንደበታቸውን ጠራረጉ "ከእንግዲህ በኔና በአንቺ መካከል የሚኖረው ግንኙነት በአባትና በልጅ መካከል የሚኖር ግንኙነት አይደለም! ማስፈራራቴ እንዳይመስልሽ። ምህረትና ይቅርታ እንደማይኖር ከኔ ይልቅ አንቺ ይህን አብልጠሽ ታውቂዋለሽ። ለጊዜው ይህን ያለቀ ጉዳይ እንርሳው...."

ወልዶ ባሳደገ አባትና ልጅ መካከል ያለ በደምና በሥጋ የተገነባ አንድነት እንዲህ በዋዛ እንደሚንዱት የእንቧይ ካብ በአፍታ ይደረባል ብላ አልገመተችም ነበረ። መንገሻ ግን አምርረዋል፤ ከምንም

በላይ የቃላቸው ሰው እንደሆኑ ስለምታውቅ መጨረሻቸው እንደቀረበ አሰበች።

"...የስነምግባር ወይም የሞራል ሰው አይደለሁምና ስለዲቃላሽ ወይንም ስለዲቃላሽ አባት የምጨነቅ እንዳይመስልሽ... የምትይውን ሰው ህይወት ከፈለግሽ ጠበቃውን ያለ አንዳች ተቃውሞ ታገኚያለሽ! ሰውየሽ ወፍ ሆኖ ወደ ምድር ሜፍ ቢበር እንኳን እንደማያመልጠኝ እወቂ..." የሚሉትን ፒፓ ከወለሉ ላይ አንስተው ቆሙ።

"በአንድ ልጅህ ህይወት እየቆመርክ መሆኑን ታውቃለህ?" አብነት ሳታስበው ጮኸች።

ከካፖርታቸው ውስጥ የተንጠለጠለ ቀጭን ትከሻቸውን ሰበቁና "ለመኖር በሚደረግ ትግል ውስጥ ሁሉም ሰው ቁማርተኛ፣ ህይወት ራሷ ቁማር ነች! የአንዱ መክሰር የሌላው መክበር፣ የአንዱ ሞት ለሌላው ህይወት መሆኑ የሚገባሽ መቼ ነው?" አሏትና በሩን በሃይል ዘግተው ወጡ።

"ሰይጣን!" አለች አብነት ከንፈሯን በጥርሷ እንደነከሰች። "ያ ምስኪን ግን ለምን አይሸሽም ? እኔ ስለ ፍቅርና ስለ ቃሌ ስል ይህን ሁሉ መከራ ስቀበል ቢያንስ ከተማውን ለቆ መውጣት ያቅተዋል ?" ስትል አሰበች።

ጓይት ሃውስ አሮጌ ሶፋ ላይ ኩርምት ብሎ እንደተቀመጠ ዓለም በጭንቅላቷ ተዘቅዝቃ የምትታየው ይመስለዋል። አናቷ ተዘቅዝቆ በምትሰቅበት ዓለም ሰሌዳ ላይ ያሳለፋቸው ዓመታት ትዝታዎች ሁሉ አንድ በአንድ እንደ ፊልም ይታዩታል። ከመነሻ እስከ መድረሻው ሁሉም የሃዘን ክል ያጠለቁ አስከፊ ዓመታት ናቸው። በልቶ ያልጠገበባቸው፣ ጠጥቶ ያልረካባቸው፣ ለብሶ ያላጌጠባቸው፣ ሠርቶ አመድ ያፈሰባቸው፣ አፍቅሮ ያልተደሰተባቸው፣ ወልዶ ተስፋ ያላየባቸው፣ በመንፈስም በሥጋም የተሰቃየባቸው እንዲሁ የባከኑ ዓመታት።

ጭንቅላቷን ዘቅዝቃ በምትሰቅበት ዓለም ላይ ምራቁን ጢቅ እያለ መልሶ ይሰቅባታል። ለማን ይድላው ብሎ ያልቅስ? ሰው ነው! እስትንፋሱ እስከትከዳው መሸነፉን ሳይቀበል የሚንገዳገድ ወንድI እየሞተ አለሁ የሚል፣ ወድቆም የቆመ የሚመስለው ጀግና።

ነገ እሁድ 'የመከነች ተስፋ' የተሰኘው ተውኔት ለህዝብ ይቀርባል። ሃያ ሁለት ዓመት በደከመበት መድረክ ላይ ጥበብ ሞታ ትቀበራለች! በርሱ ምትክ ማንን እንደሚያጫውቱ አያውቅም።



ምናልባት እዘጋጁ ራሱ፣ ምናልባትም ታሞ የተኛውን አርቲስት ከአልጋው ቀስቅሰው ያጫውቱት ይሆናል ... የራሳቸው ጉዳይ ። ቻርሊ እንደሁ የኪነት እርሙን አውጥቷል።

ሊትል ቻርሊን ባለፉት ጥቂት ቀናት አላየውም። ዛሬ ጠዋት ግን ወደ ጓይት ሃውስ መጥቶ ነበር። ዘወትር ከገጹ ላይ የማይጠፋው ፈገግታ ከስሞ፣ በአካልና በመንፈስ ደክሞ፣ ከዚህ በፊት በገጹ ላይ ያልነበሩ የህይወት መስመሮች ግምባሩን አርሰውት፣ ዐይኖቹ ስጋትና ሽብር እንደፈጠጠባቸው ጠይቆት ሄዷል።

ቻርሊ ቅብጥብጥና ለነፍሱ የአንዲት ሰከንድ እርጋታ ያልነበረውን ልጅን በጥቂት ቀናት ውስጥ መንፈሱ የበረዶ ያህል ቀዝቅዞ፣ አንገቱን እንደሰበረ፣ ፀይኖቹን ከዐይኑ እያሸሸ ሲሸማቀቅ ሲያይ በህይወቱ ውስጥ የተፈጸመ ታላቅ ለውጥ እንዳለ አላጣውም። ምክንያቱ ምን እንደሆነ ሊገለጽለት ግን አልቻለም። ሊጠይቀውም አልፈለገም። ከእንግዲህ ሊትል የራሱን ህይወት ወደፈቀደበት አቅጣጫ ለመጠምዘዝ መሪውን በገዛ እጁ ጨብጧል።

በተገለጠው ሸሚዙ ውስጥ ባለኮከብ ቅርጹን የብር ጌጥ ሲመለከት አንዳች የደስታ ስሜት ከውስጥ እየፈነቀለው የተቀመጠበት አሮጌ ሶፋ ላይ እየተቁነጠነጠ በስስት ዐይን ተመለከተው። የመጨረሻ ተስፋውን። እስከአሁን በህይወቱ ውስጥ የሞከራቸው ነገሮች ሁሉ ውድቅ ሆነው በሊትል ቻርሊ ሰው መሆን ተስፋ ያይ ይሆን? ዙሪያውን በከበበው ጨለማ መሃል ትንሽ የተስፋ ብርሃን ብልጭ ብላ ታየችው።

በምትሰቅበት ዓለም ላይ እየሳቀ ብቻውን ሲነጋገር የጓይት ሃውስ በር ከበደውና ዞር አለ። ዐይኖቹ የሚያዩትን ማመን አልቻለም። አብነት ከስታ፣ መንምናና ከሰውነት ተራ ወጥታ ነጠላዋን ከላይዋ ጣል እንዳደረገች በሩ ላይ ቆማለች።

ከአብነት መንፈስ ጋር የተፋጠጠ መስሎት ሊያማትብ እጁን ሲያነሳ አብነት ተንቀሳቅሳ ወደ ውስጥ ስትገባ አያት።

"ደህና ሰንብተሃል የኔ ዓለም..." እጇን ለሰላምታ ዘረጋችለት። አልጨበጣትም። የጠቆረውን ፊቷን፣ ዐይኖቿ ጉድጓዶች ውስጥ የተንጠለጠሉ ዐይኖቿን፣ የደረቁ ከንፈሮቿንና በተገለጠው ደረቷ ላይ ያገጠጡ የጎድን አጥንቶቿን ሲመለከት ፈራት።

አብነትም ለሰላምታ የዘረጋችለትን እጇን እንዳንጠለጠለች አሮጌው ሶፋ ላይ የተቀመጠውን ሰው ቁልቁል ስትመለከተ በስሁተት

ሌላ ሰው ቤት ውስጥ እንደገባች ተጠራጠረች። ግምባሩ ላይ በስሱ የተጋገረውን ጥላሸት የመሰለ ብልዝ፣ የእሳክሬን የመሰሉ ዐይኖቹን፣ ያቢቃለት አዛውንት ያስመሰለውን የደቀቀ ሰውነት ስትመለከት የገዘ ዐይኖቿ የሚያዩትን ካደች።

"ማነሽ?" የራሱ ባልሆነ ቀጭንና ስላላ ድምጽ ጥርጣሬ የገባቸውን ዐይኖቹን እያርገበገበ ጠየቃት።

"አ - አብነት ነኝ... በእርግጥ አንተ የኔው ቻርሊ ነህ?" ልቧ ፍጥነቱን እየጨመረ መምታት ጀመረ።

"አብነት ? ... አብነት? ምን ልትፈልጊ መጣሽ..."
"ጠላኸኝ ቻርሊ?"
"አብነት የምትባል ሴት አላውቅም!" ጭካኔውና ቁርጠኝነቱ በገጹ ላይ እንዳፈጠጠ ጮኸ።
"እርግጠኛ ነህ?!" አለችው የዐይኖቿን መስኮት አጥብባ።
በአዎንታ ራሱን ነቀነቀ።
"እባክህ እንደገና አስታውስ?"

ፍዝዝ ብሎ ሲመለከታት ቆየና በምጸት ፈገግ አለ። "አዎ... አዎን... አሁን ትዝ አልሽኝ... አብነት የምትባል አንዲት ፍቅረኛ ነበረችኝ... ሰው ነች ብዬ ሳምናት ድንገት ውሻ ሆና አገኘኋት። ሰው ሳይሆን ውሻ አፍቅሬ፣ ውሻ አቅፌ፣ ውሻ ስስም እንደነበር ሲታሰበኝ እስከ ቅርብ ቀን ድረስ በቁጭት እንጨረጨር፣ በፀፀት እበግን ነበር። አሁን ግን ከዐይኔ ሰማይ እንባ ሳይሆን ደም እያዘነብኩ ከልቤ ውስጥ አጥቤ አወጣኋት... እና አብነት የምትባል ውሻ እንጂ በሁለት እግሯ የምትሄድ የሰው ፍጥረት አላውቅም!" ድምጹ እየተቆራረጠ፣ ከንፈሩ እየተንቀጠቀጠ ዳግም ጮኸ።
"እርግጠኛ ነህ?" ያየችውን እንዳላመነች ሁሉ የምትሰማውንም ለማመን ተቸረች።

ራሱን በአዎንታ ነቀነቀ።

"እንግዲያውስ እንደገመትኩት አንተ የኔውን ውድ ፍቅረኛ ጭራሽ ቻርሊን አይደለህም... የኔው ቻርሊ በኔ ላይ እንዲህ ጨከኖ ከውሻ ጋር አያመሳስለኝም..."

"አሁን ምን ልትፈልጊ መጣሽ?" ሰውነቱ እየተንቀጠቀጠ ከተቀመጠበት ተነስቶ አፈጠጠባት።



"ባለ ራስህ የህይወት ጉዳይ!"

በመገረም ይመለከታት ጀመር። መጸነሷን ልትነግረው ፈለገች። አምኖ እንደማይቀበላት ስታስብ ደግሞ ሰውነቷ በሀፍረት ተሸማቀቀ።

"በመተትሽ የምታፈኝበት፣ በምትሃትሽ የምታደነዝዢበት ሌላ ዘዴ እስከትፈልጊ... ውሻነትሽን የምትሸፍኝበት ሌላ ጭንብል እስከታጠልቂ... ይህችን የብቸኝነትና የድህንነት ጎጆየን ለቀሽ ውጭልኝ!" በሚንቀጠቀጥ ሌባ ጣቱ በሩን አመለከታት።

ካለችበት አልተንቀሳቀሰችም። ጥርሷቿን እንደነከሰች በቅሬታ ፈገግ ብላ በትዝብትና በንቀት ፀይን አስተዋለችው። በህይወቷ ውስጥ የተፈጸመውንና በመፈጸም ላይ ያለውን ምስቅልቅል ዛሬም እንኳ ልትነግረው አትችልም።

"ውጭልኝ እኮ ነው የምልሽ!" በሚንቀጠቀጥ ድምጽ በመጮህ የኋይት ሃውስን መሠረት አንቀጠቀጠው።

"ቻርሊ... አንድ እውነት እንኳን ልንገርህ..."

የጀመረችውን አላስጨረሰትም። በሚንቀጠቀጥ እጁ በጥፊ መታት። ወዲያው አንጎሏ በጭንቅላቷ ውስጥ ሲሽከረከር፣ የዐይኗ ብርሃን ሲጨልምና ተዝለፍልፋ ስትወድቅ የቅዠት ያህል ታወቃት። ከዚያ እንደ ጥጥ በለሰለሰ ጥቁር ዳመና መሰል ነገር ውስጥ ተጠቅልላ ጢሎሽ እንደምትጫወት፣ አንድ ጊዜ ሽቅብ ወደ ሰማየ ሰማያት የምትመጥቅ፣ ሌላ ጊዜ ቁልቁል ወደ ምድር ማህፀን የምትዘቅጥ መሰላት።

"ቻርሊ... እባክህ እርዳኝ?" ብላ ለመጮኽ ብታስብም ሃይሏ ደክሞ ተዝለፈለፈች። "ሞትኩ ማለት ነው?! ለካንስ ሞት ምንም አያምም፤ አያስጨንቅም፤ ልክ በዳመና ላይ ክንፎቹን እያራገበ እንደሚንሳፈፍ አሞራ መሆን ማለት ነው... አቤት ፀጥታው! አቤት እፎይታው!... ምን አለ እስከ ዘለዓለሙ ከዚህ እንደ ጥጥ በለሰለሰ ወፍራምና ጥቁር ዳመና እቅፍ ውስጥ ባልወጣሁ!..." መላውን አዕምሮዋን ሳተች።

ምን ያህል ሰዓት አፈሩ ወለል ላይ እንደተጋደመች አታውቅም። አዕምሮዋ ትንሽ መስራት ሲጀምር ልቧ ፍጥነቱን ሳያዛባ ከደረቷ ስር ድው ድው ድው ሲል ተሰማት። ጆሮዎቿ በርቀት የውሾች

ጨኸት ይዳምጣሉ። "እሃ ለካስ ገና ፊጽሜ አልሞትኩም?" ስትል አሰበች።

ከተጋደመችበት ሆና የሆነውን ሁሉ ለማስታወስ ስትሞክር ሁሉም ነገር እውነት አልመሰላት አላት። እንገቷን ቀና ማድረግ አልተቻላትም። ጭንቅላቷ የገዛ አካሏ እንዳልሆነ ሁሉ ጋን ያክል እስኪመስላት ድረስ አንገቷ ሊሸከመው አልቻለም።

ቁጭት እየንቀጠቀጣት፣ እልህ እያፈናት እንባዋ ያለማቋረጥ ከዐይኖቿ ጠርዝ እየፈለቀ ግራና ቀኝ ወደ ጆሮዎቿ ይፈስ ጀመር። እጆቿን ተመርኩዛ እንደምንም ቁጭ ለማለት ሞከረች። ብርድ ብርድ የሚል ስሜት ያንቀጠቅጣታል፤ መላ አካሏ በላብና በገዛ እንባዋ ተጠምቋል። የሊትል ቻርሊን ታማሬ አልጋ ደገፍ ብላ ዙሪያዋን ተመለከተች። ቻርሊ ክፍሉ ውስጥ የለም።

ብቸኝነቷ አጥንት ድረስ ዘልቆ እንደሚገባ ብርድ ተሰማት። እርቃኗን ጠላች። በጓይት ሃውስ የአፈር ወለል ላይ ማን እንደዘረራት ስታስብ ከትከት ብላ ሳቀች። "ለማን፣ ለምን ስል ነው በዚህ ምድር ላይ የምኖረው?" ስትል ራሷን ደጋግማ ጠየቀች። አንድ ድምጽ ለህሊናዋ ጥያቄ መልስ የሰጣት መሰላት። "ለማንም! ለምንም! ሁሉም ከንቱ! ከንቱ! ከንቱ! የከንቱ ከንቱ ነው።"



# ምዕራፍ ሃያ ሰባት

ጨለማው ክፍል ውስጥ ሲያጨስ የቆየውን ሲጋራ ወርውሮ በጥንቃቄ እየተራመደ የተከፈተውን መስኮት ገፋ አድርጎ ውጭውን ተመለከተ። ፀሐያማ ሰንበት ነው! ናፖሊዮን እምባው የቀኑን ፀሐያማነት አልወደደውም። እንደ መጥፎ እድል ቆጠረው። ታላቁን ጀብድ ሊሠራ በታጠቀበት በዛሬው ዕለት ቀኑ ጭጋጋማና ቀፋፊ ሆኖ ቢውል ይወድ ነበር። እንዲህ ዐይን የሚያጥበረብር ብሩህ ቀን?! ሳያስበው ጥርጣሬና ስጋት ገባው።

ፈጥኖ የከፈተውን መስኮት ዘጋና ፍጹም ጨለማ በሆነው ክፍል ውስጥ እጆቹን የኋሊት አጣምሮ ይንጎራደድ ጀመር። ምናልባት የሚጠላውን ብርሃን እስከ ዘለዓለሙ የሚሰናበትበት የዛሬው ብሩህ ሰንበት ይሆናል... ምናልባት በሚወደው ጨለማ እቅፍ ውስጥ እስከ ምጽአት በእፎይታ የሚያንቀላፋባት ሰዓት ተቃርባ ይሆናል። ብቻ ከዚህ በፊት ተሰምቶት የማያውቅ ስጋት ማጅራቱን ጨምድዶ ሆዱን አቀዛቀዘው። ልቡም በፍጥነት እየመታ አሸበረው። አትክልተኛ የመሆን የልጅነት ፍላጎቱ ታወሰውና ራሱን እየወዘወዘ በቅሬታ ፈገግ አለ። ከዚያም መብራቱን አብርቶ የታጠቀውን መትረየስ ሽጉጥ ከሽንጡ ሥር አወጣና ወደ አቧራማው ጠረጴዛ ተጠግቶ ሽጉጡን እየፈታታ በቅባት በመወልወል ያጸዳ ጀመር።

ዛሬ የከተማውን ህዝብ የሚያስደንቅ፣ የወንጀል ምርመራ ፖሊሶችን የሚያስጨንቅ፣ ገዳዩን የሚያከራ ታላቅ የግድያ ወንጀል ይፈጸማል! በቲያትር ቤቱ መድረክ ላይ የሃገሪቱ ታላቅ ተዋናይ በአድናቂዎቹ ፊት ይዘረራል።

እና እና በሚሸተው ክፍል ውስጥ ስልኩ ደጋግሞ ጮኸ። ናፖሊዮን አልተገረመም። የማን ጥሪ መሆኑን ያውቃል። በእጁ የያዘውን መሣሪያ አስቀመጠና የስልኩን እጀታ አነሳ። በገጽታው ላይ የስጋት ስሜት እንዳጠላበትና ግምባሩን እንደቋጠረ ቢያዳምጥ ቆየ። "... ዛሬ የመጨረሻው ቀን ነው ጌታዬ... ምሽት ላይ አስደናቂ ዜና ይሰማሉ... የሚኮሩበት... ለቃሌ ያልታመንኩበት ጊዜ የለም ጌታዬ፤ ጤና ይስጥልኝ"

የስልኩን እጀታ አስቀምጦ ሰዓቱን ተመለከተ። 7 ሰዓት ተኩል። ታላቁን ጀብድ ሊፈጽም ጥቂት ደቂቃዎች ቀርተዋል። ልቡ በድንገት ፍጥነቱን ጨምሮ መታ፤ መንፈሱን ጨነቀው። በግምባሩ ላይ ትኩስ ላብ ሸፍ ብሎ መነጨ።

የዛሬውን ቀን አልወደደውም። በተፋፋመ ጦርነት ወቅት በእሳት መሃል እየወደቀና እየተነሳ ሲዋጋ እንኳን ያልተሰማው የፍርሃት ስሜት ለምን እንደሚፈታተነው ራሱን እየጨነቀው መሣሪያውን ወዳስቀመጠበት ጠረጴዛ ተራምዶ በሸጉጡ ካርታ ውስጥ ጥይት መሙላት ጀመረ።

በዚያው ሰዓት ከናፖሊዮን አምባው ቤት ትይዩ ባለች የሸቀጣሸቀጥ መሸጫ ኪዩስክ በር ላይ የወንጀል ምርመራ ፖሊስ አባል የሆነ ወታደር የሲቪል ልብስ እንደለበሰ ሲጋራ እያጨሰ ትዕግስት አጥቶ ይቁነጠነጣል።

ከፊት ለፊቱ በሚታየው በቆርቆሮ ከታጠረ አጥር ግቢ ውስጥ የሚወጣ ወይ የሚገባ ሰው እንዳለ እንዲከታተል ከተመደበ ዛሬ ሶስተኛ ቀኑ ነው። በፈረቃ የሚቀየሩለት ሁለት የወንጀል ምርመራ አባላት የተመደቡለት ሲሆን፣ እዚህ ቦታ ላይ ቆመው እንዲሰልሉ በተመደቡባቸው ሶስት ቀናት ውስጥ ከግቢው የሚወጣም የሚገባም ሰው ስላላጋጠማቸው ተሰላችተዋል። በቤቱ ውስጥ ስለሚኖረው ሰው ማንነት ደግሞ ማንንም ምንም አይነት መረጃ እንዳይጠይቁ ጥብቅ ትእዛዝ ስለደረሳቸው የዚህን ሰሞን ሥራቸውን "ጋርድ" (ጥበቃ) ብለው ሰይመውታል።

የሲቪል ታርጋ የተለጠፈባትን ነጭ ቮክስዋገን መኪና በርቀት ሲመለከት የአለቃው የሻምበል መብራቱን ለቅኝት መምጣት አረጋገጠና ነቃ አለ። ተረኛው።

ሻምበሉ መኪናውን በርቀት አቁሞ የሲቪል ልብስ እንደለበሰ ጋዜጣውን ጨብጦ ወደ ኪዩስኳ ተጠጋና ለወንጀል ምርመራ ባልደረባው ፖሊስ ሰላምታ አቀረበለት።

"አዲስ ነገር የለም?"
"ኧረ በጭራሽ ጌታዬ..."
"እርግጠኛ ነህ?"
"ከተመደብኩበት ደቂቃ ጀምሮ ቅንድቤን ሳልሰብር ተመልክቼአለሁ። እንኳን የሰው የወፍ ዘር ዝር አላለም።"

ሻምበሉ በጥርጣሬ መጥበብ የጀመሩ ዐይኖቹን በወንጀል ምርመራው ፖሊስ ባልደረባ ላይ እንደተከተለ ማሰብ ቀጠለ። ያ በቆርቆሮ አጥር የተከበበ ቤት ከፊት ለፊቱ በቀር ሌላ መውጫና መግቢያ እንደሌለው አረጋግጧል። ሰው የሚኖርበት ቤት ከሆነ ታዲያ



እንዴት ለሦስት ቀናት በተከታታይ ሰው ከውስጥ አይወጣም ወይም ከውጭ ወደ ውስጥ አይገባም? ናፖሊዮን አምባው በዚያ ግቢ ውስጥ መሽጎ መሆን አለበት የሚል ጥርጣሬው እያየለ መጣ።

"ጌታዬ፣ ተቀያሪ ባልደረባዬ በስድስት ሰዓት ሊተካኝ ሲገባ እስካሁን አልደረሰልኝም..." ፖሊሱ በአጭር የተቆረጠ ፀጉሩን እየደባበሰ መጠየቅ የፈለገውን ሳይጠይቅ ምላሱ ላይ እንዳንጠለጠለ አስቀረው።

ሻምበሉ ከሰመጠበት የሃሳብ ባህር ወጥቶ ሰዓቱን ተመለከተና "ለምሳ መሄድ ከፈልክ ግማሽ ሰዓት እሰጥሃለሁ... አጣዳፊ ሥራ ላይ በመሆናችን ፈጥነህ ተመለስ" አለው ግምባሩን ቅጭም አድርጎ።

ፖሊሱ ሰዓቱን ተመልክቶ "እዚሁ አካባቢ ያገኘሁትን ቀማምሼ እመለሳለሁ ጌታዬ" አለ በአለቃው ግምባር መቋጠር እንደበረገገ።
"ፍጠን!"
ፖሊሱ ከአጠገቡ እየራቀ ሲሄድ ወደ ኪዩስኳ ጠጋ ብሎ ለስላሣ መጠጥ አስከፈተና እየጠጣ ዓይኖቹን ናፖሊዮን አምባው ቤት ላይ አነጣጠራቸው።

ተአምር ነው! በዚያ በቆርቆሮ በተከበበ ቤት ውስጥ በእርግጥ ሰው የለም? እንግዲያውማ ጠበቃው ምን ፍለጋ ወደዚያ ግቢ ገባ?! በዚያን ቀን ለግማሽ ሰዓት ያህል ቤቱ ውስጥ ቆይቷል። ከማን ጋር ነበር? ከዐይነ ሥውር እያቱ ጋር ወይስ ከናፖሊዮን አምባው ጋር? ይህ የሻምበል መብራቱ የመጨረሻው እድል ነው። ዛሬ እድል ከጎኑ ካልቆመች እስከ መቼውም የወንጀለኛውን ጭራ ለመያዝ እንደማይችል ገመተ። ለበቀል ጥፍራቸውን ስለው ያሰፈሰፉ ባለሥልጣኖች በወንጀለኛው ምትክ እርሱን እንደሚቀራመቱት አላጣውም። ቀን በቀን የሚወተውቱት አለቆቹ ከዚህ በላይ ትዕግስት ኖሯቸው የአንድ ሳምንት እድሜ እንኳን እንደማይሰጡት ያውቃል።

ዐይኑን ከቆርቆሮው አጥር ላይ ሳይነቅል ያለማቋረጥ ያስባል። እስከ መቼ ድረስ ቤቱን በአባሎቹ እንደሚያስጠብቅና ጊዜ እንደሚያባክን ራሱን ይጠይቃል። የአካባቢ መረጃዎችን በመሰብሰብ በቤቱ ውስጥ የሚኖረውን ሰው ማንነት ለማጣራት ያልፈለገበት ምክንያት ምናልባት በቤቱ ውስጥ የመሸገው ሰው ናፖሊዮን አምባው ከሆነ በፖሊሶች የክትትል ቀለበት ውስጥ መግባቱን እንዳይጠረጥርና በስንት ስቃይ የተደረሰበትን ጭራውን ዳግም ሾልኮ ፈለጉን እንዳያጠፋ በመስጋት ነበር። እንዳችም ፍንጭ ካልተገኘበት የሶስት ቀን ክትትል በኋላ ግን...

ያፈጠጡት የሻምበሉ ዐይኖች የሚመለከቱት ጉድ ምንድነው? ሦስት ቀን ሙሉ ወፍ እንኳን ዝር ያላለበት የቆርቆሮው በር ከውስጥ ተከፈተ።

ሻምበል መብራቴ ትንፋሹን ዋጥ፣ ግምባሩን ቋጥር አደረገና በቆመበት ተቁነጠነጠ። ወዲያው ጥቁር የቆዳ ጃኬትና ጥቁር የፀሐይ መነጽር ያደረገ ሰው ከውስጥ ወጣና ግራና ቀኝ ተገላምጦ ሻምበል መብራቴ ወደ ቆመበት ኪዩስክ አመራ።

የሻምበሉ ልብ ደም መርጨቷን ልታቆም ምንም አልቀራት። አንድ ወር ሙሉ በደረት ኪሱ ተሸክሞት ሲዞር የሰነበተው የናፖሊዮን አምባው ፎቶግራፍ ከፊት ለፊቱ የሚመለከተው ሰው መሆኑን ቅንጣት ታህል አልተጠራጠረም። መብራቴ የወንጀለኞችን ጠባይ አጣርቶ ያውቃል። አንዳንድ ጊዜ በወንጀል ጉዳይ ተይዘው የሚቀርቡ ወንጀለኞችን እንዲሁ ሁኔታቸውን በመመልከት ብቻ ወንጀለኛ ወይንም ንጹህ ሰዎች መሆናቸውን ይተነብያል። ይህ ትንቢቱ ደግሞ ብዙውን ጊዜ ከምርመራው በኋላ ከሚገኘው ውጤት ጋር ይገጣጠማል። እና ዛሬም ናፖሊዮን አምባውን ለአፍታ ያህል ተመልክቶ ወንጀለኝነቱን አረጋገጠ።

ናፖሊዮን ወደ ሸቀጣ ሸቀጥ መሸጫው መደብር ተጠግቶ አንድ ፓኬት ሲጋራ ገዛ። ፓኬቱን ቀዶ አንድ ፍሬ ሲጋራ በማውጣት ካቀጣጠለ በኋላም ሻምበሉን ከእግር እስከ ራሱ ተመለከተው። መብራቴ በእጁ የያዘውን ጋዜጣ በስፋት በመዘርጋት ፊቱን ሸፈነ። ናፖሊዮን አሁንም ግራና ቀኝ ተገላምጦ የአካባቢውን እንቅስቃሴ አንድ በአንድ ካጣራ በኋላ ወደ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት በሚያመራው የአስፋልት መንገድ ቁልቁል ወረደ። ሻምበሉ የታጠቀውን ኮልት ሽጉጥ በማውጣት መጠበቂያውን ካስለቀቀ በኋላ በግራ ሽንጡ ሥር ከቶ የለበሰውን ጃኬት በመሸፈን በርቀት ይከተለው ጀመር።

ወር ሙሉ ሲያድነው የቆየውን አንበሳ ከብዙ ድካም በኋላ በተአምር አግኝቶታል። ይህን አንበሳ ጉዳት ሳያደርስ ከነነፍሱ መያዝ ደግሞ ሌላው አስቸጋሪ ጉዳይ ነው። እንዲህ ያሉ ወንጀለኞች ሁል ጊዜም ታጥቀውና ዝግጁ ሆነው እንደሚንቀሳቀሱ ያውቃል። በተለይ እንደ ናፖሊዮን አምባው ያለ በአየር ወለድ ሠራዊት ውስጥ የሰለጠነና በብዙ የጦር ግንባሮች ላይ የዋለ ወንጀለኛ እጁ በቀላሉ እንደማይያዝ እርግጠኛ ነው።

ሻምበሉ የርምጃውን ፍጥነት በመጨመር በቅርብ ርቀት ተከተለው።ናፖሊዮን በድሉ ሆቴ ትይዩ ሲደርስ በየአቅጣጫው



ተገላምጦ አስፋልቱን ተሻገረና ወደ ቲያትር ቤቱ አመራ። አሳዳጅና ተሳዳጅ በሃያ ሜትር ልዩነት ተራርቀዋል።

መብራቴ የናፖሊዮንን እንቅስቃሴ አልወደደውም። በጣም ተጠራጣሪና ጠንቃቃ መሆኑን ገመተ። ምናልባትም በየ አሥሩ ርምጃው እየተገላመጠ አካባቢውን ይቆጣጠራል፣ በአጠገቡ ከሚተላለፉ መንገደኞች ሁሉ በተወሰነ ርቀት ይሸሻል ። በዚህ ሁኔታው መንፈሱ እንደተቅበዘበዘ ተረዳ። ምናልባት ለሌላ የወንጀል ድርጊት መሠማራቱ ቢሆንስ የሚል ጥያቄ በጭንቅላቱ ውስጥ ሲደውል ልቡ በፍጥነት መምታት ጀመረ።

ናፖሊዮን ወደ ቲያትር ቤቱ መግቢያ በር በመታጠፍ ወደዚያው ለመግባት ከሚተራመሱት ሰዎች መሃል ሲቀላቀል ድንጋጤው ወደ ገረሜታ ተለወጠ። በነፍስ ግድያ ላይ የተሠማሩ ወንጀለኞች አብዛኞቹ በማህበራዊ ህይወታቸው ብቸኝነት የሚሰማቸውና ከመሰሎቻቸው ጋር ብቻ የሚቀላቀሉ፣ በሥነ-ምግባር የረከሱ፣ ለህይወት ደንታ የሌላቸው፣ ምንም ዓይነት የሥነ ጥበብ ሥራ የማይማርካቸው መሆናቸውን ያውቃል። ይኸኛው ግን ...

በዚያ ትርምስ ውስጥ ናፖሊዮን ከዐይኑ እንዳይሰወር ስለሰጋ ጭራውን እየተከተለ በጣም ተጠጋው ። እየቀረበው በሄደ ቁጥር ደግሞ አደጋ ይሸተው ጀመር። የአካሉን ግዙፍነት፣ የሰውነቱን ቅልጥፍና፣ የፈጣን ዐይኖቹን እንቅስቃሴ ሲመለከት የዚህን ሰው እጅ ለመያዝ ብልሀትና የሰው ሃይል እንደሚያስፈልግ ተገነዘበ። በአጋጣሚ ብቻውን ነው። ምን ማድረግ እንደሚገባው ሲያሰላስል ናፖሊዮን ወደ ቲያትር ቤቱ የመግቢያ በር እየተጠጋ ሄደ።

ሻምበሉም በቅርብ ርቀት እየተከተለው ወደ በሩ ተቃረበ። በመካከላቸው ምናልባት አሥር ሰዎች ቢኖሩ ነው። ናፖሊዮን ወደ ቲያትር ቤቱ የሚያስገባውን የግብዣ ካርድ አሳይቶና ተፈትሾ በስተግራ በኩል በመታጠፍ ወደ አዳራሹ በር እየተጣደፈ አለፈ። መብራቴ ወንጀለኛው ከዐይኑ እንዳይሰወር ስለሰጋ ከፊት ለፊቱ ያለውን ሰልፍ ጥሶ ፈታሾቹንም አልፎ በፍጥነት በመራመድ ተከተለው።

"ወዴት ነው ጌታዬ? ይቁሙ!"

ሻምበሉ ድምጹን ወደ ሰማበት አቅጣጫ ገልመጥ አለ። የቲያትር ቤቱን ስማያዊ የደንብ ልብስ የለበሰ አጭር የጥበቃ ጓድ እየሮጠ ተከትሎታል።

"ነውርም አይደል እንዴ?... ትልቅ ሰው አይደሉም እንዴ ጌታው? ወፍ ልንጠብቅ ከበሩ ላይ የቆምን ይመስልዎታል?፣ ይበሉ

የመግቢያ ካርድዎን ያሳዩኝ!" ከላይ እስከ ታች በግልምጫ እየሸነቆጠ አፈጠጠበት።

ዘቦቹን አልፎ የገባበትን ምክንያት ለመግለጽ ጊዜ የለውም። ናፖሊዮን ወደ አዳራሹ እየገሰገሰ ነው። የወንጀል ምርመራ ፖሊስ ልዩ መታወቂያውን አወጣና ለአጭሩ ዘብ በመስጠት ወንጀለኛ በመከታተል ላይ መሆኑን እየተጣደፈ ገለጸለት።

ዘቡ ለሻምበሉ ጥድፊያ ግድ አልሰጠውም። በእጁ የያዘውን መታወቂያ በጥንቃቄ እያነበበ በመታወቂያው ላይ የተለጠፈውን ፎቶግራፍ ከፊት ለፊቱ ከቆመው ሰው ጋር ደጋግሞ ካስተያየ በኋላ መታወቂያውን ከመመለሱ በፊት "መሣሪያ ይዘዋል?" ሲል ጠየቀው።

"ይገርለሁ... አሁን ይህን ሁሉ ለመነጋገር ጊዜ የለንም... ወንጀለኛው"

ዘቡ የጀመረውን አላስጨረሰውም "የመሣሪያ ቁጥርና መሣሪያውን ይዞ ወደ አዳራሹ የገባው ሰው ማንነት መመዝገብ አለበት ጌታዬ... ይህ የመሥሪያ ቤቱ ደንብና የተሰጠን ትዕዛዝ ነው!"

ሻምበሉ ትዕግስቱን ጨረሰ። የሚከታተለው ወንጀለኛ ከዘቡ ጋር ባጠፋቸው ደቂቃዎች ውስጥ የት ሊደርስ እንደሚችል ሲገምት ብስጭት አለና "ለሚፈጠረው ችግር ሁሉ ሃላፊነቱን እወስዳለሁ... ስትፈልግ መታወቂያውን ያዝ!" አለና በቆመበት ጥሎት ወደ አዳራሹ ገሰገሰ። እስከ ተወሰነ ርቀት ድረስ ከኋላው "ይቁሙ ጌታዬ!" የሚል ድምጽ ተከትሎት ነበር።

አዳራሹ በር ላይ ቆም ብሎ ዐይኑ ሊያየው በሚችለው ርቀት ሁሉ በየአቅጣጫው አማተረ። ናፖሊዮን አምባውን ሊያየው አልቻለም። በአዳራሹ ውስጥ በየማእዘኑ ላይ ከተተከሉት መብራቶች የሚረጨው ብርሃን አዳራሹን አድምቆታል። ይህ ደማቅ ብርሃን ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ እንደሚጠፋ ያውቃል። ናፖሊዮን አምባውንም መቼም መች ቢሆን አያገኘውም። በቀሩት ጥቂት ደቂቃዎች ለመጠቀም ቦታ እንደሚፈልግ ሰው ሆኖ በአዳራሹ ውስጥ እየተዘዋወረ በያንዳንዱ ረድፍ የተቀመጡትን ሁሉ በዐይኑ ይቃኝ ጀመር። ግዙፋና ባለመነጽሩ ናፖሊዮን አምባው በዚያ የለም። መሬት ተቀዳ ዋጠችው ወይስ ጣራ ሰንጥቆ አመለጠ? ያ የቢራ ጠርሙስ የሚያክል ዘብ ጉድ ሠራው! ከንፈሩን በቁጭት እንደነከሰ ከአዳራሹ በስተቀኝ ከተተከሉት ምሰሶዎች አንዱን ደገፍ ብሎ ዐይኖቹ ሊያዩ በቻሉት ፍጥነት ናፖሊዮንን መፈለግ ቀጠለ።



ናፖሊዮን አምባው የመግቢያ ካርዱን አሳይቶና ተፈትሾ ካለፈ በኋላ በቀጥታ ወደ አዳራሹ አልገባም ነበር። ወደ አዳራሹ በሚያሳልፈው ኮሪደር በስተግራ ከተሠሩት መጸዳጃ ክፍሎች ውስጥ አንዱን ከፍቶ በመግባት ቆለፈው። በተጫማው የቆዳ ቡት ውስጥ የደበቀውን መትረየስ ሽጉጥ አውጥቶ ካቀባበለ በኋላ በጃኬቱ የደረት ኪስ ውስጥ በመክተት ሲጋራውን አቀጣጠለ። ትርኢቱ እስኪጀመርና መብራት እስኪጠፋ ድረስ በብርሃን ወደ ደመቀው አዳራሽ አይሄድም።

መሣሪያ ታጥቆ ወደ ቲያትር ቤቱ አዳራሽ መግባት ቀላል ሥራ አልነበረም። መሣሪያ መደበቅ ለሚችለው ረዥም ቡት ጫማውና መሣሪያ የሚቀመጠው ሽጉጥ ሥር ብቻ ለሚመስላቸው ስልቹ ዘቦች ምስጋና ይግባቸው እንጂ የመጀመሪያውን መሰናክል ያለ አንዳች ችግር ዘሎታል። ሁለተኛውን ደግሞ በሚቀጥሉት ጥቂት ደቂቃዎች ውስጥ ቻርሊን በምትነድለው አንዲት ጥይት በሺ በሚቆጠሩ ታዛቢዎች ዐይን ፊት በመድረኩ ላይ በመዘረር ይወጣዋል።

***   ***   ***

እሁድ ተሰዓት ቻርሊ ድሮ የገዛትን በፀሐይ ተቀጥቅጣ የነጣች ጥቁር ሱፍ ኮትና ሱሪ ለብሶ ፀጉሩን በወጉ አበጥሮ ታክሲ ተሳፍሮ ወደ ቲያትር ቤቱ ሄደ።

የቲያትሩን ፖስተር በርቀት ሲመለከተው የገዛ ስሙ አሁንም በጉልህ እንደተጻፈ ነው። ወደ መግቢያው በር ሲቃረብ ወደ አዳራሹ ለመግባት ህዝቡ ይተናነቃል... አንዱ በአንዱ ላይ እየቆመ ይተራመሳል። አስተናባሪዎቹ በግ የሚያግዱ ይመስል ረጃጅም አለንጋ ይዘው ይጋረፋሉ። ተመልካቹ ግን ግርፊያው አያመውᎂ ግፊያው አይጥለውም። ካርዱን አሳይቶ ለማለፍ ይጋደላል።

ቻርሊ ራቅ ብሎ ቆመና ጫማ ጠራጊ ጠርቶ ጥቁሯን ጫማውን እያስወለወለ የአዳራሹን ውጭ ትርኢት በትዝብት ማስተዋል ጀመረ። "እኮ ምን ለማየት? ምን ለማግኘት ነው ይሄ ሁሉ ትርምስ?" እያለ ራሱን ይጠይቃል። ጫማ ጠራጊው ያበደ ሰው ጫማ እየጠረገ መሆኑን በመገመት ቀና ብሎ ደጋግሞ ያየዋል። ቻርሊ ብቻውን ይለፈልፋል። "ፈዞዞች! ጥበብ ስትሞት መሳቅᎂ የአርቲስት እድሜ ስትባክን መሳቅᎂ የገዛ ብራቸው ሲቃጠል መሳቅ። መጥኔ ለእናንተ ሣራ... እኔማ በመጨረሻው ነቃሁ። ከእንግዲህ እንኳን እኔ አሥረኛው ትውልዴም አርቲስት አይሆንም!"

ቢ.የስተውል የሰው ግፊያ ማብቂያ የለውም፡፡ ቀለል አለ ቢል ሌላ መንጋ ደግሞ ይተራመሳል፡፡ ይለፍላቸው አለና እዚያው አካባቢ ካለቡና ቤት ሻይ ለመጠጣት ጎራ አለ፡፡

ሲጋራውን ለኩሶ ከቡና ቤቱ ሲወጣ የቲያትር ቤቱ የመግቢያ በር ጭር ብሏል፡፡ በዝግታ እርምጃ ወደቲያትር ቤቱ ሲደርስ አስተናባሪዎቹ ሁሉ ከበቡት "ጋሽ ቻርሊ! እውነት አንተ ነህ? ጋሽ ቻርሊ! ደህና መጣህ ጋሽ ቻርሊ! ጋሽ ቻርሊ!" ቻርሊ ግራ ገባው፡፡ ሰው ሁሉ እየመጣ ሲጠመጠምበት ለመጀመሪያ ጊዜ በሙያ ጓደኞቹና ሰው ዘንድ ተወዳጅነት ያለው መሆኑን ተረዳ፡፡ ሁለት አስተናባሪዎች ከፊት ለፊቱ ባትሪ እያበሩ ቀደሙና ፊት ካለ ወንበር ላይ አስቀመጡት፡፡ ተውኔቱ ከተጀመረ ጥቂት ደቂቃዎች አልፈዋል፡፡

"ሰላም ቻርሊ!" አለው አጠገቡ የተቀመጠ አንድ ሰው፡፡ ቻርሊ ከማጀራቱ ጀምሮ የሆነ ነገር ጭምድድ አድርጎ መላ ሰውነቱን ሸመቀቀው፡፡ ወደ ድምጹ ዞር ብሎ ማንነቱን አላባራም፡፡ ለሰላምታውም መልስ አልሰጠም፡፡ እንዳቀረቀረ ቀረ፡፡ ያንን ድምጽ በውል ያውቀዋል - ዳንኤል ጀምር!

"...አልሞትኩም እኮ! ገና ነኝ! ትንፋሼን ጨርሼ አልሞትኩም!... ወድቋል ብለው ደስ እንዳይላቸው ... ትንፋሼን ላስደምጣቸው!... ይሄው የተሰፋን ዐዳል ከገጼ ላይ ላሳያቸው!... ይሄው!"

ጭብጨባው ከዳር እስከ ዳር አስተጋባ፡፡ የአድናቆት ድባብ አዳራሹን አጥለቀለቀው፡፡ ቻርሊ ድንገት ቀና ብሎ በመድረኩ ላይ አፈጠጠ፡፡ እናም የገዛ ዐይኖቹን ካዳቸው!

የገዛ ሰውነቱን እየዳበሰ በርግጥ እርሱ ራሱ ቻርሊ መድረክ ላይ ያልቆመና በአዳራሹ ውስጥ ከዳንኤል ጀምር ጎን መቀመጡን አረጋገጠ፡፡ ታዲያ መድረኩ ላይ የሚያየው አርቲስት ማነው?! የራሱን መንፈስ!? ዐይኖቹ እንዳፈጠጡ፣ ከንፈሮቹ እንደተንቀጠቀጡ ሌላ ጭብጨባ ሌላ አድናቆት አዳራሹን ሞላው ፡፡ ሲትል ቻርሊ መላውን መድረክ ይዞታል!

ቻርሊ ከተቀመጠበት ፍንጥር ብሎ ተነሳና "ሲትል!" ሲል ጮኸ፡፡ ወደ መድረኩ ለመሮጥ መንቀሳቀስ ከመጀመሩ በፊት ግን ዳንኤል ጀምር በፍጥነት ተነሳና ክንዱን ጨምድዶ መቀመጫው ላይ መለሰው፡፡



ጎን ለጎን እንደተቀመጡ ከመድረኩ በሚፈነጠቀው ብርሃን ፀይን ለዐይን ተፋጠጡ፡፡ የዳንኤል ጀምር ገጽ በድል አድራጊነት ፈክቷል፡፡ የቻርሊ ገጽታ ተስፋ ጨልሞበትና ግራ ገብቶት እንደከሰል ጠቁሯል፡፡ ዳንኤል ወደ ቻርሊ ጆሮ ጠጋ አለና "ቻርሊ! እኛ እንጂ ጥበብ አትሞትም፤ እኛ እንጂ ውበት አትሞትም፤ እኛ እንጂ ምንጊዜም ፍቅር አትሞትም!" አለው፡፡

ቻርሊ ክንዱን ከዳንኤል እጅ መንጭቆ አላቀቀና መላ ሰውነቱ እየተንቀጠቀጠ ተነሳ፡፡ ዞር ብሎ ዳንኤልን አላስተዋለውም፡፡ ወደ መድረኩም አልተመለከተም፡፡ አዳራሹን አቋርጦ ወደ መውጫው በር ሲያመራ የጫማው ሶል ከሲሚንቶው ወለል ጋር እየተጋጨ፣ ቋ... ቋ... ቋ... ቋ... ቋ... እያለ መድረክ ላይ ከቆመው አርቲስት ድምጽ እኩል አስተጋባ፡፡ ተመልካቹ ድብዝዝ ባለው ብርሃን ዞር እያለ በዐይኑ ይከተለዋል፡፡ መውጫው በር ላይ ሲደርስ ሆዱ አልቆርጥልህ ብሎት ዞር አለና ባሻገር ወደ መድረኩ ተመለከተ፡፡ ሲትል ቻርሊ ቃለ ተውኔቱን ያስገባል፡፡ የህዝብ ሳቅ አዳራሹን ከዳር እስከ ዳር ሲያንቃንቀው ከቻርሊ ዐይኖች የእንባ ዘለላዎች ረገፉ፡፡ እንባውን በእጁ መዳፍ ሲጠርግ ላመል ያህል ከንፈሮቹ ተንቀሳቀሱ፡፡ "መልካም እድል ሲትል!"

## ምዕራፍ ሃያ ስምንት

በዚያች ብራማ ሰንበት ተሰዓት በኋላ አብነት መንገሻ የክት ልብሷን ለብሳ በእጅጌ ጉርድ ወይን ጠጅ ቀሚስ ላይ ስስ ውሃ ሰማያዊ ሹራብ ጣል አድርጋለች። ፀጉሯ በወጉ ተበጥሮ በወርቅ ጌጠኛ አምራለች። መኝታ ክፍሏ ውስጥ ባለው የቁም ሳጥን መስተዋት ውስጥ ራሷን ለመጨረሻ ጊዜ ተመለከተች። በህይወቷ ለመጀመሪያ ጊዜ የገዛ ውበቷ እስኪደንቃት ድረስ እንደፈዘዘች ቀረች።

የገረጣው የፊቷ ቆዳ ወዝቷል፤ ዐይኖቿ ከውሃ ጠርተው ፀዳላቸውን ይረጫሉ፤ ረጅሙ ዞማ ፀጉሯ ከመቼውም ጊዜ ይልቅ ከጽልመት ጠቁሮ በትከሻዋ ላይ ቁልቁል ወርዷል። እንዲህ እንደዛሬው በአካሏ ውብ፤ በመንፈሷ ንቁ የነበረችው መቼ ነበር? በጣም ረዥም ጊዜ መስሎ ታያት። ቻርሊ በህይወቷ ውስጥ ከመግባቱ፤ እርሷም በእርሱ ህይወት ውስጥ ጣልቃ ከመግባቷ በፊት። ምን ያህል ጊዜ ሆነው?

በመስተዋቱ ውስጥ ከምታየው ከራሷ ምስል ጋር የመጨረሻውን ስንብት አድርጋ ከአልጋዋ ትይዩ ባለው ወንበር ላይ ተቀመጠች። ከፊት ለፊቷ ባለው አነስተኛ ጠረጴዛ ላይ የእንቅልፍ ኪኒኖች የያዘ ብልቃጥ ውሃ ከሞላ ጠርሙስ ጋር ተቀምጧል። ከብልቃጡ ውስጥ ሁለቱን እንክብሎች አውጥታ በውሃ አወራርዳ ዋጠቻቸው። ከዓለም ጋር የምታደርገውን ስንብት መጀመሯ ነው!

ዐይኖቿን ቡዝዝ አድርጋ ወደ እፎይታው ዓለም በሚወስዳት ብልቃጥ ላይ እንደተከለች ማሰቧን ቀጠለች። ቻርሊን ከማግኘቷ በፊት የኖረቻቸው ዓመታት ደብዛዛና በውል የማታስታውሳቸው ዓመታት ናቸው። መብላት፣ መጠጣት፣ መተኛት፣ መሥራት... አሰልቺ የህይወት ኡደት። ቻርሊን ካገኘች በኋላ የኖረችው አጭር ህይወት ግን ልክ እንደ ማራኪ የልብ-ወለድ ድርሰት በድርጊት የተሞላ፤ እያንዳንዱ ቀን የራሱን ትዝታ ጥሎ የሚያልፍ፤ የደስታ፣ የፍቅር፣ የጭንቀት፤ የእንባና የመከራ ወራት ነበሩ።

ከውጭ የመኪና ጥሩምባ ሰማች። ፈጥናም የትልቁ አጥር የብረት በር ሲከፈት አዳመጠች። ወለል አድርጋ በከፈተችው የመኝታ ቤቷ መስኮት አሻግራ ስትመለከት የጠበቃው ሲትሮይን ቀድማ ሌላ ነጭ አፔል ደግሞ ተከትላ ወደ ግቢው ተከታትለው ገቡ።

ጠበቃው ነጭ ሱፍ በጥቁር ከረቫት ለብሷል። ሌሎች ሦስት ሰዎች ደግሞ ከአፔሏ ውስጥ ወጡ። ከአንድ እናት የተወለዱ ያህል



ሶስቱም አጫጭር፤ ወፍራሞች፤ ቀያዮችና ሸበቶዎች ናቸው። ሁሉም እየተሳሳቁና እየተነጋገሩ ወደ መኖሪያ ቤቱ ዘለቁ። ጠበቃው ጥቁር ቦርሳ አንጠልጥሏል። "የአብነት አስመጭና ላኪ ድርጅት ለጠበቃው በስጦታ የሚተላለፍበት ቀን ነው። ሦስቱ ሰዎች መንገሻ የኔነህ የስጦታውን ሰነድ ሲፈርሙ እማኝ ሆነው በሰነዱ ላይ የሚፈርሙ መሆናቸውን ተረዳች። እንግዶቹን ለመቀበል ስትወጣም አባቷን በረንዳው ላይ ቆመው አየቻቸው። ሙሉ ጥቁር ሱፍ ለብሰዋል። ያልተላጨው ሪዛቸው ጠይም ገጻቸውን አጥቁሮት፤ ዐይኖቻቸው በገረጣው ፊታቸው ላይ ተንጠልጥለዋል። በመንፈስ ወድቀው፤ በአካል ደቀው፤ ተገንዞ የቆመ ሬሳ መስለው ታዩዋት። ከትቢያ ወደ ትቢያ! ከረዥም ዓመታት መራራ የህይወት ትግል በኋላ የመጨረሻዋን መራራ የህይወት ጽዋ የሚጎነጩባት ዕለት ነች - ዐይኖቻቸውን ጭፍን ግንባራቸውን ቅጭም አድርገው።

እነኛ ላባቸውን ያንጠፈጠፉባቸው ዓመታት ፍሬ፣ ያ በደም የተጨማለቁበት ሃብት ፍጻሜ ጥቂት ደቂቃዎች ብቻ ቀርተውታል። በረንዳው ላይ ከአብነት ጋር ለአፍታ ተያዩ። ሁለቱም ፍፃሜያቸው የደረሰ መሆኑን አውቀውታል። መንገሻ የኔነህ መደንዘዝ ዐጀመረ ህሊናቸው የአብነትን አለባበስና ውበት ልብ አሉ። በእርሳቸው ህልውና ግብአተ መሬት መፈጸሚያ ዕለት የእርሷ እንዲህ ሙሽራ መምሰል ምንድነው?! "ያን ያህል ትጠላኝ ነበር?" ሲሉ ለራሳቸው አዘኑ።

በጠበቃው መሪነት የበረንዳውን ደረጃ የሚወጡት እማኞች በሩ ላይ ከአባቷና ከአብነት ጋር ሰላምታ ተለዋወጡ። ሁሉም ደስተኞችና ፈገግታቸው ከገጻቸው ላይ የሚታፈስ ነው። በተለይ ጠበቃው። ህይወት ለምን ለጨካኞችና ለከፋዎች እንደምታደላ ገረማት።

መንገሻ እንግዶቹን እየመሩ ወደ እንግዳ ማረፊያው ሳሎን ይዘዋቸው ዘለቁ። በሳሎኑ በር ላይ ጠበቃው ወደ ኋላ ቀረት ብሎ የአብነትን ክንድ ጨበጠና "ደህና ሰነበትሽ ጽጌረዳዋ..." አላት። አለባበሷን ከላይ እስከ ታች እየቃኘ። ፈገግ አለችለት። ያንተ ያለህ! ዛሬ ደግሞ ከመቼውም ጊዜ ይልቅ ውበቷ በአሥር ጨምሯል። "ደህና ነኝ..." በትንሹ ተከፍተው የተንቀሳቀሱት ከንፈሮቿ በመፈልቀቅ ላይ ያለ እንቡጥ የጽጌረዳ አበባ መስሎ ታየው። ያ አርቲስት በዚህ ውበት ነው የተጫወተው? ከእንግዲህ ግን ይህ ትንግርት የሆነ ውበት የርሱ ብቻ የሆነ የግል ሃብቱ ነው።

"አዝነሽብኛል አቢ?"

"ለምን?" ትከሻውን ከፍ አድርጎ "ምንአልባት ለአባትሽ አድልተሽ ይሆናል..."

"ስለምትለው ሁሉ የማውቀው ነገር የለኝም..."

"ዛሬ የሁለታችንም የጋራ የድል ቀን ነው አቢ..."

"አመሰግናለሁ" ብላ ፈገግታዋን አሳየችውና ገፋ አድርጋው ወደ ሳሎኑ ገባች። ተከተላት።

እንግዶቹ ሶፋው ላይ ቦታ ቦታቸውን ይዘዋል። መንገሻ የኔነህ ትልቁ ሶፋ ጥግ እግራቸውን አጣምረው ኩርምት ብለው ተቀምጠዋል። ከመላ አካላቸው የሚንቀሳቀሱት ዐይኖቻቸው ብቻ ናቸው።

አብነት ወደ እንግዶቹ ተጠግታ "ምን ትወስዳላችሁ?" ስትል በፈገግታ ጠየቀች። የሁሉም ዐይኖች ከላይ እስከታች እየደባበሷት ምርጫቸው ውስኪ መሆኑን አሳወቋት። ብራማ ቀለም ባለው ትሪ ላይ የውስኪ ብርጭቆዎችን ደርድራ ስትመለስ በክፍሉ ውስጥ ውጥረት ሰፍኗል። አንዳቸውም አንዲት ቃል አይተነፍሱም። የግድግዳው ሰዓት ብቻ ቲክ - ቲክ - ቲክ - ቲክ እያለ በፀጥታው ውስጥ ያስተጋባል። ቀና ብላ አየችው 9:30! ውስኪውን ቀድታ በእያንዳንዳቸው ፊት ካኖረች በኋላ "ተጫወቱ" አለችና ክፍሉን ለቃ ወደ መኝታ ቤቷ አመራች። የጠበቃውና የእንግዶቹ ዐይን በጋራ ሸኟት።

ወደ ተከፈተው የመኝታ ቤቷ መስኮት ተጠግታ ውጭውን ማየት ጀመረች። የግቢው ልምላሜ፣ የአበቦቹ ውበት፣ ቀዝቀዝ ብሎ ሽው የሚለው የልምላሜውን መአዛ የተሸከመ ነፋስ... ተፈጥሮ እንዴት ውብ ነች?! ህይወትም ምነው እንደዚህ የማትሰለች በሆነች? ለእርሷ እንጂ ለሌሎች አሁንም የማትጠገብ ማር መሆኗን አሰበች። ለእርሷ ህይወትም የአንዲት ዓለም ሰዎች በነፍስና በሥጋ የሚሰቃዩባት ሲኦል፤ ሰዎችም ከሀዲዎችና ጨካኞች ለከንድ እፎይታ የማይገኝባት ሩጫ፤ የምትለው አንድ ናቸው። ከእንግዲህ በዚህ ምድር ላይ ለመኖር ቀረኝ ብልቃጥ ሁለት እንክብሎች አውጥታ ዋጠች። ሁሉም ከንቱ! ከንቱ! ከንቱ!...

"አቢ... ወደ ህይወትና ወደ ሞት በሚያመራ መንታ መንገድ ላይ እንደቆምሽ ይሰማኛል..." ... በኛ ህይወት ነገ የሚባል ብሩሕ ቀን የለም፤ እስከዘለዓለሙ በማይነጋ ጨለማ ውስጥ እየሮጥን እስከ ወዲያኛው እናሸልባለን..." ሠዓሊው ታወሳት።

ሰዓሊው ነብይ ነበር?! ለአብነትም ነገ በስጦታ ወረቀት የተጠቀለለ የብሩሕ ቀን ገጸ በረከት ይዞላት እንደማይመጣ አውቃለች። እያንዳንዱ ነገ ይዞላት የሚመጣው ነገር ቢኖር ጥቁር ጨለማ፤ የካንሰር ያህል የማይሽር የመንፈስ ስቃይ፤ ስጋና ነፍሷን የሚሸሙ የሰው



ጭራቆችን ብቻ ነው። ህይወት የሚባል ቋንቋ ትርጉሙ ሲቃይ ማለት ነው ስትል ደምድማለች። ራሳቸውን በሚያጠፉ ሰዎች ለምን ስትፈርድ እንደኖረችም ምክንያቱ አልገባ አላት።

በሆዷ ውስጥ የሚወራጭ ነገር የተሰማት መሰላት። ያልታደለው የቻርሊ ልጅ! ምናልባት በማህጸን መድረክ ላይ አንድ ድንቅ ተውኔት እየተጫወተ ይሆናል - ማን ያውቃል?!

ተፈጥሮ እንደምን ያለች ጨካኝ ነች?! አንዱ በህይወት ነዲድ ተቃጥሎ፤ በኑሮ ክንድ ተደቁሶ፤ ደክሞና ተሰላችቶ ፍጻሜውን በገዛ እጁ ሲያቀርብ፤ ሌላውን መራራ ጽዋ ተቀድቶ ወደማያልቀው ዓለም ዐይኑን ጨፍና እየነዳች ታመጣዋለች። እሱቱ በማይበርድ ምድራዊ ሲኦል ልትጠብሰው፤ በፈርጣማ የኑሮ ክንድ ልትደቁሰው... ተፈጥሮም እንደ ፍጡሯ ጨካኝ ነች?! ግን ለምን?

"...ቻርሊ ... እስከ መቃብር ከአንተው ጋር ነኝ ...ብቻህ የቆምክበት ምድር ትከዳኛ..." የገዛ ቃሏ በህሊናዋ ውስጥ ሲያስተጋባ ተሰማት

ውጭ ብሎ ለጠራት ሰው ለገባችው ቃል ያለመጠራጠር ቆማለች። ለአንደኛና ለመጨረሻው ፍቅሯ በታማኝነት ፀንታለች። ጥርጣሬ የህሊና ህመም፤ ከዳተኝነት የመንፈስ ሞት ነው! በህሊናዋ ቆሰላ፤ በመንፈሷ ሞታ፤ የሚተነፍስ ሬሣ ሆና ከመኖር ከቃሏ ጋር፤ ልቧ ውስጥ ካበበው ፍቅር ጋር ትሞታለች።

ሰውነቷ ሲደነዝዝ ታወቃት። ህሊናዋን ለማንቃት ራሷን ደጋግማ ወዘወዘችና ወደ እንግዳ መቀበያው ሳሎን አመራች። ጠበቃው የሰጠታውን ሰነድ በእርጋታ ያነብላቸዋል። የሁሉም ዐይኖች ቀና ቀና እያሉ አዩዋት። የሁሉም ብርጭቆዎች ባዶ ናቸው።የውስኪውን ጠርሙስ አንስታ ለሁሉም ሞላችላቸው። ጠበቃው በሞቀ ፈገግታው ከድሉ ጫፍ ላይ መድረሱን አበሰራት። መንገሻም ጭብጥ ብለው ከተቀመጡበት አቅጣጫ የሚንቀሳቀሱ የሬሳ ዐይኖች የመሰሉትን ዐይኖቻቸውን እያቁለጨለጩ ይመለከቷታል። አፍ አውጥተው አይናገሩ እንጂ ነፍሳቸው "እርጂኝ!" እያለች እንደምትማፀን አለጣችውም።

ፈገግታዋ በገጿ ላይ እንደደመቀ ክፍሉን ለቃ ወጣች። የሁሉም ዐይኖች ዳግም ሸኟት። መኝታ ክፍሏ ስትደርስ እንደገና ሁለት የእንቅልፍ እንክብሎች አንስታ ዋጠች። አዲሱ ሊትል ቻርሊ በሆዷ

ውበቱ የሚዘል መሰላት - ተውኔቱ ማለቁ ይሆን? መተጣጠፊያወቿ መዛል ጀምረዋል፤ አዕምሮዋም እየፈዘዘ ነው።

*** *** ***

መጀመሪያው ክፍል ተውኔት ተጠናቆ ለአጭር ጊዜ እረፍት መጋረጃው ተጥሏል። ከመድረኩ ጀርባ ጥግ ላይ ሊትል ቻርሊ የታጠቀውን ጉራዴ እጀታ እንደጨበጠ ብቻውን ተክዞ ቆሟል። በግምባሩ ላይ የሚንጠፈጠፈውን ላብ ያለማቋረጥ በመሀረብ እየጠረገ በላይ በላዩ ይተነፍሳል።

ገና የጥቂት ደቂቃዎች እፎይታ ማግኘቱ ነው። የተውኔቱ የመጀመሪያ ክፍል ተጠናቆ መጋረጃው በተጣለበት ቅጽበት ሣራ ጋዴም ስትንደረደር ሄዳ አንገቱ ላይ ተጠመጠመችበት። ማንም ባልጠበቀው ችሎታ ያለ አንዳች እንከን የመጀመሪያውን ክፍል ግዳጁን ትንግርት በሚሰኝ ቅልጥፍና በመወጣቱ ያልተደነቀ ተዋናይ አልነበረም። ብዙዎቹ አንገቱ ላይ ተጠምጥመው ስመውታል፤ ከንዱ የተኳጠለ እስኪመስለው ድረስ እጁን እየወዘወዙ ጨብጠውታል፤ የዱላ ያህል ትከሻውን እየጠበጠቡ አድናቆታቸውን ገልጸውለታል።

አንገቱን አቅፈው አገላብጠው ከሳሙት አንዱ ዳንኤል ጆምር ነበር። ገና መጋረጃው ተከፍቶ ተውኔቱ ከቀጠለበት ጊዜ ጀምሮ የሊትል ቻርሊን የመድረክ እንግድነት ከግምት ውስጥ በማስገባት ተውኔቱ ሊበላሽ ይችላል በሚል ስጋት ነፍሱ በጭንቀት ተወጥራ ነበር። ከአምስት ቀን የቀንና የሌሊት እልህ አስጨራሽ የመድረክ ልምምድ በኋላ በሊትል ቻርሊ የቃለ ተውኔት ጥናትና የመድረክ እንቅስቃሴ ብቃት አመነ። በአንድ ጉዳይ ግን ሊትል ቻርሊን ሊያምነው አልቻለም። በትልልቅ ቲያትር ቤት መድረኮች ላይ በሺህ በሚቆጠሩ የተውኔት ታዳሚዎች ፊት ተጫውቶ የማያውቅ በመሆኑ የመድረክ እንግድነቱን ፈራው። ስስት ወር ሙሉ የደከመበት ሥራ እንዳይበላሽ የተውኔቱን መክፈቻ ቀን ለማራዘም አስቦ ነበር። ያጀገነችው ሣራ ጋዴም ነች። ውድቀቱን ወይ ትንሣኤውን ለመቀበል ዐይኑን ጨፍኖ ልመናዋን ተቀበላት።

እና ዛሬ የሊትል ቻርሊን የመድረክ እንቅስቃሴ ሲመለከት፣ የተውኔት ጥበብ በመድረኳ ላይ በሺ ታዳሚዎቿ ፊት አንድ ታላቅ ልጇን አምጣ እንደወለደች አመነ! እውነተኛው የአባቱ ልጅ በአባቱ እግር ሥር በቅሏል። የሊትልን አንገት አቅፎ እያገላበጠ ከሳመው በኋላ "...ዐይኖቼን ማመን እስኪያቅተኝ ድረስ ተአምር እየሠራህ ነው ሊትል ... በርታ" አለው።



የሊትል መልስ አጭር ነበር "አመሰግናለሁ"። ዳንኤል ጆምር የሊትልን ገጽታና የሰውነት አቋም ሲመለከት ከቻርሊ ገጽታና የሰውነት አቋም ጋር ስለተሳከረበት፤ በዚያው በቆመበት መድረክ ላይ ከቻርሊ ጋር የፈጠረው እስደንጋጭ ግጭት ታወሰውና ሰውነቱ ሽምቅቅ ብሎ ፊጥኖ ከመድረኩ ወርዶ ሄደ።

ሊትል ተክዞ ከቆመበት ስፍራ ሳይንቃነቅ ሣራ ጋዴም ሁለት የለስላሳ መጠጥ ጠርሙሶች ይዛ መጣችና አንዱን ለሊትል አቀበለችው። ፊቷ በደስታ ፈክቷል። በሊትል የመድረክ ሥራ መዋጣት ከደስታዋ የተነሳ የምታደርገው እስኪጠፋት ድረስ ቀልቧን አጥታለች።

ሊትል የሰጠችውን የለስላሣ መጠጥ ቆርኪ በጥርሱ ከፍቶ በአንድ ትንፋሽ አጋመሰና በረዥሙ ተነፈሰ። ቀጥሎም የሣራን ጠርሙስ ተቀብሎ ቆርኪውን ከፍቶ ሰጣት።

"ጨልጠህ ጠጣው ሊትል... ወደ መድረኩ ልንገባ የቀረን ጥቂት ደቂቃ ብቻ ነው" አለችው ለተውኔቱ ያደረገችውን ረዥም አርቴፊሻል ፀጉር እያስተካከለች። ሊትል ቻርሊ ራሱን በእሽታ ነቅንቆና የለስላሳውን መጠጥ ጨለጠው።

"በርታ ሊትል... ሁለተኛውን ክፍል ደግሞ ያለ እንከን እንደምትጫወተው ተስፋ አለኝ... አርቲስት የመሆን ምኞትህ በመሳካቱ ምን ይሰማሃል?" አለችው ትናንሽ ዐይኖቿን እያርገበገበች።

"እንጃ... ምን እንደሚሰማኝ አላውቅም"

"ሊትል? ግን ምነው እንደዚህ ተከዝክ?"

ሊትል ፈጥኖ አልመለሰላትም። ዐይኖቹን በዝዝ አድርጎ ዐይኖቿ ላይ ተክሎ ሲመለከታት ቆየና "ዳዲ አዳራሹ ውስጥ እንደነበር አውቀሻል?" አላት።

"አዎን... ስምህን እየጠራ ሲጮህና በኋላም አዳራሹን ጥሎ ሲወጣ... ያየሁት ይመስለኛል"

"እና... ቅድም አርቲስት የመሆን ምኞትህ በመሳካቱ ምን ይሰማሃል ነበር ያልሽኝ?" የሣራ ገጽታ በአፍታ ጥርጣሬና ሥጋት እንደጠላበት በአምንታ ራሷን ነቀነቀችለት።

"ይቅርታ አድርጊልኝና ሣራ የመሣሪያ ምላጭ ስቤ አባቴን እንደገደልኩት ዓይነት የወንጀለኝነት ስሜት፣ የፀፀት ስሜት ነው የሚሰማኝ... የዳዲ የመጨረሻ ተስፋ እንደወደመች አልጠራጠርም...

እና ምንአልባት ከዚህ እንደሄደ ራሱን ይገድል ይሆናል የሚል ስጋት ነፍሴን ወጥሮ ይዟታል ። በጣም ፈርቻለሁ ሣራ... ይሄ ተውኔት አልቆ በፍጥነት ወደ ቤቴ በሄድኩ... አባቴ አጠገብ መሆን እፈልጋለሁ! አልደብቅሽም ሣራ፣ በጣም ሰግቻለሁ፤ ልቤ በፍርሃት እየዘለለች ነው። ሩጥ ሩጥ ይለኛል ... ከዚህ አካባቢ ጥፋ ጥፋ የሚል ስሜት ከውስጥ ይታገለኛል" አላትና ገልመጥ ገልመጥ ብሎ ዙሪያውን ቃኘ።

ሊትል ከመድረኩ ሮጦ ለመውጣት መንገድ የሚፈልግ መሰላትና ሣራ ደነገጠች። ወደ እርሱ ተጠግታ ክንዱን ጭምድድ አድርጋ ያዘችና "ምን ነካህ ሊትል ? አርቲስት የመሆን ምኞትህ እውን በሆነባት በዚች ቀን እንደዚህ ማዘንና መንፈስህን ማሸበር አይገባህም ። ተውኔቱን ከሀሳብና ከጥርጣሬ ነፃ ሆነህ መጫወት መቻል አለብህ ... ለቻርሊ እንደሆን አታስብ፤ ምንም አይሆንም። ተውኔቱን እንደጨረስን አብረን ወደ ኋይት ሃውስ እንሄዳለን..."

ሊትል አላስጨረሳትም። በተጨነቀ ገጽ ላይ ሥጋት አርግዘው የሚንከራተቱ ዐይኖቹን እያርገበገበ "እንጃ ሣራ... እንጃ... አባቴን ዳግመኛ የማገኘው አይመስለኝም... እባክሽ በነፍሱ ልድረስለት... እባክሽ እንድሄድ ተይኝ?"

ሣራ ለአጭር ጊዜ በድንጋጤ ደርቃ ቀረች። ጆሮዎቿ የሚሰሙትን ማመን አልቻለችም። መንፈስ ቅብጥብጥና ትዕግስት የለሽነቱን ጠንቅቃ ስለምታውቅ፣ በሺ የሚቆጠሩ የተውኔት ታዳሚዎቹን በተቀመጡበት ጎልቶ ከመድረክ ጠፍቶ ይሄዳል ብላ ሰጋች። በዚህ ምክንያት ደግሞ የሚፈጠረውን ችግር በቀላሉ የምትወጣው አይሆንም። -ሊትል ቻርሊ አባቱን ተክቶ መሥራት እንደሚችል ዳንኤል ጆምርን እንደቀፈፈው ያሳመነችው እርሷ ናት። በእርሷና በዳንኤል መካከል ያለው ግንኙነት እስከመጨረሻው አበቃለት ማለት ነው። በተውኔቱ በጆምር መቋረጥ ሳቢያ በዝርክርክ የቲያትር አዘጋጅነቱ ምክንያት በዳንኤል ላይ የሚወርድበት ውግዘት ታሰባት። ለጥቂት ወራት የለመለመች ተስፋው ከአናቷ ተቀንጥሳ እንደምትጠወልግና ወደ ቀድሞው የብቸኝነት በሽታው እንደሚመለስ አልተጠራጠረችም።

የሊትል ቻርሊን ክንድ ጨምድዳ እንደያዘች ሊትል በእርግጥ አንተ ጤነኛ ነህ?" ስትል ዐይኖቹን አፈጠጠችበት።

ሊትል አልመለሰላትም። ክንዱን ከእጇ አላቀቀና በግምባሩ ላይ የሚንጠፈጠፈውን ላብ በመሀረቡ ጠረገ። በዚያው ቅጽበት ወደ መድረኩ እንዲገቡ የሚያስጠነቅቃቸው የመጨረሻው ደወልም ተደወለ



"ለቻርሊ ውለታ እየዋልክለት መሆኑን ደግሞ አትዘንጋ። ገና ተውኔቱን መለማመድ ከመጀመርህ በፊት የቲያትሩን አዘጋጅ በሁለት ነገር አሳምነኸዋል አይደለም?! አባትህ በመድረኩ ላይ ለፈፀመበት የግድያ ሙከራ በህግ እንዳይጠይቀው እና ተውኔቱን አልጫወትም በማለቱ በገዛ እንጀራው ላይ ለፈፀመው በደል በመሥሪያ ቤቱ አስተዳደር ላይከሰው ቃል አስገብተኸዋል... ቻርሊ የናደውን የገዛ ህይወቱን አንተ እየገነባህለት መሆኑን አስብ" አለች ሣራ ሊትልን የምታረጋጋበትን መንገድ ሁሉ እየፈለገች።

"ዳዲ ግን ይህን ሁሉ አያውቅም። ቢያውቅም ደግሞ ግድ የለውም። ዳዲ የሚያውቀው አንድ ነገር ብቻ ነው - ከጄዋለሁ። ከሃዲነቴ የተሰማኝ ደግሞ ዛሬ ነው። ገና መጋረጃ ተከፍቶ ከህዝቡ ዐይን ጋር ስተያይ። በስሙ ነግጃለሁ ሣራ... አሣፋሪ ሥራ ነው የሠራሁት... እናም በመድረኩ ላይ በቆየሁ ቁጥር ልክ ሲሰርቅ እንደተያዘ ሌባ ሀፍረት እያሽማቀቀኝ ሄደ። አባቴ አዳራሹን ጥሎ ሲወጣ ደግሞ አርቲስት የመሆን ምኞቴ በውስጤ ሲሞት ታወቀኝ። አሁን ዋናው ነገር ይሄ አይደለም... እመኚኝ ሣራ አባቴ ወደቤት እንደተመለሰ ራሱን ያጠፋል"

"መጋረጃው እኮ ተከፍቷል ሣራ... መድረኩ እያዛጋ ህዝቡም ዐይኑን አፍጥጦ፣ ትንፋሹን ውጦ እየጠበቃችሁ ነው" አላቸውና ወደ ጆርባቸው አልፎ ቦታውን ያዘ - ቃላት ጠቋሚው።

ሣራ የሊትልን ዐይኖች በጥርጣሬ አየቻቸው። በቅድሚያ ወደ መድረኩ መግባት ያለባት እርሷ ናት። ከጥቂት ደቂቃዎች ቆይታ በኋላ ሊትል ይከተላትና ተውኔቱ ይቀጥላል።

"ሊትል... አሁን ለውይይት ጊዜ የለንም... እባክህን ያመንኩህን ያህል ታመነኝ?"

ሊትል አልመለሰላትም ። ዐይኖቹን በዐይኖቿ ላይ እንደተከለ ቀረ። ነፍስና ሥጋው እየታገሉ መሆኑን የጨፈገገ ገጽታውን ተመልክታ ተረዳች። መጋረጃው ተገልጦ ተውኔቱ ሳይቀጥል በመዘግየቱ የህዝቡ ጭብጨባና ፉጨት መሰማት ጀምሯል። ሣራ የምታደርገው ጠፍቷታል። ሊትል መወሰን አቅቶት በመንፈሱ ይዋልላል።

ከየት መጣ ሳትለው ዳንኤል ጆምር ቁና ቁናውን እየተነፈሰ አጠገቧ ቆመና "ምን እየጠበቅሽ ነው?" ሲል በጆሮዋ ላይ ጮኸባት። ከመደንገጧ የተነሳ ለምን እንደዘገየች ልታስረዳው አልቻለችም።

ከአጠገቡ ቁር ብላ ሮጠችና በመብራት ወዳሸበረቀው መድረክ ጥልቅ አለች። ከመድረኩ ጀርባ የሚፈጠረውን ችግር ለማየት ዐይኖቿ ጉልበትፕ ጆሮዎቿ ድፍረት የላቸውም። ሊትል ቻርሊ ወደ መድረኩ ይከተላት አይከተላት አታውቅም።

***   ***   ***

ሻምበል መብራቱ ናፖሊዮን እምባውን አዳራሹ ውስጥ ሊያየው አልቻለም። ተውኔቱ ሊጀመር የመድረኩ መጋረጃ ሲተረተርፕ መብራቶቹ ሁሉ ሲጠፉ በዳበሳ ከአዳራሹ ወጥቶ ነበር። እየተጣደፈ የቲያትር ቤቱን ህንፃ በመልቀቅ በህንፃው የውጭ መተላለፊያ ላይ ወደሚገኘው የህዝብ ቴሌፎን በመሄድ ወደ ወንጀል ምርመራ ቢሮ ስልክ ደወለ። የሚገኝበትን አድራሻ በመግለጽ ሃይል እንዲላክለት ከጠየቀ በኋላ ስልኩን ዘግቶ በቲያትር ቤቱ በር አካባቢ ጥግ በመያዝ የአካባቢውን እንቅስቃሴ በዐይኖቹ መቆጣጠር ጀመረ። በየደቂቃው ልቡ በፍጥነት ይመታልፕ መንፈሱ ይሸበራል። በእጁ ገብቶ የነበረው ወንጀለኛ ድንገት ከእጁ በመውጣቱ ተደናግጧል። ከእንግዲህ ዳግመኛ እንደማያገኘው ሰጋ። የመንፈሱን ውጥረት ለማርገብ በአካባቢው ከሚዘዋወሩ ሱቅ በደረቴዎች አንዲት ፍሬ ሲጋራ ገዝቶ በላይ በላዩ እየሳበ አጨሰ።

ብዙም ሳይቆይ አንድ አሮጌ ላንድሮቨር መኪና ስድስት የፖሊስ የደንብ ልብስ የለበሱ የወንጀል ምርመራ ባልደረቦች እንደጫነች ቲያትር ቤቱ በር ላይ ቆመች።

ሻምበሉ ወደ መኪናዋ ፈጥኖ በመሮጥ የኋላውን በር አስከፍቶ ገባ። ለሁሉም አባላት የወንጀለኛውን ማንነትፕ የሰውነት አቋሙንና የለበሰውን ልብስ አይነት ከገለጸላቸው በኋላ ወንጀለኛውን ከነነፍሱ መያዝ የሚችሉበትን አፋጣኝ እቅድ ነድፈው በቲያትር ቤቱ በር አካባቢ ፈንጠር ፈንጠር በማለት ቦታ ይዘው ቆሙ። ሻምበሉ ወደ አዳራሹ በመግባት ቦታ ይዞ ተቀመጠ። ተውኔቱ በጨለማው አዳራሽ ውስጥ ቀጥሏል። ሊትል ቻርሊ በመድረኩ ላይ ተአምር እየሠራ ነው።

***   ***   ***

ናፖሊዮን እምባው ከአዳራሹ ህንፃ ላይ ዐይን ቢንጉጡ በማይታይበት ጨለማ ውስጥ የህንፃውን ምሰሶ ተደግፎ ቁልቁል በብርሃን ባሸበረቀው መድረክ ላይ ሽጉጡን አነጣጥሯል!

በመድረኩ ላይ በፍጥነት የሚንቀሳቀሰው ሊትል ቻርሊ በኢላማው ሊገባለት አልቻለም። ኢላማው ውስጥ በገባለት ሰኮንድ



ውስጥ ደግሞ መድረኩ ላይ አብራው የምትጫወተው ሣራ ጋዴም በናፖሊዮን አፈሙዝና በሊትል ቻርሊ መካከል ግድግዳ ሆና ትቆማለች። ናፖሊዮን የሽጉጡን አፈሙዝ በሊትል ደረት ላይ አነጣጥሮ ምላጩን ሊስብ ጣቱን ማንቀሳቀስ ከጀመረ በኋላ እንኳን ብዙ ጊዜ እጁን መልሶ ሰብስቧል።

"ሺት!" አለ ናፖሊዮን ብስጭት ብሎ "ቀዥቃዣ አርቲስት! በአንድ ቦታ ላይ ለአፍታ እንኳን ረግቶ አይቆምም?! ያች ዝንብ የሆነች ፍጥረት ደግሞ..." ጥርሱን ቀጨጨጨጨጨ - ጭ አድርጎ አፋጩና በትዕግስት መጠባበቁን ቀጠለ። የሚተኩሳት አንዲት ጥይት መባከን የለባትም። ያለችው እድል አንድ ነች። የመጀመሪያዋና የመጨረሻዋ ጥይት የምትባክን ከሆነ እቅዱ ሁሉ ይከሽፋል። ለዚህም ነው ከመሳት ጥርጣሬ ነፃ ሆኖ በትክክለኛዋ ሰኮንድ በትክክለኛው ቦታ ላይ ምላጩን ለመሳብ በጥንቃቄ የሚያነጣጥረው።

የሊትልን እንቅስቃሴ እየጠበቀ እግረ መንገዱን ተውኔቱን ሲመለከት የመጣበትን ዓላማ እየዘነጋ በተውኔቱ የሚዋጥበት ጊዜም ነበር። ደሞም ደጋግሞ "ቻርሊ ታላቅ የሃገር ሀብት ነው" እያለ በጥይት አረር የሚቀጥፉትን ነፍስ ችሎታ ያደንቃል። ለታላቅ ሰውነቱ ክብርፕ ለታላቅ የሃገር ሃብትነቱ ውለታ እርሱም ታላቅ ሞት ደግሶለታል። በሺ ዐይኖች ታዛቢነት የሚሞተውን የክብር ሞት።

በተውኔቱ አጋማሽ ላይ ሊትል ወደ መድረኩ ጠርዝ ተጠግቶ ብቻውን መጫወት ጀመረ። ሣራ ጋዴም በሌላው የመድረክ ጠርዝ ላይ ቆማለች። የሊትል እንቅስቃሴ ዝግ ያለ ነው። ናፖሊዮን ከዚህ የተሻለ እድል እንደማይገጥመው ስለገመተ ጣቱን በምላጩ ላይ አኑሮ አፈሙዙን በሊትል ደረት ላይ አነጣጠረና ከእንቅስቃሴ ውጭ የሚሆንበትን ሰኮንድ ትንፋሹን ዋጥፕ ክንዱን ጠበቅ አድርጎ ጠበቀው። በዚያችው በትክክለኛዋ ሰኮንድ አዳራሹን ነቅንቆ የተውኔት ታዳሚዎችን ጆሮ የሚሰነጥቅ የተኩስ ድምጽ ሲሰማና ሊትል ቻርሊ እንደ ፎጣ እጥፍጥፍ ብሎ በመድረኩ ላይ ሲዘረጋ አንድ ሆነ።

ከተኩሱ ድምጽ በኋላ በመድረኩ ላይ ፈጥና የተንቀሳቀሰችው ሣራ ጋዴም ነበረች። ከቆመችበት የመድረኩ ጠርዝ ወደ ሌላኛው ጠርዝ እየበረረች ሄዳ ሊትል ቻርሊን ከወደቀበት አነሳችው። ከግራ ደረቱ ላይ ደሙ ቡልቅ እያለ በመድረኩ ላይ ይንጠፈጠፋል። በደፈረሱትና በሚስለመለሙት ዐይኖቹ አንድ ጊዜ ብቻ ቀና ብሎ አያት። ሁሉም ነገር ግራ ገብቶታል። ሣራ ከተንበረከከችበት ተነስታ ራሷን ያዘችና እሪታዋን አቀለጠችው።

ሌላ ሰው እመር ብሎ ወደ መድረኩ ወጣና ወደ ሲትል ቻርሊ አንሰስ ... ዳንኤል ጀምር። እርሱም ግራ እንደገባው ሰውነቱ ይንቀጠቀጥ፣ ትንፋሹ ይቆራረጥ ጀመር። እንደገናም አንድ ማንነቱ ያልታወቀ ሰው ከህዝብ መሃል እየሮጠ ወደ መድረኩ ወጣና የተፈጸመውን ተመልክቶ በፍጥነት ወደ አዳራሹ መውጫ በር ሮጠ - ሻምበል መብራቴ!

በጨለማው አዳራሽ ውስጥ የታጨቀው የተውኔቱ ታዳሚ ሁሉም ከመቀመጫው ተነስቶ ቆሟል። ሦስት የጥይት ድምጽ አከታትሎ ተሰማ። በአዳራሹ ውስጥ ከፍተኛ ትርምስና ግርግር ተፈጠረ። እያንዳንዱ ታዳሚ አዳራሹን ለቆ ለመውጣት በመግቢያው በር ላይ ይተናነቅ ጀመር። ከመድረኩ ላይ የተዋንያኑ ዋይታና ትርምስ እየጋለ ሽብርና ግርግሩን አባባሰው።

ሻምበል መብራቴ ..ቲያትር ቤቱ የመግቢያ በር ላይ የመደባቸውን ፖሊሶች አስተባብሮ የመውጫውን በር ከማዘጋቱ በፊት ከአዳራሹ ውስጥ ነፍስ ይዞት እየጮኸና እየሮጠ የሚተም ሽብር ያስበረገገው ታዳሚ፤ እንደ ውሃ ሙላት አጥለቅልቆት የአዳራሹን በር በመጣስ ወደ አስፋልቱ ዶሮጥ ጀመር።

ሻምበሉ ከአዳራሹ በር ላይ ዐይኖቹ እንባ አቅርረው ከንፈሩን እንደነከሰ ቆሞ ቀረ። የወንጀለኛውን ጭራ በያዘ ሰዓት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ የገዛ ዐይኖቹ ታዝቢ በሆኑበት ነፍሰ ገዳዩ ሌላ የነፍስ ግድያ ፈጸመ! መብራቴ ሙያውን ረገመ፤ ራሱን ጠላ። ይሁን እንጂ አሁንም ተስፋ አልቆረጠም። የአዳራሹን በር እየጣሰ እግሬ አውጪኝ ከሚከንፈው ህዝብ መካከል ግዙፉን ናፖሊዮንን በዐይኖቹ ይፈልገዋል። አብዛኛው ህዝብ ከአዳራሹ ወጥቶ እስኪያልቅ ድረስ ሊመለከተው አልቻለም።

"ምን አይነት ጉድ ነው ጌታዬ?"

ሻምበሉ ለቅጽበት ዞር ብሎ አጠገቡ የቆመውን ሰው ተመለከተ። ግዙፉ የወንጀል ምርመራ ሳጅን ረዥም የአፍንጫውን ጢም እያፍተለተለ ቆሟል።

"በምልክት የነገርኩህን ሰው በዐይንህ ፈልግ!" አለና ሻምበሉ ዐይኖቹን እያማተረ አሰሳውን ቀጠለ።

ወንጀለኛው አምልጧል ብሎ ተስፋ በቆረጠበት በመጨረሻዋ ደቂቃ ላይ ከአዳራሹ እየሮጡ ከሚወጡት ሰዎች መካከል ናፖሊዮንን ውልብ ሲል ያየ መሰለው! መነጽሩ በዐይኑ ላይ የለም። ጎፈሬው ፀጉሩ፤ ግዙፍ አካሉና የለበሰውን ጥቁር የቆዳ ጃኬት ግን... አዎን በትክክል ነፍሰ ገዳዩ ናፖሊዮን አምባው ነው!

አጠገቡ የቆመውን ሃምሣ አለቃ "ተከተለኝ!" አለና ሻምበሉ ከትርምሱ ውስጥ ገባ። ሳጅንም ግዙፍ ሰውነቱን አንቀሳቅሶ አቅጣጫውን ተከትሎ ሮጠ። ሻምበሉን ሊያገኘው ግን አልቻለም።

ናፖሊዮን ነፍስ ይዞት ከሚሮጠው ህዝብ ጋር እየተጋፋ አስፋልቱን ተሻገረና ቁልቁል ወደ ላዩን በር አቅጣጫ ሮጠ። ሻምበል መብራቴ በቅርብ ርቀት ተከትሎታል! በኢትዮጵያ ሆቴል ጀርባ በሚያቋርጠው ጠባብ አስፋልት አልፎ ወደ ካስ ሜዳ የሚያመራውን መንገድ ሲያያዝ የሩጫ ፍጥነቱን ቀንሶ ገልመጥ አለና አካባቢውን ቃኘ ። የሻምበል መብራቴ ሽጉጥ በጀርባው ላይ ተነጣጥሯል። "እጅ ወደ ላይ!" መብራቴ በከፍተኛ ድምጽ ጮኸ።

ናፖሊዮን ፊቱን ወደ ሻምበሉ አዙሮ ቆመ። የሽጉጥ አፈሙዝ ደረቱ ላይ ተነጣጥሯል። ይህንን ሰው የት እንዳየው ለሰከንዶች ከፍልፋይ ራሱን ጠየቀና ዛሬ ቀትር ላይ ከመኖሪያ ቤቱ ትይዩ ባለችው የሸቀጣሸቀጥ መደብር በረንዳ ላይ ለስላሳ መጠጥ እየጠጣ ቆሞ የነበረው ሰው መሆኑን አረጋገጠ። የጠበቃው ማስጠንቀቂያ ትዝ አለው። "... የወንጀል ምርመራ ፖሊሶች ማንነትህን ደርሰውበታል!"

"እጅ ወደ ላይ!" ሻምበል መብራቴ እንደገና ጮኸ። የወንጀለኛውን አደገኝነትና መታጠቁንም ያውቃል። የደገነበት አፈሙዝ ሊተፋ የሚችለውን እሳት ፈርቶና ለህይወቱ ሳስቶ ትእዛዙን ሳይቀበለው ከቀረ ከህይወቱ ሊይዘው እንደማይችል ገመተ።

ናፖሊዮን የድንጋጤና የፍርሃት ስሜት ፈጽሞ አይታይበትም። ከሻምበሉ አፈሙዝ የሚፈናጠር ጥይት ወደሚወደው ጨለማ እያንሳፈፈ የሚወስደው ሮኬት እንጂ ሌላ ምንድነው?! ሲመኘው የኖረ ሞት በአራት ሜትር ርቀት ላይ ሊውጠው አፉን ከፍቷል። ከቻርሊ ጋር መስመር ላይ እንገናኝ ይሆን? ሲል አሰበና በምጸት ፈገግ አለ።

"እጅ ወደላይ!" መብራቴ ለሦስተኛ ጊዜ አስጠነቀቀው። ናፖሊዮን ለሰከንዶች ከፍልፋይ ከሰጠመበት ሃሳብ ነቅቶ የሻምበሉን ዐይኖች ተመለከተ። በመካከላቸው ያለውን ርቀት ሲገነዘብ ፈጣን እይምሮው ከተደገሰለት ሞት ለማምለጥ አሁንም ጊዜ እንዳለው ድንገት ጮኾ ነገረው። ፈገግ እንዳለ ሁለት ርምጃዎች ወደ ሞት አቅጣጫ ተራመደ!

"ተጠንቀቅ እንዳትበላሽ!" ሻምበሉ ሁለት ርምጃዎች ወደ ኋላው አፈገፈገ። ያ ነትላ ሳጅን ምን ዋጠው?!

ናፖሊዮን እንደገና ወደፊት ሁለት ርምጃ!

ሻምበሉ ወንጀለኛውን ከነነፍሱ ለመያዝ የነበረው ተስፋ እከተመ። ከፊት ለፊቱ እየቀረበው የመጣውን ነፍሰ ገዳይ እቁስሎ ለመያዝ ወይም ወደ ሰማይ ተኩሶ በማስደንገጥ በቁጥጥር ሥር ለማዋል ባለው እግ ላይ ሲያመነታ ድንገት እንደ መብረቅ የሚጮህ ድምጽ ሲሰማና የዐይኑ ብርሃን ሲጨልምበት ታወቀው።

ሻምበሉ ሲያመነታ ባቃጠላት የሰከንድ ሽራፊ ናፖሊዮን እንደ ቀስት በአየር ላይ ተወናጭፎ በቀኝ እግሩ ቡትስ ጫማ የሻምበሉን ሽጉጥ ከእጁ ላይ አፈናጠረው! በዚያች ቅጽበት ውስጥ እጆቹም ሥራ አልፈቱም ነበር። ጠንካሮቹ የእጆቹ ጣቶች የሻምበሉን ጉሮሮ ትንፋሽ እስኪያጥረው ደጋግመው መቱት። መብራቱ እንደ ሽማ ተጣጥፎ ከእግሩ ሥር ተዘረረ።

ናፖሊዮን በቆራጥ ውሳኔውና በቀልጣፋነቱ ራሱን ለማድነቅ ግን ጊዜ አላገኘም። የሻምበሉን አወዳደቅ ተመልክቶ ቀና ሲል ለጭንቅላቱ ተነጣጥረው የተተኮሱ ሁለት ጥይቶች በደንዳናው አንገቱ ግራ ክፍል ላይ ሲጠቀጠቁ ታወቀው!

የተወጣጠረ ጡንቻው ሲላላ፤ መተጣጠፊያዎቹ ሲብረከረኩ፤ ሞቅ የሚል ነገር ሲሰማውና ዐይኖቹ ሲስለመለሙ፤ ሽጉጡን እንደደገነ እየቀረበ የሚመጣውን ግዙፉ ሰው ተመለከተ። ረዥሙን የእፍንጫውን ጢም ቢያሳጥረው ምን ነበር? ኢትዮጵያዊው ሂትለር ይሆን? በምጸት ፈገግ እንዳለ መዛል የጀመረውን እጁን በፍጥነት ሽጉጡን ወደታጠቀበት ሽንጡ ሰደደው። ግዙፉ ሳጅን ግን ሻምበል መብራቱን አይደለምና ጊዜ አልሰጠውም። ሌሎች ሁለት ጥይቶች ተኩሶ ደረቱን ደበደበው።

ናፖሊዮን ሁለት እጆቹን ወደ ታች አንዘርፍፎ ፈገግ አለ። ወፍራም ጨለማ እያቀፈው፤ ሞት እየሳቀ ሲቀበለው የቅዠት ያህል ይታወቀዋል። ግዙፉ ሰው ወደርሱ ያነጣጠረውን ክልት ሽጉጥ ለአምስተኛ ጊዜ ከመተኮሱ በፊት ህሊናውን ስቶ ወደቀ። ደህና ሁኚ ብርሃን!



## ምዕራፍ ሃያ ዘጠኝ

ቻርሊ ለልጁ መልካም ምኞቱን ገልጾ በዐይኑ ላይ የተንጠለጠሉትን የእንባ ዘለላዎች አብሶ የቲያትር ቤቱን በር እልፎ እንደወጣ፤ ጭንቅላቱ ውስጥ ያ የሚጠላው ድምጽ ሲጮህ ተሰማው፤ ጆሮዎቹን በሁለት ጣቶቹ ድፍን አድርጎ ያዘ። ድምጹ ከውስጥ እንጂ ከውጭ ባለመሆኑ በህሊናው ውስጥ መጮሁን ሊያቆም አልቻለም።

እና ድንገት ብር ብሎ መሮጥ ጀመረ። በቲያትር ቤቱ ጀርባ ዞሮ ከንግድ ሥራ ኮሌጅ ማይጨው አደባባይ ድረስ። ከዚያ ቁልቁል የቄራን አቅጣጫ ይዞ በገነት ሆቴል አቋርጦ በግ ተራ ድረስ። ለአፍታ ሳይቆም ላቡን እየረጨ፤ ፀጉሩን እየነጨ ሮጠ... ሮጠ... ሮጠ፤ ልቡ ልትፈነዳ የደረሰች እስኪመስለው ድረስ በረረ። የሚጠላው ድምጽ የሚያባርረው ይመስለዋል *መሃይም!... መሃይም!... መሃይም...! መሃይም!...*

ሰይጣን ሰፈር ደርሶ ወደ ጀማል ሱቅ ሲቃረብ ጫን ጫን እየተነፈሰ ቆም አለ። የመብራት ምሰሶ ከበው የቆሙት የመንደሩ ወጣቶች እንደ ጉድ ይመለከቱታል።

"ቻርሊ ጨብ ብሏል" አለ ታሪኩ ከራራው።

"የአንጎሉ ብሎን ላልቶ ነው" ግድንግዱ አሊባባ በጎርናና ድምጽ የራሱን ግምት ሰጠ።

"ጋሽ ቻርሊ ስለ ኪነት ንገሩን?" ተመስገን ድኩላው ድንገት ድምጹን ከፍ አድርጎ ጮኸ።

ቻርሊ በህሊናው የሚጮኸው ድምጽ ጋብ እስኪልለት ቆም አለና ማሰብ ጀመረ። ቆይቶም ትክዝ እንዳለ "ኪነትማ ሞተች!" አላቸው ድምጹን ከተመስገን ድኩላው ድምጽ ጋር አመሳስሎ። ወጣቶቹ እንደተማከሩ አይነት በአንድነት ሳቁ።

"ኪነት ስትሞት አታለቅሱም?"
"አናለቅስም!" ወጣቶቹ በአንድነት ጮኹ።
"ጥበብ ስትሞት እሪ አትሉም?"
"እሪ አንልም!"
"ውበት ስትሞት ኡኡ አትሉም?"
"ኡኡ አንልም!"
"ፍቅር ስትሞት ማቅ አትለብሱም?"
"አንለብስም!"

"ከይሲ ትውልድ!"
ወጣቶቹ በአንድነት ሳቁ።

"ወሮ በላ ሁሉ! ወደየቤታችሁ አትገቡም? መጽሃፍ ደብተር ገልጣችሁ አታነቡም? አትማሩም? ጥበብን አምጣችሁ አትወልዱም?"

"መውለድ አንችልም ወንዶች ነን!" ታሪኩ ከራራው መለሰለት። ሌሎቹ እየተንጫጩ በሳቅ ተንከተከቱ።

"ከይሲዎች፣ ደደቦች፣ መሃይም..." ድንገት ስድቡን አቋርጦ ሮጠ - ወደኋይት ሃውስ።

ከኋላው ሞቅ ያለ ጭብጨባ አጀቦታል። "ቻርሊ! ቻርሊ ቻርሊ!"

አንጎሉ በጭንቅላቱ ውስጥ የሚዞር፣ ሰማይ መሬቱ የሚሽከረከርበት ይመስለዋል። ኋይት ሃውስ በር ላይ ሲደርስ ወደ ኋላው አፈገፈገና ተንደርድሮ ገርበብ ያለውን በር በርግጫ ሲለው ወለል ብሎ ተከፈተ።

ኋይት ሃውስ እንደ ወትሮዋ ምስቅልቅሏ እንደወጣች ነች። ኮቱን አውልቆ አሮጌው ሶፋ ላይ ወረወረና ተቀመጠበት። ደረቱ እየተነፋና እየሟሸሸ በላይ በላዩ ይተነፍስ ጀመር። ላቡ ከግምባሩ ላይ እየተንጠፈጠፈ ወደ ደረቱ ይዘንባል። ደም ያረገዙት ትላልቅ ዐይኖቹ ሥራ አልፈቱም፣ በቤቱ ውስጥ ወዲያና ወዲህ ያማትራሉ። ድንገት ምጣዱ ጠረጴዛ ላይ ተጣጥፎ የተቀመጠ ደብዳቤ ተመለከተና ከመቀመጫው ተነስቶ አነሳው ። ልክ የቃለ ተውኔት ጥራዙን ጨብጦ እንደሚያነበንበውም እይነት ድምጹን ከፍ አድርጎ ማንበብ ቀጠለ።

ለሊትል፣

የስንብት ደብዳቤ ነው። ቤት መጥቼ ላገኝህ አልቻልኩም። ወንድምዬ ከዚህ በፊት ያጫወትኩህ እድል ተሳክቶልኛል። ጀማላውን አግብቼ ነገ ወደ ጂዳ እበራለሁ። ኢያስቅም?! ከበሮ ሳይጮህ፣ ሚዜ ሳይመረጥ፣ ዳስ ሳይጣል፣ ዓለም እለፈች በተባለለት ድግስ ሳልሰረግ እያስቅም? እኔ ሊሊቱን ሙሉ ስስቅ አደርኩ፤ እያለቀስኩ... 'ወግ ነው ሲዳሩ ማልቀስ' አትለኝም? ያለቀስኩት ለምን እንደሆን ታውቃለህ?! ሊትል? ፍቅር ምን እንደሆን ሳላውቅ በማግባቴ ነው! ራሴን በራሴ መግዛት ከጀመርኩ ጊዜ ጀምሮ ደስተኛ ለመሆን ያልፈነቀልኩት ድንጋይ አልነበረም። ከአንተ የምደብቀው ሚስጥር የለኝም ሊትል፣



ለአንድ ጀንበር እንኳን ህይወቴ ደስተኛ ሆና አታውቅም። ነፍሴ ዘወትር እንደተቅበዘበዘች ነች። ለፍቅር የተቁረቆረው ልቤ ለጥላቻ ሁልጊዜም ክፍት መሆኑ ደግሞ ሲገርመኝ ይኖራል። ጀማላውን እንዴት እንደምጠላው ታውቃለህ? "ለምን አገባሽው?" እንዳትለኝ። ሚስቶች ሁሉ ባሎቻቸውን የሚወዱ ይመስልሃል? ብቻ ስለሌሎች ምን አገባኝ ? የኔውን ልጨርስልህ፤ ጀማላውን ባገባሁበት ምሽት ስቅስቅ ብየ ያለቀስኩት የወግ ሆኖብኝ አልነበረም። ጥላቻን ሲያከማች የኖረው ልቤ ከዚያ በላይ መሸከም ባለመቻሉ እንጂ። ጀማላውን በዚያው ምሽት አንቄ ብገድለው በተደሰትኩ፤ አያስቅም? የልጅነት ባሌን?! አሰብኩ እንጂ አላደረኩትኩም። በገዛ እብደቴ ሳቅኩ። አትፍረድብኝ ሊትል። ማን ያሳየኝን ፍቅር ለመጀመሪያው ባሌ ላሳየው?

ጀማላው ለእኔ ቻርተር አይሮፕላን ማለት ነው። ወደ ፈለኩበት ለመድረስ የምገለገልበት ዕቃ። እርሱ ግን በፍቅሩ አብጂ ጨርቄን ልጥል የተቃረብኩ ይመስለዋል። እንደ አምላክ እንደምቆጥረው ይገምታል። የራሱ ጉዳይ! በቀደም አባትሽ ሥራው ምንድነው ብሎ ጠየቀኝ... "ተዋናይ ነው" ብዬ ብለው ከክፍሉ እንደሚያባርረኝ አውቅ ነበር። እና ምን እንዳልኩት ታውቃለህ? "በሮም የኢትዮጵያ አምባሳደር ነው" አልኩት። "የኬንያ ዋና ከተማ ነች?" ሲል ጠየቀኝ። አዲዮ ጂኦግራፊ! አትልም?

ጀማላው ብር እንጂ ትምህርት የለውም። ወንድም እንዳለኝ ሲጠይቀኝ ደግሞ ዐይኔን በጨው ታጥቤ "ፓይለት ነው" አልኩት። አትዘንብኝ ሊትል... ማን ባስተማረኝ እውነት ለልጅነት ባሌ ልታመንለት? እንዳስተዋወቀውም ጠይቆኝ ነበር። "ጊዜ ብር ነው" አልኩት። "ዘመዶቼ ከእኔና ከአንተ ጋር የሚያሳልፉት ጊዜ የላቸውም" አልኩት። ማን ለማን ይበለጣል ሊትል? የማወራውን ሀሰት ከእውነታው ጋር ሳጻጽረው ልቤ እንስኪፈርስ እስቃለሁ። ከደስታ የመነጨ ሳቅ ግን አይደለም። የእብደት፣ የቅሌት፣ የትንሽነት፣ ራስን የመጥላት ሳቅ ነው። እኔን መሰሎች ሁሉ በደረቅ ሌሊት ይህንን ሳቅ ስንት ጊዜ ስቀውት ይሆን?

ነገ ከልጅነት እስከ እውቀት የታሰርኩበትን ሰንሰለት የምበጥስበት፤ እድሜ ዘመኔን ስቃጠል ከኖርኩበት ምድራዊ ሲኦል ከሆነች ሃገር እምወጣበት፤ ዳግም የምወለድበት ዕለት ነች። ከፋህ ሊትል ? የሃገርህን ክፉ መስማት የማትወድ የአባትህ ልጅ መሆንህን ስለማውቅ እንደሚከፋህ እገምታለሁ።

ይቅርታ አድርግልኝና ሊትል 'ሃገር' የሚሉት ቋንቋ የውሸት ነው የሚመስለኝ። ሃገር ማለት አፈሩ ይሁን፣ ሰማዩ ይሁን፣ ሳርና

ቅጠሉ ይሁን፣ ሀዝቡ ይሁን አይገባኝም። ብቻ ሁሉም ሃገር እሌ - ታሪክ ነው የሚመስለኝ። 'የዳቦ ቅርጫት' ባሉኝ ሃገር ላይ እፍኝ ጥሬ ያጣ ህዝብ፣ ፈንግል እንደገባበት የዶሮ ርቢ መንደር፣ ሺበሺ ሲፈነገል አይቻለሁ። 'ድንግል ነች' ያሉኝ ጥቁር አፈር ለገዛ ልጆቿ ሆድ እንኳን አልሆነችም። 'ባለታሪክ' ነች ያሉኝ ሃገር ከእልፋ እስከ ኦሜጋ ያነበብኩላት፣ የበግሁላት ታሪኳ የጦርነት፣ የጭንቅና የሰቆቃ ነው። ሲነገረኝ የኖረውና በዐይኖቼ የማየው እውነት ባይገጣጠምልኝ... ሃገር የሚባል ቋንቋ ለኔ ትርጉም የለውም ብል ትፈርድብኛለህ? እውነት ነው ብትለኝ እንኳን በእናትነቷ ለእኔ ያደረገችልኝ ውለታ የለም። ስለ ሃገሬ የማውቀው ነገር ቢኖር እቶን ነዲዱ የማይበርድ ምድራዊ ሲኦል የመሆኗን ሃቅ ብቻ ነው።

በምሄድበት ሃገር ምን እንደሚገጥመኝ አላውቅም። ራሴን እጆቼን ዘርግቶ ወደሚጠብቀኝ አዲስ ዓለም ዐይኔን ጨፍኜ ወርውሬዋለሁ። በዚያ ምን እንደሚጠብቀኝ ለመገመት አልችልም። ምንም ቢሆን ደግሞ ግድ የለኝም ...

ሊትል ... በፊት በፊት ለህይወቴ መመሰቃቀል ሁሉ ምክንያቱ አባቴ ይመስለኝ ስለነበር እጠላው ነበር። አሁን ግን ከልቤ ይቅር ብየዋለሁ። ምን ያድርግ? ሳይታደል ተወልዶ ያልታደለን ቢያደርግን በርሱ ምን ይፈረዳል? ከቅርብ ጊዜ ወዲህ አዝንለት ጀምሬ ነበር። እባክህ አንተም እዘንለት? ሌላው ቢቀር ከእጠገቡ አትራቅ።

ወንድምዬ መለያየታችንን ሳስበው ልቤ ይሸበርብኛል። ዳግመኛ የምንገናኝ አይመስለኝም... ጠዋት አየር ማረፊያ ብቅ በልና አንድ ጊዜ ብቻ ልይህ? ሊትል? አንድ ሚስጥር ልንገርህ? አንተን ብቻ እወድህ ነበር... ቻዎ

ሃረገወይን!

'ሃረገወይን' የሚለውን ስም ጮሆ አነበበው። ከዚያ ቀስ እያለ ስሙን ደጋግሞ ጠራው። 'ሃረገወይን! ሃረገወይን! ሃረገወይን'። በደብዳቤው ላይ ካነበበው እውነት ያልሆነው ምንደኛው? ምንም። የበኩር ልጁ በሆቴል ቤት መኝታ ክፍል ውስጥ የውስኪ መለኪያ እንደጨበጠች ከአረብ ተጋቢታ ነገ ወደ ጂዳ ትበራለች። አልሳቀም - በምጸትም፣ በቁጭትም፣ በትዝብትም። ጥልቅ ሃዘን ልቡን ጠልቆት እንባ አውጥቶ አላለቀሰም። ዐይኖቹን በደብዳቤው ላይ እንዳፈጠጠ ደርቆ ቀረ። አዕምሮው ፍጹም በድን ወደመሆን ተቃርቧል።



ብዙ ቆይቶ ደብዳቤውን አጣጥፎ ከነበረበት መለስና "መረገም እንጂ ሌላ ምንድነው?" አለ ቁና ቁናውን እየተነፈሰ። እጆቹን ከሱሪው ኪሶች ውስጥ ከቶ የልጁን ስም ደጋግሞ በመጥራት ክፍሉ ውስጥ ይንቆራጠጥ ጀመር።

በየአቅጣጫው ያለ ምንክያት የሚንከራተቱት ዐይኖቹ በኋይት ሃውስ ግድግዳ ላይ በተለጠፈው የሃያ ዓመት አገልግሎት የምስክር ወረቀቱ ላይ ሲያርፉ፤ ከቲያትር ቤቱ በር ጀምሮ ሲያባርረው የመጣው ድምጽ ድንገት ህሊናው ውስጥ መጮህ ጀመረ። መሃይም! መሃይም! መሃይም! መሃይም!... የሚንቀጠቀጡ እጆቹን ወደ ምስክር ወረቀቱ ሰዶ ከተለጠፈበት ግድግዳ ላይ ገንጥሎ ወረወረው። ወረቀቱ በአየር ላይ እየተንሳፈፈ ሄዶ ምጣዱ ጠረጴዛ ላይ አረፈ። ድምጹ ግን እየደጋገመ ህሊናውን መውቀሩን አላቋረጠም። ሩጥ ሩጥ፣ ብረር ብረር፣ ሽሽ ሽሽ የሚል ስሜት ከውስጥ ታገለው።

ኮቱን ካስቀመጠበት አንስቶ በፍጥነት ለበሰና ከኋይት ሃውስ ወጥቶ ለመሮጥ ሲንደረደር ሣራ ጋዴም ከበሩ ላይ አቆመችው። የመድረክ ልብሷን እንደለበሰች ነች። የፊቷን ሜክአፕ አልታጠበችውም። ለመድረክ ሥራዋ ያደረገችው ረዥም አርቴፊሻል ፀጉር በፊቷ ላይ ተበታትኗል።

እንደደረሰች በቻርሊ አንገት ላይ ተጠምጥማ ታለቅስ ጀመር። ቻርሊም ምክንያቷ ሳይገባው እየተንሰቀሰቀ አብሯት አለቀሰ። "ማረኝ ጋሼ... ማረኝ... እኔ ነኝ ልጅህን ያስበላሁት... ማረኝ ጋሽ ቻርሊ... እኔ ነኝ ሊትልን ያስቀጨሁት... ማረኝ! ማረኝ! ማረኝ!" ከቻርሊ እግር ሥር እየተደፋች፣ እየወደቀችና እየተነሳች ጮኸች።

ቻርሊ ድንገት ከትከት ብሎ በመሳቅ የኋይት ሃውስን ጣራ አንቀጠቀጠው። ሣራ ያለ ማቋረጥ ስታለቅስ ቻርሊ ያለ ማቋረጥ ሲስቅ ጥቂት ደቂቃዎች አለፉ። ድንገት የጀመረውን ሳቅ ድንገት አቁሞ "ሊትል ምን ሆነ?" ሲል ግምባሩን ቅጭም አድርጎ ጠየቃት።

ሣራ ጋዴም ደነገጠች። ቻርሊ ገና የሊትልን ሞት አልሰማም። ዋይታዋን አቁማ ፊቷ ላይ የተበታተነውን አርቴፊሻል ፀጉር በጣቷ እየገለጠች ትናንሽ ዐይኖቿን እያርገበገበች አየችው። የልጅን ሞት ለአባት ሲያረዱ ወጉ እንዴት ነበር?

"ሊትል ወዴት ነው ሣራ?" መላ ሰውነቱ እየተንቀጠቀጠ አፈጠጠባት። ሣራ በህይወቷ ሙሉ እንደዚያ ያዘነ፣ የተጨነቀና ግራ የገባው የሰው ገጽታ አይታ አታውቅም። ቻርሊ ወደ ፍጻሜው

ተቃርጧል ስትል ገመተች። ምናው ከመጀመሪያው ባላውቀው በማለትም ተመኘች። የልጁን ሞት ልትደብቀው ግን አልሞከረችም "ሊትልን ገደሉት ጋሼ፤ አልቅስ! እናልቅስና ይውጣልን ጋሼ... ሊትል ሳያስበው ተቀጠፈ... የህይወቱን አቅጣጫ ፈለግ ባገኘ... በመጀመሪያው ቀን ወደቀ... መአት ነው የወረደብን ጋሼ ቻርሊ... መዓት ነው... እድሜውን ሙሉ ሲመኝ በኖረው የተውኔት ሙያ የልቡ ሞልቶ... ገና መድረኩን በረገጠ ቀን... ማንብኑብ የጀመረውን ቃለተውኔት ሳይጨርስ... እፉን እንደከፈተ ተንጋለለ... መዓት ነው የወረደብን ጋሽ ቻርሊ... ከወደቀበት አንስተን ዘውዲቱ ሆስፒታል እስክንወስደው ድረስ ህይወቱ አላለፈችም ነበር... ሆስፒታል በር ላይ መኪና ውስጥ እያለን... እየደከመ መሄዱን አውቆ..." እርጌው ሶፋ ላይ ያስቀመጠችውን ትልቁን ቦርሳዋን ከፍታ በደም የጨቀየውን ባለኮከብ ቅርጽ የብር ጌጥ እየሰጠችው... "ይህን እንደምንም ከአንገቱ አውልቆ 'ለአባቴ ስጭልኝ' አለኝ... ንገሪው አለኝ 'ዳዲ እባክህ እንዳታዝንብኝ በይው' አለኝ 'ከልብህ ይቅር በለኝ በይልኝ' አለኝና ስምህን ደጋግሞ እየጠራ ወደማይቀረው አላፈ... ምነው ለኔ ባረገው ሊትል!... እኔ ነኝ ያስበላሁት፣ እኔ ነኝ ገደ ቢሷ፣ ያስቀጠፍኩት፣ እኔ ነኝ ተውኔቱን እንዲጫወት ያግባባሁት... ወይኔ ሊትል! የኋይት ሃውስ መሠረት እስኪንቀጠቀጥ እየጮኸች አፈሩ ወለል ላይ ተንደፋደፈች።

ቻርሊ በልጁ ደም የጨቀየውን የብር ጌጥ በከንፈሮቹ እየዳሰሰ ሳመው... ሳመው... ለሰከንድ ክፍልፋዮች ብቻ ወደ ህሊናው የተመለሰ ያህል የብሩን ጌጥ በእጁ አንጠልጥሎ ራቅ አድርጎ ሲመለከተው ቆየና "ተቀባይ ያጣ ውርስ" ሲል ጮኸ።

ሣራ ጋዴም የምታደርገው ግራ ገብቷት ራሷን በሁለት እጆቿ ይዛ ስትንቀጠቀጥ፣ ቻርሊ የብር ጌጡን የሃረገወይን ደብዳቤ ከተቀመጠበት የምጣድ ጠረጴዛ ላይ አስቀምጦ፣ እጆቹን ደረቱ ላይ አጣምሮ አንድ ጊዜ ደብዳቤውን፤ አንድ ጊዜ ጌጡን፣ አንድ ጊዜ ደግሞ የሃያ ዐመት አገልግሎት የምስክር ወረቀቱን እየተመለከተ የማያቋርጥ ሳቅ መሳቅ ጀመረ። ጠብታ እንባ ከነጠፈበት የደረቀች ነፍስ፤ በጣር እየተጨመቀ የሚወጣ ደረቅ ሳቅ። የልብን ስቃይ፣ የነፍስን ዋይታ፣ የህሊናን ነቀርሳ አዝሎ ከግድግዳ ግድግዳ የሚነጥር ሳቅ... ሁሉን የመርሳት፣ ዓለምን የመናቅ የእብደት ሳቅ!

ለረዥም ጊዜ ይፈነዳል ብሎ ሲፈራው የኖረ ነገር በጭንቅላቱ ውስጥ ሲፈነዳ ታወቀው። አንጎሉ በጭንቅላቱ ውስጥ የሚፍለቀለቅ መሰለው። ከዚህ በፊት ሰምቷቸው የማያውቅ ልዩ ልዩ ድምጾች በጭንቅላቱ ውስጥ እየጮሁ ተንጫጩበት። በሊትል ቻርሊ ታጣፊ አልጋ ጠርዝ ላይ ቁጭ አለ። ወዲያው ሁሉም ነገር ድብልቅልቅ



አለበትና የፀይኑ ብርሃን ለአፍታ ጨለመ። ከዚያ በኋላ የሆነውን ነገር አያስታውስም።

"ሊትል ወዴት ነው ሣራ?"

አልመለሰችለትም።

"ሃረገወይንስ ወዴት ነች?"

አልመለሰችለትም።

"አቢስ... አብነቴ ዛሬ እንኳን ክሳኔ አትቆምም?"

አንድ ጊዜ በሃይል ጮሆ ሸሚዙን ተረትሮና ከኋይት ሃውስ ብር ብሎ ወጣ። ከዚያ ግራና ቀኝ ሳይገላመጥ የሰይጣን ሰፈርን ጠጠራም መንገድ ይዞ ይሮጥ ጀመር። ሣራ ጋዴም ተከትላዋለች ልትደርስበት ግን አልቻለችም። በግ ተራ ደርሶ በመኪና መተላለፊያው አስፋልት ላይ ቆም ብሎ አመነታና የቄራን መስመር ይዞ ቁልቁል በረረ። ንፋስ ስልክ፣ ቃሊቲ፣ ደብረዘይት ሞጆ... መነሻውን እንጂ መድረሻውን ማን ያውቃል?

ሣራ ጋዴም ንፋስ የሚበታትነውን አርቴፊሻል ፀጉር ከፊቷ ላይ እየገለጠች ሀውልት ሆና እንደቆመች ቀረች።

ቻርሊ የሚሮጠው አስፋልቱ መሃል ገብቶ ነው። እንደ ጥይት ከሚበሩ ታክሲዎች እግር፤ እያጓሩ ከሚከንፉ የከተማ አውቶብሶችና ከባድ መኪናዎች ጎማ እንደሚያመልጥ በመገመት ደግማ ደጋግማ አማተበች። እንባዋ ግን ያለማቋረጥ እየፈሰሰ ሜክአፕ በተቀባው ጉንጯ ላይ ቁልቁል መውረዱን አላቆመም። "ወይኔ ቻርሊ!" ስትል በድንገት ጮኸችና ያጠለቀችውን አርቴፊሻል ፀጉር ከራሷ ላይ ነጭታ አስፋልቱ ላይ ወረወረችው። ታክሲ አስቁማ ወደ ቲያትር ቤቱ ስትገሰግስም ቦርሳዋን ኋይት ሃውስ ሶፋ ላይ መርሳቷን አላስታወሰችም ነበር።

***   ***   ***

በጥቁር አንበሳ ሆስፒታል የድንገተኛ ህሙማን መቀበያና ርዳታ መስጫ ክፍል በር ላይ ሻምበል መብራቱ አንገቱን እያሻሸ ይንጎራደዳል። ቲያትር ቤቱ በር ላይ መድቧቸው የነበሩ የወንጀል ምርመራ ክፍል ባልደረቦች በህንፃው መተላለፊያ ሁሉ ጥግ ጥግ ይዘው በተጠንቀቅ ቆመዋል። ሳጂን ከሻምበሉ ኋላ እየተከተለ ጤንነቱን ይጠይቀዋል።

"አሁን ሻል አለህ ጌታዬ?"

"ሣማብ አይግባህ! ደሀና ነኝ… አሁን ዋናው ጭንቀቴ ለቁስለኛው ነው" አለ ሻምበሉ ሃሳብ እንደገባው ዐይኖቹን ቡዝዝ አድርጎ።

"ደግሞ ለነፍሰገዳይ ትጨነቃለህ? ለምን አሥር እግሩን አይበላም! ህይወቱ ብትተርፍማ አሁኑኑ ማጢያ ወስጄ እያጨማለኩ የተወለደበትን ቀን እስቆጥረው ነበር" አለ ሳጅን ረዥም ሪዙን እየጎተተ።

ሻምበል መብራቴ በቅሬታ ፈገግ አለና "የዚህን ሰው ነፍስ ከምንም በላይ እፈልጋታለሁ… ህይወቱ ካለፈች የወንጀሉን ፍንጭ ለማግኘት የነበረኝን ተስፋ ሁሉ ያጨልመዋል። ስህተት እንደሠራህ ግን ታውቃለህ?" ሻምበሉ ግምባሩን ቁጥር አድርጎ ጠየቀው።

ሳጅን ጢሙን እያፍተለተለ ሻምበሉን በመገረም ሲመለከተው ቆየና "እዎን ተሳስቼአለሁ ጌታዬ… አምስት ጥይት ለአንድ ሰው በማባከኔ አዝኛለሁ። ለወደፊቱ ግን አንድ ጥይት ለአንድ ጭንቅላት የሚለውን መርህ እከተላለሁ… ሃሃሃ…" ሲል አፌዘ።

በዚያው ጊዜ ውስጥ አንዲት መነጽር ያደረገች ረጅም ዶክተር ለናፖሊዮን ህክምና ከሚሰጥበት ክፍል ስትወጣ ሻምበል መብራቴ ቀረብ ብሎ ቁስለኛው የሚገኝበትን ሁኔታ ጠየቃት።

"ይቅርታ ያድርጉልኝና" አለች ዶክተሯ በእጇ የያዘችውን ብእር ከንፈሯ ላይ እንዳደረገች።

ሻምበል መብራቴ በስጋት ዓይን ከመመልከት በቀር የሚላት አልነበረውም። "ቁስለኛው በህይወት የመቆየት ተስፋ የለውም! አዝናለሁ…" አለችና ገፋ አድርጋው እየተጣደፈች አለፈች።

ሻምበል መብራቴ ወሽመጡ ብጥስ ሲል ተሰማው። ወር ሙሉ ሲያደክመው የከረመው የስእበተ የወንጀል ጉዳይ ዳግም ፋናው ሲጨልም ታየው። ወደ ሃምሣ አለቃው ዞር አለና "አንድ ሰው ብቻ እዚህ መድበህ ሌሎቹን አባሎች ያዝና ተከተለኝ። ዛሬውኑ የምናድነው ሌላ ወንጀለኛ አለን!" ብሎ ወደ ቮልስዋገን መኪናው በመሄድ ከሆስፒታሉ ቅጥር ግቢ ወጣ። በሳጅን የሚመራ የምርመራ አባሎች ቡድን በአሮጌዋ ላንድሮቨር ተከትሎታል። ሻምበሉ ጠበቃውን በዚያው ቀን በጁ ለማስገባት ከራሱ ጋር ተማማለ።

***    ***    ***



ሁለት የእንቅልፍ እንክብሎች በውሃ አወራርዳ ዋጠች። ስስንተኛ ጊዜ መሆኑ ነው? ዐይኖቿ መጨፈን ጀምረዋል። ልቧን ቅልጥ፣ ሰውነቷን ቅልል፣ መተጣጠፊያዎቿን ድንዝዝ የሚያደርግ ስሜት ይሰማታል። በተቀመጠችበት ወንበር ላይ መርጋት አልቻለችም። አንገቷ ራሷን ተሸክሞ መቆም አልሆነለትም። ወንበሩን ተደግፋ ተነሳችና እየተወላገደች ወደ አልጋዋ ተጠግታ ወደቀችበት። በጀርባዋ እንደተንጋለለች ረዥም ፀጉሯ ፊቷን አለበሰው። እጆቿ ግራና ቀኝ ተዘረጉ።

የመኝታ ክፍሏ በር ሲመታ የቅዠት ያህል ይታወቃታል። ለመነሳት ግን አቅሙም ፍላጎቱም አልነበራትም። እያቀፋት ካለው ደስ የሚል ደመና እቅፍ፣ እፎይታ ከሞላበት ሰመመን ሊያነቃት የሚሞክረው ማነው?!

"… አብነት? አብነት? አብነት?…" ትከሻዋን እየነቀነቀ አንድ ድምጽ ይቀሰቅሳታል። የተጨፈነውን ዐይኗን እንደምንም ገልጣ "ም … ምን-ድነው?" አለች የትንፋሽ ያህል ርቀት በማይሄድ ድምጽ

"እኔ ነኝ አብነት… እባክሽ አንድ ጊዜ ተነሺ…"

"ማ … ነው?"

"ዘሪቱ ነኝ እብየ… አንድ ጊዜ ተነሺ…" ሠራተኛዋ በአብነት ሁኔታ እየተደነቀች ውትወታዋን ቀጠለች።

"ባክሽ… ትንሽ ልተኛ…" አብነት አንጀት በሚበላ አሳዛኝ ድምጽ ለመነቻት።

"አንድ ሰው በር ላይ እያስቸገረን እኮ ነው… እባክሽ አንድ ጊዜ አነጋግሪው… እቢ… አንቺ… እብየ…"

"ማ… ማን… ነው?" ለጠየቀችው ጥያቄ መልስ ሳትጠብቅ ተመልሳ አንቀላፋች።

"እንዴ… አብነት…"

"ማ… ማነው…"

"ተካልኝ ባልቻ ነኝ ይላል… እንዴት ያለ አስቸጋሪ ሰው መሰለሽ ። በዚች ደቂቃ አንቺን ካላገኘሁ…"

"ባክሽ … ተይኝ … ዘርየ … እንደዚያ የሚባል ሰው አላውቅም … ነገ ተመለስ በይው…"

"እሺ የሚለኝ አይመስለኝም… ችክ ያለ ሰው ነው…" ዘሪቱ ቆም ብላ ቁልቁል አልጋው ላይ የተንጋለለችውን አብነትን ስትመለከት በጥልቅ እንቅልፍ መወሰዷን ተረዳችና እዘነችላት። የተዘረጋውን እጇን አስተካክላ ከተከፈተው ቁምሳጥን ውስጥ ጋቢ አውጥታ ካለበሰቻት በኋላ ክፍሉን ዘግታ ወጣች።

በፀጥታ ለመሞት የጥቂት ደቂቃዎች እረፍት እንኳን የማይገኝበት እንዴት ያለ በሁከት የተሞላ ዓለም ነው። በመጨረሻዎቹ የህይወቷ ወራቶች ያሳለፈችው ጭንቅና ትርምስ አሁን እንኳን አያበቃም?!

አፍታም ሳትቆይ ዘሪቱ ተመልሳ ወደ አብነት መኝታ ክፍል ገባች "አቢ... አብዬ... አብነት? አብነት? ዛሬ ደግሞ እንዴት ያለ እንቅልፍ ነው?... አቢ አንቺ አብነት... ትከሻዋን እየነቀነቀች እንደምንም አነቃቻት።

"ማ... ነው?"
"ዘሪቱ ነኝ..."
"ምነው ዘርዬ... ም... ነው... ትንሽ ብተኛ ምን አልኩሽ?" ዐይኖቿ ሳይገለጡ አፏ ብቻ ለአመል ያህል ተንቀሳቀሰ።
"ኸረ ሰውየው ሊጨርሰን ነው... ለጌቶች እንዳንነግር ከእንግዶች ጋር ብርቱ ቆይታ ይዘዋል። ግራ ገባን'ኮ..."
"ማነው... አልሽ..."
"ተካልኝ ባልቻ ነኝ ይላል። በር ላይ ከዘበኛው ጋር የተካረረ አታካር ገጥሟል" የዘሪቱ የተጨነቁ ዐይኖች ተንከራተቱ።

አብነት በሰውነቷ ውስጥ የቀረ የመጨረሻ ሃይሏን አጠራቅማ አልጋው ጠርዝ ላይ ቁጭ አለችና "ዘርዬ... ባክሽ ፎጣ በውሃ ነክረሽ... አቀብይኝ..." ስትል ጠየቀቻት።

ዘሪቱ በአልጋው ጠርዝ ላይ ተጣጥፎ የተቀመጠ ፎጣ አንስታ ወደ መታጠቢያው ቤት ሮጠች። ፈጥናም ወደ አብነት ተመለሰች። ውሃ ባቀረው ፎጣ ግምባሯን፣ ፊቷንና አንገቷን ስታረጥብላት የተጨፈኑት ዐይኖቿ በዝግታ ገርበብ ብለው ተከፈቱ። ከተቀመጠችበት ስትነሳ ተንገዳገደችና ዘሪቱን ደገፍ ብላ ቆመች።

ሠራተኛዋ የአብነት ሁኔታ የጤንነት አልመሰላትም። እንቅልፍ ብቻውን እንደዚያ ያደርጋል ብላ ስላልገመተች "ደህና አይደለሽም እንዴ አብየ?" ስትል ጠየቀቻት።

"ደ... ደህና ነኝ..." ተቀምጣበት ወደነበረው ወንበር እየተንገዳገደች ሄደችና ዘፍ አለችበት። እጇን እንደምንም ዘርግታ በትንሹ ጠረጴዛ ላይ ያስቀመጠችውን ውሃ የያዘ ጠርሙስ አንስታ ጨለጠችው። "ውሃ ድገሚኝ"። ተነፈሰች።



ዘርዬ... አስገቢው"

ዘሪቱ ግምባሯ በጥርጣሬ ቅጭም እንዳለ ወጣች። ተካልኝ ባልቻ?! ለሞት እንኳን ጊዜ የማይሰጥ እንዴት ያለ ክፉ ሰው ነው? በዚች በመጨረሻዋ ደቂቃ እንኳን ከሞት ጉዞዋ ያናጥባት?... አንድ ሰው ከፊት ለፊቷ እንደቆመ ይታወቃታል። ቀና ብላ ገርበብ ብለው በተከፈቱ ዐይኖቿ ማንነቱን ልታጣራ ሞከረች። ከዚህ በፊት አይታው የማታውቅ ሰው ነው።

"እንደምን ከርመሻል እመቤቴ?" ከወገቡ ጎንበስ ብሎ እጅ እየነሳ ጤንነቷን ጠየቃት - ተካልኝ ባልቻ! አብነት አልመለሰችለትም።

"ዘነጋሽኝ ይሆን እመቤቴ?"
"ላስታውስህ አልቻልኩም... በጣም አሞኛል... ምን... እንደምትፈልግ ... ልትነግረኝ ... ትችላለህ?" አለች አብነት አንገቷን ቀና አድርጋ ለመቀመጥ እየታገለች።

"ምነው ምን ነካብኝ እመቤቴ?... ኸረ ክፉሽን አያሳየኝ... በመዘንጋትሽ ግን አይደንቀኝም ጊዜው ትንሽ ረዝሟል... እኔ ግን አልዘነጋሽም... ውለታሽ እስከ መቃብር አብሮኝ ይዘልቃል..."

የደነዘዘው ህሊናዋ ከፊቷ የቆመውን ሰው ማንነትና ምን እንደሚፈልግ ለማወቅ አልቻለም። ሰውነቷ ፍጹም መዛል ስለጀመረ ከተቀመጠችበት ልትወድቅና ህሊናዋን ልትስት የቀራት የጥቂት ደቂቃዎች እድሜ ብቻ ነው። የጆሮዋ የመስማት ሃይል እየደከመ በመሄዱ የሰውየው ድምጽ የሚሰማት የንፋስ ሽውታ ያህል ብቻ ነው።

"ከሁለት ዓመት በፊት..." ተካልኝ ባልቻ ታሪኩንና አሁን የመጣበትን ጉዳይ ማብራራት ሲጀምር፤ ትንሽ በትንሽ እየነቃች የደነዘዙት የስሜት ህዋሳቶቿ ትንሽ በትንሽ እየተንቀሳቀሱ፣ ገርበብ ብለው የተከፈቱ ዐይኖቿ እየተገለጡ ትንሽ ትንሽ በአካልም በመንፈስም ነቃች።

በእንግዳ መቀበያው ክፍል ውስጥ መንገሻ የኔነህ ከጠረጴዛው ላይ በተዘረጋው፤ "የአብነት አስመጭና ላኪ ድርጅት" በስጦታ ለጠበቃው ማስተላለፋቸውን በሚያረጋግጠው ሰነድ፣ ላይ ለመፈረም ብዕራቸውን ጨብጠዋል። ዐይኖቻቸው ፈጠዋል። ከንፈራቸውና ብዕር የያዘ እጃቸው ይንቀጠቀጣሉ። ላባቸው ከግምባራቸው ላይ ይንጠፈጠፋል።

ክፍሉ ውስጥ ከመቼውም ጊዜ በላይ ውጥረት ሰፍኗል። ስለቱ እማኞች የመንገሻ ሁኔታ አሳዝኗቸው በመገረምና በጥርጣሬ ዐይን ይመለከቷቸዋል። አንዳቸውም ሰነዱን ተገደው እንደሚፈርሙ አያውቁም።

የጠበቃው የሰውነት ጅማቶች ሁሉ ተወጣጥረዋል። የደም ሥሩ በግምባሩ ላይ ፈጧል። ከወረቀት የነጡ ትናንሽ ዐይኖቹ ተንልጉለው ብዕር በጨበጠው፤ በመንገሻ የኔነህ እጅ ላይ አነጣጥረዋል። ያችን ቅጽበት ሊያምናት አልቻለም። የብር ርሃብ ጥርስ አውጥቶ ህሊናውን ያኘከዋል፤ የትልቅነት አውሊያ የነፍሱን መንጋጋ ከጫፍ ጫፍ እያላቀቀ ያዛጋዋል።

የጣልያኑን ሽማግሌ አፍና አፍንጫ በፎጣ ለማፈን የተጣደፈው የመንገሻ የኔነህ እጅ ግን በደምና በላብ ተጨማልቆ ያፈራውን ሃብት ለመልቀቅ አልፈጠነም። አሁንም ብዕሩን ጨብጦ ይንቀጠቀጣል።

ጠበቃው ሰዓቱን መልከት አድርጎ የሚቆራረጠውን ትንፋሹን አስተካክለና "ጌታዬ..." ንግግሩን ከመጀመሩ በፊት አንድ ድምጽ አቋረጠው። የእንግዳ መቀበያው ክፍል በር በሃይል ተበርግዶ ተከፈተ። አብነት መንገሻ ፀጉሯ ተበታትኖ፣ ዐይኖቿ ደፍርሰውና ፈጠው ቆማለች። የጠበቃው አፍ እንደተከፈተ ቀረ። መንገሻ ካሉበት ሳይንቀሳቀሱ በድን መስለው ዐይኖቻቸውን አፈጠጡ። እማኞቹ ብቻ ግራ ተጋብተው እርስ በእርስ ይተያዩ ጀመር።

"አባባ... በሰነዱ ላይ እንዳትፈርም!" አብነት ያላትን ሃይል ሁሉ አጠራቅማ ጮኸች። ጠበቃው በመርፌ የተወጋ ያህል ከተቀመጠበት ተፈናጥሮ ተነሳ። የእድሉ በር ለመጨረሻ ጊዜ ተጠርቅሞ ለመዘጋቷ አልተጠራጠረም። መንገሻም ልጃቸው ፈጽማ ለማበዱ ጥርጣሬ አልገባቸውም። በሩን ተደግፋ እንደ ቆመች የሚዝለፈለፍ እጇንና የሚንቀጠቀጡ ጣቶቿን ወደ ጠበቃው ጠቁማ "ይህ... ሰው... ሌባ! ሌባ! ሌባ! ነው... ሰነዱን እንዳትፈርም አባባ!" አለች። እንባዋ በጉንጮቿ ላይ ይወርዳል የድል እንባ! የበቀል እንባ!

"አባባ... አንድ ጊዜ ብቻ አነጋግረኝ" አለችና እየተንገዳገደች ወደ መኝታ ክፍሏ ሄደች። መንገሻ የጨበጡትን ብዕር ወርውረው ወደ አብነት ሮጡ። በመኝታ ክፍሏ ውስጥ አብነት ብቻ አልጋው ጠርዝ ላይ ተቀምጣለች። "ምንድነው የምታወሪው?!" በሩ ላይ እንደቆሙ ጮኸው ጠየቋት።



"ሰነዱ... በ... በጠበቃው... እጅ... የለም... ከጥቂት ደቂቃዎች በፊት... በእጄ ገብቷል" በሚዝለፈለፉት እጆቿ ከጡቷ ሥር የተጣጠፉ ቢጫ ቀለም ያላቸው ወረቀቶች አውጥታ ሰጠቻቸው።

መንገሻ የኔነህ አብነት የምትናገረውን አምነው አልተቀበሉም። ዐይኖቻቸው የሚያዩትንም አላመኑም። በሚንቀጠቀጡ እጆቻቸው የተጣጠፉትን ወረቀቶች ዘረጉና ሙሉ ብርሃን ለማግኘት ወደ ተከፈተው መስኮት በመጠጋት እያንዳንዱን ገጽ በጥንቃቄ አነበቡ። ድንጋጤአቸው በገጻቸው ላይ እንዳለ የፈጠጡ ዐይኖቻቸውን ጎልጉለው "እ - እንዴት... ልታ... ገኚው... ቻልሽ?" በማለት በሚንቀጠቀጥ ድምጽ ጠየቋት።

አልመለሰችላቸውም። ከተቀመጠችበት ተነስታ ቆመችና "በ - አባትነትህ... እስከ አሁን ላደረክልኝ ውለታ ሁሉ... በዚህ ሰነድ ህይወትህን በመግዛት እንደከፈልኩህ ይሰማኛል... ደህና ሁን..." አለችና ክፍሉን ለቃ ልትወጣ ፊቷን አዞረች።

መንገሻ ከቆሙበት ተንደርድረው ክንዷን ያዝ በማድረግ አቆሟት። ምን እንደሚሏት ጠፍቷቸው አፋቸውን እንደከፈቱ አብነት ቀደመቻቸው "አባባ ... እንደቀደሙት ዓመታት ለቃልህ ታማኝ ሰው ሁን... ከእንግዲህ ልጅህ አይደለሁም..."

መንገሻ መወሰን እንዳቃታቸውና ግራ እንደገባቸው በዝግታ ለቀቋት። አብነት እግሮቿን ግራና ቀኝ እያማታች ከቤቱ ወጣች። ጥቂት ዘግይተው ደጋግመው ይጠሯት ጀመር። የሰጠቻቸውን ጀርባ አላዞረችም... ሃውልት መስለው እንደቆሙ ሲመለከቷት ቅጥር ግቢውን አቋርጣ የውጭውን በር በትግል ከፍታ ወጣች።

ከግቢው እንደወጣችም እንግዳ ትርኢት አጋጠማት። አንዲት ቮክስዋገንና ሌላ የፖሊስ ታርጋ የለጠፈች ላንድሮቨር ቆመዋል።

እግሯን እየጎተተች ታክሲ ወደምታገኝበት አቅጣጫ ሄደች። ሰይጣን ሰፈር ስትደርስ መጨለም ጀምሯል። የኋይት ሃውስ በር ገርበብ ብሎ ተከፍቶ ስታይ ቻርሊ እንደሚኖር ገምታ በቅሬታ ፈገግ አለች። የተአምር ያህል የተጠራቀመው ጉልበቷ ብርሃን እየሰጠች በዝግታ እንደምታልቅ ሻማ ሀይሏ ቀስ በቀስ ከውስጧ እየተሟጠጠ እያለቀ ነው።

የኋይት ሃውስን በር ገፋ አድርጋ "ቻርሊ... ቃሌን እንደጠበኩ ፍህ ውስጥ ላንቀላፋ መጥቻለሁ... ሙሽራህን አትቀበላትም?!...

ወይንስ ዛሬም ውሻ ነች ብለህ ትሸሽኛለህ?..." በማለት ሞከረች። የመለሰላት አልነበረም።

ጓይት ሃውስ ከመቼውም ጊዜ ይልቅ ምስቅልቅሏ ወጥቷዋል። ደብዛዛ ባለው ብርሃን ምግዱ ጠረጴዛ ላይ ተጣጥፎ የተቀመጠ ደብዳቤ፣ በደም የተነከረ የብር ጌጥ፣ ከግድግዳው ላይ የተንጠለ የምስክር ወረቀት ስትመለከት አንድ ችግር መፈጠሩን ገመተች። እንደምንም ተወላግዳ አሮጌው ሶፋ ላይ ዘጭ አለች። እጆቿ በመደገፊያው ግራና ቀኝ ቁልቁል ተዘርግተዋል። አንገቷ በግራ ትከሻዋ ላይ ዘንበል ብሎ ፊቷ የገዛ ፀጉሩን ለብሷል።

መፍዘዝ የጀመሩ ዐይኖቿ ይንከራተታሉ። እና የምታልም መሰላት። እንደ ጥጥ የለሰለሰ ስስ ጥቁር ደመና እየቀረባት... እየቀባረት... እየቀረባት ሲጠጋ እርሷም የወፍ ላባ ያህል ቅልል እንዳለች እየሩን በእጆቿ እየቀዘፈች ትበራለች... ትወድቃለች... ትበራለች ትወድቃለች... በጨለማው እቅፍ ውስጥ ተንጋላ፣ በፀጥታው ፀጥ ብላ "እፎይ" ልትል ትበራለች... ግን ትወድቃለች ሞት ወደ ሚሉት የፀጥታ እምባ ለመድረስ። በዚያ ምናልባት ስጋና ነፍሷን የሚሻሙ የሰው ጭራቆች አይኖሩም። ጉልበተኛ የደካማን ማጅራት ረግጦ አያስገብርም። ሀብታም በደሀ የረሃብ ሰቆቃ አይስቅም። ቀጣፊዎች አይቀጥፉም። ተበዳዮችም አይከሱም። ...የጦርነት እሳት የህያዋንን ገላ አይጠብስም። ፍቅርም እንዲህ አይመርም....

ማራ ጋዴም የጓይት ሃውስን በር በርግዳ ስትገባ ቦርሳዋ በተቀመጠበት አሮጌ ሶፋ ላይ አንድ ሴት በጀርባዋ ተንጋላ አየች። በጥንቃቄ እየተራመደች ሴትየዋን አንገብላ አስተዋለቻት - አበሩት መንገሻ ነች። ትንፋሿ ይስለመለማል፣ አካሏ መቀዝቀዝ ጀምሯል። ሞትና ህይወት፣ ህይወትና ሞት እጣ እየተጣጣሉባት ነበር።